
ጋብቻና ፍቅር
ማይልስ ሙንሮ

ጋብቻና ፍቅር

ትርጉም፡- ደረጀ በቀስ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2000 ዓ.ም.

ጋብቻና ፍቅር

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው

Love & Marriage

ከሚለው መጽሐፍ ነው

By MYLES MUNROE

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
አንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው::

ራዕይ አሳታሚ
የፖ.ሳ.ቁ.2332
አዲስ አበባ

RPTR-263M
እንደገና በ2002 ዓ.ም ታተመ 2M

መቅድም

የሰብአዊው ፍጡር ታላቅ ደስታም ይሁን መሪር ስቃይ የሚገኘው በፍቅርና በግንኙነቶቹ ተውኔት ውስጥ ነው:: በዚህ ተውኔት ውስጥ ደግሞ ጋብቻ ምንጊዜም ዋነኛው አውድ ነው:: ዛሬ ዛሬ ብዙዎች ጋብቻ በትክክል መሥራት አለመስራቱ፤ በእርግጥ እውቅና ያለው መሆን አለመሆኑ ጥያቄ ፈጥሮባቸዋል:: ስለዚህ ለሰለጠነው ዓለም ማህበራዊ እድገት እንደ መሠረት ድንጋይ ሆኖ ክብሩንና አድናቆትን ይዞ መቀጠል መቻል አለመቻሉ ግልጽ በሆነ አግራሞት ውስጥ ከቷቸዋል::

እንደ ወረርሽኝ በሽታና እንደተቀጣጣይ ፈንጂ የፍች ቁጥር እየጨመረ መሄዱ፤ ጋብቻን በሚመለከት ሰዎች ባላቸው ፍራቻ፣ ተስፋ ቢስነት፣ ግራመጋባትና ተስፋ መቁረጥ ላይ ተጨማሪ ነዳጅ የሚያርከፈክፍ ሆኗል:: ብዙዎች በጋብቻ ውስጥ የስኬት እድል ይኖረን ይሆን? በሚል ጥርጥር ጥያቄ ውስጥ ወድቀዋል:: አንዳንዶች ከጋብቻ ውጭ በሚደረግ የግብረስጋ ግንኙነት ውስጥ ብቻ፤ ያለ ምንም እውቅና ያለው ግንኙነትና ህጋዊ ስምምነት መቆየት እስኪመርጡ ድረስ ጉዳዩ አሳሳቢ ሆኗል:: ይህን የሚያደርጉት ደግሞ፤ "ግዴታን በሚያስከትል ሁኔታ ውስጥ እስካልገባ ድረስ፤ በነገሮች አትጠላለፍም" ከሚል ግንዛቤ በመነሣት ነው:: ያለንበትን ሁኔታ ጠለቅ ብለን ካየነው፤ ለጋብቻ ተቋም ምንም ዓይነት አድናቆትና ክብር የሌለው፤ ፍላጎቱም የቀዘቀዘ ትውልድ እያፈላን ነው::

የፈረሱ ጋብቻዎችና የተበተኑ ቤተሰቦች ስለባ የሆኑ ብዙዎች፤ የመራራነትና የቁጠኝነትን ባህሪ አዳብረዋል:: እነዚህ ደግሞ በትውልዱ ውስጥ የተበላሹ ግንኙነቶችንና ስሜተ ሰባራነትን የሚያስርጹ ናቸው:: አንዳንዶች ውድቀትን ከመፍራት የተነሳ በጋብቻ እንደማያምኑና ለማግባትም እንደማይፈልጉ በግልጽ ይናገራሉ:: ይህ አሉታዊ ገጽታም በስፓርት፣ በመዝናኛው ኢንዱስትሪ፣ በፖለቲካው ዓለምና እጅግ አሳዛኝ ቢሆንም በቤተክርስቲያን ውስጥ እንኳን ታዋቂነት ያላቸውን ሰዎች ስለባ ያደረገ በመሆኑ ምክንያት በጋብቻቸው ውስጥ ባጋጠማቸው የትዳር መፍረስ ግንኙነቶቻቸው ተቋርጠዋል:: ይህ ሁሉ ደግሞ በእኛው ማህበረሰብ ውስጥ ጋብቻ አንድ ጊዜ የነበረውን ክብር፤ አመኔታና ላቅ ያለ ስፍራ እያደበዘዘው ሄዷል::

ይህ ሁሉ ግን ወዴት የሚያመራ ነው? ከዚህ ተነስተን ወዴት እየሄድን ነው? ጋብቻ የሚለነዘርበትን አሉታዊ ዘገባዎች፣ አስፈሪ ታሪኮች፣ ሥር ነቀላዊ የማህበረሰብ ለውጥ ጽንሰ ሃሣብ አራማጆች፣ ጋብቻ ጊዜው ያለፈበት፣ ሰብአዊው ማህበረሰብ አንዳችም ፋይዳ የሌለው ተቋም ነው እያሉ የሚያወርዱበትን ትችት ተቋቁሞ በአርግጥ ፀንቶ መቀጠል ይችላል?

ግን ግን ባህላዊ ከሆነው የጋብቻ ተቋም ፊታችንን የምንመልስ ከሆነ ይህንን ተቋም ለመተካት ምን አማራጭ መንገድ አዘጋጅተናል? ተግባራዊ ግዴታን ለመወጣት፣ ታማኝነትን፣ መደጋገፍን፣ ማህበራዊ ስሜትን ለማስፈንስ ከጋብቻ ውጭ በተሻለ መንገድ የሚሠራና ውጤታማ የሆነ ምን አይነት እቅድ ዘርግተናል? ለማፍቀር ለሰብአዊው ፍጡር በመሠረታዊ ደረጃ አስፈላጊዎች የሆኑት እንደ ፍቅር፣ የሌላው የመሆንና ሌላውንም የራስ የማድረግ ስሜት፣ ለራስ የሚሰጥ የጠቃሚነት ስሜት፣ ሁለንተናዊ ደህንነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ መከባበርን ለማስፈን ምን አዲስ ምንጭ ቆፍረናል? ይህንን ለማወቅ በብርቱ እፈልጋለሁ::

ላለፉት ስድስት ሽህ ዓመታት ያህል የትኛውም ስልጣኔ ይሁን የትኛውም ባህል ሥርዓት ያለው ማህበራዊ እድገት ለማምጣት ከባህላዊው የጋብቻ ተቋም ውጭ የተሻለ ጽንሰ ሀሳብ አላቀረበም:: ሁሉም ማህበረሰብና ባህል የቤተሰብን ጤነኛ የሆነ እድገት ለማምጣት ደመነፍሳዊ የሆነ መሻቱ ይሄው በአግባቡ የተዋቀረው የጋብቻ ጽንሰ ሀሳብ ነው::

የሰው ልጅ ምንም ያህል በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሥራ አመራር ሥርዓትና በእውቀት እያደገ ቢሄድም ጋብቻ ለማህበረሰብ እድገት የመሠረት ድንጋይ የመሆኑን አጠቃላይ እውነት መቼም መች ቢሆን ሊያሻሽለው እንደማይችል የፀና እምነቴ ነው:: ጋብቻ መልካም የሆነ ሃሳብ እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር ሃሳብ ብቻም እንደሆነ እምነቴ ነው::

ምንም እንኳን በርካታ ትዳሮች ቢፈርሱም፣ ቤተሰቦች ቢበተኑም፣ የፍች ጉዳዮች ፍርድ ቤቶችን ቢያጣብቡም፣ በፈረሱ ግንኙነቶች ምክንያት ብዙ የተጎዱ ውጤቶች ቢከተሉም፣ ጋብቻ አሁንም መልካም ሃሳብ ነው፣ እውነቱን ለመናገር እጅግ የተሻለውም ጽንሰ ሃሳብ ነው::

ማርቲን ሉተር

የቄስ ዶ/ር ማርቲን ሉተር የህይወት ታሪክና አገልግሎት በሬሲፕ ሞሳንክቶን 1549

ያ እጅግ የተከበረው ሰው፣ ማርቲን ሉተር፣ በእኛ ዘንድ በነበረበት ጊዜ፣ የገዛ ህይወቱን ታሪክ አራሱ ሊተርከው ተስፋን ሰጥቶን ነበር:: በግጭቶች በተሞሉ ሁኔታዎች ውስጥ ያለፈበትን ታሪኩን ያለጥርጥር ጽፎ ያጠናቅቀው ነበር:: ይሁንና ከወዲሁ ከዚህ ሥጋ ከሆነ ማደሪያው፣ ከእግዚአብሔር ጋርና በመንግስተ ሰማይ ካሉ የእግዚአብሔር ልጆች ጋር ህብረት ያደርግ ዘንድ ተጠራ::

በእርሱ የግል ህይወት ዙሪያ ጥልቀት ያለውን አትኩሮት መስጠት፣ ወደፊት ለሚመጣው ጊዜ ምሣሌነት የተሞላበትን ህይወት ለታሪክ በግልጽ ማስቀረት ትርፍ ያለው ነገር ነው::

ማውጫ ገፅ

ክፍል አንድ

በጋብቻ ውስጥ ያሰው ፍቅር፣ ስሁንም የከበረ ሀሳብ መሆኑን መረዳት

ምዕራፍ አንድ

ጋብቻ እንደከበረ ሰንቁ ነው 8

ምዕራፍ ሁለት

ጋብቻ ከቡር ነው 22

ምዕራፍ ሦስት

ስምንድን ነው የምናገባው? 37

ምዕራፍ አራት

ሁሉም ሰው በገነት ውስጥ ጋብቸውን ሲፈጽም ደገባሰ 54

ምዕራፍ አምስት

ደስተኛ ጋብቻ በድንገት የሚገኝ አደደስም 69

ምዕራፍ ስድስት

የታሠርንበትን ስስራት መፍታት 86

ምዕራፍ ሰባት

ሰዓዩነታችን ምስጋና ደገባው! 101

ምዕራፍ ስምንት

ንደኝነት፤ ከግንኙነቶች ሁሉ የሳቀ 123

ክፍል ሁለት

ፍቅርንና የዕብን ሚስጥር መረዳት

ምዕራፍ አንድ

ፍቅር የምንሰው ደህንን ነው 133

ምዕራፍ ሁለት

እግዚአብሔር ደመደሃሰ 148

ምዕራፍ ሦስት

እግዚአብሔርን መሙደድ 163

ምዕራፍ አራት

ራስን መሙደድ 177

ምዕራፍ አምስት

ባልንጀራን መሙደድ 193

ክፍል ሦስት

ስህደጠት ዘመን ሁሉ ፍቅርን መግንዘብ

ምዕራፍ አንድ

ጋብቻ፤ የተወሰነ የተግባር ሚና የሴለው ግንኙነት 208

ምዕራፍ ሁለት

በመግዛት ሳይ የተነሳ ጥያቄ 224

ምዕራፍ ሶስት

የግንኙነትን ጥበብ መካን 237

ምዕራፍ አራት

ጥቃቅን ነገርችን ስትርሱ 248

ምዕራፍ አምስት

ከእግዚአብሔር መንግሥት ሰባሰትዳርች የተሰሙ መርሆዎች 264

ምዕራፍ ስድስት

በጋብቻ ውስጥ የጸታዊ ግንኙነት ህብረት 281

ምዕራፍ ሰባት

የቤተሰብ ምጣኔ 300

ምዕራፍ አምስት

በሕጋዊ ውስጥ መኖር 317

ክፍለ ትንሣኤ

ምዕራፍ ስንድ

ጋብቻ ትንሣኤከዘረ ዕንቁ ነው

በዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች ስለ ጋብቻ ጉዳይ ግራ ይጋባሉ። በብዙዎች አመለካከት ጋብቻ አስፈላጊነት የሌለው፣ ጊዜው ያለፈበት የታሪክ ቅርስና ዘመኑ ከሚጠይቀው ጥበብና የህይወት አንቅስቃሴ ጋር አብሮ የማይዘልቅ ተቋም ነው። በተለይም እጅግ ነፃነት በነገለበትና ነገሮችን አብጠርጥሮ መረዳት በተቻለበት በዛሬው ባህል ውስጥ፤ እውን ጋብቻ ጠቃሚ ሃሣብ ነውን? ሲሉ ይጠይቃሉ። በዘመነው ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ክብር፣ መተማመን፣ ታማኝነት፣ ሃላፊነትን መወጣት የመሣሰሉት ጽንሰ ሀሳቦች ኋላቀርና ሊተገበሩ የማይችሉ ተደርገው ይወሰዳሉ። በጣም በሚገርም ፍጥነት ሰዎች ጫማቸውን እንደሚቀያይሩ ያህል ባልጀሮቻቸውን ይቀያይራሉ።

በየአንዳንዱ አቅጣጫ በሚገዳደረን፤ ከአለማዊ አመለካከትና ፍልስፍና በሚመነጭ በዚህ በጋብቻ ላይ በሚፈጠር ግራ የተጋባ አመለካከት ግን ልንደነቅ አይገባም። በየአንዳንዱ ቀን የምናነባቸውና የምንመለከታቸው መጽሐፍት፣ መጽሔቶች፣ ሲኒማዎች፣ ኦፔራዎች፣ አስቂኝ ተውኔቶችና ድራማዎች ውስጥ የምናያቸው ልብ የሚሰብሩ ጉዳዮችን ነው። በባሎቻቸው ላይ የሚማግጡ ሴቶችና ሚስቶቻቸውን የሚያታልሉ ባሎችን ምስልና ገጸ ባህሪ ይዘው ያለማቋረጥ ይወጣሉ። ያላገቡ ወንዶችና ሴቶች ለው ባርኔጣውን ከራሱ ላይ አንስቶ በሚመልስበት ፍጥነት ወደ አልጋ ላይ ዘለው ይወጣሉ። በወጡበት ፍጥነት ወርደው ቀጣዮን ተጓዳኛ ቸውን ለመፈለግ ደግሞ ይሮጣሉ።

በዚህ ዘመን ሰዎች ልብሶቻቸውን በሚገዙበት መንገድ ግንኙነቶችንም እንዲሁ ይገዛሉ። ልክ ያልሆኗቸውን ልብሶቻቸውን ትተው ሌሎችን ለመሞከር እልፍ እንደሚሉ ሁሉ፤ በግንኙነቶቻቸው ላይ የሚወስዱት አቋም እንዲሁ ነው። የተመቸ ልብስ ሲያገኙ አንስተው ቀለሙ እስኪለቅና ፋሽኑ እስኪያልፍ ድረስ ይለብሱታል። ከዚያ ለኋላ ግን በጓዳቸው ባለ ቁምሣጥን ውስጥ እስከፍግሜው እንጠልጥለው ምትኩን ለመፈለግ ይከንፋሉ።

የምንኖረው አውነተኛና ዘላቂነት ያለውን ነገር በማይፈልግ፤ ተጠቅሞ መወርወር፣ አኝክ መትፋት በሚፈልግ ማህበረሰብ ውስጥ ነው። የኛ አለም መረጃዎች ፈጥነው የሚለዋወጡባት ነገሮች ሁሉ አጭር እድሜ ያላቸውና ሆን ተብለው ማብቂያቸው እንዲያጥር የሚደረጉባት አለም ነች። ፍጹም የሆነ ምንም ነገር የለም። እውነትም የምትቆመው እንደተመልካቹ እይታ ነው። ስነምግባርም እንደሰዎች አመለካከት በቅጽበት ተለዋዋጭ ነው። አንግዲህ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሰዎች፤ "እና ምንም ነገር በዘላቂነት አይቀጥልም? ልታመንበት የምችል ምንም ነገር ከቶ አይኖርም?" ብለው ቢጠይቁ ይህ አስደናቂ ነገር አይደለም።

የምንኖርበት ዓለም ታማሚ ለመሆኑ ምልክት ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ፤ ሰብአዊ የሆነ ግንኙነታችንን የምናያይዘው ህያውነት ከሌላቸውና ተጠቅመን ከምንጥላቸው ከዕለት ዕለት መገልገያዎቻችን ጋር ካለን ግንኙነት አንጻር ነው። ምንም እንኳን ከየአቅጣጫው በሚሰነዘር የቀረበ ጥቃት ውስጥ ቢሆንም፤ ጋብቻ ዛሬም በሰዎች መካከል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ የጠለቀውና እጅጉን የሚቀራረቡበት ነው። ጋብቻ በዚህ በሰለጠነው ዓለም ውስጥ ስኬታማ መሆን ይችላልን? በየወቅቱ በፍጥነት በሚለዋወጥ ዓለም ውስጥ ትርጉም የሚሰጥ ይሆናል? አሁንም ጋብቻ መልካም አሣብ ነውን?

ጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሣብ ነው

ከላይ ለጠየቅነው ጥያቄ መልሱ አወንታዊ ነው። ጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሣብ በመሆኑ በርግጥ አሁንም መልካም አሣብ ነው። ያቀደውና የመሠረተውም እግዚአብሔር በመሆኑ፤ መመዘኛ ዎቹን ዝቅ ከሚያደርጉ በየጊዜው ከሚመነጩ አስተሳሰቦችና ትምህርቶች ይጠብቀዋል። ከጅማሬውም ጋብቻ የለው አስተሳሰብ ውጤት አይደለም። የለው ልጅ በታሪክ ሂደቱ አንድ ወቅት ላይ ቆም ብሎ አስፈላጊነቱንም ተመልክቶ በወንዶችና በሴቶች መካከል ላለው ግንኙነትና ሃላፊነቶች መልካም ይሆናል ብሎ አልሞ አልመሠረተውም። ወይም ደግሞ ልጆችን ስለመውለድና ስለወላጅነት ጉዳዮ አልተጨነቀም። የጋብቻ ጅማሬ መለኮታዊ ነው።



ጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሳብ በመሆኑ በርግጥ ሰዙንም መሰልካም ሃሳብ ነው

ገና በለው ልጅ ማህበረሰብ የመጀመሪያ ምዕራፍ እግዚአብሔር ራሱ ጋብቻን መሠረተ አፀደቀውም። የዘፍጥረትን መጽሐፍ ሁለተኛ ምዕራፍ፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ አስቀድሞ ከፈጠረው ሰው ጎን ላይ የጎድን አጥንትን ወስዶ ለሰው "መልካም ረዳት" ትሆነው ዘንድ ሴትን ከዚህ አጥንት እንደሠራት የተርክልናል (ዘፍ 2÷20)። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን በአንድነት አቅርቦ ግንኙነታቸው የባልና የሚስት መሆኑን አረጋገጠላቸው። በዚህም ጋብቻን እንደተቋም አፀናላቸው።

ከመነሻውም፤ እግዚአብሔር ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ወንድንና ሴትን ዘላቂነት ባለው የጋብቻ ግንኙነት "አንድ ሥጋ" ይሆኑ ዘንድ አስተሳሰራቸዋል። አዳም ከእንቅልፉ ነቅቶ ዐይኑን ሲገልጽና በሄዋን ላይ ሊያላርፍ በአግራሞት "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ይህችም ሥጋ ከሰጋየ ናት፤ ከለው ተገኝታለችና ሴት ተብላ ትጠራ አለ" (ዘፍ 2÷23) እግዚአብሔር ስለጋብቻ ያለው እቅድም በቀጣዮ ጥቅስ ላይ የተመሠረተ ነበር። "ስለዚህም ምክንያት ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፤ አንድም ሥጋ ይሆናሉ" (ዘፍ 2÷24)።

"አንድ ሥጋ" ማለት ሁለት ሰዎችን በመጫ ከማጣበቅ የዘለለ ትርጉም ያለው ነው። ይልቁንም የየራሳቸው ማንነት መግለጫ ያላቸውን ሁለት ነገሮች ወደ አሃዳዊ ውህደት ማምጣት ማለት ነው። ሁለት ጣውላዎችን በመጫ ባጣብቃቸው በርግጥ ተጣብቀዋል፤ ነገር ግን አሃዳዊ ውህደት የላቸውም። ሁለት የተለያዩ ጣውላዎች ሆነው በጥምረቱ ውስጥ ይቀጥላሉ፤ ይሁንና በቂ የሆነ መቀት ወይም ግፊት ጥምረታቸውን ሊለያየው ይችላል። በኬሚስትሪው ዓለም የተለያዩ ቁስ አካሎችን እርስ በእርስ አያይዞ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ የሚያቆያቸው ሰንሰለት ኬሚካል ቦንድ ይባላል። ይህ ሰንሰለት የሚበጠስ ከሆነ ቁስአካሎቹ ተለያይተው በየራሳቸው አቅጣጫ ይቀጥላሉ።

የአሃዳዊ ውህደት ግን እንዲህ አይደለም። ሁለት ቁስአካሎች በአሃዳዊ ውህደት ከተጣመሩ ፈጽሞ ለመለያየት አይቻልም። በሆነ ሃይል አስገዳጅነት ሊወድሙ ይችሉ ይሆናል፤ ሊለያዩ ግን አይችሉም። በእግዚአብሔር የጋብቻ እቅድ "አንድ ሥጋ" የሆኑ ወንድና ሴት፤ በሆነ አስገዳጅ ሁኔታ ታላቅ መከራ ውስጥ ካልገቡ ወይም ካልሞቱ በቀር ሊለያዩ አይችሉም። በመንፈሣዊው እሣቤ

ውስጥ እጅን ወይም እግርን ከአካላቸው ላይ የመገንጠል ያህል ነው የሚቆጠረው።

እግዚአብሔር ወንድና ሴት "አንድ ሥጋ" ይሆናሉ ብሎ ጋብቻን ሲያጸና፤ ሣጣቡ ግልጽ በሆነ መንገድ ይህ ተቋም እስከ ህይወት ፍጻሜ የሚዘልቅና ቋሚነት ያለው እንዲሆን ነው። ታላቁ የአይሁድ መምህር ኢየሱስ፤ ከአንድ ፈሪሣዊ ጋር ፍቾን በሚመለከት ባደረገው ውይይት ይህንኑ ሀሣብ በጠራ መንገድ ግልጽ አድርጎታል። ፈሪሣዊው "ሙሴ በህግ ፍቾን የፈቀደ በመሆኑ አንድ ለው ሚስቱን ቢፈታ ህጋዊ መሠረት አለው?" ሲል ጠይቆት ነበር። "ስለልባችሁ ጥንካሬ ይህችን ትእዛዝ ፃፈላችሁ። ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው። ስለዚህ ሰው አናቱንና አባቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን አንግዲህ ሰው አይለየው" (ማር 10÷9-14)።

"እግዚአብሔር ያጣመረውን አንግዲህ ሰው አይለየው"። ጋብቻን የመሠረቱት የለው ልጆች ቢሆኑ ኖሮ በተፈቀደላቸውና ሊያስወግዱት መብት በኖራቸው ነበር። ይሁንና ጋብቻን የመሠረተው እግዚአብሔር በመሆኑ ደረጃውን መወሰን፤ ህጉን መደንገግ፤ አቅጣጫውንም ማመላከት የእርሱ ስልጣን ብቻ ነው። እንዲህ ባይሆንማ መጽሀፍት፤ ጋብቻ እግዚአብሔር ያቀደው ተቋምና ወንድና ሴት አንድ ሥጋ ሆነው በህይወት ዘመናቸው ሁሉ እንዲጣመሩ ማድረጉን በግልጽ ባላሰፈሩም ነበር። ይህ ተቋም የለው ዘር በምድር ላይ እስከቀጠለ ድረስ ይቀጥላል። ሊመጣ ባለው አለም ብቻ ጋብቻ አላስፈላጊ ይሆናል።

ጋብቻ መመሥረታዊ ተቋም ነው

ሌላው ጠቃሚ እውነት ደግሞ፤ እግዚአብሔር ጋብቻን የመሠረተው በሰብአዊው ማህበረሰብ ውስጥ የመጀመሪያውና እጅግ ወሳኝ ተቋም አድርጎ ነው። ቤተሰብ የማንኛውም ጤነኛ ማህበረሰብ መሠረት እንደሆነ ሁሉ፤ ጋብቻ የዚህ ቤተሰብ መሠረት ነው። ጋብቻ ከሌሎች ተቋማት ሁሉ በፊት የተመሠረተ ተቋም ነው። ሀገሮችና መንግስታት ሳይመሠረቱ፤ ቤተክርስቲያናት፣ ት/ቤቶችና የንግድ መዋቅሮች ሳይቋቋሙ፤ ቤተሰብ ግን ተመሰርቷል። ከቤተሰብም ቀድሞ ጋብቻ ተመስርቷል።



ቤተሰብ ዩማንኛውም ጤነኛ ማህበረሰብ መሠረቶ ስንደ ሆነ ሁሉ፤ ጋብቻ የዚህ ቤተሰብ መሠረት ነው።

እግዚአብሔር ማህበረሰብን በዚህ ተቋም ላይ መመስረት በመፈለጉ ምክንያት፤ ጋብቻ መሠረት ሊሆን ግድ ሆኗል። እግዚአብሔር አዳምና ሄዋንን በኤደን ገነት ወደ አንድነት ሲያመጣ፣ እያደገ በሚሄድ ቀጣይ ግንኙነታቸው ውስጥ ጋብቻን መሠረታዊ ጉዳይ አድርጎ ነው። በዚህ አውድ ውስጥ ነበር አንዳቸው ለአንዳቸው የሚኖራቸውን ሃላፊነትና ተግባራዊ ግዴታቸውን መማር የጀመሩት።

አንድ ሰብአዊ ማኅበረሰብ ህልውናውን ጠብቆ የመቆየቱ ወይም ያለመቆየቱ ጉዳይ በጋብቻ ላይ ያረፈ ነው። ለዚህ ነው ዛሬ በአንዳንዶች አመለካከት ለጋብቻ የሚሰጠው ዝቅተኛ ግምት አደገኛ የሚሆነው። ባህላዊ እሴቶችና መሠረታዊ የሆኑ ተቋሞች በየወቅቱ ጥቃት ሲደርስባቸው ጋብቻም እየተጠቃ መሆኑ አጠያያቂ ነውን? እጅግ ብዙዎች በጋብቻ ጉዳይ ላይ ግራ በተጋቡበት ሁኔታ ማህበረሰቡ ራሱ ቅጥ-አልባ እየሆነ መምጣቱ የሚያስደንቅ ነውን? አስማቀፋዊ በሆነ መንገድ በጋብቻ ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት በእርግጥ በማህበረሰቡ ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ነው። እልፍ ሲልም የጋብቻና የማህበረሰብ ፈጣሪና ፈብራኪ በሆነው በእግዚአብሔር ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ነው። አጥቂው አንድ ነገር ያውቃል፤ ጋብቻን ማጥፋት ከቻለ ቤተሰብን በቀላሉ ያጠፋል። ቤተሰብን ካጠፋ ደግሞ ማህበረሰብን ያጠፋል። ማህበረሰብን ካጠፋም ህያው የሆነውን ፍጥረት ሁሉ ያጠፋል።

በተጨማሪም፤ ጋብቻ የእማኞች ማህበርና የእግዚአብሔር ምርጥ ማህበረሰብ ሰብሰብ የሆነችው የቤተክርስቲያን መሠረት ነው። አዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያብራራ፤ በሙሽራውና በሙሽሪት ይመስለዋል። ተምሣሌቱ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ጥምረት የሚያመላክት ወሳኝ አንድምታ ያለው ነው። ለምሳሌ ያህል ለኤፌሶን ቤ/ክ በፃፈው መልዕክቱ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይሁዳዊ ሃዋርያ ጳውሎስ የሚከተለውን አስፈሯል፤ ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ። ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያንጽ እንደሆነ፤ ባል የሚስት ራስ ነውና . . . ባሎች ሆይ ክርስቶስ ዳግም

ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ . . . ስለዚህ ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው። እኔ ግን ይህንን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ" (ኤፌ 5፥21-23፤ 25፤ 31-32)።

በኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ ቤተክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት በባልና በሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት እንደ ሞዴል የሚያገለግል ነው። በመካባበር፣ በእኩልነትና አንዱ ለሌላው መስዋእትነት በሚከፍልበት ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው።

መጽሀፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ባሉት ክፍሎች ውስጥ እጅግ ንዑስና የማህበረሰቡ መሠረታዊ ክፍል ለሆነው ቤተሰብ ብዙ ጊዜ "ቤት" የሚለውን ቃል ይጠቀማል። ይህ ማለት ደግሞ ቤተሰብ ነው። ቤት የማህበረሰብ መሠረት ነው፤ የሁልጊዜም ጤነኛ ለሆነ ቤት መሠረት ነው። በመሆኑም የማህበረሰቡ ጤነኛ ቤት የማህበረሰቡን ጤንነት የሚወስን ነው።



ጤነኛ ቤት ለጤነኛ ቤተክርስቲያንና ለጤነኛ ማህበረሰብ ቁልፍ ጉዳይ ነው

በጋብቻ ላይ ያነጣጠሩ ትመስካከት

በቤተክርስቲያንም እንዲሁ ነው። የቤተክርስቲያን ጤንነት የሚወሰነው በአባሎቿ "ቤት" ጤንነት ነው ይልቁንም በአመራር ላይ ባሉ አባሎቿ "ቤት" ጤንነት። መልካም የሆነ የቤተሰብ አመራር ለቤተክርስቲያን መሪዎች ዋንኛ ጉዳይ ነው። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክት ይህንን ግልጽ አድርጎታል። "ማንም ኢጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል፤ የሚለው ቃል የታመነ ነው" (1ኛጢሞ 3፥1)። ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ "ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንደሚያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል" (1ጢሞ 3፥4-5)።

ጤነኛ "ቤት" ለጤነኛ ቤተክርስቲያንና ለጤነኛ ማህበረሰብ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የጤነኛ ቤት መመዘኛው የጋብቻ ጤንነት ነው። ጋብቻ መሠረታዊ የሆነ ተቋም ነው።

መሞሰድ የጋብቻ ቀዳሚ አላማ አይደለም

በቤተክርስቲያንም ውስጥ ሆነ በውጭ ባሉት በብዙዎች መካከል የተሣሣተ አመለካከት አለ። ይሄውም የጋብቻ ቀዳሚው አላማ በምድር ላይ ህይወት እንዲቀጥል መባዛት እንደሆነ ይቆጥራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይህንን አይነግረንም። ምንም እንኳን በዘፍጥረት 1÷28 እግዚአብሔር እንዲበዙና እንዲባዙ ምድርንም እንዲሞሏት ትእዛዝ ቢያስተላልፍም፤ ጋብቻ የመዋለድ ሂደት የሚከናወንበት ተቋም እንዲሆን ቢፈቅድም፤ መዋለድ የጋብቻ ዋንኛ አላማ አይደለም።

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ፍጥረትንና የፍጥረትን ሥርአት የሚገዛ ነበር። "እግዚአብሔር ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት ግዙዋትም። የባህር አሣዎችንና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዟቸው" (ዘፍ 1÷28)። እግዚአብሔር ለውን ፈጠረ - ወንድና ሴት አደረጋቸው - ከሌሎች መሰሎቻቸው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት እንዲዋለዱና እንዲባዙ እግዚአብሔር ይጠብቅባቸው ነበር። በፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ ላይም ከእርሱ በታች ገዥዎች እንዲሆኑ ሾሟቸዋል። በመጀመሪያው ጋብቻ የባልንጀርነት ኪዳን ያለው ነበር። ወንድና ሴት ማለትም ባልና ሚስት በዚህ የግንኙነት መዋቅር ውስጥ አንድ ሥጋ ሆነው በጋራ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ግዛት እንዲያስተዳድሩ የሰጣቸው ተቋም ነበር። መዋለድ የጋብቻ ውጤት እንጂ ዋንኛው ትኩረት አልነበረም። በሰለጠነው ማህበረሰብ ውስጥ በግልጽ እንደሚታየው ጋብቻ ለመዋለድ ወሳኝ ነገር አይደለም። ያላገቡ ወንዶችና ሴቶች ለመውለድ ችግር የለባቸውም። በብዙ የዓለም ክፍሎች ከአገቡ ሴቶች ከተወለዱት ልጆች ይልቅ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱት ልጆች ቁጥር ብልጫ አለው። በዚህ ምክንያት ነው ብዙ ሣይንቲስቶችና የማህበረሰብ ጠበብቶች፤ ሁኔታው በዚህ የሚቀጥል ከሆነ በተከታዮቹ አንድ ወይም ሁለት ትውልዶች ውስጥ የዓለም ህዘብ ብዛት ምድር ልትመግበው ከምትችለው አቅም በላይ ይሆናል፤ በማለት ስጋታቸውን የሚገልጹት።

ጋብቻ ልጆችን ለማፍራት ዋንኛው መንገድ እንደሆነ ከሚገመተው የተለመደ አመለካከት በተቃራኒው፤ ጋብቻ አላስፈላጊ የሆኑ መዋለዶችን ለመቆጣጠር ወሣኝ መዋቅር ነው። ለዚህ ደግሞ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶችን መስጠት ይቻላል። እጅግ በብዙ

ስፍራዎች ዛሬም ድረስ ከጋብቻ ውጭ ልጆችን መውለድ እንደነውር የሚቆጠር ነው። ብዙ ሰዎች አሁንም ቢሆን ለጋብቻ የሚሰጡት የከበረ ግምት ትልቅ በመሆኑ፤ ይህ ለጋብቻ የተሰጠ ክብር ከጋብቻ ውጭ ሊከሰቱ የሚችሉ ብዙ መዋለዶችን ቁጥር ቀንሷል። የጋብቻ ተቋም ባይኖር አሁን ከተራቡት ይልቅ ሰዎች እንደ አጽዋት ወይም እንደ እንስሳት በብዙ ቁጥር ይዋለዱ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ሀላፊነታቸውን በትክክል የተረዱ ጥንዶች በእግባቡ ሊንከባከቧቸውና ሊያፈቅሯቸው ከሚችሉት በላይ ልጆችን ላለመውለድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ጳውሎስ ጠንከር ያለ አስተያየት ይሰነዝራል። "የእርሱ ሰለሆነት ይልቁንም ለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው" (1ጢሞ 5÷8)።

የቤተሰብን ምጣኔ ተግባራዊ እንዳለማድረግ ያለ ጎጢያትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሀሣብ የመውጣት የከፋ ጉዳይ የለም። (እዚህ ላይ ውርጃ እንደቤተሰብ ምጣኔ የሚተገበር ወይም ጤነኛ የሆነ አመለካከት እንዳልሆነ ለመግለጽ እውዳለሁ። ውርጃ ህይወትን የመቅጨትና በጽንሱ ውስጥ ያለውን እምቅ ከሀሎት የማውደም ተግባር ነው። የእንድ ግብ የህይወት ፍጻሜ ማስከተልና በመለኮት እቅድ ውስጥ ጣልቃ የመግባት ስህተት ነው። ውርጃ በተገለጸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ማመጽ ነው። በተቃራኒው እውነተኛ የሆነ የቤተሰብ ምጣኔ የበለሰና ሃላፊነት የሚሰማው መጋቢ ተግባር ነው።

የግብረስጋ ግንኙነት የጋብቻ ዋነኛ ዓላማ አይደለም

ሌላው የተለመደ የተሣሣተ አመለካከት፤ የጋብቻ ዓላማ የግብረስጋ ግንኙነትን ህጋዊ ለማድረግ ታስቦ እንደተቋቋመ ተቋም እድርጎ መቁጠር ነው። ጋብቻ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የሚዛመድ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም የጋብቻ ዋንኛ ዓላማ ስጋዊ ግንኙነት ባለመሆኑ ነው። የግብረ ስጋ ግንኙነት በፍጹም የጋብቻ ግንኙነት አይነት አይደለም፤ ሊሆንም ከቶ አይችልም። ጋብቻ የደም ቃል ኪዳን፣ መሃከላዊ ሃላፊነትንና ፍቅርን መሠረት ያደረገ የስጋዊ ግንኙነት ህብረት ነው (1ቆሮ 7፤3-5 ይመልከቱ)። ይሁንና እነኚህ ሦስቱ ሁሉም በሁሉ እንድ አይደሉም። ከሁሉም በፊት ጋብቻ ሃላፊነትን መወጣት ግድ ይላል። ይህን ሃላፊነት ከመወጣት አንፃር የግብረስጋ ግንኙነት ያለው ሚና ጉልህ አይደለም። ስጋዊ ግንኙነት መቶ በመቶውን ለስነልቡናዊና ባዮኬሚካላዊ (ተፈጥሯዊ) ፍላጎት

የሚለጥ ተፈጥሯዊ ምላሽ ነው። ይህ ግንኙነት በጋብቻ ውስጥ ያለን አንድ አንድ የሃላፊነት ግዳጅ ብቻ መወጣት ነው። ይሁን እንጂ በራሱ የተወሰነ ግዳጅ አይደለም። በራሱም ጋብቻን ሊፈጥር ወይም ሊያፈርስ አይችልም። ጋብቻ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ የሰፋና የጠለቀ በመጠኑም የላቀ ነው። ምናልባትም በጋብቻ ውስጥ የግብረስጋ ግንኙነት ድርሻ ከመቶ አንድ እጅ ብቻ ነው። ቀሪውን የያዘው ተለምዷዊው የዕለት ተዕለት ህይወት ነው። ለግብረስጋ ግንኙነት ተብሎ ጋብቻ የሚመሠረት ከሆነ ቀሪው ዘጠና ዘጠኝ እጅ ተግባር እንደምን ሊተገበር ይችላል?

ለብዙ ዓመታት ዝሙት ጋብቻን እንደሚያፈርስ ሲታሰብ ኖሯል። ይህ ግን ፈጽሞ እውነት አይደለም። ዝሙት ጋብቻን ሊመሠርተው ካልቻለ እንዴት ሊያፈርሰው ይችላል? ዝሙት ኀጢያት ነው፤ መጽሀፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ለአማኙ ጋብቻን ለማፍረስ ህጋዊ ፈቃድ የሚሰጥ ነው። ይሁን እንጂ ፈጣን እርምጃ አይደለም። ለእንደዚህ ያለው ሁኔታ ፍች ዋና ነገር አይደለም። ዝሙት ጋብቻን ሊያፈርስ አይችልም። ጋብቻን ማፍረስ ምርጫ ነው።

እዚህ ላይ የግብረ ስጋ ግንኙነትና የጋብቻ ግንኙነት አንድ እንዳልሆኑ መገንዘብ፤ ጋብቻ ምን እንደሆነ በአግባቡ ለመረዳት እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በጨማሪም ጋብቻና ፍች ምን እንደሆኑ ለመገንዘብ መሠረታዊ መነሻ ይሆናል። ጋብቻ እጅግ የገዘፈና የተለየ ይሁን እንጂ የግብረስጋ ግንኙነትን የሚያካትት ነው። ይህ ሲባል ግን የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመኖር ጋብቻ እንዳይኖር ያደርጋል ማለት አይደለም። መኖሩም ብቻውን ግንኙነቱን ወደ ጋብቻ አይለውጠውም። ጋብቻና ግብረስጋ የተያያዙ ነገሮች ናቸው፤ ይሁንና አንድ አይደሉም።

በጋብቻ ውስጥ ያለ የከበረ ቋንቋ

ታዲያ እንዴት ነው ጋብቻን የምንገልጸው? የጋብቻ ቀደምት አላማ መዋለድ ወይም የግብረስጋ ግንኙነት ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? እንደምንጊዜውም መልሱን መጽሐፍ ቅዱስ ይሰጠናል። "መጋባት" ወይም "ጋብቻ" ለሚለው ቃል አቻ የግሪክ መነሻ ቃል "ጋም" የሚል ሲሆን ይህም በእንግሊዘኛው ቋንቋ "ጂም" ለሚለው ቃል ወደረኛው ነው። መነሻ ቃሉ በቁሙ ሲታይ የተለያዩ ቁሶችን አሃዳዊ ውህደት የሚያሳይ ሲሆን፤ ይልቁንም የክበረ እንቁ በምድር

ጥልቅ ማህፀን ውስጥ በዚህ ውህደት እንዴት እንደሚፈጠር የሚያመለክት ነው።

የከበሩ ድንጋዮች ማለትም እንደ አልማዝ፣ ዕንቁ፣ ሰንፔርና መረገድ የሚፈጠሩት ተራ ከሆኑ አለቶች በምድር ጥልቅ ውስጥ ከፍተኛ ሙቀትና ግፊት ባለበት በረዥም ጊዜ ቆይታ ነው። ሙቀት፣ ግፊትና ጊዜ ተቀናጅተው ተራ የሆኑትን አለቶች ወደ ከበረ ድንጋይነት ይቀይሯቸዋል። ለምሣሌ የድንጋይ ከሰልን እንውሰድ፤ ይህ ከሰል የሚፈጠረው በከፊል መበስበስ ከጀመረ ግንድ ወይም ሌላ እጽዋት፤ አየር በሚያገኝበት ሁኔታ ውስጥ በተወሰነ ሙቀትና ግፊት ከእርጥበት ጋር ሲዋሃድ ነው። ይህ ሂደት በአንድ ጀንበር የሚጠናቀቅ ሣይሆን ምዕተ ዓመታትን ይጠይቃል።

በመሠረቱ የድንጋይ ከሰል ካርቦን ከተባለ ቁስ የተፈጠረ ቢሆንም፤ በኬሚካላዊ ምርመራ የተሠራባቸውን ሌሎች ቁሶች ምንነት ማወቅ ይቻላል። ለረዥም ዘመን ምናልባትም በሽህ ለሚቆጠሩ በርካታ አመታት በማያቋርጥ ሙቀት ግፊት ውስጥ የቆየ የድንጋይ ከሰል ወደ አልማዝነት ይቀየራል። አልማዝ ማለት ንጹህ የድንጋይ ከሰል ማለት ነው። አልማዙ የተፈጠረባቸው የመጀመሪያዎቹ ቁሶች ፈጽሞ በአልማዙ ውስጥ አይገኙም። ግፊቱ ዳግመኛ መለያየት በማይችሉበት ሁኔታ ወደ አሃዳዊ ውህደት እምጥቷቸዋል። ሙቀቱ ደግሞ አንጸባራቂውን ብርሃን አቀዳጅቷቸዋል።



መጋባት ጥቂት ደቂቃዎችን፤ ትዳርን መገንባት ግን የህይወት ዘመንን ጊዜ ይጠይቃል።

እግዚአብሔር ያቀደው ጋብቻ ልክ እንደከበረ ዕንቁ ሲሆን ዕድገቱ የሚገኘውም በጊዜ ውስጥ ነው። አልማዝ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ አይፈጠርም፤ በሽህ የሚቆጠሩ አመታትን ይጠይቃል። ለመጋባት ጥቂት ደቂቃዎች፤ ትዳርን ለመገንባት ግን የህይወት ዘመንን ጊዜ ይጠይቃል። እግዚአብሔር ጋብቻን ለህይወት ዘመን ሁሉ እንዲሆን ያቀደበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ከተለያየ የህይወትና የኑሮ አቅጣጫ የተለያየ ስብእና ይዘው የመጡ ጥንዶች አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድ በአሃዳዊ ውህደት እንዲዋሃዱ በቂ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ፤ መልካም ጋብቻ የሚጠነክረው በብዙ ግፊት (ነውጥ) ውስጥ ነው። በምድር ላይ ጠንካራው ቁስ አካል አልማዝ

ነው። በሚሊዬን ቶን የሚቆጠር ግፊት በብዙ መቶዎች በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ የድንጋይ ከሰልን፤ ሁሉን መቋቋም ወደሚችል ጠንካራ ቁስነት ማለትም ወደ አልማዝነት ቀይሮታል። አልማዝም መቆራረጥ የሚቻለው በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ የተሰዩ መሣሪያዎችን በመጠቀም ብቻ ነው። እንደዚሁ ሁሉ ውጫዊ ግፊቶችና (ነውጦች) ተግዳሮቶች መልካም ጋብቻን ያጠነክሩታል። ባልና ሚስቱን ይበልጥ እንዲቀራረቡ ያስችላቸዋል። ጠንካራ ሁኔታዎችን በተጋፈጡ ቁጥር ህብረታቸው እየጠነከረ ይሄዳል። ጋብቻ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ወደ አሃዳዊው ውህደት የሚያመጣ በመሆኑና የተለያዮ ውጫዊ ግፊቶች ስለሚያጠነክራቸው ምንም ሊለያያቸው አይችልም።

በእምነት ላይ የተመሠረቱ ጋብቻዎችና ዓለማዊ ጋብቻዎች ለሚከሰቱት ግፊቶች (ነውጦች) ምላሽ የሚሰጡበት ሁኔታ ይለያያል። ሁኔታዎች እየከበዱና እየጠነከሩ ሲሄዱ አለማዊያኖቹ ጥንዶች መለያየት ይጀምራሉ። እንደነዚያ በአሃዳዊ ውህደት እንዳልተጣበቁ ጣውላዎች ሙቀቱና ግፊቱ ባየለ ጊዜ ይለያያሉ። ይሄው ሙቀትና ግፊት ግን በመልካም ጋብቻ የተሣሰሩትን ጥንዶች ይበልጥ ያዋህዳቸዋል። እናም ጋብቻ ፈጽመው መለያየት እስከማይችሉበት ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ያድጋል፣ ይጠነክራል።

የታፈኸ ግጭት

ጋብቻ የሁለት ሰዎች ወደ አንድነት በቀላሉ መምጣት ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ወደ ቀደመ ታሪካቸው ግጭት ጭምር እንጂ። ይህ የባህል፣ የልምድ፣ የትውስታና የልምምዶች መጣረስ ነው። ጋብቻ በተለየ ማራኪ የህይወት ዘመን ውስጥ መጥለቅ እንደማለት ነው።

ጠንካራ ጋብቻን መመስረት ጊዜን፣ ትዕግስትንና ጠንክሮ መሥራትን ይጠይቃል። እያንዳንዱ ሰው የሚያጋጥመው ትልቁ ችግር፤ ከግለሰባዊ ህይወት ወጥቶ ወደጋብቻ ሲመጣ ያለውን የሽግግር ሁኔታ የመቋቋሙ ጉዳይ ነው። እውነቱን እንነጋገርና ሰዎች በአንድ ጀንበር አይለወጡም። አንድን ሰው ስታገባ የምታገባው አንድን ግለሰብ ብቻ ሣይሆን መላውን ቤተሰቡን እናም ሙሉ ታሪካዊ ልምምዱን ጭምር ነው። ለዚህም ነው ብዙውን ጊዜ ይህንን አብሮህ ቤትና አልጋ ሊጋራህ ያለውን ግለሰብ ማንነት ፈጥነህ መረዳት የሚያስችግረው። ሁለታችሁም ብትሆኑ የሃያና የሠላሣ ዓመት የህይወት ልምምዳችሁን ይዛችሁ ነው ወደ ጋብቻ

የምትመጡት። ያ ደግሞ ዓለምን እንዴት እንደምትመለከቷትና ለጥያቄዋም የምትሰጡትን መልስ ያካተተ ነው። በጋብቻ ውስጥ ፈጥናችሁ የምትረዱት ነገር እያንዳንዳችሁ ነገሮችን የምትመለከቱበት መንገድ የተለያየ መሆኑን ነው። ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ መመልከት በጋብቻ ውስጥ ለሚከሰቱ ችግሮችና ግጭቶች ዋንኛው መንስኤ ነው። ይህንን ልዮነት ማቻቻል ጋብቻ በህይወት እንዲቆይ የሚረዳ አብይ ነገር ነው። እንዳለመታደል ሆኖ ብዙ ጋብቻዎች በዚህ ጉዳይ በግልጽ ወድቀዋል።

ሁላችንም ብንሆን የምናየውንና የምንለማውን ሁሉ በራሳችን የህይወት ልምምድ ወንፊት እናጣረዋለን። በሰው ህይወት ላይ የሚከሰቱ አሰቃቂ ገጠመኞች፣ የአካልና የግብረስጋ ጥቃት፣ እያደገ በሄደ ቤተሰብ ውስጥ ያለ የጠራ ቤተሰባዊ ህይወት የትምህርት ደረጃ፣ እምነት ወይም እምነት የለሽነት እነዚህ ሁሉ በዙሪያችን ያለውን ዓለም በምንቃኝበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ አላቸው። የህይወት ልምምዳችንን በመሞረድ ይረዱናል፣ ሌሎች ሰዎች ስለ እኛ የሚሉትን ወይም በእኛ ላይ የሚፈጽሙትን ነገር በምንረዳበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያሣድራሉ። ወደ ጋብቻ ስንመጣ ታጥበንና ታጥነን እይደለም። በዝቅተኛ ደረጃም ይሁን በከፍተኛ እያንዳንዳችን የየራሣችንን ስሜታዊ፣ ስለልቡናዊና መንፈሳዊ ሁኔታዎች ይዘን ነው ወደ ጋብቻ የምንመጣው። በጋብቻ የተዋሃድነው ሰው ምንም ይናገር የምንለማው በራሣችን ታሪክና የልምምድ ወንፊት እያጣራን ነው። ሌላኛውም ወገን የሚያዳምጠው በዚሁ መንገድ ነው። እንግዲህ ይህንን ልዩነት መረዳትና ማቻቻል ረዥም ጊዜና ትዕግስትን የሚጠይቀው ለዚህ ነው።

ከጊዜ ጋር በዕለት ተዕለት የህይወት ግብግብ ውስጥ ባልና ሚስት እርስ በእርስ ወደመተዋወቅ ይመጣሉ። በእንድ አይነት መንገድ ማሰብ፣ ተመሣሣይ ድርጊት መፈጸም፤ ከዚያም አልፎ ተመሣሣይ ስሜት ይሰማቸው ይጀምራሉ። አንዳቸው የሌላኛውን ስሜት ማንበብ ይላመዳሉ፣ ብዙ ጊዜም ያለምንም መጠያየቅ አንዱ በአንዱ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ይገነዘባል። በዝግታም ግለሰባዊ የሆነው ባህሪያቸውና አመለካከታቸው የአንዱ በአንደኛው ውስጥ ይሰርጽና ከአዕምሯቸው ሁሉ "የእንተ" እና "የእኔ" የሚሉ ነገሮች ተወግደው "የእኛ" በሚል ቃል ይተካሉ። እዘህ ጋ ነው የከበረ ዕንቁ የሆነው ጋብቻ መጥራትና ፍንትው ብሎ ማንጸባረቅ የሚጀምረው። አሃዳዊው ውህደት አንድነትን ይፈጥራል።

በሌላ መንገድ መልካምና መንፈሣዊ የሆነ ጋብቻ የከበረውን ዕንቁ ይመስላል። በመሠረቱ የከበረ ዕንቁ ከባህር ዳርቻ አሸዋ ላይ እንደወደቀ ሼል (ቀፎ) በምንፈልገው መንገድ በቀላሉ የምንለቅመው አይደለም። የከበረውን እንቁ ለማግኘት ወደምድር ጥልቀት መቆፈር፣ አለቱን መፈልፈል ያስፈልጋል። እንደዚሁም እንደ እግዚአብሔር ሃሣብ የሆነው ጋብቻ ከመደዴው ህዝብ ጋር በተርታ እየተጓዝን፣ ሁሉም ለው የሚፈጽመውን እየፈጸምን በጭራሽ አናገኘውም። ወደ አግዚአብሔር የልብ ሃሣብ በጥልቀት እየቆፈርን መመሪያዎቹ ምን እንደሆኑ ልንረዳ ያስፈልጋል። የከበረው ዕንቁ ብርቅየ እንደሆነ ሁሉ እውነተኛ የሆነ ጋብቻም በቀላሉ አይገኝም። አቋራጭ መንገድ ወይም አንድና አንድ ሁለት ብለን እንደምናስላው የሂሳብ ስሌት ቀላል ብሎ ነገር የለም። የሚያስፈልገን አንድ ነገር አንድ ነገርም ብቻ ነው - ይመራን ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል፣ መረዳትንና መለየትን ይስጠን ዘንድ የእርሱ መንፈስ።



እንደዚሁም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ጋብቻ ከመደዴው ህዝብ ጋር በተርታ እየተጓዝን፣ ሁሉም ሰው የሚፈጽመውን ሁሉ እየፈጸምን በጭራሽ አናገኘውም።

ትልቅ ዋጋ ያለውን የከበረ ነገር ከመሬት ወድቆ ማግኘት የተለመደ ነገር አይደለም። ተፈላጊው ነገር አዘውትሮ የሚገኘው በጥልቀት ውስጥ በመሆኑ ብዙ ልንለፋና ልንሠራለት ይገባል። መልካም ጋብቻ ድንገታዊ ነገር ሣይሆን ሠርተን በጥረት የምንፈጥረው ነው። የከበረ አልማዝ የረኾም ጊዜ ያልተቋረጠ ሂደት ውጤት እንደሆነ ሁሉ፣ ጋብቻም እንደዚያው ነው።

እናም ጋብቻ ምንድነው? ጋብቻ እግዚአብሔር ያጸናው ተቋም ነው። በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረግ የህይወት ዘመን ሁሉ ግንኙነት ነው። ከጊዜ አንጻር ከህይወት ግለትና ግፊት ሁለት ሰዎች በጋብቻ ቃል ኪዳን ወደ አንድነት ይመጣሉ።

የቀደመው ማንነታቸው መቼ አብቅቶ አዲሱ ማንነታቸው መቼ እንደጀመረ እንኳን ሳይታወቅ አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ ይከስማሉ። ጋብቻ ሂደት ነው፣ የሁለት ልዩነት ያላቸው አላባዎች ወደ አሃደዊ ውህደት መምጣት ነው። ጋብቻ የሚንቦገቦግ አንጸባራቂ የፍቅር ፈርጥ፣ ታማኝነት፣ ደግሞ አጭርና ዘላቂነት በሌላት ዓለም ውስጥ ደምቆ የሚበራን ሃላፊነት የመወጣት ግዳጅ ነው።

ማጠቃለያ

1. ጋብቻ የእግዚአብሔር ሃሣብ በመሆኑ ዛሬም መልካም ሃሣብ ነው።
2. ጋብቻ ቀደምትነት ያለው መሠረታዊ ተቋም ነው።
3. መዋለድ የጋብቻ ቀደምት አላማ አይደለም።
4. የግብረስጋ ግንኙነት የጋብቻ ቀደምት ዓላማ አይደለም።
5. እንደ እግዚአብሔር እቅድ የሆነ ጋብቻ ሁለት የተለያዩ አላባዎች በአሃዳዊ ውህደት አንድ እንደ ሚሆኑበት ያለ የከበረ ዕንቁ ነው።
6. መልካምና መንፈሣዊ ጋብቻ በጊዜ ውስጥ ያድጋል።
7. መልካምና መንፈሳዊ ጋብቻ በግፊት (በተጽእኖ) ውስጥ ያድጋል።
8. መልካምና መንፈሳዊ ጋብቻ በአሃዳዊ ውህደት የሚፈጠር አንድነት ነው።

ምዕራፍ ሁለት

ጋብቻ ክቡር ነው

ከጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ ወደ ጀርመን ባደረኩት ጉዞዬ ወደ ፍች የተቃረቡ ባልና ሚስትን የማማከር እድል አግኝቼ ነበር። ከአየር ማረፊያው የተቀበለኝ ባልየው ነበር። በመኪና የሁለት ሰዓት ተኩል ጊዜ በፈጀው መንገዳችን የልቡን ሊያጫውተኝ በቂ ጊዜ ነበር። ሚስቱንም እንዴት ይወዳት እንደነበር ልቡን ከፍቶ አጫወተኝ። አሁን ግን ነገሮች ሁሉ ትክክል ሊሆኑ እንዳልቻሉ ነገረኝ። ባልተቋረጠ ሁኔታ በትዳራቸው ላይ የተፈጠረ ጫናና ፍትጊያ "የትዳር ነገር ይብቃን" ወደሚሉበት ሁኔታ ገፍቷቸዋል። በአንድ አልጋ ላይ እስከማይተኙበት ሁኔታ ነገሮቹ እጅግ መረዋል። ይህ የተቸገረ ባል በእርሱና በሚስቱ መካከል ነገሮች እንደዚህ የከረሩበትን ምክንያት ሊረዳ አልቻለም። አንድ መልስ እንድሰጠውም ይጎተጉተኝ ጀመር። እኔም ጋብቻ ሁለት ሰዎች በጋራ የተሳተፉበት ተቋም በመሆኑ ለብቻው መልስ እንደማልሰጠው ነገርኩት። ሁለቱንም በአንድነት ማነጋገር ነበረብኝ።

ወደ ቤታቸው ስደርስ ጨላልሞ ነበር። ወደ መኝታችን ግን አልሄድንም፤ ሦስታችንም ተቀምጠን በጉዳዩ ላይ ውይይት ጀመርን። ነገራችንን በቋጠርን ጊዜ ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖ ነበር። የገጠማቸውን ችግር በገለጹልኝ ጊዜ፤ በጋብቻ ውስጥ ትልቅ ውድቀት የሆነውን ነገር ለመረዳት ቻልኩ። ይህም ሰዎች የገቡበት ይህ ተቋም እጅግ ክቡር መሆኑን ካለመገንዘባቸው የተነሣ የሚመጣ ችግር ነው።



በጋብቻ ውስጥ ስኬት ስማምጣት ጠላኑ ነገር ተጋቢዎች እርስ በእርሳቸው ስንዳቸው ለሌላቸው በታማኝነት መሠጠታቸው ሣይሆን፤ ፍጹም ለሆነ የጋራ ተጠቃሚነት ለገቡበት ተቋም፤ ለጋብቻ፤ በታማኝነት መሰጠታቸው ነው።

ጋብቻ በጽኑ መሠረት ላይ የማይለወጥ ሆኖ የተዋቀረ ተቋም ነው። በዚህ ተቋም ውስጥ የሚገቡት ሁለት ሰዎች እያደጉና እየበሰሉ በሄዱ መጠን ያለማቋረጥ ይለወጣሉ። እነዚህ ለውጦች መጽናናት የሌለባቸው፣ በፍርሃት የተሞሉና በቀላሉ ግጭትን የሚጭሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና የከበረውና የጸናው ጋብቻ ባለትዳሮቹ ወደ አሃዳዊ ሙህደት በሚያደርጉት ጉዞ በለውጦቹ

ማዕበልና ወጀብ እንዳይናወጡ ጠንካራ መልዕቅ ይሆንላቸዋል። ጋብቻን እንደተቋምነቱ የማይለወጥ ባህሪውን አምኖ መቀበል፤ ባለትዳሮቹ በግጭት ጊዜ ትዳራቸውን አፍርሰው ሌላ አማራጭ ፍለጋ እንዳይማልሉ ብርቱ መጽናናት ይሆንላቸዋል።

በጋብቻ ውስጥ ስኬት ለማምጣት ወሳኙ ነገር ተጋቢዎቹ እርስ በእርሳቸው እንዳቸው ለሌላቸው በታማኝነት መሰጠታቸው ሳይሆን፤ ፍጹም ለሆነ የጋራ ተጠቃሚነት ለገቡበት ተቋም፤ ለጋብቻ፤ በታማኝነት መሰጠታቸው ነው።

ዋነኛው ነገር ማንን መውደድህ ሣይሆን ምን መውደድህ ነው

መጽሐፍ ቅዱሣችን ጋብቻን ከሌሎች ተቋማት ይልቅ የከበረና እጅግ ዋጋ ያለው ነገር አድርጎ ያቀርብልናል። ዕብ 13÷4 እንዲህ ይላል፤ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹህ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል"። በኪንግ ጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ደግሞ ይህ ጥቅስ እንዲህ ይነበባል፤ "ጋብቻ በሁሉ ክቡር ነው"። "ክቡር" የሚለው ቃል የክሪክ ቋንቋ መነሻ ቃል "ቲሚዮስ" የሚል ሲሆን ይህም እሴት ያለው፣ ውድ፣ ክቡር፣ ግምት የሚሰጠው፣ የተወደደ፣ ብርቅ ማለት ነው። "በሁሉ" የሚለው አቻ የግሪክ መነሻ ቃል "ፓስ" የሚል ሲሆን ትርጓሜውም ሁሉ፣ ጥቅል፣ እያንዳንዱ፣ ሙሉ፣ በነገር ሁሉ፣ ምንም ቢሆን፣ ማንም ቢሆን የሚል ነው። በመሆኑም ጋብቻ ሊከበርና ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባዋል። በየትም ሥፍራ፣ በሁሉም ለምት፣ በነገር ሁሉ ከፍተኛው ክብር ሊቸረው ያስፈልጋል። እንግዲህ ስለ ጋብቻ የእግዚአብሔር እቅድ ይህ ነው።

ጥቅሱ "ጋብቻ በሁሉ ዘንድ ክቡር ይሁን" እንደሚል አስተውል። ይህ ጥቅስ የሚናገረው በጋብቻ ውስጥ ስላሉ ሰዎች አይደለም። በብዙ ሰዎች ዘንድ የተሰመደው ትርጉም የጋብቻ ተጣማሪዎች እርስ በእርስቸው እንዲከባበሩና አድናቆት እንዲለጣጡ የሚል ነው። እንዲህ መሆኑ መልካም ቢሆንም በፍጻሜው ላይ ግን ጋብቻ ውጤታማ እንዲሆን አያደርግም። እጅግ ጠቃሚው ነገር ጋብቻን ራሱን ማክበርና ማድነቅ ነው። ሁላችንም ሁልጊዜ ተወዳጆች ልንሆን እንደማንችል ያለውን እውነት አምነን እንቀበል። አንዳንድ ጊዜ የባሎቻችንን ወይም የሚስቶቻችንን ልብ የሚሰብርና የሚያስቆጣ ንግግር ወይም ድርጊቶች እናደርጋለን። ምናልባት እርሱ ወይም እርሷ እጸፋውን ይመልሳሉ። በየትኛውም መንገድ

ይሁን ለጋብቻ ክብርንና አድናቆትን መስጠት፤ አንዳችን ለአንዳችን ክብርንና አድናቆትን መስጠት በማንችልባቸው እንደዚህ ባሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችና ወቅቶች ደግፎ ሊያቆመን ይችላል።

ዘላቂነት ያለውን ደስተኛ ጋብቻ ለማምጣት ቁልፍ የሆነው ጠቃሚ ጉዳይ ማንን መውደዳችን ሣይሆን ምን እንደወደድን መረዳቱ ነው። ይህንን ሃሳብ ጥቂት ላብራራው። እስኪ በመካከለኛ እድሜ ላይ የሚገኙ ሁለት ጥንዶችን በምሣሌነት ወስደን ዩሐንስና ሣራ እንበላቸው። ዮሐንስና ሣራ በአንድ የግብዣ ሥፍራ ላይ ተገናኝተው ጨዋታ ጀመሩ። ዮሐንስ እድሜው 22፣ መልክ ቀናና ባለጥቁር ፀጉር፣ ሰውነቱ ሽንቃጣ፣ ወፈር ያለ ደመወዝ የሚያገኝ ነው። ሣራ እድሜዋ 20፣ ቆንጅዬ፣ አስተዋይ፣ ዘንፋላ ፀጉር ያላትና ጥሩ ሥራ ያላት ነች። ልባቸው ስለተፈቃቀደ አብረው መውጣት አዘወተሩ። ግንኙነታቸውም እያደገ መጣ። አንድ ቀን ዮሐንስ "ሣራ . . . እወድሻለሁ" አላት። ሣራም መልሣ "እኔም አወድሃለሁ ጆን" አለችው።

ዮሐንስና ሣራ በፍቅር ከወደቁበት ቀን ጀምሮ ለመጋባት ወሰኑ። ዮሐንስ ለሣራ የእጮኝነት ቀለበት አጠለቀላትና የጋብቻቸውን ጉዳይ ማውጠንጠን ጀመሩ። በመካከላቸው ያለው ፍቅር ደስተኞች አደረጋቸው፤ ይህም ፍቅር በዘላቂነት በደስታ እንደሞላቸው እንደሚቀጥል ተስማቸው። ጊዜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር ግን አንዳቸው በአንዳቸው ላይ የወደዱት ነገር ምን እንደሆነ አብልጠው ለማወቅ ፈለጉ። ወደፊት ባለው ትዳራቸው ላይ ችግር እንዳይገጥማቸውም ሰጉ።

ዮሐንስ ራሱን መጠየቅ ጀመረ፤ "ሣራን የወደድኳት ለምንድን ነው? እርሷን እንድወድ ምክንያት የሆነኝ ነገር ምንድን ነው? የወደድኩት ማንነቷን ይሆን? ወይስ ሌላ ምክንያት አለኝ? ምናልባት የወደድኩት ውብ የሆነ ሁለንተናዋን ይሆን? ወይስ ዘንፋላ ጸጉሯን? ምናልባትም ጥሩ ሥራዋን?" እርግጥ ነው ሣራ በ20 ዓመት እድሜዋ የተዘረዘሩት መልካም ነገሮች ሁሉ አሏት . . . ግን ግን በአርባ አመት እድሜዋስ? ሣራ በአርባ ዓመት እድሜዋ ሦስትና አራት ልጆች በመውለዷ ምክንያት ውፍረት ብትጨምርና ይህ ሽንቃጣ ሰውነቷ ቢከዳትስ? እነዚያን ህፃናት ማሣደግ ስላለባት እቤት ብትውልና ሥራዋን ብታጣስ? ሣራ በ20 ዓመት እድሜዋ ላይ ያላትን እነኝህን ሁሉ ነገሮች ቢወድ በ40 ዓመቷ ላይ የሚከሰቱትን ችግሮች ዮሐንስ እንዴት ሊቀበላቸው ይችላል?

ሣራም እንደ ዮሐንስ ሁሉ ያንኑ ጥያቄ ራሷን ትጠይቃለች፤ በ22 ዓመት እድሜው አንድ ወንድ ሊኖረው ይገባል ብላ የምታስበው ነገር ሁሉ በዮሐንስ ውስጥ አግኝታዋለች። ዕድሜው 42 ዓመት በሞላ ጊዜና ያን ውብ ጥቁር ፀጉሩን ባጣ ጊዜስ? ለተከታዮቹ 20 ዓመታት በቢሮ ውስጥ በመሰራቱ ያን ቀልጣፋና ሽንቃጣ የሰውነት ውበት ባጣ ጊዜስ? የሚሠራበት ካምፓኒ በኪሣራ ምክንያት ቢዘጋና ሥራውን ቢያጣ በዚህ ምክንያት ሊያገኝ የቻለው ሌላ ሥራ የማንበኛ ረዳትነት ብቻ ቢሆንና ቀድሞ ይከፈለው የነበረው ደመወዝ አሁን ከሚያገኘው በግማሽ ቢቀንስስ?

ማንን እንደወደድን ማወቁ ብቻ በቂ አይደለም፤ ይልቁንም ምን እንደወደድን ልናውቅ ያስፈልገናል። ደስተኛና ስኬታማ የሆነ ትዳር ለመገንባት ይህ እጅግ ዋነኛ ነገር ነው።



ሰብረን የምንኖረው ካገባነው ሰው ጋር ስደደበም፤ ምክንያቱም ያ ሰዉ ሁሌጊዜም በለውጥ ሂደት ውስጥ ነው።

ላስጨብጣችሁ የምፈልገው ነጥብ ይህ ነው። የምንኖረው ካገባነው ሰው ጋር አይደለም። ምክንያቱም ያ ሰው በየጊዜው በለውጥ ሂደት ውስጥ ነው። የዛሬ ሚስቴ ያኔ ያገባኋት ያች ሴት አይደለችም። እኔም እርሷ ያነየ ያገባችኝ ሰው አይደለሁም። ሁለታችንም በብዙ መንገድ በየዕለቱ በለውጥ ሂደት ውስጥ ነን።

በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፍን፤ እርስ በእርስ በመተማመን ብቻ ትዳራችን እንዲቀጥል ስንፈልግ ያን ጊዜ ጠንካራ ችግር ውስጥ እንወድቃለን። ምን ያህል እርስ በእርሳችን ብንዋደድ፣ አድናቆትን ብንሰጣጥ፤ ይህ እስከ ዘለቄታው ለመራመድ ዋስትና አይደለም። ክቡር የሆነውን ጋብቻ እንደማይለወጥ ተቋም በመቁጠር ከበሬታችንንና አድናቆታችንን መግለጽ በየጊዜው በሚለዋወጥ ግንኙነታችን ውስጥ ተረዳድተን እንድንኖር ይረዳናል።

ያገባነው ሰው አብረን የምንኖረውን አይደለም። ለዚህ ነው ጋብቻ ራስ ከባልና ከሚስት ይልቅ ሊከበርና ሊደነቅ የሚገባው። ሰዎች ይለወጣሉ ጋብቻ ግን ጸንቶ ይኖራል። ከትዳር ጓደኞቻችን ይልቅ አብልጠን ልንወድ የሚገባው ትዳራችንን ነው።

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ ይልቅ ትልቅ ነው

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ ይልቅ ሊከበርና ሊደነቅ እንደሚገባው ስንናገር፤ በእርግጥ ምን እያልን ነው? ይህን ጉዳይ በምሳሌ ለማብራራት ጋብቻን ሥራን በመሥራት እንመስለው። እንበል እኔና አንተ በአንድ ካምፓኒ ውስጥ ነው የምንሰራው። ካምፓኒው እንደ አንድ ተቋም ቢሆንና እኛም ተቀጥረን የምንሠራ ሠራተኞች በመሆናችን ተቋሙ የሚፈልግብንን ተግባራዊ ግዳጅ እየተወጣን ነው።

የሥራ ገበታችን አጠገብ ለአጠገብ ባሉ ጠረጴዛዎች ላይ በመሆኑ መልካም የሥራ ግንኙነት ለረዥም ጊዜ አዳበርን። አንድ ቀን ግን በሥራ ጉዳይ ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጠረና አላስፈላጊ የሆኑ ቃላት ተለዋወጥን። ዳግመኛ እርስ በእርሳችን መነጋገር እንደሌለብንም ወሰንን።

እና ቀጥሎ ምን ተከሰተ? ሥለተጋጨን ብቻ ሥራችንን መልቀቅ አለብን? እንደዚያ ሊሆን አይችልም። (አንዳንዶች በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሥራቸውን ለቀው እንደሚወጡ አውቃለሁ፤ ይህ ግን ያለመብሰል ምልክት ነው።) ይልቁንም እንደተቆጣንና እንደተደበርን ወደቤታችን እንሄዳለን፤ በቀጣዩ ቀን እንደገና ወደ ሥራችን ተመልሰን እዚያው ጠረጴዛችን ጀርባ እንቀመጣለን። ለምን? ምክንያቱም ከቀጠረን ተቋም የተቀበልነው የሥራ ሃላፊነት፤ በውስጡ አብረውን ከሚሠሩ ሠራተኞች ጋር ካለን ግንኙነት ይልቅ ለእኛ ወሣኝ ነገር ነው። አንድ ሣምንት አለፈ፣ አሁንም አንነጋገርም። ነገር ግን ክእነዚያው ጠረጴዛዎች ጀርባ ተቀምጠን መሥራታችንን ቀጥለናል። በመካከላችን ግጭቱ እንዳለ ነው፤ ይሁንና የቀጠረን ተቋም የጣለብንን የሃላፊነት ግዳጅ በመወጣት ላይ ነን።

ሌላ ሣምንት አለፈ፤ እናም አንድ ቀን በድንገት "ላፒስህን ልታውሰኝ ትችላለህ?" ስትል ጠየከኝ። እኔም ይቻላል አልኩ። ቀስ በቀስ ያለመግባባታችን እየከሰመ ሄደና ግንኙነታችን እንደቀድሞው ተመለሰ። ብዙም ሣይቆይ ልክ ብዙ ዘመን አብረው እንደቆዩ ጓደኛ ሞች መሣቅ፣ መጫወት፣ አብረን ለምሣ መውጣት በመጀመራችን ሁኔታዎች ሁሉ ወደ መረጋጋት መጡ። ከግጭታችን በኋላ ወደ እርቅ የመጣነው፤ አንዳችን ለሌላችን ካለን ስሜት ይልቅ ከቀጠረን ተቋም ጋር የተሣሰርንበት ምክንያት ጠንካራ በመሆኑ ነው። እንደዚህ ያሉ ጉዳዮች ሁልጊዜም በተቋማት ውስጥ የሚከሰቱ

ነገሮች ናቸው። ይሁን እንጂ እጅግ ዘግይተው ቢሆን እንኳን ልዩነታቸውን ያስታርቃሉ፤ ምክንያቱም በመካከላቸው ካለው ችግር ይልቅ የቀጠራቸው ተቋም ትልቅ በመሆኑ ነው።

ይህ እውነት ጋብቻን በአግባቡ ለመገንዘብ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የጋብቻ ተቋም ከግለሰባዊ ስሜታችን ይልቅ አስፈላጊ ነው። ክትዳር ጓደኞቻችን ጋር ለላም የማንሆንበት ጊዜ አለ፤ ያ ግን ክትዳራችን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ግለሰባዊ ስሜታችንና ግጭቶቻችንን ከጋብቻችን ጋር ማያያዝ የለብንም። ጋብቻ የከበረና የማይለወጥ ሲሆን እኛ ግን አንዳንድ ጊዜ ክብር የጎደለንና ሁልጊዜም የምንለዋወጥ ነን። ጋብቻ ፍጹም ነው፤ እኛ ግን ፍጹማን አይደለንም።

ለትዳር ጓደኞቻችን ታማኝ ከመሆን ይልቅ ለትዳራችን ታማኝ መሆን ለጋብቻ ስኬታማነት ቁልፍ ጉዳይ ነው። ባለቤቴ ምንም ብትናገረኝ ወይም ብታደርስብኝ ስፍራ መቀየር አልችልም። እኔም ምንም ላድርጋት እርሷም ከሥፍራዋ አትንቀሳቀስም። እርስ በእርሳችን ከተቆራኘንበት ነገር ይልቅ ከጋብቻችን ጋር የተቆራኘንበት ጉዳይ ጥብቅ ነው። ስምምነት ሲጠፋና ግጭት ሲፈጠር ፈጥነን ሁኔታውን እናስተካክላለን፤ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ጊዜያዊ ናቸው። በእነዚህ ጊዜያዊ ነገሮች ምክንያት ጋብቻችንን አናፈርስም። ከእኛ ይልቅ ጋብቻችን ትልቅ ነውና።

በሥራ ቦታ ከአንድ ሰው ጋር ብትጋጩ፤ ስለቀጠራችሁ ተቋም ስትሉ ፈጥናችሁ ወደ እርቅ ትመጣላችሁ። ምክንያቱም ካምፓኒው ከሁለታችሁም ይልቅ ትልቅ ነው። የግድ አብራችሁ መሥራት ስላለባችሁ ችግራችሁን መፍታት አስፈላጊ ነው። ስለጋብቻ ይህንኑ መርህ ልንገለገልበት እንችላለን። ባልና ሚስት በግጭት ውስጥ ሲገቡ ፈጥነው ወደ አንድነትና ወደ ስምምነት መምጣት አለባቸው። እርግጥ ነው ልዩነታችን እንዳለ ነው፤ ደግሞም በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ ነን፤ ይሁንና ከሁለታችንም ይልቅ ጋብቻችን ትልቅ ነው። ለረዥም ዘመን አብሮ የመኖር ተስፋ የገባንበት ተቋም በመሆኑ ልዩነትን ማቻቻል ግድ ነው። ይህ ጉዳይ ተግባራዊ እንዲሆንም የሚገባንን ሁሉ ለማድረግ ቸል አንበል።

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ ይልቅ ትልቅ ነው። እግዚአብሔር ቀድሞውኑ ሊያቅደው እንዲህ እንዲሆን አድርጎ ነው። ጋብቻ የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ አይደለም። ጋብቻ ሁለት ብቁ ያልሆኑ ለዎች ፍጹምነት በሌላቸው ከናፍርቶቻቸው፤ ፍጹም በሆነው

እግዚአብሔር ፊት ምህላ አድርገው የሚገበብት ፍጹም የሆነ ተቋም ነው።

ፍጹም የሆነ ምህላና ፍጹም ያልሆኑ ከናፍርት

ምህላ ከቃል ኪዳን የተለየ ነው። ቃል ኪዳን እንድ ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ለሌላ ለው የሚሰጥ የተስፋ ቃል ነው። ለምሳሌ አባት ልጁን ወደ ዱር እንሰሳት ማቆያ ፓርክ እወስድሃለሁ ብሎ ቃል እንደሚገባለት ማለት ነው። በሌላው አንጻር ምህላን የወሰድን እንደሆነ፤ ምህላ እርግጠኝነትና እስገዳጅነት ባለው ቃል ውስጥ፤ ምህላ እድራጊውን በተወሰኑ ድርጊቶች፣ አገልግሎቶችና ሁኔታዎች ውስጥ የሚያስር ነው። ያላገባ፣ ያገባ፣ የፈታና ከፍች በኋላ ያለ ህይወት በሚል ርዕሰ ቀደም ብዬ በጻፍኩት መጽሀፍ እንደገለጽኩት ማለት ነው።

ቃል ኪዳን ወደፊት እንድን ነገር ለማድረግ የሚነገር ቃል ሲሆን፤ ምህላ ግን የምህላው ቃል ጸንቶ እሰከሚቆይበት ጊዜ ድረስ እንድን ነገር ለማድረግና እያደረጉም ለመቆየት በገቡት ቃል ውስጥ መታሰር ነው። እንዳንድ ምህላዎች ለህይወት ዘመን ሁሉ የሚገቡ ሲሆን ሌሎች ምህላዎች ግን በጊዜ ቅጥር ውስጥ የሚሰጡ ናቸው።

እግዚአብሔር ምህላን የሚመለከተው በእጽንኦት ነው። ምህላ እስከሞት የከበደ ነገር በመሆኑ ምክንያት ነው እግዚአብሔር "ልትጠብቀው የማትችል ከሆነ ምህላን አታድርግ" ያለው። "እስከሞት" ማለት እስከ ተፈጥሯዊው ሞት ማለት አይደለም። በብሉይ ኪዳን ምህላ ማድረግ ማለት፤ ምህላውን ልንፈጽመው ባንችል እግዚአብሔር እንዲገድለን ፈቃድ መሰጠታችን ነው። በዚያን ዘመን ሰዎች ምህላን ቢያፈርሱና የእግዚአብሔር ምህረት ጣልቃ ካልገባ መራራ ነገር ይከሰታል።

ምህላ ለሌላ ሰው የሚገባ ቃል አይደለም። ምህላ ለእግዚአብሔር ይደረጋል ወይም በእግዚአብሔር ፊት ይደረጋል። በሌላ አባባል እግዚአብሔርን እንደ ምስክር በመጥራት ይፈጸማል።

እግዚአብሔር በምህላ ላይ ያለው አቋም ምን እንደሆነ ብዙ ጊዜ በቃሉ ላይ ተገለጿል። "ሰነፎች ደሰ አያስኙትምና ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልክ ጊዜ ትፈጽመው ዘንድ እትዘግይ፤ የተሳልከውን ፈጽመው" (መክ 5÷4-5)።

ጋብቻ ምህላ ነው። ይህንን ምህላ ማፍረስ ከባድ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ምህላን ባፈረስን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት አብሮ ይፈርሳል። የቀደመው የብሉይ ኪዳን ነብይ ሚልኪያስ እግዚአብሔር የጋብቻን ምህላ በሚመለከት ያለውን አክብሮት እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ "ይህንን ደግሞ አድርጋችኋል፤ እግዚአብሔር ዳግመኛ ቁርባኑን እንዳይመለከት ከእጃችሁም በደስታ እንዳይቀበለው፣ መሰዊያውን በእንባና በለቅሶ በሀዘንም ትከድናላችሁ። እናንተም ሰለምንድንነው? ብላችኋል። ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንም ሚስትህ ሆና ሣለች እርሷን አታለሃታልና፤ እግዚአብሔር በእንተና በልጅነትህ ሚስት መካከል ምስክር ስለሆነ ነው" (ሚል 2÷13-14)።

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ ይልቅ ትልቅ ነው

ጋብቻ በሁለት ፍጹምነት በሌላቸው ሰዎች፤ ፍጹም በሆነው እግዚአብሔር ፊት የሚከናወን ፍጹም የሆነ ምህላ በመሆኑ ውጤታማ የሚያደርገው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከጋብቻ ጓደኛህ ፍጹም የሆነ ነገር አትጠብቅ፤ ጋብቻ ፍጹም ቢሆንም ሰዎች ግን ፍጹማን አይደለንም። ይህንን ልትቀበል ካልፈቀድህ እስኪ ወደ መስታወት ሄደህ ተመልከት። የጋብቻ ተቋም ዘላቂነት ያለውና የፀና በመሆኑ ፈጽሞ አይለወጥም። ሰዎች ግን በጊዜ ውስጥ ሁሉ እንለወጣለን። በጋብቻህ ስኬታማ መሆን የምትፈልግ ከሆነ ለማይለወጠው ተቋም ታማኝ ሁን። ይህም የጋብቻ ተቋም ነው። በጥንካሬ እንድትቆም የሚያጸናህ ይህ ብቻ ነው።

ተቋሙን ከመቀያየር ለችግር ከመፍትሔ ስደደሰም

አንድ ጊዜ ጋብቻ ሊከበርና ዋጋ ሊሰጠው የተገባ ተቋም መሆኑን ከተረዳን፤ የፍች ሀሣብ ወደ አይምሯችን አይገባም። ለዚህ የጋብቻ ተቋም አክብሮት መሰጠት፤ ከተጋቢዎች እንደኛው ወገን ወይም ሁለቱም ክብር በሌለው ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ ደግፎ ሊያቆም የሚችል ረዳት ነው። በመካከላችን በሚፈጠሩ ችግሮችና ግጭቶች ምክንያት ይህንን ተቋም እርግፍ አድርገን ጥለን እንሄድም።

በምንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የብዙ ሰዎች ችግር፤ ሁኔታዎች እነርሱ በሚፈልጉት መንገድ ሆነው ካላገኟቸው በተደጋጋሚ ሥራቸውን ትተው ወደ ሌላ ሥራ ይኮበልላሉ። ይህ ደግሞ አለመብለል፣ ችግርን ተጋፍጦ መፍትሄ የመፈለግ ብቃት እንደሌላቸው የሚያሣይ ብቻ ሣይሆን፤ ብቃት ባላቸው አሰሪዎች

አይን ታማኝነት የጎደለው አድርጎ ያስቆጥራል። እስኪ እንዲህ ሆነ ብለን እናስብ፤ ሥራ ለመቀጠር ሄደህ ለቃለ መጠይቅ ቀረብክ። ጠያቂዎቹ፤ በመጨረሻ የሠራኸው የት ነበር? የሚል ጥያቄ አቀረቡና ይህንን መለስክ። እንደገና፤ ለምን ሥራህን ለቀቅህ? የሚል ጥያቄ ተከተለ። የዚህ ጥያቄ አላማ ምን ያህል ታማኝ እንደሆንክ ለመገምገም ነው። ይህ የአሁኑ ቀጣሪህ ምን አይነት ሰው እንደሆንክና ለካምፓኒው ዋጋ ያለህ ሰው መሆንና አለመሆንህን ጭምር አጣርቶ ማወቅ ይፈልጋል።

ምናልባት "ከሥራ የለቀኩት አለቃዬን ስላልወደድኩት ነው" ወይም "በዚያ ከሚሠሩ አንዳንድ ሠራተኞች ጋር ችግሮች ስለነበሩኝ ነው" ብለህ መለስክ እንበል። ይህ የአሁኑ አሠሪህ አንተን ለመቅጠር ፈቃደኛ ባይሆን አትደነቅ። ቀድሞ ከሠራህለት አሠሪ ይልቅ ለእርስዱ ልዩ ነገር ልታደርግ እንደምትችል በምን ማረጋገጥ ይችላል? ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ አሥር አሠሪዎች እንዳቀያየርክ ካወቀ በእርግጠኝነት እነግርሃለሁ አይቀጥርህም። አንተ መዝግበህ ከያዝካቸው የቀደሙ አሠሪዎችህ ዝርዝር ውስጥ በአሥራ አንደኛ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገብ አይፈልግም።

ተቋምን መቀያየር የችግር መፍትሔ አይሆንም። ለእድገትና ለብስለት ቁልፍ የሆነው ነገር፤ አስቸጋሪ በሆኑ ጊዜያቶች ጸንቶ መቆምና ችግሮችን ለመፍታት ጠንክሮ መሥራት ነው። ይህ ደግሞ በሥራው ዓለም እርግጥ እንደሆነ ሁሉ ለትዳሩም ዓለም የሚሠራ ነው። ብዙዎች፤ በትዳራቸው ውስጥ ችግር ሲፈጠር፤ ትዳራቸውን አፍርሰው ሌላ ትዳር ቢመሰረቱ ችግሩ የሚቃለል ይመስላቸዋል። እውነቱ ግን ይህ አይደለም። የጋብቻ ችግሮች ብዙውን ጊዜ በአንድ ወገን ምክንያት የሚፈጠሩ አይደሉም፤ ችግሩን ከመሠረቱ ሣይፈቱ ሌላ ትዳር ቢመሠርቱና ጊዜያዊ እፎይታን ቢፈልጉም፤ ያንኑ የቀደመውን ችግር ወደ አዲሱ ትዳር ይዘው መግባታቸው የማይቀር ነው። ምናልባት ችግሮቹ የተለየ ቅርጽ ይዘው ሊከሰቱ ይችሉ ይሆናል፤ ዞሮ ዞሮ እነዚያው የቀደሙ ችግሮች ናቸው።



ተቋምን መቀየር ለችግሬ መፍትሄ አይደለም። ለእድገትና ለብስለት ቁልፍ የሆነው ነገር ለስቸጋሪ በሆኑ ጊዜያቶች ጸንቶ መቆምና ችግሮችን ለመፍታት ጠንክሮ መሥራት ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በምዕራብ ዓለም ውስጥ ለጋብቻና ለቤተሰብ ከፍተኛ ክብር የሚሰጥበት ጊዜ ነበር። የፍች ጉዳይ እምብዛም የማያሳስብ ከመሆኑም በላይ ቢከሰት እንኳን ክብድ

ማህበራዊ ቅሌትን የሚያስከትል ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የጋብቻና የቤተሰብ ጽንሰ ሀሣብ ከፍተኛ ጥቃት የደረሰበት ባለፉት ሁለትና ሦስት ትውልዶች ውስጥ ነው። ዛሬ በየትም ሥፍራ በከፍተኛ ፍጥነት የተስፋፋው ሰዋዊ የሆነው ፍልስፍና በፍች ላይ ይሰነዘር የነበረውን ማህበራዊና ሥነ ምግባራዊ ነቀፌታ እንዲወገድ አድርጎታል። በውጤቱም ጋብቻና ፍች ተራ የሆኑ ነገሮች ተደርገው በብዙዎች ዘንድ ከመቆጠራቸውም አልፎ በአማኞችም መካከል ይሄው አመለካከት ተቀባይነት እስከማግኘት ደርሷል። ጉዳዮ ከዚህም ዘሎ የአንድ ወንድ ወይም ሴት ማንነት የሚመዘነው በሏቸው የግብረስጋ ጓደኞች ቁጥር እየሆነ መጥቷል። ይህ ጽንሰ ሐሳብ ውጥንቅጡ የወጣ ነው። በሽተኛ የሆነ ሰይጣናዊ አመለካከትም ነው። ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት ማህበረሰብ ውስጥ እየተከናወነ ያለውን እውነት ጠቋሚ ነው።

ጋብቻንና ቤተሰብን በሚመለከት በመላው ዓለም በፍጥነት በመሠራጨት ላይ በሚገኘው ዓለማዊ ፍልስፍና ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ማንነት ለመረዳት አቅቷቸው ደንዝዘዋል። እዚህ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ደግመን ልናጤነው ይገባል። "በፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው። ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ስለዚህ አንድ ስጋ ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው" (ማር 10፥6-9)።

እነዚህ ጥቅሶች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነው ጋብቻ ሁለት ነገሮችን ይነግሩናል። የመጀመሪያው ማጣመር የሚችል እርሱ ብቻ በመሆኑ ወደ አንድነት የሚያመጣውም እግዚአብሔር እራሱ የመሆኑን እውነት ነው። እርሱ በማንኛውም መንገድ ህግ የመጣስ ሀጢያት አያደርግም። በውኑ እግዚአብሔር ሁለት ሃጢያተኞችን ወስዶ አንድነት ሊያጣምራቸውና ሊባርካቸው ይችላል ብሰው ይገምታሉ? ይህን ማድረግማ ሀጢያትን እንደማጽደቅና እንደማበረታታት ይቆጠራል። በፍጥረት መጀመሪያ እግዚአብሔር አዳምንና ሄዋንን ወደ አንድነት ሲያመጣቸው የተቀደሉ፣ ያላደፉና በሀጢያትም ያልጨቀዩ ነበሩ። ከውድቀት በፊት የነበረው ጋብቻቸው እግዚአብሔር ላቀደው ነገር ሁሉ እንደ ናሙና ነበር። እግዚአብሔር ሃጢያት የተሞላበትን ግንኙነት አልባረከም ወደ ፊትም አይባርክም። እግዚአብሔር ይሁንታ ያልሰጠው ባላመኑት

መካከል ወይም በህይወታቸው የተደበቀና በንስሀ ያልነፃ ሀጢያት ይዘው ወደ ጋብቻ የመጡ ወይም የእግዚአብሔርን መመዘኛ ባላሟላ ሁኔታ ውስጥ ከነሀጢያታቸው ወደ ጋብቻ ህብረት የመጡ ጥንዶች ጋብቻቸው በቀላሉ ዘላቂነት ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም::

በማርቆስ 10÷6-9 ባለው ጥቅስ ውስጥ ያለው ሁለተኛው እውነት ደግሞ፤ "እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው" የሚለው ነው:: ሰብአዊ የሆነው የሲቪል መንግስት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተውን የእማኞች ጋብቻ ለማፍረስ ስልጣንም ይሁን ሃይል አልተሰጠውም:: ፍጥረታዊ የሆነው የሲቪል ጋብቻ የተመሠረተው በሲቪል ህግ ላይ ነው:: በመሆኑም ይሄ ጋብቻ በሲቪል ህግ ሊፈርስ ይችላል:: ከእግዚአብሔር ውጭ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ያሰ እግዚአብሔር ጋብቻቸውን ሊበትኑ ይችላሉ:: እግዚአብሔር የቀደሰው መንፈሳዊ ጋብቻ ግን ሰው በደነገገው ትእዛዝ ከቶውንም አይፈርስም:: ይህ ደግሞ ምናልባት እግዚአብሔር እንዲያጣምራቸው ወደ ጋብቻ መሰዊያው ከመጡት እማኞች መካከል ለምንድን ነው ብዙዎቹ ለፍች ወደ ፍርድ አደባባይ የሚወጡት? የሚል አንድ ጠቃሚ ጥያቄ ያስነሣል::

ሰው የመሠረታቸው ፍርድ ቤቶች እግዚአብሔር ያጣመረውን ጋብቻ ሊያፈርሱ ስልጣን የላቸውም:: እንደ እግዚአብሔር ሃሣብ የሆነው ጋብቻ በአሃዳዊ ውህደት የተዋሃደ እንጂ ፈጥነው በሚበጠሱ አቆራኝ ሰንሰለቶች የተያያዘ አይደለም:: እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሊለያየው የሚችለው እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ግን ይህንን አያደርግም፤ ምክንያቱም ይህ በራሱ ማንነት ላይ እንደማመጽ ነው:: ለእማኞች ተቋምን መለወጥ የችግራቸው መፍትሔ አይደለም::

ስኬታማ ጋብቻ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ነው

መልሱ እውቀት ነው:: ስኬታማ ጋብቻ ከፍቅር ጋር ያለው ግንኙነት በመጠኑ ነው:: ፍቅርም ለስኬታማ ጋብቻ ዋስትና አይሰጥም:: ፍቅር ጋብቻን ደስታ የተሞላበት ለማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም፤ በራሱ ጋብቻ በአግባቡ እንዲከናወን አያደርግም:: ጋብቻን በአግባቡ እንዲከናወን ማድረግ የሚችለው እውቀት ብቻ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነ ማናቸውም ነገር በአግባቡ እንዲከናወን የሚያስችለው እውቀት ብቻ ነው:: ስኬት ስለ አንድ ነገር ምን ያህል

በማወቃችን ላይ የተመሠረተ እንጂ ስለነገሩ በሚለማን ስሜት ላይ የተጨሠረተ አይደለም::

ብዙ ባለትዳሮች ይዋደዳሉ፤ በመሆኑም አንዳቸው ለአንዳቸው ያላቸው ስሜት መልካም ነው:: እጅግ ብዙዎች ግን ግንኙነታቸውንና የሚኖራቸውን ትሥሥር እንዴት ውጤታማ ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም:: በግጭቶች አፈታት ጉዳይ ላይ የእውቀትንና የስሜትን ምንነት በመረዳቱ ጉዳይ ስፊ ልዩነት አለ:: አንዳንድ ሰዎች የአይምሮ ምጡቅነት" (Intelligence) ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን የመፍታት ክህሎት አለው ይላሉ:: በጣም እርግጠኛ የሆነው አመለካከት ግን የአይምሮ ምጡቅነት በተረጋጋና ጤነኛ በሆነ አይምሮ እውነትን የመጋፈጥና ችግሮችን የመፍታት ክህሎት ወይም ብቃት ነው:: እዚህ ላይ አንድ ነገር እናስተውል፤ ችግሮችን መጋፈጥ ችግሮችን የመፍታት ያህል ዋጋ ያለው ጉዳይ አይደለም:: አንዳንድ ችግሮች ከቶውንም አይፈቱም:: በአይምሮው ምጡቅ የሆነ ሰው በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ተረጋግቶና የራሱን ማንነት ጠብቆ መኖር የሚችል ሰው ነው:: ሁኔታዎችን ይገመግማል፤ ከችግሮች ጋር በአግባቡ ይጋፈጣል እናም ከችግሩ የሚወጣበትን መንገድ ይፈልጋል::

ዛሬ እየተስፋፋ ያለውን በጋብቻ ላይ የሚሰነዘር የድንቁርና ያህል የተዳፈነ አመለካከት ለመመከት ምጡቅ አይምሮና የእውቀት አስፈላጊነት ወሳኝ ነው:: በጋብቻ ጉዳይ ላይ የሰልጣን ድምጽ የሆነችው ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ እየተቸገረች ትገኛለች:: ምክንያቱም አማኞችም ሆኑ መሪዎቻቸው ጋብቻንና ቤተሰብን በሚመለከት የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ማይምነት ይታይባቸዋል:: ቀድሞ ዋጋ የነበራቸው ነገሮች ሁሉ በቤተክርስቲያንም ይሁን ከቤተክርስቲያን ውጭ አስፈላጊ እንዳልሆኑ በተቆጠሩበት በዚህ ጊዜ፤ ብዙዎች ግራ በመጋባትና ምን አምኖ መቀበል እንደሚገባቸው እርግጠኛ ወዳልሆኑበት ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል:: የዚህ ግራ መጋባት መሠረታዊ ችግር ደግሞ የእውቀት ማጣት ነው::


እውቀት በማናቸውም ጉዳይ ውጤታማ ለመሆንና አስከመጨረሻው ለመዝለቅ ወሣኝ ጉዳይ ነው:: በሆሴ 4÷6 እግዚአብሔር "ህዝቤ እውቀት ከማጣት የተነሣ ጠፍቷል" ይላል:: "ህዝቤ" የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ልጆች የሚያመለክት ነው:: ክርስቲያኖችም እውቀት ያስፈልጋቸዋል:: ከእውቀቶችም ሁሉ ታላቅ

የሆነው እውቀት ደግሞ እግዚብሔርን ማወቅ ነው። ምሣ. 1÷7 "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይጠላሉ" ይላል። ወደ ቤተክርስቲያን አዘውትረን መምጣታችንና እግዚአብሔርን ማምለካችን መልካም ቢሆንም፤ ያለ እውቀት ግን የስኬት ዋስትና ሊኖረን አይችልም።

ወጣት ክርስቲያን በነበርኩበት ጊዜ እጅግ ከምቸገርበት ጉዳይ አንዱ፤ የብዙ ክርስቲያኖችን የፍች ሪፓርት መስማት ነበር። የክርስቶስ ተከታዮች ሆነው በጋብቻቸው ውድቀት ካጋጠማቸው ሌላውማ እንግዲህ ምን ተስፋ ሊኖረው ነው? እነዚህ ክርስቲያኖች እኮ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና ቅዱስ እግዚአብሔርንም እንዲያውቁ የሚጠበቅባቸው ነበሩ። ይሁን እንጂ አብረው ለመኖር በአንድነት መጓዝ አልቻሉም። ይህ እውነት ከሆነ እንግዲህ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገን እንተወው?

በጋብቻ ውስጥ ስኬት ለማምጣት፤ ጌታን ተቀብሎ ከመዳንና በፍቅር ጦፎ ከመንደድ ሌላ ተጨማሪ ነገር እንደሚያስፈልግ የተረዳሁት ዘግይቼ ነበር። እርግጥ ነው አማኝ መሆንም ይሁን ፍቅር በጋብቻ ውስጥ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ለጋብቻ እርግጠኛ የሆነ ስኬት ግን መሠረቱ፤ እግዚአብሔር ራሱ በእቅዱ ውስጥ የደነገጋቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ማወቅ ነው። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሄዋን የሰጣቸው፤ ለስኬታማ ጋብቻና ለቤተሰብ ጠቃሚ የሆኑ መርሆዎች ዛሬም ይሠራሉ። በየትኛውም ዘመን ይሁን ባህል ውስጥ በጽንፈ ዓለም ሁሉ ሊተገበሩ ይችላሉ። ችግር መከሰት የሚጀምረው በእነዚህ መርሆዎች ላይ ስናምጽ ወይም ቸል ልንላቸው ስንጀምር ነው።

በፍቅርም ይሁን በስሜታችን ላይ የተመሠረተ ጋብቻ አረኽም መንገድ አይዘልቅም። ዳግም መወለድም በራሱ ስኬትን አስተማማኝ ለማድረግ በቂ አይደለም። ውጤታማ የሆነ ጋብቻ የተመሠረተው በእውቀት ላይ ነው የእግዚአብሔርን መርሆዎች በማወቅና በመረዳት ላይ።



እግዚአብሔር ጋብቻን ሲያቅድ ስኬታማ እንዲሆን አድርጎ ነው። የርሱ ምክር ብቻ ጋብቻን ስኬታማ ያደርገዋል።

ጋብቻ ክቡር ነው፤ ያቋቋመውም ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ በመሆኑም ጋብቻ የሚመራባቸውን ደንቦች የሚደነግገውም እርሱ ብቻ ነው። የጋብቻ ተቋም፤ በህግ፣ በደንብ፣ እግዚአብሔር

በደነገጋቸውና በቃሉም ውስጥ በገለጣቸው ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ የሚተዳደር ነው።

እግዚአብሔር ጋብቻን ሲያቅድ ስኬታማ እንዲሆን አድርጎ ነው፤ የእርሱ ምክር ብቻም ጋብቻን ስኬታማ ያደርገዋል። ማንኛውም ሌላ ሰው አስቀድሞ አንድ ነገር ከሠራው ሰው በተሻለ ሁኔታ ያንን ነገር ውጤታማ አድርጎ ሊሠራው አይችልም። የቶዮታ መኪና መለዋወጫ ዕቃዎች የታቀዱት ለቶዮታ መኪናዎች እንጂ ለፎርድ መኪናዎች አይደለም። ፎርድ መኪናዎችን የሚወስዱት ፎርድ መኪናዎችን ለማደስ ፈቃድ ወዳለው ጋራዥ ነው። የፎርድ መኪናን ከፎርድ ካምፓኒ ይልቅ የሚያውቀው የለም። አስተዋይ ሰው ከሆነ ማርሰዲስ መኪናዎትን ለጥገና ወደ ፎርድ ካምፓኒ አይወስዱም። የእርሶን ማርሰዲስ መኪና በትክክል ጠግኖ ሊሠራት የሚችለው የማርሰዲስ ጋራዥ ነው። አስተማማኝ ስኬት ማለት ትክክለኛውን "አገልግሎት ሰጭ ሰው" መጠቀም መቻል ነው። ይህም ማለት ከመጀመሪው ሥራውን አርቅቆ ወደ ሠራው ሰው መውሰድ ነው።

የጋብቻም መንገድ እንደዚህ ነው። የጋብቻ ስኬት ማለት በትክክለኛው አገልግሎት ሰጭ ሰው ወይም ህጋዊ መብት ባለው ካምፓኒ መገልገል መቻል ነው። ይህም ማለት የመጀመሪያ ባለቤቱን ምክርና እርዳታ ማግኘት መቻል ማለት ነው። ከፈብራኪው የተሻለ የፋብሪካውን ምርት የሚያውቀው ሌላ የለም። እግዚአብሔር የሚገነዘበውን ያህል ማንም ጋብቻን ሊገነዘበው አይችልም። የፈጠረው እርሱ ነው፤ የመሠረተው እርሱ ነው፣ ያጸናው እርሱ ነው የባረከውም እርሱ ነው። በአግባቡ እንዲከናወን የሚያደርገውም እርሱ ነው። ጋብቻ ክቡር የሆነውም ምንጩ መለኮት እንጂ ሰው ባለመሆኑ ነው። ጋብቻችን የከበረና ስኬታማ እንዲሆን ከፈለግን እግዚአብሔር በቃሉ የገለጸውን መርህ ማወቅ፣ መረዳትና መከተል ይጠበቅብናል። አለማዊው በሆነው አመለካከት ስለጋብቻ ያለውን አለዋቂነትና ያልተስተካከለ መረጃ በትክክል ለማረም ምርጫው ይሄ ብቻ ነው።

መርሆዎች

1. ጋብቻ ሁሰት በማያቋርጥ ለውጥና ብስለት ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች የሚገቡበት ጽኑና የማይለወጥ ተቋም ነው::
2. ክግለሰባዊ ለሜቶቻችን ይልቅ የጋብቻ ተቋም ጠቃሚው ጉዳይ ነው::
3. ሰትዳር ጓደኛ ታማኝ ከመሆን በተሻለ ሁኔታ ለጋብቻ ታማኝ መሆን የለኬት ቁልፍ ነው::
4. ጋብቻ ሁሰት ፍጹማን ያልሆኑ ሰዎች ፍጹም ለሆነው ተቋም ራሳቸውን አሳልፈው የሚለጠቡት፣ ፍጹምነት ከሌላቸው ከናፍርት ፍጹም የሆነ ምህላ የሚሰጥበት ነው::
5. እግዚአብሔር የፈቀደውን ብቻ በአንድነት ያጣምራል::
6. እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን እንግዲህ ሰው አይለየው::
7. የለኬት መሠረቱ በአንድ ነገር ላይ ያለን ለሜት ላይሆን ነገሩን ባወቅንበት መጠን ነው::
8. ለኬታማ ጋብቻ የተመሠረተው በእውቀት ላይ ነው የእግዚአብሔር መርሆዎች በማወቅና በመገንዘብ::

ምዕራፍ ሦስት

ለምንድን ነው የምናገባው?

ሰዎች በበርካታ ምክንያቶች ይጋባለ፤ ምክንያቶቹ አንዳንዶቹ ጥሩ አንዳንዶቹ መልካም ያልሆኑ ናቸው:: ዛሬ ብዙ ትዳሮች ከሚፈርለባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ፤ ተጋቢዎቹ አንድም የለኬታማ ጋብቻን አላማ ወይም መርሆዎችን አለመገንዘባቸው ነው:: እውቀትን አጥተዋል:: የሰሰጠነው ማህበረሰብ በጋብቻ ላይ ያለው የተሳከረ አመለካከት ብዙ ባለትዳሮች በተሣሣተ ዓላማ ወደ ጋብቻ እንዲገቡ አድርጓቸዋል:: እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ ጤነኛና እስከ ህይወት ዘመን የሚዘልቅ ትዳርን አጽንቶ ሊያቆሙ የሚችሉ አይደለም::

ማንም ሰው ቢሆን በጥንቃቄና በግልጽ ሰምን? የሚለውን ጥያቄ ላይመልስ ወደ ጋብቻ መግባት የለበትም:: ሆን ተብሎና በጥልቀት ጉዳዮን በመመርመር ይህን ጥያቄ መመለስ ከጊዜ በኋላ ከሚደርስ በርካታ ችግር፣ የልብ ስብራትና ህዘን ያድናል:: ሰምን እንደሚያገቡ ማወቅም በጋብቻ ላይ መልካም ውሳኔ እንዲወስኑ የሚረዳም ሲሆን በተቃራኒው ስህተት ከሆነ ውሳኔም ይጠብቅዎታል::

ጋብቻን ለመመስረት ጤነኛ ያልሆነ ሰሥር ምክንያቶች

ለማንኛውም ለኬት እውቀት ወሳኝ ነገር በመሆኑ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች ጋብቻን ለማድረግ እንዲወስኑ የሚያደርጓቸውን የተለመዱ ጤነኛ ያልሆኑ ምክንያቶች እንዲገነዘቢቸው ይረዳል:: ከዚህ በታች አለር የሚሆኑ ምክንያቶቻቸውን በዝርዝር አለፍሬያለሁ:: እነዚህ ዝርዝሮች ግምት ወይም ተምኔታዊ ሥራዎች ላይ የተመሠረቱ አይደሉም:: ይልቁንም ከብዙ ለኬታማ ያልሆኑ ወይም የፈረሱ ትዳሮች ተሞክሮ በጥንቃቄ የተወሰዱ ናቸው:: አሁን የህይወትን እውነታ እንጂ ልቦለድ የምናወራበት ጊዜ አይደለም::

1. ቤተሰብን ለመጉዳት

እመናችሁም አላመናችሁ አንዳንዶች ትዳርን የሚመሰርቱት ወላጆቻቸውን ለመጉዳትና በእነርሱ ላይ ጀርባቸውን ለማዞር ነው:: "አሁንስ እነርሱ የሚሉኝን ሁሉ ማድረግ ታከተኝ! እኔ ደግሞ አሳያቸዋለሁ! ከዚህ በኋላ እዚህ የምቀመጥበት ምክንያት የለም!"

ይላሉ። ምናልባትም ወላጆቻቸው በደነገጓቸው ህጎች ከውሃ የቀጠኑ ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶች እጅግ ተማረው ይሆናል። ምናልባትም ወላጆቻቸው የወንድ ወይም የሴት ፍቅረኞቻቸውን ሳይቀበሉላቸው ቀርተዋል። እንደዚህ ያሉ በሚያስቆጡና ምሬትን በሚያስከትሉ ሁኔታዎች አለገዳጅነት በነገሩ ላይ በጥልቀት ሣያስቡና ሳይዘጋጁ ጋብቻን ለመመስረት ይገደዳሉ። በእውነቱ ይህ የሞኝነት እርምጃ ነው። ስለ ጋብቻ ምንም ነገር ባያውቁ እንኳን ከቤተሰቦቻቸው ቁጥጥር የሚያመልጡበት ፈጣኑና ቅርቡ እድል በመሆኑ ዘለው ወደ ጋብቻ ይገባሉ።

ወላጆችን ለመበቀል ሲባል የሚደረግ ጋብቻ እብደት የተሞላበት ነው። ይህም ጋብቻ በፍጥነት ወደ ችግር የሚገሰግስ ነው። ለዚህ ዐይነቱ ጋብቻ ሰዎችን የሚያነሳሱ ስሜቶች ጥላቻ፣ ቁጭትና መራራነት ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ ዘላቂነት ያለውንና ጤናማ ግንኙነት ለመመስረት አስፈላጊዎች አይደሉም። ለስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ፍቅር፣ ራስን ለትዳር አላማ አሳልፎ የመስጠት ቁርጠኝነትና ታማኝነትን የመላሰሉ ብቃቶች አንድም የሉም ወይም ከበቀል ጀርባ ሁለተኛ ደረጃ የትዳር ሰበብ ነገር ሆነው ተቀምጠዋል። በዚህ የበቀል ዓላማ ትዳር የመሠረተ ማንም ሰው የትዳር ጓደኛውን የሚመለከተው እንደ ፍቅረኛ፣ እንደ አጋር ወይም እንደጓደኛ ሳይሆን ጨቋኝ ከሆኑ ወላጆቹ እንደ ማምለጫ መንገድ ነው። ይህ ደግሞ ደስተኛና ሰኬታማ ጋብቻን ለመመስረት በቂ መሠረት አይደለም።

2. ደስተኛ ካልሆነ ቤተሰብ ለማምለጥ

ይህ እንደመጀመሪያው ያለ ጤነኛ ያልሆነ ምክንያት ነው። አንዳንዶች ደስተኛ ባልሆነ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አድገዋል፤ እናም ማድረግ የሚፈልጉት አንድ ነገር ካሉበት ሁኔታ ውስጥ ማምለጥ ነው። ምናልባትም አካላዊ፣ ጾታዊና በቃላት የሚሰነዘሩ ጥቃቶች ኖረው ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ከሁለቱ ወላጆች አንደኛው የአልኮል ወይም የዕጽ ሱሰኞች ሆነው ይሆናል። በቤት ውስጥ ያለው ህይወት ሰውጥ በሌላውና በተደጋገመ ቁጣ፣ ጩኸት፣ ርግማንና ብጥብጥ የተሞላ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ከመሳሰለ ቤት መውጣት ከሞት የማምለጥን ያህል ይቆጥሩታል፤ እናም ጋብቻ የማምለጫ በር ሆኖ ይታያቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ ወሰን ያለፈ ሞኝነትና ጥበብ የጎደሰው እርምጃ ነው። ደስተኛ ካልሆኑ ቤቶች ለማምለጥ ታቅዶ የሚመሠረት ጋብቻ ለመጋባት ምክንያት ሲሆን አይችልም። ከዚህ ይልቅ ከዚያ ቤት

መውጣት የሚፈልጉ ከሆነ ይወጡና ሥራ ይፈልጉ፤ ቤት ተከራይተው በራሰዎ መኖር ይጀምሩ። ደስተኛ ካልሆነ ቤት በመውጣት ትዳርን የሚመሰርቱ ሰዎች እጅግ ብዙውን ጊዜ የተመኙትን ደስተኛ ህይወት አያገኙትም። ይልቁንም ትተውት በወጡት ቤት አብሯቸው የኖረ ህዘንተኝነት በመጨረሻው መልኩን ቀይሮ በአዲሱ ሁኔታቸው ውስጥ ይገጥማቸዋል።

3. ስለ ራስ የሚወሰድ ዝቅተኛ አመለካከት

እንዳሰመታደል ሆኖ አንዳንድ ሰዎች የሚያገቡት ስለራሳቸው ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት ጋብቻ ዋጋ ያላቸው ሰዎች አንደሚያደርጋቸው ተስፋ በማድረግና ለሕይወታቸው ትርጉም ለመስጠት ነው። ስለ ራሳቸው ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ ሁልጊዜም ሌላ ሰው ዋጋ ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን እንዲያረጋግጥላቸውና ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን እንዲነግራቸው ይፈልጋሉ። በዚህ አይነት ሁኔታ የተመሠረተ ትዳር ገና ከጅምሩ ነው ለችግር የሚጋለጠው።

ለራስ የሚሰጥን ዝቅተኛ አመለካከት ይዞ ወደ ጋብቻ የሚገባ ባለትዳር ወደግንኙነቱ ሲመጣ ግማሽ ሰው ሆኖ ነው። ሁለቱም ባለትዳሮች ስለራስ በሚወሰድ ግንዛቤ ላይ ተመሳሳይ ችግር ካላቸው የሚጠብቃቸው ፈታኝ ጊዜ ነው። ጤነኛ የሆነ ትዳር ሁለት ሙሉ የሆኑ ሰዎችን ወደ አንድነት ያመጣል እንጂ በጋብቻ ሲኖር ከሚገባው የቁጥር ድምር ዝቅ ያለ ስሌት ለማምጣት ሁለት ግማሾችን አያጣምርም። ወደ ጋብቻ ህብረት የሚመጡ፤ ዋጋ ያላቸው ሰዎች ለመሆናቸው እርግጠኞች የሆኑ፣ በግለሰባዊ ማንነታቸውና ባህሪያቸው ሰላም የሚሰማቸው ጥንዶች ብቻ ትርጉም ያለው፣ ጤነኛና ሰኬታማ ጋብቻን ይመሠርታሉ። ጋብቻ ስራስ ምንነት የሚሰጥን ዝቅተኛ ግምት ችግር ሲያስወግድ አይችልም። እንዲያውም ጋብቻ በባህሪያችን ያለውን ጉድለት አጉልቶ የሚያሣይ፣ ስለራሣችን ያለንን አመለካከት የሚያጋልጥ ነው። በመሆኑም ችግሩን ይልቁን ያባብለዋል። ሁላችንም ብንሆን ዋጋ ያለን ሰዎች መሆናችንን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለን ግንኙነት ለአግዚአብሔር የተወዳጁ ልጆች፣ የመንግስቱ ወራሾች፣ ክርስቶስ ኢየሱስ የሞተልን፣ በአግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን ድንቅ ነፍሳት መሆናችንን ልንረዳ ያስፈልጋል። የንጉስ ልጆች መሆናችንን በእርግጠኝነት መረዳት በአስተሳሰባችን፣ በስሜታችንና በድርጊታችን ላይ ለውጥ ያመጣል። ለራስ ከሚሰጥ ዝቅተኛ አመለካከት ለማመነጭ በሽታ መድሃኒቱ ይሄ ነው።

4. እንደገና ለመታሰር የሚደረግ ጋብቻ

እንዲህ አይነቱ ጋብቻ፤ ከላይ ከገለጽነው ጋር ተመሳሳይነት አለው። በቀደመ ጋብቻቸው ወይም ግንኙነቶቻቸው የተጎዱ ሰዎች በራስ መተማመን ስሜታቸው ስለሚንኮታኮት ተስፋ ያጣሉ፣ ድብርት ውስጥ ይገባሉ። በዚህ ምክንያት የመጽናናትን መልካም ቃል ከሚናገራቸው ወይም ከሚጠነቀቅላቸው ከማንኛውም ሰው ጋር በሚመሠረት ግንኙነት ውስጥ ዘሰው ይገባሉ። እንዲህ ማድረጋቸው የተጎዳውን ልባቸውን ለመጠገን ብቻ ሳይሆን በቀደመው ግንኙነታቸው ውስጥ ችግሩ የእነርሱ እንዳልነበረ ለራሳቸው ለማረጋገጥ ነው። ግንኩ ይህንን ሰማሣየት ሌላ ብዙ መንገድ ነበር። እሁን እንደገና ለራስ ወደሚሰጥ ግምት ልንመለስ ነው። እርሶ ትክክለኛ ሰው ከሆኑ በቃ ትክክለኛ ሰው ነዎት። በእንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጋብቻ ይህን ሲቀይረው አይችልም።

በጋብቻ እንደገና በመታሰር ምክንያት የሚመሠረት ትዳር የፍቅር ጋብቻ ሳይሆን ከችግር ማምለጫ ነው። እራስዎን ይጎዳሉ፣ እራስዎን ይጠራጠራሉ እናም ሁልጊዜ በመልካም ቃላት የማያጽናናዎንና ርህራሄ የሚያሳይዎትን ይፈልጋሉ። ባለትዳሮች ሁለታችሁም ብትሆኑ ይህን እንደትክክለኛ ፍቅር ቆጥራችሁ ወደ ጋብቻ ለመግባት ፈጥናች ወስናችሁ ከሆነ ስህተት ነው። ይሁንና በእውነታው ህይወት ውስጥ ፍቅር እንዲህ አይደለም። ለእርሶ ይህ ከችግር የማምለጫ ትዳር ነው። በውስጥዎ ከተፈጠረ ግጭት ለማምለጥ ፈጣኑና ቀላሉ መንገድ። በዚህ ላይ እይውደቁ። እንደገና ለመታሰር የሚያደርጉት ሩጫ ከፊቱ ችግር አለ።

5. ያለ ጋብቻ የመቆየት ፍርሃት

ይህ ፍራቻ ወንዶችንም ይሁን ሴቶችን የሚያጠቃ ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ በብርቱ የሚጎዳው ግን ሴቶችን ነው። በተለይም ዕድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ ችግሩ የበረታ ይሆናል። በዚህ ሰለጠነ በተባለው ማህበረሰብ ውስጥ እንኳን ሴቶች ከወንዶች ይልቅ የራሳቸውን ዋጋ የሚተምኑት ከጋብቻ፣ ከቤት እና ከቤተሰብ ጋር እያይዘው ነው። ብዙ ሴቶች ገና እድሜያቸው ሠላሣውን መዝለል ሲጀምር መጨነቅ ይጀምራሉ። እንዳንድ ጊዜ ክፉ ሃሳብ ወደ አይምሯቸው ይመጣና ምን ባደርግ ይሻለኛል? ከእኔ በቀር ሁሉም እያገቡ ነው! ጓደኞቼ ሁሉ አግብተዋል። አብረን ከተመረቅናቸው የት/ቤት ጓደኞቼ ትዳር ያልመሠረትኩ እኔ ብቻ ነኝ። ግን ችግሬ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ይጭራል።

በእንደዚህ ያለ ሃሣብ የተሞላች ሴት ወደ እርሷ ቀርቦ ጥቂትም ፍላጎት ያሣያትን የመጀመሪያውን ወንድ ሰቀም ከማድረግ አትመለስም። ያ ሰው ለእርሷ ጥሩ ሰው ላይሆን ይችላል። ይሁንና ይህ በጊዜው ችግሯ አይደለም። ምናልባትም ይህ ሰው ብዙ መጥፎ ባህሪያት ያሉት ሕይወቷን ወደ ውድቀት የሚመራ ሰው ሊሆን ይችላል። በጊዜው ግን ይህ አይታያትም። ፈጽሞ ተስፋ የቆረጠች ነች። የምትመለከተው አንድ ነገር ይህ ሰው እርሷን ከጅሏል። ምንም እንኳ ይህ ሰው ከእርሷ ከሚፈልገው የራሱ ጥቅም አንጻር የተጠጋት ቢሆንም፤ እንደሚወዳትና እርሷም እንደምትወደው ራሷን ታሳምናለች። ጥያቄውን ሲያፈነዳላት "እግዚአብሔር ይመስገን" ብላ በታላቅ ስስት ትቀበለዋለች። ዋንኛው ችግር ደግሞ በዚህ ነገር ላይ እግዚአብሔር ምንም ማድረግ አለመቻሉ ነው። በራሷ ውስጥ የተፈጠረ ጭንቀትና "የተጣለች አሮጊት ገረድ" የመባል ስጋቷ ወደማይሆን ውሳኔ ገፍተዋታል።

ወንዶችም ይህነኑ ስህተት ይፈጽማሉ። በዘመናቸው ሁሉ ወንደላጤ ሆኖ በመኖር ፍርሃት ምክንያት ጥቂት ወንዶች ከእነርሱ ጋር አቻ ያልሆነችውን ሴት ያገባሉ። ለጋብቻ ያልተፈለገ ወይም ብቃት የሌላቸው ከመባል ፍርሃት የተነሣ ብዙ ወንዶችና ሴቶች፤ ቢታገሉ ኖሮ ሊያገኟቸው ከሚችሉ የትዳር ጓደኞች እጅግ ባነሰ ደረጃ ያሉ የትዳር ጓደኞችን ለማግባት ተገደዋል። ያለትዳር ከመቅረት ፍርሃት የተነሣ ጋብቻን የሚመሠርቱ ሰዎች ብዙውን ጊዜ እነዚህ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። እንድም ጋብቻቸው ይፈርሣል ወይም የፈጸሙትን ስህተት ለእስም በተለይም በጓደኞቻቸውና በቤተሰቦቻቸው ፊት እምነው ለመቀበል ስለማይፈልጉ በዚያው ጋብቻ ውስጥ የዘሩትን እያጨዱ ይቀመጣሉ። በሁለቱም መንገድ ቢሆን የተመኙትን ደስታ አያገኙም፤ ይልቁንም በምትኩ ሀዘን ያገኛ ቸዋል።

6. የጥገኝነት ፍርሃት

እንዳንድ ሰዎች በወላጆቻቸው ትከሻ ላይ ተደላድለው ስለሚያድጉ በሙሉ እድሜ ላይ በሚደርሱበት ጊዜ በራሳቸው ወጥተው ህይወትን ፊት ለፊት መጋፈጥ ይፈራሉ። ለለዚህም ጋብቻን የሚመሠርቱት ሌላ የሚደላደሉበት ትከሻ ፍለጋ ነው። ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ሲሸከሙት የሚገባውን ብዙ ሀላፊነቶች ራሳቸው ስለሚሸከሙ ልጆቻቸው በእነርሱ ላይ እጅጉን እንዲደገፉ ያደርጋሉ።፤ አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ልጆቻቸው ሲያደርጉት

የሚገባውን ሁሉ ራሳቸው ያደርጉላቸዋል፤ አንጂ ልጆቻቸው እንዴት ማሰብ ወይም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አያስተምሯቸውም። እንዲያውም አንዳንድ ወላጆች ያደጉ ልጆቻቸውን እንደ ህፃናት ይቆጥሯቸዋል፤ አስከ ህይወት ፍጻሜያቸውም ከእነርሱ ጋር ለማኖር ይሞክራሉ።

በወላጆቻቸው ጫንቃ ላይ ተደላድለው ያደጉ ልጆች፤ ብዙውን ጊዜ ከጋብቻቸው ቀድሞ የለመዱትን እንክብካቤና ደህንነት ይጠብቃሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ በራሳቸው ወጥተው ነፃነታቸውን ሲያገኙ በራሳቸው ከመራመድ ይልቅ መዳህ ይጀምራሉ ምክንያቱም እንዴት መራመድ እንደሚችሉ አልተማሩም። ሀላፊነትን የመሸከም አስፈላጊነት መጋፈጥን ተጨንቀውበት አያውቁም፤ አንዳንዶቹ እንዲያውም ጉዳዮን ማንሣት እንኳን አይፈልጉም።

ሀላፊነትን መሸከም የሚፈራ ማንም ቢሆን ለትዳር ብቁ አይደለም። ስኬታማ ጋብቻ ከባለትዳሮቹ በራስ የመተማመንንና የመረጋጋትን ብቃት ይጠይቃል።

7. ለሌላው ሰው ለመጠንቀቅ ወደ ጋብቻ መምጣት

ለምሳሌ ሁለት ወጣቶች በእጮኝነት ጊዜያቸው ውስጥ ናቸው እንበል። እርሷ ብዙ ጊዜ ስለ ጋብቻቸው ታወራለች፤ እርሱ ግን እርግጠኛ አይደለም። እንደማይወዳትና በሁለታቸው መካከል ላለው ግንኙነት መልሱ ጋብቻ እንዳልሆነ ቢገነዘብም እጮኝነቱን ቢያፈርስ ምን ሊከሰት እንደሚችል ፍርሃት አለው። ምናልባትም ደጋግማ "ብትተወኝ እሞታለሁ" ወይም ሁኔታውን ዘርዘር አድርጋ "እንተ የምትተወኝ ከሆነ ራሴን አጠፋለሁ" ስትል ስምቷታል። በቀላሉ እንዴት ወደዚህ የውድቀት ሀሣብ እንደከተታት ባያውቅም ሊጎዳት አይፈልግም፤ በመሆኑም ጋብቻውን መቀበሉን ይመርጣል። ይህን ሁኔታ፤ በቀላሉ በጋብቻዋ ላይ መወሰን ያልቻለች ልጃገረድና ጋብቻን በተጽእኖ ለመመስረት የሚሞክር ወንድ አድርገን ገልብጠን ልናየው እንችላለን።

እንዲህ አይነት ችግሮች የሚፈጠሩት አንዳንድ ሰዎች የጓደኝነት ልዮ ልዩ ደረጃዎች ባለማወቃቸው ነው። አንድ ወጣት አንዲት ልጃገረድ ወደ ቡና ቤት ወስዶ አይስክሬም ስለጋበዛት ብቻ ለጋብቻ ደርሰዋል ማለት አይደለም። በቃ ጓደኞች ናቸው። ከሁለት አንዳቸው በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት ብዙ ማሰብና መረዳት እስኪጀምር ሁሉም ነገር መልካም ነው። እናም ሌላኛው ወገን የጥፋተኝነት ስሜት እስኪሰማውና ነገሩ ግዳጅ እስኪሆንበት ድረስ

ይሄኛው ተጽእኖ ማሣደር ይጀምራል። ማንኛውም ጋብቻ በማንኛውም ዐይነት ፍርሃት ላይ የተመሠረተ ከሆነ እድለቢስ ነው። "ሌላውን ወገን አጎዳዋለሁ" በሚል ፍርሃት ተነሳስተው ዘለው ወደ ጋብቻ አይግቡ። ለሁለታችሁም ቢሆን በጋብቻ ተሣስራችሁ የእድሜ ልክ ሀዘን ከምታተርፉ ዛሬ ጨክናችሁ በአጭር ሀዘን ውስጥ ማለፍ ይሻላችኋል።

8. የትዳር ጓደኛ አማካሪ ወይም ችግር አቃላይ ለመሆን የሚመሠረት ትዳር

ነገሩ የእብደት ቢመስልም አንዳንድ ሰዎች ግን ትዳር በዚህ ምክንያት ይመሠርታሉ። የእነርሱ ጥበብና ምክር ስሚያስፈልጋቸው ሰዎች ትልቅ የሀላፊነት ስሜት ይሰማቸዋል። ይጠንቀቁ! በዚህ መቀጠል የለብዎትም። ወንድየው ይህን ያድምጡ፤ እርሶን ለማማከር የምትመጣዋን ሴት የግድ ማግባት አለብዎ ማለት አይደለም። ለሴቶቹም እላለሁ፤ በሆነ ጉዳይ ምክር ሊሰጣችሁ የመጣው ወጣት የእናንተ ባል ሊሆን ይችላል ማለት አይደለም። ጋብቻ ለችግሮቻችን ወጌሻ ሆነው ከቀረቡን ሰዎች ሁሉ ጋር የምንተሣሰርበት ግንኙነት አይደለም። ጋብቻ ሌሎች ብዙ አስፈላጊ ዘርፎች አሉት።

ለሰዎች በተለያየ ጉዳይ ከሚያማክሯቸው ሰዎች ጋር ከጊዜ ብዛት የፍቅር ስሜት ውስጥ መግባታቸው ያልተለመደ ክስተት አይደለም። ሰዎች በእነርሱ ላይ ስልጣን ካላቸው ሰዎች ጋር እንዲያም ሲል ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር በቀላሉ በፍቅር እንደሚወድቁ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በማማከር ሥራ ላይ በቋሚነት የተሰማሩ ሰዎች እንዲህ አይነት ነገሮችን ሁልጊዜም በጥንቃቄ ሊያስተውሉ ይገባል።



ደስተኛ ጋብቻ ወንድና ሴት ባስትዳሮች እኩል ተሣታፊነት፣ ዙሰቱም በስሜት በመስማው፣ ስለራሳቸው ያሳቸው ስመስካከት ጤናማ ሆኖ የየራሳቸውን የስብእና ማንነት ይዘው ወደ አንድነት የሚመጡበት ነው።

ደስተኛ ጋብቻ ወንድና ሴት ባለትዳሮች፤ በእኩል ተሳትፎ፣ ሁለቱም በስሜት የበለሉ ሆነው፣ ለራሳቸው ይላቸው አመለካከት ጤናማ ሆኖ የየራሳቸውን የስብእና ማንነት ይዘው ወደ አንድነት የሚመጡበት ነው። እርሶን ሁልጊዜ እንደ አማካሪው የሚመለከተውትን ሰው ቢያገቡ፤ መቼም ቢሆን እረፍት አያገኙም

ስሜትዎንም ይጎዳሉ። በራስ መተማመን የሌላቸውና የሚተማመኑት በሌላኛው ወገን ችሎታ የሆነ ተጋቢዎች ሁልጊዜ በጥቃቅን ነገሮች እንኳን የባሎቻቸውን ወይም የሚስቶቻቸውን ምክር ይጠይቃሉ። በራሳቸው ማሰብ እንደማይችሉ ወይም በራሳቸው መወሰን እንደማይችሉ ሚስቶች እና ባሎች ፈጥነው የሚያደክሙ ሰዎች የሉም። በዚያ ወጥመድ እንዳይያዙ ይጠንቀቁ። በማያቋርጥ ሁኔታ ሁልጊዜ ምክር ፈላጊ የሆነ ሰው ለትዳር ብቁ አይደለም።

9. ለግብረስጋ ግንኙነት ሲባል የሚመሠረት ጋብቻ

አንድ ወንድና አንድ ሴት የግብረ ስጋ ግንኙነት ከፈጸሙ በህገ እንደተጋቡ ይቆጠራል የሚል ቆየት ያለ ትምህርት አለ። ይህ ግን ትክክል አይደለም። የግብረ ስጋ ግንኙነትና ጋብቻ በእኩል አይን እንደማይታዩ ቀደም ሲል ተመልክተናል። የግብረ ስጋ ግንኙነት በራሱ ጋብቻን ሊመሠርት ወይም ሊያፈርስ አይችልም። እንደ እግዚአብሔር እቅድ የግብረስጋ ግኙኙነት በጋብቻ አጥር ክልል ውስጥ ብቻ መፈጸም ያለበት ነው። በሌሎች ለጋብቻ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተን ትዳር እንዲሠራ ለማድረግና ለማዳበር አስፈላጊ ነው። ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የግብረስጋ ግንኙነት ትክክለኛ ያልሆነና ስነልቡናዊ ጉዳት የሚያስከትል፣ ለስሜትም አደገኛና ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ሀጢያት ነው። ስለዚህም ጋብቻን ለመመስረት ምክንያት አይደለም። ምክንያት የሚሆነው ለንስሀ ብቻ ነው። ላልተጋቡ ጥንዶች በተሰይም ለአማኞች ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብ ብቻ ትክክለኛ የሆነ ስነምግባር ነው።



ላልተጋቡ ጥንዶች በተለይም ላልተጋቡ አማኞች ከግብረስጋ ግንኙነት መታቀብ ብቻ ትክክለኛ የሆነ ስነምግባር ነው።

10 በእርግዝና ምክንያት የሚመሠረት ጋብቻ

በእርግዝና ምክንያት ጋብቻን መመስረት፣ በግብረስጋ ፍላጎት ምክንያት ጋብቻን ከመመስረት የበለጠ ምክንያት አይደለም። በምክንያቶች አስገዳጅነት የሚመሠረት ጋብቻ ጊዜው አልፎበታል። ዛሬም አንዳንዶች ግብረስጋ ግንኙነት ትዳር ለመመስረት ምክንያት ባይሆንም፣ እርግዝናን በሚመለከት ግን ጉዳዩ የተለየ ነው ይላሉ። በተለይ የልጁን አባት እስመልክቶ ያለ ጥርጥር የሞራልና የህግ ጉዳዮች መነሳታቸው አይቀሬ ነው። ይሁን እንጂ እርግዝና ብቻውን ጋብቻን ለመመስረት በቂ መሰረቶች የሉትም ጉዳዩን በግልጽ ያየን እንደሆነ እርግዝና የሚያረጋግጠው የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸሙን ብቻ ነው። እርግዝና እንዲፈጠር ባደረጉት በሴቷ ወይም በወንዱ መካከል ፍቅር መኖሩን ወይም አንዱ ለሌላኛው መሰጠቱን አያመለክትም። ከጋብቻ ውጭ በተደረገ የግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት የተሠራን ጎጢያትና የተደረገን ስህተት በተሟሟተ ጋብቻ ማስተካከል መሞከር ሞኝነትና ማስተዋል የጎደለው ነው። እንዲህ አይነቱ ጋብቻም ተጋቢዎቹንና በዚህ ጋብቻ መካከል ሊያድግ ሰሚገደደው ምስኪን ህፃን ለእድሜ ዘመን ሰሚተርፍ የልብ ሀዘንና ስብራት የሚዳርግ ነው።

በህይወታዎ የሚፈጽሙት አንድ ስህተት ከህይወት ሩጫ ገፍትሮ አያወጣዎትም። ከጋብቻ ውጭ አርግዘው ልጆችን የወለዱ ብዙ ሰዎች በኋላ ደስተኛ ወደሆነ ጋብቻ ገብተዋል። እንደ ግብረስጋ ግንኙነት ሁሉ ያልተፈለገ አርግዝናም ለንስህ እንጂ ለጋብቻ ምክንያት አይሆንም ።

ሰመጋባት ጤነኛ የሆኑ ምክንያቶች

ለጋብቻ ምክንያት የሆኑ ጤናማ ያልሆኑ ምክንያቶችን ስንመለከት ቆይተናል፤ አሁን ደግሞ ጤናማ ምክንያቶችን ልንመረምር ጊዜው ነው። ቀጥሎ የተመለከቱት አስር ነጥቦች እርስ በእርስ የተያያዙ እንደሆኑና ባተኮርንበት ጭብጥ ላይ ትልቁን ድርሻ እንደያዙ ልናስብ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን አስሩም ጋብቻን ለመመስረት መልካም ምክንያቶች ቢሆንም የትኞቹም ቢሆኑ በተናጠል በቂ ምክንያቶች አይደሉም። ጤናማ፣ ስኬታማና መልካም ጋብቻ ከነዚህ ምክንያቶች አብዛኞቹን ሊያካትት ቢችልም ሁሉንም ሊያጠቃልል የግድ አስፈላጊ ነው ማለት አይደለም።

1. የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ምክንያት

ከምክንያቶቹ ሁሉ ይህኛው እጅግ ጠቃሚው ምክንያት ነው። ጋብቻን ያቀደው እግዚአብሔር በመሆኑ ከእርሱ በላይ ስለ ጋብቻ የሚያውቅ የለም። እንደ አማኞች ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ በማንኛውም ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ መረዳትና ለተረዳነውም እውነት መታዘዝ ነው። ይህ የጋብቻ ጓደኛ ምርጫችንንም የሚያካትት ነው። በአንዳንድ ምክንያቶች ማለትም ከእውቀት ማነስ ወይም በእግዚአብሔር ላይ መታመን ካለመቻል የተነሣ አንዳንድ አማኞች በጋብቻም ዙሪያ በእግዚአብሔር ላይ መታመን አቅቷቸው በሕይወታቸው ችግር

ላይ ባልተመሠረተው አጋፔ በሆነው በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ በእግባቡ መገንባት አለባቸው።

4. መልካም በሆነ መንገድ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ፍላጎት ለማርካት

የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሲሆን በትክክለኛው መንገዱ ጤናማና መልካም ነው። በራሱ ግን የጋብቻ ምክንያት ለመሆን የማይችል ደካማና ጠባብ የሆነ ምክንያት ነው። ይሁንና ፍቅርንና መልካም ጓደኝነትን መሠረት ያደረገ የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎት ጠንካራና ተፈጥሯዊም ምክንያት ነው። በተጨማሪም በወንድና በሴት ውስጥ የሚቀሰቀሰው በዘላቂነት አብሮ በመኖር ሀሣብ ላይ የተመሠረተን ፍቅር የግብረ ስጋ ግንኙነትን ፍላጎት ያቀጣጥላል። ለክርስቶስ ኢየሱስ በእርግጠኝነት ራሣቸውን የሰጡ አማኞች የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎታቸውን አግባብነት ባለው ሁኔታ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ጋብቻ እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠውን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ለማሟላት አራሱ እግዚአብሔር ያጸናው ጎዳና ነው። ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለሚኖሩ አማኞች በፃፈው ቃል ጥበብ የተሞላበትና ተግባራዊነት ያለው ምክሩን እንዲህ ሲል ያካፍላል።

"ስለ ፃፋችሁልኝ ነገር ከሴት ጋር አለ መገናኘት ለሰው መልካም ነው። ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራሷ ባል ይኑራት። *ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፤ እንዲሁም ደግሞ ሚስት ለባሏ*። ሚስት በገዛ ስጋዋ ላይ ስልጣን የላትም፤ ስልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ስጋው ላይ ስልጣን የለውም ስልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። *ለፀሎት ትተገ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በእርሳችሁ አትከላከሉ፤* እራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ . . . ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ፤ እንደእኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው። *ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ*" (1ቆሮ 7÷15፤ 8-9)።



ጋብቻ እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ያስቀመጠውን የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎት ለማሟላት እራሱ እግዚአብሔር ያፀናው ጎዳና ነው።

5. ቤተሰብን ለመመስረት

ልጆችን የማፍራት ፍላጎት መልካም ፍላጎት ነው። ይሁን እንጂ ይህም በራሱ በጋብቻ ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠውና እጅግ አስፈላጊው ምክንያት አይደለም። ፈቅደውም ይሁን በተፈጥሮ አስገዳጅነት ልጆች ሳይኖሯቸው ደስተኛ ትዳር ያላቸው ብዙ ጥንዶች አሉ። ስኬታማና ደስተኛ የሆነ ትዳር በልጆች መገኘት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ልጆች ድንቅ የሆኑ በረከቶችና ጋብቻን የሚያጣፍጡ በመሆናቸው ልጆችን ለመውለድ ፍላጎት ያላቸው ጥንዶች መልካምን ተመኝተዋል። በመዝ (127)÷ 3-5 እንዲህ ተጽፏል "እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፤ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው። በሃያል እጅ እንዳለ ፍላጻዎች የጎልማሳነት ልጆች እንዲሁ ናቸው። ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው። ጠላቶቻቸውን በአደባባይ በተናገሩ ጊዜ እርስ አያፍርም"። እንደ ጠንካራ መልዕቅ በሆነ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ላይ እንደተመሠረተ ክርስቲያናዊ ትዳር ልጆችን ለማሳደግ ሌላ የተመቸ ስፍራ የለም።

6. ጓደኝነት

የጓደኝነት ፍላጎት ለጋብቻ እጅግ የከበረው ምክንያት ነው። ማንኛውም ሰው በተፈጥሮው ቅርብ የሆነ ጓደኛ ወይም ባልንጀራን የመፈለግ ባህሪ አለው። ይህ ጓደኝነትና ባልንጀርነት ከጋብቻ ውጭ ሊገኝ የሚችል ቢሆንም፤ በባልና በሚስት መካከል ያለው እጅግ የቀረበ ጓደኝነት ግን የላቀ ነው። ለምች ማህበራዊ የሆኑና የተፈጠሩትም እንዳቸው በእንዳቸው ባልንጀርነት እንዲደሰቱና እንዳቸው በእንዳቸው ጓደኝነት ውስጥ እንዲያድጉ ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው በፈጠረ ጊዜ፤ ለእርሱ ተስማሚ የሆነ ረዳት ከፈጠራቸው ሌላ ፍጥረቶች መካከል አላገኘለትም።

ባል የሚስቱ ሚስትም የባልዋ እጅግ የቀረበ ጓደኛና ባልንጀራ ሊሆኑ ይገባቸዋል። "እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፤ እንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወሰዶ ስፍራውን በስጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፤ 'ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ ስጋም ከስጋየ ናት እርስዋም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል'። ስለዚህ ሰው አናትና አባቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል። ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ"። (ዘፍ 2÷21-24)።



በሷ የሚሰቱ ሚስትም የባሏ እጅግ የቀረበ ጓደኛና ባልንጀራ ሲሆኑ ይገባቸዋል።

7. ሁሉን ነገር ከሌላው ሰው ጋር ለመጋራት

"ሀዘንህን ለሌላው ሰው ስታካፍለው ይቀልሃል፤ ደስታህንም ከሌላው ሰው ጋር ብትጋራው እጥፍ ይሆንልሃል" በሚለው ጥንታዊ አባባል ውስጥ ብዙ እውነት አለ። በሕይወታችን የሚያጋጥሙን ሀዘንና አስቸጋሪ የፈተና ጊዜያቶችን ተቋቁሞ ለማለፍ የልብን ሸክም የሚያካፍሉት አጋር አብሮ ሲኖር የቀለሉ ይሆናሉ። ደስታና ሣቃችንን የሚካፈል የቅርብ ባልንጀራ በአጠገባችን ሲኖር ፍስሀችን በእጥፍ ይልቃል። ወንድንና ሴትን የሚያስተሳስር እውነተኛ ፍቅር፤ ሁሉን ነገር በተለይም የየዕለቱን የህይወት አስደናቂ ገጠመኝ ለመጋራት መሻትን ይፈጥራል።

ጋብቻ መጀመሪያውን የታቀደው በቀሪ የሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በአንድነት ለመኖር፤ በጋራ ፍቅር ለመተሣሰር ለመከባበርና ሁሉን ለመጋራት ለወሰኑ ወንዶችና ሴቶች ነው።

8. የጋራ ፍላጎትን ለማሟላት በህብረት ለመስራት

በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠር ፍቅር የትዳር ተጋሪ የሆኑ ባልና ሚስትን አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት እንዲያደርጉ ፍላጎትን ያነሣሣል። ይህ የመስጠትና የመቀበል ሂደት በሁሉም ወገን ከፍተኛ ማስተዋልን የሚጠይቅ ነው። ማንኛውም ለው የተወለደው ከማያቋርጥ አካላዊ፤ አይምሯዊ፤ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ጋር ነው።

የምግብ፤ የውሃ፤ የአልባሳት፤ የመጠለያ፤ የአይምሮ ሰላምና የደህንነት፤ ከፍርሃት ነፃ የመሆን፤ በስነጥበብና በውበት የመበልጸግ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ለመሆንና የቀረበ ግንኙነት ፍላጎቶች ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ፍላጎቶች ናቸው። ጋብቻ ደግሞ እነኝህን አግባብ የሆኑ ፍላጎቶች በጋራ በመስራት ለማሟላት በልክ እንደተሰፋ ልብስ ነው። በአንድነት ሆነው፤ በጌታ ላይ በጽኑ በመታመን ማንኛውንም ችግር ለመቋቋምና መሰናክሎችን ሁሉ ለማለፍ ይቻላል። "አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ፤ በሦስት የተገመደ ገመድ ፈጽሞ አይበጠስም" (መክ 4÷12)።

9. እምቅ ችሎታን ለማሳደግ

ለራስም ካለሞት አመለካከት በዘለለ መንገድ በትምህርት አስተሳብዎን መግራትና አተገባበርዎን በመለወጥ እምቅ ተፈጥራዊ ችሎታዎን ማሳደግ የስኬታማ ህይወት ቁልፍ ነው። በጋብቻ ውስጥ ሁለቱም ባለትዳሮች ያላቸውን እምቅ ችሎታ ሁሉ በመጠቀም እርስ በእርስ ይረዳዳሉ። የሚወዱትን ለው እርሱ ወይም እርሷ መድረስ አስከምትችልበት ድረስ ለማድረስ የሚቀሰቀስ የማገዝ ፍላጎት ጤናማ የሆነ የትዳር ምክንያት ነው። በጋብቻ የሚደረግ ውህደት የተጋቢዎቹ ግለሰባዊ፤ መንፈሳዊና የሥራ ክህሎታቸውን ብቃት ከፍ ባለ ደረጃ ለመከወን ሙሉ ህይላቸውን እንዲጠቀሙ፤ አመች ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። የባልንጀርነት ህብረታቸው አንዳቸው አንዳቸውን በማበረታታት፤ በማነቃቃት፤ በማጽናናት፤ አንዳቸው ለአንዳቸው በመጸለይ፤ አንዳቸው የሌላኛውን ስህተት በማረም፤ አንዳቸው ሌላኛው የሚያደርገውን እያደነቁና እያጸኑ አንዲኖሩ መንገድ ይከፍታል።



በጋብቻ የሚደረግ ውህደት የተጋቢዎቹን ግለሰባዊ፤ መንፈሳዊና የሥራ ክህሎታችውን ብቃት ከፍ ባለ ደረጃ ለመከወን ሙሉ ህይላቸውን እንዲጠቀሙ ያደርጋል።

10. መንፈሳዊ አድገትን ለመጨመር

ምንጩ ከእግዚአብሔር በመሆኑ ምክንያት ጋብቻ ቀድሞውንም የታቀደው ለክርስቲያኖች ነው። እነዚህ ወንዶችና ሴቶች ክርስቲያኖች ደግሞ በእምነት እንጂ በማየት የማይመላለሱ፤ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያላቸው የግል ፍቅር ህብረት በእየዕለቱ ህይወታቸው ውስጥ እያደገ የሚሄድ ነው። ሁለቱም ባልና ሚስት ለማደግ ያለማቋረጥ እርስ በእርስ መበረታታት ይገባቸዋል። በጋራ ማምለክ፤ በጋራ መጸለይ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መወያየት፤ ከክርስቶስ ጋር ለሚኖራቸው መንፈሳዊ እርምጃ አንዳቸው ለአንዳቸው እንደ መንፈሳዊ አረኛ ሊሆኑ ያስፈልጋቸዋል። በስልጣን ደረጃ የየነው እንደሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እንዲሁ ባል የሚስት ራስ ነው (ኤፌ 5÷23) ለክርስቶስ በመስጠቱና በመሪነቱ ባል የቤተሰቡን መንፈሳዊ እድገት የመከታተል ሃላፊነት አለበት። ይሁን እንጂ ሁለቱም ባልና ሚስት በእኩል ደረጃ ለትዳራቸው ጤናማነት ህላፊነትን ሊሸከሙ ይገባል። በአርግጥ መልካም ትዳር እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ጥንዶች ከማንኛ

ውም ነገር ይልቅ አንዳቸው የአንዳቸውን መንፈሳዊ ህይወት በማጥራት ወይም በማሳደግ ተግባር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ።

* * *

በመሠረቱ፤ አስሩም ለጋብቻ ጤናማ ያልሆኑ ምክንያቶች አንድ የጋራ ባህሪ ይታይባቸዋል፤ ይሄውም ራስን መካከለኛ ያደረጉ ናቸው። ራስ ወዳድነት ትዳርን ለመገንባት በጭራሽ ጤናማ ብቃት ሊሆን አይችልም። በተቃራኒው አስሩ ጤናማ የጋብቻ ምክንያቶች ከመሠረታቸው ራስ ወዳድነት የማይታይባቸው ናቸው። በእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ፍቅር ላይ ተመስርተው፤ በሌላው ወገን ፍላጎትና ደህንነት ላይ በማተኮር ራስን አሳልፎ ለመስጠት ምክንያቶች ናቸው። በስኬትና በውድቀት፣ በደስተኝነትና በሀዘንተኝነት፣ በጥሩና ጥሩ ባልሆነ ጋብቻ መካከል ጉልህ የሆነው ልዩነት ይህ ነው።

መርሆዎች

1. ጤነኛ የሆነ ትዳር ሁለት ሙሉ የሆኑ ሰዎችን ወደ አንድነት ያመጣል እንጂ፤ በጋብቻ ሊኖር ከሚገባው የቁጥር ድምር ዝቅ ያለ ስሌት ለማምጣት ሁለት ግማሾችን አያጣምርም።
2. ሁላችንም ብንሆን ፈልገን ልንደርስበት የሚገባ ነገር አለ፤ ይሄውም ከክርስቶስ ጋር ካለን ህብረት የተነሳ፤ እግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን፣ የመንግስቱ ወራሾች በመሆናችን፣ በክርስቶስ ሞት ምክንያት በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠራችን የከበረ ማንነት አንዳለን ነው።
3. የጋብቻ ጤናማ ምክንያቶች
   - የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ ምክንያት።
   - የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌላው ሰው ለመግለጽ።
   - ግላዊ የሆነ ፍቅርን ለሌላው ሰው ለመግለጽ።
   - መልካም በሆነ መንገድ የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎትን ለማርካት
   - ቤተሰብን ለመመስረት።
   - ጓደኝነት።
   - ሁሉን ነገር ከሌላው ሰው ጋር ለመጋራት።
   - የጋራ ፍላጎትን ለማሟላት በህብረት ለመስራት።
   - እምቅ ችሎታን ለማላደግ።
   - መንፈሳዊ እድገትን ለመጨመር።

ምስፈሩ ስፈጥ

ሁሉም ሰው በገነት ውስጥ ጋብቻውን ሲፈጽም ይገባዋል

የመጀመሪያው ጋብቻ የተከናወነው በኤደን ገነት ነበር። በዚያ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ወንድና ሴት መረቃቸው ቀደሳቸውም። በዘፍጥረት መጽሐፍ አንድና ሁለት፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ ባቀደው መሠረት የተዘጋጀውን የጋብቻ ምስል እንመለከታለን። በነዚህ ክፍሎች አዳምና ሄዋን በሰላም፣ በህብረት፣ በእኩልነት፣ በማያቋርጥ ሁኔታ ከፈጣሪያቸው ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እናጤናለን። ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ግን የተለየ ስዕል ያቀርብልናል። ሀጢያት በመካከላቸው በነበረው ህብረት መካከል ገብቶ ሲጋረጥና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውንም ህብረት ሲያፈርሰው እንመለከታለን። ምዕራፍ አንድና ሁለት ገነት ውስጥ የነበረውን ጋብቻ ያሣዮናል። ምዕራፍ ሦስት ግን ከገነት ውጭ የሆነውን ጋብቻ ያመለክተናል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሆነው ጋብቻ ውስጥ የምናልፍበት ብቸኛ ስፍራ ከገነት ውስጥ ነው። ከገነት ውጭ የሚመሠረት ማንኛውም ጋብቻ ከእግዚአብሔር የሆነ ጋብቻ አይደለም።

ዘፍጥረት አንድ እና ሁለት ከውድቀት በፊት የነበረውን፤ እንደ እግዚአብሔር አቅድ የተመሠረተውን ጋብቻ ያሳየናል። ዘፍጥረት 3 ደግሞ ከውድቀት በኋላ አለም ያመሰቃቀለችውን የጋብቻ አይነት ያመለክተናል። አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ይህ ማለት፤ በምዕራፍ አንድና ሁለት ውስጥ በገነት ውስጥ የነበሩ ሁኔታዎች፣ ባርኮቶች፣ የተሰፋ ቃሎች ሁሉ፣ ከገነት ውጭ በምዕራፍ 3 ለተመለከተው ጋብቻ ዋስትና የሚሰጡ አይደሉም። በገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን በጋራ ፍቅር፣ በመከባበር፣ በእኩልነት ፍቅር ደስታን ያጣጥሙ ነበር። ከገነት ውጭ ግን ስህተታቸውን ለመደበቅ ሞከሩ፣ እርስ በእርስ ተወነጃጀሉ፣ አንዳቸው ስለ ሌላቸው በእግዚአብሔር ፊት ወሸትን ተናገሩ። በገነት ውስጥ አንዱን መንፈስ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ይካፈሉ ነበር። ከገነት ውጭ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ስለተለያቸው አንዳቸው ለአንዳቸው እንደማይተዋወቁ ሰዎች ሆነው ነበር። በገነት ውስጥ በመንፈስም በስጋም ተጣምረው እናያቸዋለን። ከገነት ውጭ ግን ያላቸው ሥጋ ብቻ ነበር።

የእግዚአብሔር የጋብቻ መስፈርት የተመሠረተው በገነት ውስጥ በነበረው ደረጃው ነው። ማንም ሰው ቢሆን በገነት ውስጥ እንደ ነበረው ጋብቻ ባልሆነ መንገድ በተመሠረተ ጋብቻ ውስጥ ተጋቢዎቹን እግዚአብሔር አጣምሯቸዋል ብሎ በእውነት ለመናገር አይችልም። አስቀድሞውንም የታቀደው ለአማኞች በመሆኑ፤ ትክክለኛ ጋብቻ የመንፈሶች ውህደት ሳይሆን የስጋ ውህደት ነው። በኤደን ገነት አዳምና ሄዋን በመንፈስ መጋባት አላስፈለጋቸውም፤ ምክንያቱም ቀድሞውኑ አንድ መንፈስ ተጋርተዋል። መንፈሶቻቸው ቀድሞውኑ ተዋህደዋል። ይሁንና በስጋ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ነበሩ። በገነት ውስጥ የነበረው ጋብቻቸው ምክንያት በአካል መዋሃዳቸው ነው። አስቀድሞውኑ አንድ መንፈስ እንደነበሩ አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድ ነው።

በእያንዳንዱ ቀን፤ በመላው ዓለም በሽህ የሚቆጠሩ ጥንዶች እግዚአብሔር አጣምሮናል ብለው ጋብቻን ይመሠርታሉ። በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ይህ ግን እውነት አይደለም፤ ምክንያቱም ጋብቻቸው የተመሠረተው በገነት መስፈርት አይደለም። ሁለቱም ወይም ከሁለት አንዳቸው ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዱ ባለመሆናቸው አንዱን መንፈስ አብረው አልተጋሩም። በዚህም ምክንያት የስሜት ዋስትና ሊያሳጣቸውና ጋብቻቸውን ሊያፈርስ ከየአቅጣጫው የሚጐትትን ሃይል ለመቋቋም አስተማማኝ ጥበቃ የላቸውም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃሎች የሚሠሩት ለሚያምኑና ለሚታዘዙት፣ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑትና መንፈሱን ለተጋሩት አማኞች ነው። ከእግዚአብሔር መንፈስ ውጭ የሆነ ማንም የተሰፋ ቃሎቹን ለመቀበል ዋስትና የለውም። ጋብቻን በተመለከተም ስሜቱም ይሁን ውድቀቱ እጅጉን የሚመሠረተው ጋብቻው በገነት ውስጥ የመሆኑ ወይም ያለመሆኑ እውነት ነው።



ምንም እንኳ ዳግም የተወለዱ ቢሆኑም ብዙ ክርስቲያኖች በትዳራቸው ውስጥ ችግር ያጋጥማቸዋል፤ ምክንያቱም ሳያውቁት እግዚአብሔር ነገሮችን ከሚመዝንበትና ከሚመሰክትበት በተሰየ መንገድ ስለሰማዊው ሚዛንና እደታ ቁሪቤታ ስላላቸው ነው።

እውቀት በማንኛውም ነገር ስሜታማ ለመሆን ወሳኙ ቀልፍ ነገር ነው፤ ጋብቻ ደግሞ ከእነዚህ ነገሮች ውጭ ሊሆን አይችልም።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች ቢሆኑ እንኳን በገነት ውስጥ እና ከገነት ውጭ ስላለው ጋብቻ ልዩነት ጠንቅቀው ካላወቁ በስተቀር በትዳራቸው አክል ሊያጋጥማቸውና ሊወድቁ ይችላሉ። ምንም እንኳን ደግም የተወለዱ ቢሆኑም ብዙ አማኞች በትዳራቸው ውስጥ ችግር ያጋጥማቸዋል፤ ምክንያቱም ሳያውቁት እግዚአብሔር ነገሮችን ከሚመዝንበትና ከሚመለከትበት በተለየ መንገድ ለአለማዊው ሚዛንና እይታ ቀረቤታ ስላላቸው ነው። ጋብቻቸው በገነት ውስጥ እንዲሆን አውቀትንና ጥበብን እንዲያገኙ ወደ መንፈስ ቅዱስ አንዴት መመልከት እንዳለባቸው መማር ያስፈልጋቸዋል።

ክፍል ሰባት፡ የበላይነት

የመጀመሪያዎቹ ሁለት የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፎች፤ ጋብቻ ማለት ምን ማለት እንደሆነና፣ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ጠቃሚ የሆነ መጠነኛ መረጃ ይሰጠናል። ስድስተኛውና የመጨረሻው በሆነው የፍጥረት ቀን ማለትም ሰማይና ምድር ከተፈጠሩና መሬትም በዕጽዋት፣ በእንስሳትና፣ በባህር ፍጥረታት ከተሞላች በኋላ እግዚአብሔር ትልቁን የመፍጠር ክህሎቱን ሰውን በመፍጠር ተጠበበበት። ሰው፤ ውንድና ሴት የእግዚአብሔር ፍጥረት ክብር ሁሉ ቁንጮ ወይም ዘውድ ሆነው ተፈጠሩ። ከፈጠራቸው ፍጥረቶች ሁሉ የተለዩ ሰሆኑ ለእነዚህ ፍጥረቶች እግዚአብሔር የተለየ ስፍራና እቅድ ነበረው። "እግዚአብሔር አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባህር አሶችንና የሰማይ ወፎችን፤ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ባረካቸው እንዲህም አላቸው። ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉዋት፣ ግዙዋትም፤ የባህርን አሣዎችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙዋቸው" (ዘፍ 1፥26-28)።

እዚህ ላይ ልብ ይበሉ፤ የተፈጠሩትን የመግዛት፣ የመብዛት፣ የመባዛትና ምድርን የመመላት ስልጣን የተሰጠው ለሁለቱም ወንድና ሴት በአንድነት ነበር። ወንዱም ሴቷም ሁለቱም የተፈጠሩት አንደ እግዚአብሔር ምሳሌ ሲሆን የታቀዱትም አንዱ ሌላውን እንዲያሳለና ፍጹምም ሆነው ነው። ሁለቱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌዎች ሆነው በፍጥረታዊው አለም ላይ

እንዲሰለጥኑ አስፈላጊ የሆነው ብቃትና ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። እንደገናም ልብ ይበሉ! የተሰጣቸው ስልጣን ዝቅ ያሉትን የእግዚአብሔር ፍጥረቶች እንደ አሣ፣ አእዋፍና የምድር አንስሳትን እንዲገዙ እንጂ አንዳቸው ሌላቸውን እንዲገዙ አልነበረም። የእግዚአብሔር የቀደመ እቅድ ወንድና ሴት እኩል ስልጣንና እኩል የበላይነት እንዲኖራቸው ነበር።

እግዚአብሔር ያዘዘው፤ ወንድም ሴትም በእኩልነት የበላይነትና የመግዛት ስልጣናቸውን እንዲጠቀሙ ነው። በኤድን ገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን አንድን መንፈስ ተቀብለዋል፤ በአንድ አይነት ስልጣን ተጋርተዋል፣ እንድ አይነት የመግዛትን ሀይል ተለማምደዋል። በምድር ላይ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም ህይወት ባለው ፍጥረት ላይ የበለይነት ነበራቸው። ይህ ደግሞ እባቡንም ይጨምራል። ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ግልጽ እንደሚያደርግልን፤ የወደቀው መላአክ፣ ፈታኙ፣ ክሳሹ እየተባለ የሚጠራ ሰይጣንም በእባብ መልክ በኤድን ገነት ውስጥ ነበር። አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሁሉ በበላይነት ይወክሉ ስለነበርና ሰይጣን በእነርሱ ግዛት ውስጥ ስለነበር በእነርሱ ስልጣን ስር ወድቆ ነበር። አዳምና ሄዋን ሁለቱም ሰይጣንን ለመግዛት ስልጣንና ሃይል ነበራቸው። ይህን የማድረግ ሃላፊነታቸውን መወጣት ባልቻሉ ጊዜ ግን ወደ ቀውስ ውስጥ ገቡ።

በገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን በሰብአናም ይሁን በስልጣን አኩል ነበሩ።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ሁለተኛው ምዕራፍ እንዲሁ በገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን በሰብአናም ይሁን በስልጣን አኩል እንደነበሩ ይገልጽልናል። ዘፍጥረት 2፥18-24 እግዚአብሔር ሄዋንን ለአርሱ የተስማማች ረዳት ትሆን ዘንድ እንዴት አንድ የጎድን አጥንት ከአዳም ወስዶ እንደሠራት ይተርክልናል። እርሷም በፍጹምና በመለኮነት ከአዳም ጋር በአካል አቻ ነበረች። በይብራይስጥ "ጎድን" የሚለው ቃል "ጎን" ተብሎም ይተረጎማል። ሄዋንም የተሠራችው ከአዳም ጎን ነበር። አዳም ያለው ነገር ሁሉ ነበራት። አንድ አይነት መንፈስ፣ አንድ አይነት አይምሮ፣ አንድ አይነት ስሜትና አንድ አይነት መለኮታዊ መልክ። የተወለደችው ከአጥንቱ አጥንት ከስጋው ሥጋ ሆና ስለነበር በማንኛውም አስፈላጊና መሠረታዊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ አኩል ነበረች። ተቀባይነት ባለው ታልሙድ በሚባል ጥንታዊ የዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ አንድ ምሣሌ እንዲህ

ይላል፤ “እግዚአብሔር ሴትን ከሰው ጫንቅላት አልፈጠራትም፤ እንደዚያ ቢሆን መሪዋ ይሆን ነበር፤ ከእግሩም አልፈጠራትም፤ እንደዚያም ቢሆን ባሪያ ልትሆን በተገባት ነበር፤ ነገር ግን ከጎኑ ፈጠራት፤ ይህም ለልቡ የቀረበች ትሆን ዘንድ ነው”።



በገነት ውስጥ የነበረች አንዲት ወንድና ሴት አንድ መንፈስ አንድም አካል ስለነበሩ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ፍጥረታዊና ምድራዊ ግዛት ሁሉ ለመግዛት በአንድነት አኩል ሃይልና አኩል ስልጣን ይጠቀሙ ነበር።

የሰንድ ራስነት የተመሠረተው በእውቀት ባዩ ነው

የሰብእና፣ የሃይልና የስልጣን አኩልነት ማሰት በኤድን ገነት ውስጥ በአዳምና በሄዋን መካከል የመሪነት ቀዳሚነት ሥፍራ አልነበረውም ማለት አይደለም። የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት እግዚአብሔር ወንዱን የዚያ ትንሽ ቤተሰብ መሪ አድርጎ እንዳስቀመጠው ግልጽ ያደርግልናል። በእግዚአብሔር እቅድ በጋብቻ ውስጥ የራስነት ሃላፊነት መወለድ የወንዱ ነው። እግዚአብሔር አዳምን በኤድን ገነት እንዳስቀመጠው፤ ሰው እንዴት መኖርና መሥራት እንደሚገባው የሚያሳዩ ደንቦች መሠረታዊ ህግጋትን ሰጥቶት ነበር።

“እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤድን ገነት አኖረው። እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፤ ከገነት ዘፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዘፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።(ዘፍ 2÷15-17)።

ገነትን የማበጀት ሃላፊነቱ አዳምን ፍሬያማና ውጤታማ ሥራ ለጥቶት ነበር። በዚያው ጊዜ ውስጥ በአካባቢው እርሱ የሚያስተዳድረውን ነፃ ግዛትን እግዚአብሔር ለጠው። አዳም ተከልክሎ የነበረው ክፋውንና መልካሙን ከሚያስታውቀው ዛፍ ብቻ ነበር። እዚህ ጋ አንድ ነገር ማስተዋል ጠቃሚ ነው። አዳም ይህንን መመሪያ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ሄዋን ወደ ፍጥረት

ታሪክ ከመምጣቷ በፊት ነው። አስቀድሞ በመፈጠሩ ምክንያት ሄዋን ያልተሣተፈችበትን በግል መረጃ የማግኘት እድል ነበረው። የተቀበለውን ይህንን ትእዛዝ ለሚስቱ ማስተላለፍ የአዳም ሃላፊነት ነበር። እንደዚያች ትንሽ ቤተሰብ ሃላፊነቱ ቤተሰቡን ከጉዳት መጠበቅ ይጠበቅበታል። ያ ከሰላ የመስጠት ተግባሩ የተመሠረተው ሃላፊነት ላይ ነበር።

አዳም የቤተሰቡ ራስ የተደረገው ለምንድን ነበር? በአካሉ ጠንካራ ስለነበር ይሆን? በጭራሽ። ዛሬ ዛሬ ግልጽ እየሆነ እንደ መጣው በመሠረቱ ወንዶችና ሴቶች በአካላዊ ጥንካሬ አኩል ናቸው፤ ልዩነቱ የጥንካሬያቸው መንገድ ነው። በአጠቃላይ ወንዶች ከወገባቸው በላይ የበሰጠ ጠንካሮች ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ ከወገብ በታች ባለ የአካል ጥንካሬ ብልጫ አላቸው። የሴቶች አካል በወሊድ ጊዜ የሚፈጠረውን የሃይል ግፊት ለመቋቋም ታቅዶ በተለይ የተሠራ ነው። እንደዚያ ያለውን ህመም ሊቋቋሙ የሚችሉ ጥቂት ወንዶች ብቻ ናቸው። አዳም የቤተሰቡ ራስ የሆነው በነበረው አካላዊ ጥንካሬው አልነበረም።

በለውነቱ ውበትስ ይሆን? አይመስለኝም። በጥቅሉ ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ውቦች ናቸው። አንዱ አንድ ጊዜ እንደተናገረው ወንዱ በመጀመሪያ በመፈጠሩ ምክንያት እጅግም ረቂቅነት የሌለው ጅምር ሥራ ነው። ሴቲቱ ግን በወንዱ ያለው ጉድለት የታረመባት የፍፃሜ ውጤት ናት።

አዳም የአይምሮ ብልጫ ስለነበረው ይሆን? አይደለም። ወንድም ሆነ ሴት ያላቸው የአይምሮ ብቃት ተመሣሣይ ነው። አዳም ይበልጥ መንፈሳዊ በመሆኑስ ይሆን? ይህም አይደለም። አዳምና ሔዋን የተጋሩት አንዱን መንፈስ ነበር።

ከሌሎች ምክንያቶች ሁሉ ለአዳም ራስነት አጥጋቢ ምክንያት ሆኖ የሚታየው አዳም የነበረው የአፈጣጠር የጊዜ ቀዳሚነት ነው። አዳም ራስ የሆነው ቀድሞ በመፈጠሩና ሄዋን የሌላትን መረጃ አስቀድሞ በማወቁ ነው። የአዳም ራስነት የተመሠረተው በእውቀት ላይ ነበር። ይሄ እውነታ ራስነት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ ቁምነገራዊ እንድምታ አለው። ባል የሚስቱ ራስ ነው (ኤፌ 5÷23 ይመልከቱ) ይህ ማለት ግን እንደ አሰቃዋ ሆኖ ገዥዋ ይሆናል ማለት አይደለም። ራስነት ገዥነት ማለት አይደለም፤ ይልቁን መሪነት ነው። እንደ ራስነቱ ወንዱ መንፈሳዊ አመራር ይሠጣል፤ ቤተሰቡን ይመራል። የቤተሰቡን እቅድ ሲያወጣ ይጠበቅበታል፤

የእርሱ መንፈሳዊ ህይወት በቤተሰቡ መንፈሳዊ ህይወት ላይ የሚያሣርፈው አሻራ አለ።



ሩስነት ገዥነት ሣይሆን መፈነት ነዉ

ዛሬ እጅግ ብዙ ትዳሮች የክርስቲያኖችንም ጨምሮ በችግር ውስጥ ወድቀዋል። ምክንያቱም ባሎች እንደ ቤተሰብ ራስነታቸው የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ባለመረዳታቸው ነው። ብዙውን ጊዜ ሴቶችንና ህፃናትን በስልጣን ወደመግዛትና ወደመጫን ስለሚያመሩ ራስነታቸው ከደረጃው ዝቅ ይላል። አንዳንድ ጊዜ መላውን ራስነታቸውን በሴቶቹ ላይ ስለሚጥሉ የራስነት አመራሩ በስም እንኳን ባይሆን በተግባር በሚስቶቻቸው ላይ ይወድቃል።

የራስነትን ጉዳይ በሚመለከት ሁለቱም ባልና ሚስት ጥርት ያለ ግንዛቤ ካላቸው ይህ መረዳት በጋብቻ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ህብረትና ስኬት ያቀለጥፈዋል። ባልየው ቤተሰቡ የት መሄድ እንደሚገባው ቢወሰን፤ ሚስቲቱ ደግሞ እዚያ እንዴት እንደሚደርሱ ትወስናለች። ወንድየው አጠቃላይ መመሪያ ሲሰጥ፤ ሴቲቱ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ታተኩራለች። ባልየው ሚስቱ ምን እንደምትሠራ ትኩረት ቢሰጥ፤ ሚስቱ ባሏ የት መሄድ እንደሚገባው ታመቻቻለች። ሁለቱም አስፈላጊ ሰዎች በመሆናቸው የሚሠሩት አብረው ነው። መመሪያ መስጠት የመጀመሪያው፤ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ደግም ቀጣዩ እርምጃ ነው።

አዳም የቤተሰቡ ራስ በመሆኑ ምክንያት፤ በሄዋን ህይወት ደህንነት ላይ ተጽእኖ ሊያመጣ የሚችል ጠቃሚ የሆነ መረጃ ከእግዚአብሔር አግኝቷል። ክፉውንና በጎውን ለመለየት ስለምታስችለው ለዚች ዛፍ እግዚአብሔር የሰጠውን ትእዛዝ ሊያብራራላት ሃላፊነት ነበረበት። ይህ የሚያሳየው የወንዱ ራስነት የተመሠረተው በእውቀት ላይ መሆኑንና በቅድሚያም ቤተሰቡን የእግዚአብሔር አሠራርና በጥቅሉ መንፈሳዊ የሆነውን ነገር የማስተማር ሀላፊነት አለበት።

ከገነት መባረር

ውብ በሆነው በኤደን ገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን በእግዚአብሔር የተፈጠሩትን ሁሉ ይገዙ ነበር፤ በጋብቻ ውስጥ ባለው በረከትና ህብረት ደስተኞች ነበሩ፤ ከፈጣሪያቸውም ጋር የማያቋርጥ ህብረት ነበራቸው። ይህ እንከን የለሽ ሁኔታ ግን

በጠላታቸው ረቂቅ የተንኰል ብልሃት ፈጥኖ ተሰባበረ። ውጭውን በአባብ የተመሰለው የእግዚአብሔር ዋነኛ ጠላት በገነት ያለውን ንጽህና፤ የዋህነትና የተለመደውን የህይወት አደት ለማፈራረስ አይኖቹን ጣለ። ሴቲቱ ዋነኛው ኢላማ ነበረች፤ የተጠቀመው መሣሪያ ደግሞ ጥርጥርን ነው።

"እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዟልን? አላት። ሴቲቱም ለእባቡ አለችው በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤ ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር አለ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፤ አትንኩትም። እባብም ለሴቲቱ አላት፤ ሞትን አትሞቱም ከእርሷ በበላችሁ ቀን አይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለአይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች። ከፍሬውም ወሰደችና በላች። ለባሏም ደግሞ ሰጠችው፤ እርሱም ከእርሷ ጋር በላ፤ የሁለቱም አይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱ ዕራቁታቸውን እንደሆኑ አውቁ፤ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለአራሳቸው ግልድም አደረጉ" (ዘፍ 3፥1-7)።

እባቡ ባነጋገራት ጊዜ ሄዋን ምንም አይነት የመደነቅ ሁኔታ ያላሳየች በመሆኑ፤ በእባቡና በእርሷ መካከል የነበረው የሀሣብ መለዋወጥ ምናልባትም የመጀመሪያቸው አልነበረም ብሎ ለመገመት ያስደፍራል። መልካምንና ክፉውን ስለምታሳውቀው ዛፍ የነበራት እውቀት በቅንነት ላይ የተመሠረተ ስለነበር፤ ሄዋን የእባቡን ሀሣብ ላለማመን ወይም በልቡ ያለውን ተንኮል ለመጠርጠር አልቻለችም። ጥያቄው ላዮን ማር እንደተቀባ መርዝ ስውር ነበር።

የእግዚአብሔርን እውነተኛነት እንድትጠራጠር በአይምሮዋ ውስጥ የተዘራው የጥርጥር ዘር አዘራሩ በከፍተኛ ጥበብ ነበር። "በእውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን? " ጠላት የሚሠራበት መንገድ ይሄው ነው። የእግዚአብሔር ዋንኛው ጠላት የሆነው በይሁዳ መጽሐፍ ውስጥ "ዲያብሎስ" ወይም "ሰይጣን" ተብሎ የተጠራው የሚፈልገው የሰዎች አይምሮ የእግዚአብሔርን ባህሪ ዝቅ አድርጎ እንዲመለከት ሲሆን፤ ይህን

የሚፈጽመውም መላምታዊ የሆነ ሀሣብንና ጥርጥርን ወደ አይምሮ በማሸለክና እውነትን በማጣመም ነው::



የጠላታችን ዋነኛው ብልሃት ማንነታችንን እንድንጠራጠር ማድረግ ነው::

ሄዋን ለአባቡ ከሰጠችው ምላሽ፤ መልካሙንና ክፉውን ስለምትለየው ዛፍ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ ለእርሷ በማላወቅ አዳም ሃላፊነቱን እንደተወጣ እናያለን:: ሄዋን ከዛፏ መብላት ወይም መንካት ሞት እንደሚያስትል ስትናገር፤ ሰይጣን ሽምጥጥ አድርጎ ነገሩን እንዲህ አቃረነው፤ "ሞትን አትሞቱም፤ ከእርሷ በበላችሁ ቀን አይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉውን የምታውቁ እንድትሆኑ ነው እንጂ":: የጠላታችን ዋነኛው ብልሃት ማንነታችንን እንድንጠራጠር ማድረግ ነው:: አዳምና ሄዋን የተፈጠሩት በማን መልክ? በማንስ ምሳሌ ነበር? በእግዚአብሔር:: እንደ እግዚአብሔር ለመሆን አዳምና ሄዋን መልካምንና ክፉውን የምትለየውን ዛፍ መብላት አያስፈልጋቸውም ነበር:: እስቀድሞውንም እርሱን ይመስሉ ነበር!

እግዚአብሔር ምን እንዳሰና የእራሷንም ማንነት እስክትጠራጠር ድረስ የተዘራው የጥርጥር ዘር በሄዋን አይምሮ ውስጥ እያደገ ነበር:: በውስጧ ከተፈጠረው ግራ መጋባትና የዛፉ ፍሬ መልካም ሆኖ ስለታያት ለመብላት ውሣኔ አደረገች:: ይሄ ሁሉ ነገር ሲከናወን አዳም ግን ወዴት ነበር? በቁጥር ስድስት ላይ እንደምንመለከተው ቢያንስ ቢያንስ ፍሬውን በበላች ጊዜ እርሱ ከእርሷ ጋር ነበር:: ምክንያቱም ከፍሬው ጥቂት እንደሰጠችውና እርሱ ደግሞ እንደበላ እንመለከታለን:: የክፍሉ ምንባብ ሄዋን ከእባብ ጋር በተነጋገረችበት ጊዜ አዳም የት እንደነበር አይነግረንም:: የቃላት ልውውጡ የተካሄደው ያለ ምንም ማቋረጥ መሆኑ ግን የግድ ሄዋን ከፍሬው ወስዳ የበላችው ወዲያውኑ ነው ወደሚል እንድምታ አይወስደንም:: ምናልባትም ጥርጥሩ በውስጧ እስኪያድግና ፍሬውን ለመብላት ያላት ፍላጎት እስኪጠነክር ጥቂት ጊዜ ወስዶ ይሆናል::

እባቡና ሄዋን በተነጋገሩ ጊዜ አዳም በስፍራው እንዳልነበር እናያለን:: በስፍራው ባለመገኘቱ ምክንያት ሚስቱን የመጠበቅና ከክፉ የማዳን ሃላፊነቱን አልተወጣም:: ምንም እንኳን ሁለቱም ሰይጣንን ለማግዛት ስልጣን ያላቸው ቢሆንም፤ ሰይጣንን በመስማት ይሄን ስልጣን አሳልፈው ሰጥተውታል፤ በዚህም ምክንያት ሊቆጣጠራቸው ችሏል:: ሄዋን ሰይጣን አስቷት ነበር:: አዳም

ሃጢያት ያደረገው ግን አይኖቹ እንደተከፈቱ ነበር:: ለችግሮቻቸው ሁሉ የተቀበሉት እውቀት ሃጢያትን እንደሠሩና የእግዚአብሔር መንፈስ ከእነርሱ እንደተለየ አሣወቃቸው:: በድንገትም እርስ በእርሳቸው እንደማይተዋወቁ፤ እግዚአብሔርን እንደማያወቁ ሆኑ:: አስደሳቹ የጫጉላ ጊዜ አበቃ:: ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ምክንያት ጋብቻቸው ከገነት ወጣ::

አዳም ዉዴት ነህ?

አዳምና ሄዋን በገነት ውስጥ እግዚአብሔርን ባልታዘዙ ጊዜ፤ ሀጢያታቸውን በሚመለከት እግዚአብሔር ፊት ለፊት ተቋቋማቸው:: በዚህ ምልልስ ውስጥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለጋብቻ አስቦት ስለነበረው ነገር ጠቃሚ የሆነ እውነት እንረዳለን::

"እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔር አምላክን ድምፅ በገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ:: እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ? አለው:: እርሱም አለ፤ በገነት ድምጽህን ሰማሁ ራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ፤ ተሸሸግኩም:: እግዚአብሔርም አለ፣ ራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ:: ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ:: እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን ይህ ያደረግሽው ምንድን ነው? አላት:: ሴቲቱም አለች፤ እባብ አሣተኝና በላሁ"::

አንድ ነገር ልብ ይበሉ፤ እባቡን ያዳመጠችው፣ የሳተችውና የተከለከለውን ፍሬ የወሰደችውና የበላችው ሄዋን ብትሆንም እግዚአብሔር ፊት ለፊት ስለሀጢያታቸው በተቋቋማቸው ጊዜ የፈለገው አዳምን ነበር:: "እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ?" አለው:: ይህ ጥያቄ የስፍራ ጥያቄ ሣይሆን ከማዕረግ የመውረድ ጥያቄ ነበር:: እግዚአብሔር አዳም ያለበትን ስፍራና ምን እንደሠራም አስቀድሞ ያውቃል:: የጥያቄው አላማ አዳም የሠራውን ሀጢያት እምኖ እንዲቀበልና በዚህ ድርጊቱም ሀላፊነትን እንዲወስድ ነበር:: ጌታም አዳምን እንዲህ አሰው:: "አሁን ባለህበት ሁኔታ ውስጥ እንዴት ልትገባ ቻልክ? ወድቀሃል መንፈሴም ከአንተ ተሰይቷል:: ከዚህ በኋላ በእኔና በአንተ መካከል ምንም ህብረት አይኖርም:: እንዴት ወደዚህ ዝቅታ ወረድህ?"

ሄዋን የተከለከለውን ፍሬ በመብላት ላለመታዘዝ የመጀመሪያዋ ከሆነች፤ እግዚአብሔር አዳምን አስቀድሞ የፈጠገበት ምክንያት ምንድን ነው? ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ምንም እንኳን በመጀመሪያ ሃጢያት ያደረገችው ሄዋን ብትሆንም ከእርሷ ተቀብሎ ፍሬውን በመብላቱ እንደ እርሷ ሀጢያተኛ ነው። ላለመብላት ሊቃወም ይችል ነበር-አላደረገውም። ከዚህ በጣም ጠቃሚ የሆነው ጉዳይ ግን፤ እግዚአብሔር ወደ አዳም የመጣበት ምክንያት አዳም የቤተሰቡ ራስ በመሆኑ ሃላፊነት ስለነበረበት ነው። አዳም፣ እግዚብሔር ስለ ዛፏ ምን እንደተናገረ ለሚስቱ የማስረዳት ሃፊነት የተጣለበት ብቻ ሣይሆን (በግልጽ እንደተመለከትነው ይሄን ሃላፊነቱን ተወጥቷል) እርሷን መጠበቅና ከክፉ መጋረድ ጭምር ነበር። ለእርሷ እንደ ጋሻ ሊሆንላት ይጠበቅበት ነበር። ከጠላቷ ትልቅ ፈተና በገጠማት ጊዜ አዳም ወዴት ነበር? መገኘት በሚጠበቅበት ሥፍራ ስላልተገኘ ወይም ማድረግ የሚጠበቅበትን ስላሰደረገ፤ ለውድቀታቸው ቀጥተኛ የሆነውን ሃላፊነት አዳም ይሸከማል።



ፍርሃትና መለያየት እግዚአብሔር ካቀደልንና ካሰበልን ነገሮች መካከል ይደደሱም።

ጌታ ለጠየቀው ጥያቄ አዳም ከሰጠው መልስ ግልጽ የሆነው ነገር፤ በመካከላቸው በነበረው ግንኙነት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ መከሰቱን እንረዳለን። "በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ራቁቴንም ስለሆንክ ፈራሁ፤ ተሸሸግኩም"። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት ሲያጣ በርካታ በግልጽ የሚታዩ ነገሮች ይከሰታሉ። በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር መለየታቸውን ሲረዱ ከእግዚአብሔር ይርቃሉ። አዳም ራሱን ደበቀ። በሁለተኛ ደረጃ በፍርሃት ይሞላሉ። አዳም ፈርቶ ነበር። እግዚአብሔርን እስካልታዘዘበት ጊዜ ድረስ አዳም ፍርሃትን አያውቅም ነበር። አሁን ግን ፍርሀት ለእያንዳንዱ እርምጃው መሰናክል ሆነበት።



ፍቅርና ፍርሀት ስብረው ይደሄዱም። ፍቅር ከሞላበት ስፍራ ፍርሃት ሸሽቶ ይዴዳል፤ ፍርሃት ራሱን ቀና ሲያደርግ ፍቅር ይቀዘቅዛል።

ፍርሃትና መለያየት እግዚአብሔር ካቀደልንና ካሰበልን ነገሮች መካከል አይደሉም። እግዚአብሔር የፈጠረን እርሱን እንድንወደውና ከእርሱም ጋር ዘላቂነት ያለው ህብረት እንዲኖረን

ነው። ፍርሃት በዚህ ህብረት ውስጥ ባእድ የሆነ አላባ ነው። ፍቅር በነፃነት እንዳይተገበር እንቅፋትም ነው። የጢሞቴዎስ መንፈሳዊ አባትና የመጀመሪያው ከፍሰ ዘመን ታላቅ ሚስዮናዊና አስተማሪ የነበረው ጳውሎስ በ2ኛው የጢሞቴዎስ መልዕክቱ እንዲህ ጽፏል፤ "እግዚአብሔር የሃይልና የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና" (2ኛጢሞ 1፥7)። ለአይን አፋርነት የተሰጠው ሌላው ስም ፍርሃት ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊና ከኢየሱስ ክርስቶስ ሀዋርያት አንዱ የሆነው ዮሐንስ ሲጽፍ . . . እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል . . . ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን እውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም። ፍርሃት ቅጣት አሰውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም። (1ኛ ዮሐ 4፥16፤18)።

ፍቅርና ፍርሃት አብረው አይሄዱም። ፍቅር ከሞላበት ስፍራ ፍርሃት ሸሽቶ ይሄዳል፤ ፍርሃት ራሱን ቀና ሲያደርግ ፍቅር ይቀዘቅዛል። በሀጢያቸው ምክንያት አዳምና ሄዋን ፍቅርን፣ ሰላምን፣ ከጌታ ጋር የነበራቸውን ህብረት ከማጣታቸው የተነሣ የነበረበቸውን ደስታ አጡ፤ በምትካቸው የወንጀለኝነት ስሜትና ፍርሃት ተተኩ። ይህ ሰውጥ ደግሞ በሕይወታቸው ማንኛውም ዘርፍ ላይ ጋብቻቸውን ጨምሮ ተጽእኖ አስከተሰ። ፍቅር የሌለበት ጋብቻ ሰፍርሃትና ሰመሰያየት ባሪያ የሆነ ጋብቻ ነው። እንግዲህ ከገነት ውጭ ያሰው ጋብቻ ያህንን በመሰሰ መገለጫዎች ይታወቃል።



ፍቅር የሌለበት ጋብቻ ስፍርሃትና ስመሰያየት ባሪያ የሆነ ጋብቻ ነው።

የመመነጀጀል ጨዋታ

በአዳምና በሄዋን መካከል የነበረው ግንኙነት ውስጥ የታየው መሠረታዊ ሰውጥ ሌላው ምልክት እርስ በእርስ የመወነጃጀል ጨዋታ ነበር። መወነጃጀል የሚፋፋው ፍቅር ስፍራ ሲሰቅ ነው። አዳም ሄዋንን ወነጀሰ፤ ሄዋን በእባቡ ላይ አላከከች፤ ማናቸውም ቢሆኑ ስሰሀጢያት ድርጊታቸው ሃላፊነትን ሰመውሰድ ፈቃደኞች አልነበሩም። ሰዎች ብዙጊዜ ከሃላፊነት ሰመሸሽ በፈሰጉ ጊዜ እንግዳ የሆነ አስገራሚ ነገር ይናገራሰ ወይም ይሠራሰ። አዳም ያሰውን ለብ በሰ "ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠሽኝ ሴት እርሷ ከዛፉ

ሰጠችኝና በላሁ” በዚህ ንግግሩ ውስጥ ምንም ማድረግ እንደማይችል አድርጎ ራሱን ሲያቀርብ ይታያል። በእርግጡ አዳም ለእግዚአብሔር እየተናገረ ያለው፤ ጥፋቱ የዚች ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት ነው። በሃይል አስገድዳ፣ ጉሮሮየን አንቃ፣ አፌን በግድ አላቃ ፍሬውን ጨምራ መንጋጋየን ላይና ታች እያወዛወዘች በል አኝካት! አለችኝ እያለ ነው።



ዘዘነጀደበ የሚፋፋው ፍቅር ስፍራ ሲሰቅ ነው።

በግልጽ ለማስቀመጥ፣ አዳም በቤተሰቡ ውስጥ ስለተከሰተው ነገር ሃላፊነትን መውሰድ አልፈለገም ነበር። ሄዋንም እንደዚሁ። እግዚአብሔር “ይህ ያደረግሽው ነገር ምንድን ነው?” ብሎ ሲጠይቃት ሃላፊነቱን በሌላው ትከሻ ላይ ለመጣል “እባቡ አሳተኝና በላሁ” አለች። ላይ ላዩን ሲታይ የተናገረችው ትክክል ነው፤ እባቡ አስታት ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ከሃላፊነት ነፃ የሚያወጣት አልነበረም። እግዚአብሔር የተናገረውን ታውቅ ነበር። ላለመታዘዝ ግን መረጠች። ሃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኛ አለመሆን በዚህ በለለጠነውም ማህበረሰብ መካከል በሰፊው የሚስተዋል ችግር ነው። ይህም ሀጢያተኛው ፍጥረተ ዓለም በፈጣሪያችን ላይ የማመጽ አንዱ መገለጫ ነው። “ፓኘ” የተሰኘው የስነ አይምሮ ጥናት ሁላችንም የዚህ ችግር ለለባዎች መሆናችንን ይነግረናል። ምናልባት ከዚህ ችግር ውስጥ ብንሆን ምክንያቱ ከአካባቢያችን ሁኔታ፣ ጥቃቱ በልጅነታችን የደረሰብን፣ አለዚያም በማህበራዊ ወይም በኢኮኖሚያዊ ዝቅጠት ውስጥ ስለሆንን ወይም በሌላ በርካታ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። ለአደረግነው ድርጊት ሃላፊነት አንወስድም፤ ምንም ነገር ይፈጠር ሁልጊዜም የሌላው ሰው ስህተት ነው። ያ ሰው ባላችን፣ ሚስታችን፣ ልጆቻችን ወይም አለቃችን የሆነ ማንም ሰው ሊሆን ይችላል፤ ከራሳችን በቀር።

በትክክል ይህን በመሰለው ባህሪ ነው እንግዲህ ከገነት ውጭ የሆነው ትዳር የሚፈረጀው። ማንም ሰው ሃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኛ ባልሆነበት ሁኔታ እያንዳንዱ ሰው በችግር ውስጥ ይገባል። ሰዎች ሃላፊነትን ለማስወገድ ሲፈልጉ አመለካከታቸው ሚዛናዊነት የጎደለው ይሆናል። ሃላፊነት የጎደለውን ባህሪያቸውን ትክክል እንደሆነ ለማሣመንና ለመከላከል የሚያቀርቡት ምክንያት ትርጉም የለሽ በመሆኑ ከህጉ ማምለጥ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ።

ዓለም ጋብቻን ያቀደችበት መንገድ እግዚአብሔር ጋብቻን ካቀደበት መንገድ በተቃራኒው ነው። ከገነት ውጭ ያለው ጋብቻ

የመወነጃጀል፣ ሃላፊነት የጎደለው ተግባር የሞላበት፣ ሸክምን በሌላው ላይ የሚጭንበትና ወንዶች በትክክል የእነርሱ የሆነውን የቤተሰቡ ራስነት ክብር ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑበት ጋብቻ ነው። ነገሮች እየከበዱ ሲመጡ አለማዊው ጋብቻ እየዘቀጠ መውረድ ይጀምራል።

ሌላኛው ከገነት ውጭ የሆነው ጋብቻ መለያ ጠበይ ባሎች በሚስቶቻቸው ላይ የሚያሳዮት የባለስልጣንነት አገዛዝ ነው። ይህ የሄዋን ሀጢያት ያስከተለው ችግር ነው። እግዚአብሔር ሄዋንን እንዲህ አላት። “በፀነስሽ ጊዜ ጭንቀትሽን እጅግ አበዛዋለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደባልሽ ይሆናል፤ እርሱም ገዥሽ ይሆናል”። (ዘፍ 3፥16-19)



ለሚስቱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ሲል ባል ማንኛውንም ስደነት ሃላፊነት ደሸከማል እንጂ በቤቱ ውስጥ የስበቃን ቦታ ተክቶ ስደመሳለስም።

እንደ እግዚአብሔር እቅድ በሆነው ጋብቻ ውስጥ ባል ሚስቱን አይገዛትም፤ ይልቁን የራስነት ሃላፊነቱን ይወጣል። እርሱ አመራርን ይሰጣል፣ አቅጣጫን ያሳያል አብረው ይጓዛሉ። ባል ለሚስቱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ሲል ማንኛውንም አይነት ሃላፊነት ይሸከማል እንጂ በቤቱ ውስጥ የአለቅነትን ቦታ ተክቶ አይመላለስም። እንደ ቤተሰብ ራስነቱ እንደ ጨቋኝና አምባገነን ገዥ ሳይሆን በፍቅር፣ በፀጋ፣ በጥበብና በአውቀት በክርስቶስ ኢየሱስ ጌትነት ሥር ቤተሰቡን ይመራል።

መርሆዎች

1. እንደ እግዚአብሔር የቀደመ እቅድ ወንድና ሌት እኩል ስልጣንንና እኩል አገዛዝን ሊለማመዱ ይገባል።
2. እግዚአብሔር እንዳቀደው የጋብቻ አይነት የቤተሰቡ ራስ መሆን የወንድ ሃላፊነት ነው።
3. ራስነት አመራር ስጭነት እንጂ ገዥነት አይደለም።
4. የወንድ ራስነት የተመሠረተው በእውቀት ላይ ሲሆን፤ ዋነኛ ተግባሩም ቤተሰቡን በእግዚአብሔር መንገድ መምራትና ባጠቃላይ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በማስተማር ላይ ያተኮረ ነው።
5. ከገነት ውጭ ያሰው ጋብቻ የመወነጃጀል፣ ሃላፊነት የጎደለው ተግባር የሞላበት፣ ሽክምን በሌላው ላይ አስተላልፈው የሚጭነብትና ወንዶች በትክክል የእነርሱ የሆነውን የቤተሰቡ ራስነት ክብር ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑበት ጋብቻ ነው።
6. ባል እንደ ቤተሰብ ራስነቱ እንደ ጨቋኝና አምባገነን ገዥ ሳይሆን በፍቅር፣ በፀጋ፣ በጥበብና በእውቀት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ጌትነት ሥር ቤተሰቡን ይመራል።

ምዕራፍ አምስት

ደስተኛ ጋብቻ በድንገት የሚገኝ አይደለም

ደስተኛ ጋብቻ በድንገት የሚገኝ አይደለም። እንደሌሎቹ የሕይወት ዘርፎች ሁሉ በትዳር የሚገኝ ስኬትም ፈጥኖ የሚመጣ አይደለም። ልንጨብጠው በምንሠራለት በማንኛውም ጉዳይ ስኬታማ የመሆን ሚስጥሩ እቅድ ሲሆን ይህ ውጤታማ የሆነ እቅድ ደግሞ መሠረቱ እውቀት ነው። ሰስኬት እቅድን የምናወጣው ትክክለኛና የጠራ መረጃ ሲኖረን ብቻ ነው።

ብዙዎቻችን በመረጥነው የሕይወት ጎዳና ስኬት እንደሚያመጣልን አምነን አመታትን በት/ቤቶች ውስጥ ትምህርት እየተማርን ለመቆየት ፈቃደኞች ነን። ትምህርታችንን የምንከታተልበት ምክንያት ትምህርት የተሰያዩ ተግባራትን ለመከወን ብቃት ያለውን ክህሎት ስለሚያስጨብጠን ነው። ይህ ደግሞ ተፈላጊነታችንን ይጨምረዋል። ተፈላጊነታችንም የስኬታማነታችንን ህልም እውን ያደርገዋል። ስኬታችን እንዲለውጠን በዝምታ አንጠባበቅም፤ ይልቁንም ለስኬት በጥንቃቄ እናቅዳለን።

ቀደም ባለው ጊዜ ሰዎች በ18 ወይም በ20 አመት እድሜያቸው ወደ አንድ ሥራ ይገቡና እድሜ ዘመናቸውን ሁሉ ከአንድ አለቃ በታች ሲሠሩ ይኖራሉ። አሁን ግን ከአራት ወይም ከአምስት ጊዜ በበለጠ ሥራቸውን ወይም አለቆቻቸውን የሚቀይሩ ሰዎችን ማግኘት በዚህ ዘመን እንግዳ ነገር አይደለም። ሥራን በተደጋጋሚ የመለወጡ እውነታ በዚህ በሰለጠነም ማህበረሰብ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱ፤ ትምህርትንና እውቀትን ከቀድሞ ጊዜ ይልቅ ለስኬት እጅግ ጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

በመደበኛ ሥራችን ስኬታማዎች ለመሆን በጥንቃቄ የምናቅድ ከሆነ፤ በትዳራችን ስኬታማ ለመሆን እቅድ ለማውጣት ለምን ጠንቃቆች አንሆንም? እውነቱን ለመናገር በየጊዜው ለምንቀያይረው ሥራ የአመታት ዝግጅት ስናደርግ፤ እስከ ህይወት ዘመን ፍፃሜያችን እንዲቀጥል ተስፋ ለምናዳርገው ግንኙነት ለመዘጋጀት የምንለጠው ጊዜ በጣም ጥቂት ነው።

ጥንቃቄ የማንወስድ ከሆነ፤ በፍፃሜያችን ላይ ብዙ ጊዜ ሊወስዱብን ለሚችሉ የተሣሣቱ ነገሮች እንድንዘጋጅ እንገደዳለን።

ወደ ት/ቤት መሄድና ሄዶም ትምህርትን መከታተል ወይም በሥራችን ስኬታማዎች ለመሆን ይሁን ብለን የምናቀደው እቅድ በራሱ ችግር የለውም። ችግሩ በሥራቸው ስኬታማዎች ሆነው በትዳራቸው ግን ውድቀት ያጋጠማቸው በርካታ ሰዎች መኖራቸው ነው። በዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሰፊውን ጊዜያቸውን የሚያውሉት፤ ከአለቆቻቸው ጋር እንዴት መስራት እንደሚገባቸው ሲማሩ የሚያሳልፉት ጊዜ ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ለመማር ከሰጡት ጊዜ ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ያህል በመሆኑ ነው። ብዙውን የዝግጅት ጊዜ የምንሰጠው ለኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሰማሚላት በሚያስፈልገን ነገር እንጂ ህይወትን በትክክለኛው መንገድ ለመኖር በሚያስፈልገን ነገር ላይ አይደለም።

በህይወታችን ልንጨብጣቸው ተግተን እንደምንሠራላቸው ነገሮች ሁሉ፤ በትዳር ውስጥ ያለው ስኬት የሚመሠረተው በመረጃና በእቅድ ነው። ጋብቻ መዋእለንዋይ ነው፤ ስኬትም ባለን የእውቀት መጠንና ባዋልነው የጊዜ መጠን የሚወሰን ነው። ስኬት ስጦታ አይደለም፤ ይልቁንም ጥንቃቄ የተሞላበትና የታሰበበት ዝግጅት ውጤት ነው። ስኬት ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከመዋእለንዋይ ጋር የተያያዘ ነው። ጊዜዎንና ጠንካራ መንፈስዎን ባቀዱት ነገር ላይ የሚያውሉ ከሆነ የስኬትዎ እውን መሆን ህልም አይደለም።

ማንም ቢሆን አዲስ የሆነ ቤት ለመገንባት ሲነሣ ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶች ሣያሟላ አይነሣም። በዚህ አይነቱ ሥራ ላይ መሬቱን መግዛት፤ ለሥራው አስፈላጊ የሆነውን የህንፃ ንድፍ ሠራተኛ ማዘጋጀት፤ የግንባታውን ሥራ ፈጽሞ ለማጠናቀቅ በቂ የሆነ ካፒታል መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። አንድን ነገር ከመጀመራችን በፊት ስለ ፍፃሜው መጀመሪያ እናቅዳለን፤ ዋጋውን እንተምናለን፤ በሥራው ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ከግምት ውስጥ አስገብተን እናቅዳለን። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ስላለው ቅድመ ዝግጅት አስፈላጊነት እንዲህ ብሏል "ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ኪሣራውን የማይቆጥር ማን ነው? ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት ለመደምደም ቢያቅተው ያዩት ሁሉ፡- ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ጀምራሉ" (ሉቃ 14÷28-30) ምንም እንኳን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ስፍራ በተለይ የሚናገረው እርሱን የሚከተል ደቀመዝሙር ዋጋ ሊተመን እንደሚገባው ቢሆንም፤ የተናገረው ቃል ለስኬት ተግተን

ለምንሠራበት ማንኛውም ጉዳይ ጥበብ የተሞላው ምክር ይሰጠናል። ለስኬት የግድ ማቀድ አለብን። ልክ አንድን የመኖሪያ ህንጻ ልንገነባ ስንነሣ የሚኖረንን ትኩረት ያህል፤ ለቤታችን ትልቅ አትኩሮት ልንሰጥ ያስፈልገናል። እጅግ ውብ የሆኑ የመኖሪያ ህንፃዎች ሁሉ ቤቶች አይደሉም።

ስኬትና ፈሰጼ

ጋብቻ የተሰየ አይደለም። አሁንም የሚተገበረው ተመሣሣይ መርህ ነው። ደስተኛ ጋብቻ ለእድል የሚተው ነገር አይደለም። ልክ እንደ ህንፃ ግንባታ ሁሉ ስኬታማ የሆነ ትዳርም ጥንቃቄ የተሞላው እቅድ፤ ታስቦበት የተሠራ ንድፍ፣ ትክክለኛ የሆነ የግንባታ ቁሳቁስ፤ ጥሩ የሆነ አማካሪና በሥራ ልምድ የበሰለ የህንፃ ተቋራጭ ውጤት ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስን ስለሚያውቁና መንፈስ ቅዱስም ስላለቸው የትዳራቸው ስኬት አስተማማኝ የሚሆን ስለሚመስላቸው ስህተትን ይሠራሉ። ምሳሌ 17 እንዲህ ይላል። "እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ"። እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ የመጀመሪያው ስፍራ ነው። ምንም ያህል ቀልጣፎች ወይም ምሁራን ብንሆን፤ ጌታን እስካላወቅን ድረስ እውነተኛ እውቀት የለንም። ልንጀምርበት የሚገባ ስፍራ ይሄ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ተማሪዎች ልንሆን ያስፈልገናል፤ ህይወትን በሚገዙት መንፈሣዊ መርሆዎች ልንቀኝ የግድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ለህይወታችን ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ፤ እኛን ወደ እውነት እውቀት ማምጣት ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሣሰባችኋል" (ዮሐ 14÷26)።

እኛ ለመማር እስካልተቀመጥን ድረስ መንፈስ ቅዱስ ሊያስተምረንና ያላወቅነውን አንድ ነገር ሊያሳስበን አይችልም። የእግዚአብሔር ቃል ተማሪዎች ልንሆን ያስፈልገናል፤ ህይወትን በሚገዙት መንፈሣዊ መርሆዎች ልንቃኝ የግድ ነው። እንዲህ ሲሆን ብቻ ነው መንፈስ ቅዱስ ሊያስተምረንና ሊያሣስበን የሚችለው።

ወደ ትዳር ስንመጣም፤ የስኬትን መርሆዎች ካላወቅን በስተቀር ለሰኬታማ ትዳር ዋስትና የለንም። በመጀመሪያ ያልተማርናቸውን ወይም ያላወቅናቸውን መርሆዎች፤ መንፈስ ቅዱስ "ያሳስባናል" ብለን አንጠብቅም። ከትዳር ጓደኞቻችን ጋር እንዴት ህብረት ሊኖረን እንደሚችል አስቀድመን ካልተማርን፤ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዴት እንደሚኖረንና፤ ግጭቶችን እንዴት እንደምንፈታ ካላወቅን፤ መንፈስ ቅዱስ ሊያሣስበን የሚችለው ነገር የለም። ለዚህ ነው እውቀት ጠቃሚ የሚሆነው። በተመሣሣይ ሁኔታ አውቀት በራሱ ደግሞ ብቻውን በቂ አይደለም። እውቀት ብቻውን ወደተሳሳተ ድምዳሜ ሊያመራን ይችላል። እውቀታችንን በአግባቡ እንድንገነዘብና እንድንተገብር የሚያስችለን የመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ያስፈልገናል።

እውቀት በጋብቻ ውስጥ ያለውን ግንዛቤ አስባነትን ያሸንፋል

በዚህ ዘመን ያገቡትንም ሆነ ገና ያልተጋቡት ጥንዶች ታላቅ ተግዳሮት የሆነው ስለጋብቻ ያላቸው ግንዛቤ አልባነት ነው። ብዙ ጋብቻዎች የሚፈርሱበት አለያም ትልቅ ህልማቸው በአጭር የሚቀጭበት ምክንያት ጥንዶቹ ጋብቻ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አለማወቃቸው ነው። ያላቸው ግንዛቤ አንድም ጠባብ የሆነ አለዚያም ዓላማዊ በሆነ ፍልስፍና የተቃኘ ወይም ሁለቱም እንጂ በእግዚአብሔር የጋብቻ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ አይደለም።

ስኬታማ የመሆን እድል እጅጉን እየጨመረ የሚሄደው በግንዛቤ እጦት የተዛቡ አመለካከቶች በእውነትና በእውቀት ብርሃን እየጠሩ የሄዱ እንደሆነ ነው።

የጋብቻ ግንኙነት ትምህርት ቤት ነው፤ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ሁለቱም ተጓዳኞች በጊዜ ውስጥ እያደጉና እየዳበሩ የሚሄዱበት የመማር ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ትዳር የግድ ፍጹም መሆንን አይጠይቅም፤ ይሁን እንጂ የፍጹምነት ጉዳይ በትዳር ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። ጋብቻ ሀጢያተኞችን ጨምሮ ሰዎችን ያቀፈ ተቋም ነው። እነዚህም ሀጢያተኞች እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ታላቅ የፍቅርና የጽድቅ መርሃ ግብር እንዲተገብሩ በጋብቻ ውስጥ እየመራቸው እንደሆነ እየተመለከቱ ክብሩንም እንዲፈልጉ ይሆናሉ።

ጋብቻ የመማርያ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ ሁለቱም ተጓዳኞች በጊዜ ውስጥ እያደጉና እየዳበሩ ይሄዳሉ።

ጋብቻ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ፍቅር በሙላት ለመግለጽ ብቃት ያለው ነው። የተጋቢዎቹ ፈቃደኝነት ደግሞ ዋነኛው ጉዳይ ነው። የጋብቻ ግንኙነት የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲገልጽ የሚችለው ሁለቱም ባለትዳሮች ጌታ ኢየሱስ በእነርሱ ውስጥና በእነርሱ እንዲሠራ ፈቃደኞች ሲሆኑ ብቻ ነው። "እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ" (ኤፌ 5፣21)። "ሚስቱም ባልዋን ትፍራ" (33)። "ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ" (22) "ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት. . . ራሱን አሳልፎ ሰጠ" (25)። ሁለት ፍጹም የተለያዩ ሰዎች ወደ አንድነት መጥተው እንደ አንድ ሰው ሲኖሩና ሲሰሩ፤ ያለምንም ራስ ወዳድነት ራሳቸውን ሲሰጣጡ፣ ሲፋቀሩ፣ ይቅር ሲባባሉ፣ እርስ በእርሳቸው ሲግባቡና ሲቀባበሉ፤ ከውጭ የማመለክቱ ቢያንስ ቢያንስ የእግዚአብሔር ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በጥቂቱ ሊመለከቱ ይችላሉ።

ጋብቻ እግዚአብሔር ወንድና ሴትን እርሱ እንደሚፈልጋቸው አይነት ሰዎች እስኪሆኑ ደረስ የሚቀርጽበትና የሚያጠራበት ሂደት ነው።

ጋብቻ እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን እርሱ እንደሚፈልጋቸው አይነት ሰዎች እስኪሆኑ ድረስ የሚቀርጽበትና የሚያጠራበት ሂደት ነው።

ክርስቲያዊ ጋብቻ ባልና ሚስት በፍጹምነት አንዳቸው ለአንዳቸው የሚሰጣጡበትና በግል ደግሞ ራሳቸውን ለክርስቶስ ኢየሱስ የሚሰጡበት ነው። ይህን መሰጣጠት በፍጥረታዊውም ይሁን በመንፈሣዊው ዓለም ውስጥ ወደ ኋላ ሲጎትተው የሚችል ነገር የለም። ጋብቻ ለመተማመን ቢጋራ የሚገባ ምህላ፣ ለጋራ ጥቅም አንዱ ለሌላው ራሱን ዝቅ የሚያደርግበት ነው።

በጽኑ መሠረት ላይ መገንባት

ዘላቂነት ወይም ረጅም ዕድሜ ያለው ነገር ሁሉ የሚገነባው ጽኑና ጠንካራ በሆነ መሠረት ላይ ነው። ጋብቻም ከዚህ የሚለይ አይደለም። እርግጠኛ የሆነና ብቸኛ መሠረት ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እጅግ ዝነኛ ከሆኑት ትምህርቶቹ ውስጥ በአንደኛው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማማኝ ባልሆነ መሠረት ላይ ሕይወትን መገንባት ስለሚያስከትለው አደጋ፤ አስደናቂ በሆነ ተምሣሌታዊ ገለፃ እንዲህ አብራርቶታል። "ስለዚህ ይህንን ቃሌን ሰምቶ

የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራን ልባምን ሰው ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ንፋስም ነፈሰ ያንንም ቤት ገፋው። በአለት ላይ ስለተመሠረተ አልወደቀም። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንንም ቤት መታው ወደቀም አወዳደቁም ታላቅ ሆነ" (ማቴ 7፥24-27)።


በጽኑ መሠረት ላይ ያልተመሠረተ ሀንፃ በብርቱ ንፋስ እንደሚወድቅ፤ ጋብቻም እንዲሁ በጽኑ መንፈሣዊ መርሆዎች ላይ ያልተመሠረተ ከሆነ የህይወት ተግዳሮቶች በገጠሙት ጊዜ መቋቋም መቻሉ የሚያጠራጥር ነው። እስኪ ደስተኛና ስኬታማ ጋብቻ የሚመሠረትባቸውን አስር የመርህ አሰቶች እናጢን።

1. ፍቅር

ፍቅር በብዙ መንገዶች ሊገለጽ ቢችልም፤ እዚህ ስፍራ የምንመለከተው የእግዚአብሔርን ባህሪ ገላጭ በሆነው አጋፔ ከሆነው መለኮታዊ ፍቅር ጋር በተያያዘ መልኩ ነው። አጋፔ ራስን የሚክድ፤ ራስን ለሌላው አሣልፎ የሚሰጥ፤ ከኢዲስ ኪዳን መጽሐፍት ፀሐፊዎች አንዱ የሆነው ጳውሎስ የዓለት መሰዋእትነት የተሞላበት ፍቅር ነው።

"ፍቅር ይታገሣል ቸርነት ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም ፍቅር አይመካም አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፤ የራሱንም አይፈልግም አይበሳጭም፤ በደልን አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል አንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሣል ሁሉን ያምናል፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይፀናል" (1ቆሮ 13፥4-8)።

በጋብቻ ውስጥ ያለ ፍቅር ከስሜት የዘለለ ነው-ምርጫ ነው። ፍቅር የጋብቻ አቻዎችን በሚመለከት በየዕለቱ እንደገና የሚያድሱት ውሣኔ ነው። በማለዳ ከእንቅልፍዎ ሲነሱ፤ ማታ በመኝታዎ ሲያርፉ ወይም የእለት ተግባርዎን በሚያከናውኑበት ጊዜ ሁሉ ያለማቋረጥ ያገቢትን ሴት ወይም ያገቡትን ወንድ ለማፍቀር መርጠዋል።



በጋብቻ ውስጥ ያለ ፍቅር ከስሜት የዘለለ ነው-ምርጫ ነው።

ፍቅር ምርጫ መሆኑን መገንዘብ መከራ በመጣ ጊዜ ከችግር ለማምለጥ ይረዳል። ሚስትዎን ወይም ባልዎን ለመውደድ መወሰንዎን ማወቅ፤ ባሰቆጡዎ ጊዜ፣ በቢሮዎቸው ውስጥ አብሯቸው የሚሠራ መልከ ቀና ወይም ቆንጆ በተመለከቱ ጊዜ እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ ለማለፍ ይረዳል። ሌላ ሰው ማግባት ይችላሉ፤ ቁምነገሩ ግን ይህ አይደለም። ቁም ነገሩ እርሶ ውሳኔ ማድረግዎ ነው። የትዳር ጓደኛዎን ባገቡበት ወቅት በህይወት ዘመናቸው ሊወዷቸውና ሊንከባከቧቸው መርጠዋል። ያ ፍቅር በየእለቱ ሊታደስ ይገባዋል።

2. እውነት

እውነት በትዳር ውስጥ መሠረታዊው ጉዳይ ሲሆን፣ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ ጋብቻ ደግሞ ሩጫው ወደ ችግር ነው። ትልቁና አስተማማኙ የእውነት ምንጭ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። እግዚአብሔር ራሱ እውነትና የጋብቻ ተቋም የመጀመሪያው አቃጅና መሥራችም ነው። እውነትን የሚያውቁ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚገኙ በማይለወጡ የመርህ መመዘኛዎች መለካት ያስፈልጋቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ስየትኛውም የህይወት ዘርፍ እውነተኛና አስተማማኝ መመሪያ ነው።



እውነትን የሚያውቁ ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚገኙ በማይለወጡ የመርህ መመዘኛዎች መለካት ያስፈልጋቸዋል።

በባልና ሚስት መካከል ያለ እውነተኝነት ለስኬታማ ጋብቻ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ባልና ሚስት እርስ በእርስ እውነተኞች ካልሆኑ የሁለቱም ፍላጎት ሊሟላ ከቶውንም አይችልም። ታማኝነትና ወረተኝነት የሌለበት ፍቅር እውነተኛነት የሚከሰትበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

3. መተማመን

መተማመን ከእውነት ጋር የተያየዘ ነው። ባለትዳሮች ትዳራቸው ደስተኛና ስኬታማ እንዲሆን የሚፈልጉ ከሆነ እርስ በእርሳቸው ሙሉ በሙሉ ሊተማመኑ ያስፈልጋቸዋል። እንደ አለመተማመን ያለ ጋብቻን ሊጎዳ የሚችል ነገር የለም። መራራነት፣ ሞገደኝነትና ጥርጥር ባለበት ሁኔታ ውስጥ ጋብቻ ሊያድግና ሊበለጽግ ይችላል ተብሎ አይገመትም። ስለዚህም ነው

ተጋቢዎች እርስ በእርሳቸው እንዲጠራጠሩ ወይም እንዳይተማመኑ የሚያደርግ ማናቸውም ነገር እንዳይናገሩ ወይም እንዳይሠሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው። መተማመን ባልና ሚስት በግልጽነት ላይ በተመሠረተ ምንም አይነት በመካከላቸው ልዩነትን የሚፈጥር ድብቅነትና ሚስጥራዊ ጉዳይ በሌለበት ግንኙነት እንዲደለቱ የሚያደርግ ነው። መተማመን ራስን የመስጠት እንድ አላባ ነው።



ስንደ ስስመተማመን ያስ ጋብቻን ሲጎደ የሚችል ነገር የስም።

4. መለጠት

በዚህ ዘመን ለብዙ ሰዎች መሠጠት የሚለው ቃል እስፈሪ ነው። የሚፈሩት በማንኛውም አይነት ዘላቂ በሆነ ግንኙነት ውስጥ መቆለፍን ወይም መታሰርን ነው። ብዙ ጋብቻዎች ረዥም ርቀት ከማይሄዱበት ምክንያት እንዱ ይህ ነው። ተጋቢዎቹ ሙሽሮች ወደ ጋብቻው መሰዊያ ቀርበው ምህላቸውን ይለዋወጣሉ፤ ይሁን እንጂ ከስሚታዊነት የመነጨና እፋዊ የሆነ የመሰጠት ኪዳን ነው። ስለ ጋብቻ ያላቸው እመለካከት ሁኔታዎች እስቸጋሪ እስከሚሆኑበት ጊዜ ድረስ እብሮ ለመሆን ስለሆነ ችግሩ በፀና ጊዜ ይለያያሉ። ትዳራቸው "የሚሠራ" ከሆነ ይቀጥላሉ፤ "የማይሠራ" ከሆነ ግን መቼስ ምን ይደረጋል . . . ጥቂት ለዎች ጋብቻቸው እንደሚወድቅ እያለቡ እቅድ ያወጣሉ እንጂ ማናቸውም በተለይ ለስኬት አያቅዱም። ለስኬት የማያቅዱ ሁሉ እግረመንገዳቸውን የውድቀታቸውን እስተማማኝነት ያጸኑታል። መሰጠት፣ ደም ህይወት እንደሆነ ሁሉ ለትዳር ህይወት ነው። የችግራችን እንዱ ዘርፍ ደግሞ መለጠት ምን እንደሆነ እናውቅም። ጋብቻ በደም እንደተሣለረ ኪዳን ያለ ነው። እንደ ቀደመው የደም ኪዳን እስከ ህይወት ዘመን ይዘልቃል። የደም ቃል ኪዳን በዘፈቀደ የሚገቡት ኪዳን እንዳልሆነ ሁሉ በቀላሉ የሚሰበርም አይደለም። ይህን የደም ቃል ኪዳን መስበር ተከታታይ ችግሮችን ያስከትላል። ጋብቻ እጅግ ቁም ነገራም የሆነ መሰጠትን ይጨምራል። በመጀመሪያ ደረጃ መሰጠቱ ለጋብቻ ተቋም ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በህይወት ዘመናችን ሁሉ ልንወደውና ልንንከባከበው ለመረጥነው ለው ሁሰንተናዊ መሰጠት ነው።



መስጠት፤ ደም ህጼጠት እንደሆነ ሁሉ ሰትዳር ህጼጠቱ ነው።

5. መከባበር

ጋብቻ ከሚያካትታቸው ጤነኛ የሆኑ ግንኙነቶች አንዱ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መከባበር ነው። እንድን ለው ማክበር ማለት ለዚያ ዘው ከፍተኛ ግምት መስጠትና እርሱን ወይም እርሷን ከፍተኛ ዋጋ እንዳላቸው ሰዎች መቊጠር ነው። ሚስቶች ባሎቻቸውን ባሎችም ሚስቶቻቸውን ሊያከብሩ ይገባቸዋል። በጋብቻ ውስጥ ከሚፈጠረው ችግር እንዱ ባሎች ለሚስቶቻቸው ተገቢ የሆነውን አክብሮት መስጠት አለመማራቸው ነው። ብዙ ለዎች ያደጉት ሴቶች የግል ንብረት ሊደረጉ የሚገባቸው፤ ለግብረ ስጋ መጠቀሚያ ከሚያገለግል ቁሣቁስ በጥቂቱ በለጥ የሚሉ እንደሆነ ብቻ እየገመቱ ነው። ከዚህ የተሰየ ነገር ሣይማሩ ይህንን ያላዋቂነት እመሰካከት ይዘው ወደ ጋብቻ ይመጣሉ።



ማንም መከበርን የሚፈልግ ቢኖር ሰሴሎች የግድ አክብሮትን ማሣየትና የከበረውንም ህይወት ሊኖር ይገባል።

እግዚአብሔር ሰውን በአምሣሉ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ሊፈጥራቸውም በማንኛውም መንገድ እኩል አድርጎ ነው፤ በእግዚአብሔር አምሣል እንደተፈጠረ ሰው እርስ በእርስ የሚተያዩ ወንድና ሴት ለመከባበር ችግር የለባቸውም። ማንም መከበርን የሚፈልግ ቢኖር ለሌሎች የግድ እክብሮትን ማሣየትና የከበረውንም ህይወት ሊኖር ይገባል። ሊከበር የተገባው ማንም የተከበረ ሊሆን ያስፈልገዋል።

6. መታዘዝ

ጤናማ የሆኑ ጋብቻዎች የሚገነቡት በመከባበር ላይ ብቻ ሳይሆን በእኩልነት ላይ በተመሠረተ የመታዘዝ ፍቃድ ጭምር ነው። ብዙ ጊዜ እንደምንለማው ለባሎቻቸው ሊታዘዙ የሚገባቸው ሚስቶች ብቻ እንደሆኑ ነው። ይሁን እንጂ እዘው ትረን የምንረሣው፤ መታዘዝ በሁለቱም አቅጣጫ መሆኑን ነው። ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ፤ ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ . . . ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ወደዱ" (ኤፌ 5÷21-22፤ 25) ክርስቶስ ለሞት ራሱን እሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ቤተክርስቲያንን መውደዱ ከፍተኛው የመታዘዙ መግለጫ ነው። ኤፌ 5÷25 እንደሚናገረው፤ ባሎች ሚስቶቻቸውን ለወዱ

የሚገባው ልክ በመስዋእትነትና ራስን በፈቃደኝነት ለመገዛት አሣልፎ በመስጠት በተገለጠው የፍቅር አይነት ነው።



መታዘዝ፤ መብታችንን ስሱሳችን ስሳልፈን በመስጠት ፈቃደኝነት፣ ዘልጊዜም የእኛ በሆነው መንገድ ፀንተን ስመጓዝ በነፃነት መፍቀድ ነው።

በአግባቡ ለመረዳት፤ መታዘዝ የሚጠይቀው ምንም ነገር የለም። በማንም ምን ሊጫንብን የተገባ ሣይሆን ነፃ ምርጫ ነው። በመሠረቱ መታዘዝ፤ መብታችንን ለራሣችን አሣልፈን የመስጠት ፈቃደኝነት፤ ሁልጊዜም የእኛ በሆነው መንገድ ፀንተን ለመጓዝ በነፃነት መፍቀድ ነው። መታዘዝ ማለት ፍላጎትን፣ መብትንና ደህንነትን ጭምር ከራሳችን አስቀድመን ለሌላው መስጠት ነው። በዚህ መታዘዝ ላይ የሚገነባ ትዳር፤ ጤነኛ፣ ጠንካራና ስኬታማ ሆኖ ያድጋል።

7. እውቀት

እውቀት የጋብቻ የፀና መሠረት መሆኑን አግንነን ሣንገልጽ ማለፍ የማይቻል ነው። ብዙ ጋብቻዎች ለመውደቅ የሚንገዳገዱት ወይም የወደቁት ከእውቀት ማነስ የተነሣ ነው። ጋብቻ ምን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ጥቂት ፍንጭ እንኳን ሳይኖራቸው ጥንዶች ወደ ትዳር ይገባሉ። ስለራሳቸው፣ ስላገቡት ሰውና በጥቅሉ ስለሚኖራቸው ግንኙነት ያላቸው አመለካከት ከእውነታ የራቀና ምክንያታዊነት የጎደለው ግምት ነው።

አሁን ካለው በቂ የሆነ የመረጃ አቅርቦትና በጉዳዮ ላይ ብዙ አትኩሮት የተሰጠ በመሆኑ ምክንያት፤ በጋብቻ ላይ ያለ አላዋቂነትና መሀይምነት ይቅርታ የሚደረግለት አይደለም።

8. ታማኝነት

ታማኝነት ከመስጠት ጋር የተያያዘ ሲሆን ከመተማመን ጋርም በእጅጉ የተዛመደ ነው። በጋብቻ ውስጥ ስለ ታማኝነት ስንናገር፤ ብዙውን ጊዜ የግብረስጋ ግንኙነትን በአይምሯችን ይዘን ነው። ታማኝ የሆኑ ተጓዳኞች እርስ በእርሳቸው ብቻ በግብረስጋ ግንኙነት አንዳቸው ለሌላቸው የተወሰኑ ናቸው። ለዚህ ነው ከጋብቻቸው በፊት ከሌሎች ጋር የግብረስጋ ግንኙነት የነበራቸው ጥንዶች በጋብቻ ውስጥ ችግር የሚያጋጥማቸው። የታማኝነት ዋነኛው አላባ ጠፍቷል። ምንም እንኳ እርስ በእርሣቸው ሊተማመኑ ቃል

ቢገቡም፤ ሁልጊዜም የጥርጥር ጥላ እንዳጠላባቸው ይኖራል። ያ ጥላ ደግሞ ወደ ጥቁር ነጎድጓዳማ ደመና ለመለወጥና በሁለም ነገር ላይ ክንፉን ለመዘርጋት ብዙ ጊዜ አይወስድበትም።



ለጋብቻ ታማኝ መሆን ማለት፤ ስባለቤትዎ ጤንነት፣ ደስተኛ ነትና በአስተማማኝ ደህንነት በእርስዎ ህይወት ትልቁን ስፍራ የሚይዝበት፤ ከጌታም ጋር በግል ካለዎት ግንኙነት በቀር በህይወትዎ ውስጥ ትልቁን ድርሻ መስጠት ማለት ነው።

በጋብቻ ታማኝ መሆን በግብረስጋ ግንኙነት ብቻ ታማኝ ከመሆን የዘለለ ነው። ለሚስትዎ ታማኝ መሆን ማለት ሁልጊዜ አርሷን ከጥቃት መከላከል፤ ውበቷን፣ አስተዋይነቷንና ሁለንተናዋን ማድነቅ ይልቁንም ይህንን በሌሎች ፊት መግለጽ ነው።

ለባለቤትዎ ታማኝ መሆን ማለትም ከአርሱ ጋር መቀራረብ፣ ሁልጊዜም ገንቢ የሆኑ ቃላትን መናገርና በፍጹም ዝቅ አድርገው አለመመልከት ማለት ነው። ለጋብቻ ታማኝ መሆን ማለት፤ የባለቤትዎን ጤንነት፣ ደስተኛነትና አስተማማኝ ደህንነት በእርሶ ህይወት ውስጥ ከፍተኛውን ስፍራ የሚይዝበት፤ ከጌታ ጋር በግል ካለዎት ግንኙነት በቀር በህይወትዎ ትልቁን ሥፍራ መስጠት ማለት ነው።

9. ትእግስት

ትእግስት ስኬታማና ደስተኛ የሆነ ጋብቻን ለመመስረት ሌላው አስፈላጊ የመሠረት ድንጋይ ነው። ለምን? ጋብቻ ሁለት ፈጽሞ የተለያዮ ሰዎችን ማለትም የተለያየ የህይወት ልምምድ፤ የተለያየ የህይወት መነሻ፣ የተለያየ የህይወት ቅኝት፤ የተለያየ ፍላጎቶች አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፍጹም የተለያየ ባህል ያላቸውን ወደ አንድነት የሚያመጣ ነው። በእነዚህ ልዮነቶች ምክንያት ተጋቢዎቹ ትዳራቸውን ስኬታማ ለማድረግ ህይወትንና ባህልን የማጣጣም ለውጦችን ማምጣት ይጠበቅባቸዋል።

ግጭቶችና መጎዳዳት የማይቀሩ ነገሮች ናቸው። ምናልባት አገራችን የምትሠራበትን ሁኔታ እርሱ ላይወድላት ይችላል። እርሱ ደግሞ ምናልባትም በሥራ የቆሸሸ ልብሶቹን በየስፍራው በታትኖ የመውጣት ጠባይ ሊኖርበት ይችላል። በአመለካከቶቻቸው፣ በገንዘብ አወጣጣቸው፤ በትርፍ ጊዜ አጠቃቀማቸው፣ በግብረስጋ ግንኙነትና የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ ግጭቶች ይከሰቱ ይሆናል። እነኝህን ግጭቶች ለመፍታትና ልዩነቶችን በማቻቻል ተግባር ውስጥ

ትእግስት ዋነኛውን ሚና ይጫወታል። ሁለቱም ተጓዳኞች በዚህ ትእግስት ሊሞሉ ያስፈልጋቸዋል።



ግጭቶችን ለመፍታትና ልዩነቶችን በማቻቻል ተግባር ውስጥ ትክክለኛ ዋነኛውን ሚና ይጫወታል።

10. አስተማማኝ ኢኮኖሚ

አስተማማኝ ኢኮኖሚ አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት ከማይሰጣቸው ከጋብቻ የመሠረት አለቶች አንዱ ነው። ለመጋባት የሚያቅዱ ብዙ ወጣት ጥንዶች በጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት ላይ ተደላድለው ወደ ጋብቻ ስለመግባት ጉዳይ የሚሰጡት ትኩረት አናሣ ነው። እኔ እራሴ ይህንን ያየሁባቸው አጋጣሚዎች ተቆጥረው የሚዘለቁ አይደሉም። አንድ ወጣት ወደ እኔ መጥቶ ስመጋባት እንፈልጋለን አለኝ።

"ከሁለት አንዳችሁ አንኳን ትሠራላችሁ?"

"አንሠራም"

"ታዲያ አንዴት ጋብቻውን ልትመሠርቱ አሰባችሁ?"

"እንፋቀራለን . . . ስለዚህ ይሣካልናል . . . ፍቅር ራሱ መንገዱን ይፈልጋል። "

እርግጥ ነው ፍቅር አስፈላጊው ነገር፤ አንዲያውም ወሣኝ ነው፤ ይሁንና የአውነትን ፊር አንልቀቅ። ፍቅር የቤት ኪራይ አይከፍልም ወይም ምግብ አይሸምትም። የጋብቻን የሕይወት ልዩነት ማቻቻል በራሱ ፈታኝና አስቸጋሪ ነው። ወደ ጋብቻ የሚገቡ ተጓዳኞች ማወቅ የሚገባቸው የመጨረሻው ነገር ወደ ጋብቻ የሚገቡት ከብዙ ጉድለቶች ጋር የመሆኑን አውነት ሲሆን አስተማማኝ ያልሆነ ኢኮኖሚ ደግሞ ከእነዚህ ዋነኛ ከሆኑት ጉድለቶች አንዱ ነው።

የገንዘብ ችግር ያለባችሁ ከሆነ ከመጋባታችሁ በፊት ይሄ ችግር አስቀድሞ ቢወገድ የተሻለ አይመስላችሁም?

ስለገንዘብ ማሰብ ያለብን ጊዜ ከጋብቻችን ጊዜ እጅግ በጣም አስቀድሞ መሆን ይገባዋል። ሁለቱ ተጋቢዎች ወደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ከመሄዳቸው እጅግ አስቀድሞ፤ በጉዳዩ ላይ በግልጽና በታማኝነት ሊወያዩበትና ግልጽ የሆነ እቅድ ሊያወጡ ያስፈልጋቸዋል። አስተማማኝና የማያቋርጥ የገቢ ምንጭ ሊኖር

የግድ ነው። ቢያንስ ቢያንስ ወንዱ ቋሚ የሆነ ሥራ እንዲኖረው ይገባል። ማንኛዋም ቋሚ የሆነ ሥራ ያላትና አየሠራች ሰመቀጠል የምትፈልግ ሴት፤ ሥራ የሌለውን ወንድ አታገባም፤ ብታደርገው እርሱን አየደጎመች ሰመኖር ትገደዳለች። ይህ ደግ የተገላቢጦሽ መሆኑ ነው።

የኢኮኖሚ ችግር ለጋብቻ መፍረስ ምክንያት ከሆኑ ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ነው። በጋብቻ ውስጥ ስኬትን የሚፈልግ ከሆነ አስተማማኝ ኢኮኖሚ ችላ የሚባል ነገር አይደለም።



የኢኮኖሚ ችግር ለጋብቻ መፍረስ ምክንያት ከሆኑ ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ ነው።

ስምንቱ ጠቃሚ "የጋብቻ ክህሎቶች" ልዩ ባህሪያት

ከእነዚህ የመሠረት አለቶች በተጨማሪ በርካታ "የጋብቻ ክህሎት" ፈታኝ ነገሮች ላይ ልናተኩርባቸው ይገባል፤ እነዚህም የስብእና ብቃትና ጠንካራ ጋብቻን ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑ ባህሪያት ናቸው። ስምንት ነጥቦችን አስፍራያለሁ፤ ዝርዝሮቹን ይመልከቱና በየት ስፍራ እንደቆሙ ይመልከቱ።

1. ከሁኔታዎች ጋር መላመድ

ይህ በቀላሉ በተሰወጠው ሁኔታ ውስጥ ራስን ማላመድ ማለት ነው። ምንም ያህል በጥንቃቄ ስለ ጋብቻ ብናቅድም ሊሆን ያለውን ሁሉ አስቀድመን አንገምታለን ማለት አይደለም። ያልተጠበቁ ሁኔታዎች በተደጋጋሚ ብቅ ብቅ በማለት ያወጣናቸውን እቅዶች እንድንለውጥ ያስገድዱናል። ልክ የሁለቱ ሙሉ በሙሉ ልዩነት ያላቸው ለዎች አንድ ለው ወደ መሆን የመምጣት አውነት ሁኔታዎችን ማቻቻልን የግድ እንደሚጠይቅ ማለት ነው። ከሁኔታዎች ጋር መላመድ የምንችል ልንሆን ይገባል። ይከሰታሉ ተብለው የማይታሰቡ ነገሮች ሊከስቱ እንደሚችሉ ያስቡ። እነኝህን ነገሮች ለማደግና አስበውት በማያወቁት አቅጣጫ ለመንዝ በር እንደሚከፍቱ አጋጣሚዎች አድርገው ይወስዷቸው።

2. ለሌላው መጠንቀቅ

ይህ ስለሌላው ፍላጎት፤ ልብና እቅድ የነቃ ትኩረት መስጠት ነው። እነርሱ የሚለማቸው ስሜት እንዲሰማን፤ እነርሱ በሚገነዘቡበት መንገድ አለምን የመለማመድ ክህሎትን ይመለከታል። በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ በርካታ ግጭቶችና

አለመግባባቶች ሁለቱ ባለትዳሮች፤ አንዱ ለሌላው የመጠንቀቅን ክህሎት ቢያዳብሩ በቀላሉ ሊወገዱ ይችላሉ። ይህ ለዘለቄታው አንዱ በአንደኛው ጫማ ውስጥ የመራመድ ችሎታ ነው።

3. በችግሮች ውስጥ የመራመድ ክህሎት

ይህ ችግሮችን መፍታት ማለት አይደለም። አንዳንድ ችግሮች መፍትሔ የላቸውም። ባለትዳሮቹ እነዚህን ችግሮች የመለየትና በትኩረት የመመርመር፤ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማቅረብና አግባብነት ያለውን አማራጭ መስዶ በዚያ ውስጥ ማለፍን ግድ ይላል። በዚህ መንገድ አብዛኞቹን ችግሮች ሊፈቱ ከመቻላቸውም በላይ፤ ሊፈቱ በማይችሉትም ችግሮች ውስጥ እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ይማሩ። እጅግ ጠቃሚው ነገር ችግሮችን ለመፍታት መጋፈጥ እንጂ ከችግሮች መሸሽ አይደለም።

4. ፍቅርን የመስጠትና የመቀበል ክህሎት

በቃል እንደምንለው ይህ ቀላል ነገር አይደለም፤ በተለይም ለተወሰኑ ሰዎች ፍቅርን መስጠትና መቀበል ብዙውን ጊዜ በተፈጥሮ ለሴቶች ነው። በሌላው ወገን ወንዶች በማህበረሰቡ እንደሚታሰበው እንደ ወንድ ሊሆኑ ይጠበቅባቸዋል፤ ማለትም ስሜታቸውን በግልጽ ማሣየት አይገባቸውም። በዚህ ምክንያት ብዙ ወንዶች እውነተኛ የሆኑትን ስሜቶቻቸውን ለመግለጽ ይቸገራሉ። ጋብቻ በማያቋርጥ ሁኔታ መስጠትና መቀበል ሲሆን ይህ ደግሞ ፍቅርን መግለጽን ያካትታል።

5. የተረጋጋ ሰሜት

ይህ ስሜታችንን የመቆጣጠርና ከእኛ አምልጠው እንዳይወጡ የመያዝ ብቃት ነው። ይህም ማለት ግንፍል ቁጣችንን መቆጣጠርና ተግዳሮቶች ብስለት ወደሌለው ስሜታዊ ጩኸት እንዳይወስዱን ማድረግ መቻል ነው። አልፎ አልፎ የሚሆን ስሜትን መቆጣጠር አለመቻል ተፈጥሯዊ ነው፤ ከዚህ አልፎ የየዕለት ተግባር ከሆነ ግን ጥልቀት ያለውን ችግር ያመለክታል። ማንም ቢሆን በተከታታይ ስሜቱ ከነነፈለ በኋላ "ምንም ማድረግ አልችልም" ቢል ይህ የሚታመን ነገር አይደለም። ነገሩ እውነተኛ ከሆነ ግን ያ ሰው የባለሙያ እርዳታ ያስፈልገዋል። ይሁንና ብዙ ጊዜ ችግር አንድን ነገር ማድረግ አለመቻል ሳይሆን ይልቁንም ፈቃደኛ አለመሆን ነው። የተረጋጋ ስሜት ማለት፤ ፈቃደኝነትና ለስሜታችን፤

ለቃሎቻችንና ለድርጊታችን ሃላፊነትን መውሰድ መቻል ማለት ነው።

6. ግንኙነት የመፍጠር ክህሎት

እውነተኛ ግንኙነቶች ቀላል ያልሆኑና የሚፈጠሩትም አልፎ አልፎ ብቻ ነው። ግንኙነት ማለት ለሆች እርሶ የተናገሩትን መረዳታቸው ብቻ ሣይሆን፤ እርሶ ምን እንዳሉ መረዳታቸውን እርግጠኛ የመሆን ክህሎትና በተጨማሪም ሰዎች የሚናገሩትን የማድመጥ ችሎታ ነው። በሁለቱም ረገድ የግንኙነት ችሎታን ማሣደግ ረዥም ጊዜን፤ ትእግስትንና ጠንክሮ መስራትን የሚጠይቅ ነው።

7. በጥንዶቹ በራሳቸው መካከል ያለ ተመሣሣይነት

ማንኛውም ጋብቻ ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ሰዎች የሚጣመሩበት ሂደት ቢሆንም፤ በዚሁ አንፃር ጥቂት መመሳሰሎችም ደግሞ ይኖራሉ። ለምሣሌም የጋራ ፍላጎት፤ ተመሣሣይ የትርፍ ጊዜ ማሣለፊያ ተግባራት፤ ተመሣሣይ እምነት ወይም ተመሣሣይ የፖለቲካ አመለካከቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ በሁለቱ መካከል የጋራ መገናኛ መድረኮች ሆነው ያገለግላሉ።

8. ተመሣሣይ የቤተሰብ ሁኔታዎች

ምንም እንኳን ይህ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ባይሆንም፤ የተወሰነ የአስተዳደግ ልዩነት ያላቸው ሰዎች በየዕለቱ ስኬታማ የሆነ ጋብቻን ይገነባሉ፤ ለዚህ ነው ተመሣሣይ ከሆነ ቤተሰብ መውጣት ሁልጊዜ ጠቃሚ የሚሆነው። ጥንዶቹ ወደ ጋብቻ የሚገቡት በተቻላቸው መጠን የበሳ ሳን ፀጋዎችን ሁሉ ይዘው ሊሆን ይገባል። የቤተሰብ ተመሣሣይነት ደግሞ በትክክል አንዱ በሳ ሳን ነው።

* * *

እጅግ ጠቃሚ የመሆናቸውን ያህል፤ የመሠረት አለቶች ብቻቸውን በቂ አይደሉም። ሙሉ የሆነው መዋቅር የሚገነባባቸው መሠረቶች ብቻ ናቸው። የመሠረት አለቶች የሆኑት ፍቅር፤ እውነት፤ መተማመን፤ መሰጠት፤ መከባበር፤ መታዘዝ፤ እውቀት፤ ታማኝነት፤ ትእግስትና ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ መሠረት በራሳቸው ፍጻሜ ያላቸው አይደሉም። ይልቁንም የሁለት ልዩነት ያላቸው ሰዎች አሃደዊ ወደሆነ አካል፤ በነፍስና በመንፈስ የሚዋሃዱበትን

ውብ ጌጥ ብለን የምንጠራውን ጋብቻ ገንብተን የምናሳይበት መሠረቶች ናቸው። ስኬትና ደስተኝነት ገጠመኞች አይደሉም፤ እንዲያውም በትኩረት ለተደረገ እቅድ፣ በትኩረት ለታቀደ ግብ፣ በትእግስት ለተደረገ እድገት ውጤቶችና ለዚህም የተሰጡ ገፀ በረከቶች ናቸው።

መርሆዎች

1. ጋብቻ እንደመዋእለንዋይ ነው፤ ስኬትም በዚህ መዋዕለንዋይ ላይ በምናፈሰው እውቀትና ጊዜ እድገቱ ይወሰናል።
2. ስኬታማ የሆነ ጋብቻ በጥንቃቄ የተሠራ እቅድና ታስቦበት የተተሰመ ትልም ውጤት ነው።
3. ስኬታማ የሆነ ጋብቻን ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑ ጽኑ የመሠረት አለቶች።
   - ፍቅር
   - እውነት
   - መተማመን
   - መስጠት
   - መታዘዝ
   - እውቀት
   - ታማኝነት
   - ትእግስት
   - አስተማማኝ ኢኮኖሚ
4. ስምንቱ ጠቃሚ "የጋብቻ ክህሎቶች" ልዩ ባህሪያት
   - ከሁኔታዎች ጋር መላመድ
   - ለሌላው ሰው መጠንቀቅ
   - በችግሮች ውስጥ የመራመድ ክህሎት
   - ፍቅርን የመስጠትና የመቀበል ክህሎት
   - የተረጋጋ ስሜት
   - ግንኙነት የመፍጠር ክህሎት
   - በጥንዶቹ በራሳቸው መካከል ያለ ተመሳሳይነት

ምዕራፍ ስድስት

የታሠርንበትን እስራት ጠፍታት

ማንኛውም በተሞክሮ የዳበረ ልምድ ያለው የጋብቻ አማካሪ እንደሚናገረው፤ በሌሎች የህይወት ግንኙነቶች ውስጥ የሚፈጠሩት ችግሮች ሁሉ ተደምረው በጋብቻ ውስጥ የሚነሱትን ችግሮች አያክሉም። ከዕጽ፣ ከወንጀል፣ በገንዘብ ምክንያት ከሚነሱ ግጭቶች፣ ከሰሜታዊና ሰነልቦናዊ ቀውሶች ይልቅ፤ በጋብቻ ውስጥ ከፍተኛ ችግሮች ይፈጠራሉ። ለባህላችን ማደግና ለስልጣኔያችን መፋጠን እጅግ ወሳኝ የሆነው ይህ ተቋም በዚህ ቀውስ ውስጥ መግባቱ የዘመናችን አሳሳቢ ምልክት ነው።

አዲስ ተጋቢዎች የጋብቻ ህይወታቸውን ለማቻቻል በሚያደርጉት ጥረት ከሚያጋጥሟቸው ጠንካራ ተግዳሮቶች አንዱ፤ ከቀደሙ ወላጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከአዲሱ ሁኔታቸው ብርሃን ጋር እንዴት ማገናዘብ እንደሚማሩ ነው። ጋብቻ በባለትዳሮችና ባደጉባቸው ቤተሰቦች መካከል በነበረው የቀደመ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል። ብዙ አዲስ ተጋቢዎች ከወላጆቻቸው ጋር የተሣሰሩበት ገመድ የመበጠስና ከማግባታቸው በፊት ከለመዱት የሕይወት ልምምድ ፈጥኖ ለመውጣት ይቸግራቸዋል። ብዙውን ጊዜም ለአዲሱ ባለቤታቸውና ለቀደሙት ቤተሰቦቻቸው በሚኖራቹው ሀላፊነት ምክክል ልባቸው ይከፈላል። ይህ ውጥረት በጋብቻ ውስጥ ግጭት ይፈጥራል፤ በተለይም ደግሞ አንደኛው ወገን ከሌላኛው ይልቅ ቀድሞ ከነበረው የግንኙነት ቀለበት ውስጥ ፈጥኖ መውጣት ሲያቅተው ችግሩ ይከሰታል።

የጋብቻን ህይወት ማቻቻል በተጋቢዎቹ ላይ ችግር እንደሚፈጥር ሁሉ በተጋቢዎቹ ቤተሰች ላይ ተመሣሣይ ችግር ያስከትላል። አንዳንድ ጊዜ ወላጆች ልጆቻቸውን ከጋብቻቸውም በኋላ ቢያንስ በስሜት ደረጃ ይዘዋቸው በመቆየት ችግሩን ያወሣስቡታል። አውቀውትም ሆነ ሣያውቁት ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ራሳቸውን ችለው በመውጣታቸው የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋሉ። ህፃኑ ጎጆውን ጥሎ በመሄዱ ሀዛብ ከራሳቸው ጋር ብዙ ይታገላሉ። ምናልባት በስሜትም ይሁን በኢኮኖሚ ጉዳይ በልጆቻቸው ጥገኞች ከነበሩ፤ በልጆቸው ህይወት ውስጥ ጣልቃ

በሚገባው በአዲሱ ሰው ምክንያት ከልጆቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንደሚለወጥ በማሰብ ስጋት ውስጥ ይገባሉ።

ከየትኛውም አቅጣጫ ይምጣ፤ አዲስ ተጋቢዎች ከወላጆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በትዳራቸው ላይ ተጽእኖ ያስከትላል። ይህንን ችግር እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ካልተማሩ ያሠራቸው ገመድ በአፍንጫቸው ውስጥ ተቀርቅሮ ለመተንፈስ ችግር እንደሚፈጥር መሰናክል የግንኙነታቸውን ሕይወት ሊያንቀው ይችላል።

ጋብቻ የመጀመሪያው ስብስቧ ግንኙነት ነው

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፤ ከግንኙነቶች ሁሉ ዋንኛውና በጣም ጠቃሚው ግንኙነት፤ በግለሰብ ሰብአዊ ፍጥረትና በእግዚአብሔር መካከል ካለው ግንኙነት ቀጥሎ ዋንኛው በወንድና በሴት መካከል ያለ የጋብቻ ግንኙነት ነው። ሁልጊዜም ችግሮች የሚከተሉት ከእነዚህ ግንኙነቶች አንደኛው ከተገባው የቀዳሚነት ስፍራ ሲለቅ ነው። ከብዙዎቹ የችግር ምንጭ ከሆኑ ምክንያቶች ዋንኛው ግንድ፤ ሰዎች ለእግዚአብሔር ወይም ለትዳር ጓደኞቻቸው መስጠት የሚገባቸውን ከፍተኛ ቅድሚያ ለሌሎች ሰዎች ወይም ነገሮች አሳልፈው ሲሰጡ ነው።

በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው፤ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሊፈጠር የሚገባ መሠረታዊ ግንኙነት አድርጎ በመጀመሪያ ስለመሠረተው ነው።

"እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፤ አንቀላፋም። ከጎኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ስፍራውን በስጋ ዘጋው። . . . እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ ስጋም ከስጋየ ናት። እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው እናቱንና አባቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል" (ዘፍ 2÷21-24)።

ልብ ይበሉ፤ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሊፈጥር የጀመረው ከባልና ከሚስት እንጂ ከወላጅና ከልጅ አይደለም። በእግዚአብሔር አቅድ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት በወላጅና በልጅ መካከል ካለው ግኙኙነት ይልቅ ቀደምቱና የመጀመሪያ ደረጃ ግንኙነት ነው። ቁጥር 24 እንደሚናገረው፤ ሰው እናቱና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል። "መተው" የሚለው ቃል

"ሰጊዜው" የሆነ መለየትን ሊያመለክት፤ መጣበቅ የሚለው ቃል ግን "ዘለቄታነት" ያለውን ሁኔታ ይናገራል። በትዳር ውስጥ የባልና የሚስት ቀደምት ሃላፊነታቸው እርስ በእርስ ላላቸው ግንኙነት እንጂ ለወላጆቻቸው ወይም ቀድሞ ለነበሩበት ሁኔታ አይደለም።

የጋብቻ ግንኙነት በሕይወት ውስጥ ካሉ ሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ መሠረታዊና ቁልፍ የሆነ ግንኙነት ነው። አዳምና ሄዋን ወላጆች ከመሆናቸው በፊት ባልና ሚስቶች ነበሩ። በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት በወላጅና በልጅ መካከል ካለው ግንኙነት ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጠው ከተገባባቸው ምክንያቶች አንዱ፤ ባልና ሚስት ለህይወት አስፈላጊ የሆነውን ፍላጎት አንዳቸው ለአንዳቸው ለማሟላት ኪዳን ስለገቡ ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን የመውደድና የመንከባከብ፤ አካላዊ፣ ስሜታዊና መንፈሣዊ ፍላጎቶቻቸውን የማሟላት ሃላፊነት አለባቸው። ይሁን እንጂ ባልና ሚስት በአንድነታቸው ውስጥ ከሚጋሩት ህይወት አንፃር ሊታይ ይህ በመሠረቱ የተለየ ነው።



በወላጆችና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ጊዜያዊ በመሆኑ ሊሠበር ይገባዋል። በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ግን ዘላቂ በመሆኑ ሊሰበር አይገባውም።

በመሠረቱ፤ በወላጆችና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት ጊዜያዊ በመሆኑ ሊሠበር ይገባዋል። በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ግን ዘላቂ በመሆኑ ሊሰበር አይገባውም። ወላጆች ልጆቻቸውን ሆን ተብሎ በታቀደ ማለትም የበሰሉ መሰ ሰዎች አድርጎ በማሣደግ ዓላማ ላይ ተመስርተው ሊያሳድጓቸው ይገባል። ልጆች አንድ ጊዜ በራሳቸው መንገድ የሚያድጉ ከሆነ፤ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ይከሰታል። ይህ ለውጥ ደግሞ ልጆቹ ጋብቻን ከመሰረቱ በኋላ ጎልቶ የሚታይ ይሆናል። ምንም እንኳን ወላጆች ልጆቻቸውን ሁል ጊዜም ሊወዷቸውና ሊያከብሯቸው ቢገባም በልጆቻቸው ላይ ዘላቂ የሆነ የበላይነት ስፍራ ወይም ቅድሚያ አይኖራቸውም። እነዚህ ያገቡ ልጆች ከወላጆቻቸው ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጧቸው ከሚገቡ ከአዲስ ሰዎች ጋር ግንኙነት ጀምረዋል - ከትዳር ጓደኞቻቸው። መሆን የሚገባው እንዲህ ነው። ጊዜያዊ የሆነው በወላጆችና በልጆች መካከል የነበረው ግንኙነት ዘላቂ ለሆነው የባልና የሚስት ግንኙነት ስፍራ ሊለቅ ይገባዋል።

ማግባት ማለት የቀደመውን ቤት መልቀቅ ማለት ነው

በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ እንደተለመደው አስተላለፍ ጋብቻ የሁለት ቤተሰቦች ወደ አንድነት መምጣት ነው። ባልየው የራሱን ቤተሰብና የትውልዱን ዞር ይወክላል፤ ሴቷም እንደዚሁ የራሷን፤ በዚህ ውህደት ውስጥ እነርሱና ዘመዶቻቸው ሁሉ አንድ ትልቅ ደስተኛ ቤተሰብ ይሆናሉ። ይህ ለአይምሮ የሚመች፣ የተለመደ ሁኔታና ትክክለኛ ስፍራውን የያዘ ቢመስልም አግባብነት የሌለውና መጽሀፍ ቅዱሣዊም ያልሆነ ነው። ጋብቻ ሁለት ቤተሰቦች በአንድነት የሚጠቀላለሉበት አይደለም፤ ይልቁንም ሦስተኛ ቤተሰብ የሚፈጠርበት ነው። ባልና ሚስት ወደ አንድነት ሲመጡ የራሳቸው የሆነ፣ የተለየ፣ ሙሉ የሆነ የእነርሱን ቤተሰብ ይመሠርታሉ። ይህም ቤተሰብ ከቤተሰቦቻቸውና ከዘራቸው ተጽእኖ ነፃ የሆነ ቤተሰብ ነው። ለዚህ ነው ዘፍ 2፥24 "ስለዚህም ምክንያት ሰው *አባቱንና እናቱን ይተዋል* ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፤ አንድም ሥጋ ይሆናሉ" የሚለው። በጋብቻ ውስጥ ከሁለት የተለያየ ቤተሰብ የወጡ ወንድና ሴት ከሁለቱ ቤተሰቦች የተለየ ሦስተኛ ቤተሰብ ይመሠርታሉ። ምንም እንኳን ይህ ጥቅስ በተለይ ባልየው ቤቱን ለቆ እንደሚወጣ ቢናገርም፤ ሚስቱንም የሚያጠቃልል ነው። እንደዚህ ባይሆንማ እንደርሱ ቤቷን ትታ ካልወጣች ሚስት ጋር እንዴት ሊጣበቅ ይችላል? በተሣካ ሁኔታ የራሣቸውን ቤት ለመመስረት ብቸኛው መንገድ ሁለቱም ቤተሰቦቻቸውን ተለይተው ሲወጡ ነው። ይህ ክፍል ስለ ወንዱ የሚጠቅሰው ጋብቻው ከተመሠረተ ጀምሮ የአዲሱ ቤተሰብ ራስና አዲሱ አመራር ለጭ እርሱ በመሆኑ ነው።

በጋብቻ ውስጥ ፈጥኖ ወደ ግጭት ለመሮጥ ፈጣኑ መንገድ ባልየው የግንኙነት ቅድሚያን በሚመለከት ከሚስቱ ቤተሰቦች ጋር ሩክክር ውስጥ ሲገባ ነው። ባሏ ከወላጆቹ ጋር የነበረውን የግንኙነት ትስስር ፈጥኖ ያልበጠሰ ሚስት የሚገጥማት ችግርም ተመሣሣይ ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው መመሪያ ግልጽና ጠንካራ የሆነው። አባትና እናታቸውን ይተዋሉ እርስ በእርሳቸው ይጣበቃሉ።

የቀደመውን ቤት ለቆ መውጣት የጋብቻ መሠረታዊ መርህ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጋብቻን በተመለከተ የተሰጠው የመጀመሪያ መመሪያ "ይተዋል" የሚል ነው። ምንም እንኳ ዋነኛው ሃሣብ ቤትን መተውን ቢመለከትም፤ በአካል ለቆ ከመውጣት

የዘለለ ሀሣብን የያዘ ነው። ባልና ሚስት ሲጋቡ የወጡበትን ቤተሰብ የሚተወት በአካል ብቻ ሣይሆን በአይምሮ፣ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና በስሜታቸውም ጭምር ሊሆን ይገባል። ይህ ማለት ግን በመጭው ዘመናቸው ከቀደሙት ቤተሰቦቻቸው ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እርግፍ አድርገው ይተዋሉ ማለት ሳይሆን፣ ባልና ሚስቱ ቤታቸውንና ትዳራቸውን በሚገነቡበት መንገድ ወይም እንደ ባልና ሚስት በሚወስኑት ውሳኔ ላይ ቤተሰቦቻቸው ወሣኝ ሚና አይጫወቱም ማለት ነው። "መተው" ማለት የተጋቡት ጥንዶች በቤተሰባቸው ላይ ጥገኞች አይሆኑም፣ ቤተሰቦቻቸውም የእነርሱ ጥገኞች አይሆኑም ማለት ነው።



ባልና ሚስት ሲጋቡ የወጡበትን ቤተሰብ የሚተዉት በአካል ብቻ ሳይሆን በአይምሮ፣ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችና በስሜታቸው ጭምር ሲሆን ይገባዋል።

"መተው" በሚለው ቃል ተጋቢዎቹ የወጡበት ቤተሰብ መሄዳቸውን ሊፈልጉትም ሳይፈልጉትም ይችላሉ የሚል እንድምታ አለው። ብዙ ወላጆች በዚህ ነገር ይቸገራሉ፣ ልጆቻቸው እንዲወጡ እንደ ሙሉና የበሰለ ሰው የራሳቸውን ህይወት እንዲኖሩ ሊተዋቸው ይከብዳቸዋል። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በጥበቡ ይህንን ጉዳይ ለወላጆች ውሳኔ እንደ ምርጫ ያልሰጠው። የትልቅ ሰው ህፃን የሆነው ሰው አግብቶ ጎጆውን ሊለቅ እርሱ ወይም እርሷ እንዲህ ይላሉ፣ "አሁን የግል ሕይወቴን ልተው ዝግጁ ነኝ። ይህችን ሴት እስከ ሕይወት ዘመኔ ፍፃሜ አብሬያት ልኖር መርጫለሁ። እወድሻለሁ ይሁንና የራሴን ውሳኔ ልወስን ያስፈልገኛል። ምንም ያህል ሊሰማሽ ይችላል፣ ይሁን እንጂ እሄዳለሁ። እርግጥ ነው የምትሰጭው አስተያየት ለእኔ ዋጋ አለው፣ ቢሆንም ለማደርገው ድርጊት ወሳኙን ሚና እንዲጫወት አልፈልግም። ለእኔ መልካም የሆነውን ነገር መምረጥ አለብኝ"።

ብዙ ወጣቶች የወላጆቻቸውን የይሁንታ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር ቤታቸውን አይለቁም። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እንዲሆን ባይጠይቅም ነገሩ በራሱ ችግር የለውም። ቤተሰብ ያፈራውን በረከት ይዞ መለየት ሁልጊዜም መልካም ነው፣ ያለዚህም በረከት ቤትን መልቀቅም ጥሩ ነው። ዋናው ቁም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው። የቤተሰብን ፍላጎት ከመታዘዝ ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዝ እጅግ ጠቃሚ ነው።

እግዚአብሔር ትተው እንዲወጡ ከተናገረዎት በኋላ፣ የቤተሰብን ፈቃድ እያሚሉ መኖር እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነው።

ባልንጀርነትን መንከባከብ

ወጣት ተጋቢዎች በአካልም ይሁን በስሜታቸው ቤታቸውን ሰቀው የመወጣቱ ጉዳይ ለምን እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ በርካታ ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ። በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ ተጋቢዎቹ ገና ከጅምሩ እርስ በእርሳቸው የጋብቻ ባልንጀራነታቸውን የሚንከባከቡት እድል ለማመቻቸት ነው። ባልንጀርነት ሰፋሉም ስኬታማ ትዳሮች መሠረት የሆነ ነው። የወላጆችና የልጆች ግንኙነት በወሊድ ወይም ጉዲፈቻ በማድረግ ይጀመራል፣ የባልና የሚስት ግንኙነት የሚመሠረተው ግን በቃል ኪዳን በመሆኑ ልዩነት አለው። ጋብቻ እግዚአብሔር የመሠረተው ኪዳን በመሆኑና የታተመውም በመንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ጠንካራ የደም ትስስርን የሚተካ ነው። ደም ምናልባት ከውሃ ሊወፍር ይችላል፣ ምንም ቢሆን ግን ከቃል ኪዳን አይወፍርም።



የወላጅና የልጆች ግንኙነት በወሊድ ወይም ጉዲፈቻ በማድረግ ይጀመራል፣ የባልና የሚስት ግንኙነት ግን የሚጀመረው በቃል ኪዳን በመሆኑ ልዩነት አለው።

በጋብቻ ውስጥ ባለቤታችን በምድር ላይ ካለ ማንኛውም ሰው ይልቅ ለእኛ እጅግ በጣም ጠቃሚው ሰው ነው። ከጌታ በቀር ማንም ቢሆን፣ አሰረግጬ እናገራለሁ፣ ማንም ቢሆን ከባላችን ወይም ከሚስታችን በፊት በትኩረታችንም ይሁን በስሜታችን ቀዳሚውን ሰፍራ ማንም ሊይዝ አይገባውም። ወላጆች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ወይም ከማንኛውም ቤተሰባዊ የደም ትስስር ይልቅ በላጭነትና ልዩነት ያለው ስፍራ እርስ በእርሳችን ልንሰጣጥ ይገባናል። የቤተሰባችን አባላቶች የሚሰጡት አስተያየት፣ ፍላጎትና ልዩ ልዩ ጥያቄዎቻቸው ከጋብቻችን በኋላ ተጽእኖ ሊያመጡብን አይገባም። ባለትዳሮች እርስ በእርሳቸው ቀዳሚውን ስፍራ ሊሰጣጡ ያስፈልጋል። እንደባልና ሚስት ወይም እንደጓደኞች ብቻ ሣይሆን እንደ መልካም ባልንጀሮች ይሆኑ ዘንድ፣ ባለትዳሮች በቂ የመተዋወቂያ ጊዜ እንዲኖራቸው አብረው ሊሆኑ የራሳቸው ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በጋብቻ ውስጥ ያለ ባልንጀርነት በደም ወይም በመወለድ ከተገኙ ማንኛውም ሁኔታዎች ይልቅ በላጭ ነው።



በጋብቻ ውስጥ ያሰ ባልንጀርነት በደም ወይም በመወለድ ከተገኘ ከማንኛውም ሁኔታ ይልቅ በላጭ ነው።

እንደማናቸውም በፍላጎታችን ለስኬት ጥረት እንደምናደርግባቸው ነገሮች ሁሉ ባልንጀርነትን መገንባት ጊዜን፣ ትእግስትንና ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል። ባልንጀርነት ክብካቤን ይፈልጋል። ማንም ውብ የሆነ የአትክልት ስፍራ እንዲኖረው ቢፈልግ፤ ጊዜውን ሰጥቶ አፈሩንና ማዳበሪያውን ሊያዘጋጅ፣ ዘሩን ሊተክል፣ የመስኖውን ውሃ ሊያዘጋጅ፣ በጥንቃቄ አረሙን ሊነቃቅል፣ ትዕግስት ለማድረግ ፈቃደኛ ሊሆን ያስፈልገዋል። በጋብቻ ውስጥ ያለ ባልንጀርነትም ከዚህ ባላነሰ መንገድ ክብካቤ ያሻዋል። በአንድ ምሽት ወይም እንዲያው በአጋጣሚ ግን አይዳብርም። ማንኛውም አይነት የከበባውን እድገት የሚያቀጭጭ አረም ሁሉ በነቂስ ተነቅሎ መጣል አለበት።

በብዙ ትዳሮች ላይ ችግር የሚያስከትለው አንዱ አረም ታስቦበት የሚደረግ አላስፈላጊ የሆነ በባልና ሚስት ህይወት ዕለታዊ ጉዳዮችና ግንኙነቶች ውስጥ የቤተሰቦቻቸው አባላት ጣልቃ ገብነት ነው። ባልና ሚስት አንድ ጊዜ ከተጋቡ በኋላ ከወላጆቻቸው ሊቀበሉ የሚገባው ምክራቸውን ብቻ ነው - ይህንንም ቢሆን የሚቀበሉት ሲጠይቁ ነው። ወላጆች ካልተጠየቁ በቀር ምክራቸውንም ይሁን አስተያየታቸውን ሊሰጡ አያስፈልግም። እንዲህ ቢያደርጉ ግን የተጋቢዎቹን አመራር ሰጭነት በራስ የመወሰን እድገት ከግምት ውስጥ አለማስገባት ይሆናል። በተጋቡ ጊዜ፤ አመራር የመስጠቱና በግል የመወሰኑ ሃላፊነት ከቀደመው ቤታቸው አዲስ ወደሚገነቡት ቤት ተዘዋውሯል። ማንኛውም አመራር ሰጭነት የሚያድገው በእነርሱ ነው። በራሳቸው ሊወሰኑ አሁን ሀላፊነትን ለመውሰድ ብቁ ናቸው። ባልንጀርነትን ከመንከባከብ ተግባራት ከፊሉ ይህንን ሃላፊነት በጋራ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ መማር ነው።

ይህ የነፃነት መርህ ለአዲሱ ትዳር መሣካት እንዴት ወሳኝ መሰላችሁ! ለባለትዳሮቹ ምንም እንኳን ጋጠወጥና ልብ የሚሰብር ተግባር ቢመስል እንኳን፤ እነርሱ ሳይጋብዙ የወላጆቻቸውና የቤተሰብ አባላቶች የሚጭኑባቸውን አስተያየትና ምክሮች ለመከላከል የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። አዎ! ቀላል ላይሆን ይችላል፤ የእግዚአብሔር ቃል ለመታዘዝ ግን አስፈላጊ ነው።

ክርስቲያኖች ወላጆቻቸውን መርዳት አለባቸው?

አሁን ብዙ ወጣት ተጋቢዎች ለትዳር ህይወት ከወጡ በኋላ ለወላጆቻቸው የሚኖራቸውን ሃላፊነት ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ። በምኖርበት በበሀማስ የተለመደው አመለካከት ያደገ ልጆቻቸው ካገቡም ባኋላ ቢሆን በዘላቂነት በገንዘብም ይሁን በሌሎች መንገዶች እንዲረዷቸው ይጠብቃል። በነገራችን ላይ ወላጆች ልጆቻቸውን በማሳደግና በመንከባከብ ላደረጉላቸው ነገር ልጆች በማንኛውም መንገድ ውለታቸውን መክፈል ትክክለኛ ተግባር ነው። እንዲህ አይነቱ አመለካከት ለበሀማስም ይሁን ለመላው የሥስተኛ ዓለም አገሮች እንግዳ ነገር አይደለም። በመጠኑ ይለያይ እንጂ ይህ በማንኛውም ባህል ውስጥ በተለይም የጠበቀ ባህላዊ ትስስር ባለባቸው ቤተሰቦችና ጎሣዎች ውስጥ ይገኛል።

ይህ አመለካከት ትክክል ነውን? ያገቡ ልጆች ወላጆቻቸውን የመርዳት ሀላፊነት አለባቸውን? የዚህን መልስ ለማግኘት ጋብቻንና ቤተሰብን ከመጀመሪያው ያቀደውን የእግዚአብሔርን ቃል፤ መጽሐፍ ቅዱስን መመልከት ያስፈልገናል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ሚስዬናዊ፣ የስነ መለኮት ሰውና ፀሀፊ የሆነው ጳውሎስ የሚለውን እንመልከት፤

"እነሆ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛየ ነው፤ አልከብድባችሁም፤ እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውም" (2ቆሮ 12÷14)።



እውነተኛ ነፃነት በሁሉም ወገን ጠቃሚነት ስለው፤ ልጆች የወላጆቻቸው ጥገኞች አይደሉም፤ ወላጆችም የልጆቻቸው ጥገኞች አይሆኑም።

ምንም እንኳን ጳውሎስ በቆሮንቶስ በምትገኘው ቤተክርስቲያን በሚገኙ መንፈሳዊ ልጆች አውድ ላይ ተመሰርቶ ቢጽፈውም፤ ያሰፈረው መርህ በመላው ዓለም ለሚገኝ ስብአዊ የሆነ ቤተሰባዊ ግንኙነት ሁሉ ሊተገበር የሚገባው ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው እንጂ ልጆች ለወላጆቻቸው ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ቃል የሚገባው ሊጎበኛቸው በመጣ ጊዜ ሸክም ሆኖ እንደማይከብድባቸው ነው። በዚሁ ሁኔታ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ በገንዘብ ጉዳይም ይሁን በማንኛቸውም ሌሎች ሁኔታዎች ሸክም መሆን የለባቸውም። ይህ

ጥቅስ በሌላ መንገድ የሚናገረው ወላጆች ለልጆቻቸው እንዲያከማቹ ነው። ወላጆች ልጆቻቸው የበሰሉ፣ ምርታሞች፣ ራሳቸውን የቻሉ ሙሉ ሰዎች እንዲሆኑ በሚችሉት ሁኔታ ሁሉ መንገድ የማዘጋጀትና የመደገፍ ሃላፊነት አለባቸው። እውነተኛ ነፃነት በሁለቱም ወገን ጠቃሚነት አለው፤ ልጆች የወላጆቻቸው ጥገኞች አይደሉም፤ ወላጆችም የልጆቻቸው ጥገኞች አይሆኑም።

ለተጋቢዎች እንኳንስ ወላጆቻቸውን የመርዳት ባህላዊ ተጽእኖ ስሜት ወድቆባቸውና የትዳርን ጉዳዮች ማስተካከል በራሱ ፈታኝ ተግዳሮት ነው። የገዛ ቤታቸውን ለመመስረት፣ የራሳቸውን ወጭ ለመበጀት፣ ቅድሚያ የሚሰጡትን ነገር ለመወሰን ነፃነት ያስፈልጋቸዋል። ይህ ማለት ግን አሁንም በወላጆቻቸው ጉዳይ ፈጽሞ ምንም አያገባቸውም ማለት አይደለም። ወላጆቻቸው በእርግጥ በችግር ውስጥ ከሆኑና ተጋቢዎቹም ሊረዷቸው የሚችሉበት መንገድ ካለ መርዳታቸው መልካም ነው። ለመርዳት የሚወሰደው ውሳኔ በባለትዳሮቹ ነፃ የሆነ ምርጫ ላይ የሚመሠረት እንጂ ውጫዊ ከሆነ አካል በባህልም ይሁን በሌሎች ፍላጎት የሚጫንባቸው አይሆንም።

በተመሳሳይ ሁኔታ፤ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያመለክተው ልጆች ለወላጆቻቸው በተለይም መበለቶች የሆኑትንና ራሳቸውን ለማስተዳደር ምንም ገቢ የሌላቸውን ለመንከባከብ የተወሰኑ ሃላፊነቶችን ሊሸከሙ ይገባል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ እንኳን፤ የምድራዊ ቤተሰቡ ታላቅ ልጅ እንደመሆኑ መጠን፤ ደቀመዝሙሩና የቅርብ ጓደኛው ለነበረው ለዮሐንስ እናቱን እንዲንከባከብለት ሃላፊነት ሲጥልበት እንመለከታለን (ዩሐ 19÷26-27 ይመልከቱ)። ያዕቆብ ወላጆች የሌሏቸውን ልጆችና ባልቴቶችን አማኞች ሊንከባከቧቸውና የመርዳትም ሃላፊነት እንዳለባቸው ይናገራል (ያዕ 1÷27)። በዚያ ዘመን ወላጆች የሌሏቸው ልጆችና ባልቴቶች የማህበረሰቡን ዝቅተኛ ና ሀይል የሌላቸው ክፍሎችን ይወክሉ ነበር። ማንም አነርሱን ወክሎ የሚናገርላቸው የሌላቸው ሰዎች ናቸው። ምንም እንኳን ያዕቆብ የሚናገረው ለመላው ቤተክርስቲያን ቢሆንም፤ ከእነኝህ ወላጅ አልባ ህፃናትና ባልቴቶች መካከል በዚያች ቤተክርስቲያን ውስጥ ወላጆች ወይም ዘመዶች ያሏቸው ጥቂት ሰዎች እንደሚኖሩ ጥርጥር የለውም።

በጢሞቴዎስ መልዕክት አምስተኛው ምዕራፍ ላይ ጳውሎስ፣ በተለይም ባልቴቶችን በሚመለከት ተግባራዊ ሊሆን የሚገባውን ምክር ይሰጣል።

"በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ባልቴቶች አክብር። ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሯት አነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተሰቦቻቸው አግዚአብሔርን መምሰል ያሳዮ ዘንድ ለወላጆቻቸው ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ። . . . ነገር ግን የአርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካዳ ከማያምን ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው" (1ጢሞ 5÷3-5፤8)።

በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ "በትክክል መረዳት የሚያስፈልጋቸውን" ቤተክርስቲያን ልትንከባከብ ሃላፊነትና የአገልግሎትም ሽክም ነበረባት። እነኝህ ሴቶች ባል የሌላቸው በመሆኑ ማንም የሚንከባከባቸው አልነበረም። ምናልባትም ብዙዎቹ ባሎቻቸውን ያጡት በእምነታቸው ምክንያት ሰማዕታት በመሆናቸው ይሆናል። ስደት የባልቴቶችን እርዳታ ፈላጊነት ሰለሚያፋጥነው በዚህ ረገድ የቤተክርስቲያን የገንዘብ አቅም ያልተጠበቀ ችግር ሊደርሰበት ይችላል። ጳውሎስ እንደተናገረው የቤተክርስቲያን ቀዳሚው ሃላፊነት ምንም ረዳት፣ ልጅ ወይም የልጅ ልጆች እንኳን የሌላቸውን ባልቴቶች መንከባከብ እንደሚገባ ነው። ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ያሏቸውን ባልቴቶች የመንከባከብ ሀላፊነት ግን የልጆቻቸው ወይም የልጅ ልጆቻቸው ይሆናል።

በሌላ አባባል ልጆችና የልጅ ልጆች፤ በጤና ምክንያት፣ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን ያጡትን ወይም በተለያየ ምክንያት ራሣቸውን መርዳት ያልቻሉ ወላጆቻቸውንና አያቶቻቸውን ከአግዚአብሔር በታች የመንከባከብ ሃላፊነት አለባቸው።

ጤነኛና አራሳቸውን መርዳት የሚችሉ ወላጆች የልጆቻቸው ሽክም ሊሆኑ አይገባቸውም። በሌላው በኩል ግን ልጆች ራሳቸውን መደገፍ ለማይችሉ ወላጆቻቸው ሁለንተናዊ ደህንነት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

ስለቀድሞ የግንኙነት መስፈርቶችን ማስቀመጥ

በተጋቢዎችና በቤተሰቦቻቸው መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች በቀላሉ መወገድ እንዲችሉ፤ ገና ከመጀመሪያውም

ጊዜ ወስዶ በመነጋገር በመካከላቸው ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት መሠረታዊ የሆኑ መስፈርቶችን በማስቀመጥና እያንዳንዱ ወገን እነኝህን መስፈርቶች በትክክል መረዳቱን እርግጠኛ መሆን አለባቸው። የእጮኝነት ጊዜ ያስፈለገበት ጠቃሚ አላማም ይህ ነው። የእጮኝነት ጊዜ ሁለቱ ጓዳኞች እርስ በእርስ የሚጠናነቡበትና የጋብቻቸውን እቅድ የሚያወጡበት ብቻ ሳይሆን፤ ይልቁንም የሁለቱም ቤተሰብ አባላት በአግባቡ እንዲተዋወቁ መንገድ የሚከፍት ነው።



ተጋቢዎች፤ ከመጀመሪያውም ጊዜ ወስደው በመነጋገር ከወላጆቻቸው ጋር እንዴት ግንኙነት ማድረግ እንዳሰባቸው በመሠረታዊ መስፈርቶችን ማስቀመጥ እንደገናም እያንዳንዱ ወገን እነኝህን መስፈርቶች በትክክል መረዳቱን እርግጠኛ መሆን አለባቸው።

በእጮኝነት ጊዜያቸው እጮኛሞቹ በየጊዜው ስለሕይወት ፍልስፍናቸው መወያየት ጋብቻቸውን ሊመሩ በሚችሉ መሠረታዊ መርሆዎች ላይ መስማማት ያስፈልጋቸዋል። ራዕዬቻቸውን እርስ በእርስ መጨዋወት፤ ግባቸውን ለይተው ማወቅና እነዚያን ራዕዮችና ግቦቻቸውን እውን ለማድረግ የረጅም ጊዜ እቅዳቸውን ከወዲሁ ሊተልሙ የግድ ነው። በገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፤ በምዕዋለንዋይ ፍለት፤ በገንዘብ ቁጣባና በዕለት ተዕለት ወጭ ጉዳዮች ላይ የጋራ የሆነ መግባባት ላይ ሊደርሱ ይገባቸዋል።

በዚህ የእቅድ ጊዜያቸው ውስጥ ተገቢዎቹ የሚያደርጉት ማንኛውም ድርጊት ራሳቸውንና ትዳራቸውን በመጠበቅ አላማ ላይ የተመሠረተ ነው።

የሁለቱም ተጋቢዎቹ ቤተሶቦች፤ የሚመሠረተው አዲስ ትዳር እንደሆነ፤ የተሰየ ቤተሰብ እንደሆነ፤ ተጋቢዎቹ እርስ በእርስ የተገናኙበት መንገድ ከወጡበት ቤተሰብ በአንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮች ሊለይ እንደሚችል መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው። እስኪ ተመሣሣይ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ሁለት ያህል ታሪኮችን በመመልከት ፈጥነው እርምት ካልተወሰደባቸው በቀር በብዙዎች ላይ ችግር ሊያደርሱ ስለሚችሉ የተለመዱ ጉዳዮች እንመለከት።

አንድ ወጣት (ስሙን ዩሐንስ እንበለው) ጋብቻውን ከመፈጸሙ በፊት ጥሩ ስራ ስለነበረው የወላጆቹን ወርሃዊ ተከፋይ ዕዳዎችና ልዩ ልዩ ወጭዎች በመሸፈን ይረዳቸው ነበር። እንደነዚህ

አይነት ወጭዎችን መሸፈኑ፤ በተለይም አብሯቸው እየኖረ እስከሆነ ድረስ የተሰየ እንግዳ ነገር አይደለም። ወላጆቹ ወጫቸውን ለመሸፈን የሚተማመኑት የእርሱን የገንዘብ ድጋፍ ከሆነ፤ ትዳር በሚመሠርትበት ጊዜ ችግር ውስጥ መግባታቸው አይቀሬ ነው። ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? ልጆቸው ከዚያ በኋላ ሊረዳቸው ባይችል የኑሮን ጣጣ እንዴት ሊወጡት ይችላሉ?

ጋብቻውን ከፈጸመ ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ዮሐንስ ከእናቱ የስልክ መልዕክት ደረሰው። "ዮሐንስ" አሉ እናቱ፤ "ችግር በደረሰብን ጊዜ ሁሉ መቼም የምትረዳን አንተው ነህ . . . አሁን ደግሞ የመብራት ሂሳብ ወሩ ደርሶ ተጠይቀናል . . . እና ደግሞ ጥቂት የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመን ልትረዳን ትችላለህ?" በዚህ ጉዳይ ላይ ዮሐንስ ሦስት አማራጮች አሉት። "አልችልም" ሊል ወይም "እችላለሁ" ሊል አለበለዚያም "እስኪ ከሣራ ጋር (ሚስቱ ነች) ልነጋገርበትና . . . ከበጀታችን ጋር ሊጣጣም የሚችል መሆኑን እንይ" ሊል ይችላል።

ዩሐንስ ከእናቱ ጋር ላለው ግንኙነት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ከሆነ፤ ምናልባትም በቀጥታ አልችልም ብሎ መልስ አይሰጥም። በትዳሩ ውስጥ ላለው ሰላምና መግባባት ቦታ የሚሰጥ ከሆነም ወዲያውኑ አዎ የሚል መልስ አይሰጥም። አስተዋይ ሰው ከሆነ እንዲህ አይነቱን ገንዘብን በሚመለከት ጉዳይ ላይ የመጨረሻውን ውሣኔ ለመስጠት የእናቱን ጥያቄ ከሣራ ጋር ይወያይበታል። ዮሐንስና ሣራ የገንዘብ እቅዳቸውን ያወጡት አብረው ከሆነ፤ ወርሃዊ በጀታቸውንም የበጀቱት በአንድነት ከሆነ፤ በእቅዳቸው ላይ የሚከሰተውን ማንኛውንም ሰውጥ አብረው ሊወስኑ ይገባቸዋል። በመጀመሪያ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ የራሳቸው ቤት ጥንካሬና የእነርሱ ጉዳይ መረጋጋት ነው። በጀታቸው የእናቱን የመብራት ወጭ ለመሸፈን የሚያስች ከሆነና ወጭውንም ለመሸፈን ሁለቱም ከተስማሙ መልካም ነው። አሁን እርዳታው የሚገኘው ከሁለቱም እንጂ "ከእማማ ትንሹ ልጅ" አይደለም። በጀታቸው የማይፈቅድላቸው ከሆነ ግን በጣም በትህትና ነገር ግን በግልጽ "አዝናለሁ በዚህ ጊዜ ልረዳሽ አልችልም" ብሎ መልስ ሊሰጥ ያስፈልጋል።

ዮሐንስና ሣራ በተጋቡ ጊዜ ቅድሚያውን የተሰጣቱት አንዳቸው ለአንዳቸው ነው። እንዲህ አይነቱን መረዳት እርስ

በአርሳቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር አስቀድመው ግልጽ አድርገው ከሆነ ብዙ የልብ ሀዘንንና ስብራትን ሊያስወግዱ ይችላሉ::

ሌላው አዲስ ጎጆ ውጭዎችን አልፎ አልፎ የሚያጋጥማቸው የተለመደ ችግር፤ ወላጆች ወይም ሌላ የቤተሰብ አባላት፣ ሣይጋበዙ በአንግድነት መጥተው በቤት ውስጥ እንደቤታቸው ማድረጋቸው ወይም ያልተጠየቁትን አስተያየትና ምክር መስጠታቸው ነው:: አንዳንድ ጊዜ ባለትዳሮች ብቻቸውን መሆን ይፈልጋሉ፤ በዚህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ ይህንን ፀጥታ ቀጠሮ የሌላቸው የቤተሰብ አንግዶች ሊሠብሩት አያስፈልግም:: የዮሐንስ እናትና እህት ያለቀጠሮ ድንገት መጡ ብለን እናስብ:: እህቱ ፈጥና ወደ ማቀዝቀዣው በመሄድ ሳይበሉ የተረፉ ምግቦችን ወስዳ መመገብ ጀመረች:: እናቱ ደግሞ በወለሉ ላይ አንድ ምንጣፍ አዮና "ይህንን ምንጣፍ አልወደድኩትም ሌላ የሚያስፈልግህ ይመስለኛል" አሉ:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዮሐንስ በሁለት ሃሣቦች ግራ ይጋባል:: እህቱንም ይሁን እናቱን ሊያሣዝናቸው አይፈልግም፤ ይሁንና ሣራ በአንድ ጥግ በንዴት ትኩላት ግላ ቆማለች:: የዮሐንስ እህት ሣታላውቅ ወደ ቤቷ ከመግባቷ አልፎ ሳታስፈቅድ ማቀዝቀዣውን እያራቆተች ነበር:: ከዚህ የከፋው ደግሞ የዮሐንስ እናት፣ ሣራ ራሷ ገዝታ ያመጣችውን ምንጣፍ በማንቋሸሽ ሣራንና ምርጫዋን እየወቀሱ ነበር:: ታላቅ ፍንዳታ ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ እየተጠነሰሰ ነው::

ሁኔታው የዮሐንስ እናትና እህት በቤቱ ውስጥ ባሉበት ጊዜ ላይፈነዳ ይችል ይሆናል፤ ፍንዳታው የሚጀምረው እነርሱ ከሄዱ በኋላ ነው:: ሣራ ስለሁኔታው ማማረር ከጀመረችና ዮሐንስ መከላከል ከጀመረ ነገሩ እየከረረ ይሄዳል:: እየወቀሰች ያላችው እኮ ምንም ቢሆን ቤተሰቦቹን ነው:: ዮሐንስ ችግሩን ከቤተሰቦቹ ጋር ፈጥኖ ካልተነጋገረ፤ የሣራ ቁጣ እየገረረ ይሄድና በሚቀጥለው ጊዜ እናቱንና እህቱን ከቤቷ እንዲወጡላት ስትናገራቸው፤ ያነየ በሣራና በዮሐንስ ቤተሰቦች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ መርዝ ይቀላቀልበታል::

በዚህ አይነቱ አለመግባባት ውስጥ እጅግ አስከፊው ነገር፤ ተጋቢዎቹ የየራሳቸውን ቤተሰቦች ደግፈው ውዝግብ ውስጥ መግባታቸው ነው:: ትክክለኛው ነገር ዮሐንስ ወደ እናቱና ወደ እህቱ ዘንድ ሄዶ "ያለቀጠሮ ወደ ቤት መምጣትሽን አልደግፈውም አማማ፤ ደግሞ ለለ ምንጣፉ ላንጠይቅሽ የሰጠሽው አስተያየት

የሣራን ስሜት ጎድቶታል:: እህቴ ሆይ እንደገና ወደቤታችን ስትመጭ በምግባችን ራስሽን የማስተናገድ መብት የለሽም" ብሎ ሊናገራቸው ይገባል::

ለጊዜው ሊቆጡና ሊያኮረፉ ይችላሉ፤ ይሁንና አሁን ዮሐንስ የራሱ ቤተሰብ አለው:: በጉዳዮ ላይ እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር በመደራደሩ፤ ሣራን እየጠበቃት በመሆኑ የቁጣቸውና የኩርፊያቸው ኢላማ ከመሆን ያድናታል::

እነዚህ የተለመዱ ከሆኑ በተጋቢዎችና በቤተሰቦቻቸው ባለ ግንኙነቶች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች ሁለቱ ብቻ ይሁኑ እንጂ መርሁ ግን ግልጽ ነው::

የባልየው ቀዳሚ ጉዳይ ሚስቱ፤ የሚስቱም ቀደምት ጉዳይ ባልዋ ነው:: ሁለቱም በጋራ ሆነው እርስ በእርስ መጠባበቅ፣ ጋብቻቸውን ማጠናከር፣ ባልንጀርነታቸውን መንከባከብ ይጠበቅባቸዋል:: ባለትዳሮች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያለተሣሠራቸውን ገመድ መበጠስ ሁልጊዜም ቀላል ነገር አይደለም፤ ይሁን እንጂ፤ አስቀድሞ የግንኙነት መስፈርቶችን ማስቀመጥ የትስስሩን ገመድ ለማላላት ለሁለም ወገን ሂደቱን ቀላል ለማድረግ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ፤ ለአዲሱ ትዳር ለስኬት አስፈላጊ ከሆኑት ጠቃሚ ነገሮች አንዱን በጎ ጎን ይጨምሩለታል::

መርሆዎች

1. የባልና የሚስት ግንኙነት የመጀመሪያው ለብአዊ ግንኙነት ነው።

2. የባልና የሚስት ግንኙነት፤ መሠረት የሆነና ለሌሎች ግንኙነቶች ሁሉ ቁልፍ የሆነ ጉዳይ ነው።

3. የወላጆችን ቤት ለቆ መውጣት የጋብቻ መሠረታዊ መርህ ነው።

4. ባልንጀርነት ለስኬታማ ትዳሮች ሁሉ መሠረታዊ ነገር ነው።

5. በጋብቻ ውስጥ ያለ ባልንጀርነት በደምና በውልደት ከተገኙ ሁኔታዎች ሁሉ በላይ ነው።

6. ጤነኞችና ራሳቸውን ለማስተዳደር ብቃት ያላቸው ወላጆች የልጆቻቸው ሸክም መሆን አይገባቸውም። በሴላ በኩል ልጆች ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ወላጆቻቸውን ሁለንተናዊ ደህንነት የመንከባከብ ሃላፊነት አለባቸው።

7. ገና ከመጀመሪያው፤ ባለትዳሮቹ ቤተሰቦቻቸው ከእነርሱ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ግልጽ የሆኑ መስፈርቶችን ማስቀመጥ አለባቸው።

8. የባልየው ቀዳሚ ጉዳይ ሚስቱ፤ የሚስቱም ቀዳሚ ጉዳይ ባልዋ ነው። ሁለቱም በጋራ ሆነው እርስ በእርስ መጠባበቅ፤ ጋብቻቸውን ማጠናከር፤ ባልንጀርነታቸውን መንከባከብ ይጠበቅባቸዋል።

ምዕራፍ ሰባት

ስብዕነታችን ምስጋና ይግባው!

ይህን እውነት እንጋፈጠው፤ ወንዶችና ሴቶች ልዮነት አላቸው። በዚህ ጥርጥር የለም። ምንም እንኳን ግልጽ የሆነው አካላዊ ልዩነት ሙሉ በሙሉ የታወቀው ገና ከመጀመሪያው ቢሆንም፤ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው መሠረታዊ የሆነ ስነልቡናዊና ስሜታዊ ልዩነት ሳይንሣዊ በሆነ መንገድ የተለየውና የተረጋገጠው ባለፈው ትውልድ ዘመን ነው።

የሰው ዘር የሆኑት ወንዶችና ሴቶች አፈጣጠር ልዩነት አለው። በአንድ በተወሰነ ተመሣሣይ ሁኔታ ላይ በማሰብ፤ በመናገርና በድርጊት የሚሰጡት ምላሽ የተለያየ ነው። ወንዶችና ሴቶች መረጃን የሚልኩበት፤ የሚቀበሉበት፤ ሂደቱን የሚያቀላጥፉበት መንገድ ይለያያል። አለምን የሚመለከቱበት አይምሯዊና ስሜታዊ መነጽር የተለያየ በመሆኑ፤ ወንዶችና ሴቶች አንድን ነገር የሚመለከቱት ሙሉ ለሙሉ በተለያየ አቅጣጫ ነው። አንድ ተመሣሣይ መረጃ ሊሰጣቸው ይችላል፤ ነገር ግን በዚያው ጉዳይ ላይ ፍጹም የማይመሳሰል ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። አንድ የተወሰነ መረጃን እየገመገመ ያንን መረጃ የሚተረጉመበት ልዩነት "ን የምድር ሁለት ጫፎችን ያህል ልዩነት ይኖረዋል።

ወንዶችና ሴቶች የሚያስቡበትና ነገሮችን ተግባራዊ በሚያደርጉበት መንገድ መካከል ያለው ይህ መሠረታዊ ልዩነት፤ በዘመናት መካከል በነዚህ ጸታዎች መካከል ለተፈጠሩት ግጭቶች፤ መመሰቃቀሎችና አለመግባባቶች ዋነኛው ምንጭ መሆኑን መናገር ጠቃሚ ላይሆን ይችላል። በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የመግባባት ችግር የተለመደ ነገር ነው። እንዲህ አይነቱ ንግግር የተለመደ ይሆን? "ፈጽም ልረዳው (ልረዳት) አልቻልኩም . . . መቼም መች ይሁን መነጋገር ስንጀምር ልክ ሁለት የሬዲዮ ጣቢያዎችን የከፈትን አይነት ነው የሚሆነው"።

እንደሌሎች ማናቸውም ነገሮች ሁሉ፤ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት የሚፈጠረውን ምስቅልቅል ሊያርቅ የሚችለው እውቀት ነው። በማንኛውም ደረጃ ያለውን በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን መግባባትና ግንኙነት ለማሻሻል፤ ወንዶችና ሴቶች ልዩነት እንዳላቸው መረዳቱ ብቻ በቂ አይደለም፤ ይልቁንም ልዩነታቸው እንዴት እንደሆነ ማወቅ ወሣኝ

ጉዳይ ነው። ይህ እውቀት በተሰይ ደግሞ ትዳራቸው በከፍተኛ ደረጃ የስኬትና የደስታ አድል ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ስሚፈልጉ ወጣት ባለትዳሮች እጅግ ጠቃሚ ነው።

በመጀመሪያው፤ እግዚአብሔር ሰውን እንደ መንፈስ አድርጎ በመፍጠር ይህንን መንፈስ በሁለት ሰጋና ደም ቤቶች ውስጥ አኖረው - ወንድና ሴት። ይህ የወንድና የሴት ቤቶች ውህደት እግዚአብሔር ያፀደቀው አዳዲስ ቤቶች የመሥራት ብቸኛው መንገድ ነው። የወንዶችና የሴቶች ቤቶች መሠረታዊ አላማ አዳዲስ ቤቶችን መመሰረት ነው።

መንፈስ ጸታ የለውም። ወንዶችም ይሆኑ ሴቶች ሁሉም የህያው ፍጥረት አባላት አንድ መንፈስና ተመሣሣይ መገኛ ነው ያላቸው። ይሁንና እንደ እግዚአብሔር አቅድ ወንዶችና ሴቶች ስነ አካላዊና ስነ ልቡናዊ ልዩነቶች አሏቸው። የተለያየ ተግባር ያላቸው በመሆኑም እግዚአብሔር የወንዱን ቤትና የሴቷን ቤት የፈጠረው የተለያየ አድርጎ ነው።



የወንዱ ስፊት ስምክንያታዊ ስስተሳሰብ የሴቷ ስፊት ደግሞ ስሜታዊ ስሆኑ ምሳሾች ነው።

ወንዶችና ሴቶች በተለያየ መንገድ እንዲያስቡና ባህሪያቸውም የተለያየ እንዲሆን ያደረጋቸው የተለያዩ ኬሚካሎችና ሆርሞኖች ሚዛን በተለያየ መጠን ስላሏቸው ነው። እግዚአብሔር ወንዱን የቤተሰቡ ራስ እንዲሆን ከመጀመሪያው ያሰበ በመሆኑ ምክንያት፤ ለምክንያታዊ አስተሳሰብ ጠቃሚ የሆኑ ኬሚካሎችንና ሆርሞኖች ሰጠው። የወንዱ ሰሪት ለምክንያታዊ አስተሳሰብ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሴቷ ስሪት ስሜታዊ ስሆኑ ምላሾች ነው። የአካሏ ኬሚካላዊና ሆርሞናዊ ሚዛን ተግባሯን የምታከናውነው ስሜታዊ መሠረት ካለው ማዕከል እንዲሆን አድርጓታል። ሁለቱም ጸታዎች ሁለቱንም የወንድና የሴት ሆርሞኖች የያዙ በመሆኑ ምክንያት "ምክንታዊያን" ወንዶች "ስሜታዊ" ጎን ያላቸው ሲሆን "ስሜታዊያን" ሴቶችም "ምክንያታዊ" ጎን አላቸው። በአጠቃላይ፤ ወንዶችና ሴቶች አለምን የሚመለከቱት እንደሰሪታቸው ሲሆን፤ ይህም ወንዶች ከምክንያታዊነት ማዕከል ሴቶች ደግሞ ከስሜታዊነት ማዕከል እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል።

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉ ስምንቱ ስምንት መሠረታዊ ልዮነቶች

ብዙ ባልና ሚስቶች አንዳቸው ከሌላቸው የሚለያቸውን መሠረታዊ የሆኑ ልዩነታቸውን ባለማወቃቸው ምክንያት፤ አላስፈላጊ በሆኑ ምስቅልቅሎች፣ አለመግባባቶችና የውስጥ ስሜቶች ይቸገራሉ። በተለይ ጋብቻን አለመልክቶ እርስ በእርስ ባለ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸውን አሥራ እምስት ያህል በወንዶችና በሴቶች መካከል ያሉ የተወሰኑ ልዩነቶችን እንመልከት። እነዚህ አሥራ አምስት መግለጫዎች ሁሉንም ወንዶችንና ሴቶችን በጅምላው በአንደኛው ወይም በሌላኛው ጎራ እንዲፈርጁ የታቀዱ አይደሉም። ሁልጊዜም በየትኛውም ሁኔታ የተሰዩ ሰዎችና ሁኔታዎች በመኖራቸው እነዚህ መግለጫዎች በጥቅሉ እውነት የሚሆኑት እንደ ስነልቡናዊና ስሜታዊ ግብአታቸው ለአብዛኞቹ ወንዶችና ሴቶች ነው።

1. ወንድ ምክንያታዊነትን መሠረት እድረጎ ያስባል፤ ሴቶች ግን ፍልቅ ስሜታውያን ናቸው።

ምክንያታዊነት ማለት ምክያቶች ላይ የተመሠረተ፣ በአግባቡ የተደራጀና ሥርዓትን በተከተለ መንገድ ማሰብ ማለት ነው። ምክንያታዊነትን መሠረት አድርጎ የሚያስብ ሰው አይምሮ ሚሠራው፣ ልክ እንደ ኮምፒዮተር መረጃዎችን በመገምገምና በማገናዘብ ሂደቶቹንም በማቀላጠፍ ሲሆን፤ ትክክለኛና መጭ ሁኔታዎችንም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው። አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ከሆነ፣ ሁለት ግማሽ ቁራጮች ደግሞ ሁለት አንዶች ይሆናሉ፤ ይህ ምክንያታዊነት ነው። በጥቅሉ ወንዶች የሚያስቡት እንዲህ ነው። እውነታዎችን ይመለከታሉ በዚያው መሠረትም ይተገብራሉ።

ሴቶች ፍልቅ ስሜታውያን ናቸው። ነገሮችን የሚመለከቱት ብዙውን ጊዜ ከምክንያታዊነት አንፃር ሳይሆን ከስሜታቸው አንፃር ነው። ይህ መጥፎ ነገር አይደለም። ልዩነት አላቸው ማለት እንጂ ከፍልቅ ስሜት ማዕከል ነገሮችን መመልከት ከምክያታዊነት ማዕከል ነገሮችን ከመመልከት የከፋም የተሻለም አይደለም። በሌላ መንገድ ጉዳዮን ማየት ቢያስፈልግ ወንድ በአይምሮው ይመራል ሴት ደግሞ በልቧ ትመራለች እንደ ማለት ነው።

ላይ ላዮን ስንመለከት ምክንያታዊነትና ፍልቅ ስሜታዊነት እርስ በእርስ የሚቃረኑ ቢመስልም እውነታው ግን እርስ በእርስ በጣም ተደጋጋፊዎች መሆናቸው ነው። ሰው ሁሉ ምክንያታዊ ቢሆን ይህች ዓለም ምን ልትመስል ትችል ነበር? ያለመንፈስ፣ ያለጠንካራ ስሜት፣ ያለ እሣትና ያለ ምንም ወይም ጥቂት ስነጥበብ ሕይወት ባዶ ትሆን ነበር። በዚሁ አንጻር ፍልቅ ስሜት ያለ ምክንያታዊነት ባግባቡ ያልተደራጀን ሥርዓት የሌለው ሕይወት ያስከትል ነበር። ምክንያታዊነትና ፍልቅ ስሜታዊነት ሁለቱም ለእርካታም ብቻ ሳይሆን በህይወት ለመቆየትም ጭምር አስፈላጊዎች ናቸው። ይህ የሚገልጽልን የእግዚአብሔርን ድንቀኛና ጥልቅ ጥበብ ነው።



ወንድ በስዬምርው ደመፌሰ ሴት ደግሞ በሰባ ትመፌሰች።

እስኪ አንድ ምሳሌ እንውሰድ። ዮሐንስና ሣራ በሣሎን ውስጥ ናቸው። ዮሐንስ የሶፋው መቀመጫ አየር ማቀዝቀዣውን በቀላሉ መጠቀም እንዳይቻል ማገዱን አስተዋለና "ይህ ወንበር መንገድ ዘግቷል ልናስወጣው ያስፈልጋል" አለ። እያለበ ያለው በምክያታዊነት ነው። በዚሁ ሰዓት ሣራ ደግሞ ይሄው የሶፋ ወንበር አጠገቡ ካለው ትልቁ ሶፋ፣ ከመጋረጃው፣ ከአበባ ማስቀመጫውና አጠገቡ ካለው ጠረጴዛ ጋር ያለውን ህብርና ህብሩም የፈጠረውን ውበት ታስብ ነበር። እያለበች ያለችው በፍልቅ ስሜቷ ነው። የአንዳቸው አመለካከት ከሌላኛው ይልቅ ትክክለኛ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መልካም ወይም መጥፎ አይደለም። ያላቸው ልዩነት ብቻ ነው። ዮሐንስና ሣራ አንድ ሁኔታ በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንደሚመለከቱ ከተረዱ የጋራ ወደሆነ ድምዳሜ ይደርሳሉ።

በጥቅሉ ወንዶች ምክንያታዊያን ሴቶች ደግሞ ፍልቅ ስሜታውያን ናቸው።

2. የሚናገሩት ቋንቋ፣ ለሴቶች የውስጥ ስሜታቸውን ለወንዶች ደግሞ በውስጣቸው የሚያስቡትን የሚገልጽ ነው።

ሴት በልቧ ውስጥ ያለውን የምትናገር ሲሆን ወንድ የሚናገረው ደግሞ በአይምሮው ውስጥ ያሰውን ነው። ይህ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን የፍልቅ ስሜታዊነትና የምክንያታዊነትን ልዩነትና ህብር የሚገልጽ ነው። ሴቶች ፍልቅ ስሜታዊያን በመሆናቸው የሚናገሩትን ነገር በዚህ ረገድ ልንረዳላቸው ያስፈልጋል። ወንዶች ምክንያታውያን በመሆናቸው ብዙ ጊዜ ቃላቸው እውነተኛ

ስሜታቸውን የሚገልጽ አይደለም። ሁለቱም ተመሣሣይ ሃሣብና ስሜት ሊኖራቸው ይችላል፣ ይሁንና ይህንኑ የሚገልጹት በተለያየ መንገድ ነው። ይህንን ልዮነት ካልተረዱት፣ ባለትዳሮች የመግባባት ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል።



ሴት በልቧ ውስጥ ያለውን የምትናገር ሲሆን ወንድ የሚናገረው ደግሞ በስዬምርው ውስጥ ያሰውን ነው።

እስኪ እንዲህ ሆነ ብለን እናስብ፣ ዮሐንስ ሣራን ከስራ መልስ በ11:00 ከቤት በመኪና ወደ አንድ ቦታ ሊወስዳት ቃል ገባ። ይሁንና ዮሐንስ ዘገየ፣ መዘግየቱ ደግሞ ሣራን አሰቀጣት። ሣራ በቤት ውስጥ ወዲያና ወዲህ ትንጎራደዳለች፣ አልቧታል፣ ቁጣዋ ገንፍሏል፣ ዮሐንስ ወደቤት ሲደርስና ገና ስታየው የምትለውን ነገር በሃሳቧ ታውጠነጥናለች።

በመጨረሻው ዮሐንስ በ12:00 ገደማ ቤት ደረሰ። ይቅርታ የሚጠይቅ ፈገግታውን እያሣየ፣ "በመዘግየቴ በጣም አዝናለሁ" አላት። ደግሞ እውነቱን ነበር፣ በመዘግየቱ አዝኗል። የነገራት ኢያሰበ ያለውን ነው። ምናልባት ምን ያህል እንዳዘነ ለማሣየት ተቸግሮ ይሆናል። ይሁንና ቢያንስ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት አስቧል። የዮሐንስን ንግግር ቸል በማለት ወደ መኪናው ገብታ በሩን በሀይል ዘጋችና ከእርሱ መራቅ የምትችለውን ርቀት ያህል ርቃ ተቀመጠች። ዮሐንስ መኪናውን አንቀሳቅሶ መሄድ ሲጀምር አንዳች ነገር አልተነፈሰችም።

ከብዙ የዝምታ ደቂቃዎች በኋላ ዮሐንስ "ችግሩ ምንድነው?" ሲል ጠየቃት። እንደእርሱ እንደርሱ ነገሩ ሁሉ ገና ድሮ አልቋል። በእርግጥ ዘግይቷል፣ ለመዘግየቱም ይቅርታ ጠይቋል-በቃ። ማንም ሰው ከአለታት አንድ ቀን የመዘግየት መብት አለው። ያ ደግሞ የእርሱ ምክንያታዊነት አስተሳሰብ ነው።

"ችግር የለም" ሣራ ነገሩን በአጭሩ ቆረጠችው።

እንደገና ብዙ የዝምታ ደቂቃዎች አለፉ። ዮሐንስ እንደገና ሞከረ "ለምን ለእራት አንወጣም፣ በጣም ድንቅ የሆነ ሥፍራ እወስድሻለሁ" አላት። "መሄድ አልፈለኩም" በአንድ አበባ መሸጫ መደብር በር ላይ መኪናውን አቆመና ሌላ መከራ ደግሞ አደረገ፣ "ወደ ውስጥ ዘልቄ ጥቂት አበባዎች መግዛት እፈልጋለሁ"። "ለምን? ያን ያህል የምትወደኝ ከሆነ፣ እመጣለሁ ባልከኝ በ11:00

መድረስ ነበረብህ" ሣራ ምን ያህል እንደተሰማት በዚሁ ሁሉ ውስጥ ዮሐንስ አብልጦ መስማት የሚገባው ሣራ እንዴት እንደተሰማት እንጂ ምን እንደምትናገር መሆን አልነበረበትም። አንዳንድ ጊዜ ሰው ስሜቱን ወይም ስሜቷን ለመግለጽ በተፈለገ ጊዜ ቃላት ፈጥነው አይወጡም። ምክንያታዊው ዮሐንስ ፍልቅ ስሜታዊዋን ሣራን ሊገነዘባት ያስፈልገዋል። በዚሁ ረገድ ሣራ ደግሞ ዮሐንስ በአይምሮው ውስጥ ያለውን እንደነገራት ልትገነዘብ ይገባል። ሁለቱም ቢሆኑ ከሚነገሩ ቃላት አድማስ ባሻገር ሊግባቡ ሃላፊነትና በዚህ አንፃር አንዳቸው አንዳቸውን ሊያገለግሉ ሃላፊነት አለባቸው።

3. ሴት የምትሰማው ቋንቋ ከፍልቅ ስሜት ልምምዷ ጋር የሚያያዝ ነው። ወንድ በሚሰማው ቋንቋ የሚቀበለው መረጃን ነው።

ሴት በምትናገርበት ጊዜ እያደረገች ያላችው ምናልባት ስሜቷን እየገለጸች ነው። ወንዱ ደግሞ ብዙ ጊዜ ይህን ንግግር የሚቀበለው ግላዊ ባልሆነ መልኩ እንደ መረጃ ነው። ወንዱ በሚናገርበት ጊዜ ምንም እንኳን በቀላሉ በአይምሮው ውስጥ ያለውን ቢናገርም፤ ሴቷ ብዙውን ጊዜ ቃሉን የምትቀበለው ጥልቅ በሆነ ግላዊና ፍልቅ ስሜታዊ ደረጃ ነው። በዚህ ምክንያት ግጭቶች እንዴት እየከረሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ዮሐንስ እራት ሊጋብዛት እያወጣት ነበር። ነገር ግን "መሄድ አልፈልግም" አለች። ዮሐንስ ይህን የተቀበለው እንደ መረጃ ነበር። ጥሩ ነው፤ ልትሄድ አልፈለገችም ችግሩ ያለው ሣራ የምትናገረው የምታስበውን ሳይሆን የሚሰማትን ነው። "ባንተ በጣም ተናድጃለሁ። አንድ ሰዐት ሙሉ ጎልተኸኝ ስታበቃ፤ አሁን ደግሞ ምንም ያልተፈጠረ ያህል ራት ልጋብዝህ? አልዘገየህም ጌታው?"

መስማት ማለት አንድን ነገር መረዳት ማለት አይደለም። አንዱ ሰው የተናገረው ሌላው ሰው የሰማው ነው ማለትም ላይሆን ይችላል።

ዮሐንስ የሚነገረውን ቃል የሚሰማው እንደመረጃ ስለሆነ፤ የሣራን ጥልቅ የሆነ ፍልቅ ስሜታዊነት ሙሉ ለሙሉ አልተረዳላትም። እርሷ ደግሞ በሌላው በኩል የእርሱን ቃላት የምትተረጉማቸው ቀላል፣ ሥርዓት የጎደላቸውና ተራ ቃላት አድርጋ ነው። ሁለቱም በቅንነት ለመግባባት ሞክረዋል፣ ይሁንና

አልተገናኙም። ምክንያቱም አንዳቸው የአንዳቸውን ነገሮች የሚመለከቱበት ማዕከል አልተረዱም።

መስማት ማለት አንድን ነገር መረዳት ማለት አይደለም። አንዱ ሰው የተናገረው ሌላው ሰው የሰማው ነው ማለት ላይሆን ይችላል፤ ለዚህ ነው ግንኙነት ስነ ጥበብ የሚሆነው። ባሎች፤ የሚናገሯቸውን እያንዳንዱን ቃላት የሚሰሙት በፍልቅ ስሜት የሚመሩት ሚስቶቻቸው መሆናቸውን ሊያስተውሉ ይገባል። ሚስቶች ደግሞ የሚናገሯቸውን ማናቸውንም ቃላት ባሎቻቸው የሚቀበሉት እንደ መረጃ መሆኑን ሊያስታውሱ ያስፈልጋል። እርስ በእርስ በተሻለ ሁኔታ ለመግባባት፤ ባሎችም ሆኑ ሚስቶች ሌላኛው ወገን ቃላቸውን የሚቀበልበትንና የሚተረጉምበትን መንገድ መማርና በዚያው ረገድ መናገር ተገቢ ነው።

4. ሴቶች ነገርን ሁሉ ከግላዊ ነገራቸው ጋር የማያያዝ አዝማሚያ አላቸው፤ ወንዶች ሁሉን ነገር ግልጥ የማድረግ አዝማሚያ አላቸው።

ይህ ልዩነት በቀጥታ የሚያያዘው እንደ ወንዱና ሴቲቱ ስሪትነት ነው። ወንዶች ምክንያታዊ አሣቢዎች ሴቶች ደግሞ ፍልቅ ስሜታውያን ናቸው። ሴት ሁሉን ነገር የምትተረጉመው ከስሜቷ አንፃር ሲሆን ወንድ ደግሞ መረጃን የሚፈልግ ነው። ዩሐንስ ምናልባት "ሣርየ፤ ዛሬ ፀጉሽን የተሠራሽበት ፋሽን አላማረኝም" ሲል ስለ ፀጉሯ አስተያየት ሰጥቷት ይሆናል። "ዛሬ" የሚለውን ገላጭ ቢጠቀምም እየሰጠ ያለው መረጃ ነው። ሣራ ደግሞ ያንን አላዳመጠችም። የሰማችው ነገር "ፀጉርሽን የተሰራሽበት ፋሽን አላማረኝምን" የሚለውን ብቻ ነው። ዮሐንስ የሰጠውን መረጃ ሣራ የተነተነችው በፍልቅ ስሜታዊነት ነው። በመሆኑም ተቆጣች፤ ውስጧም ተጎዳ። በዚህ ምክንያት ወደ ፀጉር ሠሪዋ ስትሮጥ ሄዳ ፀጉሯን ተቆርጣው ወይም በሌላ ፋሽን ተሰርታው ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ዮሐንስ ሣራ ነገሩን ሁሉ ይህን ያህል አግንና ያየችበት ምክንያት አስገርሞታል። ምክንያቱም እርሷ ጉዳዮን የወሰደችው ግላዊ አድርጋ ነው።

ምናልባት ሣራ ዮሐንስን ይህ ያደረከው ፓንት ልክህ አይደለም፤ አያምርብህም ብላው ይሆናል። ዮሐንስም፤ "መልካም፤ ጣጣ የለውም፤ ነገ ልብሶቼን ስቀይር እቀይረዋለሁ ሲል መልሶላታል። የእርምት ቃላቶቿን የተቀበለው እንደ መረጃ በመሆኑ ልክ እንደ ኮምፒዮተር ወዲያውኑ በአይምሮው የመረጃ ማጠራቀሚያ ፋይል

ውስጥ አስቀምጦታል። ምናልባት ለሰጠችው አስተያየት ምላሽ ለመስጠት ተግባራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፤ ይሁን እንጂ ነገሩን የወሰደው ግላዊ በሆነ መልኩ አይደለም።

ሴቶች ነገሮችን ግላዊ አድርገው የሚመለከቱ ስለሆነ ወንዶች ስሴቶች የሚናገሩትንና እንዴት እንደሚናገሩትም በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚባ ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል። ሴቶች ስሜትን የሚጎዱ ድርጊቶችንና ያለ ጥንቃቄ የሚሰነዘሩ አስተያየቶችን ሰረዥም ጊዜ ሊያስታውሷቸው ይችላሉ። በሌላው ረገድ ወንዶች ነገሮችን የሚወስዱት ግላዊ አድርገው ባለመሆኑ፤ ሴቶች በተናገሩት ነገር ላይ ወንዶች የሚሰጡትን ምላሽ በሚተነትኑበት ጊዜ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ያስፈልጋል። እንደ ሴቶች ሁሉ ወንዶች ከፍልቅ ስሜታዊ ማዕከል በመነጨ መንገድ በሁኔታዎች ላይ ምላሽ አለመስጠታቸው፤ ስሜት የላቸውም ወይም ለነገሩ ግድ አልሰጣቸውም ማለት አይደለም። ወንዱ መረጃን እየፈለገና ምላሽ ለመስጠት ትክክለኛ የሆነውን መንገድ እየመረጠ ነው።

5. ሴቶች "በዝርዝር ጉዳዮች ላይ" ፍላጎት አላቸው። ወንዶች "ዋነኛ" በሆኑ ጥልቅ ጉዳዮችና ፍልስፍናዎች ላይ ፍላጎት አላቸው።

ሣራ ዮሐንስን እንዲህ ስትል ጠየቀችው፤ "ዛሬ ቀኑ እንዴት ነበር?" ዮሐንስም "ጥሩ ነበር" ሲል መሰሰ። ይህ ግን ሣራ የጠበቀችው መልስ አልነበረም። መስማት የፈለገችው ዮሐንስ ባሳለፋት በዚያች ቀን ደረጃ በደረጃ፤ ደቂቃ በደቂቃ ስላከናወነው ነገር ዝርዝር ማብራሪያ ነበር። ነገሩን በአንክሮ መመልከት አላስፈለጋትም፤ በታ የምታስበው እንዲሁ ነው። የዮሐንስ ቀላል ምላሽ የሚያንጸባርቀው እርሱ የሚያስብበትን መንገድ ነው። "ጥሩ ቀን ነበረኝ፤ እጅግ መልካም ነው። እስኪ አሁን ወደ ሌላው ጉዳያችን እንሂድ" እርሱ ያተኮረው አንኳር በሆነው ዋነኛ ጉዳይ ላይ ማለትም፤ ጥሩ ቀን እንዳሳለፉ እንጂ በጥቃቅኑ ጉዳይ ሁሉ ይህን ሠራህ ከዚያ ያንን ቀጠልክ የሚል አልነበረም።

ዮሐንስ ሊሉኝ ባልና ሚስትን ለእራት ጋበዘ እንበል። የእርሱ ትኩረት ያረፈበት አንኳር ጉዳይ እነዚህን ጓደኞቹን በመልካም እንግዳ አቀባበል ማስተናገድ ላይ ነው። ለሣራ በነገረበት በዚያው ቅጽበት እርሷ ደግሞ ሁሉንም ዝርዝር ነገሮች ተመለከተች። እራት የምናቀርብባቸው ሳህኖች የትኞቹ ናቸው? ምን አይነት ምግቦች መቅረብ አለባቸው? ጠረጴዛዎቹ እንዴት መዘጋጀት አለባቸው? ይሄ

በሳሎን ውስጥ ያለው ደረጀ ምንጣፍስ እንዴት ሊሆን ነው? የሶፋ ጨርቆቹም ቆሽሸዋል ልናጸዳቸው እንችል ይሆን? ያስ በግድግዳው ላይ ያለው ቆሻሻ?

ዮሐንስ ያሰበው ጓደኞቹን በማስተናገድ በዚያ ምሽት ስለሚኖራቸው የጨዋታ ጊዜ ብቻ ነው። ስለቆሸሸት የሶፋ ልብሶች፤ በግድግዳው ላይ ስላለው ቆሻሻ፤ ስላረጀው ምንጣፍ ወይም ስሰሚቀርቡት ሳህኖች አልተጨነቀም። ለእርሱ አንኳር ጉዳይ የሆነው ለሣራ የጥቃቅን ጉዳዮች ዝርዝር ሊሆን ይችላል።

መሪዎች አንኳር የሆኑ ጉዳዮችን እንጂ ዝርዝር የሆኑ ጥቃቅን ነገሮችን መመልከት አያስፈልጋቸውም። የስራ መሪዎችና የካምፓኒ ፕሬዝዳንቶች በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለማተኮር ጊዜ የላቸውም። ሃላፊነታቸው አብይ ጉዳዮችን መመልከት፤ ካምፓኒው ወዴት ማምራት እንዳለበት በሚጠቀመው ፍልስፍናና በድርጅቱ ግብ ላይ ማተኮር ነው። መሪው ራዕዮንና መሪ ሃሣቦችን ያቀርባል፤ በበታቹ ያሉ ሠራተኞች ራዕዮን እውን ለማድረግ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ይሠራሉ። እግዚአብሔር ለቤት ባቀደው እቅድ መሠረት ባል አንኳር የሆነውን ራዕይና መመሪያ ያስቀምጣል። ያ ስጦታውና ሊጫወተው የሚገባ ሚና ነው። ሚስት ራዕዮ እንዴት ውጤታማ እንደሚሆን ታውቃለች - ዝርዝር ጉዳዮን ማለት ነው። ይህ አንድነት ሣያል የሆነ ቅንብር ነው።

6. **ቁሣዊ ነገሮችን በሚመለከት፤ ሴቶች ውጤቱን የመመልከት አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች እዚያ እንዴት መድረስ እንደሚቻል ዝርዝር ነገሩን ማወቅ ይፈልጋሉ።**

ሣራ እርሷና ቤተሰቦቿ ሊኖራቸው የሚገቡ ልዩ ልዩ ነገሮችን ታልማለች። አንዳንድ አዳዲስ ጌጣጌጦች፤ አዲስ ማቀዝቀዣ፤ አዲስ መኪናና አዲስ ቤት። ዮሐንስ ደግሞ ምንም እንኳን እንደሣራ ተመሣሣይ ምኞት ቢኖረውም በጥቅሉ አይመለከታቸውም፤ ምክንያቱም እርሱ ነገሮችን የሚያስበው ከምክንያታዊነት አንፃርና በትንተና ነው። የሚያተኩረውም ከምኞቶቹ ተጨባጭነት አፈፃጸም ላይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ተግዳሮቶች አኳያ ነው። እነዚህን ነገሮች እንዴት ልንፈጽም እንችላለን? ገንዘቡን ከየት እናገኛለን? በዚህ ጊዜ አዲስ ማቀዝቀዣ ለመግዛት በጀታችን ይፈቅዳል? አዲስ መኪና ለመግዛትስ ሁኔታው ይፈቅድልናል?

ይህ እንግዲህ በትዳር ውስጥ እንዴት አድርጎ ግጭቶችን እንደሚፈጥር በቀላሉ ያሣየናል። ዮሐንስ እንደ እርሷ ባለ ከፍተኛ

ገንዘብ ምኞቷን አብሮ የተካፈለ ስላልመሰላት ሣራ አዝናለች፣ ተናዳለችም። እንደ እርሷ አመለካከት ምኞታቸውን እውን ለማድረግ አንዳች ፍላጎት የሌለው በመሆኑ ወደ ተግባር ላለመግባት ገና እግሮቹን እየጎተተ ነው። በዚያው ቅጽበት ደግሞ ዮሐንስ የሣራ ጉዳይ እያስፈራው ነው፤ የገንዘቡ እውነታ ጉዳይ የገባት አልመሰለውም። "ይች ሴት ምን ነክቷታል? ገንዘብ እንደ ቅጠል ከዛፍ ላይ የሚሸመጠጥ መሰላት እንዴ?"። እንደ እውነቱ ከሆነ ዮሐንስ የሣራን ምኞት ሣይጋራ ቀርቶ አይደለም፤ ይሁንና ሃላፊነት በሚሰማው መልኩ ተግባራዊ በሆኑ እነኛን ምኞቶች እውን በሚያደርጉ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ነው።



ቁሣዊ በሆኑ ጉዳዮች ሴቶች "ምን?" ወንዶች ደግሞ "እንዴት" በሚሉ ጉዳዮች ሳይ ያተኩራሉ።

ቁሣዊ በሆኑ ጉዳዮች ሴቶች የሚያተኩሩት ውጤቱ ላይ ሲሆን፤ ወንዶች ደግሞ እዚያ ውጤት ላይ እንዴት እንደሚደረስ ዝርዝር ነገሮችን ማወቅ ይፈልጋሉ። ይህን በሌላ መንገድ ለማስቀመጥ ሴቶች "ምን?" ወንዶች ደግሞ "እንዴት?" በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ።

7. መንፈሣዊ ወይም ተጨባጭ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ወንዶች በውጤቱ ላይ ያተኩራሉ። ሴቶች ደግሞ በውጤቱ ላይ እንዴት እንደሚደረስ ማወቅ ይፈልጋሉ።

በመንፈሣዊው አለም ውስጥ፤ ወንዶች በውጤት ላይ ሲያተኩሩ ሴቶች ግን ዝርዝር ነገሮችን ማወቅ ይፈልጋሉ። አሁንም እንደገና በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት በእግዚአብሔር የታቀደ ነው። በመንፈሣዊ ነገር ባልየው የቤቱ ራስ መሆን ስለሚጠበቅበት የቤተሰቡን መንፈሣዊ እድገት አቅጣጫ፣ ግብና አላማ ማወቅ ያስፈልገዋል። የሚስት ፍላጎት ወደ መንፈሣዊ ግባቸው እንዴት እንደሚደርሱ ውስን በሆኑ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ነው። ይህ በቀጥታ ቁሣዊ በሆነው ጉዳይ ካላቸው አዝማሚያ ተቃራኒው ነው። በዚህ ጉዳይ ወንዶች "ምን?" ሴቶች ደግሞ "እንዴት?" በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ።

ዮሐንስ ለሣራ፤ እንደ ቤተሰብ ግባቸው ወደ ጌታ ማደግ እንደሆነ ነገራት። *ያ ራዕይ ነው - እንኳን ጉዳይ ሣራ እንዴት? ብላ* ስትጠይቅ፤ ዮሐንስ፤ "በየጠዋቱ ከስራ በፊት እኔና አንቺ

ከልጆቻችን ጋር እንጸልይ፤ በየምሽቱ ደግሞ የእንድ ሰዓት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይኑረን" ሲል ሃሳብ አቀረበ። ተግባራዊነቱን እስከተከታተሉት ድረስ ይህ ጥሩ እቅድና ፍሬያማ ውጤት ያለው ነው። ዮሐንስ ተግባራዊ ሲሆን ወደማይችል ጉዳይ ቢገባ ኖሮ ሣራ ፍርሃት ሊገባት ይችላል።



በመንፈሣዊ ነገሮች፤ ወንዶች "ምን?" ሴቶች ደግሞ "እንዴት?" በሚሉ ጉዳዮች ሳይ ያተኩራሉ።

መንፈሣዊ የአመራር ስፍራቸውን መቀበልና በዚህ ጉዳይ ቤታቸውንና ትዳራቸውን መምራት ያቃታቸው ወንዶች ጉዳይ ዛሬ ዛሬ ትላልቅ ከሆኑ ችግሮች አንዱ ሆኗል። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሴቶች ባሎቻቸው ይሄንን ሚና ለመጫወት ባለመፈለጋቸው ወይም ባለመቻላቸው ምክንያት በቤታቸው ያለውን የመንፈሣዊ መሪነት ቦታ ተገደው ይዘዋል። ይህ ማለት ግን ሴቶች የቤታቸውንና የትዳራቸውን መንፈሣዊ እድገት ግብ በሚመለከት ዝርዝር እቅዶችን በማውጣት መርዳት አይችሉም ማለት ሣይሆን፤ ባልየው ባለራዕይ ሆኖ አቅጣጫውን መወሰንና ግቡን ማስቀመጥ ይገባዋል ለማለት ነው።

8. የወንድ አይምሮ እንደ ፋይል ከዝና ነው። የሴቶች አይምሮ ደግሞ እንደ ኮምፒዮተር ነው።

ለአንድ ወንድ አንድን ችግር አሣየው ወይም የሆነ የሚከናወን ሥራ ስጠው፤ መረጃን ይወስዳል፣ በአይምሮው ውስጥ ፋይል ያደርጋል፣ ካዝኖውን ይዘጋል፤ በቻለ ጊዜ ተግባሩን ይከውነዋል። በዚሁ ጊዜ ውስጥ ሌሎች ተግባሮቹን በአርጋታ ያከናውናል። ሴቶች አንድን ችግር ወይም ሊሠራ ያለውን ተግባር ለይተው ያወጡና ልክ ሣያቋርጥ እንደሚሠራ ኮምፒዮተር ችግሩ እስኪቃለል ወይም ሥራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ዘና ሣይሉ ይሠራሉ።

ሣራ ወደ ዮሐንስ መጥታ እንዲህ አለች፤ "የመታጠቢያ ቤቱ ግድግዳ ቀለም መቀባት አለበት"። ዮሐንስም "መልካም ነው" ሲል መለሰና መረጃውን በአይምሮው መዝግቦ ያዘ። ይህንን ነገር አልረሣውም፤ ይልቁንም ሥራውን ለመሥራት አመቺ ጊዜ እየጠበቀ ነው። ዮሐንስን በሚመለከት ጉዳዮ አብቅቷል። ሣራ ችግሩን ለይታ በማውጣት ለዮሐንስ አሣልፋ ሰጥታለች፤ እርሱ ደግሞ መረጃውን በሂደት ውስጥ አስገብቶታል። ያከናውነዋል።

ከሁለት ቀን በኋላ "የመታጠቢያ ቤቱ ግድግዳ አሁንም ቀለም አልተቀባም" አለች ሣራ። ሥራው እስኪከናወን ድረስ በዚህ ጉዳይ ላይ አይምሮዋ አላረፈም። ዮሐንስ በሰጠችው ማስገንዘቢያ በመጠኑ አየተረበሸ፤ "አውቃለሁ፤ አልረሳሁትም፤ እሠራዋለሁ . . . ጥቂት ጊዜ ሰጭኝ"። ሚስት ባሏ ለማሰብ ከአይምሮው የፋይል ካዝና አያወጣ ለሚሠራበት አሠራር ጥንቃቄ ልትወስድ ይገባል፤ አደርገዋለሁ ያለውን ነገር እንዲያደርገው ጊዜ ልትሰጠውም ይገባል። በሌላው በኩል ባል ደግሞ የሚስቱ አይምሮ ለሚሠራበት መንገድ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤ ሁኔታዎችና ጊዜው በፈቃደ መጠን ፈጥኖ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። ይህ በሁለቱም ወገን አድሏዊነት የሌለበትን የመስጠትና የመቀበል ግንኙነትን ይጠይቃል።

9. ለሴት ቤቷ የሰብአናዋ ቀጣይ ነገር ነው። ለወንድ ሥራው የሰብአናው ቀጣይ ነገር ነው።

ለሴት ልጅ ለምን እንደሆነ ሣታውቀው በቤቷና በባሏ መደሰት በጣም ቀላል ነገር ነው። ለወንድ ደግሞ ሚስቱ እንቆቅልሽ እስኪሆንባት ድረስ በአንድ ሥራ ተጠምዶ መዋል እንግዳ ነገር አይደለም። አንድ ሴት ለአመታት ያህል አንድን ሥራ ልትሠራ ነገር ግን በሳምራሽ በሥራው ላትጠመድ ትችላለች። ለወንዱ ግን እንዲህ አይደለም። ሥራው የእርሱ አካል ይሆናል። የራሱ የሰብአናው መገለጫ አካል ይሆናል። የወንድ ሥራው የሰብአናው ቀጣይ ነገር ነው። ሴት በስራዋ ሥፍራ አያለች ከሥራዋ ተለይታ ሠዓቢን ወደ ቤቷ ማድረግ ትችላለች። ወንዶች ግን ብዙ ጊዜ በእጃቸው እንኳን ባይሆን ቢያንስ ቢያንስ በአይምሯቸው ሥራቸውን ወደ ቤት ይዘውት ያመጣሉ።

ለዮሐንስ ሥራው የወንድነቱ ምልክት፣ ጠቃሚ ሰው መሆኑን የሚያውቅበትና ሣራና ልጆቹ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማቅረብ መቻሉን የሚያረጋግጥበት ነው።

ሣራ ያለንን ልትረዳና የዮሐንስን ሥራ በሚመለከት ነቀፌታና ማንቋሸሽ ያለበትን ታል እንዳትናገር ጥንቃቄ ልትወስድ ይገባታል። ሥራውን ወይም የመረጠውን የሙያ አይነት የምትነቅፍ ከሆነ የነቀፈችው እርሱን ራሱን ነው።

በተመሣሣይ መንገድ፤ ለሴት ቤቷ የሰብአናዋ ቀጣይ ነገር ነው። ቤቷ ማን እንደሆነች እርሷነቷን የሚወክልና አራሷን እንዲት

እንድምታይ የሚገልጽ በመሆኑ ምክንያት፤ የሴትን ቤት የሚነካ ነገር ሁሉ እርሷን ራሷን የሚነካ ነው።

ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ ሴት ለቤቷ ሁኔታና ውበት አብዝታ የምትጨነቀው። እጅግ ብዙ ጊዜ ባሎች በአግባቡ ይህን አይገነዘቡትም። ባሎች፤ የመኖሪያ ቤታቸው ውበት ለሚሰቶቻቸው የክብራቸውና የጠቃሚነታቸው መግለጫ እንደሆነ ባለመገንዘባቸው በአግባቡ አድናቆትን አይሰጧቸውም። አንድ ሴት ለቤቷ የምታወራ ከሆነ የምታወራው ስለራሷ ነው። ሣራ ለዮሐንስ ለሣሎናቸው አዲስ መጋረጃ እንደሚያስፈልግ የምትናገር ከሆነ፤ በአርግጥ ምን እያለች እንደሆነ ጥንቃቄ መውሰድ አለበት። ለአርሱ መጋረጃው ጥሩ ሆኖ ታይቶት ይሆናል፤ ነገር ግን ሣራ አርሱ ያላያቸውን ነገሮች አይታ ይሆናል። ለአርሷ ሲል፤ በአራሱ ሣይሆን በአርሷ አይኖች ውስጥ ቤታቸውን መመልከት መማር ይኖርበታል።

10. ወንዶች በየስፍራው ተዘዋዋሪዎች (ዘላኖች) ሊሆኑ ይችላሉ። ሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነትንና መደላደልን ይፈልጋሉ።

ሴቶች ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ያለጥርጥርና ያለ ፍርሃት በጋብቻ ግንኙነታቸው መረጋጋትንና መደላደልን ይፈልጋሉ። ያለምንም ማቋረጥ በባሏ ህይወት ውስጥ እጅግ ጠቃሚውን ስፍራ የያዘች መሆኗ ተረጋግጦ እንዲነገራት ትፈልጋለች። ሂዳቱን ሣያዛንፍ አብዝቶ እንደሚወዳት ሊነግራት ያስፈልገዋል። ያንን ታውቃለች ብሎ መገመት ብቻውን በቂ አይደለም፤ ከአፉ ልትሰማው ትፈልጋለች። ይህ ማለት ባሏን አታምነውም ማለት ሣይሆን - በቃ ስሪቷ እንደዛ ስለሆነ ነው። ወንድ እንደ ሴቶች ፍልቀሰሜታዊነቱን ጭረው የሚያቀጣጥሉ ነገሮች አያስፈልጉትም።



አንድን ነገር ደጋግሞ ማረጋገጥ ሁለንተናዊ ደህንነት ያመጣል።

ወንድ ልክ እንደ ግመል ነው፤ አንድ ጊዜ "ጠጥቶ" ለረዥም ጊዜ መሄድ ይችላል። ሴት በመዝሙር መጽሐፍ 42፥1 ላይ እንደተገለጸችው ዋላ "ዋላ ወደ ውሃ ምንጭ እንደሚናፍቅ" አይነት ናት። በተደጋጋሚ "መጠጣት" ትፈልጋለች። ወንዶች ዘላናዊ በሆነ ተፈጥሯቸው ምክንያት ከሴቶች ይልቅ ረዥም ጊዜ ብቻቸውን በራሳቸው መሆን ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ሚስቶች፤ ባሎቻቸው ለተወሰነ ጊዜ ብቻቸውን መሆን እንደሚፈልጉ ሲገነዘቡ ይጨነቃሉ።

ሚሰቶች ከባሎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤንነት የሌለው መስሎ ከታያቸው፤ ይህንን የሚተረጉሙት እንደመገለል ወይም ባላቸውን እንዳላስደሰቱትና እንዳላረኩት ነው። ለዚህ ነው ባል ሁልጊዜ ፍቅሩን በተደጋጋሚ መግለጽ በቃሉና በተግባሩም ሊያረጋግጥላት የሚገባው። አንድን ነገር ደጋግሞ ማረጋገጥ ሁለንተናዊ ደህንነት ያመጣል።

ብዙ ወንዶች ካሰማቸውን ነቅለው በቀላሉ መሄድ ይችላሉ። ሴቶች ግን የተደላደለ ጥልቀት ያለውን መሠረት ይፈልጋሉ። በአንድ ስፍራ ተደላድለው መቀመጥ ይመርጣሉ። ወንድ በአንድ ጊዜ ተነስቶ መቀየር ይችላል፤ ይህ ግን ለሴቶች ቀላል አይደለም። ምክንያቱም ፍለቀ ስሜታዊ በመሆኗና ከወንዶች ይልቅ ከስፍራዎችና ከነገሮች ጋር ራሷን በጥብቅ የምታቆራኝ በመሆኗ ነው። ይህንን ከአይምሮ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰቱን በአንድ ስፍራ ተደላድሎ በመቀመጥ የሚገኝን ሁለንተናዊ ደህንነት ፍላጎት ተገንዝበ፤ ዝም ብሎ በመነሣት መንቀሣቀስ የለበትም።

11. ሴቶች ራሳቸውን የመኮነን አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች ወደ ምሬት ያዘነብላሉ።

ፍልቀስሜታዊ ከሆነው ማዕከል ነገሮችን የምትመለከት በመሆኑ ሴት ጥፋቱ የእርሷ ባይሆን እንኳን በግንኙነታቸው መካከል ለሚፈጠረው ማንኛውም ችግር ሃላፊነትን በመውሰድ ራሷን ትኮንናለች። እንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ደግማ ደጋግማ በአይምሮዋ ውስጥ ለምን መኮነን እንደተገባት ምክንያቶችን በመዘርዘር ታጠናቸዋለች።

በየቀኑ ብዙ ሴቶች የሚንቀሳቀሉት፤ ጽድቅ በጎደለው መንገድ በራሳቸው ላይ የጫኑትን የበደለኝነት ደመና ተከናንበው ነው። በግንኙነታቸው መካከል ችግር በተፈጠረ ጊዜ ሴቶች ራሳቸው ጥፋተኞች እንደሆኑ ይገምታሉ። "እንደዚህ የተናደደው ምን ብየ ተናግሬው ይሆን? እንዳንጣላ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?" ማለትን ያዘወትራሉ። ብዙ ጊዜ ጭርስኑ የሴቷ ጥፋት ላይሆንም፤ ጥፋተኛ ነኝን አምና የመቀበል ችግር አለባት።

ወንድ እንዲህ አይደለም። በግንኙነታቸው መካከል የሆነ ችግር ከተፈጠረ፤ ራሱ ሃላፊነትን ከመወሰድ አስቀድሞ በፊት በሴቷ ወይም በሌላ ሰው ላይ ምሬቱን ይገልፃል። ብዙ ወንዶች የበደለኝነትን ስሜት ከመሸከም ይልቅ፤ ማድረግ የሚችሉትን ማንኛ

ውንም ድርጊት ይፈጽማሉ። ወቀሳን ከመቀበል ይልቅ በቁጣ መንደድ ይቀላቸዋል።

እነዚህ ሁለት ምላሾች ተቃራኒና እርስ በእርስም የሚመጋገቡ ናቸው። ወንድ ጥፋቱን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም፤ ሴቷ ደግሞ ጥፋተኛ ባትሆን እንኳን ሃላፊነትን ወደ ራሷ ትወስዳለች። በመሆኑም የወንዱ ሃላፊነትን ለመውሰድ ላልፈቀደባቸው በደሎች ሁሉ፤ የምሬቱና የቁጣው ማብረጃ ከመሆኗም በላይ ሆን ብሎ ለሚፈጽመው ጉዳቶች ኢላማ ትሆናለች። ባለ ትዳሮች አስተዋዬች ሊሆኑና ችግሮች የሚፈጠሩባቸውን እነዚህን ሁኔታዎች አስቀድመው ማጤን ያስፈልጋቸዋል፤ ምክንያቱም ከማንኛውም ነገር ይልቅ ግንኙነታቸውን ፈጥነው ሊያወድሙባቸው ስለሚችሉ ነው።

12. ወንዶች የተረጋጉና የሁኔታቸውን ደረጃ ጠብቀው መዝለቅ የሚችሉ ናቸው። ሴቶች ሁልጊዜ ይለወጣሉ።

አሁንም እንደገና ይህ ልዩነት በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚከሰተው በስውነታቸው ውስጥ ባለው የኬሚካልና የሆርሞን መጠን ሚዛን ልክ ነው። በተለይም ደግሞ እንደሚሠሩበት ከምክንያታዊነት ወይም ከፍልቅ ስሜታዊነታቸው አንፃር የሚታይ ነው። ብዙ ወንዶች እንደሚናገሩት፤ በአይምራቸው ሁልጊዜ ከሚለወጡት ሴቶች ይልቅ፤ ጥቂት ነገሮች እነርሱን ወደ ከፋ ችግር ውስጥ ይከቷቸዋል። በሌላ በኩል ሴቶች፤ ወንዶች ብዙ ጊዜ ምንም ነገር ሊፈጠር ፈጥነው ምላሽ የማይሰጡ ቀዝቃዞች ወይም በጉዳዩ ላይ ፍላጎት የማያሳዩ ናቸው ሲሉ ይከራከራሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ይህ የአመለካከት አቅጣጫ ልዩነት ነው።

በጥቅሉ፤ ወንድ ውሳኔ ሊሰጥና በዚያው ሊፀና ይችላል፤ አንዳንድ ጊዜ ይህ እስከ ግትርነት ይዘልቃል። ሲታ አንድ ነገር ትነግረውና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፤ ሃሣቤን ቀይሬያለሁ ትለዋለች። አንደኛው ከሌላኛው የበለጠ ወይም መጥፎ አይደለም። ይህ የሚያመለክተው የወንዶችና የሴቶች አይምሮ ነገሮችን የሚያከናውኑበት የተለያየ መንገድ መሆኑን ነው።

ዮሐንስና ሣራ ወደ ራት ግብዣ ስፍራ ለሄዱ እየተዘጋጁ ነው እንበል። ዮሐንስ ግራጫውን ሱፍ ልብሱን መርጦ ለብሷል። አሁን ሣራን እየጠበቀ ነው። መጀመሪያ ሰማያዊውን ቀሚሷን ሞከረች፤ ቀጥሎ ቀዮን ቀሚስ ከዚያ በኋላ ቀጫጭን ቅጠሎችና የሚያማምሩ አበቦች ያሉበትን አረንጓዴውን ቀሚሷን . . .

በመጨረሻ መጀመሪያ በሞከረችው ለማያዊ ቀሚስ ላይ ልቧ አረፈ። ልክ እንደቤቷ ሁሉ ለሣራ ልብሷ የግላዊ ማንነቷ መግለጫ ነው። እያንዳንዱ ነገር ፍጹም መሆን አለበት፤ ውብ ሆና መታየት ያስፈልጋታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ዩሐንስ ትዕግስት አጥቶ እየተንቀራጠጠ ያስባል። "እባክሽ በፈጣሪ ይሁንብሽ አንድ ነገር ምረጭና እንሂድ!" የለበሰው ሱፍ ንጹህ እስከሆነና ከረባቱ ትክክል እስሆነ ድረስ ለርሱ በቂ ነው።



ጠቂጋትም ደሁን በፍጥነት መስሞጠጥ ሁለቱም ጤናማና ስኬታማ ለሆነ ግንኙነት ጠቃሚዎች ናቸው።

ይህንን ልዩነት በሌላ መንገድ ለመግለጽ፤ ወንዶች በጣም የተረጋገጉና በያዙት አቋም የሚፀኑ ሲሆኑ፤ ሴቶች የበለጠ በፍጥነት ሚለዋወጡ ናቸው። መረጋጋትም ይሁን በፍጥነት መለዋወጥ ሁለቱም ጤናማና ስኬታማ ለሆነ ግንኙነት ጠቃሚዎች ናቸው። መረጋጋት አስፈላጊውን መሠረት ይጥላል፤ በፍጥነት መለወጥ ደግሞ ጤነኛ የሆነ ጀብድ የተሞላበትን ተግባር ያከናውናል።

13. ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በሁኔታዎች ውስጥ በቀላሉና በፍጥነት የመግባት አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች በሁኔዎች ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ከጀርባ ቆመው የመገምገም አዝማሚያ አላቸው።

ሴቶች ፍልቱስሚታዊያን በመሆናቸው ከወንዶች ይልቅ ራሳቸውን በጉዳዮች፤ በእንትስታሴዎችና በፕሮጀክቶች ውስጥ በፍጥነት ያስገባሉ። ሴቶች ዘልቀው የመመራት አዝማሚያ አላቸው። ልባቸውን የሚነክዉን መሠራት ያለበትን ወይም ክብርና ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ጉዳይ ያስተውሉና ፈጥነው ለሥራ ይታጠቃሉ። ይሁንና ምክንያታውያን የሆኑት ወንዶች፤ በአይምሯቸው ይመራሉ፤ ተዘቀዝዘ ብለው ወደ ኋላ ይሸሻሉ፤ ራሳቸውን ለተግባር አግልፈው ከመስጠታቸው በፊት ሁኔታዎችን በጥንቃቄ ይገመግማሉ፤ ይመዘናሉ። ወንዶች ከምክንያታዊነት አይታቸው የተነሣ በቀላሉ ነገሮችን አይቀበሉም፤ ወደ ጉዳዩ ውስጥ ገብተው ከመጣተፋቸው በራት እንድን ነገር ከሁሉም አቃጣጫ ተንትነው ይመለከቱታል። ለወንዶች በአንድ ጉዳይ ውስጥ ለመግተፋ ጊዜ የሚወስድበት በሆንም፤ አንድ ጊዜ ከወሰነ በኋላ ግን ከሰጊ እስከ ለተዳዩ ተስጥቶ ይሠራል። ወንድና ሴት የሚሄዱበት አቅጣጫ የተለያየ በዘንም በመጨረሻው ግን ከአንድ መዳረሻ ላይ ይገናኛሉ።



ምክንያታዊነትና ፍልቅ ስሜት እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ናቸው።

እዚህ ጋ አሁንም የእግዚአብሔር ጥልቅ ጥበብ ይገለላል። ምክንያታዊነትና ፍልቅ ስሜት እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ናቸው። ሁለቱም በአንድነት ለህይወትና ለእምነት ምልዑነትን ያስገኛሉ። ምክንያታዊነት ያለ ስሜት ደረቅ ግትርና ህይወት የለሽ ነው። ያለ ምክንያት የሆነ ስሜትም ሥርዓትና መረጋጋት የጎደለው ነው። የምክንያታዊነትንና የፍልቅ ስሜትን ህብራዊ ትስስር የተገነዘቡና የሚያደንቁ ባለትዳሮች፤ በጥንካሬ፤ በፍቅር፤ ስሜት ባለው ደስተኛ ነት የሚገለጥ ትዳር ለመገንባት ከፍተኛ እድል አላቸው።

14. ወንዶች በተደጋጋሚ ሊነገራቸው ያስፈልጋል። ሴቶች በጭራሽ አይረሱም።

የወንድ አይምሮ ልክ እንደ ፋይል ካዝና ነው። የሚነገረውን ነገር ሁሉ በኋላ አውጥቶ ሊገለገልበት በአይምሮው ካዝና ውስጥ ፋይል ያደርገዋል። አንድን ነገር ወዲያውኑ አለማከናወኑ የተነገረውን ረስቶታል ወይም ችላ ብሎታል ማለት አይደለም፤ በቀላሉ በአይሞሮው መዝግቦ ይዞታል። ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ ወንድ አሁንም አሁንም አንድ ነገር ተደጋግሞ ሊነገረው እንደሚያስፈልግ የሚታሰበው። የሴት ጭንቅላት ማንኛውንም ነገር በጭራሽ እንደማይረሳ ኮምፒዮተር ነው፤ ይልቁንም ለሥራ በተፈለገ ጊዜ ወዲያውኑ ምላሽ ለመስጠት አዘጋጅቶ ያስቀምጣል። ሴቶች ለወንዶች የተናገሩትን ወይም ወንዶች ለእነርሱ የተናገሩትን በጭራሽ አይረሱም፤ እርሱም ነገሩን እንዳደረለው።

እነዚህ ሁለቱም ብቃቶች እንደየሁኔታው ጠቃሚም ጎጂም ሊሆኑ ይችላሉ። ወንዶች ነገሮችን ግላዊ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ የሌላቸው በመሆኑ፤ በራሳቸው የተሰነዘሩ ወይም በሌሎች የተነገሯቸውን ትችቶችና አስተያየቶች አድበስብሰው ለማለፍ ወይም ለመርሣት የተጋለጡ ናቸው። በአጠቃላይ ወንዶች በአለፈ አስከፊ ትዝታ መብሰልሰል ለመጠቃት እምብዛም የተጋለጡ አይደሉም። በተቃራኒው ይህ ነገሮችን መርሣት ለሚስቶቻቸውና ለልጆቻቸው ፍላጎት መልስ ለመስጠት የሚችግራቸው በከባድ ሁኔታ ስሜቱ ቀዝቀዝችና ፈጥነው ምላሽ የማይሰጡ ያደርጋቸዋል።

ሴት ሁሉን ነገር የምትቀበለው በፍልቅ ስሜቷ በመሆኑና ቃላቶችንና ስሜቶችን በልቧ ውስጥ ስለምትይዝ፤ በአካባቢዋ

ለምታየው ፍላጎት በስሜቷ የነቃችና ፈጥና መልስ ለመስጠት በተፈጥሮዋ የታደለች ነች። በሌላው በኩል የሴት ነገሮችን ሁሉ የማስታወስና ከግላዊነት አንፃር መመልከት፤ ልብ የሚሰብር አስተያየት፣ ውግዘትና ጥቃት በተፈጸመባት ጊዜ፤ በፍጥነት ለማያድግና ለሳምንት፣ ለወራት ከዚያም አልፎ ለአመታት ለሚቆይ ዘላቂነት ላለው የስሜት ውጥረት፣ ንዴትና ለልብ ስብራት ትጋለጣለች።

ባልና ሚስት ይህንን ልዩነት በግንኙነታቸው ውስጥ እንዴት አድርገው በአግባቡ ማቻቻል ይችላሉ? ባሎች አንድን ነገር ለምን እንደሚናገሩና እንዴት እንደሚናገሩትም ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። እዚህ ላይ የምሣሌን መጽሐፍ ጥበባዊ ምክር ማስታወሱ ጠቃሚ ነው፤ "የለዘበች ምላስ ቁጣን ትመልሣለች፤ ሻካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሣለች" (ምሣ 15÷1)። ሴቶች ቁጣቸውን በጸጋ ማለዘብ እንደሚገባቸው ሊያስታውሱ ይገባል፤ ጳውሎስ እንደሚናገር "ፍቅር አይበሳጭም፤ በደልንም አይቆጥርም" (1ቆሮ 13÷5)።

15. ወንዶች ከዝርዝር ነገሮች ይልቅ መሠረታዊውን ጉዳይ የማስታወስ አዝማሚያ አላቸው። ሴቶች ዝርዝር ነገሮችን የማስታወስ አዝማሚያ ሲኖራቸው አንዳንድ ጊዜ መሠረታዊ ጉዳዮችን ያዛቧቸዋል።

ይህ "የተናገረው አሉ ነው፤ የተናገረችው እርሷ ናት" እንደሚል ከቶየ ውዝግብ ጋር ተመሣሣይነት ያለው ነው። ወንዶች የንግግር ልውውጦችንና ድርጊቶችን በአጠቃላይ አይታ የማስታወስ አዝማሚያ ሲኖራቸው፤ ሴቶች ዝርዝር ነገሮችን በነቂስ አብጠርጥረው ያስታውሣሉ። ሴቶች አንዳንድ ጊዜ ወንዶች የተናገሩትን ነገር እንደሚደብቁ አድርገው ይከሷቸዋል። እውነታው ግን በቀላሉ ወንዶች በቃላት ልውውጥ ወቅት የሚናገሩትን ዝርዝር ነገር ስለማያስታውሱት ነው። ወንዶች ስለሚናገሩት ነገር አጠቃላይ ጉዳይ ግልጽ ናቸው፤ ለእነርሱ ዝርዝር ጉዳዮቹ እምብዛም አስፈላጊ አይደሉም። ሴቶች በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ንቁ ናቸው፤ ይህንና አንዳንድ ጊዜ አጠቃላይ ጉዳዮችን እንደ ዝርዝር ጉዳዮች አያስታውሱም።

ሁለቱም አዝማሚያዎች እውነትን ሊያዛቡ ይችላሉ። አንኳር ነገሩን ያለዝርዝር ነገሩ ማስታወስ ልክ ዝሆንን በደመና ውስጥ በደበዘዘ አይታ ማየት እንደማለት ነው። "የማውቀው ትልቅ

እንደነበረ ነው"። ዝርዝር ነገርን ብቻ ለይቶ ማወቅ፤ ልክ አራት አይናቸውን የታሠሩ ሰዎች በአንድ ክፍል ውስጥ አንድን ዝሆን በመንካት ብቻ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንደሚያደረጉት መከራ ነው። አንዱ እግሩን አንዱ ደግሞ ወገቡን፣ ሦስተኛው ጭራውን አራተኛው ደግሞ ጆሮውን ይዳስሳሉ። የአንዳቸው ገለጻ ከሌላቸው የተለየ ነው። በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ ነገሮችን የማስታወስ ልዮነት በመካከላቸው ለሚፈጠር የግንኙነት ችግር ዋንኛው ምክንያት ነው። አዲስ መስመር ላይ ሣራ፤ ዮሐንስ ከዚህ ቀደም የተናገረውን አንድ ጉዳይ አስታወሰችውና እርሱም አምኖ ተቀበለ። "ልክ ነሽ፤ እንደዚያ ያለ ነገር እንደተናገርኩ አስባለሁ"።

"አይደለም" አለች ሣራ "የተናገርከው በትክክል እንደዚያ ነው"

"ደህና፤ እንደዚያ ማለቴ ግን አልነበረም"

"ምናልባት ላይሆን ይችላል፤ የተናገርከው ግን ያንን ነበር"

ዮሐንስ ያስታወሰው አንኳር ነገሩን ሲሆን፤ ሣራ ደግሞ ዝርዝር ነገሩን አልረሣችም። እንዲህ አይነቱ ያለመግባባት ምስቅልቅል በመልካም የሚደመደመው እንዲህ በሚል መግለጫ ነው። "እኔ የተናገርኩትን ነገር የተረዳኸው አንተ ባሰብከው መንገድ እንደሆነ ተረድቻለሁ። ነገር ግን የሰማኸውን ነገር የተገነዘብከው እኔ ማለት የፈለኩትን እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ"

እንደ ሁልጊዜውም፤ ወንዶችንና ሴቶችን በተፈጥራዊ ልዮነቶቻቸውና በሚያስቡበት የተለያየ መንገድ ምክንያት የሚፈጠሩ ውጥረቶችንና ውዝግቦችን ለማርገብ ትዕግስትና መግባባት ረኀቦም ርቀት ያስኬዳሉ።

* * *

በወንዶችና በሴቶች መካከል ባለ ልዩነት የሚሰማው የተለመደ ብሶት "አንተ እኔን ምንም አታውቀኝም" ወይም በሌላ አገላለጽ እኔም ልክ እንዳንተ አንድሆን ትፈልጋለህ የሚል ነው። በቀላሉ ነገሮች እንዲህ አይደሉም በመሆኑም ባልሆኑበት መንገድ እንዲሆኑ አንመኝም። ወንዶችና ሴቶች ልዩ ናቸው፤ ስለዚህም ደግሞ እግዚአብሔር ይመስገን።

ባል ልክ እርሱ እንደሚያስብበት ምክንያታዊነትንና ትንተናን መሠረት ባደረገ መንገድ ሚስቱ ማለብ እንድትጀምር መጠበቅ ወይም መመኘት የለበትም። እንደዚሁ ደግሞ ሚስት፤ ባሏ እርሷ በምታስብበት ፍልቅ ስሜታዊ ከሆነ አቅጣጫ እንዲያስብ መጠበቅ አይገባትም። ሁለቱም እግዚአብሔር "ሰው" ብሎ በፈጠረው በሁለቱም ጾታ ውስጥ ያስቀመጠውን መሠረታዊ ልዩነት ዋጋ መስጠትንና ማክበርን ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል።

እነኝህ ልዩነቶች እንዴት እርስ በእርስ እንደሚደጋገፉ እንመልከት። ስሜት አልባ የሆነ የምክንያታዊነት ዓለም አይምሮ አልባና ልብ የለሽ ሕዝብ ያቀፈ የኮምፒዮተር አለም በሆነ ነበር። እግዚአብሔር ኮምፒዮተሮችን አልፈጠረም እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ በእነዚህም ፍጥረቶቹ ውስጥ ህይወት እንዲበለጥግና ምልዑ እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑትን የተለያዩ ግን ተደጋጋፊ ብቃቶችን ሞላባቸው።

ወንዶችና ሴቶች አንድ አይደሉም፤ ይህ ግን ለመልካም ነው። በልዩነቱ ደስ ይበለን!

መርሆዎች

1. ወንድ ምክንያትን መሠረት አድርጎ ያስባል፤ ሴት ግን ፍልቅ ስሜታዊ ናት።
2. የሚናገሩት ቋንቋ፤ ለሴቶች የውስጥ ስሜታቸውን ለወንዶች ደግሞ በውስጣቸው የሚያስቡትን የሚገልጽ ነው።
3. ሴት የምትለማው ቋንቋ ከፍልቅ ስሜት ልምምዷ ጋር የሚያያዝ ነው። ወንድ በሚሰማው ቋንቋ የሚቀበለው መረጃን ነው።
4. ሴቶች ነገርን ሁሉ ከግላዊ ነገራቸው ጋር የማያያዝ አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች ሁሉን ነገር ግልጥ የማድረግ አዝማሚያ አላቸው።
5. ሴቶች በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ፍላጎት አላቸው። ወንዶች ዋነኛ በሆኑ ጥልቅ ጉዳዮችና ፍልስፍናዎች ላይ ፍላጎት አላቸው።
6. ቁሳዊ ነገሮችን በሚመለከት፤ ሴቶች ውጤቱን የመመልከት አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች እዚያ እንዴት መድረስ እንደሚቻል መንገድ ይፈልጋሉ።
7. መንፈሳዊ ወይም ተጨባጭ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ወንዶች በውጤቱ ላይ ያተኩራሉ። ሴቶች ደግሞ ከውጤቱ ላይ እንዴት እንደሚደረስ ማወቅ ይፈልጋሉ።
8. የወንድ አይምሮ እንደ ፋይል ካዝና ነው። የሴቶች አይምሮ ደግሞ ልክ እንደ ኮምፒዮተር ነው።
9. ለሴት ቤቷ የሰብአናዋ ቀጣይ ነገር ነው። ለወንድ ደግሞ ሥራው የሰብአናው ቀጣይ ነገር ነው።
10. ወንዶች በየስፍራው ተዘዋዋሪዎች (ዘላኖች) ሊሆኑ ይችላሉ። ሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነትንና መደላደልን ይፈልጋሉ።
11. ሴቶች ራሳቸውን የመኮነን አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች ወደ ምሬት ያዘነብላሉ።
12. ወንዶች የተረጋጉና የሁኔታቸውን ደረጃ ጠብቀው መዝለቅ የሚችሉ ናቸው። ሴቶች ሁልጊዜ ይለወጣሉ።
13. ሴቶች ከወንዶች ይልቅ በሁኔታዎች ውስጥ በቀላሉና በፍጥነት የመግባት አዝማሚያ አላቸው። ወንዶች በሁኔታዎች ውስጥ

ከመግባታቸው በፊት ከጀርባ ቆመው የመገምገም አዝማሚያ አላቸው::

14. ወንዶች በተደጋጋሚ ሊነገራቸው ያስፈልጋል:: ሴቶች በጭራሽ አይረሱም::

15. ወንዶች ከዝርዝር ነገሮች ይልቅ መሠረታዊውን ጉዳይ የማስታወስ አዝማሚያ አላቸው:: ሴቶች ዝርዝር ነገሮች የማስታወስ አዝማሚያ ሲኖራቸው አንዳንድ ጊዜ መሠረታዊ ጉዳዮችን ያዛቧቸዋል::

ምዕራፍ ስምንት

ጓደኝነት፤ ከግንኙነቶች ሁሉ የላቀ

የባልና የሚስት ግንኙነት ቀደምትና አብይ የሆነ ሰብአዊ ግንኙነት ነው:: የወላጅና የልጅ፤ የአናትና የሴት ልጅ፣ የአባትና የወንድ ልጅ፣ የወንድምና የእህት ግንኙነትን ጨምሮ ከማንኛቸውም አይነት ግንኙነቶች ይልቅ ቀደምት አድሜ ያለውና የመጀመሪያው ነው:: በባልና በሚስት መካከል እንዳለው ግንኙነት፤ ማንኛውም ሴላ ግንኙነት የቀረበ፣ በጣም ግላዊ ወይም የልብ የሆነ ግንኙነት ይኖራል ተብሎ አይጠበቅም:: አንዲህ ያለው የቀረበ ጓደኝነት ፍቅር ብቻ ሣይሆን መተዋወቅንም ይጨምራል:: ባልና ሚስት በምድር ላይ ከሚያውቁት ከማናቸውም ሰው ይልቅ እርስ በእርስ ሊተዋወቁ ያስፈልጋቸዋል:: እርስ በእርሳቸው የሚወዱትን፣ የሚጠሉትን፣ ልዩ ባህሪያቸውንና ቶሎ የሚያስቆጣቸውን፣ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን፣ ጥሩና መጥፎ ባህሪያቸውን እንዲሁም ልዩ ተሰጥኦዋቸውንና ችሎታቸውን፤ ቀድመው የሚገምቱትን፣ ፈጥነው የማይገነዘቡትን እንግዳ ጠባያቸውን ሁሉ፤ በእጭሩ ባልና ሚስት በሁሉ ነገር እርስ በእርስ መተዋወቅ ይገባቸዋል፤ ይህ ሲባል ከሌሎች የሚደብቁትን አላስፈላጊ የሆነ ልዩ ባህሪያቸውን ጭምር ማለት ነው::

ግንኙነት የግድ መተዋወቅን ያጠጣል ማለት አይደለም::

አሁን የምንነጋገርበት የትውውቅ አይነት ፈጣን አይደለም:: ሁለት ሰዎች ስለተጋቡ ብቻ በቀላሉ የሚከሰትም አይሆንም:: ግንኙነት የግድ መተዋወቅን ያመጣል ማለት አይደለም:: በጋብቻ ውስጥና በማንኛውም ሰብአዊ ግንኙነቶች ውስጥ ከሚፈጠሩት ታላላቅ ችግሮች መካከል አንዱ፤ የምንጠቀምባቸው መጠሪያዎች ናቸው:: ባል፣ ሚስት፣ እናት፣ ሴት ልጅ፣ እህት፣ ወንድም፣ አባት፣ ወንድ ልጅ የሚሉት ቃላት በቤተሰብ መካከል ያሉትን የተለያዩ ግንኙነቶች የሚገልጹ ናቸው:: እነኝሁ ቃላት በተጨማሪ በሰዎቹ መካከል ያለውንም ይሁን የሌለውን መተዋወቅና መቀራረብ ያመለክታሉ::

ለምሣሌ አንዲት እናትና ሴት ልጇ በቀላሉ እርስ በእርሳቸው የሚተዋወቁ ይመስላቸዋል፤ ምክንያቱም መጠሪያቸው የሚያመለክተው የቀረበ ግንኙነትን በመሆኑ ነው:: እርግጥ ነው እናት ልጇን፤ ልጅም እናቷን ታውቃለች:: ነገር ግን ይህ አጠቃላይ

እውነት አይደለም። ለተለያዩ አይነት ግንኙነቶችም ይህንኑ ልንናገር እንችላለን። ወንድሜ ወይም እህቴ ብየ ብጠራ ይህ አጠራሬ የሚገልጸው እንደማውቃቸው ነው። እርስ በእርስ የምንተዋወቅ በመሆኑ እርስ በእርሳችን ለመተዋወቅ ጊዜ ወስደን አንድ ላይ መሆን እንደማያስፈልገን እገምታለሁ።



ጋብቻ ወደ ወዳጅነት ብቻ ሳይሆን ወደ ጓደኝነትም የሚደረግ የህይወት ዘመን ጉዞ ነው።

ቅርበትንና በግልጽ መተዋወቅን የሚያሣዩ መጠሪያዎች እውነተኛ ግንኙነትን ለመገንባት እንቅፋቶች ናቸው። ባልና ሚስት በመጋባታቸው ብቻ በቀላሉ እርስ በእርሳቸው የሚተዋወቁ ይመስላቸው ይሆናል። በዚህም ምክንያት፤ እርስ በእርስ እንዱ የሌላውን ባህሪ ላይ ላዩን እየዳበሰ ይፈትሻል እንጂ በጥልቀት በመቆፈር የጠለቀና የቀረበ ግንኙነትን ለመመስረት እውነተኛ እውቀት ለማግኘት ጥረት አያደርጉም።

ጋብቻ ወደ ወዳጅነት ብቻ ሣይሆን ወደ ጓደኝነትም የሚደረግ የህይወት ዘመን ጉዞ ነው። ባልና ሚስት እንዳቸው የሌላቸው የቀረበ ጓደኛ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ከዚህ የበለጠ ሌላ ግንኙነት የለም። ከጓደኛችን በላይ እኛን የሚያውቀን ሰው ማን ነው? ብዙዎቻችን ለራሣችን ቤተሰቦች ነግረናቸው የማናውቀውን እንዳንድ ነገሮቻችንን ለጓደኞቻችን እናካፍላቸዋለን። ባልና ሚስት እንዳቸው ከእንዳቸው የሚደብቁት ሚስጥር ሊኖር አይገባም። የግንኙነታቸው እድሜ እየረዘመ በሄደ ቁጥር እንዱ የሌላውን መልካምም ይሁን መጥፎ ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ፤ ይሁንና ሁኔታውን በፍቅር የሚቀበል እውነተኛ ጓደኛ ወደ መሆን ሊያድጉ ያስፈልጋቸዋል።

ጓደኞች እንጂ ከእንግዲህ ባሏያሞች አይደሉቱም

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት፤ "ከጓደኝነት" የሚበልጥ ሌላ ምን ዓይነት ግንኙነት የለም። በመጽሐፍ ውስጥ ከተገለጹት ባለታሪኮች መካከል እርሱ ወይም እርሷ የእግዚአብሔር ወዳጅ ከተባሉት በስተቀር ከፍተኛ ምስክርነት የተሰጠላቸው የለም። ለዚህ አባባላችን አብርሃምን በዋቢነት ማቅረብ ይቻላል። "አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔር ወዳጅ ተባለ" ያዕ 2፥23። ሌላው እግዚአብሔር እንደ ወዳጅ የሚያውቀው ሰው ሙሴ ነበር። "እግዚአብሔር ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር፤ ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር

ነበር" ዘፀ 33፥11። ሁለተኛው የእስራኤል ንጉስ የነበረው ዳዊት እግዚአብሔር እንደ ልቡ ያለው ሰው ነው (1ሣሙ 13፥14 ይመልከቱ) ይህ በሌላ አባባል ዳዊት የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበረ ማለት ነው።



በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከግንኙነቶች ሁሉ የላቀው ግንኙነት ጓደኝነት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ላይ የወዳጅነትን የከበረ ስፍራ ግልጽ አድርጎታል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 15፤ ለተከታዮቹ በእርሱና በእነርሱ መካከል ሊኖር የሚገባው መቀራረብ በወይን ቅርንጫፍና በወይኑ ግንድ መካከል ያለው አይነት መቀራረብ እንደሆነ ከነገራቸው በኋላ፤ ኢየሱስ ይህንን መቀራረብ ከባልንጀርነት ጋር አገናኝቶታል፤ "እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት፤ ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም፤ እኔ ያዘዝኳችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን እያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አሳውቄያለሁና" (ዮሐ 15፥12-15)።

በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ለተከታዮቹ የሚያበስረው፤ ከተከታዮቹ ጋር ያለው ግንኙነት እዲስ ወደሆነ አቅጣጫና ብልጫ ወዳለው ግንኙነት መለወጡን ነው። አሁን አንዱ ከሌላኛው ጋር የሚዋሃድበት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ተከናውኗል። "እርስ በእርሳችሁ" ተዋደዱ ከሚለው ትእዛዝ ቀጥሎ፤ ያ መዋደድ እስከ ምን መድረስ እንደሚገባው ይገልጻል፤ በዚህም ከፍቅር ሁሉ የሚበልጠው ፍቅር ራስን ለወዳጆቹ አሳልፎ ለመስጠት የሚፈቅድ ሰው ፍቅር እንደሆነ ያበሰራል። ኢየሱስ እንዲህ ስላለው ፍቅር ምንነት በሚቀጥለው ቀን ወደ መስቀል በመንገዝ በተግባር ሊያሣያቸው እየተዘጋጀ ነበር። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ "ወዳጆች" እያለ የሚጠራው ቤተሰብን አይደለም። በእውነተኛ ወዳጅነት ውስጥ ከቤተሰባዊ ግንኙነት እንኳን የላቀና ከፍ ያለ የከበረ ነገር አለ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእስራኤል ላይ ንጉስ ሊሆን ባለው በዳዊትና በጊዜው ንጉስ በነበረው በሳኦል ልጅ በዮናታን መካከል ከቤተሰብ ይልቅ አስደሳች የነበረ ግንኙነት ያለው ባልንጀርነት ነበር። ሳኦል የዳዊትን ነፍስ ሊያጠፋ ቢፈልግም እንኳን፤ ዮናታን ለዳዊት

ይከላከልለት ነበር። ምክንያቱም ከዳዊት ጋር አንድ መንፈስ ነበር፤ "እንደ ነፍሱም ይወደው ነበር" (1ሳሙ. 18÷1)።

ከዚያ በመቀጠል ኢየሱስ የአዲሱንና ጥልቀት ያለውን ግንኙነት ባህሪ ይተነትን ጀመር። "ያዘዝኳችሁን ብትፈጽሙ፤ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ" መታዘዝ ከክርስቶስ ጋር ያለን ወዳጅነት የሚፈተንበት እንደገናም የፍቅርም መመዘኛ ነው። ኢየሱስ ባሪያ እንደሚያደርገው የታዘዝነውን ለመፈጸም ባለን ግዳጅን የመወጣት አላማ እንድንታዘዘው አይፈልግም። ይልቁንም ከወዳጅነት ግንኙነት መንጭቶ በጎለበተ በፍቅርም ላይ የተመሠረተ መታዘዝን እንድንታዘዘው ይፈልጋል። የመጀመሪያው አይነት መታዘዝ ያለፈቀደኝነት የተጫነን ግዳጅ ለመወጣት የሚደረግ መታዘዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው አይነት መታዘዝ ግን ከውስጥ የመነጨ ነፃ የሆነ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ነው። በእነዚህ ሁለቱ ምክንያት አለም ተለያይታለች።



መታዘዝ ከኢየሱስ ጋር ባለን ወዳጅነት መፈተኛው ነው፤ እንደገናም የፍቅር መመዘኛው ነው።


በቀረው የጥቅሱ ክፍል ደግሞ፤ ስለቀደመውና ስለአዲሱ የግንኙነትና እርሱና ተከታዮቹ ስለሚተሣሠሩበት መንገድ፤ ኢየሱስ ግልጽና የጠራ ልዩነት ያስቀምጣል። ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና። ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፤ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አሣውቄያለሁና።

ባሮች የምርጫ ነፃነት አልነበራቸውም። የራሳቸውንም ፈቃድ ለማድረግ አይሠሩም፤ ይልቁንም የጌታቸውን ፈቃድ ለማድረግ ታስረዋል። የጌታቸውንና የቤተሰቡን የጠለቀና የቀረበ ግንኙነት ሚስጥር ለመጋራት የሚችሉት አልፎ አልፎ ብቻ ነው። ምንም እንኳን በጌታቸው ቤት ውስጥ ቢኖሩም፣ ቢሠሩም፣ ቢበሉም፣ ቢጠጡም፣ ቢተኙም የሚሠራውን ነገር አያውቁም። ቤተሰቦችና ባልንጀሮች ግን እንዲህ አይደሉም። ለእርሱ የቅርብ ሆነው እንዲመላለሱ እድል የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ በህይወቱ ግላዊ የሆኑ ሁኔታዎችን እንኳን እንዲካፈሉ ተፈቅዶላቸዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ "ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም። ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ።" ለተከታዮቹ እያላቸው ያለው፤ "ከዚህ ቀደም የነበረውን ተልዕኮን ለመፈጸም ያህል ትታዘዙኝ እንደነበረው ባለ መታዘዝ ግንኙነታችን እንዲቀጥል

አልፈልልም። ከዚህ በኋላ እንደ ባሪያ እንድታስቡ አይገባችሁም። ከአባቴ የተማርኩትን ሁሉ እናንተ ወዳጆቼ ስለሆናችሁ ሁሉን በግልጽ አካፍላችኋለሁ።"

በተዘዋዋሪ መንገድ ኢየሱስ የተናገረው "ከአባቴ የተማርኩትን ሁሉ ታውቁት ዘንድ አላደረኩምን?" ሲል ነው። የቅርብ ወዳጆቹና ተከታዮቹ ስሆኑት ደቀመዛሙርት ለሌላ ለማንም ያልገለጸውን ለእነርሱ የተናገረው ምን ነበር? ህይወቱንና ልቡን ለእነርሱ ከፍቶላቸው ነበር። ያስቀረባቸው እንዳች አልነበረም። ኢየሱስ ለሀዘበ የሚናገረው በምሣሌ ነበር፤ በኋላ በግል ከወዳጆቹ ጋር ሲሆን ግን እያንዳንዱን ነገር በግልጽ አብራርቶ ይነግራቸዋል፤ (ማር 4÷33 ይመልከቱ)። ከእነርሱ ጋር እየኖረና በቅርበት ሆኖ እየሠራ፤ ከእነርሱ ጋር የማይኖርበት ጊዜ ሲመጣ ሀላፊነትን መሸከም እንዲችሉ ያሰለጥናቸውና ያዘጋጃቸው ነበር።



ወዳጆች እርስ በእርሳቸው መሰካከሩንና ከፍጡን፣ ደስታቸውንና ሀዘናቸውን ይካፈላሉ።

የባልንጀርነት አንዱ መለያ ጠባይ እርስ በእርሳቸው መልካሙንና ክፉውን፤ ደስታቸውንና ሀዘናቸውን መካፈላቸው ነው። ወዳጆችን የቅርብ ካልሆኑ ሌሎች ሰዎችና ብዙውን ጊዜ የቤተሰብ አባላት ከሆኑት እንኳን የሚለያቸው ነገር ይህ ነው። ከኢየሱስ ጋር አብሮ በነበራቸው የቆይታ ጊዜ በወዳጅነታቸው ምክንያት ወደፊት ስለሚደርሰው መጥፎና አስደሣች ያልሆኑ ነገሮች አስፍሷቸዋል። ታልፎ እንደሚሰጥ፣ እንደሚያዝ፣ እንደሚመታ፣ እንደሚገረፍና ጢሙንም እንደሚነጭ ተናግሯቸዋል። እንደሚሰቀል፣ እንደሚሞትና እንደሚቀበር፣ በሦስተኛውም ቀን ከመቃብር እንደሚነሣ ገለጸላቸዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ ጋር ወዳጆች በመሆናቸው ምክንያት እንደሚጠሉ፣ እንደሚናቁ እንደሚሳደዱና እንደሚገድሏቸውም እንኳን አስታውቋቸዋል። በተጨማሪም ሁልጊዜም ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና በእርሱ ሃይልና ስልጣን እንደሚኖሩ አረጋግጠላቸዋል። የደበቃቸው እንድም ነገር አልነበረም። ያስቀረባቸው ቁልፍ ሚስጥር ከቃሉም የጋረደባቸው እንዳች የለም። እንዲህ አይነቱ የተከፈተ ልብና ግልጽነት የእውነተኛ ወዳጅነት ምልክቱ ነው።

ወዳጆች እርስ በእርሳችሁ ግዴዜና እውነተኞች ናችሁ

ኢየሱስ ክርስቶስ ለወዳጆቹ እነዚህን ሊሆኑ ያሉትን ነገሮች ሁሉ አስቀድሞ ማሣወቅ የፈለገው፤ ነገሮቹ በተከናወኑ ጊዜ ተዘጋጅተው እንዲቆዮ ነው። "እንዳትሰናከሉ ይህን ነግሬአችኋለሁ . . ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ ይህንን ታስቡ ዘንድ ነግሬአችኋለሁ" (ዮሐ 17፥1-4)። ነገሮች በሆኑ ጊዜ መደነቅ እንዲሆንባቸው አልፈለገም።

ይህ አንድን ጠቃሚ እውነት ያሣየናል። ወዳጆች እርስ በእርሳችው ግልጽና እውነተኞች ናቸው። ይህ መርህ ደግሞ በባልና ሚስት መካከል ካለው ግንኙነት ይልቅ በየትኛውም ስፍራ ጠቃሚ አይሆንም። በብዙ ትዳሮች ውስጥ ትልልቅ ከሆኑት ችግሮች አንደኛው ባልና ሚስት እንደወዳጅ ሊተያዩ ያለመቻላቸው ነው። ወዳጆች ከመሆን ይልቅ "ባሮች" ናቸው፤ ባልና ሚስት ከመሆን ይልቅ በእጅጉ ወንድምና እህት ናቸው። ልክ ለቤተሰቦቻቸውና አንግዳ ለሆኑ በሩቅ ለሚያውቋቸው ራሳቸውን ግልጽ ማድረግ እንደሚችግራቸው ሁሉ፤ እርስ በእርስም እንዲሁ ናቸው። ብዙ ሰዎች ውስጣዊ ማንነታቸውን ለወላጆቻቸው ወይም ለስጋ ወንድሞችና እህቶቻቸው እያካፍሏቸውም። ከፍ ያለውን አላማቸውን፣ ውስጣዊ ስጋታቸውን፣ የከበረ ስነምግባራዊ አቋማቸውንና የከፋ ድክመታቸውን በግልጽ አውጥተው አይናገሩም። ይሁንና አነኝህኑ ነገሮች ለወዳጆቻቸው ይገልጹላቸዋል። በባልና በሚስት መካከል በእውነትና በግልጽነት ባህሪ ላይ የተመሠረተ ባልንጀርነት፤ ደስተኛ፣ ስኬታማና ታዳጊ የሆነ ትዳር ለመመስረት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

ብዙ ጥንዶች ወደ ጋብቻ የመጡት ስለ እራሳቸው ሁሉንም ነገር ሣይነጋገሩ ነው። በአንዳንድ መንገዶች ይህ የሚጠበቅ ነገር ነው። ገና ከመጀመሪያው ሁሉንም ነገር ለመገላለጥ የማይቻል ነገር ነው። ምክንያቱም አንዳንድ ነገሮች በግልጽ የሚወጡት ግንኙነት ከጊዜ ጋር እያደገ ሲመጣ ነው። ይሁን እንጂ ተጋቢዎች እርስ በእርስ መተዋወቅ የቻሉትን ያህል ሊተዋወቁ ያስፈልጋቸዋል። በጋብቻው መሠዊያ ፊት ከመቆማቸው በፊት መልካሙንና ክፉውን ሁሉ ሊነጋገሩት ይገባል።

ከጋብቻ በፊት ያለ የመተዋወቅና የእጮኝነት ጊዜ በግልጽ ለመተዋወቅ እጅግ ጠቃሚ ወቅት ነው፤ ይህንና እጅግ ብዙውን ጊዜ ወንዶችና ሴቶች ትኩረታቸውን የሚሰጡት ሁልጊዜ ጥሩ

የሆነውን ባህሪያቸው ለሌላው በማሣየት ነው። ጥንቃቄ የሚያደርጉትም ይህንኑ መልካም ጎናቸውን ብቻ ለመግለጽ ነው። ለጓደኝነት ግንኙነታቸውን እንዳያጡት በመስጋት በችግሮቻቸው ዙሪያ የሚራመዱት በጥንቃቄ በመሆኑ፤ ሌላውን ወገን ሊያስከፉ የሚችሉ ጠባዮቻቸውን ወይም በሌላው ላይ የሚያስተውሉትን እንግዳ የሆነ ባህሪ ገልጸው አይነጋገሩም። ገና በዚህ ደረጃ ላለግንኙነታቸው እርስ በእርሳቸው ግልጽ መሆንን ሲማሩ ካልቻሉ፤ ከጋብቻቸው በኋላ እነዚህ ነገሮች በግልጽ መታየት ሲጀምሩ ድንገት ከእንቅልፋቸው መባነን ይጀምራሉ።



ተጋቢዎች እርስ በእርሳቸው መተዋወቅ የቻሉትን ያህል ሲተዋወቁ ያስፈልጋቸዋል። በጋብቻ መሰዊያቸው ላይ ከመቆማቸው በፊት መልካሙንና ክፉውን ሁሉ ሊነጋገሩ ይገባል።

አንድ ምሳሌ እንውሰድ፤ ዮሐንስ የቁጠኝነት ችግር ካለበት፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ለሣራ ሳይዘገይ እጅግ ፈጥኖ እውነተኛ መሆን አለበት። "በቁጣ ጉዳይ ላይ ችግር አለብኝ። በቀላሉ ነው ቁጣ የምለው። በዚህ ችግሬ ላይ ጌታ እየሠራኝ መሆኑን አውቃለሁ፤ ይሁንና ገና ብዙ ይቀረኛል። ይህን ልነግርሽ የፈለኩት በተቆጣሁ ጊዜ ይቅርታ እንድታደርጊልኝና ጉዳዩን ከግል ሁኔታዎች ጋር እንዳታገናኚው ነው"። በዚህ ሁኔታ የዮሐንስ ቁጣ ለመጀመሪያ ጊዜ መፈንዳት ሲጀምር ሣራ በጉዳዩ እንግዳ አትሆንም።

ሣራ ደግሞ ምናልባትም በሌሎች ሰዎች ላይ የምትቀና ወይም በሆነ ባልሆነው ሁሉ ነቀፌታ የምታዘወትር ልትሆን ትችላለች። በዚህ ጉዳይ ላይ ለዮሐንስ ግልጽ ሆናለት ከሆነ ችግሩ ከመከሠቱ በፊት ሊፈጠር የሚችለውን አለመግባባት ማስወገድ ይችላሉ። በእንድነት ሆነው ሌሎች ችግሮችን ለማስወገድ ይሠራሉ፤ እንዳቸው በእንዳቸው ውስጥ ከአንዳቸው በላይ ለማደግ ይረዳዳሉ።

እንዲህ ዐይነቱ እውነተኝነት ማደግ ካለበት፤ በእውነቱ የትኞቹም ባለትዳሮች በአንድነት እፎይታ ስሜት ሊለማቸው ይገባል። እንዲህ አይነቱን የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር አስፈላጊው ነገር በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መከባበርና መተማመን ሊሆን ይገባዋል። ምንም እንኳን እንዲህ ያሉት ብቃቶች የሚያድጉት በፍቅር ውስጥ ቢሆንም ሊንከባከቧቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ባልንጀርነትና ፍቅር በእጅጉ የተያያዙ ነገሮች

ናቸው። "ወዳጅ በዘመኑ ሁሉ ይወዳል፤ ወንድምም ለመከራ ይወለዳል" (ምሣ 17÷17) "ብዙ ወዳጆች ያሉት ለው ይጠፋል፤ ነገር ግን ከወንድም አብልጦ የሚጠጋጋ ወዳጅ አለ" (ምሳ 18÷24)። "እፉ እጅግ ጣፋጭ ነው፤ እርሱም ፈጽሞ ያማረ ነው፤ እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ፤ ውዴ ይህ ነው ባልንጀራየም ይህ ነው"። (መኃ 5÷16)።

ጋብቻ በለምች መካከል ከሚፈጠር ግንኙነት ሁሉ የላቀው ሊሆን ወዳጅነትም የዚህ ግንኙነት ከፍተኛው ደረጃ ነው። ሁሉም ባለትዳሮች ወደዚህ ከፍታ ለመድረስ ትኩረታቸውን በዚህ አቅጣጫ ማድረግና እስከሚደርሱበትም ድረስ ማረፍ አይገባቸውም። በዚህ አረገድ ማደጋቸውን ሊያቆሙ አይገባም። እውነተኛ የሆነ ወዳጅነት ምንም ያህል ጊዜና እድገት የማያታክቱት ስፋትና ጥልቀት ያለው ነው።

ጋብቻ በሰዎች መካከል ከሚፈጠር ግንኙነት ሁሉ የላቀው ሲሆን ወዳጅነትም የዚህ ግንኙነት ከፍተኛው ደረጃ ነው።

ወዳጅነት፤ ባልና ሚስት ከፍተኛ ወደሆነ የከበረ እንቁነት ለመለወጥ የሚያደርጉትን አሃደዊ ውህደት የሚያቀላጥፍ ነው። ጋብቻ በመንፈሣዊው አለም ውስጥ፤ በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መካከል ብቻ ሣይሆን፤ በእግዚአብሔር እና በፈጠረው የለው ዘር መካከል ያለውንም ግንኙነት የሚያሣይ ምድራዊና ስጋዊ የሆነ ስዕል ነው። ወዳጅነትም በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ፍጹማዊ አህዳዊነትና የመቀራረብ ባህሪ ከማሣየት አልፎ፤ በኤደን ገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን ይደሰቱበት የነበረውን በእነርሱና በእግዚአብሔር እንዲሁም እርስ በእርሳቸው የነበራቸውን የግንኙነት ባህሪ ያመላክታል።

የእግዚአብሔር እቅድ፤ ሀጢያት ያፈራረሰውን በእርስና በሰዎች መካከል የነበረውን የባልንጀርነት ግንኙነት እንደገና ማደስ ነው። ይህ የሰለጠነው አሰም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሚመስል በግልጽና በእውነት ልዩ በሆነ አመለካከት ሊያይ ያስፈልገዋል። የትኛውም የግንኙነት እይነት ይሁን በጋብቻ ከሚደረግ ግንኙነት ይልቅ ቅርበት የለውም፤ ጋብቻም ባልና ሚስት እውነተኛና ቅርበት ያላቸው ባልንጀሮች የሚሆኑበት ነው።

የሰለጠነው ማህበረሰብ በጋብቻ ተቋም ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት ተቋቁሞ፤ የለው ፍጥረት በምድር ላይ እስሚቆይበት ጊዜ ድረስ ይዘልቃል። ጋብቻን የመሠረተውና ያፀናው እግዚአብሔር ራሱ በመሆኑ፤ ፍጥረታዊውን አለም ወደ ፍጻሜው እስኪያመጣው ድረስ ችግሮችን ተቋቁሞ ይጸናል። ምንም ያህል ስነምግባራዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ቢቀያየሩም፤ ጋብቻ እንደምንጊዜውም እንደ አለት ጠንክሮ፣ በለብአዊው ግንኙነት ውስጥ ከሚታወቁት አስተሳሰቦች ሁሉ የላቀ ሆኖ እንደጸና ይኖራል፤ ምክንያቱም ጋብቻ የእግዚአብሔር ሣጣብ ነው።

ዛሬም ቢሆን ጋብቻ የከበረ ሣጣብ ነው!

መርሆዎች

1. ባልና ሚስት አንዳቸው የሌላቸው የቀረበ ባልንጀራ ሊሆኑ ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ የላቀ ግንኙነት የለም።
2. እውነተኛ ባልንጀርነት፤ በቤተሰባዊነት ከተሣሰረው ግንኙነት ይልቅ ከፍ ያለ ነው።
3. የተከፈተ ልብና ግልጽነት የእውነተኛ ባልንጀርነት ምልክቶች ናቸው።
4. ወዳጆች እርስ በእርሳቸው ግልጾችና እውነተኞች ናቸው።
5. በባልና በሚስት መካከል ያለ፤ በእውነትና በግልጽነት ባህሪው የተገለጠ ባልንጀርነት፤ ደስተኛ፣ ስኬታማና ታዳጊ ስሆነ ትዳር እጅግ አስፈላጊው ነገር ነው።
6. ወዳጅነት፤ ባልና ሚስት ከፍተኛ ወደሆነ የክበረ እንቁነት ሰመሰወጥ የሚያደርጉትን አሃዳዊ የሆነ ውህደት የሚያቀላጥፍ ነው።

ክፍል ሁለት

ፍቅርንና የልብን ሚስጥር መረዳት

ምዕራፍ ስንድ

ፍቅር የምንለው ደህንነ ነው

ባለቅኔው አንድ ጊዜ፤ "ማፍቀር ማለት በህይወት መኖር፤ በህይወት መኖርም ማፍቀር ነው" ሲል ጻፈ። ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ግን ምን ማለቱ ነው? ባለቅኔው ያለውን ነገር ከቶ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም። ይህ ፍቅር የሚባል ነገር ምንድን ነው?

ምናልባትም የእውነተኛ ፍቅር ባህሪ ምን እንደሆነ በጥልቀት የተስላሰለ፣ ውይይት የተካሄደበት፣ የአደባባይ መወያያ ርዕስ የሆነ፣ የተተነተነና ብዙ የታለመለት ሌላ ርዕሰ ጉዳይ ላይኖር ይችላል። ፍቅርን በየትም ሥፍራ አናገኘዋለን፤ በዘፈኖች በመጽሐፍቶቻችን፣ በቴሊቪዥኖቻችንና በሲኒማ መስኮቶች ሁሉ። የፍቅር ጨዋታ ሁልጊዜም በምላሣችን ጫፍ ነው። ከሀሣባችንና ከንግግራችንም ብዙ አይርቅም።

ይሁን እንጂ፤ በዚህ ሁሉ አስተሳሰባችን፣ ንግግራችን፣ ውይይታችን፣ የአደባባይ ክርክሮቻችን በኋላ ስንቶቻችን ነን ፍቅርን በእግባቡ የተረዳነው? እውነተኛ ፍቅር ምን እንደሆነ በእርግጥ አውቀናል? ፍራኮይስ ደክ ደላ ርችፎህከልድ የተባለ በአሥራ ስባተኛው ክፍለ ዘመን የኖረ ፈራንሣዊ ደራሲና የስነ ምግባር መምህር፤ አስመካከቱን እንዲህ ሲል ጽፎታል፤ "እውነተኛ ፍቅር ልክ እንደ መንፈስ ነው፤ ብዙዎች ያወሩለታል የሚያዮት ግን በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው።" እውነተኛ ፍቅርን በሚመለከት ህቀኛ የሆነውን እውቀት ለማግኘት ፈታችንን ወዴት እንመልስ? ዓለም እጅግ ብዙ የፍቅር ጽንሰ ሀሣቦችን ታቀርብልናለች፤ በእርግጥ ግን የታመኑ ናቸውን? የታወቀው የምዕራቡ ዓለም ባህል ፍቅርን ሞቅ ካለ ስሜት፤ ከተፈጥሯዊ መስብና ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር አቻ ወደማድረጉ አመዝኗል። ስለ ፍቅር የሚሰጡ እንዲህ ያሉ አመለካከቶች፤ በምናነባቸው መጻሕፍትና መጽሄቶች በምንሰማቸው

ዘፈኖችና በምንመለከታቸው የቲሌቪዥን ፕሮግራሞችና ሲኒማዎች በየዕለቱ ወደ አይምሯችን እንዲጠቀጠቁ ይደረጋል::

በዘመናዊው ማህበረሰብ ውስጥ የሚታዮትን የግንኙነቶች ፈጥነው መፍረስ፣ የተበተኑ ትዳሮች፣ የተለያዩ ቤተሰቦችን ስንመለከት የሚነግሩን አንድ እውነት አለ፤ ይሄውም ስለ ፍቅር ያለን አመለካከት በእስከፊ ሆኔታ የታዛባ መሆኑን ነው::

ሁሉን ነገር በአግባቡ ለመረዳት እጅግ ጠቃሚው ነገር ባለሙያን ማማከር ነው:: የጎልፍ እጨዋወታችንን ማሻሻል የምንፈልግ ከሆነ ወደ ጎልፍ ጨዋታ አሰልጣኝ፤ ፒያኖ ለመጫወት እቅድ ካለንም ወደ ሰለጠነ የፒያኖ መምህር መሄድ ያስፈልገናል:: በፍቅር ጉዳይ ላይ ባለሙያው ማነው? ፍቅርን ከእግዚአብሔር በላይ የሚረዳው የለም:: በሀያዋን ፍጡር መካከል እንደ መካከለኛ መሠረት ድንጋይ አድርጎ ፍቅርን መፍጠርና መመሥረት ብቻ ሣይሆን፤ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ራሱ ፍቅር ነው:: (1ዮሐ 4÷8፤16 ይመልከቱ) ፍቅር የእግዚአብሔር ባህሪ መግለጫው ነው::

ፍቅር የእግዚአብሔር ባህሪ መግለጫው ነው::

እግዚአብሔር ስለ ፍቅር ምን ይላል? በዓለም እጅጉን ከተዘወተረው አመለካከት በተቃራኒ መንገድ በመጽሀፍ ቅዱስ እንደተገለጸው፤ ፍቅር በቅድሚያ በሰው ፍልቅ ስሜት ላይ ያረፈ ላይሆን የልብ ጉዳይ ነው:: የሰው ፍልቅ ስሜት ትእዛዝን የሚቀበል አይደለም፤ በአንድ ነገር ወይም ሰው ላይ ያለህ ስሜት ምን ሊሆን እንደሚገባው ማንም ትእዛዝ ሊሰጥህ አይችልም:: ነገር ግን በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ ጌታ የእርሱ የሆኑትን እንዲፋቀሩ ሲያዛቸው እንመለከታለን:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ፍቅር ትእዛዝ ነው:: እስኪ ይህን ምሣሌ ተመልከተው፤ "እምላክህን እግዚአብሔርን፣ በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹምም ሃይልህ ውደድ" (ዘዳ 6÷5)::

"አትበቀልም፣ በህዝብህም ልጆች ቂም አትያዝ፤ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ " (ዘሌ 19÷18)::

"እኔ ግን እላችኋለሁ . . . ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ " (ማቴ 5÷44)::

"እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፤ እንደወደድኳችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ አለጣችኋለሁ" (ዮሐ 13÷34)::

"እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" (ዮሐ 15÷12)::

"እርስ በእርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ሌላውን የሚወድ ህግን ፈጽሞታልና" (ሮሜ 13÷8)::

"ህግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፣ እርሱም ባልንጀራህን እንደራስህ ወደድ የሚል ነው" (ገላ 5÷14)::

"ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹምም ሃሣብህ ውደድ:: ታላቂቱና ፈተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት:: ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች:: እርስዋም፤ ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት:: በእነኝህ በሁለቱ ትእዛዝ ህግም ሁሉ ነብያቱም ተለቅለዋል" (ማቴ 22÷37-40)::

ልንወድ ትእዛዝ ከተሰጠን እንዴት አድርገን ነው የምንፈጽመው? እግዚአብሔርን መውደድ ምን ማለት ነው? ሌላውን ሰው መውደድስ ማለት ምን ማለት ነው? ትርጉም ያለውን ግንኙነት በአግባቡ ለመረዳት እነዚህ ጠቃሚ ጥያቄዎች ናቸው:: በዚህ ዘመን የፍቅርን ጽንሰ ሀሣብና ምንነት በአግባቡ ባለመገንዘብ ምክንያት ብዙ ግንኙነቶች ፈራርሰዋል::

ፍቅር በቅድሚያ በሰው ፍልቅ ስሜት ላይ ያረፈ ሳይሆን የልብ ጉዳይ ነው::

የችግሩ አንድ ክፍል ደግሞ ቢያንስ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪው ዓለም፤ የቋንቋው ውሱንነት ነው:: በእንግሊዝኛው ለፍቅር ያለን አንድ መሠረታዊ ቃል ብቻ ነው:: በመሆኑም እጅግ ሰፊ በሆኑ ጫፎች መካከል ባሉ ጉዳዮችና ነገሮች ላይ የሚሰማንን ስሜትና በነገሮቹ ላይ የምናሳድረውን ዝንባሌ በዚሁ አንድ ቃል

እንገልፃለን:: "ከአይብ የተሠራ ጣፋጭ ኬክ እወዳለሁ" ወይም "ውሻየን እወዳለሁ" እንላለን:: እንደዚሁ ደግሞ "ልጆቼን እወዳለሁ" እንዲሁም "ሚስቴን እወዳታለሁ" ወይም "ባሌን እወደዋለሁ" እላለን:: ይህም ብቻ አይደለም በዚሁ ቃል "ወደ ባህር ዳርቻ የመዋኛ ስፍራ መሄድ እንወዳለን" ወይም ወደ "መናፈሻ ስፍራ መሄድን እንወዳለን" እያለን እንናገራለን:: በእነዚህ ከፍተኛ የአይታና የመጠን ልዩነት ባላቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያለንን ስሜትና በነገሮቹ ወይም በሁኔታዎቹ ላይ ያለንን ዝንባሌ ለመግለጽ የተጠቀምነው ያንኑ አንድ ፍቅር የሚል ቃል ነው:: ከአይብ ለተሠራው ጣፋጭ ኬክና ለልጆቻችን ወይም ለባለቤቶቻችን ያለን ፍቅር ተመሣሣይ ወይም እኩል እንደማይሆን ተስፋ እደርጋለሁ::

በጣም ብዙ ቋንቋዎች፤ በተለይም መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ የተጻፈባቸው የኢብራይስጥና የግሪክ ቋንቋዎች ፍቅርን ለመግለጽ እንደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የውስንነት ችግር አይታይባቸውም:: ጥንታዊው የግሪክ ቋንቋ ፍቅር ለሚለው ቃል አራት ቃላትን ይጠቀማል:: እነዚህም ፊሊዮ፣ ስቶርጅ፣ ኢሮስ እና አጋፔ የሚሉ ሲሆኑ፤ እያንዳንዱ ቃል ከሌላኛው በተለየ መንገድ አይነትንና መጠንን ለይቶ የሚገልጽ ነው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፊሊዮ እና አጋፔ የሚሉት ሁለት ቃላት ብቻ የሚገኙ ቢሆንም ፍቅር ምን እንደሆነና እንዳልሆነም ሊገልጹልን የሚችሉ በመሆኑ አራቱንም በቅርበት እንመለከታቸዋለን::

ፊሊዮ፤ የባልንጀርነት ፍቅር

ፊሊዮ የሚለውን ቃል መሠረታዊ የሆነውን ትርጉም የወሰድን እንደሆነ "ባልንጀርነት" የሚል ትርጉም የሚሰጠን ሲሆን፤ በግሪክ ቋንቋ ለፍቅር መግለጫ የሚነገር አጠቃላይ ቃል ሆኖ እናገኘዋለን::

ይህ ቃል የሚያመለክተው አንድ ሰው ለባልንጀራው ወይም በግል ለሚያውቀው ሰው ያለውን ፍቅር ነው:: ፊሊዮ ቤተሰባዊነት ለሌለበት ባልንጀርነትና በግል ለምናውቀው ማንም ሰው ያለንን የፍቅር ደረጃ የሚገልጽ ቃል ነው::

ጥቅልና በግል ለምናውቀው ማንም ሰው የሚኖረንን ፍቅር የሚገልጽ ቃል በመሆኑ ፊሊዮ ወደ ጋብቻ ለሚወሰድ ፍቅር የምንጠቀምበት ቃል አይደለም:: ጋብቻ ፊሊዮ ከሚገልጽልን ፍቅር የጠለቀና የረቀቀ የፍቅር አይነትን የሚጠይቅ ነው:: ባልና ሚስት

እርስ በእርሳቸው የሚለማቸው የፍቅር ስሜት እንዲህ ያለ በቅርብ በሚተዋወቁ ጓደኞች መካከል ያለ ዓይነት ፍቅር ከሆነ፤ ትዳራቸው ወደ ችግር እየገሰገሰ ነው::

ፊሊዮ በማናችንም ውስጥ የሚገኝ ዓይነት ፍቅር ነው፤ ምክንያቱም ሁላችንም በተፈጥሯችን ማህበራዊ ባህሪ ስላለ ነው:: በተፈጥሯችን ከእኛ ጋር ተመሣሣይ ፍላጎት ወይም ዝንባሌ ባላቸው ሌሎች ሰዎች እንሳባለን:: እውነተኛ ጓደኝነት የህይወት ቅመም ነው:: ባልንጀራችን ጥልቅ የሆነ ሀሣባችንን የምናካፍለው፤ ውስጣዊ ማንነታችንን የምንገልጽለትና፤ ብዙውን ጊዜ የቤተሰባችን አባላት እንኳን የማያውቁትን ሚስጥር የምንጋራው ነው:: የሚያስፈልገን አንድ ነገር እጅግ ጥቂት ከሆኑ የቅርብ ጓደኞቻችን ጋር ትርጉም ያለውን ግንኙነት መቀባበል ብቻ ነው:: ፊሊዮ የሚገልጸው እንዲህ አይነቱን ፍቅር ነው::

እውነተኛ ጓደኝነት የህይወት ቅመም ነው

ፊሊዮ አወንታዊ የሆነና ለህይወታችን ጠቀሜታ ያለውን ፍቅር የሚገልጽ ይሁን እንጂ፤ ከፍ ያለውንና የጠለቀውን የፍቅር አይነት የሚገልጽ አይደለም:: እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ጥንቃቄ ካላደረግን ፊሊዮ ብዙውን ጊዜ በግንኙነታችን ላይ ችግር የሚያስከትሉ የተወሰኑ ባህሪያትን ሊያዳብር ይችላል:: ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በግዴታ ውስጥ የመግባት ዝንባሌ ነው:: ብዙውን ጊዜ ይህ የፍቅር ግንኙነት የሚመሠረተው በጋራ ጥቅም ላይ በመሆኑ ወደ እከከኝ ልከክልህ አይነት ግንኙነት ሊያመራ ይችላል:: በዚህ ግንኙነት ምክንያት እርስ በእርሳችን ለመቀባበል የመገደድ ጫና ሊሰማን ይችላል::

የፊሊዮ ሌላው የተለመደ ጠባይ በስብእናና በውጫዊ ሁኔታዎች ላይ ማዘንበሉና ማተኮሩ ነው:: ከእውነተኛ ፍቅር ጋር እስካላዛመድነው ድረስ ይህ ተፈጥሮአዊ የሆነና ምንም ችግር የማያስከትል ነው:: የስብእናችን ባህሪያትና ውጫዊ ማንነታችን ከጊዜ ጋር ይለወጣል፤ በመሆኑም እስከ ህይወት ዘመን ፍጻሜ የሚዘልቅ ቋሚ ግንኙነትን ለመመሰረት ብቻውን አስተማማኝ ነገር አይደለም:: በዚህ በስብእናና በውጫዊ ማንነት ላይ ማተኮር ብዙውን ጊዜ የፊሊዮን ግንኙነት ወደ አቻ ጥቅም ፈላጊነት ያዞረዋል:: በዚህ ረገድ ግንኙነት ከሚመሠረትባቸው ምክንያቶች እንደኛው በአንድም ይሁን በሌላ ደረጃ እርስ በእርስ ተቻችሎ ለመቀጠል ነው:: እንዲህ አይነቱ ጉዳይ ብዙም ትኩረት

ለማንሰጠው ግንኙነት እምብዛም ችግር የለውም፤ ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ይህን በጋራ ጥቅም የመቻቻልን ግንኙነት ባልን ወይም ሚስትን ለመምረጥ እንደ መመዘኛ አድርገው ይወስዱታል። የእንደዚህ አይነቱ አስተሳሰብ ዋንኛ ችግር፤ በሁሉም ነገር የሚቻቻሉ ወይም በጣም አቻነት ያላቸው ሁለት ሰዎች የሚመሠረቱት የረዥም ዘመን ግንኙነት ውስጥ፤ ያንኑ ተቻቻይነት ወይም አቻነት ይዘን እንዘልቃለን ብለው ማለባቸው ነው። ከብዙ ተሞክሮ እንደተገኘው ልምድ እጅግ ስኬታማ የሆነው ግንኙነት የሚመሰረተው፤ አንድም ተቃራኒ ወይም ቢያንስ ቢያንስ ልዩነት ባላቸው በሁለት ሰዎች መካከል ነው። በልዩነታቸው ምክንያት ሚዛናቸውን ጠብቀው ይጓዛሉ፣ አንዳቸው የአንዳቸውን ጉድለት ይሞላሉ። በማግኔት ውስጥ እንዳለው ግንኙነት ሁሉ ሁለት ተቃራኒነት ያላቸው ባህሪያት እርስ በእርስ ይሣሣባሉ።

እንግዲህ በእንደዚህ ያለ መመዘኛ፤ ፊሊዮ በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ፍቅር ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ተሟልተው እስከተገኙ ድረስ ግንኙነቱ ይቀጥላል። ሁኔታዎቹ ከተቀየሩ ግን ግንኙነቱም ይቀየራል። በግንኙነት ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች ከሌሎች እንድንጠብቅ ያደርጉናል፤ ከሌሎች የምንጠብቀው ነገር ደግሞ አይቀሬ ወደሆነ ግራ የመጋባት ውጤት ላይ ያደርሰናል። ለዚህም ነው በሁኔታዎች ላይ የሚመሠረት ግንኙነት ለረዥም ጊዜ ታቅዶ ለሚመሠረት እንደ ትዳር ላለ ግንኙነት በቂ የማይሆነው። ባልና ሚስት በእርግጠኝነት አንዳቸው የሌላኛው፤ የፊሊዮ ጠባይ ባለው ትህትና በተሞላው መተሳሰብ ባልንጀራ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ ግንኙነታቸው በዘላቂነት እንዲቀጥል ከዚያ የዘለለ ነገር ያስፈልጋል።

ስቶርጅ፤ ቤተሰባዊ ፍቅር

ከፊሊዮ ጋር በቅርብ የተያያዘ ቢሆንም፤ ግሪክኛ "ስቶርጅ" የሚለውን ቃል የሚገለገለበት እጅግ በቀረበ ቤተሰባዊ ትስስር ውስጥ ላለ ግንኙነት ነው። ስቶሮጅ ወላጆች ለልጆቻቸው ልጆችም ለወላጆቻቸው ያላቸውን ርህራሄና መተሣሰብ ያለበትን ፍቅር የሚገልጽ ነው። በተጨማሪም ለወንድሞች፣ ለእህቶች፣ ለቤተሰቡ ቀጣይ የዘር ግንድ ማለትም ለአያቶች፣ ለአጎቶች፣ አክስቶች፣ ለወንድምና ለእህት፣ ወንድና ሴት ልጆች፣ ያለንን ተቆርቋሪነትና የቅርብ ስሜት የሚያመለክት ነው።

ስቶርጅ ከፊሊዮ ይልቅ በቅርብ ለተሣሰረ ግንኙነት የተሰጠ ቃል ነው፤ ምክንያቱም ስቶርጅ ቤተሰብንና በቤተሰብ መካከል ያለን ግንኙነት ያመለክታል። በትክክል እዚያ ጋ ነው በአንደዚህ አይነቱ ግንኙነት ውስጥ ያለው ቁልፍ አደጋ የሚያርፈው። ቤተሰባዊ ግንኙነት ያለን በመሆኑ ቤተሰቦቻችንን፣ ወንድሞችና እህቶቻችንን እንደምንወድ እነርሱም እንደሚወዱን እንገምታለን። ያ ፍቅር አስተማማኝ እንደሆነም እንቆጥረዋለን፤ ምንም ቢሆን እኮ ቤተሰብ ነን፤ እይደለንም እንዴ? ምንም እንኳን ብዙውን ጊዜ ያ ፍቅር እውነተኛ ፍቅር ቢሆንም እሁንም አደገኛ ግምት ነው። ችግሩ ቤተሰብ መሆን አስተማማኝ ግንኙነት ነው ማለት አይደለም። በደም ትስስር መያያዝ ባልንጀራ አያደርገንም።

እስኪ የራስህን በቤተሰብ ውስጥና ከቤተሰብ ውጭ ያለህን ግንኙነት ተመልከት። ለአንተ የቅርብ የሆነ ማነው? በጣም ግላዊ የሆነውን ሃሳብህንና ስሜትህን የሚጋራው ማን ነው? ከማንም ሌላ ሰው ይልቅ እውነተኛውን አንተን የሚያውቅህ ማነው? ከቤተሰብ አባሎችህ አንዱ ወይስ ጓደኛህ? እውነት እንነጋገር ካልን ብዙ ጆችን ከቤተሰቦቻችን ይልቅ ከባልንጀሮቻችን ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳለን እምነን እንቀበላለን። ወላጆቻችንንና ወንድም እህቶቻችንን በሚመለከት፣ ግንኙነት እንዳለንና ቤተሰቦችም ስለሆንን እንደምንወዳቸው እንገምታለን። አንድ ለው፤ "ቤተሰቦችህን ትወዳለህ?" ብሎ ቢጠይቅህ፤ ምናልባትም በፍጥነት፤ "አዎን እወዳቸዋለሁ" ብለህ ትመልስ ይሆናል። ጠያቂህ እንደገና፤ "ለምን?" ብሎ ቢጠይቅህ እንዲህ ትልም ይሆናል፤ "ማለት . . . ምክንያቱም ቤተሰቦቼ ናቸው"። ሁሉም ነገር የሚያበቃው እዚህ? ነው። ምንም እንኳን ለወላጆቻችንና ለወንድም እህቶቻችን ያለን ፍቅር እውነት ቢሆንም፤ የምንወዳቸው ግን መውደድ ስላለብን እንደሆነ የሚያመለክት ስሜት አለን። ከቤተሰባችን አባላት ውስጥ በማንኛውም ላይ ይሁን የጥላቻ ስሜት በውስጣችን ሲቀሰቀስ፤ ብዙውን ጊዜ የበደለኝነት ስሜት ይሰማናል። እነርሱን የመውደድ ስሜት ባይሰማንም በዚያው ሰዓት ግን ልንወዳቸው እንደሚገባ ይሰማናል።

ከዚህ እይታ አንጻር፣ ስትሮጅ ከፊሊዮ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምክንያቱም የመገደድን ስሜት በቀላሉ ስለሚያመጣ ነው። የምንወደው መውደድ ስለፈለግን አይደለም፤ ይልቁንም መውደድ ስላለብን ነው። የግዴታ ጫናን ይፈጥራል፤ ጫና ደግሞ ውጥረትን ያስከትላል፤ ውጥረት እየጨመረ ሲሄድ ማንኛውም ግንኙነት አደጋ ላይ ይወድቃል። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ባለ ግንኙነት

ተጠላልፈን ከሆነ፤ ግዴታችንን መወጣት ባልቻልንበት በማንኛውም ጊዜ የበደለኝነት ስሜት ይሰማናል። ሰዎች ሌሎች ሰዎች ሰለ እነርሱ መኖር ባልቻሉ ጊዜ የሚሰማቸው ስሜትም ይሄው ነው፤ ንዴትና መራራነት።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከልም ይህ የተለመደ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸውና እንደ ጌታቸው አምነው የተቀበሉ አማኞች፤ በጥቅሉ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት አድርገው ያስባሉ፤ እርስ በእርሳቸውም በክርስቶስ እህቶችና ወንድሞች እንደሆኑ አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ አመለካከት በትክክል ከእግዚአብሔር ቃል እውነት ጋር የሚሄድ ነው። በገላቲያ 6፥10 ጳውሎስ "የሀይማኖት ቤተ ሰዎች" እያለ ይናገራል። ዕብ 2፥11 እኛ ሁላችን በክርስቶስ የተቀደሰን ለእርሱ ወንድሞች ሆነናል፤ የእርሱም ቤተሰብ አባላት ሆነናል ሲል ይናገራል። በ1ኛ ጴጥ 4፥17 ጴጥሮስ እማኞችን "የእግዚአብሔር ቤተሰቦች" ሲል ይጠራቸዋል።በደም የተሣሠሩ ቤተሰቦች ግንኙነት ፡እሰን ብለው እንደሚገምቱት፤ ቤተሰባዊነታቸው እስተማማኝነት ያለው ግንኙነት እንዳላቸው እንዲቆጥሩ እንደሚያደርጋቸውና በአይምሮ ላይ ግዴታን የሚያሣድር ተጽእኖ በመፍጠሩ እንደሚችገሩ ሁሉ፤ በቤተሰባዊነት ስሜት ምክንያት የክርስቲያኑ ማህበረሰብ በዚሁ ተግዳሮት ይቸገራል።

ምንም እንኳን በአይምሮ ተቀርጾ በተቀመጠ ምክንያታዊነት ሰነገሮች መልሰ እንድንሰጥ ግዴታዊ የሆነ ስሜት የሚያሣድግብን ቢሆንም፤ ስትሮጅ በደም ለተሣሠረ ቤተሰብም ይሁን ለክርስቲያናዊ የእምነት ቤተሰብ አስፈላጊ፤ ጠቃሚና ሃያል የሆነ ሰብአዊ የህይወት ልምምድ ነው። ቤተሰባዊ ፍቅር ለአንድ ማህበረሰብ ሰላምና የተረጋጋ ህይወት መሠረታዊ የሆነ ነገር ነው። ቤተሰብ የማህበረሰቡ የመሰረት ድንጋይ ነው። ቤተሰብ የሚበተን ከሆነ ማህበረሰብ ያንኑ መንገድ ፈጥኖ ይከተላል።



ቤተሰባዊ ፍቅር ሰለንድ ማህበረሰብ ሰላምና የተረጋጋ ህይወት መሠረታዊ የሆነ ነገር ነው።

ሲርስ፤ ዩታዊ ፍቅር

ኢሮስን ጾታዊ ፍቅር ነው ብለን ስንናገር በጣም እርግጠኞች ሆነን አይደለም፤ ምክንያቱም እርግጡን ሰመናገር ጾታዊ ግንኙነት ከእውነተኛ ፍቅር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ጾታዊ ግንኙነት

ያለ ፍቅር ሊደረግ ይችላል፤ ይህ ደግሞ ሁልጊዜም የሚደረግ ነው። ፍቅር ግን ያለ ጾታዊ ግንኙነት ብቻውን ሊቆም ይችላል። ፍቅርና ጾታዊ ግንኙነት የአንዳቸው ህልውና በሌላኛው ላይ ተጽእኖ ያለው አይደለም። በእግዚአብሔር እንደተመሠረተውና እንደ ጸናው ሀይማኖታዊና አንድ ለአንድ በሆነው ጋብቻ ውስጥ ጾታዊ ግንኙነት በራሱ ፍቅር ያይደለ፤ ነገር ግን ሞቅ ያለ፣ የቀረበና ውብ የሆነ ፍቅርን የመግለጫ መንገድ ነው። እዚህ ቦታ ላይ ነው ዓለማዊው አመለካከት ሙሉ ለሙሉ አቅጣጫውን አዙሮ የሚሄደው።

ጥንታውያን ግሪኮች የሰውን ተፈጥሯዊ አካል ውበትና ጾታዊ ግንኙነትን ከማምለክ ደረጃ አስኪደረሱ ድረስ በዚህ ነገር በጣም ይደሰታሉ። እንግዲህ ኢሮስ በማንኛውም ሁኔታ ለሚደረግ ጾታዊ ግንኙነት የሚሰጡት የፍቅር አይነት ነው። እንደገናም ኢሮስ ግሪኮች ለፍቅር አምላካቸው የለጡት ሰም ነው። ኢሮስን ማምለክ ደግሞ ከሌሎች ነገሮች ጋር ተደምሮ የጾታዊ ግንኙነት ሃይማታዊ ሥርዓትና ዝሙትን መፈጸምን ይጨምራል። ኢሮስ የተባለው አምላክ ዛሬም ቢሆን በማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል ውስጥ ከሞላ ጎደል አየተመለከ ይገኛል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በየቀኑ በኢሮስ መሠዊያ ፊት ቀርበው ያመልካሉ ያንንም ፍቅር ብለው ይጠሩታል።



በእግዚአብሔር እንደተመሠረተውና እንደጸናው፤ ህይማኖታዊና አንድ ለአንድ በሆነው ጋብቻ ውስጥ ጾታዊ ግንኙነት በራሱ ፍቅር ያይደለ፤ ነገር ግን ሞቅ ያለ፣ የቀረበና ውብ የሆነ ፍቅርን የመግለጫ መንገድ ነው።

መሉና እውነታዊ በሆነ መልኩ፤ ኢሮስ የሚለው ቃል የጾታዊ ግንኙነት ፍላጎትን፣ ጠንካራ የሆነ መሻትን፣ ያለምንም የቅድስና ሃሣብ ወለን የለቀቀ ደስታን ለመቀዳጀት የሚደረግን ግንኝ ነት ያቀፈ ነው። ይህ ደግሞ መጠንንና ልክን ዘሎ የሄደ ነው። ኢሮስ የሚለውን ቃል የሚታካው ሌላ ሃሣብ "የሥጋ አምሮት" የሚለው ነው። መሠረታዊ ሀሣቡ ፈጽሞ በስግብግብነት ላይ ያረፈ በመሆኑ፤ ኢሮስ የስጋዊ አምሮቱን በሌላው ኪሣራ ለሚሟላት የመፈለግ ዝንባሌ አለው።

እንደ እውነተኛ ፍቅር ሣይሆን፤ ኢሮስ ፍጹም ሥጋዊ የሆነ ፍቅር ነው። ማዕከል የሚያደርገውም በአምስቱ ተፈጥሯዊ የስሜት ህዋሣት ማለትም በማየት፣ በማሽተት፣ በመሰማት፣ በመቅመስ፣ በመንካትና መነቃቃት ላይ ነው። ኢሮስ በባህሪው

ተፈጥሯዊ በመሆኑ የተነሣ ይህን ፍቅር የሚቆጣጠረው በሰው አካል ውስጥ ያለ ኬሚካላዊ ውህደትና እንቅስቃሴ ነው። ኢሮስ ሙሉ ለሙሉ የሚመራው በስጋ በመሆኑ፤ ሥጋ የፈቀደውን ሁሉ በማድረግ እርካታን ለማግኘት ይፈልጋል። ጾታዊ ፍቅር ፍልቀ ስሜታዊ ነው፤ ሃይልን የሚያገኘውም ከፍልቅ ስሜት ማዕከል ነው። በመሆኑም ስሜት ከፍና ዝቅ ባለ ቁጥር ይህም ፍቅር አብሮ ይዋዥቃል። በተቃራኒው እውነተኛ ፍቅር ፍልቅ ስሜት የማያንቀሳቅሰው ወይም የማይቆጣጠረው የተረጋጋ ፍቅር ነው።

በኢሮስ ብቻ የሚንቀሳቀስ ማንም ሰው፤ የጾታ ተጓዳኙን የሚመለከታት ወይም የምትመለከተው ልክ እንደ ጾታዊ ግንኙነት መገልገያ ዕቃ ብቻ ከመሆኑም በላይ አላማውም በዚህ ግንኙነት እሸናፊ መሆን ነው። የሰለጠነው ማህበረሰብ ብዙውን ጊዜ በጾታዊ ግንኙነት የሚጣመሩ ተቃራኒ ጾታዎች እርስ በእርላቸው የማሸነፍና ነጥብ የማስቆጠር ፋክክር ባለበት ግንኙነት ውስጥ "ፍቅር" እያሉ የሚጠሩትን አመለካከት ማበረታታቱ እጅግ አሳዛኝ ነው። በኢሮስ ላይ የተመሠረተው ግንኙነት የሚዘልቀው፤ በመጀመሪያው ደረጃ መቀራረብ ሰዎቹ እንዲቀራረቡ ያደረገው ተፈጥሯዊ መስብና ፍላጎት እስካለ ድረስ ብቻ ነው።

ኢሮስ በስግብግብ ባህሪው፤ ለሌላኛው ሰው ስሜትና ፍላጎት የሚጨነቅ ላይሆን፤ ፍላጎቱ የተመሠረተው ከዚያ ሰው ከሚገኝ ግለሰባዊ የወሲብ እርካታ ላይ ነው። ኢሮስ ስለ ሰብአዊነት አድናቆትና ክብር የሚያውቀው ጥቂት በመሆኑ ጥንቃቄ የሚያደርገውም በመጠኑ ነው። ፍላጎቱ ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ፤ መረን በተሰቀቀና ባልተገደበ፤ "ጥሩ ሆኖ ከተሰማህ አድርገው" በሚል ዘመናዊ ፍልስፍና መንፈስ የሚመራ ነው።

አጋፔ፤ መለኮታዊ ፍቅር

አራተኛውና ከፍተኛ የሆነው የፍቅር አይነት አጋፔ፤ በብዙ መንገድ እራሱን የቻለ ጎራ ነው። እጅግ ልዩ በሆነው ባህሪው ምክንያት ይህን አይነቱን ፍቅር ለመግለጽ የተለየ ቃል ያስፈልጋል። ጥልቁት ያለውን ትርጉሙንና የሚወክለውን ከፍተኛ የፍቅር ደረጃ ለመግለጽ እንደ ፊሊዮ፤ ስትሮጅና ኢሮስ የመሳሳት ተራ ቃላት ሊገልጡት ባለመቻሉ፤ የአዲስ ኪዳን ጸሀፊዎች በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት ከፍተቱን ለመድፈን አጋፔ የሚል ቃል ተጠቅመዋል።

ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውጭ አጋፔ በጥንታዊ የግሪክ ጽሑፍ ውስጥ ብቸኛ ለሆነ ልጅ ለሚሰጥ ፍቅር መግለጫ ሆኖ በአንድ ሥፍራና በአንድ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ተጠቅሷል። በመሠረቱ አጋፔ እጅግ በተለየ ሁኔታ መንፈሳዊ ባህሪ ያለው፤ ሰተለየ ጽንሰ ሀሳብ የሚሰጥ የተለየ ቃል ነው።

አጋፔ መለኮታዊ የሆነውን እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ፍቅርና ህዝቡም ለእርሱ የሚሰጡትን የፍቅር መልስ የሚገልጽ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ህዝብ እርስ በእርሱ እንዲዋደድበት የሚጠበቅበትን ፍቅርም ያካትታል። አጋፔ እንደ ፊሊዮ እና ስትሮጅ ምንም አይነት ግዳጅ የሌለበት፤ ከሌላው ወገን ምንም የማይጠብቅና ምንም ቅድመ ሁኔታዎችን የማያስቀምጥ ፍቅር ነው። አጋፔ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ፍቅር ነው። በስግብግብነት ባህሪው እንደሚገለጠው እንደ ኢሮስ ሣይሆን፤ አጋፔ በመጀመሪያ ደረጃና በላቀ ሁኔታ ለሌላኛው ወገን መልካም በማድረግ ለሁለንተናዊ ደህንነቱ የሚሠራ ነው። አጋፔ ራስን የሚያገለግሉበት አይነት ፍቅር ላይሆን ራስን የሚለጠቡበትና መስዋእትነት የሚከፍሉበት፤ ለሌላኛው ወገን ራስን የሚያፈሰበት ፍቅር ነው።



በስግብግብነት ባህሪው እንደሚገለጠው እንደ ኢሮስ ሣይሆን፤ አጋፔ በመጀመሪያ ደረጃና በላቀ ሁኔታ ለሌላኛው ወገን መልካም በማድረግ ሁለንተናዊ ደህንነቱ የሚሠራ ነው።

አጋፔ የሆነውን ፍቅር በላቀ ሁኔታ ሊገልጽ የሚችል አንድ ምሳሌ፤ ሃጢያትን የማያውቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ሃጢያተኞች ለሆንነው ስለ እኛ ስለሀሳችን፤ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ ነፍሱን በመስቀል ላይ አሳልፎ መስጠቱ ነው። ይሄ ሃሣብ እጅግ በታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውስጥ እንዲህ ተጠቅሶ እናገኘ ዋለን፤ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፤ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለመን እንዲሁ ወዷልና (አጋፔ)" (ዮሐ 3፣16)።

የአጋፔ ምንጭ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ውጭ ሊታወቅ ከቶ አይችልም። እግዚአብሔር አጋፔን የገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፤ ይህንኑ ፍቅር በክርስቶስ ኢየሱስ ስላመኑና ስለታመኑ የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑ ሁሉ ሰጥቷቸዋል። እነርሱ ደግሞ በዚህ ፍቅር እርስ በእርላቸው እንዲዋደዱ ይጠበቅባቸዋል።

እግዚአብሔር መለኮታዊ በሆነው አጋፔ በአለም ላይ ያሉትን ለዎች ሁሉ ይወዳል፤ ይሁን እንጂ በግል የህይወት ልምምዳቸው ይህንን ፍቅር የሚያውቁት የአማኙ ማህበረሰብ አባላት ብቻ ናቸው። በዓለም ላይ በስፋት እንደሚታየው አጋፔ እጅግም ያልታወቀ ነው።

በእግዚአብሔር እና በህዝቡ መካከል ያለውን በአጋፔ ላይ የተመሠረተውን ግንኙነት አስመልክቶ ከተሰጡት ምሣሌዎች መካከል አንዱ በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ እንደኛ ዮሐንስ መልዕክት ውስጥ ይገኛል።

"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ። እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀ እኛን እያወቀንም . . . ከመጀመሪያ የሰማችኋት መልዕክት፤ እርስ በእርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና . . . እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ህይወት እንደተሸጋገርን እናውቃለን፣ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል . . . እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ለጥቷልና በዚህ ፍቅርን እውቀናል፣ እኛም ስለወንድሞቻችን ነፍሣችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። (ዮሐ 3÷1፤ 11፤ 14፤ 16-18)።

"ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለተወለደ እግዚአብሔርን ስለሚያውቅ እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በህይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅር እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለህጢያታችንም ማስተሰሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጅ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድን አይደለም። ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በእርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በእርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል፤ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኗል" (1ዮሐ 4÷7-12)።

እነኝህ ጥቅሶች ስለ አጋፔ በርካታ ጠቃሚ እውነቶችን እንድንረዳ ይጠቅሙናል። በመጀመሪያ ደረጃ አጋፔ ፍጥረታዊ፣ ኬሚካላዊ ወይም ፍልቅ ስሜታዊ አለዚያም ፍልስፍና አይደለም። አጋፔ ስብእና ነው። 1ዮሐ 4÷8 እንደሚነግረን እግዚብሔር ፍቅር ነው። አጋፔን ስናውቅ ጽንሰ ሀሣቡን የፈጠረው ማን እንደሆነ

እናውቃለን። ኢየሱስ ክርስቶስ በሲጋ የተገለጠ አጋፔ ነው፤ እርሱም ፍቅር የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ሁለተኛ፤ አጋፔ አሀዳዊነት ነው። አጋፔን የሚያውቁ ሁሉ በልብም በመንፈስም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ናቸው፤ እርስ በእርሳቸውም አንድ ናቸው። ቀጥተኛ በሆነ ቋንቋ አጋፔ ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው። በክርስቶስ፤ ዝቅተኛ ማንነታችንን ወስደ፤ እርሱን እንድንመስል ያደርገን ዘንድ እኛን ሊመስል ተገባው።



ቀጥተኛ በሆነ ቋንቋ ስጋፔ ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው።

ሦስተኛ፤ አጋፔ በሌሎች ላይ ያተኮረ እንጂ በራስ ላይ ያተኮረ አይደለም። አጋፔ ያለምንም ማቋረጥ በመጀመሪያ በሌሎች ሁለተናዊ ደህንነት ላይ ያተኩራል፤ ባለማቋረጥም ለሌሎች መስጠት የሚችልበትን አጋጣሚ ይመለከታል። እውነተኛ ፍቅር ራሱን አሣልፎ እስካልሰጠ ድረስ ሙሉ አይደለም።

አራተኛ፤ አጋፔ የራስ ተነሳሽነት ነው። አጋፔ ሃላፊነትን የሚሸከምም ነው። ሌሎች ቀድመው እንዲንቀሣቀሱ የሚጠብቅ አይደለም። ሮሜ 5÷8 እንዲህ ይላል፤ "ነገር ግን ገና ሀጢያተኞች ሣለን ክርስቶስ ስ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል"። አጋፔ ቀድሞ የሚንቀሳቀስ ነው። ማንም ምላሽ ቢሰጥ ወይም ባይሰጥ አጋፔ ቀድሞ ይንቀሳቀሳል። ኢየሱስ "ሌሎች ለእናንተ ሊያደርጉላችሁ የምትሹትን እናንተ ደግሞ ለሌሎች አድርጉ" ይላል (ሉቃ 6÷31) አጋፔ የሚያደርገው እንደዚያ ነው። አጋፔ ቀዳሚውን እንቅስቃሴ ይጀምራል።

በመጨረሻም፤ አጋፔ ምርጫ ነው። የተመሠረተው በፍልቅ ስሜታችን ላይ ሳይሆን፤ አውቀንና ይሁነኝ ብለን በምንወስነው ውሳኔ ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚነግረን፤ እግዚአብሐር እንደሚወደን እንጂ ለምን እንደወደደን አይደለም። ለምን የሚል ነገር የለም። እግዚአብሔር የወደደን ፍቅር በመሆኑና ማፍቀርም ባህሪው ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር እኛን የወደደበት ምክንያት እኛን መውደድ በመፈለጉ ነው። የእርሱ ፍቅር ማንንም ከማን የማይለይና አድልኦ የሌለበት ነው። አጋፔ ማንን መውደድ እንዳለበት አይመርጥም፤ በቀላሉ የሚመርጠው መውደድን ነው። የሚወደደው ነገር "ምን" መሆኑ ዋጋ የሚሰጠው አይደለም።



አጋፔ ማንን መውደድ እንዳለበት ስደመርጥም፤ በቀላሉ የሚመርጠው መውደድን ነው።

ሆን ተብሎ በተወሰነ ውሣኔ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ አጋፔ የማይለዋወጥ ነው። ፍልቀስሜታዊ እንደሆነ ፍቅር አጋፔ የሚለዋወጥ አይደለም።

አጋፔ በአለም ላይ ብቸኛው እውነተኛ ፍቅር ከመሆኑም በላይ አንዳንድ ጊዜ "ፍቅር" እያልን ስምንጠራቸው ሁሉ መሠረት ነው። ፊሊዮ፣ ስትሮጅ፣ ኢሮስ በአግባቡ ከተገነዘብናቸውና በተገቢው ሁኔታ ውስጥ ከተሰማመድናቸው ለአጋፔ እውቅና የሚሰጡና ውበትን የሚጨምሩ ናቸው። ይሁን እንጂ ማናቸውም ቢሆኑ በራሳቸው ትርጉም ያለውና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ለመገንባት በቂ መሠረት ሊሆኑ አይችሉም። ለዚህ በቂ የሆነው አጋፔ ብቻ ነው።

አጋፔን መረዳት ማለት የስውን የልብ ሚስጥር ለመረዳት ቁልፍ የሆነ ጉዳይ ነው። ይህንን ለማድረግ አንጻባራቂ የከበረ ጌጥ የሆነውን የአጋፔን በርካታ እውነታዎች ልንዳስስ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር፣ እኛ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር፣ እኛ ለአራሣችን ያለንን ፍቅርና ለሌሎች በተለይም ለሚስቶቻችንና ለእጮኞቻችን የሚኖረንን ፍቅር ሁሉ ልንመለከት ግድ ነው።

መርሆዎች

1. ፊሊዮ፤ እጅግም ቅርበት በሌለው ደረጃ ባለ ግንኙነት ውስጥ ሰዎችን የምንወድበት ፍቅርና፤ ለምናውቃቸው ሰዎች ያለን መውደድ የሚገለጽበት ነው።
2. ስትሮጅ፤ ወላጆች ለልጆቻቸው ልጆችም ለወላጆቻቸው ያላቸውን ርህራሄ አዘል መውደድ የሚገልጽ ነው።
3. ኢሮስ፤ ጠንካራ ጾታዊ ግንኙነትን የሚፈጥር፤ ሃይለኛ መሻትን የሚያነሣሣ፣ ቅድስና በሌለው ሁኔታ ከፍ ያሰ ስሜታዊ እርካታን ለማግኘት ሲባል ልኩን ለቆ የሄደ፣ ድርሻንም ያላገናዘበ የፍቅር አይነት ነው።
4. አጋፔ፤ መለኮታዊ የሆነውን ፍቅር የሚገልጽ፤ እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውንና ህዝቡም ለእግዚአብሔር የሚሰጡትን የምላሽ ፍቅር የሚያመለክት ፍቅር ነው።
5. አጋፔ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩር አይደለም።
6. አጋፔ ራሱን የሚሰጥ ፍቅር ነው።
7. አጋፔ ስብእና ነው።
8. አጋፔ አሃዳዊነት ነው።
9. አጋፔ በሌሎች ላይ ያተኮረ ነው።
10. አጋፔ የራስ ተነሳሽነት ነው።
11. አጋፔ ሃላፊነትን የሚሸከም ነው።
12. አጋፔ አስቀድሞ ለድርጊት የሚንቀሣቀስ ነው።
13. አጋፔ ምርጫ ነው።
14. አጋፔ ፍፁም አይለወጥም።

ምዕራፍ ሁለት

እግዚአብሔር ይመስላል

ስለ እውነተኛ ፍቅር ምንነት ለመረዳት የምንፈልግ ከሆነ፤ ከምንጩ መጀመር ይኖርብናል። ገጣሚው እንዲህ ሲል ተቀኘ፤ "ፍቅር ለመኖር ነው፤ መኖርም ለፍቅር"። ይህ አባባል እጅግም ድንበሩን ዘሎ የሄደ አይደለም፤ ምክንያቱም ፍቅርም ሆነ ህይወት መነሻቸው ከአንድ ምንጭ፤ ከፈጣሪ ከእግዚአብሔር ነው። "በእርሱ ህያዋን ነንና እንንቀሣቀሳለን እንኖርማለን" (ሐዋ 17÷28) ተብሎ እንደተጻፈው በህይወት መኖራችን በእርሱ ነው። አጋፔ የሆነውን ፍቅር ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው። "ወዳጆች ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሆነ <u>የሚወደውም ሁሉ</u> <u>ከእግዚአብሔር</u> ስለተወለደ <u>እግዚአብሔርን ስለሚያውቅ</u> እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔር አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና" (1ዮሐ 4÷7-8)።

ለሰው ልጅ ከተገለጠት እውነቶች ሁሉ እጅግ የላቀው እግዚአብሔር እኛን እንደሚወደን የተገለጠው እውነት ነው። እግዚአብሔር ከሠራውና ለህያዋን ላደረገው ነገር ሁሉ መሠረቱ ያረፈው በፍቅር ላይ ነው። ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ባሉት ገጾቹ ሁሉ እንደምንመለከተው የመጽሐፍ ቅዱስ አብይ ጭብጥ እግዚአብሔር ስለ እኛ ያለው ፍቅር ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ የትኛቹም የህይማኖት መጽሐፍት እንዲህ ያለውን መልዕክት አላካተቱም። እግዚአብሔር አቅዶና አስቦበት ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታዎን ሳያስቀምጥ ሁሉንም ለዎች እንደሚወድ የሚያውጅ በመሆኑ፤ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የተለየ መጽሐፍ ነው።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።

"አንተም አምላክህ እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደሆነ ለሚወዱትም ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንና ምህረቱን እስከ ሽህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደሆነ እወቅ" (ዘዳ 7÷9)።

"በዘላለም ፍቅር ወድጀሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብኩሽ" (ኤር 3÷13)።

"ነገር ግን ገና ሃጢያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቷልና፤ እግዚአብሔር ስለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5÷8)።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፤ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ወዷልና" (ዮሐ 3÷16)።

"ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ፤ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ህይወት ለጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና" (ኤፌ 2÷4-5)።

"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ" (1ዮሐ 3÷1)።

"ፍቅር እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢያታችን ማስተሠሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም" (1ዮሐ 4÷10)።

መጽሐፍ ቅዱሳችን፤ እግዚአብሔር ስለእኛ ያለውን ፍቅር በግልጽ ይናገራል፤ የማይገልጽልን አንድ ነገር ለምን እንደወደደን ነው። ለምን ብሎ ነገር የለም። ለምን የሚል ፍቅር በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ፍቅር ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አይደለም። የተወደድንበት ምክንያት ስለወደደን ነው። እኛን መውደድ ባህሪው ስለሆነ ነው። ለምን እንደወደደን ምክንያቱን ለመፈተሽ የምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ውጤቱ ከንቱ ድካም ነው።



እግዚአብሔር ስቅዶና ስስቦበት ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታዎች ሳያስቀምጥ፤ ሁሉንም ሰዎች እንደሚወድ የሚያውጅ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የተለየ መጽሐፍ ነው።

እንዲህ ይሁን እንጂ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ባህሪና የብቃት ደረጃ ከመጽሀፍ ቅዱስ ብዙ ልንማር እንችላለን። ስለ እውነተኛ ፍቅር እውነተኛ የሆነ እውቀት ለማግኘት የመነሻ ስፍራችን ያ ነው። ስለ እግዚአብሔር ፍቅር አንዳች ነገር እስክንረዳ ድረስ፤ ፍቅርን በማናቸውም አይነት መልኩ፤ በተለይም በህይወታችን ወሳኝ በሆኑ ከወዳጆቻችንና ከቤተሰቦቻችን ጋር

የሚኖሩን ግንኙነቶች ላይ ስለሚያስከትለው ውጤት አንዳች ልናውቅ አንችልንም።

ፍለጋችን ራሱ ወደ ፍጥረት መጀመሪያ ይወስደናል።

ዝፈጠርና ዝመሬት

የመጀመሪያዎቹ ሦስት የዘፍጥረት መጽሐፍ ምዕራፎች፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተክታትለው ስለሚመጡ ነገሮች መሠረት ይጥሉልናል። ዘፍጥረት አንድ እና ሁለት እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለውን የመጀመሪያ እቅድ ይገልጹልናል፤ ምዕራፍ ሦስት ደግሞ ያ አቅድ እንዴት እንደተደናቀፈ የሚገልጽ ሲሆን ሌሎቹ የመጽሐፉ ምዕራፎች ደግሞ እግዚአብሔር ነገሮችን እንደገና እንዴት እንዳስተካከላቸው ይናገራሉ። ጉዳዩን በቀላሉ ለማብራራት፤ መጽሐፍ ቅዱስ በዘገበው ታሪክ ገነት ተመሠረተች፣ ገነት ጠፋች፣ ገነት እንደገና ታደሰች። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተከናወኑት ነገሮች ሁሉ የሰውን ዘር እንደገና ለማደስና ፍጥረትን ሁሉ በዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች በነበረበት ሁኔታ እንደገና በማደራጀት ዓላማ ላይ ተመሥርተው የተከናወኑ ናቸው።

ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድንና ሁለትን በአግባቡ ለመረዳት፤ በምዕራፎቹ የተጠቀሱትን "እንፍጠር" እና "እንሥራ" የሚሉትን ሁለት ጠቃሚ ቃላት ልዩነት በግልጽ መረዳት ያስፈልጋል። በምዕራፍ 1 የሰፈሩ ሦስት ጥቅሶች እነኝህን ልዩነቶች ያሳዩናል።

እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሣላችን እንሥራ፤ በባህር አሶች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፤ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው አለ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው። በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉዋት፣ ግዟትም የባህርን አሳዎች፣ የሰማይን ወፎች እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ህያዋን ፍጡር ሁሉ ግዟቸው፤ ብሎ ባረካቸው።" (ዘፍ፡ 1፥26-28 አዲሱ መደበኛ ትርጉም)።

በቁጥር 1 እና 27 "ተፈጠሩ" ለሚለው ቃል የዕብራይስጡ አቻ ቃል "ባራ" የሚል ሲሆን፤ በቁጥር 26 ላይ እንስራ ለሚለው ቃል አቻ ቃሉ "አስአህ" የሚል ሆኖ እናገኛለን። በዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፍ ውስጥ በጠቅላላው "ባራ" የሚለው

ቃል ለባት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፤ "አስአህ" የሚለው ቃል ግን አሥር ጊዜ ተጠቅሷል። ምንም እንኳን እነኝህ ሁለት ቃላት በተወሰነ ደረጃ አንዳቸው አንዳቸውን እየተኩ በተለዋዋጭነት በጥቅም ላይ የዋሉ ቢሆንም በትርጉሞቻቸው ላይ ግን መሠረታዊ የሆነ ግልጽ ልዩነት እናስተውላለን። "ባራ" ማለት ከምንም ነገር ውስጥ አውጥቶ ለአንድ ነገር ቅርጽ መስጠት ነው። ፍጹማዊ በሆነ ስሜቱ ፍጥረትን የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ተያይዞ የተነገረ ቃል ነው። ምክንያቱም እርሱ ብቻ ነው ከምንም ነገር ውስጥ አንዳች ነገር መፍጠር የሚችል። ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ብቻውን ነበር፤ አንዳች ነገር አልነበረም። ከዚህ ባዶነት ውስጥ እግዚአብሔር እንዲሆኑ በመፍቀድና ህልውና እንዲኖራቸው በመናገር በቀላሉ ለማይንና ምድርን ፈጠረ። አንግዲህ "ባራ" የሚባለው ይህ ነው።

በሌላ በኩል አስአህ ማለት ለአንድ ለነበረ ነገር ቅርጽን መለጠት ነው። በቁጥር 26 ከተጠቀለው በተጨማሪ አስአህ፤ በእግዚአብሔር የተደረገውን ጠፈር (1፥7)፤ ፀሐይና ጨረቃን (1፥16) የምድር አራዊትን (1፥25)፤ ምድርንና ሰማይን (2፥4) እንዲሁም የወንድ ረዳት የሆነችውን ሴት መፈጠር ለማመልከት ተጠቅሷል።

በእነዚህ "ባራ" እና "አስአህ" በተሰኙት ሁለት ቃላት፤ በእግዚአብሔር የመፈጠር ሥራ ውስጥ ሁለት የተለዩ አቅጣጫዎችን እንመለከታለን። ይህም የአንድን ነገር ከባዶ ውስጥ መፈጠርና አስቀድሞ ከተፈጠረ ቁስ አካል ውስጥ ሌላ ነገርን የመፍጠር ሂደት ነው። በየትኛውም አቅጣጫ ይሁን መርሀ ግን አንድ ነው፤ እግዚአብሔር የሚፈጥረው በመናገር ነው።

በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ውስጥ "እግዚአብሔርም አለ . . " የሚል ቃልና ቃሉንም ተከትሎ የተለየ የመፈጠር ሂደት ሲከናወን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ይሁን ብሎ የሚፈጥር አምላክ ነው። ነገሮችን የሚያከናውነው በመናገር ነው። ቃላት ሃሣብን፤ ያልተገለጠውን ውስጣዊ ሀሳብ የሚገልጡ ናቸው። ስለዚህ ሀሳብ ያልተነገረ ቃል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ሃሣቡን የሚገልጥ ነው። እግዚአብሔር ከመናገሩ በፊት ያስባል። እግዚአብሔር አንድ ነገር ከመናገሩ በፊት፤ አስቀድሞ ያንን ነገር አስቦታል። ምንም ነገር ከማድረጉ

በፊት፤ የሚያደርገው ነገር ምስል ወይም ስዕል በእርሱ ዘንድ አለ። በመጀመሪያው፤ ስለሚፈጥራቸው ነገሮች ሁሉ ያሰበውን ሀሣብ በመተግበር እግዚአብሔር ነገሮችን ፈጥሯል። ማንኛውም ህልውና ያገኘ ነገር ሁሉ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ሀሣብ ውስጥ የነበረ ነው።



በመጀመሪያው፤ ስለሚፈጥራቸው ነገሮች ሁሉ ያሰበውን ሀሣብ በመተግበር እግዚአብሔር ነገሮችን ፈጥሯል።

በዘፍጥረት መጽሀፍ የመጀመሪያው ምዕራፍ እንደ ተገለጸው እግዚአብሔር አንድን ነገር "ሰማድረግ" አስአህ ሲዘጋጅ፤ አስቀድም "ለፈጠረው" ነገር-ባራ ይናገራል፤ እናም ከተናገረው ከዚያ ነገር ውስጥ እግዚአብሔር ያቀደው ነገር ይወጣል። ይህንን በምሣሌ ለማስረዳት፤ እግዚአብሔር ምድርን በአትክልቶች ለመመላት በፈለገ ጊዜ፤ እግዚአብሔር የተናገረው ለምድር ነው።

"እግዚአብሔርም ምድርን ዘር የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወገኑ ዘሩ ያለባትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ። እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔር ያ መልካም እንደሆነ አየ።" (ዘፍ 1÷11-12)።

ጌታ በሰማይ ላይ ከዋክብት እንዲሆኑ በፈለገ ጊዜ፤ ሰሰማያት ተናገረ። "ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ" (ዘፍ 1÷14)፤ በባህር ውስጥ አሣዎች እንዲኖሩ በፈለገ ጊዜ ለውሃው ተናገረ፤ "ውሃ ህያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ . . ." (ዘፍ 120)፤ የምድር አራዊት እንዲኖሩ በፈለገ ጊዜ እንደገና ለምድር ተናገረ፤ "ምድርም ህያዋን ፍጥረታት እንደ ወገኑ እንስሳትንና ተንቀሣቃሾችን የምድር አራዊት እንደ ወገኑ ታውጣ . . ." (ዘፍ 1÷24)።

የፍጥረት መሠረታዊ መርህ ከሆኑት ነገሮች አንዱ፤ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ለቀጣይ ህይወት አስፈላጊ የሆነውን ነገር የሚያገኙት ከተፈጠሩበት ነገር መሆኑ ነው። ዕጽዋትና እንስሳት ለህይወት አስተማማኝ የሆነውን ነገር ለማግኘት መጠጊያቸው ምድር ነች፤ ምክንያቱም ከምድር ተገኝተዋል። አሣዎች የህይወት ዋስትናቸው ውሃ ነው፤ ምክንያቱም የተገኙት ከዚያ ነው።

ህያው የሆነውን የሰውን ፍጥረት ስንመለከት ግን ታሪኩ ለየት ያለ ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍ የመጀመሪያው ምዕራፍ ግልጽ እንዳደረገው፤ ቢያንስ በሦስት ምክንያቶች ከሌሎች ፍጥረታት አፈጣጠር ይልቅ የሰው ልጅ አፈጣጠር የተለየ ነው። በመጀመሪያ፤ የሰውን መፈጠር ለማመልከት ሁለቱም "ባራ" እና "አስአህ" የሚሉት ቃላት በተለያየ ስፍራ ተጠቅለዋል። ይህ ምናልባትም በክፊል ሁለቱ ቃላት አንድን የተወሰነ ነገር ለማመልከት በተለዋዋጭነት ገብተው በመሆኑ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ከዚህ የተለየ ነገር እንዳለ አምናለሁ። እጅግ በጸና እውነታዊ እይታ፤ ሰው የተፈጠረም የተደረገም ነው። እግዚአብሔር "ሰው" ብሎ የጠራቸውን መንፈሳዊ ህልውናዎች ፈጠረ "ባራ"፤ በመቀጠልም ወንድና ሴት የሆኑት አካላት በውስጡ የሚያድሩበትን ፍጥረታዊ "ቤት" ከምድር አፈር አበጃቸው "አስአህ"።

ይህ ወደ ሁለተኛው ነጥብ ያመጣናል። እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ሲዘጋጅ፤ ተክሎችና እንስሣት በተፈጠሩ ጊዜ እንዳደረገው ለምድር አልተናገረም፤ ወይም ከዋክብት እንዲኖሩ በፈለገ ጊዜ እንዳደረገው ለጠፈር አልተናገረም። እግዚአብሔር ለውን ለመፍጠር በተዘጋጀ ጊዜ የተናገረው ለራሱ ነበር። "እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" (ዘፍ 1÷26-27)። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፤ ለራሱ በተናገረበት ጊዜ ከእርሱ የወጣው እንዲሁ መንፈስ ነበር። እንደ ሰብአዊነታችን፤ እኛ መንፈሣዊ ህልውናዎች ነን፤ በመሆኑም ከሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ የሚለየን ይሄ ነው። እርግጥ ነው መላእክት መንፈሳዊ ህልውናዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ እንደኛ አይደሉም፤ ይህ ደግሞ ወደ ሶስተኛው ነጥብ ይወስደናል።



እንደ ሰብአዊነታችን፤ እኛ መንፈሣዊ ህልውናዎች ነን፤ በመሆኑም ከሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ የሚለየን ይሄ ነው።

እግዚአብሔር የፈጠረን በመልኩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ሥፍራ ይህንን ገለጻ ስለመላእክት ወይም ስለ ሌሎች ፍጥረታት አልተናገረም። ከእግዚአብሔር ፍጥረቶች ሁሉ በእግዚአብሔር መልክና እንደምሣሌውም የተፈጠርን ሰዎች ብቻ ነን። በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርን መንፈሣዊ ህልውናዎች

በመሆናችን፤ እኛ የተለየን ነን። እግዚአብሔር የፈጠረን እርሱን እንድንመስል አድርጎ ነው።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ስመቀበል ተፈጥሯናል

እዚህ ላይ የተዘወተረ ጥያቄ ይነሣል፤ "እግዚአብሔር ለውን ለምን ፈጠረ?" እግዚአብሔር ሁሉን በሁሉ፣ ራሱም ሙሉ የሆነ ከሆነ፤ በመልኩና በምስሉ መንፈሣዊ ህልውና ያለውን ፍጥረት ለመፍጠር ምን አነሣሣው? መልሱ የሚገኘው "ፍቅር" በሚለው ቃል ውስጥ ነው። ይህን ሣጣብ ላብራራው።

እግዚአብሔር ለእኛ ራሱን የገለጠው በተለያየ መንገድ ነው፤ ይሁን እንጂ በተለይ የተገለጸው በቃሉ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። እያንዳንዱ ገጽ ስለ ማንነቱና ስለ ባህሪያቱ በርካታ ነገሮች ይነግሩናል። እርሱ ቅዱስ፣ ጻድቅ እና ፍጹም ነው። እርሱ ሁሉን ቻይ፣ ሃያልና ብርቱ ነው። እግዚአብሔር በሁሉም ሥራ በአንድ ጊዜ የሚገኝ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችልና ሁሉን የሚያውቅ ነው። እርሱ ታማኝ ነው። እግዚአብሔር እንዲህና ከዚህም በላይ ነው። እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ የሆነ፣ በራሱ ብቁ የሆነ፣ ምንም ነገር የማይፈልግና ማንም ጉድለቱን የማይሞላለት ነው። ሁሉን በሁሉ በመሆኑም እግዚአብሔር "ሙሉ" ነው፤ ይህም እግዚአብሔር "ብቻውን" መሆኑ የሚገለጥበት ሌላው መንገድ ነው። ይህ ማለት እግዚአብሔር እኩያ የሌለው የተለየ ነው፤ እንደርሱ የሚመስል ማንም የለም ለማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ይናገራል፤ ችግር ካልነው ችግሩ የሚነሣው እዚህ ስፍራ ነው። እግዚአብሔር ብቻውን ነው ብለናል እንደገናም እግዚአብሔር ፍቅር ነው ብለናል፤ ይሁንና ፍቅር ብቻውን ሊኖርም፣ ሙሉ ሊሆንም አይችልም። ፍቅር ሙሉ እና ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የሚወደደው አንድ ነገር ያስፈልጋል። ፍቅር በባህሪው ራሱን የሚገልጽ ነው፤ በመሆኑም ራሱን የሚገልጥበት አንድ ነገር መኖር አለበት። ራሱንም ለመግለጽ ራሱን መስጠት አለበት። በዚህ ምክንያት ፍቅር ተቀባይ ሊኖረው ይገባል።

በመጀመሪያው እግዚአብሔር ሁሉን በሁሉ የሆነ ብቻውን ያለ ነበረ። እርሱ ፍቅር ነበረ፤ እንደ ፍቅርነቱ ደግሞ መስጠት ይፈልግ ነበረ፤ ይሁን እንጂ የሚለጠው ማንም ተቀባይ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሥላሴዎች እንደሆነ ይገልፃል።

ራሱን በሦስት የተለያዩ ስብእናዎች የሚገልጥ አንድ አምላክ ነው- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ። በዚህ ሦስትነት ውስጥ ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ያለማቋረጥ ራሱን እየገለጸ ይኖራል። ምንም እንኳን ዘላለማዊ የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር ሁልጊዜም ራሱን ሊሰጥ ቢፈልግም፤ ብቻውን ስለነበርና ማንም ስላልነበረ፤ እግዚአብሔር ይህንን ፍቅር የሚቀበል ለራሱ ማዘጋጀት ነበረበት።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅር ደግሞ መስጠትን ይፈልጋል፤ መስጠትም ለጭውን የሚመስል ተቀባይ ይፈልጋል። ያንን ተቀባይ እውን ለማድረግ እግዚአብሔር ለራሱ ተናገረ፤ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር . . . እግዚአብሔርም ለውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክም ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" (ዘፍ 1፥26-27)።

እንደ እግዚአብሔር መልክ መፈጠር ማለት፤ ሌሎች ነገሮችንም ጨምሮ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ ሁሉ እያንዳንዳችን መንፈሳዊ ህልውና ሆነን መፈጠራችን ነው። በመንፈሣችን ጾታ የለንም፤ ምክንያቱም መንፈስ ጾታ የለውም። እግዚአብሔር የፈጠረን የእርሱን ፍቅር እንቀበል ዘንድ እንደ እርሱ መንፈሳዊ ህልውና ያለን አድርጎ ነው። ከዚያ ቀጥሎ ነው ምድርንና በእርስዋ ያለውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ መግዛት እንችል ዘንድ ጉልህ ጾታዊ ልዩነታችን የተገለጸበትን ፍጥረታዊ አካላችንን የሠራው። መንፈሣዊ ህልውና ያለን ሆነን የተፈጠርነው የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመቀበል አላማ ነው። ወንድና ሴት ሆነን የተፈጠርነውም በአንድነት ሆነን የተፈጠሩትን እንድንገዛና የእግዚአብሔር ረዳቶች እንሆን ዘንድ ነው።



መንፈሳዊ ህልውና ያለን ሆነን የተፈጠርነው የእግዚአብሔርን ፍቅር ስመቀበል ዓላማ ነው። ወንድና ሴት ሆነን የተፈጠርነውም በአንድነት ሆነን የተፈጠረትን እንድንገዛና የእግዚአብሔር ረዳቶች እንሆን ዘንድ ነው።

እግዚአብሔር የወደደን እርሱ ፍቅር በመሆኑና ራሱንም በመውደድ ባህሪው መግለጽ ስለፈለገ ነው። እግዚአብሔር የወደደን የፈጠረን ለዚሁ ዓላማ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር የወደደን የእርሱን ፍቅር ለመቀበል ከመላእክትም ይሁን ከሌሎች ፍጥረታት መካከል እርሱን የሚመስል ማንም ስለሌለ ነው። ተቀባዩ የግድ ለጭውን መምሰል አለበት። በመልኩና እንደ ምሳሌውም

የተፈጠርን እኛ ብቻ ነን። ሰጭውን እግዚአብሔርን የምንመስል እኛ ብቻ ነን። ስለዚህም የእርሱን ታላቅ ፍቅር ለመቀበል ብቃት ያለን እኛ ብቻ ነን።

እግዚአብሔር ከእኛ በቀር የሚወደው ሌላ የለውም። ሰዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለምን እንደወደደን በጭራሽ የማይነግረን። ለምን የሚባል ነገር የለም። እግዚአብሔር የወደደን ለዚሁ ዓላማው ስለፈጠረን ነው። ከጅምር እስከጭርሱ የወደደን በመሆኑ እግዚአብሔር እንዲወደን እኛ የምናደርገው ነገር የለም።

ጳውሎስ በሮም ለሚገኙ አማኞች በፃፈው የአዲስ ኪዳን መልዕክቱ እንዲህ ሲል ጽፏል። "ነገር ግን ገና ኀጢያተኞች ሳለን፤ ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል (ሮሜ 5÷8)። ገና ኀጢያተኞች ሳለን እግዚአብሔር ይህን በሚያህል ፍቅር ከወደደን፤ ከዚያ ይበልጥ ይወደን ዘንድ እንዴት ሌላ ነገር ማድረግ እንችላለን? ለተነጣጠረ የእግዚአብሔር የፍቅር ቀስት ኢላማ ሆነን፤ ግልጽ በሆነው እይታው ውስጥ ሁላችን አለን።

እግዚአብሔር የወደደን ስለዚሁ ዓላማ ስለፈጠረን ነው።

የላተላይት ዲሾች ልዩ ልዩ ሞገዶችን ለመቀበል እንዲችሉ ተደርገው እንደተሰሩ ሁሉ የእኛም ስሪት እንዲሁ የእግዚአብሔርን ፍቅር መቀበል እንዲችል ተደርጎ የታቀደ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረን ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ለእነርሱ እጅግ ይቀናል፤ እናም ከእነርሱ ጋር ያለው ግንኙነት ቀጣይ እንዲሆን ማንኛውንም አስፈላጊ ነገር ሁሉ ያደርጋል። ሮሜ 5÷8 ይህንኑ እውነት ያረጋግጥልናል። ኀጢያት ይህንን ፍቅር የመቀበል ብቃታችንን ባበላሸብንና የግንኙነት መስመሩን ባቋረጠብን ጊዜ፤ ግንኙነቱን ለማስተካከልና ለማደስ እግዚአብሔር ልጁን ላከ።

እግዚአብሔር ዘር ይፈጥራል

እግዚአብሔር ለውን የፈጠረው ፍቅሩን እንዲቀበል ነው። ፍቅር ራሱን የሚገልጸው በመስጠት ውስጥ ነው። በራሱ ፍቅር ተነሳሽነት እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ ለፈጠረው ሰው ምድርን እንዲገዛ ስጦታን ሰጠ። የእግዚአብሔር እቅድ በምድር ላይ የተፈጠረው ሁሉ ለሰው ይገዛ ዘንድ ነበር። ሁሉን ከሚገዛ ከእግዚአብሔር እጅ በታች፤ ምድር የሰው ግዛትና መንግስቱ ትሆን ዘንድ የተሰጠች ነበረች።

በዚህ መንገድ ግን ነገሮች መስመራቸውን ጠብቀው መሄድ አልቻሉም። በዚያ በወደቀው መልአክ፣ የእግዚአብሔር እና የሰው የጋራ ጠላትና ፈታኝ በሆነው በሰይጣን ተገፋፍተው በልጅነት መብታቸው የተሰጣቸውን ምድርን የመግዛት ስልጣን፤ ጊዜያዊ ሰይኖና የተሟሟተ ራስን በመግዛት ስሚገኝ ደስታ "የተከለከለውን ፍሬ" በመብላታቸው አሟልፈው ሸጡ። አንዳች ተቃውሞ ባለማሟየታቸው ትክክለኛ ስፍራቸው በሰይጣን በሀይል ተነጠቀ፤ እርሱም በምድር የገዥነት ዙፋን ላይ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣን አገኘ።

ይህ ሁኔታ ግን እግዚአብሔርን አላስደነቀውም። ይህ እንደሚሆን ያውቅ ነበር። ወዲያውኑ ገና ከአለም ፍጥረት በፊት አስቀድሞ ያዘጋጀውን እቅድ፤ ይሄውም እቅድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰው ምላሌ ወደ ዓለም በመላክ፤ ለሰው ዘር ተህድሶን በማምጣት ሰውን ወደቀደመው ምድርን የመግዛት ስልጣኑ የመመለስና ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ህብረት እንደገና የመቀላቀል እቅድ ነው። ይሁንና የእግዚአብሔር ልጅ ይህን እቅድ ለመፈጸም ለው መሆን ለምን አስፈለገው? እግዚአብሔር በቀላሉና በቀጥታ ራሱ ጣልቃ በመግባት ወዲያውኑ ነገሮችን ለምን አላስተካከለም? ሰዚህ የምንለጠው መልስ ስለ አገዛዝ ወዳለው አጠቃላይ ጉዳይ ወደ ኋላ ይመልሰናል።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ለሰው ምድርን የመግዛት ስልጣን የሰጠው በመሆኑ፤ ሰይጣን እንዳደረገው ይህን ስልጣን በሃይል አልነጠቀውም። የእግዚአብሔር ስጦታ ተመልሶ የሚወሰድ አይደለም። እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር የሚራመድ በመሆኑ ያለውን ሁሉ ያደርገዋል። የእግዚአብሔር ቃል ከሰው ድርጊት አንጻር የሚሰዋወጥ ሳይሆን በራሱ የቆመ ነው። መጽሀፍ ቅዱስ ደግሞ ደጋግሞ ይህንን እውነት ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር በፀጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትም (ሮሜ 11÷29)። እግዚአብሔር ምንም ነገር ይስጥ መልሶ ሊወስድ ቃሉን አያጥፍም።

"የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፤ የልቡም ሀሳብ ሰልጅ ልጅ ነው" (መዝ (33)÷11)።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ካቀደ፤ ያ እቅድ ሰዘላለም ነው። እግዚአብሔር የሰው ልጅ ምድርን እንዲገዛ ያቀደውን የመጀመሪያ እቅድ በጭራሽ አይሰውጠውም።

"ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ፀንታ ትኖራለች" (ኢሣ 40÷8)።

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ ማለት፤ ተናገረ ማለት ነው!

"ከአፌ የሚወጣው ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፡ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም" (ኢሳ 55÷11)።

እግዚአብሔር የሚናገረው ቃል ሁሉ ይፈጸማል።

እግዚአብሔር ለሰው ምድርን እንዲገዛት ሰልጣን ሲሰጥ፤ የሰጠው መሠረታዊ ነገር በዚች ፕላኔት ውስጥ የሚካሄዱትን ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች እንዲቆጣጠር ነበር። ይህ በማንኛውም መንገድ ሉአላዊነቱንና በጽንፈ ዓለሙ ሁሉ ላይ ያለውን የፈጣሪነት ጌትነቱን የሚነካ ነገር አይደለም። ይህ ማለት በቀላሉ ምንም እንኳን ምድርን ለመግዛት ሙሉ ሀጋዊ መብት ያለው ቢሆንም፤ በምድር ላይ ያለው ይህን ሥልጣኑን በራሱ ፈቃድ መገደብ መረጠ ማለት ነው። ይህን ሥልጣኑን መጠቀም ከፈለገ የሰውን ፍቃደኛ ትብብር ይጠይቃል።

እግዚአብሔር ቃሉን ያከብራል። የሰው ዘር የተወለደበትን ፍቅር እንደገና እንዲያገኝና ከኀጢያታችን ሁሉ ሊያጥበን እግዚአብሔር ሰብአዊ የሆነ ዘር ፈለገ።



እግዚአብሔር ምድርን ለመግዛት ሙሉ ሀጋዊ መብት ያለው ቢሆንም በምድር ላይ ያለውን ይህንን ሥልጣኑን በራሱ ፈቃድ መገደብ መረጠ።

በዚህ ምክንያት ነው እግዚአብሄር አብርሃምን የጠራው። እርሱና ሚስቱ ሣራ አንድ ልጅ እንኳን ባልነበራቸውና ዕድሜያቸውም ልጅ ለመውለድ ከተላለፈ በኋላ በልጅ ሊባርከው የተስፋን ቃል ሰጠው። እግዚአብሔር በአቀደው ጊዜ ውስጥ ዘሩን ወደ ዓለም ለማምጣት፤ ዘሩን የሚሸከሙና በነፃነት የሚሠራባቸው ሰዎች ያስፈልጉት ነበር።

የአብርሃምና የሣራ የቃል ኪዳን ልጅ የሆነው ተዓምራዊ ሀፃን ይስሀቅ ተወለደ። እርሱም መንትያ የሆኑ የራሱን ልጆች ያዕቆብንና ኤሣውን አፈራ። ያዕቆብም እስራኤል ተብለው

ለመጠራት ወደ አሥራ ሁለት ነገድነት ያደጉ የአስራ ሁለት ወንዶች ልጆች አባት ሆነ።

ከያዕቆብ ልጆች አንዱ የሆነው ይሁዳ ንጉስ ዳዊት የተገኘበት ዘር ነው። ኢየሱስ በስጋ የተገኘባቸው ማርያምና ዮሴፍ ሁለቱም ደግሞ ከዳዊት ሥርና ዘር ናቸው። ከአብርሃም እስከ ማርያም ድረስ ያለው ይህ የዘር ሃረግ፤ ልጁ ኢየሱስ ሀጋዊ በሆነ መንገድ ወደ አለም እንዲገባ እግዚአብሔር ይፈልግ የነበረውን ስብአዊ የዘር ሃረግ ሰጥተዋል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ውስጥ አንዱ፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ አንዳች ነገር ለማድረግ ሲዘጋጅ፤ ሁልጊዜም የሚሠራው ለእርሱ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ በሆነ፤ በጠራው ወይም በጠራቸው ሰዎች ውስጥ ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሚያደርገው ነገር ሰዎች የሚያሣዩት ተሣትፎ ቁልፍ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት ሲዘጋጅ መሴን ጠራው። ህዝቡን እስራኤልን ከምድያማውያን እጅ ሊታደጋቸው በፈለገ ጊዜ ጌዲዮንን ጠራው። እግዚአብሔር በማይታዘዙት ህዝቡ ላይ እንደሚፈርድባቸው ሊያስጠነቅቅ በፈለገ ጊዜ ኤልያስን፣ ኢሳያስን፣ ኤርምያስን፣ አሞጽንና ሌሎች ነብያትን ጠራ። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ለመላክ በፈለገ ጊዜ፤ በገጠር ትኖር የነበረችውን ትሁት የሆነች ድንግል ማርያምን እናት ትሆነው ዘንድ መረጠ። ኢየሱስ ክርስቶስ የመዳን ወንጌሉን መልዕክት ወደ ዓለም ሁሉ ለመላክ በተዘጋጀ ጊዜ ወንዶችንና ሴቶችን ጠራ-ቤተክርስቲያን! ቀባቸው ለተልዕኮም ሾማቸው።

ይህ ምላሌ የሚነግረን እግዚአብሔር የሚሠራበትን ለማመን የሚያስቸግር መርህ ነው። ያለ እግዚአብሔር አንዳች ልናደርግ አንችልም፤ እግዚአብሔርም ያለ እኛ ላይሠራ ይችላል። እግዚአብሔር በምድር ላይ ሊያደርግ ላቀደው ነገር ሁሉ፤ አስቀድሞም እንዲገዟት ለልጣን ከሰጣቸው ጋር በጋራ ለመሥራት ይስማማል።

ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር እንዴት ታላቅ ነው? የፍቅሩ ታላቅነት ልክ ደግሞ፤ ገና ኀጢያተኞች ሳለን፤ ገናም ለእርሱ ጠላቶች ሆነን ሳለን፣ ኀጢያት የማያውቀውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ ስለ ኀጢያታችን እስከ ሞት አሳልፎ እስከመስጠት የሚደርስ ነው። በዚህም እንደገና ወደ እግዚአብሔር የፍቅር

ሀብረት ተቀላቀልን። ከወደደንም ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ፤ በራሳችን ልናደርገው የማንችለውን ይህንን ታላቅ ሥራ ሠራልን። ከሰው የተወለደውን ፍቅሩን እንደገና ለሰው ለመመለስ እግዚአብሔር የማያደርገው ነገር የለም፤ አድርጎም አሣይቷል።

እስከ በኤፌሶን ይኖሩ ለነበሩ አማኞቹ ጳውሎስ የጻፈውን ይህን የአዲስ ኪዳን መልዕክት እንመልከት፤ "በበደላችሁና በኀጢያታችሁ ሙታን ነበራችሁ . . . ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፤ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ፤ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፤ በፀጋ ድናችኋልና (ኤፌ 2፥1፤ 4-5)።

ክርስቶስ ኢየሱስ ይህን ያከናወነው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ልጅ ስለነው ለእርሱ የነበረው ብቸኛ መንገድ የሰውን ስጋ ለብሶ የሰው ልጅ መሆን ነበር። እኛ እርሱን እንመስል ዘንድ እኛን መሆን ተገባው። ኢየሱስ ክርስቶስ ያከናወነውን ይህን ሥራ የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ የገለጸው እንዲህ ነው። "ነገር ግን በእግዚአብሔር ፀጋ ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የከብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን . . . እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ስልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፤ ይሄውም ዲያብሎስ ነው። በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በስጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም። ስለዚህ የህዝብን ኀጢያት ለማስተሠረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው" (ዕብ 2፥9፤ 14-17)።

ከዚህ ይልቅ ፍቅር የሚገለጥበት ሌላ መንገድ የለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ እንዲህ አለ፤ "ነፍሱን ስለወዳጆቹ አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ፤ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" (ዮሐ 15፥13)። እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ያድነን ዘንድ የላከው ስለወደደን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃዱ የሞተልን ስለወደደን ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ የሆነ ፍቅር ነው፤ በፍጹም አይጠፋም አያረጅም። ፊጽሞ እንዲህ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ፍቅር የራሱ የእግዚአብሔር ባህሪ ነው።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅርም የሚሰጥ ነው። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር የእርሱን ፍቅር እንድንቀበል የፈጠረን። ፍቅርም ሙሉ ይሆን ዘንድ ተቀባዮ ለጭውን ይመስል ዘንድ ይገባዋል። እና የተፈጠርነው በእግዚአብሔር መልክና እንደ ምሳሌውም ነው። እርሱ መንፈስ እንደሆነ ሁሉ እኛም መንፈስ ነን። እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ ሁሉ እኛም ፍቅር ነን። የእግዚአብሔር ፍቅር መቀበል የምንችል ሆነን ተሠርተናል፤ ይልቁንም መልስን እርሱን እንድንወደውና እንዲሁ ሌሎችን ደግሞ እንድንወድ።

መርሆዎች

1. እግዚአብሔር የሚፈጥረው በመናገር ነው።
2. እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር በተዘጋጀ ጊዜ የተናገረው ለእራሱ ነው።
3. እግዚአብሔር ሰውን እንደ መልኩ ፈጠረው።
4. እግዚአብሔር ፍቅር ነው።
5. ፍቅር ሙሉ ይሆን ዘንድ መሰጠት ያስፈልገዋል። ስለዚህም ምክንያት ፍቅር ተቀባይን ይፈልጋል።
6. ፍቅር ተግባሩን በትክክል ይፈጽም ዘንድ ተቀባዩ ሰጭውን ሊመስል የግድ ነው።
7. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የእርሱን ፍቅር እንዲቀበል ነው።
8. እግዚአብሔር ሰው ምድርን እንዲገዛት ስልጣን ሲሰጥ፤ የሰጠው መሠረታዊ ነገር በዚች ፕላኔት ውስጥ የሚካሄዱትን እንቅስቃሴዎች ሁሉ እንዲቆጣጠር ነበር።
9. እግዚአብሔር የጠፋበትን የእርሱን ፍቅር (ይዜውም የሰው ዘር ነው) እንደገና መልሶ ለማግኘትና ከሀጢያታችንም ሊታደገን፤ ስብአዊ ዘር ፈሰገ።.
10. ያለ እግዚአብሔር አንዳች ልናደርግ አንችለም፤ ያለ እኛም እግዚአብሔር ላያደርግ ይችላል።

ምዕራፍ ሦስት

እግዚአብሔርን መውደድ

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ፍቅርም መስጠትን ይጠይቃል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ሰውን እንደ እርሱ መንፈሳዊ ህልውና ያለው አድርጎ ፈጠረው፤ በዚህም ምክንያት የሚወደውንና ፍቅርንም የሚሰጠውን አግኝቷል። እዚህ ስፍራ እንድትረዱ የምፈልገው "ሰው" ስል ብእሸቃላይ የሰውን ዘር ማለቴ እንደሆነ ነው፤ "ሰው" የሰው ዘር መጠሪያ። በዚህ እሳቤ "ሰው" ወንድም ሴትም ያልሆነ ነገር ግን መንፈስ የሆነ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነውና።

ሰፈጠረው ለዚህ መንፈስ ለሆነ ሰው እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠው ነገር፤ ፍጥረታዊውን ዓለም- ምድርን እንዲገዛ ነው። መንፈሳዊ ህልውና ፍጥረታዊ የሆነ እውነታን ሊገነዘበው ወይም ሊያደንቀው አይችልም፤ ምክንያቱም መንፈሳዊውና ፍጥረታዊ እጅግ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የምድርን አፈር ወስዶ (ይህ የፍጥረታዊ ዓለም አካል ነው)፤ መንፈስ የሆነው ሰው ይኖርበት ዘንድ ልክ እንደ "ቤት" አድርጎ ፍጥረታዊ አካል አበጀ። ይህንን አካልም በልብ፤ በሳንባ፤ በስርዓተ ነርቭና በአምስቱ የስሜት ህዋሳት በማየት፤ በማሽተት፤ በመቅመስ፤ በመዳሰስና በመስማት ሞላው። ስለዚህም የፈጠረው መንፈስ የሆነ ሰው ይገዛው ዘንድ የተሰጠውን ፍጥረታዊ ዓለም ሙሉ በሙሉ ይገዛውና ያደንቀውም ይችል ዘንድ ህጋዊ የሆነ ችሎታ አገኘ።

የተከናወነውን ነገር ስንመለከት፤ እግዚአብሔር ያበጀው የመጀመሪያው አካል በጸታው ወንድ ነበር። አዳም። ወንድ የሆነው ሰው እግዚአብሔር ከፍጥረት በፊት ብቻውን እንደነበር፤ እርሱም በራሱ አለም ውስጥ ብቻውን እንደ ሆነ በተረጋገጠ ጊዜ፤ እግዚአብሔር ከአዳም አካል አንድ ክፍል ወስዶ "ሴት" የሆነች አካል አበጀ፤ ይህም አካል መንፈስ ለሆነ ለሰው ማደሪያ ሆነው። ከዚህ በኋላ ወንድና ሴት አንዳቸው በአንዳቸው ሙሉ የመሆንና ከእግዚአብሔር ጋር በማያቋርጥ ህብረት ውስጥ ደስታን አገኙ። አዳምና ሄዋን በሪፐንፈሣቸው የተሟሉ ይሆኑ ዘንድ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም አላስፈለጋቸውም። ወንድና ሴት በመሆናቸው ግን

ሙሉ ለመሆን አንዳቸው ለሌላቸው አስፈላጊዎች ናቸው። አሁን ላለነውም ለእኛ ነገሩ ሁሉ እንዲሁ ነው።

እግዚአብሔር እኛን የፈጠረበት ዋንኛው ምክንያት ይወደን ዘንድ ነው። ምድርን እንድንገዛት ለእኛ መስጠቱም የመጀመሪያው ስጦታ ነበር። የፈጠረን ሊወደን ነው፤ መውደዱንም ሊያረጋግጥልን ግዛትን ሰጠን። እና ነገሩ ሁሉ እንዲህ ከሆነ ሰው በምድር ላይ አላማው ምንድን ነው? በዚህ ያለነው በቃ በቀላሉ የተፈጠሩትን እየገዛን ልንኖር ብቻ ነው? አዳምና ሄዋን ይገዙት ዘንድ የተሰጣቸውን ፍጥረታዊ አለም ይገዙ ነበር፤ ይሁን እንጂ በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ያልተቋረጠ ህብረት ይደሰቱም ነበር።

እኛ የእግዚአብሔር ፍቅር የምንቀበል ነን፤ ምክንያቱም ስንፈጠር ስሪታችን እንዲህ እንዲሆን ተደርጎ ነው። እንዲህም ብቻ ሳይሆን የተቀበልነውን ፍቅር መልሰን መስጠት እንድንችል አድርጎ ፈጥሮናል። ከእግዚአብሔር የመጣ ሁሉ እግዚአብሔርን የመሰለ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፤ በመንፈሳችን እኛም እንዲሁ ፍቅር ነን፤ ምክንያቱም የተገኘነው ከእግዚአብሔር ነው። በምድር ላይ ያለንበት ቀዳማይ አላማ የመግዛት ዓላማ አይደለም፤ ይልቁንም የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመቀበልና መልሰንም እርሱን እንወድ ዘንድ ነው። የዌስት ሚኒስተር (በሎንደን የምትገኝ የመንግስት አስተዳደር ከተማ ናት) አጭር የአቋም የክርስትና እምነት መርህ መግለጫ የተባለ፤ የክርስትና እምነት መሠረታዊ እውነቶች ታዋቂ መግለጫ፤ "የሰው ትልቁ ግብ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠትና በእግዚአብሔር ለዘላለም መደሰት ነው" ሲል ይናገራል። ይህ ውብና ታላቅ አስተዋይነት የተሞላበት በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለውን የፍቅር መቀባበል የሚያስረዳ አገላለጽ ነው።



በምድር ላይ የምንኖርበት ቀዳማይ ስላማ የመግዛት ዓላማ አይደለም፤ ይልቁንም የእግዚአብሔርን ፍቅር ስመቀበልና መልሰንም እርሱን እንወድ ዘንድ ነው።

ዋነኛና ቀዳሚው አላማችን እግዚአብሔርን መውደድ ነው። አንዳንድ ጊዜ ምድራዊ የሆነውን ነገር ስናግበሰብስ እግዚአብሔር የተናገረውን እንዘነጋለን፤ "የመጀመሪያው ተግባራችሁ እኔን መውደድና ማምለክ ነው" ብሎ የተናገረውን እንዘነጋለን።

"አንድ የህግ አዋቂ ሊፈትነው፤ መምህር ሆይ ከህግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፤ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ሃሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፤ እርስዋም፤ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለዋ ናት። በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዝ ህጉም ሁሉ ነብያቱም ተሰቅለዋል" (ማቴ 22÷35-40)።

እንደ ሰውነታችን ቅድሚያ የምንለጠው የመጀመሪያው ነገር "ታላቁ ግባችን" ባለን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን መውደድ ነው። ይህን ካደረግን ብቻ ነው ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የሚለውን ሁለተኛውን ትእዛዝ በእውነት ልናሟላ የምንችለው። በማንኛውም ግንኙነታችን ውስጥ ስኬትና እውነተኛ ደስታ የሚሸከረከሩት "እግዚአብሔርን የምንወደው እንዴት ነው?" በሚለው ጉዳይ ዙሪያ ነው። እግዚአብሔር እንደወደደን ሁሉ እኛም እርሱን መልሰን ልንወደው ይገባናል። ይህንን ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው? እግዚአብሔርን መውደድ ማለትስ ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ፍቃድና እቅዱ (ደስታው ማለት ነው) እርሱን እንድንወደው ነው። እግዚአብሔርን የማንወድ ከሆነ ደስ ልናለኘው አንችልም። ካላወቅነው በስተቀር ልንወደው አንችልም፤ በእርሱም ላይ እምነት ከሌለን ልናውቀው ደግሞ አንችልም፤ "ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሚሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" (ዕብ 11÷6)።

እግዚአብሔርን ለመውደድ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እርሱን በእምነት ማወቅ ነው። እግዚአብሔርን ካላወቅነው ከቶውንም ልንወደው አንችልም። እግዚአብሔርን ወደማወቅ የምንደርሰው፤ የበደላችንን ተግሳጽ ይቀበል ዘንድ በመስቀል ላይ በሞተው፤ ከሰማያዊው አባታችን ጋር ትክክለኛ ህብረት ይኖረን ዘንድ የተሃድሶን በር በከፈተው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፉ እንደጻፈው፤ "ሁሉ ኃጢያትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔር ክብር ጎድሏቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ"(ሮሜ 3÷23-24)።

ኃጢያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ህብረት አፈረሰው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በደሙ የፈረሰውን ህብረት እንደገና አደሰው። በእምነት ከኃጢያታችን ተመልሰን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል

እዳኛችንና ጌታችን ስናምነው፤ "ኀጢያታችንን ይቅር ሊለን፣ ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው" (1ዮሐ 1÷9)። በተጨማሪም ከአባታችን ጋር በማያቋርጥ ህብረት ውስጥ እንድንራመድ በሚያስችለን በመንፈስ ቅዱስ ይሞላናል። እንደዚህና እንደዚህም ሲሆን ብቻ እግዚአብሔርን በእውነት መውደድ እንችላለን።

ስምዕኮ

እንደ አማኝነታችን ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምንገልጽበት በርካታ ልምምዶችና በግልጽ የምናሣይባቸው መንገዶች አሉ። እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት አንዱ በአምልኮ ውስጥ የምንገልጥበት መንገድ ነው። እዚህ ጋ ብዙውን ጊዜ እምልኮ ብለን የምንጠራው ብዙ ነገራችን እንደ እውነቱ ሌላ ነገር እንደሆነ መረዳት ያስፈልገናል። እውነተኛ አምልኮ የሚከናወነው አካላዊ በሆነው ማንነት ላይሆን መንፈሳዊ በሆነው ማንነት ነው። አምልኮ እያልን የምንጠራው ብዙው ነገራችን የሚከናወነው በአካላዊ ማንነታችን ነው፤ መዘመር፤ መፀለይ፣ እጆችን ማንሣት፣ ማሸብሸብ፣ በልሳን መጸለይና የመሳለሉት። እነዚህ እንቅስቀሴዎች ከለውነታችን ጋር የተያያዙ በመሆኑ፤ የግድ ወይም ወዲያውኑ ከመንፈሣችን ጋር ይያያዘሉ ማለት አይደለም። እነዚህን ነገሮች ሁሉ በሙሉ ሃይላችን ከምራችን ልናደርጋቸው እንችላለን፤ ይሁንና እውነተኛ ወደሆነው አምልኮ በጭራሽ ላንገባ እንችላለን።

እውነተኛ ስምዕኮ የሚከናወነው ስካላዊ በሆነ ማንነት ሳይሆን መንፈሳዊ በሆነው ማንነት ነው።

ብዙ አማኞች አምልኮ ብለው የሚጠሩት እውነታ ምስጋና ነው። እግዚአብሔርን ስለታላቅነቱና ስለመልካምነቱ እውቅና ይሰጡታል፤ ስለተአምራቱ፣ ስለባርኮቱ፣ በመካከላቸው ስለተገኘው ህልውናውና ሃይሉ ያመሰግኑታል፤ ያከብሩታል። እግዚአብሔርን ማመስገን ማለት እርሱን ከፍ ከፍ ማድረግ፣ መልካምነቱን መናገር፣ ከፍ ያለውን አድናቆትና አክብሮት መስጠት፣ ክብሩን፣ ልዕልናውን ታላቅነቱን ማግነን ነው። እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካምና አግባብ የሆኑ እንዲሁም ትክክለኛ ነገሮች ናቸው። ነገር ግን እውነተኛ አምልኮ አይደሉም። ምስጋና ለአምልኮ መንገድ ጠራጊ ነው፤ ብዙ አማኞች የሚሄዱት ግን እዚያ ድረስ ብቻ ነው።

የእውነተኛ አምልኮ አድማስ ከምስጋና አልፎ የማዕዘን ከዝማሬ፣ ከፀሎትና ከማንኛውም አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲሁም አምልኮ ናቸው ብለን ከምናስባቸው ነገሮች ሁሉ የላቀ ነበር። ምስጋና ጥቅሙ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለእኛው ነው። ምስጋና እውነተኛ አምልኮን እንድናደርግ አካላችንን ወደ መገዛት ለማምጣት የሚረዳ ለእውነተኛ አምልኮ መንፈሳችንን የሚያዘጋጅ ነው። ይህ ማለት አምልኮ ከራሣችን አካልና ከስጋችን ውስንነት ውስጥ እንድንወጣ በማድረግ መንፈሣችን ሙሉ በሆነ ነፃነት እንዲያመልክ ይረዳል ማለት ነው። በዚህ ምክንያት ጥንቃቄ ካላደረግን ሊጎዳንም እንደሚችል ማስብ ይኖርብናል።

እውነተኛ አምልኮ ሁልጊዜም የሚከናወነው ከመንፈስ ወደ መንፈስ ነው። የእኛ መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሲዋሃድ ነው። ብዙውን ጊዜ ይህ የሚከናወነው ያለ ቃላት ነው። አምልኮ ማለት በእግዚአብሔር ውስጥ ማንነታችንን ስናጣው ነው። በምስጋናና በሌሎች እንቅስቃሴዎች በእጅጉ ከተያዝን ትኩረታችን በስጋችን ላይ፤ በአካላችን ላይ ማለት ነው፤ በመሆኑ በሙሉ ልብ ሆነን ወደ አምልኮ መግባት አንችልም። በአካል ሆነን ከምናመልክበት ደረጃ አልፈን ከእግዚአብሔር ጋር ንጹህ በሆነ መንፈሣዊ ህብረት ወደምናመልክበት ደረጃ ልንደርስ ጊዜው መምጣት አለበት። ምስጋና አንድ ሮኬት ለመመንጠቅ የሚያስፈልጋትን ሃይል እንደሚሰጣት ቦስተር ሮኬት፤ ከእኛነታችን ውስጥ እንድንነጠቅ የሚያስችል ነው። ይሁንና መንፈሣችን ብቻ ነው ተነጥቆ ወደ ምህዋሩ የሚገባው።

አምልኮ የሚለው ቃል ተራክቦን ማድረግ፣ ቁልቁል መስገድና መሣም ማለት ነው። በአጭሩ አምልኮ ማለት መጣበቅ ማለት ነው። አምልኮን ከምስጋና የሚለየው ይሄው ነው። ከሩቅ ሆኖ መጣበቅ የሚባል ነገር የለም። እግዚአብሔርን ከርቀት ሆነን ልናመለግን አንችላለን፤ ከርቀት ሆነን ግን ልናመልከው አንችልም። ምስጋና አካላዊ ነው፤ አምልኮ ግን መንፈላዊ ነው። አምልኮ ማንነትን መለዋወጥ ነው።

እግዚአብሔርን ከርቀት ሆነን ልናመሰግን እንችላለን፤ ከርቀት ሆነን ግን ልናመልከው አንችልም።

እግዚአብሔር ፍቅር ነው። የፈጠረንም የእርሱን ፍቅር እንድንቀበል ነው። ፍቅርን ሰጭ ከሆነው አፍቃሪ አምላክ የተገኘን በመሆኑ፤ ፍቅርን ለመቀበል ብቻ ላይሆን ለመስጠትም ብቃቱ

አለን:: አምልኮ የሚጀምረው እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲለጥ ነው:: ፍቅሩን የተቀበልን እኛ መልሰን ደግሞ እንለጠዋለን:: መንፈሳችን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር በተገናኘ ጊዜ ያነየ ፍቅር እንለዋወጣለን:: እግዚአብሔር ይወዳል ይለጣልም፤ እኛም እንቀበላለን ምላሽንም እንለጣለን፤ አስቀድሞ በእኛ ላይ ያፈሰለውን ፍቅሩን መልሰን ለእርሱ እንለጣለን::

በክርስቶስ ውስጥ ጠኖር

እንዲህ ያለውን ወዳጅነት የተሞላበት ፍቅር ለመለዋወጥ ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት ሆነን መቆየት ይኖርብናል:: በርቀት ሆኖ መጣበቅ ፈጽሞ የማይቻል ነው:: ከእርሱ ጋር ያለንን መጣበቅ ጠብቀን መቆየት የፍቅር አንድ አካል ነው:: እርሱ አሁን እኛ ላለንና ይኖረናል ብለን ተስፋ ለምናደርገው ማናቸውም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው:: ላሉን ጥያቄዎች ሁሉ መልሱ በእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔው የተከማቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው:: ግራ ለተጋባንቸው ነገሮች ሁሉ መልስ የሚሆን ለላም ማደሪያው በእርሱ ዘንድ ነው:: ለእንቆቅልሾቻችንና ላልተረዳናቸው ነገሮች መፍቻ የሚሆን ቁልፍ በእግዚአብሔር እጅ ነው:: ጥበብ፤ እውቀትና ራሱ ሕይወትም ጭምር የመገኛ አድራሻቸው በእግዚአብሔር ነው::

እዚህ ነጥብ ላይ ነው ኢየሱስ በእርሱና በተከታዮቹ መካከል ለላለው ግንኙነት በንጽጽር፤ በወይኑ ቅርንጫፍና በወይኑ ግድ ምላሉ የተናገረው::

"እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው . . . በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ:: ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንደማይቻለው እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም:: እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ:: ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና፤ በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል:: በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል፤ ይደርቅማል እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሏቸውማል፤ በእኔ ብትኖሩ ቀሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችኋል . . . አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኳችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ:: እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደጠበቅኩ በፍቅሩም እንደምኖር ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ::" (ዮሐ 15÷1፤ 4-7፤ 9-10)::

የወይን ቅርንጫፎች በራሳቸው ህይወት የላቸውም፤ ህይወታቸው በግንዱ ላይ ነው:: ከግንዱ የተለየ ማንኛውም ቅርንጫፍ ይሞታል፤ ምክንያቱ በራሱ መዝለቅ ስለማይችል ነው:: ምንም እንኳን ቅጠሉንና ፍሬውን የሚያበቅሉት ቅርንጫፎቹ ቢሆኑም፤ ይህን ማድረግ የሚችሉት ከግንዱ ጋር ተጣብቀው እስከ ቆዩ ድረስ ብቻ ነው:: በግንዱ ውስጥ ያለው ሕይወት ወደ ቅርንጫፎቹ እየፈለሰ ፍሬ እንዲያፈሩ ያደርጋቸዋል:: የትኛውም ቅርንጫፍ በራሱ ፍሬ መስራት ወይም መስጠት አይችልም::

ልክ እንደዚሁ፤ ኢየሱስ ከእርሱ በቀር አንዳች ማድረግ እንደማንችል ተናገረ:: እኛ ቅርንጫፎች ነን እርሱም የወይን ግንድ የህይወታችንና የፍሬያችንም ምንጭ ነው:: የምንፈልገው ማንኛውም ነገር፤ ሊኖረን የሚችለውና አሁን ያለን ሁሉ በእርሱ ውስጥ ነው:: በህልውናችን አላማ ሁሉ ፍሬያማና ውጤታማ ለመሆን፤ ህይወት ያለን ሆነን መኖር ያስፈልገናል፤ ለዚህም ከወይን ግንዳችን ከኢየሱስ ጋር ዘላቂነት ባለው መጣበቅ ልንያያዝ ይገባናል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ" (ዮሐ 15÷4) ሲል አዟቸዋል:: ይህንን ትእዛዝ ተከትሎም ተስፋን ይለጣቸዋል፤ ". . . ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ" (ዮሐ 15÷10) ከክርስቶስ ጋር መቆየት ወይም መጣበቅ፤ በእኛና በጌታ መካከል ለሚኖረው የፍቅር መቀባበል እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው:: ምክንያቱ ቀላል ነው፤ በእርሱ ላይ ተጣብቀን በአንድ ስፍራ መቆየት ፍቅሩን መሉ ለመሉ ለመቀበል ያስችለናል::



በህልውናችን ለላማ ሁሉ ፍሬያማና ውጤታማ ለመሆን፤ ህጀመት ያለን ሆነን ጠኖር ያስፈልገናል፤ ለዚህም ከወይን ግንዳችን ከኢየሱስ ጋር ዘላቂነት ባለው ጠጣበቅ ልንያያዝ ይገባናል::

ማንኛውም ፍቅር ምንጩ ከእግዚአብሔር ነው:: ማንንም ልንወድ የቻልነው ማለትም እግዚአብሔርን፤ ራሳችንን ወይም ሌሎችን ሊሆን ይችላል ምክንያቱ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው:: መውደድ የቻልነው አስቀድሞ እግዚአብሔር ለለወደደን ነው:: ዮሐንስ በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን መልዕክቱ በራሱ መንገድ እንዲህ ገልጾታል::

"ወዳጆቼ ሆይ ፍቅር ከእግዚአብሔር ለለሆነ፤ የማወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ለለተወለደ እግዚአብሔርንም ለለማያውቅ

እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፤ በእርሱ በኩል በህይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅር እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢያታችንም ማስተሰሪያ እንዲሆን ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም" (1ዮሐ 4፥7-10)።

የፍቅር ቁልፉ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም፤ ይልቁንም እግዚአብሔር እንደወደደን ልጁንም እንደላከ ነው። እግዚአብሔርን የምንወደው እንዴት ነው? እግዚአብሔርን የምንወደው ከእርሱ ጋር ተቀራርበን በአንድ ስፍራ ተጣብቀን በመቆየት ነው። ያን ጊዜ ፍቅሩን እንቀበላለን። ወደ ልባችን የሚገባው ፍቅሩም፤ ለእርሱ የፍቅር ምላሽ ለመስጠት ያስችለናል። ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት መሆን የምንችለውስ እንዴት ነው? ይህን ማድረግ የምንችለው በአምልኮ ውስጥ፣ በፀሎት ውስጥ፣ ቃሉን በማንበብ በምናጠፋው ጊዜ፣ በጥሞና ውስጥ፣ ቃሉን መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት፣ በእግዚአብሔር መንፈስ በመመላለስና ከሌሎች አማኞች ጋር ያልተቋረጠ ህብረት በማድረግ ነው። ከምንወደው ከማንም ጋር ረዥም ጊዜ እናሳልፋለን። ከእርሱ ጋር ጊዜ በማሳለፍና በመጠጋጋት እግዚአብሔርን እንወዳለን፤ ስለዚህም ምክንያት ይወደናል እርሱን እንመስል ዘንድ መንገዱን ያስተምረናል።



እግዚአብሔር የምንወደው ከእርሱ ጋር ተጠጋግተን በአንድ ስፍራ ተጣብቀን በመቆየት ነው።

ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ

አንድ እጅግ ግልጽ የሆነ የህይወት መርህ አለ፤ ብዙውን ጊዜያችንን አብረናቸው የምናሳልፋቸውን ሰዎች እንመስላቸዋለን። አንድን ሰው በትክክል ለማወቅ የምንፈልግ ከሆነ ከዚያ ሰው ጋር ብዙ መቆየት ይኖርብናል። እግዚአብሔርን ከምንወድበት መንገድ አንዱ እርሱን በማወቅ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ለሚለው ሌላ ቃል መጠቀም ካስፈለገን ከእግዚአብሔር ጋር መጣበቅ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእውቀትና የመጣበቅ ጽንሰ ሀሳብ በእጅጉ የተቀራረበ ነው። በብሉይ ኪዳን "ያዳ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፤ እግዚአብሔርን ማወቅ የሚለውንና ጸታዊ ግንኙነትን የሚያመላክት ነው። ለምሳሌ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት

ለፊት ያውቀው ነበር፤ (ዘዳ 34፥10 ይመልከቱ) እንዲሁም አዳም ሚስቱን ሄዋንን አወቃት በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ ቃሉ የሚያመለክተው (ዘፍ 4፥1 K.J.V) ቅርበትንና ወዳጃዊ የሆነ ቤተሰባዊነትን ነው።



እግዚአብሔርን ከምንጠይበት መንገድ አንዱ እርሱን በማወቅ ነው።

ምሳሌ 1፥7 "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ" ይላል። እግዚአብሔርን ማወቅ ለማንኛውም እውነተኛ ለሆነ እውቀት መነሻ ነው። በስኬትና በውድቀት መካከል ያለው ልዩነትም ይሄው ነው- በፍቅርና በሕይወትም። የእውቀት ተቃራኒው ያለማስተዋል ነው። ያለማስተዋል የፈጠራ ክህሎትን እምቅ ችሎታ ገድቦ በመያዝ፤ ሰለባዎቹን ምሁራዊና መንፈሳዊ በሆነ ቀንበር ያሰራቸዋል። እውቀት በሌላ በኩል፤ ነፃ ያወጣል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቶቼ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነት አርነት ያወጣችኋል" (ዮሐ 8፥31-32)።

እውነት በራሱ ብቻ አይደለም ነፃ የሚያወጣን፤ ይልቁንም በእውነት እውቀት እንጂ። ልዩነት የሚያወጣው ይሄው ነው። የማናውቀው እውነት ለእኛ ምንም ማለት አይደለም። ኢየሱስ እንደተናገረው እውነትን የምናውቀው በቃሉ በመኖር ነው። ማንኛውም ኢየሱስ የተናገረው ያደረገውም፤ ሙሉው የህይወት ምሳሌነቱ ማለት ነው፤ አላማው አባቱን ለመግለጽ ነበር። የኢየሱስ ትምህርት አላማ ያደረገው እኛ እግዚአብሔርን እንድናውቅ ነው። እግዚአብሔርን ስናውቅ ፍቅርን እናውቃለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነው። እግዚአብሔርን ስናወቅ ህይወትን እናውቃለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ህይወት ነው።

እግዚአብሔርን እንደምንረዳው ተስፋ ማድረግ የጀመርን እንደሆነ እንኳን እናም እንዴት እንደምንወደው ካወቅን፤ እርሱን ወደማውቅ መጥተናል። እግዚአብሔርን መረዳት ለእኛ የሚቻል ነገር ነውን? በአንድ በኩል መልሱ አይቻልም ነው። ውስን በሆነ አይምሯችን የማይወሰነውን እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳትና ለማስተዋል ምንም መንገድ የለም። ይሁንና በሌላ በኩል እግዚአብሔር ስለ እርሱ ማስተዋል የሌለን እንድንሆን አይፈልግም። እርሱን በማወቅ ወዳጃዊ በሆነ ግንኙነት ከእርሱ ጋር

ህብረት እንድናደርግ ይፈልጋል። ስለዚህም ነው ራሱን ለመግለጽ በቃሉ ውስጥ፣ በልጁ በኩልና በመንፈሱ በኩል አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ያደረገው።



እግዚአብሔርን ስናውቅ ፍቅርን እናውቃለን፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። እግዚአብሔርን ስናውቅ ሀይማትን እናውቃለን፤ እግዚአብሔር ሀይማት ነውና።

ብዙ አማኞች እግዚአብሔርን መረዳት አይቻልም በሚል በተሳሳተ አመለካከት ሥር ናቸው። እርሱ ለዘለዓለም ሚስጥር ሆኖ ሊኖር ያስፈልጋዋል ብለው ያስባሉ። ይህ ግን በቀላሉ እውነት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሂደትና እያደገ በሚሄድ ሁኔታ ራሱን ለፍጥረት ሁሉ መግለጹን የሚዘግብ የታመነ መጽሀፍ ነው። መዝ 98፥2፤ "እግዚአብሔር ማዳኑን አስታወቀ፤ በአህዛብም ፊት ጽድቁን ገለጸ" ይላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሊታወቅ የማይቻል ሚስጥር ነው ለሚሉት ሀሳባቸው ድጋፍ አድርገው የሚያቀርቡት በ1ቆሮ 2፥9 "ነገር ግን አይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተፃፈ እንዲህ እንናገራለን"። የሚለውን ቃል ነው። ነገር ግን ቀጥሎ ያለውን ጥቅስ ብዙ ጊዜ ልብ አይሉትም፤ ". . . ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው" (1ቆሮ 2፥10)።

እግዚአብሔር የሚታወቅ ነው፤ እኛ እንድናውቀውም ይፈልጋል። እኛ እናውቀው እንችል ዘንድ ራሱን በብዙ መንገድ ገልጿል። እግዚአብሔርን የምንወደበት አንዱ መንገድ ጊዜያችንን ወስደን እርሱን ለማወቅ ጥረት ማድረግ፤ ከእርሱ ጋር ተጣብቆ ጊዜን ማሳለፍ ነው። ለግብጦው መልስ እንሰጥ ዘንድ ቆሞ ይጠብቃናል፤ "ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል" (ያዕ 4፥8)።

እግዚአብሔርን የሚመቁያ መንገዶች

እግዚአብሔር አንድናውቀውና እንድንወደውም ይፈልጋል። ይህ ስለ እግዚአብሔር ብዙ እውነቶችን ከማወቅ ከፍ ያለ ነው። ከአይምሮ እውቀትም በላይ ነው። ማወቅ ማለት የአንድን ነገር ወይም ሰው ተፈጥሮና ባህሪያት መረዳት ማለት ነው። ጥሩ መካኒክ ዘዴንክ ስለ መኪናዎች ምንነት አካላቸውን ከማወቅ በላይ

ታውቃለህ። እንዴት እንደሚሰሩ አጠቃላይ መርሆዎችን ትረዳለህ። ሞተሩን ከውስጥና ከውጭ ታውቀዋለህ፣ ስለትራንስሚሲዮን፣ ስለ ጭስማውጫው፣ ስለ ኤሌትሪክ ሲስተሙ አጣርተህ ታውቃለህ። መኪናው በአንድ ችግር ምክንያት በተበላሸ ጊዜ ብልሽቱን ለይተህ ታውቃለህ፣ ትጠግነውማለህ፤ ምክንያቱም የአውቶሞቢልን አሠራርና ባህሪውን ታውቀዋለህ። ያን ጊዜ በእውነት ስለ መኪና አውቃለሁ ማለት ትችላለህ።

አንድን ሰው ማወቅ ማለት የእርሱን ወይም የእርሷን ባህሪና ስብእና ማወቅ ማለት ነው። ይህም ማለት የዚያን ሰው እምነት፣ ስሜት፣ የሚወዳውን፣ የሚጠላውን፣ ጥንካሬውን፣ ድክመቱን ማመቅ ማለት ነው። አንዲህ አይነቱ እወቀት ውጭ ውጭውን ከማወቅ እጅግ የዘለለ ነው። በውጭ ከሚነገር ቃልና ከሚታይ ድርጊት የላቀ ነው፤ ይህ የዚያን ሰው ውስጣዊ ስብእና እንደ መዳሰስ ማለት ነው።

አንድን ነገር በእርሱ ላይ ተጣብቆ ማወቅ፤ በአይምሮ ማወቅን ብቻ ሳይሆን በልብ ማወቅን ይጨምራል። ይህም ማለት የሰውየውን ድርጊት ብቻ ማወቅ ሳይሆን መንገዱን ጭምር ማወቅ ማለት ነው።

እግዚአብሔርን መውደድ ማለት መንገዱን ማወቅና መማር ማለት ነው። ይህ ማለት ቃሉንና አሠራሩን ከማወቅ እጅግ የተለየ ነው። በመዝ 95፥10 ጌታ እንዲህ ይላል፤ ያችን ትውልድ አርባ አመት ተቆጥቻት ነበር፤ ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል፣ እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልኩ" (መዝ 95፥10)። እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው ስለተመረጠው ነገር ግን መንገዱን ስላላወቀ ህዝቡ ስለእስራኤል ነው። እነዚህ እግዚአብሔር ከግብጽ ባርነት ነፃ ባወጣቸው ጊዜ በግብፃውያን ላይ ደረገውን መቅሰፍት ሁሉ ምስክር ሆነው የተመለከቱ ናቸው። እግዚአብሔር ቀይ ባህርን ሲከፍለውና ከፈርኦን ሠራዊትም ሲታደጋቸው ተመልክተዋል። በምድረ በዳው ቀን የደመናውን አምድ ሌትም የእሳቱን አምድ ተከትለው ሄደዋል። አለት ሰንጥቆ ይጠጡ ዘንድ ውሃን አዘጋጅቶላቸዋል። በምድረ በዳው አርባ አመት ሙሉ ተአምራዊውን መና አየተመገቡ ሄሉት አድርገዋል። በዚያ ጊዜ ሁሉ ውስጥ ልብሳቸው አላረጀም ጫማቸው አላለቀም። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ተመልክተዋል። ሥራውን ያውቃሉ፤ መንገዱን ወደ ማወቅ ግን በጭራሽ አልደረሱም።



ሰንድን ነገር በስርሱ ሳይ ተጣብቄን የምናውቀው ማወቅ የስደምር እውቀት ብቻ ሳይሆን የሰብም ነው።

በሌላው በኩል ግን ሙሴ በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር በጣም በተጣበቀ ህብረት ሃሴት ያደርግ ነበር። ዳዊት በመዝ 10÷37 ስለጌታ በጻፈበት ስፍራ "መንገዱን ለሙሴ አስታወቀ፤ ለእስራኤል ለልጆችም አደራረጉን" ሲል አስፍሮታል። እዚህ ጋ ሁለት አይነት ግንኙነቶችን እንመለከታለን። ሙሴ የእግዚአብሔርን ልብና ሃሣብ ይዳስስ ነበር፤ ህዝቡ ግን እግዚአብሔር የሚሠራውን ይመለከቱ ነበር። ለዚህ ነበር ህዝቡ በጭራሽ በእውነት ወደ እግዚአብሔር ህልውና ያልገቡት።

ዛሬም ተመሳሳይ ችግር ተከስቷል። የእግዚአብሔርን ታምራቶች አይተው የሚያረጋገጡ ብዙ አማኞች አሉ። የእግዚአብሔርን ባርኮት የተለማመዱ፣ እግዚአብሔር አንዳንድ ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንደሚያዘጋጅ የሚናገሩ፣ የእግዚአብሔር ነገርና ሃይሉን ማድነቅ ይችላሉ ይሁንና ፈጽመው የእግዚአብሔርን ህልውና አያውቁም። ልባቸውን ወደ ልቡ ወይም ሀሳባቸውን ወደ ሃሳቡ መልሰው አያውቁም።

የእግዚአብሔርን መንገዶች ማወቅ እግዚአብሔርን የመውደድ አላባዎች ከሆኑት አንዱን ምናልባትም ከሁሉም እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ጉዳይ ወደ አይታችን ያመጣል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ . . . ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝን አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ . . . የሚወደኝ ቢኖር ቃሴን ይጠብቃል አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን (ዮሐ 14÷15፤ 21:23)።

እግዚአብሔርን መታዘዝ እኛ ለእርሱ ያለን ፍቅር በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት እውነትነቱም የሚረጋገጥበት ነው። እግዚአብሔርን የምንወደው እርሱን በመታዘዝ ነው። ባለመታዘዝ የምናደርገው የመውደድ ተግባርና ለእግዚአብሔር መስጠታችንም ቢሆን ባዶ፣ ትርጉም የለሽና ግብዝነት ያለበት ነው፤ ኢሳ 29÷13 በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔርን አቋም በግልጽ ያስፈረዋል፤ "ጌታም ይህ ህዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፣ በከንፈሮቹም ያከብረኛልና፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና"።



እግዚአብሔርን መታዘዝ እኛ ለእርሱ ያለን ፍቅር በከፍተኛ ደረጃ የሚገለጥበት እውነትነቱም የሚረጋገጥበት ነው።

ዓላማህ ምንድን ነው? ዝም ብለህ የእግዚአብሔርን ባርኮት ትከታተላለህ ወይስ እግዚአብሔርን ማወቅ ትፈልጋለህ? ሃሣብህ ያረፈው ከእርሱ በምትቀበለው ነገር ላይ ነው ወይስ ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀ ግንኙነት ለማድረግ ጠንካራ መሻት አለህ? እግዚአብሔር የሚሠራውን እያየህ በመደሰት ትረካለህ? ወይስ ወዳጁ ለመሆን ወደፊት ትራመዳለህ?

ፍቅር ሙሉ ይሆን ዘንድ ራሱን መስጠት ይኖርበታል፤ ስለዚህም ፍቅር ተቀባዮን ይፈልጋል። ፍቅር ሙሉ ይሆን ዘንድ ተቀባዩ መልሶ ለሰጭው ይመልስለት ዘንድ ያስፈልጋል። ይህን ግንኙነት ነው እግዚአብሔር ለሁላችን ያዘጋጀው፤ እናም ወደዚህ ፍቅር ሁላችንን ይጋብዘናል። የተፈጠርነው የእግዚአብሔር ፍቅር ለመቀበልና የተቀበልነውንም መልሰን ለመስጠት ነው። እርሱ ለእኛ ያለው እቅድ ወደ ጠለቀና ወደቀረበ የፍቅር ግንኙነት፤ በውጫዊ ሁኔታዎች ከሚገለጽ ግንኙነት ባለፈ መንገድ ልብ ለልብ፣ መንፈስ ከመንፈስ ጋር ወደ ሆነ ህብረት እንድንገባ ነው። እግዚአብሔር የጠራን በሙሉ ልባችን፣ በሙሉ ነፍሳችን፣ በሙሉ ሃሳባችን እርሱን እንድንወድ ነው። እንዲህ አይነቱ ፍቅር ነው ዋንኛ የሆነውን የህይወት ግባችንን እንድናከናውን የሚያስችለን፤ እግዚአብሔርን ማክበር በእርሱም ለዘላለም መደሰት።



እግዚአብሔር የሚሠራውን እያየህ በመደሰት ተረካለህን ወይስ ወዳጁ ለመሆን ወደፊት ትራመዳለህ?

መርሆዎች

1. ዋነኛና ቀዳማይ አላማችን እግዚአብሔርን መውደድ ነው::
2. እግዚአብሔርን ለመውደድ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እርሱን በእምነት ማወቅ ነው::
3. እውነተኛ አምልኮ ሁልጊዜም ከመንፈስ ወደ መንፈስ ነው::
4. አምልኮ ማንነትን መቀባበል ነው::
5. እግዚአብሔርን ከምንወድባቸው ነገሮች አንዱ ከእርሱ ጋር ያለንን ህብረት ጠብቀን መቆየት ነው::
6. ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ፤ በእኛና በጌታ መካከል ለሚደረግ የፍቅር መቀባበል መሠረታዊ ነገር ነው::
7. እግዚአብሔርን ማወቅ የእውነተኛ እውቀት መነሻ ስፍራ ነው::
8. እግዚአብሔርን ከመውደድ መንገዶች አንዱ ጊዜ ወስዶ እርሱን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ነው፤ ይህ ማለት ከእርሱ ጋር የተቀራረበ የህብረት ጊዜ ማላሰፍ ማለት ነው::
9. እግዚአብሔርን መውደድ ማለት መንገዱን ማወቅ ማለት ነው::
10. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው እቅድ ወደ ጠለቀና ወደ ቀረበ የፍቅር ግንኙነት፤ በውጫዊ ግንኙነት ከሚገለጥ ግንኙነት ባለፈ መንገድ፤ ልብ ለልብ፣ መንፈስ ከመንፈስ ጋር ወደ ሆነ ህብረት እንድንገባ ነው::
11. እግዚአብሔር የምንወደው እርሱን በመታዘዝ ነው::

ምዕራፍ ስድስት

ራስን መውደድ

በለዎች መካከል ያሉ የፍቅር ግንኙነቶች ሁሉ፤ ፍጥረታዊውም ይሁን መንፈሣዊው እግዚአብሔርን መሀከል አድርጎ የታቀደ ነው:: ኢየሱስ እንደተናገረን ከሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛት አንዱ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ሀሳብህም ውደድ" (ማቴ 22÷37):: ሁለተኛው ደግሞ፤ "ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ወደድ" የሚለው ነው(ማቴ 22÷39) የሚል ነው:: ሁለቱ መለያየት እንዳይችሉ ሆነው የተያያዙ ናቸው:: እግዚአብሔር የፈጠረን የእርሱን ፍቅር እንድንቀበል ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም መልሰን ለእርሱ ልንለጥና ለሌሎችም ደግሞ እንድናስተላልፍ ነው:: ጎጢያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በማቋረጥ ፍቅርን የመቀበልና የመስጠት ብቃታችንን እንድናጣ የግንኙነት መስመሩን ይቆርጠዋል:: ከእግዚአብሔር ጋር መሠረታዊ የሆነው የፍቅር ግንኙነት ሣይኖረን ባልንጀሮቻችንንም ይሁን ራሳችንን መውደድ እንደሚገባን መውደድ አንችልም:: እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ፍቅር እርግጠኞች ከሆንን፤ ያንን ፍቅር ለእርሱ መልሰን እንሰጣለን፤ ይህ ነፃ የሆነ የፍቅር ቅብብልም ራሳችንንና ሌሎችንም እንድንወድ ያስችለናል::

ራስን መጥላት በሰብአዊው ማህበረሰብ በየትኛውም ባህል ውስጥ ዋነኛው ችግር ነው:: በስነልቡና ዘርፍና በባህሪ ላይ ለአስርት ዓመታት የተደረጉ ምርምሮች፣ ጥናቶችና የተገኙ ልምዶች እንደገለጡት፤ ራስን መጥላት ለአይምሮ፣ ለፍልቅ ስሜትና ለስነአይምሮ ችግሮች ዋነኛ ምክንያት ነው:: ብዙ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ችግር የሚፈጥሩበት ምክንያት ከራሳቸው ጋር ጠበኞች በመሆናቸው ነው:: ፍቅርን ለመስጠትም ይሁን ለመቀበል ከባድ ሆኖ የሚያገኙበት ምክንያት ራሣቸውን መውደድ ባለመቻላቸው ነው::

እንዳለመታደል ሆኖ ራስን የመጥላት ችግር በአለማዊው ማህበረሰብ ውስጥ ወይም በአይምሮው በሽተኛ በሆነውና በፍልቅ ስሜቱ መረጋጋት በማይችለው ዓለም ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ይሄው ተላላፊ በሽታ ብዙ የክርስቶስ ተከታዮችንም በክሏል:: ብዙዎቻችን አማኞች የሆንን ለራሳችን ዝቅተኛ ግምት

መርሆዎች

1. ዋነኛና ቀዳማይ አላማችን እግዚአብሔርን መውደድ ነው።
2. እግዚአብሔርን ስመውደድ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ እርሱን በእምነት ማወቅ ነው።
3. እውነተኛ አምልኮ ሁልጊዜም ከመንፈስ ወደ መንፈስ ነው።
4. አምልኮ ማንነትን መቀባበል ነው።
5. እግዚአብሔርን ከምንወድባቸው ነገሮች አንዱ ከእርሱ ጋር ያለንን ህብረት ጠብቀን መቆየት ነው።
6. ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ፤ በእኛና በጌታ መካከል ለሚደረግ የፍቅር መቀባበል መሠረታዊ ነገር ነው።
7. እግዚአብሔርን ማወቅ የእውነተኛ እውቀት መነሻ ስፍራ ነው።
8. እግዚአብሔርን ከመውደድ መንገዶች አንዱ ጊዜ ወስዶ እርሱን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ነው፤ ይህ ማለት ከእርሱ ጋር የተቀራረበ የህብረት ጊዜ ማሳለፍ ማለት ነው።
9. እግዚአብሔርን መውደድ ማለት መንገዱን ማወቅ ማለት ነው።
10. እግዚአብሔር ለእኛ ያለው እቅድ ወደ ጠለቀና ወደ ቀረበ የፍቅር ግንኙነት፤ በውጫዊ ግንኙነት ከሚገለጥ ግንኙነት ባለፈ መንገድ፤ ልብ ለልብ፣ መንፈስ ከመንፈስ ጋር ወደ ሆነ ህብረት እንድንገባ ነው።
11. እግዚአብሔር የምንወደው እርሱን በመታዘዝ ነው።

ምዕራፍ አራት

ራስን መውደድ

በሰዎች መካከል ያሉ የፍቅር ግንኙነቶች ሁሉ፤ ፍጥረታዊውም ይሁን መንፈሣዊው እግዚአብሔርን መሀከል እድርጎ የታቀደ ነው። ኢየሱስ እንደተናገረን ከሁለቱ ታላላቅ ትእዛዛት አንዱ "ጌታ እምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ሀሳብህም ውደድ" (ማቴ 22÷37)። ሁለተኛው ደግሞ፤ "ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ወደድ" የሚለው ነው(ማቴ 22÷39) የሚል ነው። ሁለቱ መለያየት እንዳይችሉ ሆነው የተያያዙ ናቸው። እግዚአብሔር የፈጠረን የእርሱን ፍቅር እንድንቀበል ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም መልሰን ለእርሱ ልንሰጥና ለሌሎችም ደግሞ እንድናስተላልፍ ነው። ጎጢያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በማቋረጥ ፍቅርን የመቀበልና የመስጠት ብቃታችንን እንድናጣ የግንኙነት መስመሩን ይቆርጠዋል። ከእግዚአብሐር ጋር መሠረታዊ የሆነው የፍቅር ግንኙ ነት ሣይኖረን ባልንጀሮቻችንንም ይሁን ራሳችንን መውደድ እንደሚገባን መውደድ እንችልም። እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ፍቅር እርግጠኞች ከሆንን፤ ያንን ፍቅር ለእርሱ መልሰን እንሰጣለን፤ ይህ ነፃ የሆነ የፍቅር ቅብብልም ራሳችንንና ሌሎችንም እንድንወድ ያስችለናል።

ራስን መጥላት በለብአዊው ማህበረሰብ በየትኛውም ባህል ውስጥ ዋነኛው ችግር ነው። በስነልቡና ዘርፍና በባህሪ ላይ ለአስርት ዓመታት የተደረጉ ምርምሮች፣ ጥናቶችና የተገኙ ልምዶች እንደገለጡት፤ ራስን መጥላት ለአይምሮ፣ ለፍልቅ ስሜትና ለስነአይምሮ ችግሮች ዋነኛ ምክንያት ነው። ብዙ ሰዎች ከሌሎች ለሎች ጋር ችግር የሚፈጥሩበት ምክንያት ከራሳቸው ጋር ጠበኞች በመሆናቸው ነው። ፍቅርን ለመስጠትም ይሁን ለመቀበል ከባድ ሆኖ የሚያገኙበት ምክንያት ራሣቸውን መውደድ ባለመቻላቸው ነው።

እንዳለመታደል ሆኖ ራስን የመጥላት ችግር በአለማዊው ማህበረሰብ ውስጥ ወይም በአይምሮው በሽተኛ በሆነውና በፍልቅ ስሜቱ መረጋጋት በማይችለው ዓለም ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ይሄው ተላላፊ በሽታ ብዙ የክርስቶስ ተከታዮችንም በክሏል። ብዙዎቻችን እማኞች የሆንን ስራሳችን ዝቅተኛ ግምት

በመስጠት ችግር እንጠቃለን። በዚህም ችግር ውስጥ ሆነን ያለማቋረጥ ራሳችንን በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ እናስቀምጣለን፤ ስለራሳችን አሉታዊ የሆኑ ነገሮች እንናገራለን፤ ተሰጥኦዎቻችንን፣ ልዩ ችሎታዎቻችንንና ብቃቶቻችንን እንክዳለን። ይሄ ራስን ዝቅ የማድረግ ችግር ደግሞ፤ ራሳችንን መውደድ አይገባንም ከሚል ለመቶ አመታት ያህል ስንማረው የቆየ የቤተክርስቲያን ትምህርት ውጤት ነው። እንዲህ አይነቱ ትምህርት ራስን መኮነንን፣ ትህትና በተሞላበት መንገድ የራስን ማንነት መቀበልን (መገንዘብን) እኩል ያደርጋል። እውነታውን ከተመለከትን ግን ሁለቱ በፍጹም አንድ አይደሉም። ራስን መኮነን "እኔ ምንም ማለት አይደለሁም። ምንም ጥቅም የሌለኝ፣ የማልረባ፣ ለማንም ጥቅም መስጠት የማልችል ዋጋ ቢስ ነኝ" ይላል። በትህትና የራስን ማንነት መገንዘብ ግን፤ በቀላሉ እግዚአብሔር ስለ እኛ የተናገረውን ያምናል፣ ይቀበላልም። እግዚአብሔር ያለው ደግሞ እኛ ሁሉንም ነገር የሆንን እጅግ ዋጋ ያለን እንደሆንን ነው።

ኢየሱስ "ባልንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ" ሲል፤ ጎረቤቶቻችንን፤ ልክ ራሳችንን መውደድ በቻልንበት ፍቅር መጠን እንድንወድ ነው የነገረን። ይህን በሌላ መንገድ ለመግለጽ፤ ጎረቤቶቻችንን መውደድ የምንችለው እኛ ለራሳችን ባለን ፍቅር ልክ ነው። ራሳቸውን የማይወዱ ሰዎች ማንንም በእውነተኛ ፍቅር ሊወዱ አይችሉም።



በትህትና የራስን ማንነት መገንዘብ ግን፤ በቀላሉ እግዚአብሔር ስለ እኛ የተናገረውን ያምናል፣ ይቀበላልም።

እባካችሁ አንድ ነገር ተረዱልኝ፤ እዚህ ስፍራ እየተናገርኩ ያለሁት ከመጠን ባለፈ መንገድ የራስን ማንነት መውደድንና ከመጠን ባለፈ መንገድ ለራስ ትኩረት መስጠትን **(eqotistical)** የሆነውን ራስን መውደድ አይደለም። ይህ ስለራስ በማይጨበጥ ጉም ያልሆነ ምስል መሣልና ሌሎችን ደግሞ ዝቅ አድርጎ መመልከት ነው። እኔ ራስን መውደድ ስል፤ ስለ አራስ አወንታዊ የሆነ እይታና ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት፤ በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ያለንን ስፍራ በትክክል በመረዳት ጤነኛ የሆነውን ለራስ ዋጋን በመስጠት ላይ የተመሠረተውን ራስን መውደድ ማለቴ ነው።

ራሳችንን ለምን መውደድ አስፈለገን? ለዚህስ ምን ምክንያት አለን? መልሱ የሚያርፈው በእግዚአብሔር ልብና በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ነው። እግዚአብሔር እንደ መልኩና በምሣሌውም ፈጠረን። ከፍጥረቶቹ ሁሉ ታላቅ የክብር ዘውዶች የሆንን የእጁ ሥራዎች ነን፤ እግዚአብሔር ይህንን ተመልክቶ መልካም እንደሆነ አየ። ኀጢያት ግን ይህንን በእኛ የነበረ መልክ አጠፋው። ይሁን እንጂ አሁንም ለእግዚአብሔር እጅግ ጠቃሚዎች ነን፤ ለዚህም ነው እንደገና ከእርሱ ጋር የነበረንን ግንኙነት ያድስ ዘንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ ስለኀጢያታችን በመስቀል ላይ እንዲሞት ያደረገው። በኢየሱስ ክርስቶስ፤ እግዚአብሔር እንደገና በመልኩ ፈጠረን፤ አስቀድሞ እንደነበረው እንደገና ሠራን፤ እንደገናም ሥራውን ተመልክቶ መልካም እንደሆነ አየ። እጅግ መጠኑን ባለፈ እይነት ሁኔታ ሳይሆን በሰጠን ስፍራና በቀላሉ እግዚአብሔር ዋጋ ለጥቶ እኛን ያስቀመጠበትን ሥፍራ አምነን በመቀበል ራሳችንን ልንወድ ይገባል።

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስግኘተናል

ጤነኛ የሆነ ራስን መውደድ ልናዳብር ከሚያስችሉን የመጀመሪያ ደረጃዎች አንዱ፤ ሙሉ በሙሉና ፍጹም በሆነ መንገድ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያገኘን መሆኑን መገንዘብና መረዳት ነው። ጳውሎስ በኤፌሶን ለሚገኙ አማኞች በጻፈው የአዲስ ኪዳን መልዕክቱ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፦

"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን። በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የለጠን በፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ፤ በውድ ልጁም እንደ ፀጋው ባለጸጋነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፤ እርሱም የበደላችን ስርየት። ፀጋውንም በጥበብና በአይምሮ ሁሉ አበዛልን" (ኤፌ 1፥4-8)።

በኪንግጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ላይ ቁጥር 6 እንዲህ ይነበባል፤ "የጸጋው ክብር ይመሰገ ዘንድ በውድ ልጁ ተቀባይነት እንዲኖረን አደረገ"። በዚህ ስፍራ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው የአሁን ጊዜ ስለሆነ እውነታ እንጂ ስለ ሃላፊ ጊዜ አይደለም። ባለፈው ጊዜ ተቀባይነት አልነበረንም። በኀጢያታችን ምክንያት እግዚአብሔር ሊቀበለን አልቻለም ነበር። የተጣልን፣ በራሳችን ወደ እርሱ

ለመመለስ አንዳች ተስፋ ያልነበረን፣ ከእግዚአብሔር የተለየን ነበርን። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ በመስቀል ላይ ሞተ ተቀባይነት ያሳጡንን ነገሮች ሁሉ ወሰዳቸው። በራሱ አካል ውስጥ ቀበራቸው፤ የኃጢያታችንን ብዛት ደመሰሰው፣ እስከ ሞት ድረስ ታዘዘ፣ በሦስተኛውም ቀን ከመታን ተለይቶ ተነሣ። በደሙም ከኃጢያታችን አጠበን፤ እንደገናም ንጹህና ቅዱስ አደረገን። እናም ወደ አባቱ አቀረበን፣ አባቱም "ተቀብያቸዋለሁ" አለ።

እግዚአብሔር የተቀበለን ከሆነ፤ ራሳችንን ልንቀበል ይገባናል። እግዚአብሔር ውጫዊ ስለሆነ መልካችን ግድ የለውም፤ ይህ ለእርሱ ምንም ማለት አይደለም። ድካማችንን ጉድለታችንን እንደሌለ ቆጥረን ራሳችንን ልንመለከት ወይም ሙሉ እንደሆንን ልንገምት ያስፈልገናል፤ እግዚአብሔር ወደ እኛ ተመልክቶ "እወዳችኋለሁ። ተቀብያችኋለሁ። እናንተ ለእኔ ውብ ናችሁ" ይላል።

እግዚአብሔር የተቀበለን ከብዙ ጉድለታችን ጋር ነው። ታዲያ ሰምንድን ነው ራሳችንን ለመቀበል የምንቸገረው? እንደኛው ምክንያት ስለራሳችንም ሆነ ስለሌሎች ዋጋ ያለን ሰዎች መሆናችንን የምንገነዘብበት መንገድ ነው። አንዳንዶቻችን እየተንጎራደድን "እኔ ዋጋ ያለኝ ሰው ነኝ። እግዚአብሔር ዋጋ ያለኝ ሰው እንድሆን አድርጎኛል" እንላለን። ነገር ግን ከውስጣችን ውስጥ አሁንም ዋጋ የሌለን ሰዎች እንደሆንን ይሰማናል። መማራችንን ወይም አለመማራችንን፤ አካላዊ አቋማችንን፣ የሥራ ችሎታችንን ወይም የተለየ ሙያ የሌለን መሆናችንን፣ ተሰጥኦዎችንን፣ ስጦታችንንና ክህሎታችንን ወይም ምንም የተለየ ብቃት የሌለን መሆኑን እንገመግምና ያን ያህን ዋጋ ያለን አይደለንም እንላለን።

እግዚአብሔር ቸል ካለው መመዘኛ አንጻር የራሳችንን ዋጋ የምንተምን ከሆነ ነገሩ ሁልጊዜም የሚያበቃው ስለራሳችን የተሳሳተ ምስል በመሣል ነው። ስለራሳችን የምንሰጠው ዋጋ፤ ብዙውን ጊዜ የራሳችንን ማንነት ለመመዘን በምናስቀምጣቸው ደረጃዎችና አካላዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች አይመለከታቸውም።

የማንኛውም ነገር አውነተኛ እሴት የሚተመነው ሌሎች ለእርሱ በሚሰጡት ዋጋ ነው። ለምሳሌ፣ ወርቅ በቀላሉ የሚያንጸባርቅ ቢጫ ብረት ነው። ይህ ብረት ከምድር የተገኘ

ውጤት ሲሆን፣ ሰዎች ዋጋውን ባይተምኑበት ኖሮ ምንም ዋጥም የሌለው ተራ ብረት ይሆን ነበር። ብዙ ሰዎች በወርቅ ላይ ከተተመጠው እሴት ምክንያት ስጋቸውን ለገመት አሳልፈው ይሰጣሉ፤ ይጣላሉ፣ ይጋደላሉ ይሞታሉም። እንደዚሁ ሁሉ ዋጋችንን ለመተመን ወደራሳችን መመዘኛዎች ልንመለከት አይገባንም። ይልቁንም እግዚአብሔር ፈጣሪያችን በእኛ ላይ ወዳስቀመጠው እሴት ልናይ ያስፈልገናል።



እግዚአብሔር ቸል ካለው መመዘኛ አንጻር የራሳችንን ዋጋ የምንተምን ከሆነ፤ ነገሩ ሁልጊዜም የሚያበቃው ስለራሳችን የተሳሳተ ምስል በመሣል ነው።

በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋችን ምን ያህል የከበረ ነው? ወደ ኋላ መለስ ብለን ወደ ኤፌሶን መልዕክት (1፥4-8) ስንመለከት "መረጠን . . . አስቀድሞ . . . ፍጥረት . . . በፊቱ ቅዱስና ያለነውር" (ቁ. 4)፤ "በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን" (ቁ. 5)፤ "እንደ ጸጋው ባለጠግነት በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመስገን ዘንድ ይህን አደረገ (ቁ. 6)፤ በውድ ልጁም እንደጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፤ እርሱም የበደላችን ስርየት (ቁ. 7)፤ "ፀጋውንም በጥበብ ሁሉ በአይምሮ ሁሉ አበዛልን" (ቁ. 8) የሚሉ ሃሣቦች እናገኛለን።

እኛ ለእግዚአብሔር ውድ ነን፤ ያውም በዋጋ የማንተመን። በአንድ ነገር ጥንቃቄ ልንወስድ ያስፈልገናል፤ ይሄውም በእግዚአብሔር የተሰጠንን የራሳችንን ማንነት ዋጋ፤ ከራሳችን መልክ፣ ካለን ሀብት ወይም ባህሪ ወይም ዝንባሌ አለበለዚያም ሌሎች ስለእኛ ካላቸው አመለካከት ጋር አሳክረን እንዳንመለከተው ነው። ድንቁርና የተሞላበት ስህተት ሰርተን ከሆነ፤ ማለት ያለብን "ስህተት ሰርቻለሁ" እንጂ "እኔ ስህተት ነኝ" የሚል መሆን የለበትም። አንድ ነገር ማድረግ ተስኖን ወድቀን ቢሆን፤ ለዚህ የምንሰጠው ምላሽ "ወደቅሁ" የሚል እንጂ "እኔ ወዳቂ ነኝ" ማለ መሆን አይገባውም። ሁልጊዜም ባህሪያችንንና የሥራ አተገባበራችንን ስለራሳችን ካለን ግምት ጋር ነጣጥለን መመልከት ይኖርብናል። ምንም ይሁን ምን ይፈጠር፤ ምንም አይነት ምስቅልቅል ነገር ውስጥ ምንም ጊዜ ያህል እንግባ፤ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥም በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋችን የከበረና ተቀባይነት

ያለን ነን። እንዲህ እንደሆንንም አስቀድሞ ደንግጎታል፤ ቃሉም በጭራሽ አይለወጥም።

በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነን

ያለፈው በቃ አልፏል። ማን እና ምን እንደነበርን ከዚህ በኋላ የሚፈይደው ነገር የለም። አሁን ዋጋ ያለው ነገር ማንና ምን መሆናችን ወደፊትስ ማንና ምን እንደምንሆን ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች በጻፈላቸው በሁለተኛው መልዕክቱ፤ እንደ እግዚአብሔር ልጅነታችን ማን እንደሆንና እግዚአብሔር እኛን ስለሚመለከትበት መንገድ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ስለዚህም ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል" (2ቆሮ 5፥15)።

በክርስቶስ ሁሉም ነገር አዲስ ነው። አሮጌው ነገር ሁሉ አልፎ ሄዷል። ይህም ማለት ስዎች ስላለፈው ማንነታችን የሚናገሩትን አሉታዊ፤ የሚሰብርና ተስፋ አስቆራጭ ንግግር ሁሉ ልንረሣው ያስፈልገናል። እነርሱ አልፈዋል። አሁን አዲሱን ነገር ልንጨብጥ ነው የሚገባው፤ በክርስቶስ ባገኘነው በአዲሱ ማንነታችን ላይ ተመስርተን የተለየ አለባበስ፤ የተለየ አረማመድ፤ የተለየ አነጋገር፤ ለህይወት ጥያቄ የተለየ ምላሽ መስጠት እንችላለን። ከዚህ በኋላ ድህነት እንደቀጠቀጣቸው ለማኞች ልንኖር፤ በአሉታዊ ሁኔታዎች ማጥና በድብርት፤ ያለመጽናናት ተስፋ ቆርጠን፤ ራሳችንን አቀርቅረን ልንመላለስ አንፈቅድም።

ስለራሳችን የምንለው ስእል፤ ስለራሳችን ያለን ግንዛቤ ማለት ነው፤ ሁልጊዜም ለህይወት እንዴት መልስ እንደምንሰጥ ይወስናል። እኛ ማን እንደሆንን መልስ ለመስጠት ወደ ሌሎች መመልከት አይገባንም። እግዚአብሔር አስቀድሞ ነግሮናል፤ በቃሉም ውስጥ አሳይቶናል። እኛ አዲስ ፍጥረት፤ የተወደድን፤ ተቀባይነት ያገኘንና በፊቱ የከበርን ነን።



ስለራሳችን የምንለው ስእል፤ ስለራሳችን ያለን ግንዛቤ ማለት ነው፤ ሁልጊዜም ለህይወት እንዴት መልስ እንደምንሰጥ ይወስናል።

በዚህ መንገድ ራስህን ለማየት ችግር ያለብህ ከሆነ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ስላንተ ምን እንደሚለማው የሚገልጹ ጥቅሶችን ሁሉ ዝርዝር አውጣ። በመስተዋትህ አጠገብ ወይም በሌላ ሁልጊዜ ልታየው በምትችልበት ስፍራ ለጥፈህ፤

"ንጉስና የድንፋ ዓለሙ ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር የተወደደ ልጅ" እንደሆንክ እንድታስብና በዚህ አላቤም ውስጥ እንድትመላለስ እንዲረዳህ እድርግ። የምትለጥፈው ዝርዝር ምናልባት ይህን ሊመስል ይችላል።

እኔ የታጠብክ ነኝ፤ እኔ ይቅርታ ያገኘሁ ነኝ፤ እኔ ሙሉ ሰው ነኝ፤ ተፈውሻለሁ፤ የነጻሁና የክብር ተስፋ ያለኝ ነኝ፤ በምድር የምኖረው በእንግድነት ነው፤ በዚች ፕላኔት ውስጥ ወደ ፍጽምነት የምጎለግስ ተንቫር ነኝ፤ ማን እንደሆንክ የተረዳሁ በመሆኔ ማንም ስለማንነቴ እንዲነግረኝ አልፈልግም፤ በክርስቶስ ኢየሱስ የደም ዋጋ የተገዛሁ እኔ የንጉስ ልጅ ነኝ፤ በኢየሱስ ዳግመኛ ተወልጃለሁ እኔ እዲስ ፍጥረት ነኝ፤ ፍጹም አዲስ፤ ሁልጊዜም በእግዚአብሔር የተወደድክ፤ ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር አባት እንደ ልጅ የተቀበለኝ፤ በፊቱም የከበርክ ነኝ።

ፍቅርን በመቀበልና በመስጠት እጅግ ስኬታማ የሆኑ ሰዎች፤ ሁልጊዜ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱና ከፉ ክፉ ነገር እየተናገሩ የሚመላለሱ ሳይሆኑ፤ ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን የሚወዱና ሙሉ ለሙሉ በእግዚብሔር እንደተወደዱ ያወቁት ናቸው። ስለራሳቸው ከራሳቸው ጋር ሰላም ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ፍቅርን ለመስጠትም ይሁን ሌሎችም ይወዷቸው ዘንድ ለመፍቀድ ነፃ ናቸው።

ራሳቸውን በመጥላት የተሞሉ ሰዎች ፍቅርን ለመቀበል ችግር አለባቸው። እንዲህ ብለው የማሰብ አዝማሚያ አላቸው "እኔ የተወደድክ አይደለሁም፤ ማንስ ቢሆን እንዴት አድርጎ እኔን ይወዳል?" እንዲህ አይነቱ ስለራስ የሚሳል አሉታዊ ምስልና በአይምሮ የተቀረጸ የዝቅተኝነት ሀሳብ፤ ከሌሎች የሚለጣቸውን የፍቅር መግለጫ የውሸት ወይም የማስመሰል ነው ብለው ስለሚያስቡ አይቀበሉትም። በዚሁ አንጻር ደግሞ የራሳቸው የፍቅር ቋት ተሟጦ ያለቀ በመሆኑ ፍቅርን በአግባቡ መስጠት እይችሉም። ያላቸው የፍቅር ክምችት መጠን በቂ ባለመሆኑ አውጥተው ለሌሎች የሚለጡት ፍቅር የለም።

ምንጊዜም ቢሆን ስለራሳችን ያለን አመለካከት የተመሠረተው በስሜታችን ላይ ከሆነ ችግር ላይ መውደቃችን አይቀሬ ነው፤ ምክንያቱም ስሜታችን ይለዋወጣል። ጥሩ ስሜት እስከተሰማን ድረስ ለራሳችን ያለን አመለካከት ጥሩ ይሆናል። ይሁንና ጥሩ

ስሜት ባልተሰማን ጊዜ ደግሞ ለራሳችን ያሰን እመለካከት ቁልቁል ይወርዳል።

አማኞች በሆንን ጊዜ፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነናል፤ በእርሱ ምስል እንደገና ተፈጥረናል። በእኛ ውስጥ ያለው የክርስቶስ ምስል ከቶውንም አይለዋወጥም። ምንም እንኳን ውጫዊ መልካችን በጊዜ ውስጥ ቢለወጥም፤ በእኛ ውስጥ የተሣለው የክርስቶስ ሳይለወጥ ይቆያል። መልካምም ይሁን መጥፎ ስሜት በተሰማን ጊዜ ሁሉ፤ በከፍታም ይሁን በዝቅታ ውስጥ እንሁን፤ ኢየሱስ ያወደናል፤ ተቀብሎናል። ዋናው ቁም ነገር ያለው እርሱ ስለእኛ ያለው አመለካከት ብቻ ነው። ስለእራሳችን ያለን አመለካከት ሊመሠረት የሚገባውም እርሱ ስለእኛ በሚያስበው ላይ ሊሆን ይገባል እንጂ ሌሎች ስለኛ በሚያስቡት ወይም ራሳችን ስለራሳችን በምናስበው እንኳን ሊሆን አይገባም።

እኛ አማኞች የሆንን ሁሉ ለራሳችን የሁሉተኛ ደረጃ መደብ ግምት ሰጥተን የምንመላለስበት ሁኔታ ሊያበቃ ጊዜው አሁን ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን በማሰባችን እንኳን እየተሸማቀቅን ይቅርታ መጠየቃችንን ማቆም አለብን። በምድር ላይ የታደልነውን ፀጋ ሳናገኝ በመሞታችን እግዚብሔር በዚህ ደስ አይሰኝም። በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነን፤ በአለም ሁሉ ፊት በዚህ መንገድ መመላለስ ስንጀምር፤ በድል መኖራችን፣ በደስታና ከራሳችን እንዲሁም ከሌሎች ሁሉ ጋር ሰላም ኖሮን ሊመለከቱ ብዙ እጅግ ብዙም ሰዎች ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ።



ስራሳችን የሁለተኛ መደብ ግምት ሰጥተን የምናመላልስበት ሁኔታ ሊያበቃ ጊዜው አሁን ነው።

ራስን ያለመቀበል የተመለኑ መገለጫዎች

ራስን የመጥላት ሌላው መግለጫ ራስን አለመቀበል ነው። ራሳቸውን የሚጠሉ ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ራሳቸውን መቀበል አይችሉም። ራስን አለመቀበል በብዙ የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ይገለጻል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጋር በተገናዘበ መልኩ ችግሮቹን ማስወገድ እንችል ዘንድ የተለመዱ አስራ ሁለት ያህል ራስን ያለመቀበል መገለጫ ምልክቶች አስፍራያለሁ። ሁልጊዜም ቢሆን ባህሪያችንንና አመለካከታችንን ልንቃኝና ልንመዝን በዚያው አንጻር ልናስተካክል የሚገባን ከእግዚአብሔር ቃል መመዘኛዎች አኳያ ነው።

1. ለአለባባስ ከተገቢው በላይ ትኩረት መስጠት

ለአለባበሳቸውና ሰፋሽን እጅግ ከመጠን በላይ የሚጨነቁ ሰዎች ምናልባት የሚታዩ ጉድለቶችን ወይም የማይፈልጉትን ነገር ግን ሊለውጡት የማይችሉ የአካላዊ አፈጣጠራቸውን ችግር ለማካካስ ጥረት እያደረጉ ነው። ጥሩ ልብስ መልበስ ምንም ችግር የለበትም፤ ይሁንና የምንለብሰው ልብስ እኛ ማን እንደሆንን እንዲገልጸን ልንፈቅድለት አይገባም። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ፤ "እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንንስ ሁሉ አህዛብ ይፈልጋሉ። ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፣ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ 6፥31-33)።

2. በእግዚአብሔር ላይ መታመን አለመቻል

ራስን ያለመቀበል ችግር ያለባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ለመታመን ችግር ያለባቸው ናቸው። እግዚአብሔር እነርሱን ያበጀበትን መንገድ ለመቀበል ያለመርካት ስሜት ከተሰማቸው፤ በሌሎች ህይወታቸው ጉዳይ ላይ በእግዚአብሔር ለመታመን እንዴት ይቻላቸዋል? ጠላታችን የሆነው ሰይጣን፤ ስለእግዚአብሔር እውነት ያልሆነና የተዛባ አመለካከት እንዲኖረን በማድረግ ደስታችንንና ተስፋችንን ሊሰርቅ ይፈልጋል። ይህን አስመልክቶ ኢየሱስ፤ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለሌላ አይመጣም፤ እኔ ህይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ" (ዮሐ 10፥10) ሲል ይናገራል። ፍርሃት አይግባችሁ፤ ጌታን ሙሉ ለሙሉ ልንታመነው እንችላለን።

3. ከመጠን ያለፈ አይናፋርነት

የአይናፋርነት መሠረቱ ሌሎች ስለእኛ ከሚያስቡት ነገር የመነጨ ፍርሃት ነው። ከመጠን ያለፈ አይናፋርነት የሚታይባቸው ሰዎች፤ ለማንም ምንም ለመስጠት አንዳች ዋጋ ያለው ነገር እንደሌላቸውና ምንም አይነት ጠቃሚ አስተዋፅኦ ለማድረግ እንደማይችሉ የሚሰማቸው ናቸው። መጎዳትን ስለማይፈልጉ በራሳቸው ትንሽ አለም ውስጥ ራሳቸውን ዘግተው ይቀመጣሉ። አይናፋር መሆን ማለት ዝምተኛ መሆን ማለት አይደለም። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሯቸው ዝምተኞች ናቸው። የአይናፋርነት መሠረቱ ፍርሃት ነው። ጌታ ያለው እንዲህ ነው፤ "አልጥልህም ያልሁህ

ሆይ፣ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፣ እረዳሀለሁ” (ኢሳ 41÷10)::

4. ሌሎችን ለመውደድ አለመቻል

እርግጥ ነው የዚህ ችግር መሠረቱ፤ በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ካለመታመን የተነሣ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ራሳቸውን መውደድ ካለመቻላቸው ምክንያት የሚፈጠር ችግር ነው:: የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመጠራጠር ምንም ምክንያት የለም:: እርሱ ራሱ በቃሉ እንዲህ ሲል አረጋግጦልናል:: “በዘላለም ፍቅር ወድጃሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብኩሽ” (ኤር 31÷3) ሲል አረጋግጦልናል::

5. ራስን መውቀስ

ይህ በአንድ ሰው ሰብእና ውስጥ ሲሰወጡ በማይችሉ ነገሮች ማጉረምረምን ወይም ተቃውሞ ማቅረብን ይጨምራል:: ለምሣሌም ችሎታን፣ የወላጆች ሁኔታ፣ ከማህበረሰቡ የተወረሱ ችግሮች ወይም ያልተፈለገ የአካል ጉድለት ሊሆን ይችላል:: በኢሣ 45÷9 ለእንደዚህ አይነቱ አዝማሚያ የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ አለ፤ “ከሠሪው ጋር ለሚታገል ወዮለት በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው:: ጭቃ ሠሪውን ምን ትሠራለህ ወይስ ሥራህ እጅ የለውም ይላልን? አባትህን ምን ወልደሃል? ወይም ሴትን ምን አማጥሽ ለሚል ወዮ!”:: ልትለውጣቸው ስለማትችል ነገሮች አትጨነቅ:: ልክ አሁን እንዳላኸው እግዚአብሔር ፈጥሮሃል ደግሞም ይወድሃል፤ ይህም ብቻ አይደለም ማንም ሰው ሊሠራው የማይችሰውን ነገር ለመሥራት በአንተ ይጠቀምብሃል:: ራስህን መሆን እንድትችል ያደርግህ ዘንድ ለእግዚአብሔር ፍቀድለት::

6. ከሌሎች ጋር ራስን የማወዳደር ምኞት

ይህ ራስን ከመውቀስ ችግር ጋር የተያያዘ ነው:: በተለይም ሊሰወጡ በማይችሉ ችግሮች አንድ ሰው ከሌሎች ልዩ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ይገለጣል:: ልዮነቱ የሚያርፈው ግን፤ ይህኛው ችግር መለወጥን የሚፈልግ ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ላይ የሚታዩ የተለየ መገለጫዎችን መመኘት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንጂ ሌሎች ሰዎችን ለመምሰል ማለም የለብንም:: ጳውሎስ በሮሜ ላሉ አማኞች “የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ

በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ” (ሮሜ 12÷2)::

7. መራርነት

አንዳንድ ሰዎች በጭራሽ የሚናገሩት አወንታዊ ነገር የለም:: ምንም አይነት መልካም ጨዋታ ብትጀምሩላቸው ወዲያውኑ ሀሜት፣ ማጉረምረም፣ አይቻልም የሚል ንግግር ይጀምራሉ፤ ወይም ስለሌላ ነገር ቁጣቸውንና ምሬታቸውን ይገልጻሉ:: በልባቸው ውስጥ በምሬት ተሞልተው የሚመላለሱ ሰዎች ለራሳቸው ዝቅተኛ አመለካከት በመስጠት የሚጠቁ ሰዎች ናቸው::

ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ አማኞች በጻፈው መልዕክቱ ስለንግግራችን ያለው ነገር አለ፤ “ለሚሰሙት ፀጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውንም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ” (ኤፌ 4÷29)::

8. ፍጹማዊነት

መልካምን ነገር ማድረግ ወይም ያለማቋረጥ እየተሻሻሉ ለመሄድ መሻት በራሳቸው ምንም ችግር የለባቸውም:: ሁለቱም ጤነኛ አዝማማያዎች ናቸው:: ብዙውን ጊዜ ለፍጹምነት መጣጣር ለራስ የሚሰጥን ዝቅተኛ ግምት ለማካካስ የሚደረግ ጥረት ነው:: ፍጹማውያን እጅግ ህግ ጠባቂዎች፣ አግባብ ነው ከተባለው ነገር በጥቂቱ እንኳን ዝንፍ ያለን ነገር ያለመቀበል አዝማሚያ አላቸው:: ይህ የአንተ ችግር ከሆነ አድምጥ! እንደገና ጳውሎስ ለሮማውያን እንዲህ ይላል፤ “በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የህይወት መንፈስ ህግ፤ ከኀጢያትና ከሞት ህግ አርነት አውጥቶናል” (ሮሜ 8÷2)::

9. ትልቅነትን የማሳየት አዝማሚያ

ራሳቸውን ያለመቀበል ችግር ያለባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ በሌሎች ላይ ስልጣናቸውን ወይም የበላይነታቸውን በማሳየት ችግራቸውን ለማካካስ ይሞክራሉ:: የተሳከሳቸውን ነገሮች አለመሣይነት በተሞላባቸው ቃላት ጉራ መንዛትና ከተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ለመገናኘት አለመፍቀድ፤ የኩራት፤ ውስጣዊ ስጋትና ሁለንተናዊ ደህንነት የማጣት ምልክቶች ናቸው:: የበላይነትን የማሳየት አዝማሚያ እንደ ጭምብል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ምክር እንዲህ ይላል፤ “ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳን አታድርጉ፤

ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከእርሱ እንደሚሻል በትህትና ይቁጠር" (ፊሊ. 2፥3)::

10. የማይለወጡ ጉድለቶችን ለመደባበቅ የሚደረግ የማይሆን ሙከራ

ለዎች የማይለወጡ ነገሮችን ለመሸፈን ስለራሳቸው ማንነት የሚናገሯቸው ነገሮች ወይም የሚያደርጓቸው ድርጊቶች ምናልባትም ራስን ያለመቀበል ችግራቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙባቸው ሊሆኑ ይችላሉ::

በራሳችን ልንለውጠው የማንችል ችግር ካለብንና እግዚአብሔር በዚህ ረገድ የፀለይነውን ፀሎት ገና ያልመለሰ ከሆነ፣ በለጠን የተስፋ ቃል ላይ ተመስርተን ልንጠይቀው ይገባል:: "ፀጋየ ይበቃሃል ሃይሌ በድካም ይገለጻል አለኝ" (2ቆሮ 12፥9)::

11. እባካኝነት

አድናቆትን ለማግኘት ተስፋ አድርገውና በሌሎች ላይ በቅናት ተነሳስተው ብዙ ጊዜ ያለምጣኔ ወድ ዋጋ ባላቸው ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ወጭን የሚያወጡ ለዎች፣ ምናልባትም ራስን ያለመቀበልና በራስ ማንነት ያለመርካት ስሜታቸውን ለመሸፋፈን የሚያደርጉት መከራ ሊሆን ይችላል:: ሕይወት ማለት የቁሳቁሶች ክምችት ባለቤት ከመሆን ያለፈ ነገር ነው:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "የሰው ህይወቱ ከገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፣ ከመንምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው" (ሉቃ 12፥15)::

12. ቅድሚያ ለሌላቸው ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት

በሌሎች ዘንድ አድናቆትንና ከበሬታን ለማግኘት ሲባል ነገሮችን ለማከማቸት እጅግ ብዙ ጊዜን ማጥፋትና እግዚአብሔር የሰጠውን ሃላፊነት ቸል ማለት፣ ምናልባትም ራስን ያለመቀበል ችግር አንድ ምልክት ሊሆን ይችላል:: ለህይወት ዋነኛ ለሆኑ ጉዳዮች አጭር ቅንስናሽ የሆኑ ስዓቶችን የሚመድብና ሁለተኛ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ አትኩረት የሚሰጥ ማንም ለው ቢሆን የሚሮጠው ወደ ችግር ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ማዳመጥ ብልህነት ነው፣ "ለው አለመን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል" (ማር 8፥36)::

የእግዚአብሔር ፈቃዱን እንጂ የሰው ሰያሰፈልገንም

ራስን የመቀበል ችግርን ለማስወገድ አንዳንዶች የንደኞቻቸውንና የቅርብ ዘመዶቻቸውን ይሁንታ በታላቅ መሻት ይፈልጉታል:: ማንም ቢሆን ይሁንታንና የሌሎችን ተቀባይነት ይፈልጋል:: ለራሳቸው ይሁንታ መስጠት የማይችሉ ለዎች የሌሎችን ይሁንታ ይፈልጋሉ:: እዚህ ጋ የሚነሳው ትልቁ አደጋ ዓለም የምትሰጠው ይሁንታ ባዶ የሆነና ሊከናወን የማይችል መሆኑ ነው:: ከእግዚአብሔር የሚመጣ ይሁንታ ብቻ ገንቢና አጥጋቢ ነው:: የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ይሁንታ እንጂ የሰው ይሁንታ አይደለም::

በ2ቆሮ 10፥17-18 ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይጽፋል፣ "የሚመካ ግን በጌታ ይመካ፣ እግዚአብሔር የሚያመሰግነው እንጂ ራሱን የሚያመሰግነው፣ እርሱ ተፈትኖ የሚወጣ አይደለም":: አማኞች የሆኑት ሁሉ እግዚአብሔር ይሁንታ ሰጥቷቸዋል፣ የሚንም ቅቀባይነት አያስፈልገንም:: እግዚአብሔር ራሱ አስቀድሞ ድጋፍ ሰጥቶናል:: ድጋፍ መስጠት ማለት ስለ አንድ ለው ታላቅነት የሚነገር ነገር ነው:: ምንም እንኳን ሌሎች ስለ እግዚአብሔር ህዝብ ብዙ ዝቅ የሚያደርጉ ነገሮች ቢናገሩም፣ እግዚአብሔር ስለ ህዝቡ ታላቅነት ተናግሯል:: ምናልባትም ከህይወት ደህንነታችን ቀጥሎ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘታችን እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትልቁ መገለጥ ነው::

ከመጠን ባለፈ መልኩ ከአለም ተቀባይነትን ለማግኘት መሻት በተለይም ለአማኖች አላስፈላጊ የሆነ ጥረት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል አረጋግጦ እንደነገረን ሲሆን የተገባው ነገር ተቀራኒው ነው:: የጌታን የኢየሱስን ስም የተሸከሙና ለእርሱም እየታዘዙ መኖርን የመረጡ ሁሉ ከዓለም ለስሙ ጠላቶች ሆነው ከሚመላለሱ ስዶት እንደሚደርስባቸው አረጋግጠላቸዋል:: ጳውሎስ በአገልግሎት እያሳደገው ለነበረው ለወጣቱ ለጢሞቲዎስ እንዲህ ሲል ጽፎለታል፣ "በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" (2ጢሞ 3፥12)::

የአለም ተቀባይነት ማለት መጨረሻው ባዶ ነው:: የእውነተኛ ባርኮትና የደስተኛነት መንገድ በክርስቶስ ኢየሱስ በእግዚአብሔር መታወቅና በመታዘዝ የሚገኝ ነው:: ኢየሱስ ይህንን እንዲህ ሲል አረጋግጦታል፣ "ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብጹአን ናቸው፣ መንግስተ ለማያት የእነርሱ ናትና:: ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ፣

በእኔም ምክንያት ከፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብጹአን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፤ ሀሴትንም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነብያት እንዲሁ አሳደዋቸዋልና" (ማቴ 5÷10-12)።

በጣም በርካታ ሰዎች የሌሎች ሰዎችን ተቀባይነት ለማግኘት ሲሉ ዘመናቸውን ይኖሩታል። እጅግ ብዙ አማኞችም ሌሎች ሰዎች ስለ እነርሱ ምን እንደሚያስቡ ለማወቅ ይህን የሚያራግቡላቸውን ሰዎች በመፈለግ ይጨነቃሉ። እኛ ስለሚቀበሉንም ይሁን ስለማይቀበሉን ሰዎች ከፍተኛ ትኩረት ልንለጥ አይገባንም፤ እንድ ነገር ግን ልብ ልንል ይገባል፤ ይሄውም በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ማግኘታችን ነው።

እግዚአብሔር የተቀበላቸው እነርሱ በቃ አንድ ጊዜ ተቀባይነት አግኝተዋል። ኢየሱስ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፤ "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንም ስጋንም በገሀነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ" (ማቴ 10÷28)።



እኛ ስለሚቀበሉንም ደሁን ስለማይቀበሉን ሰዎች ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጥ ስይገባንም፤ ስንድ ነገር ግን ልብ ልንል ይገባል ይሄውም በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ማግኘታችን ነው።

ተቀባይነትን ፈላጊዎች ብዙውን ጊዜ በቀላሉ በቡድናዊ አስተሳሰብ ይያዛሉ፤ ለእንደዚህ አይነቱ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ከአፋቸው የማይጠፋ ቃል ደግሞ፤ እንዲህ እናድርግ፣ ይህን እናድርግ፣ ያንን እናድርግ የሚል ነው። እንዲህ እናድርግ በሚል ነገር ውስጥ የገባ ሰው ምንም አይነት ስብእናዊ መለያ የለውም። ያለማቋረጥ የሌሎችን ሰዎች ተቀባይነት የሚፈልጉ እነዚያ የራሳቸው የሆነ አይምሮ የላቸውም። ራሳቸውን ከውስጥ መቆጣጠር አይችሉም፤ ይልቁንም ሊያስደስቷቸው ብብርቱ ከሚጥሩላቸው ሰዎች ማንኛውም ከውጭ ሆነው በጥበብ ይቆጣጠሯቸዋል፣ ይጠቀሙባቸዋል።

የዚህን ዓለም ተቀባይነት ለማግኘት ከንቱ የሆነ ሩጫ የአንድን ትልቅና የአንዲትን ትንሽ ድመት ታሪክ ይመስላል። ትልቁ ድመት ትንሹ ድመት ጭራውን ሲከተል ተመለከተና፣ "ለምንድነው እንዲህ ያለማቋረጥ ጭራህን የምትከተለው?" ሲል ጠየቀው።

መ·ጭሊቱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ለድመቶች ታላቁ ነገር ደስታ እንደሆነ ተረድቻለሁ፤ ያ ደስታየ ደግሞ ጭራየ ነው፤ ለዚህ ነው ያለማቋረጥ የምከተለው"።

ትልቁ ድመትም ለመ·ጭሊቱ እንዲህ ሲል መለሰለት፤ "ልጄ ሆይ፤ እኔም ደግሞ በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ ላለው ችግር ሁሉ ትኩረትን ሰጥቻለሁ። እኔም እንዳንተ ደስታየ ጭራየ እንደሆነ ፈርጀ ነበር። ነገር ግን አንድ ነገር ተረድቻለሁ፤ ጭራየን እየተከተልክ በሄድክ ቁጥር ከራሴ እየራቅሁ እንደምሮጥ ተገነዘብክ፤ ጭራየን መከታታል ትቼ ሥራየን መስራት ሰቀጥል፤ ጭራየ እኔን እንደሚከተለኝ ተሰማኝ"።

ነጥቤ ያለው እዚህ ጋር ነው፣ እጅግ የተወደዱት ሰዎች መወደድን ፍለጋ የሚሮጡ ለዎች አይደሉም፤ ነገር ግን በቀላሉ ዘና ብለው በራሳቸው ላይ ትኩረትን የሰጡ ሰዎች ናቸው። በእግዚአብሔር ተቀባይነት ካገኘን፣ የሚያስፈልገንን ተቀባይነት ሁሉ ተቀብለናል። በእርሱ ፍቅር ከተሞላን፤ እርሱን መልሰን የመውደድና ራሳችንንም የመውደድ ፈቃት ይኖረናል። የሌሎችን ለዎች ተቀባይነት ማግኘት ከዚህ በኋላ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነገር አይደለም።

የእግዚአብሔር ፍቅር የሌሎችን ተቀባይነት ከመፈለግ ነፃ አውጥቶናል። በእግዚአብሔር መወደዳችንን፣ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ማግኘታችንን፣ በእግዚአብሔር ይሁንታ ማግኘታችንንና በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆናችንን ከተረዳን፤ ይህ ራሳችንን ያለመቀበል ችግራችንን የሚያስወግድና ጤነኛ የሆነ ራስን መውደድን ሊያነቃቃ የሚችል ነው። እግዚአብሔር ለእኛ ባለው ፍቅር፤ እኛም ለእርሱ ባለን ፍቅር እንዲሁም እኛ ለሌሎች ባለን ፍቅር የምንተማመን ከሆነ፤ ይህ ባልንጀራችንን እንደገዛ ነፍሳችን እንድንወድና ሁለተኛውን ታላቁን ትእዛዝ እንድንፈጽም ያዘጋጀናል።

መርሆዎች

1. ራሳችንን ልንወድ የሚገባን ትዕቢት በተሞላበት መንገድ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ተምኖ በእኛ ላይ ያስቀመጠውን ዋጋ በቀላሉ በመቀበል ነው።

2. እኛ ሙሉ በሙሉ በፍጹምም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አግኝተናል።

3. እኛ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆንን፣ የተወደድን፣ ተቀባይነትን ያገኘን፣ በፊቱም የከበርን ነን።

4. አማኞች በሆንን ጊዜ፣ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነናል፡ በእርሱም መልክ እንደገና ተፈጥረናል። በእኛ ውስጥ የተሣለው ይህ የኢየሱስ መልክ በጭራሽ አይለወጥም።

5. አማኞች የሆንነውን ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ ተቀብሎናል፣ የማንንም ተቀባይነት ማግኘት አያስፈልገንም።

6. የእግዚአብሔርን ተቀባይነት ካገኘን፣ የሚያስፈልገንን ተቀባይነት ሁሉ አግኝተናል።

ምዕራፍ አምስት

ባልንጀራን መውደድ

እንደማንኛውም ሌሎች እውነታዎች ሁሉ፣ በግንኙነትም ውስጥ እውቀት ለስኬት ቁልፍ ነገር ነው። አላዋቂነት አደገኛ ነው። ስለጋብቻም ይሁን ስለሌሎች መለስተኛ የተለመዱ ወዳጃዊ ግንኙነቶች ስንናገር፣ ለእነዚህ ግንኙነቶች አለመሳካት በተደጋጋሚና በዋነኛነት ምክንያት የሚሆነው የእውቀት አለመኖር ነው።

ብዙውን ጊዜ በግንኙነቶች ውስጥ ግጭቶችና ውጥረቶች የሚነሱበት ምክንያት፣ በቀላሉ በወንዶችና በሴቶች መካከል እርስ በእርስ መግባባት ባለመኖሩ ምክንያት ነው። ወንዶችና ሴቶች አንዱ ከሌላው በተለየ መንገድ ማሰብና መተግበር ያለባቸው ብቻ ሳይሆን፣ አካባቢያቸውን ጭምር በተለያዩ መንገዶች መገንዘብ እንዳለባቸው ያለውን እውነት አምኖ ለመቀበልና ለመፍቀድ ይቸገራሉ። አብዛኛው እንዲህ አይነቱ የግንዛቤ እጦት የሚከሰተው፣ ወንዶችና ሴቶች በስብእዊ ተፈጥሯቸውና በስብእናቸው እኩል የሆኑ ናቸው፣ በተጨማሪም ያላቸው ፍላጎት ተመሣሣይ ነው፣ ከሚል የተሣሣተ ግንዛቤ የሚነሣ ነው።

በእግዚአብሔር መልክ እንደተፈጠረው መንፈሣዊ ህልውና፣ እርግጥ ነው ወንዶችና ሴቶች እኩል ናቸው። የተለየ ስብእና በመሆናቸው እኩል ናቸው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ የሆነ ውጤታማ መንፈሳዊ ግንኙነት በመፈለጋቸው እኩል ናቸው፣ በስልጣንና ምድራዊ በሆነው ዓለም ላይ ባላቸው አገዛዝ እኩል ናቸው። ወንድና ሴት የሆነ አካል እንዳላቸው ሰብአዊ ህልውናዎች ግን ፍላጎታቸው የየግልና የተለያየ ነው። ይህ የፍላጎት ልዩነት የሚመነጨው ደግሞ እንደ ወንድ እና እንደ ሴት ካላቸው ተፈጥሯዊ ስሪትና ከአተገባበራቸው ነው።



ባልተሳኩ ግንኙነቶች ተደጋጋሚና ዋነኛ ምክንያት የሆነው የትዕቢት አለመኖር ነው።

እሠራር ስሪትን ይወስናል፣ ስሪትም ፍላጎትን ይወስናል። የአንድ አውቶሞቢል እሠራር በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ነው። ይህን አገልግሎት ለመስጠት፣ ብዙ አውቶሞቢሎች ውስጣዊ የሆነ ሀይልን ወደ

እንቅስቃሴ መለወጥ የሚያስችል የሞተር ለሪት (design) ይኖራቸዋል። ያ ሞተር በአቅዱ ውስጥ ሥራውን በአግባቡ ያከናውን ዘንድ ቤንዚን ያስፈልገዋል። እቅድ ፍላጎትን የሚወስነው ለዚህ ነው። ውስጣዊ የሆነ ሀይልን ወደ እንቅስቃሴ መለወጥ የሚያስችል የሞተር ዲዛይን ያለው አውቶሞቢል ሥራውን ያከናውን ዘንድ ቤንዚን ያስፈልገዋል። በጋዝ ወይም በናፍጣ ሊሠራ አይችልም። ቤንዚን ብቻ መኪናው ሊለጥ የሚገባውን አገልግሎት እንዲለጥ ያደርገዋል።

በወንዶችና በሴቶች ሁኔታ ውስጥ ነገሩ እንዲሁ ነው። አሠራር ለሪትን ይወስናል፤ ለሪት ፍላጎትን ይወስናል። ወንዶችና ሴቶች ግላዊ የሆነ የተለያየ ፍላጎት አላቸው፤ ምክንያቱም ሥሪታቸው የተለያዩ አሠራርን ለመተግበር ታቅዶ የተሠራ ነው። በለብአዊው ግንኙነት ውስጥ ለኬት የሚወለነው እነኚህን ልዩነቶች በመረዳት ልዩነቱንም በመቀበል ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔን በሙሉ ልባችን፣ ነፍላችንና ሀሳባችን፤ እንዲሁም ጎረቤታችንን አንደ ነፍላችን አንድንወድ ተናገረ። ለዚህ ምዕራፍ አላማ "ጎረቤት" የሚለውን ቃል የጾታ ልዩነት ባላቸው ባልና ሚስት፣ በእጮኛሞች፣ በጓደኞች ወይም ብዙም ቅርበት በሌለው ሁኔታ ውስጥ ግንኙነት ባላቸው ለዎች መካከል ያለ ወዳጅነት አድርገን እንመልከተው። እርግጥ ነው "ባልንጀራህን ውደድ" የሚለው ይህ ቃል የሚያመለክተው፤ ፊሊዮ፣ ስቶርጅና በጋብቻ አውድ ውስጥ ያለን ኢሮስ የሚጠቀልለውን መለኮታዊና ከፍ ያለውን አጋፔን ነው።

እርሱ ወይም እርሷ ማንም ይሁን፤ ወይም ግንኙነቱ ምንም ይሁን ባልንጀራችንን መውደድ እንደ እግዚአብሔር ፍጥረታዊ ሥሪታቸው ያለውን የወንድና የሴት የተለያየ አተገባበር ከዚህም የአተገባበር ልዩነት የሚመነጭ ፍላጎታቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ከሰጋ ዉደ ሠንፈስ

እግዚአብሔር በመጀመሪያው በራሱ ምላሌና በመልኩ መንፈሳዊውን ህልውና ፈጠረ፤ ከእርሱ እንደተገኘ የተናገረለትን ይህንን ህልውና "ሰው" ብሎ ጠራው። ከዚያ በኋላም እግዚአብሔር ለዚህ መንፈሣዊ ለው ቤቱ ይሆን ዘንድ ከምድር አፈር ፍጥረታዊ አካል አበጀለት። በዚህ ደረጃ የመጀመሪያው ለብአዊ አካል በጾታው

ወንድ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፤ እግዚአብሔር ካበጀው የወንድ አካል ላይ አንድ ክፍል ወስዶ ከእርሱ የሴትን አካል አበጀ፤ ይህም አካል መንፈስ ለሆነው "ሰው" ማደሪያ የሆነ ቤት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚነግረን ደህንኑ ነው፤ ". . . እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረው ቀን በእግዚአብሔር ምላሌ አደረገው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ ባረካቸውም ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው" (ዘፍ 5÷1-2)።

እግዚአብሔር ለውን ፈጠረ፤ ነገር ግን ወንድና ሴት አደረጋቸው። ይሁንና እዚህ ጋ የሚነሣው የተለመደ ጥያቄ፤ ለምን? የሚል ነው። በምዕራፍ ሁለት ላይ እንዳየነው፤ በመጀመሪያው እግዚአብሔር ብቻውን ነበር - በራሱ ሙሉና ሁሉን በሁሉ ብቃት ያለው። እግዚአብሔር ብቻውን ነበር- ብቸኛ ግን አልነበረም። በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ፍቅር ነበር፤ ፍቅር ደግሞ ሙሉ ይሆን ዘንድ የሚለጠው ተቀባይ የግድ ያስፈልግ ነበር። ፍቅር መስጠትን የሚጠይቅ ነው፤ ለለዚህ እግዚአብሔር የሚለጠው አንድ ለው ያስፈልገው ነበር። ለለዚህም እንደ የፍቅር ባህሪ መግለጫው እግዚአብሔር ለውን ፍቅሩን ይቀበል ዘንድ ፈጠረው።

ፍቅር ሙሉ ይሆን ዘንድ፤ ተቀባዮ ለጭውን መምለሉ የግድ ነው። ፍቅሩን የሚቀበለው እርሱን መምለል ይገባው ለለነበረ ነው፤ እግዚአብሔር ለውን በፈጠረ ጊዜ ለራሱ የተናገረው። እንደ መንፈላዊ ህልውና ለው በእግዚአብሔር መልክ በተፈጠረ ገዜ አደቱ ሙሉ ይመለላል። እግዚአብሔር ለጭ ነው፤ ለው ተቀባይ ነው፤ እግዚአብሔር አፍቃሪ ነው፤ ለው ተፈቃሪ ነው። እግዚአብሔር የፍቅር አፍላቂው ለው ደግሞ ምላሽ ለጭው ነው።

የእግዚአብሔር አላማ ለፈጠረው መንፈላዊ ለው በፍጥረታዊው ዓለም ላይ ገዥ ሆኖ እንዲለጥንበት ነበር። ነገር ግን መንፈላዊ የሆነ ህልውና ፍጥረታዊውን እውነታ ሊረዳውና ዋጋ ሊለጠው የማይችል በመሆኑ፤ እግዚአብሔር የፈጠረውን መንፈላዊ ለው ስጋዊ አካል አለበለው። "እግዚአብሔር አምላክ ለውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የህይወት እስትንፋስ አፍ አለበት። ለውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍ 2÷7)

አሁን ለው ፍጥረታዊ በሆነ አካል ውስጥ መኖር ጀመረ። ከምድር አፈር የተበጀው ይህ ለብአዊ "ወንድ" አካል አስቸጋሪ የምርጫ ፈተና ውስጥ ገባ። ለው የእግዚአብሔርን ፍቅር ተቀባይና

ለተቀበለው ፍቅር መልስ ሰጭም ነው፤ ከእርሱ የተገኘና - እርሱንም የሚመስል በመሆኑ ምክንያት ይህ ወንድ የሆነ ሰው ልክ እንደ እግዚአብሔር ፍቅርን ሰጭና ወዳጅ ነበር። ይሁንና እርሱን የሚመስል ፍቅሩን የሚሰጠው ወይም የሚቀበለው ማንም አልነበረም። እርሱን እንደፈጠረው እንደ እግዚአብሔር ወንድ "ሰው" ብቻውን ነበር። ሙሉና የተጠናቀቀ ይሆን ዘንድ ፍቅሩን የሚቀበል ያስፈልገው ነበር።

በዚህ ልዩ ጉዳይ ላይ ግልጽ መሆን እፈልጋለሁ። የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመቀበልና ምላሽም ለመስጠት መንፈሳዊ የሆነው "ሰው" ሙሉና የተጠናቀቀ ነበር፤ ፍጥረታዊ ህልውና የሆነው ወንዱ "ሰው" ግን የእርሱን ፍቅር የሚሰጠውና የሚቀበለው እርሱን የሚመስል ሌላ ፍጥረታዊ ህልውና ስላልነበረ ሙሉና የተጠናቀቀ አልነበረም። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል የፍጥረታዊውን ሰው ፍላጎት ማለትም ፍቅርን የመስጠትና የማፍቀር ፍላጎቱ ያልተሟላለት ነበር፤ ምክንያቱም እርሱን የሚመስል ማንም አልነበረም።

እግዚአብሔር ፍላጎቱን ስለተረዳ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቅ ነበር።

እግዚአብሔር አምላክ አለ፤ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት። እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት፤ እንቀላፋም ከጎኑም አንዱን አጥንት ወሰደ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ ይህች አጥንት ከጥንቴ ናት ስጋም ከሥጋየ ናት እርስዋም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል" (ዘፍ 2÷18:21-23)።

ለእርሱ የምትስማማ ረዳት ልትሆን የምትችለው፤ የወንዱን ፍቅር መቀበልና መመለስ ብቃት ያላት ናት። ስለዚህም ይህች ረዳት፤ በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ መንፈስ የሆነው ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ይቀበልና ይሰጥ እንደነበር፤ በፍጥረታዊው ዓለም ውስጥ የወንዱን ፍቅር መቀበልና ምላሽ መስጠት የምትችል መሆን ነበረባት።

እግዚአብሔር በወንዱ ላይ እንቅልፍ ከጣለበት በኋላ ከጎኑም አንድ የአካሉን ክፍል ወሰደ ሴትንም ሠራት። ወንዱ እንደተናገረው

እርሷ፤ "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፤ ሥጋም ከስጋየ ናት" እንደ ወንድ ሁሉ አንድ አይነት ከሆነ ቁስ የተሠራች ናት፤ "ሴት" ብሎም ጠራት፤ ባለ "መሀፀን" ሰው። ልክ መንፈሳዊው ሰው ከእግዚአብሔር እንደተገኘ ሁሉ፤ ሴትም የተገኘችው ከወንዱ ነበር። ልክ መንፈሳዊው ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲቀበልና ምላሽ እንዲሰጥ እንደተፈጠረ ሁሉ፤ እንዲሁ ደግሞ ሴት የተፈጠረችው የወንዱን ፍቅር እንድትቀበልና ምላሽም እንድትሰጥ ነበር።

እዚህ ጋ ሌላውን የተለየ ነገር ማስተዋል ጠቃሚ ነው። ወንድም ሆነ ሴት በመንፈሳዊ ህልውናቸው "ሰው" ናቸው። ሁለቱም ማንነቶች በመንፈስ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኙ ሲሆኑ መነሻና መድረሻቸውም እርሱ ነው። ከእርሱ ፍቅርን ይቀበላሉ ለእርሱም የፍቅርን ምላሽ ይሰጣሉ። ስለዚህም ሁለቱም ልክ እንደ እግዚአብሔር ፍቅርን ይሰጣሉ ይወስዳሉም። ይሁንና በፍጥረታዊ አሳቤ፤ የወንዱ ስሪት ለሴቷ ፍቅርን እንዲሰጥና ሴቷን እንዲወድ ተደርጎ ነው። የሴቷም ሥሪት የወንዱን ፍቅር እንድትቀበልና ምላሽ እንድትሰጥ ነው። ወንዱ ይሰጣል ሴቷ ትቀበላለች፤ ወንዱ ይወዳል፤ ሴቷ ምላሽ ትሰጣለች።

መስጠትና መቀበል

ለእግዚአብሔር፤ ወንድንና ሴትን በተመለከተ ይህ የፍጥረት መሠረታዊ መርህ ነው። እግዚአብሔር ለወንድ ይሰጣል፣ ወንድ ለሴት ይሰጣል። ሰው ከእግዚአብሔር ይቀበላል፤ ሴት ከወንድ ትቀበላለች። ብዙ ግንኙነቶች የሚፈርሱበት ምክንያት፤ ወንዶች ሴቶችን አስመልክቶ ከተቀባይነት ይልቅ ሰጭዎች መሆናቸውን ባለመገንዘባቸው፤ ሴቶችም ወንዶችን አስመልክቶ ከሰጭነት ይልቅ ተቀባዮች መሆናቸውን ባለመገንዘባቸው ነው። በማንኛውም ግንኙነት ውስጥ ሰው የእርሱ ለሆነችው ሴት መስጠት ካልቻለ በትክክል መስራቱን አቁሟል ማለት ነው። እንደዚሁ ደግሞ ሴት የእርሷ ከሆነ ሰው መቀበል ካልቻለች ወይም እንድትሰጥ ከተገደደች በትክክል መስራቷን አቁማለች።



ወንድ ይሰጣል፤ ሴት ትቀበላለች፣ ወንድ ይወዳል ሴት ምላሽ ትሰጣለች።

በግንኙነቶች ውስጥ የሚፈጠሩ አብዛኛዎቹ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት የሚችሉት፤ ማንኛውም ወንድ ወይም ሴት ቀላል የሆነውን እውነት ሲያውቁና ሲተገብሩትም ከቻሉ ነው።

የወንዶች ስሪት እንዲሰጡ ተደርገው ሲሆን የሴቶቹ ስሪት ደግሞ እንዲቀበሉ ተደርገው ነው። ለዚህ ደግሞ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው አካላዊ ልዮነት ማስረጃ የሚሆን ነው። የወንድ ወሲባዊ ብልት ስሪቱ እንዲሰጥ ነው፤ የሴት ደግሞ ለመቀበል ነው። የግብረሶዶማውያን ወንዶችና የሴት ለሴት የፆታ ግንኙነት አድራጊዎች ተግባር ግብረገባዊነት የጎደለውና አግባብነት የሌለው የሚሆንበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። እነዚህ ወገኖች እግዚአብሔር ለሰው ዘርና ለፍጥረቱ አቅዶ ያዘጋጀውን ሰብአዊ የግንኙነት መርህ እየተቃወሙ ነው። በሁለት ሰጭዎችና በሁለት ተቀባዮች መካከል አግባብነት ያለውና ውጤታማ የሆነ እውነተኛ ግንኙነት ለማድረግ በፍጹም አይቻልም።



በግንኙነቶች ውስጥ የሚፈጠሩ አብዛኛዎቹ ችግሮች መፍትሔ ሚገኘት የሚችሉት፤ ሚገኛውም ወንድ ወይም ሴት ቀባል የሆነውን እውነት ሲያውቁና ሲተገብሩትም ከቻሉ ነው።፤ የወንዶች ስሪት እንዲሰጡ ተደርገው ሲሆን የሴቶቹ ስሪት ደግሞ እንዲቀበሉ ተደርገው ነው።

ከወንዱ አካል ከተወሰደው ክፍል እግዚአብሔር ሴትን በሠራት ጊዜ፤ ከወንዱ ለመቀበል በአካል ብቃት ያላት ትሆን ዘንድ ከተጨመረላት ክሮሞዞም በስተቀር፤ በሁሉም መንገድ ልክ እንደ ወንዱ ሆና ነው የተሠራችው። ልጅን የመጸነስና የመውለድ ብቃት ያገኘችውም በዚህ ነው። የወንዱ ዘርን የመስጠት ብቃት አስቀድሞ የነበረ ሲሆን፤ ይፈልግ የነበረው ተቀባይ ነበር። ልክ እግዚአብሔር ለውን ሲፈጥር (ወንድን ማለቴ አይደለም) በመንፈሳዊ ማንነቱ ከእርሱ ይቀበል ዘንድ እንደነበረ፤ ሴትንም የፈጠራት በአካላዊ ማንነት ከወንዱ ትቀበል ዘንድ ነው።

ይህ በወንድና በሴት መካከል ያለው መቀባበል ከወሲባዊው ጉዳይ ያለፈና የሰፋ እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ አፈልጋለሁ። እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያውኑ እንደመሠረተው መርህ፤ በጋብቻ ውስጥ ያልሆነ ጾታዊ ግንኙነት ሁሉ ኀጢያት የሆነ፤ ስነምግባር የጎደለውና፤ አግባብነት የሌለው ነው። ወንዶች በተፈጥሮ ስጪዎች ሴቶች ደግሞ በተፈጥሮ የሚቀበሉ ናቸው፤ ይህ ደግሞ በማንኛውም የህይወት እንቅስቃሴ በሚደረግ ግንኙነት ውስጥ እውነት ነው።

እግዚአብሔር ብቻ ነው ሰጭ፤ እንደ ፈጣሪነቱ የፍጥረት ሁሉ መገኘት አነሳሽ ነው። ማንኛውም ህልውና ያገኘ ነገር

ህልውናውን ያገኘው እግዚአብሔር መነሻ ስለሰጠው ነው። በሉአላዊነቱ ፍጥረትን ሁሉ በፈቃዱ ህልውና የሰጣቸው እርሱ ነው። በመንፈሣዊው ዓለም ውስጥ ለው (ወንድ ማለቴ አይደለም) ከእግዚአብሔር የተገኘ በመሆኑ እርሱም እንዲሁ አነሳሽ ነው።

በፍጥረታዊው ዓለም ውስጥ ወንዱ እንደ ሰጭ እንዲሁ አነሳሽ ነው። እንደተቀባይም ሴቷ በውንዱ አነሳሽነት ፍቅርን ለመቀበል እንድትችል ተደርጋ የተሠራች ነች። አሁን ስህተት እንደተናገርኩ አድርጋችሁ አታስቡ፤ ሴቶች በዚህ ነገር ረቂቅ ናቸው። እግዚአብሔር የወንድን ያህል አይምሮ ነው የሰጣቸው (እንዲያውም ብዙውን ጊዜ የበለጠውን ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሲሠራቸው፤ እንደሴት ወንዱ እግባብ ያለወ ትክክለኛ አነሳሽነትና አመራር ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጎ ነው።

ብዙ ወንዶች በእነርሱ ህይወት ውስጥ ያሉ ሴቶች አይምሯቸውን ማነቃቃት ያቃታቸው ሲመስላቸው በፍርሃት ውስጥ ይገባሉ። እናንተ ወንዶች ለእናንተ መልካም ዜና አለኝ። እንደ ወንድ እኛ አነሳሾች ነን። ሴቶች በቀላሉ አይምሯችንን አስክናነሳሳ ድረስ ይጠብቁናል።

ከዚህ ቀጥሎ የምዘረዝራቸው በወንዶችና በሴቶች መካከል ላለ የመስጠትና የመቀበል ግንኙነት ጠቃሚ የሆኑ ጥቂት መርሆዎችን ነው።

1. ወንድ ሲጠይቅ፤ ሴት ትቃወማለች፤ ምላሽ አትሰጥም።
2. ወንድ ሲሰጥ፤ ሴት ምላሽ ትሰጣለች።
3. ወንድ ራሱን ሲሰጥ ሴት ትቀበላለች። ወንድን እንደመቀበል ያህል ለሴት ልጅ የከበረ ነገር የለም። እራሱን እንደማይሰጣት ወንድ ሴት ልጅን የሚደብራት ነገር የለም። ሚስጥሩ እዚህ ነው ወዳጆች፤ ሴት ልጅ እንድትቀበልህ የምትፈልግ ከሆነ ራስህን መስጠት የምትችል ወንድ ሁን። ነገሩ ይህን ያህል ቀላል ነው።
4. ወንድ በሀይል የሚያስገድድ ከሆነ ሴት ፈቃደኝነቷን ትነፍጋለች፤ ወንድ ወደ ሴት በማስገደድና በጉልበት የሚቀርብ ከሆነ፤ ሴት ምላሽ የመስጠት ፈቃደኝነቷን ትነፍጋለች።

5. ወንድ ሲያካፍል፤ ሴት ትንከባከባለች። በህይወቱ ውስጥ ከሴት ጋር መካፈል የሚፈልግን ሰው ካገኛችሁ፤ የእርሷ ለሆነው ለዚህ ሰው እንክብካቤ የምታደርግ ሴት ታገኛላችሁ።

6. ወንድ ሲመራ፤ ሴት ትከተላለች። ወንድ እግዚአብሔር የሰጠውን የመሪነት ሃላፊነት ለመወጣት ሊተጋ፤ ሴት ለእርሱ መሪነት ምላሽ ትሰጣለች። መሪነት ማለት ልክ እንደ አሰቃ ሁልጊዜ ሌሎች ማድረግ የሚገባቸውን ነገር የሚናገር ማለት አይደለም። መሪነት ማለት ከፊት መቅደም ማለት እንጂ ሌሎችን ከፊት ማስቀደም ማለት አይደለም። መልካም መሪዎች መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በዲግሪ የሚመሩ አይደሉም። ኢየሱስ ክርስቶስ የመራው ምሳሌ በመሆን ነው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ታላላቅ መሪዎች ሙሴ፣ ጴጥሮስ፣ ጳውሎስና ሌሎችም የመሩት ምሳሌ በመሆን ነው። ምሳሌ በመሆን መምራት ማለት ሌሎች እንዲያደርጉት የምንፈልገውን ራሳችን አስቀድመን ማድረግ ማለት ነው።

የፍላጎት መርህ

እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረው አስቀድሞ በወሰነው የተለየ መርህ እንዲሠሩ አድርጎ ነው። መርሆዎች፤ ፈጣሪ የፍጥረቱን አሠራር ይገዛና ይቆጣጠር ዘንድ የመሠረታቸው መሠረታዊ መመሪያዎች፤ መሠረታዊ ህግጋትና ደረጃዎች ናቸው። ማንኛውም ህያው የሆነ ፍጥረት ሁሉ የተፈጠረው በመርህ እንዲኖር ነው። ያለእነኝህ መርሆዎች ህይወት ያልተረጋጋና ፍጻሜያቸው ያልታወቀ ልምምዶች እንጂ ሌላ ልትሆን አትችልም።

ለመርህ የምንጠቀመው ሌላ ቃል ፍላጎት ነው። ፍላጎት፤ ፈብራኪዎች ስለምርታቸው ትክክለኛ አሠራር አስቀድሞ የታቀደውን የሚያስተውቁ መርሆዎች ናቸው። በሌላ ቃላት ለመግለጽ፤ ፍላጎት ማለት ውጤታማ ለሆነ አሠራር መሟላት ያለበት አስፈላጊ ሁኔታ ነው። ማንኛውም ፈብራኪ ሞርቱን ሲሠራ ሲያቅድ በተወሰነ ሞንገድ ተግባሩን እንዲያከናውንና አስፈላጊ ሁኔታዎችን ወይም ፍላጎቶችን አቅዶ ነው። ስሊዘህም የአንድ ምርት አግባብነት ያለው አሠራር ገና በአቅድ ላይ እንዳለ አስቀድሞ የተወሰነለት ነው።

ማንኛውም የምርት ውጤት የሚመጣው አስፈላጊ የሆነ ፍላጎትን በውስጡ ይዞ ነው። አንድ የምርት ውጤት በራሱ ውስጥ የያዘውን ፍላጎት እንደማይወስን ሁሉ ተጠቃሚውም ሊወስን

አይችልም። ምክንያቱም ያ ፍላጎት ገና ምርቱ ሲመረት በውስጡ አለ። ገና በስሪቱ እቅድ፤ ውስጣዊ ነዳጅ አቀጣጣይ ሞተር፤ ለቤንዚኑና ቅባትነት ላለቸው ዘይቶች እጅግ አስፈላጊ ነገር ተደርጎ ነው የታቀደው። ያለዚያ ሊሠራ አይችልም።

እንደዚሁ ሁሉ፤ ማናቸውም ወንድና ሴት፤ በአግባቡ ይሰሩ ዘንድ፣ ህይወት ውጤታማ እንዲሆንና እንዳንድ ጊዜም ህይወትን ጠብቆ ለመቆየት እንኳን፤ ወደ ምድር ሲመጡ አስቀድሞ የተወሰነና በውስጣቸው የተቀመጠ ፍላጎት ይዘው ነው። ብዙውን ጊዜ በግንኙነት ውስጥ ሰሚከሰቱ ችግሮች ቀዳሚ ምክንያት የሚሆነው እውነት፤ ወንዶችና ሴቶች አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለይተው አለማወቃቸው ነው። ምርት ላይሸጥ ሲቀር ወይም ግንኙነቶች በፈረሱ ጊዜ ሁሉ ዋነኛው ችግር የአንደኛው ወይም የሌላኛው ፍላጎት አለመሟላት ነው።

እነኝህን ፍላጎቶች ችል ማለት መጨረሻው የምርቱ መውደቅ፣ የግንኙነቱም መሞት ይሆናል። ፍላጎት ላይ ጥንቃቄ ከተወሰደ ችግሮች ላይ ጥንቃቄ ተወሰደ ማለት ነው። በእውነቱ ጉዳዩ ይህን ያህል ቀላል ነው።

ብዙውን ጊዜ በግንኙነት ውስጥ ሰሚከሰቱ ችግሮች ቀዳሚ ምክንያት የሆነው እውነት፤ ወንዶችና ሴቶች አንዱ የሌላውን ፍላጎት ለይተው አለማወቃቸው ነው።

ለዚህ ነው በሰዎች ህይወት ፍላጎት እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ በጣም ጠቃሚ የሚሆነው።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ፍላጎት ባህሪን ይቆጣጠራል፤ ያነሳሳልም። ማንኛውም ሰው የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ፍላጎቱን ለማሟላት የሚያደርገው ጥረት ነው። ፍላጎት ባህሪን ይወስናል። ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ ህይወታቸውን እንኳን እስኪጥሉ ይሰጣሉ። ለምሳሌ ያህል ለምንድነው እጅግ ብዙ ሴቶች ባልፈሰጉት አፀያፊ የሆነ ግንኙነት ውስጥ የሚገቡት? መልሱ የተወሳሰበ ቢሆንም፤ ብዙውን ጊዜ ግን፤ ቢያንስ በከፊል፤ ያ ግንኙነት ከሚያስከትለው ያልተፈሰገ ተግባር ጀርባ የህይወታቸውን ፍላጎት ለማሟላት የሚፈይደው ነገር አለ።

ለዚህ ነው በወንዶችና በሴቶች መካከል ባለ ግንኙነት እንዳቸው የሌላኛቸውን ፍላጎት ማወቁ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው። የማንኛውም ግንኙነት ህይወት የሌላውን ሰው ፍላጎት ማሟላት

ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ፍቅር የሚገለጥበት አንዱ መንገድ ይሄ ነው፤ ፍቅር የሌላውን ሰው ፍላጎት ለማሟላት ቁርጠኛ ተግባር የሚያደርግ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፤ ሊሟላ ያልቻለ ፍላጎት የፍርሃትና የውጤት አልባነት ምንጭ ነው። በግንኙነት ውስጥ ፍርሃት የሚፈጠር ከሆነ ያ ሊሟላ ያልቻለ ፍላጎት እንዳለ የሚያመለክት ነው። በፍርሃት የተሞላ ሰው ውጤታማ ያልሆነ ሰው ነው።

የህይወት ቁልፍ ነገር ፍላጎትን ማሟላት ነው። ነገሩ ያን ያህል ቀላል ነው። ፍላጎቶች የሚሟሉ ከሆነ ፍጥረት መስራት ይጀምራል። የረኩ ፍላጎቶች ውጤታማ የሆኑ ሰዎችን ያስገኛሉ፤ ውጤታማ ሰዎች ደግሞ እንደ ሰብአዊ ፍጡርነታቸው ያላቸውን ሙላት ያለውን እምቅ ችሎታቸውን ተግተው ሊፈልጉና ሊለማመዱት ነፃ ናቸው። በማንኛውም ግንኙነቶች ውስጥ አብይ ግብ የሆነው የፍላጎቶች መሟላት ነው፤ በግንኙነታችን ውስጥ አብረውን ያሉትን የሌሎች ሰዎች ፍላጎት እንጂ የራሳችንን ፍላጎት ለማሟላት ትኩረት መስጠት የለብንም። ጤነኛ የሆነ ግንኙነት እያደረግን መሆኑን ለመፈተን፤ በየጊዜው ራሳችንን አንድ ጥያቄ ልንጠይቅ ያስፈልገናል፤ የማንን ፍላጎት ነው እያሟላን ያለነው፤ የራሳችንን ወይንስ የሌሎችን? በራሳችን ፍላጎት ላይ ትኩረት ሰጥተን ከሆነ፤ ግንኙነታችን በችግር ውስጥ ነው። ውጤታማና ጤናማ በሆነ ግንኙነት ውስጥ ሁሉቱም ወገኖች አንዳቸው የሌላኛ ቸውን ፍላጎት ለማሟላት ቅድሚያ ይሰጣሉ።

[redacted] የህይወት ቁልፍ ነገር ፍላጎት ማሟላት ነው።

ስለ ጤናማ ግንኙነት ጠቃሚና ታላቅ የሆነ ነገር ደግሞ፤ የሌላውን ሰው ፍላጎት ለማሟላት ትኩረት በሰጠን ጊዜ፤ ብዙውን ጊዜ የእኛው ፍላጎት ይሟላል። ይህ ሰጥቶ የመቀበል፤ ጎድሎ የመሞላት ህግ ነው። ፍላጎቱ የተሟላለት ሰው የሌላውን ፍላጎት ለማሟላት ትኩረት ለመስጠት ነፃነት አለው።

ስምንቱ የጠንድና የሴት ፍላጎቶች

በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያለውን ልዩነት አጉልተው የሚያሳዩ አምስት መሠረታዊ የሆኑ የወንድና የሴት ፍላጎቶች አሉ። አብሮን ያለውን ጓደኛችንን ምን ያህል እንደምንወደው የሚወስነው፤ አብዛኛውን ጊዜ እነኝህን ፍላጎቶች በማወቅና ልዮነቶቹንም በመገንዘብ ነው።

የወንድ የመጀመሪያው ፍላጎት የግብረስጋ ግንኙነት ፍላጎት መሟላት ነው። ወንዶች በዚህ ረገድ ጠንካራ ፍላጎት አላቸው። ይህ ጠንካራ ፍላጎትም ከእግዚአብሔር የተሰጠና በወንዱም ላይ በጉልህ የሚታይ ሲሆን፤ ምክንቱም የሰብአዊው ቤተሰብ ቀዳሚና ዘር ተሸካሚ በመሆኑ ነው። ስለዚህም ነው ወንዶች ምንጊዜም ሰወሲባዊ ግንኙነት ዝግጁዎች የሆኑት። የወሲብ ጠንካራ ፍላጎታቸው ጊዜ ቆጥሮ የሚመጣ አይደለም።

እርግጥ ነው፤ በጋብቻ ግንኙነት አውድ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በወንድም ሆነ በሴት የሚፈጸም ጾታዊ ግንኙነት ጎጢያትና አግባብነት የሌለው ነው። እንግዲህ ለአካለ መጠን የደረሰ ያላገባ ሰው ጠንካራ የወሲብ ፍላጎቱን ምን ሊያደርገው ይችላል? ፍላጎቱን የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ደግሞ አቅርቦትን የሚያዘጋጅ ነው። ለሚፈልጉት ለእነርሱ፤ አግባብ ባለው ጋብቻ ውስጥ እስኪጠቃለሉ ድረስ፤ ያንን ጠንካራ ፍላጎት የሚቆጣጠሩበት ፀጋና ችሎታ ይሰጣቸዋል።

የሴት የመጀመሪያው ፍላጎቷ እንክብካቤ ነው። ሴቶች እንደ ወንዶች ወሲብን የሚፈልጉ አይደሉም። እርግጥ ነው ብዙ እንክብካቤ ተጨምሮበት ከባሏ ጋር በምታደርገው ጾታዊ ግንኙነት ትደሰታለች። ሴት እንክብካቤ ካላገኘች ተግባሯን በአግባቡ አታከናውንም። በግንኙነት ውስጥ አብሯት ያለው ወንድ እንክብካቤ የማግኘት ፍላጎቷ መሟላቱን ማረጋገጥ አለበት።

እንክንካቤ ማለት በአካልም ይሁን በቃሉ ፍቅርን፤ ህላፊነት የሚሰማው መሆኑን መግለጽና አካላዊም ሆነ አካላዊ ባልሆነ ተግባሮቿ ድጋፉንና እርዳታውን መስጠት ማለት ነው። ይህንም ክንዷን በመያዝ፤ በመሣም፤ አበባ፤ የስጦታ ካርዶችና ስጦታዎችን በመስጠት፤ ትህትና የተሞላበት ገጽታ በማሳየት እንዲሁም በየእለቱ መጠነኛ የሆነ ስለ እርሷ እንደሚያስብ ማሳየትና ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች በመተግበር ይገለጻል።

ሁለተኛው መሠረታዊ የወንድ ፍላጎት ደስታ የተሞላበት ባልንጀርነት ነው። ወንድ ሴት የደስታው ተካፋይ ትሆን ዘንድ በህይወቱ ስፍራ እንዲኖራት ይፈልጋል። ብዙ ሴቶች በወንድ ህይወት ውስጥ ያለውን ይህንን ፍላጎት ጠቃሚነት አይገነዘቡትም። ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ለይታችሁ አወቁና በዚህ ተግባሩ ውስጥ አብራችሁ ተሳተፉ። ምንም እንኳን ራሳች ነገሩን ባትወዱትም ቢያንስ ቢያንስ ነገሩን እንዲገልጽላችሁና እንዲያስተምራችሁ በቂ

ፍላጎት ማሟየት ያስፈልጋል። ስፓርት የሚወድ ከሆነ ውድድሮችን አብራችሁ ተመልከቱ። በዝግታ በእግሩ መጓዝ የሚወድ ከሆነ ከእርሱ ጋር አብራችሁ ተጓዙ። ሙዚቃ መስማት ወይም መጫወት የሚወድ ከሆነ ፍላጎት በማሟየት ከእርሱ ጋር ተሳተፉ። ይህንን አስታውሱ፤ ቁልፉ ጉዳይ የእርሱን እንጂ የራስን ፍላጎት ማሟላት አይደለም።

የሴት ሁለተኛው ትልቁ ፍላጎቷ ልዩ ልዩ ግንኙነቶችንና ጭውውቶችን ማድረግ ነው። አብሯት ያለው ወንድ ከእርሷ ጋር እንዲያወራ ትፈልጋለች። ብዙ ወንዶች በዚህ ረገድ ችግር አለባቸው። አንዳንዶች እንዲያውም ወንዳወንድ የሆነ ወንድ ዝምተኛ መሆን አለበት የሚል የተሳሳተ አመለካከት አላቸው። ዝምተኛ ወንድ በሴቷ ፍልቀስሜት ላይ ርሃብ የሚፈጥር ነው። ጭውውትን ትራባለች። ብዙውን ጊዜ የዚህ የመጨረሻው ውጤት ጭውውት ለእርሷ አስፈላጊ እንዳልሆነ እስከመቁጠር ትደርሳለች። ስለዚህ ወንድየው፤ ከእርሷ ጋር አውራ። የምተወራውንም አዳምጣት። ሀሳብህን ለእርሷ ለማካፈል ጊዜ ስጣት፤ ይህም የበላይነት ስሜት ባለበት ሁኔታ ሳይሆን ስሜቷን በመጋራት መንፈስ ሊሆን ይገባዋል። ለዚህ የምታውለው ጊዜ በመጋራት መንፈስ ሊሆን ይገባዋል። ለዚህ በምታውለው ጊዜ ጠንካራና ጤነኛ በሆነ ግንኙነት ውስጥ ውጤታማ ትርፍ ታፍሣለህ።

ሦስተኛው የግንኙነት መሠረታዊ የወንድ ፍላጎት፤ ውበት ያላት ሴት ነች። የዚህ ምክንያት ደግሞ ወንድ በእይታ የሚማረክ መሆኑ ነው። ስሪታቸው በቃ እንዲህ ነው። መዋብ የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ በተለይም ከሚሰጠው ከእካላዊ ቁንጅና የዘለለ ትርጉም ያለው ነው። ውበት ያላት ሴት ራሷን የምትንከባከብና በአለባበስና በፀጉር አሠራሯ ከእርሷ ጋር ያለውን ወንድ ልትስብና እርሱን ለመማረክ ለማነሣሣት አስፈላጊ የሆነውን ነገር የምታደርግ ናት።

የሴት ሦስተኛው መሠረታዊ ፍላጎት ሀቀኝነትና ግልጽነት ነው። እነኝህ ሁለት ቃላት ብዙ ወንዶችን አረፍት ይነሷቸዋል፤ ምክንያቱም በግልጽ መናገር ስለማይወዱ ነው። ግልጽና ሀቀኛ መሆን ማለት፤ በግንኙነት ውስጥ አግባብነት ያለውን አስፈላጊ ሀሳብ በግልጽና ሙሉ በሙሉ ለመከፋፈል ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው። ለምሳሌ ያህል በጊዚያዊነት ከተገናኙ ወንዶችና ሴቶች ይልቅ ባልና ሚስት በጉዳዮች ላይ በጥልቀትና በቀረበ መልኩ ይወያያሉ። ወንዶች ሆይ ጥቂት ልመርቅላችሁ፤ ግልጽነታችሁና ሀቀኝነታችሁ ለእርሷ በጨመረ መጠን ያህል፤ እርሷ በእናንተ ላይ ያላት እምነት

ይጨምራል፤ ይበልጥም ትቀርባችኋላች፤ ምክንያቱ ደግሞ ግልጽነትን የምትተረጉመው እንደ ፍቅር መግለጫ አድርጋ በመሆኑ ነው።

የመጨረሻዎቹ ሁለት የወንድና የሴት ፍላጎቶች ምንም እንኳን መርሆዎቹ በማናቸውም ሁኔታዎች ውስጥ እኩል ተግባራዊ የሚሆኑ ቢሆንም፤ ካልተጋቡ ጥንዶች ይልቅ ይበልጡን ባገቡና ቤት ንብረት በያዙ ባለትዳሮች የሚተገበሩ ናቸው። ገና ያልተጋቡ ጥንዶችም በራሳቸው ሁኔታ ውስጥ ነገሮችን የተሟሉ ለማድረግ እነዚህን መርሆች ሊለማመዷቸው ያስፈልጋል።

አራተኛው የወንድ መሠረታዊ ፍላጎት የቤተሰቡ ድጋፍ ነው። ወንድ በየእንዳንዱ ቀን መጨረሻ ላይ ሰላምንና ፀጥታን የሚያገኝበትን ገነት፤ የደህንነት ዋስትና ያለውን መጠለያ ይፈልጋል። በእጭሩ ትብብርን የሚያገኝበት የቤተሰብ ሁኔታን ይፈልጋል። ወንዶች የቤተሰባቸው መጋቢዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ተሠርተዋል። ወንዶች ስጭዎች መሆናቸውን አስታውሱ። ወንድ ቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ሰማቅረብ ወጥቶ ከሀይወት ጋር ሲፋለም ውሎ ወደ ቤቱ ሊመለስ የማይፈልገው ነገር ከቤተሰቡ ጋር መፋለም ነው። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሴቶችም ወደ ስራው ዓለም እየተቀለቀሉ ስለሆነ ይህ የቤተሰብ ድጋፍ ለባልም ሆነ ለሚስት በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው። በቤት ውስጥ ሌላ ብጥብጥ ሳይጨመርበት እንኳን የቀኑ ወፍጮ በራሱ ብዙ ችግር ያለበት ነው። ሁለቱም ባልና ሚስት በዚህ በጣም አስፈላጊ በሆነ የቤተሰብ ድጋፍ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሊሰጡበት ያስፈልጋል።

የሴት አራተኛው መሠረታዊ ፍላጎት የገንዘብ ድጋፍ ነው። ይህ ምናልባትም ከቤት ውጭ ለምትሠራ ሴት እጅግም ዋነኛ ጉዳይ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ከቤት መስራት ለመረጠችና ይልቁንም ልጆች ለምታሳድግ ሚስት ዋንኛ ጉዳይ ነው። እነዚህ ፍላጎቶች እርስ በእርስ የተሳሰሩ ናቸው። ወንዱ በተመቻቸ ቤት ውስጥ የቤተሰቡን ድጋፍ የሚፈልግ ከሆነ፤ በዚህ መንገድ ልትረዳው ትችል ዘንድ ሚስቱ ገንዘብ ያስፈልጋታል። እስተማማኝ ዋስትና እንዲሰማት የቤተሰቡ የገንዘብ ፍላጎት መሟላቱን ማረጋገጥ ትፈልጋለች።

የመጨረሻው፤ ወንድ መደነቅንና መከበርን ይፈልጋል። እዚህ ጋ የሚፈጠረው ችግር ብዙ ወንዶች አሁን በህይወታቸው ውስጥ በቤቶቻቸው ላይ የሚያሣዩት ሁኔታና የሚሠሩት ሥራ

ከሴቶች አድናቆትንም ይሁን ከበሬታን የሚያስገኝላቸው አይደሰም። ይሁን እንጂ ይህ አድናቆትንና ከበሬታን የማግኘት ፍላጎታቸውን አይሰውጠውም። ወንዶች የተሠሩት የሚንከባከቧቸው ሴቶች የሚያደንቋቸውና የሚያከብሯቸው መሆኑን ከማወቅ ፍላጎት ጋር ነው። ይሁንና አድናቆትና ከበሬታ ሊሰጠው የሚገባ ሃላፊነት ያለበት ባህሪን ማሳየት ይጠብቅባቸዋል።

ሴት ለቤተሰቧ የተለጠ ህይወት ትፈልጋለች። በሌላ አባባል፤ ሚስት ባሏ ለቤቱና ለትዳሩ የተሰጠ ህይወት እንዳለው፤ እርሷን ከሌሎች ሴቶች ሁሉ እንደሚያስቀድማት፣ ልጆቿንም ከሌሎች ልጆች ሁሉ እንደሚያስቀድም ማወቅ ትፈልጋለች። የጊዜ አጠቃቀሙን በሚመለከት በምሽት ፈጥኖ ወደ ቤት መግባቱንና ለቤተሰቡ ቅድሚያ መስጠቱን ማወቅ ትፈልጋለች።

ወንዶችም ሆንን ሴቶች፤ ያገባንም ሆነ ያላገባን፤ ማንም እንሁን በማንኛውም ግንኙነት ውስጥ ባልንጀራችንን ለመውደድ ማድረግ የምንችለው ትልቅ ነገር፤ የእርሱን ወይም የእርሷን የተለየ ፍላጎት መፈለግና መረዳት፤ እነዚህንም ፍላጎቶች እንደሚሟሉ ለማድረግ ራስን መስጠት ነው። በዚህ ዓለም ሰዎች ምን እንደሚያገኙ እንጂ ምን እንደሚሰጡ ፍላጎት በሌላቸው ሁኔታ ውስጥ ራስንና የራስን ጥቅም ፍለጋ ሲባል ብቻ የሚመሰረቱ ብዙ ግንኙነቶች አሉ።

ልብ በሉ አጋፔ፤ እውነተኛው ፍቅር በተፈጥሮ የሚሰጥ ነው። የሌሎችን ፍላጎት ለማሟላት ራሳችንን ስንሰጥ ፍቅርን በእውነተኛ መልኩና በንጽህናው እየገለጽነው ነው። ይህም ፍቅር፤ እርሱ ራሱ ፍቅር የሆነውንና ፍቅርም ከእርሱ ዘንድ የሆነውን የእግዚአብሔር ልብ የሚገልጽ፣ ከማንም ምንም ሳይጠብቅ እንዲሁ የሚሰጥና ምላሽን ተስፋ የማያደርግ ፍቅር ነው።

መርሆዎች

1. መንፈስ የሆነው "ሰው" ከእግዚአብሔር እንደተገኘ "ሴት" የተገኘችው ከወንድ ነው። ልክ መንፈስ የሆነው "ሰው" የተፈጠረው የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊቀበልና መልስ ሊሰጥ እንደነበር፤ እንዲሁ ደግሞ ሴት የተሠራችው የወንድን ፍቅር እንድትቀበልና ምላሽም እንድትሰጥ ነው።

2. እግዚአብሔር ሰውንድ ይሰጣል፤ ወንድ ለሴት ይሰጣል፤ ወንድ ከእግዚአብሔር ይቀበላል፤ ሴት ከወንድ ትቀበላለች።

3. ልክ እግዚአብሔር ሰውን (ወንድን ማለት አይደለም) በመንፈሳዊው ደረጃ ከእርሱ እንዲቀበል እንደፈጠረው፤ በፍጥረታዊው ደረጃ ከወንዱ ትቀበል ዘንድ ሴትን ሠራት።

4. ወንዶች በፍጥረታቸው የሚለጡ ሴቶች ደግሞ በፍጥረታቸው የሚቀበሉ ናቸው። ይህ ደግሞ በማኛውም የህይወት አቅጣጫ ግንኙነቶች ውስጥ እውነት ነው።

5. ምርት በወደቀ ግንኙነቶችም በፈረሰ ጊዜ ሁሉ፤ አንድ ዋንኛ ችግር ተከስቷል፤ አንድ ወይም ሌላ ፍላጎቶች አልተሟሉም።

6. ፍቅር የሌላውን ሰው ፍላጎት ለማሟላት ራሳችንን እንድንሰጥ ያደርጋል።

7. የወንድ ቀዳሚው መሠረታዊ ፍላጎት የወሲባዊ ግንኙነት ፍላጎቱ መሟላት ነው። ለሴት ደግሞ ርህራሄ የተሞላበት እንክብካቤ ነው።

8. ሁለተኛው የወንድ በጣም መሠረታዊ የሆነው ፍላጎት ደስተኝነት የተሞላበት ባልንጀርነት ሲሆን፤ የሴቷ ደግሞ ልዩ ልዩ ግንኙነቶችና የንግግር ልውውጦች ናቸው።

9. በግንኙነት ውስጥ ሦስተኛው የወንድ መሠረታዊ ፍላጎት ቆንጆ ሴት ነች፤ የሴት ደግሞ ሀቀኝነትና ግልጽነት ነው።

10. አራተኛው የወንድ መሠረታዊ ፍላጎት የቤተሰብ ድጋፍ ነው፤ የሴት ደግሞ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

11. አምስተኛው የወንድ መሠረታዊ ፍላጎት አድናቆትና ከበሬታ ሲሆን የሴት ደግሞ ለቤተሰቧ የተለጠ ህይወት ነው።

ክፍል ሦስት

ስህደጠት ዘመን ዙሱ ፍቅርን መገንዘብ ምሰፉፍ ስንድ

ጋብቻ፤ የተመሰነ የተግባር ሚና የሴሰው ግንኙነት

ጋብቻ አስደናቂ የህይወት ልምምድ ነው። በቅርብ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ብዙዎች በዚህ እንደሚስማሙ አስባለሁ፤ የጋብቻ ሂደት አንድ ጊዜ አስደሳች፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ስጋት የተቀላቀለበት በመጨረሻም መጠነኛ የሆነ ፍርሃት ያለበት ነው። ምንም ቢሆን ጋብቻኩ አብሯት ወይም አብራው ለመኖር ካለሙት ሰው ጋር አዲስ ቤትና አዲስ ቤተሰብ ለመመስረት የተደላደለን የልጅነት ዓለም መኖሪያ ቤት ትቶ መውጣት ነው። ይህ ደግሞ ቀድሞ ከነበሩበት የቤተሰብና የዘመድ አገር የሆነ ገንዘብ ወስዶ ውቅያኖስን በማቋረጥ በሌላ አገር ውስጥ አዲስ ህይወት መጀመርን የመሰለ ነው። መጋባት በውስጡ የሆነ የጥርመሣ መንፈስ ያለበት ነገር፤ የትልቅ ነገር ግኝት ጣህም የተዋሃደውም ነው። እያንዳንዱ ነገር አዲስና የተለየ ነው፤ በመጀመሪያው ሾላ በድፍን አይነት የሆነበት እንዲያውም በውል ያልተወቀ አደጋ የሚሸትበት ጭምር ነው።

በነዚያ አስደሳች በሆኑ የትውውቅና የቃል ኪዳን የጋብቻና ከጋብቻ በኋላ ያለ የሽርሽር ጊዜ፤ አየሩ ራሱ በሆነ ምትህታዊ ሃይልና በአስገራሚ ነገሮች የተሞላ ይመስላል። አዲሶቹ ባለትዳሮች በሙሉ የህይወትና የአካል ጥንካሬ አለምን ለመጠቅለል በተዘጋጀ ስሜት ይሆናሉ። በዚያ ጊዜ ለእነርሱ የሚዘጋ በር የለም፤ ምንም ዓይነት ግብ ለእነርሱ ሩቅ አይደለም፣ የትኛውም ህልም ከባድ አይሆንም። አለም ለእነርሱ አይስተር እንደሚባል ከባህር እንደሚገኝ የምግብ አይነት ጣፋጭ ናት። ምንም ነገር ሊይዙትና ሊጨብጡት ከሚችሉት በላይ አይደለም።

ይሁን እንጂ እየቆየ፤ እውነታ መገለጥ ይጀምራል። በጋብቻ ሽርሽር ውስጥ ያንጸባረቀው ወሲባዊ ግለት አንድ ቦታ ላይ ይደበዝዛል፤ "አለምን እናሸንፋታለን" የሚለው አዝማሚያ ዝግ

ብሎ ይወርዳል። አንድ ቀን ጥንዶቹ ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ከአንድ አዲስ የእውነት እውቀት ጋር ይነቃሉ። አንዳቸው የአንዳቸውን ፊት እያስተዋሉ አንድ ነገር ይገነዘባሉ፤ "እሽ ተጋባን፤ ከዚህ በኋላ ምን ይሁን?" አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር በህይወት ዘመናቸው ሁሉ አብረው ሊሆኑ የተስፋን ቃል ገብተው ራሳቸውን ሰጥተዋል፤ ይሄን እንዴት ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ? ከዚህ ተነስተው እስከፍጻሜያቸው ባለው መንገድ ሁሉ ስኬታማ የሆነውን ትዳር እንዴት ይገነባሉ? በፍቅር፤ በደስታ፤ በወዳጅነትና ፍሬያማ በሆነ ባህሪው የሚገለጸውን የህይወት ዘመን ሙሉ ግንኙነታቸውን ህልም ለማሳካት ምን ማድረግ ይገባቸዋል? እንዴት አድርገው ነው ስሜታማ ትዳርንስ የሚገነቡት?

እነዚህ ተምኔታዊ የሆኑ ጥያቄዎች አይደሉም። በጋብቻ ውስጥ ስኬት ወዲያው የሚመጣ ነገር አይደለም። እንደዚሁ ደግሞ መጋባት በራሱ ለአብሮነትም ይሁን ለግንኙነት ዋስትና የሚሰጥ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ መጋባት የሚያሳየው ነገር ባልና ሚስት አንዳቸው ስለሌላቸው ያለውን እውነት እንደማያውቁ ነው። በትውውቅና በእጮኝነት ጊዜ የራሳቸውን ጥሩ ጎን ብቻ በማሣየት አንዳቸው አንዳቸውን ለማድነቅና ለማክበር መሞከራቸው ቀላልና የተለመደ ነገር ነው። ሁልጊዜም መልካም ሆኖ መታየት፤ መልካም መልበስና መልካም ማድረግ። ከጋብቻ በኋላ ነው ውበቱ ዝቅ ያለ መልክና ከሚጠበቀው የወረደ ባህሪ ራሱን መግለጥ የሚጀምረው። ይህ መሆን በጀመረ ጊዜ አስደንጋጭ ነው። እያንዳንዳቸው በሌላው ውስጥ አይተዋቸው የማያውቁትና ይኖራሉ ብሎው ያላለሙዋቸውን ነገሮች ማየት ይጀምራሉ። የተጋቡ ጥንዶች ፊት ለፊት ከሚጋፈጧቸው ተግዳሮቶች የመጀመሪያው፤ አንዳቸው ስለሌላቸው ማንነት ያላቸው የጋራ ግንዛቤና በጋብቻ ውስጥ ያላቸው ሚና ነው። ባልና ሚስት በቤተሰብ ውስጥ በጋራ በመወሰን የተበላሸውን ለማስተካከል አብረው መስራትና አንዳቸው ከሌላቸው የሚጠብቁትን በግልጽ ሊነጋገሩ ያስፈልጋቸዋል። ውሳኔዎች እንዴት ይወሰናሉ? ማንስ ተግባራዊ ያደርጋቸዋል? የባል ሚና ምንድን ነው? የሚስትስ ሚና ምንድን ነው?

ብዙ ባለትዳሮች ወደጋብቻ የሚገቡት ሚናን በሚመለከት አስቀድመው የሚያውቁትን ግንዛቤ ይዘው ነው። ለምሳሌ ያህል፤ ባል በቆሻሻ ማጠራቀሚያው ውስጥ ያለውን ቆሻሻ ያስወግዳል፤ ሚስት ደግሞ ድስቶችን ታጸዳለች። ባል በግቢው ውስጥ ያለውን የአትክልት ስፍራና ከቤቱ ውጭ ያለውን ነገር ይንከባከባል፤ ሚስት

የልብሶችን እጥበት፣ ምግብ ማብሰልና የማጽዳት ሥራዎችን ታከናውናለች። ባል የቤተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ይሠራል፤ ሚስት ደግሞ በቤት ውስጥ ያለውን ሥራና የልጆችን ጉዳይ ትከታተላለች።



ባልና ሚስት በቤተሰብ ውስጥ በጋራ በመወሰን የተበላሸውን ለማስተካከል ስብሏው መስራትና አንዳቸው የሚጠብቁትን በግልጽ ሊነጋገሩ ያስፈልጋቸዋል።

በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖረን ሚና ወይም ድርሻ አስቀድሞ የነበረን ግንዛቤ ሁልጊዜም ትክክል አይሆንም። ለምን? አንደኛው ምክንያት አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ግንዛቤዎች የተመሠረቱት ኋላቀር በሆኑ ልማዶች ወይም ባህላዊ አስተሳሰቦች ሊሆን ይችላል። ሌላው ምክንት ደግሞ፤ ብዙውን ጊዜ የግድ ጾታዊ ልዮነትን ለማይጠይቁ የግል ችሎታዎች፣ ተሰጥኦዎች፣ ልዩ ክህሎቶች ስፍራ ስለማይሰጡ ነው። ስኬታማ የሆነ ጋብቻ ድርሻንና አግባብ ያለው ሚናን በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ ግንዛቤ ከፊሉ ደግሞ፤ የጋራ ሚና ግንዛቤ ምንጮችን ማወቅንና የእነዚህን ግንዛቤዎች በሥራ ላይ መዋል አለመዋላቸውን በመፈተን መገምገምን ይጨምራል።

በጋብቻ ውስጥ የጋራ ሚና ግንዛቤ ምንጮች

በምዕራቡ ዓለም ባህል ውስጥ በጋብቻ ውስጥ ሊኖር የሚገባው ሚና ግንዛቤ ቢያንስ ቢያንስ ከአራት የተለመዱ ምንጮች ይፈልቃል-ባህል፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ ወይም ቤተክርስቲያን።

እያንዳንዳቸው እነዚህ ምንጮች ባልና ሚስት ራሳቸውንና አንዳቸው ሌላኛውን በሚያዩበት ሁኔታ ላይ ጠንካራ የሆነ ተጽእኖ ያሳድራሉ።

ባህል፤ በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖረን ሚና አብዛኞቹ የተለመዱ አመለካከቶቻችን እየተላለፉ እኛ ዘንድ የደረሱት በባህል ውስጥ ነው። የተወለኑ ሚናዎቻችንን የተላመድናቸው "ሁልጊዜም ሲሠራባቸው የኖረው በዚህ መንገድ ነው" በሚል ምክንያት ነው። ወንዶች የቤተሰቡን ዳቦ ለማሟላት በቢሮ ወይም በፋብሪካ ውስጥ ይሠራሉ፤ ሴቶች በቤት ውስጥ ምግብ በማብሰል፣ በጽዳትና ልጆችን በመንከባከብ ይሠራሉ። ባሎች ሚስቶቻቸውን ጨምሮ በቤት ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገርና ማንኛውንም ሰው

ይገዛሉ። ሴቶችም ያለምንም ተቃውሞ ራሳቸውን ለባሎቻቸው አመራር ያስገዛሉ። ባሎች ቤተሰቡን የሚመለከቱ አብዛኛውን ውሳኔዎች ይወስናሉ፤ ሚስቶች ሊዘሀ ውሳኔ እጅ ሰጥተው ተግባራዊ ያደርጋሉ።

ይህ ማለት ባህል መጥፎ ነገር ነው ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ መረጋጋትንና ሥርዓትን ለማስፈን አስፈላጊ ነገር ነው። ይሁን እንጂ እንደዚሁ ደግሞ አንድ ነገር እንገንዘብ፤ አንድ ነገር ባህላዊ ስለሆነ ብቻ ትክክል ነው ማለት አይደለም። ባህል በቀላሉ በእውነት ላይ ሊመሠረት እንደሚችል ሁሉ ስህተት በሆነ ነገር ላይ ሊመሠረትም ይችላል። ምንም እንኳን በአንድ ወቅት ትክክል የነበሩ ቢሆንም፤ ባህሎች እንዲገኙ መነሻ የሆኗቸው ሁኔታዎች ወቅታቸው ሲያልፍ ባህሎችም እንደዚሁ ኋላ ቀር ይሆናሉ።

ባለትዳሮች፤ በባህል ላይ ብቻ ተመስርተው በትዳር ውስጥ ያላቸውን ሚና ምንነት እንዳይወስኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል።



ባህሎች እንዲገኙ ምክንያት የሆኗቸው ሁኔታዎች ወቅታቸው ሲያልፍ፤ ባህሎችም እንዲሁ ኋላ ቀር ይሆናሉ።

ወላጆች፤ ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ ምናልባትም እጅግ ተጽእኖ ያለውን የሚና ግንዛቤ የሚማሩት ከወላጆቻቸው ነው። እርግጥ ነው ወላጆች በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖር ሚና ያለውን ግንዛቤ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚያሸጋግሩ ዋነኛ አሸንዳዎች ናቸው። ብዙ ሰዎች ውስን ሚናቸውንና የግንኙነት ሥርዓትን የሚያዳብሩት ባደጉባቸው ቤቶች ውስጥ ባዩት ምሳሌ ነው። እነዚያ ሥርዓቶች አወንታዊም ይሁኑ አሉታዊ፤ ፍላጎታቸው ወይም እቅዳቸው በተቃራኒው ቢሆንም እንኳን ያለፍላጎታቸውና ያለ ፈቃዳቸው ብዙ ልጆች ወላጆቻቸውን መስለው እንዲያድጉ ሆነዋል። በተለይ ይህ እውነት የሆነበት አንዱ ልጆችን በማሳደግና ልጆችን በመቅጣት ጉዳይ ላይ ነው። ወላጆች ይከተሉት የነበረው የተለያየ የህይወት ፍልስፍናና ሥርዓት በወጣት ተጋቢዎች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች የተለመዱ መነሻ ነጥቦች ናቸው።

እንደ ባህል ሁሉ፤ በጋብቻ ውስጥ ስለሚኖር ሚና ከወላጆች የተወሰዱ ስርዓቶች ምናልባትም ስህተት ሊሆኑ ስለሚችሉ

በጥንቃቄ ሊገመገሙ ያስፈልጋቸዋል። እማማና አባባ ላለፉት 40 እና 50 ዓመታት ያደርጓቸው ስለነበር ብቻ ነገሮቹ ትክክል ነበሩ ማለት አይደለም።

ማህበረሰብ፤ ታዋቂ የሆኑ ልማዶች፤ በጋብቻ ውስጥ ያለውን ሚና ለመወሰን ሌሎች ዋንኛ ምንጮች ናቸው። ይህ ከባህል የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ባህሎች ሳይለወጡ ለምእተ አመታት ሲቆዩ፤ ማህበራዊ ለውጦች ግን ያለማቋረጥ አዳዲስ ልማዶችና አሠራሮችን ይፈጥራሉ። የሰለጠነው ማህበረሰብ እሴቱንና የእምነት ሥርዓቱን የሚያስተላልፈው በመጀመሪያ በትምህርት ቤቶች፤ በመዝናኛ ኢንዱስትሪዎች (በተለይም ቴሌቭዥን፤ ፊልሞችና ታዋቂ በሆኑ ሙዚቃዎች) እንዲሁም በመገናኛ ብዙሀን ነው። በብዙዎቹ የምዕራብ አገሮች እነዚህ ባህልን የሚቀርጹ አመለካከቶች መሠረት የሚያደርጉት ምክንያታዊነት (rationalistic) እና መለኮታዊ ወይም መንፈሳዊ ከሆነው ነገር ይልቅ በለው ማንነት ላይ በሚያተኩር (humanistic) በሆኑ አለማዊ ፍልስፍናዎች ላይ ስለሆነ፤ ከፍ ላለው ለእግዚአብሔርና እውነት ለሆነው የመንፈሣዊ ዓለም ህይወት ስፍራ አይሰጥም።

ይህ ተጽእኖ እጅግ የተስፋፋ በመሆኑ ጥንቃቄ የማይወስዱ አማኞችና ማንም ቢሆን እነዚህን አመለካከቶች በቀላሉ ያለማስተዋል ተቀብለው ከራሳቸው ጋር ያዋህዷቸዋል። አማኞች በግንኙነታቸው ውስጥ ዓለማዊ የሆኑ አመለካከቶችና አዝማሚያዎችን ሲያስገቡ ሁልጊዜም ችግር ይከሰታል። ለምንም ነገር መመዘኛና የእውቀታቸው ምንጭ ይሆን ዘንድ እይታቸውን የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማድረግ ጠቃሚ ነው።



አማኞች በግንኙነታቸው ውስጥ አለማዊ የሆኑ አመለካከቶችንና አዝማሚያዎችን ሲያስገቡ ሁልጊዜም ችግር ይከሰታል።

ቤተክርስቲያን፤ በምዕራብ አለም ውስጥ እንደተለመደው በጋብቻ ውስጥ ያለን ሚና ግንዛቤ በዋናነት ከሚቀርጹት አንደኛዋ ቤተክርስቲያን ናት። ምንም እንኳን በማህበረሰቡ ውስጥ ለምትገኝ ቤተክርስቲያን ይህ አግባብነት ያለው ተግባሯ ቢሆንም፤ እንደአለመታደል ሆኖ የጋብቻን ሚና፤ በጥቅሉ የወንድና የሴት ግንኙነቶችን በተለይም ሴቶችን በሚመለከት ያለው የቤተክርስቲያን ልማዳዊ አስተምህሮዎች አሉታዊ ገጽታ ያላቸው ናቸው።

ለምሳሌ ያህል፤ ቤተክርስቲያን ባጠቃላይ ለብዙ ዓመታት ያህል፤ ሴቶች "በቀላሉ የሚሰበር ማድጋ"፤ "ደካማው ጾታ"፤ "በታላቅ ጥንቃቄ ሊያዙ የሚገባቸው በቀላሉ የሚሰበሩ ሸክላዎች"፤ አካላዊም ይሆን አይምሯዊ ለሆኑ ከባድ ተግባራት ሊጋለጡ እንደማይገባቸው አድርጋ ስታስተምር ኖራለች። የዘመኑ የስነ ህይወትና የህክምና ጥናቶች አላማኝ በሆነ መንገድ በማስረጃ እንዳረጋገጡት ይህ እውነት አይደለም። በተለያየ መንገድ ቢሆንም እንኳን በአካልም ይሁን በአይምሮ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ናቸው።

ሌላው ስህተት የተሞላበት ትምህርት ደግሞ፤ በቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ህይወት ውስጥ ሴቶች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በጣም ጥቂት ነው ወይም ምንም የለም የሚለው ነው። በጓዳ በሚሰጡት አገልግሎት፤ በህጻናት እንክብካቤና በኪየር ውስጥ ይሳተፉ እንጂ ጠንከር ባሉ አገልግሎቶች ማለትም በትንቢት አገልግሎትና በታመመት ላይ እጆችን በመጫን በመሳሳሉት አገልግሎቶች አይሳተፉም።

እንደገናም ደግሞ በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ተጽእኖ ቢያደርጉባቸው ሴቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ ታስተምራለች። ይህም ለባሎቻቸው የሚገባውን አክብሮት እንደማሳየት ተደርጎ ይወሰዳል። ባሎቻቸው ለሚያደርሱባቸው ያልተገባ ድርጊት አጸፋውን የሚመልሱ ሴቶች በቤተክርስቲያን የተወገዙ ተደርገው ይወሰዳሉ።

"በመገዛት" ላይ የተሰጡት ብዙዎቹ ተለምዷዊ ትምህርቶች የተመሠረቱት በጥቅሉ በተዛባ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ላይ ነው፤ ይህም ደግሞ በብዙ ሴቶች ህይወትና ግንኙነት ላይ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል።



በመገዛት ላይ የተሰጡ ብዙዎቹ ተለምዷዊ ትምህርቶች የተመሠረቱት በጥቅሉ በተዛባ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ላይ ነው፤ ይህም ደግሞ በብዙ ሴቶች ህይወትና ግንኙነት ላይ ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል።

በፍቅር መተሳሰር

ባህላዊ ከሆነው ምንጭ የተቀዳው በትዳር ውስጥ የወንዶችና የሴቶች ሚና ግንዛቤ ሁልጊዜም እውነትና አሰራላጊ ሊሆን ካልቻለ፤ ምን መደረግ አለበት? አስተማማኝ የሆነውን መመዘኛ ለማግኘት

ባለትዳሮች ፊታቸውን መመለስ ያለባቸው ወዴት ነው? ስኬታማ ለሆነ ትዳር አሠራር የሚያገለግል መመሪያ ይኖር ይሆን? አዎን አለ። ስለማንኛውም ምርት ቴክኒካዊ መረጃ ለማግኘት ተመራጩ ፈብራኪው ነው። ጋብቻም የተለየ አይደለም። እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ካሉ ተቋማትና ከሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ የመጀመሪያና ብልጫ ያለው አድርጎ ጋብቻን ፈጥሮታል፣ መስርቶታልም። እንደ ጋብቻ ፈብራኪነቱ ከማንም ይልቅ ጋብቻን የሚገነዘበው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ጋብቻ እንዴት እንደሚሠራ ለማወቅ የእርሱን የማስተማሪያ መዝገብ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ማገላበጥ ብቸኛው ትርጉም የሚሰጥ መንገድ ነው።

በሚያስደንቅ ሁኔታ፤ አብዛኞቹ በጋብቻ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች ስለሚኖራቸው ሚና በተለምዶ የሚነገሩት ነገሮች፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተለይተው በግልጽ የተቀመጡ አይደሉም። ዝርዝር መግጫዎች የሉም፣ አንደኛውን ከሌላኛው ጋር ለማመዛዘን የሚያስችሉ መግለጫዎችም የሉም፤ እንዲሁም አውነታዎችን በአጭሩ ገልጸው የሚያሳዩ ቀመሮች የሉም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን መርሆዎችን ነው። ባልና ሚስት እንዴት ባለ ሁኔታ መዋሃድ እንዳለባቸው ምናልባትም ጠቃሚ የሆነው መግለጫ የሚገኘው፤ የመጀመሪያው ክ/ዘመን አይሁድ ክርስቲያን ምሁር፣ የቤተክርስቲያን መሪና ሚስዮናዊ ከሆነው ከጳውሎስ መልዕክት ነው።

"ሚስቶች ሆይ ለጌታ እደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ። ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ፤ ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችን ውደዱ፤ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደገዛ ስጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል ማንም የገዛ ስጋውን የጠላ ከቶ የለምና፤ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል፣ ይንከባከበዋልና። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል

ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምስጥር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህንን ስለክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ እራሱ አድርጎ ይውደዳት፤ ሚስቱም ባልዋን ትፍራው" (ኤፌ 5÷22-33)።

እነኝህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ባልና ሚስት የተለየና ውስን የሆነ ሚና እንዳላቸው የሚገልጹ ሳይሆኑ፤ ነገር ግን ግንኙነታቸውን ሊመሩ የሚያስችላቸውን መገዛት፣ ፍቅርና አክብሮት የመሳሰሉ የተወሰኑ መርሆዎችን ለይተው ያመለክታሉ። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ አራት ጊዜ ያህል ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድ እንደሚገባቸው ሲናገር፤ አንድም ጊዜ እንኳን ሚስቶች ባሎቻቸውን መውደድ እንደሚገባቸው አለመናገሩን ማስተዋል አስደናቂ ነገር ነው። ፍቅራቸው ለባሎቻቸው በመገዛታቸውና ከበሬታ በመስጠታቸው ውስጥ የሚገለጥ ነው።

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ትኩረት ሰጥቶ በግልጽ እየተናገረ ያለው ስለ ባሎች ዝንባሌና ባህሪ ጉዳይ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳትና ለእርሷም ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ነው። በዚህ ላይ በሁለት ዋነኛ ምክንያቶች ትኩረት ልንሰጥ ያስፈልገናል። የመጀመሪያው እግዚአብሔር እንዳቀደው ባል የሚስት ራስ እና የቤቱ መንፈሳዊ መሪ ነው። የእርሱ ዝንባሌና ባህሪ በቤተሰቡ መንፈሳዊ ሁኔታና በተለይም በሚስቱ መንፈሳዊና ሁለንተናዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሣድራል።

ሁለተኛው ጉዳይ ባለንበት ማህበራዊ ግንዛቤ ውስጥ እጅግም ጎልቶ የማይታይ ነው። ጳውሎስ እነዚህን ቃላት በጻፈበት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በአይሁድም ይሁን በሮማውያን ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶች እንደ ሁለተኛ ዜጋና በራሳቸው ጥቂት መብት ብቻ እንዳላቸው ይቆጠር ነበር። ሚስቶች የሚታዮት ከባሎቻቸው ንብረቶች ጥቂት ከፍ ያሉ ተደርገው ነበር። ጳውሎስ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ጥሪ ያደረገው በተለይ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት የግል መስዋእትነት በሚጠይቅ መልኩ ነው። ይህ ደግሞ ስር ነቀላዊ የሆነ አዲስ ጽንስ ሀሳብና እንዲያውም አብዮታዊ የሆነ እንድምታ ያለው ነበር።

ፍቅር በባልና በሚስት መካከል በራሱ አዲስ ነገር አይደለም፤ በማንኛውም ባህል ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ ስነ-ጽሁፎች

በፍቅር ዘፈኖች የተሞሉ ናቸው። የጳውሎስ ገለጻ ግን የተለየ ነበር። እርሱ ፍቅርን የገለጸው ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዳገለገላት ባል ሚስቱን ማገልገል እንደሚገባው፤ ክርስቶስም ለቤተክርስቲያን ህይወቱን እንደሰጠ ባልም ለሚስቱ ህይወቱን መስጠት እንደሚገባው ነው። መስዋእትነት ያለበት ፍቅር በራሱ መገዛት ነው። ጳውሎስ እየተናገረበት ያለው ፍቅር፤ ሚስት በባሏ አይታ ስብእዊነቷ ወደተጠበቀበት የእኩልነት ደረጃ ከፍ የሚያደርጋት ነበር።



መስዋእትነት ያለበት ፍቅር በፈቃ መገዛት ነው።

ይህ ምንባብ በጋብቻ ውስጥ ስላለው ሚና የሚሰጠው ቅርብ የሆነ መግለጫ፤ የባል ሚና መስዋእትነትን በሚያስከፍልና ራስን መስጠት ባለበት መልኩ ሚስቱን መውደድ፤ የሚስትም ሚና ለጌታ እንደምትገዛ ለባሏ እንድትገዛና ባሏን እንድታከብረው ነው። ማንኛ ውንም ባል የራሱን ሚና በእውነት ለመወጣት ታማኝ ከሆነ ሚስቱ የራሷን ድርሻ እንድትወጣ ለማስቻል ነገሮችን ያቀልላታል። እንደዚሁም ማንኛውም ባልዋ በዚህ ሁኔታ የሚወዳት ሚስት፤ ባሏን ለማክበር፣ ለእርሱ ለመገዛትና ራስነቱን ለመቀበል ችግር አይገጥማትም።

ያስ ውስን ሚና መተሳሰር

በመሠረቱ ጋብቻ ውስን ሚና የሌለው ግንኙነት ነው። ለዚህ ደግሞ ጋብቻ እውነተኛ በሆነ መስዋእትነት ባለበት ፍቅር ላይ ከመመስረት ውጭ ሌላ አማራጭ መንገድ የለም። መስዋእትነት ያለበት ፍቅር ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቅ፣ በምክንያትም ላይ የተመሠረተ አይደለም። እውነተኛ ፍቅር ምክንያት አይጠይቅም። በቃ እንደዚህ ነው። ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቅ ፍቅር የሚወደው፤ የተወዳጁን ባህሪ ወይም ተወዳጅነትን ባላገናዘበ መልኩና የሰጠው ፍቅር ቢመለስለትም ባይመለስለትም ጭምር ነው። አዲስ ኪዳን እንዲህ አይነቱን ፍቅር በግሪክ ቋንቋ አጋፔ ሲል ለይቶ ይገልጻዋል። እንዲህ አይነቱ ፍቅር እግዚአብሔር ኀጢያተኛ ለሆነው ዓለም የገለጸው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ኀጢያተኛ ለሆነው ሰው ዘር በፈቃዱ በመስቀል ላይ ሲሞት ያሳየው ፍቅር ነው። ጳውሎስ በሮም ለሚገኙ አማኞች በጻፈው መልእክቱ፤ "ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለኀጢያታችን ሞቷልና ስለጻደቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና። ስለቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳን የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኀጢያተኞች

ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ሲል ገልጾታል (ሮሜ 5፥6-8)።



መስዋእትነት ያለበት ፍቅር ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቅ በምክንያትም ላይ የተመሠረተ አይደለም።

እግዚአብሔር እኛን ሲወደን ምንም አይነት ምክንያት አልፈለገም፤ የወደደን ፍቅር ባህሪው ስለሆነ ነው። እርሱ እኛን የወደደበት ፍቅር፤ "ወደ አዲስ ህይወት ዘወር ስላልን"፣ "ክክፉ ሥራችን ስለነጻን" ወይም መልሰን እርሱን በወደድንበት ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥን አይደለም። አጋፔ እንዳች ነገር አይጠይቅም፣ ምንም ነገር ተስፋ አድርጎ አይጠብቅም፤ እንዲሁም ራሱን ዋስትና ከማድረግ ውጭ የዋስትናን ጥያቄ አያቀርብም። ጌታ የሰጠን ዋስትና ፍቅሩን ብንመልስለትም ባንመልስለትም ሲወደን ነው።

የክርስቶስ ፍቅር ሚና ተኮር ያልሆነ ክሌላው የሚጠብቅ ላይሆን የራሱን ምላሽ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ነው። በመስቀል ላይ የሆነው ሞቱ ለፍጥረት ይቅርታ አስፈላጊ የሆነ የፍቅር ምላሽ ነበር። ኢየሱስ ስለከፈለው መስዋእትነት እንደ ቅድመ ሁኔታ ክእኛ የጠበቀው ምንም ምላሽ አልነበረም። ማናችንም ብንሆን መልሰን እርሱን እንድንወደው ዋስትና ሳይጠይቅ ህይወቱን እንዲሁ አሳልፎ ሰጠ። ኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋ ያደረገው የራሱን ደስታና በእባቱ ፊት መክበሩን ነበር። "የእምነታችንን ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትእግስት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሶ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጧልና" (ዕብ 12፥2)።

የእርሱ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተና ግልጽ የሆነ ግብዣው "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን ሁሉ እንዲሁ ወዷልና" (ዮሐ 3፥16) የሚል ነው። "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው" (ዮሐ 1፥12)። እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱት ኢየሱስ ዋስትና እንዳልነበረው ነው። የገዛ ፍቅሩ ወደ መስቀል ሞት ወሰዳው፤ ዛሬም ቢሆን ማንም በእርሱ ባያምንና ባይቀበለውም እንኳን ራሱን ይሰጥ ነበር። አጋፔ ምክንያታዊ አይደለም።

ምክንያትን የሚፈልግ ፍቅር ከቅድመ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ፍቅር ነው። ቅድመ ሁኔታዎች ደግሞ አንድን ነገር በምላሽ የሚጠብቁ ናቸው። ምላሽ መጠበቅ ስል፤ ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ የራሳቸው ሚና አድርገው የቆጠሯቸው፤ አንዳቸውም ከሌላኛቸው የሚጠብቋቸውን አስደሳችነት የሌላቸው፣ ተደጋጋሚ የሆኑ ሥራዎች፣ ተግባራት ወይም እንቅስቃሴዎችን ነው። እነዚህ ደግሞ ድስቶችን ማጠብ፣ ምግብ ማብሰል፣ ቤት ማጽዳት፣ ሣር ማጨድ፣ አልጋ ማንጠፍ፣ ልጆችን ማጠብ እና የመሳሰሉት ናቸው። ከሌላው የምንጠብቃቸው ነገሮች ወደማይቀር ግራ መጋባት ያመጡናል። ግራ መጋባትም ወደ አሰመግባባት ሊያመራን ይህም ግንኙነታችንን የሚያቆስልና ሀብረትንም በአደጋ ላይ የሚጥል ይሆናል።

እነኝህ ሁሉ የገለጽናቸው ነገሮች በጋብቻ ውስጥ ስላሰ ሚና አልባ ግንኙነት ምን ጠቀሜታ አላቸው? በጋብቻ ውስጥ ያሰ ፍቅር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰቤተክርስቲያን ያሰውን ፍቅር እንዲመስል ይጠበቅበታል። ይህም ቅድመ ሁኔታን የማይጠይቅ፣ መስዋእትነት የተሞላበትና ከሌላ ምንም ሳይጠብቅ ወይም ዋስትና ሳይቀበል ፍቅርን መግለጽ ነው። ሰምላሌ ያህል፤ ሚስት በአትክልት ሥፍራ ያለውን ሣር ማጨድ የባሏ ሚና አድርጋ ካየችው፤ ይሄ ሚና በአይምሮዋ ውስጥ የሚፈጥረው ግምት አለ፤ ይሄውም ሣሩ ባደገ ጊዜ ባሏ እንደሚያጭደው ነው። ይህንን ባያደርገው ዋስትናውን አፍርሷል። የጠበቀችው ግምቷ የመጨረሻው ውጤት ግጭት ወደሚሆንበት ግራ መጋባት ወይም ቁጣ ያመራታል። ባል ደግሞ ምግብ ማዘጋጀት የሚስቱ ሚና እንደሆነ ካመነ፤ ከሥራ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሲመጣ ምሳው ከጠረጴዛ ላይ ካልጠበቀው ይበሳጫል። በእርሱ ግምት የሚስቱ ሚና እንደሆነ የተገነዘበውን ተግባር ባለመፈጸሟ ዋስትናዋን እንዳፈረሰች ይቆጥራል።



ውስንነት ያለው ሚና ከሴሎች ስንዳች ነገር መጠበቅን ያስከትላል፤ ይህም በተራው ዋስትናን ያመሳክታል።

የዚህ ሁሉ ድምዳሜ፤ ምክንያታዊ ያልሆነ ፍቅር ከማንም ምንም ምላሽ የማይጠብቅ ፍቅር ነው የሚል ነው። ከሌሎች የምንጠብቀው ምንም ምላሽ ከሌለ ውስን የሆነ ሚናም አይኖርም። እንዲህ ከሆነ ጋብቻ ለፍላጎቶች ምላሽ በምንሰጥበት ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንጂ፤ ግትር የሆነ ቅድመ ግንዛቤ ይዘን የምንገታገትበት አይሆንም። ባልና ሚስት አንዳቸው ከአንዳቸው

ግትር የሆነ የማይለወጥ ሚና የማይጠብቁ ከሆነ ሁለቱም ግራ ወደ መጋባት አይመጡም። ለሌላው ፍላጎት መልስ የመስጠት አቀራረብ በጋብቻ ውስጥ የጠለቀ፣ ንጹህ የሆነና በተሰየ አዲስ አቅጣጫ ግንኙነትን እንድናይ ያደርገናል። ባለትዳሮች ያለ ውስን ሚና እንዴት ግንኙነታቸውን መቀጠል እንደሚችሉ በተማሩ መጠን ታላቅ ስኬትና ደስተኛነትን በህይወታቸው ይለማመዳሉ።

ጊዜያዊ የሆኑ ሀላፊነቶች፤ ቋሚ የሆኑ ሚናዎች ስይደሉም

በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ውስን ያልሆነ ሚና ማለት፤ ማንም ሰው ምንም አይሠራም ወይም ባለትዳሮች በመደዴው አሰዚያም ስርዓት በሌለው መልኩ የቤት ህይወታቸውን ይመራሉ ማለት አይደለም። ይልቁን በተቃራኒው ባልና ሚስት ነገሮችን እንዴት እንደሚያከናውኑ ግልጽና የጋራ ወደሆነ ግንዛቤ መምጣታቸው በጣም ጠቃሚ ነው። ያሰ ውስን ሚና የሚደረግ ግንኙነት ማለት፤ እያንዳንዱ ተጓዳኝ እንደ ፍላጎቱ፣ እንደ ልዩ ችሎታውና እንደ አገኘው አጋጣሚ ምላሽ ይሰጣል ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ ምግብ የሚያበስለው ማነው? ይህ ምን አይደለም። ብዙ ጊዜ ምግብ የሚያበስለው ማነው? ይህ ምን አልባት ማንኛቸው የተሻሉ ምግብ አብሳዮች በመሆናቸው ላይ የተመሠረተ ይሆናል። እንዳንድ ባሎች ከሚስቶቻቸው የተሻሉ ምግብ አብሳዬች ናቸው። በዚህ ሁኔታ በባህላዊ ሚናዋ ብቻ ሚስት ምግብ እንድታበስል ሰምን ህላፊነት ይጫንባታል?

ሚና፤ ምላሽ በሚሰጠው ሰው ልዩ ችሎታ ላይ የተመሠረተ ጊዜያዊ የሆነ ህላፊነት ነው። እንዲህ ከሆነ ሚና ከአንዱ ቀን በሌላው ቀን፤ ከአንዱ ደቂቃ በሚቀጥለው ደቂቃ፤ እንደ ጊዜው ተጨባጭ ፍላጎት ከአንድ ሰው ወደ ሌላኛው የሚሸጋገርና የሚለዋወጥ ነው። የትኛው ፍላጎት ነው መሟላት ያለበት? በጥሩ ሁኔታ የሚያከናውነው ማነው? በዚህ ጊዜ ውስጥ ድርጊቱን ለማከናወን በተሻለ ሁኔታ ውስጥ ያለው ማነው? ይህ የፍላጎት፣ የልዩ ችሎታና የመልካም አጋጣሚ ጉዳይ ነው። ምናልባትም የጋብቻ ተግባራትን እንደ ሚና ሳይሆን እንደ ህላፊነቶች ልንቆጥራቸው የሚያስፈልገን ለዚህ ነው። ፍላጎቱ ምንም ይሁን በዚያ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ለመስጠት የሚችለውና አስፈላጊ የሆነው ሰው እርሱ ህላፊነቱን ይወስዳል።

ውስን ባልሆነ ሚና በግንኙነት መጣመር፤ ባልና ሚስት በእውነተኛ እኩልነት አጋፔ በሆነው ፍቅር ላይ የሚመሠረቱበት፤ ጋብቻቸውም አግባብነት ያለው እድገት የሚያድግበት ሁኔታ ነው።

አጋፔ ለማገልገል እንጂ ለመገልገል ቅድሚያ የማይሰጥ ፍቅር ነው። ኢየሱስ ይህንን መርህ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ (ዮሐ 13÷3-17) ጠንካራ በሆነ ምሳሌ አሳይቶታል። ከሰቅለቱ በፊት ባለ ምሽት፤ ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ከተከታዮቹ ጋር ተሰብስቦ ነበር። ደቀመዛሙርቶቹ በገቡ ጊዜ እግሮቻቸውን ለማጠብ የቀረበ ማንም አልነበረም (ይህ ደግሞ ዝቅተኛ ለሆኑ አገልጋዬች የተመደበ የተለመደ ተግባር ነው) እናም ይህንን ለመከወን ማንም ፈቃደኛ አልነበረም። ያልተናገሩት ዝንባሌያቸው ያ የእኔ ሥራ አይደለም! የሚል ነበር። ኢየሱስ ራሱ ከመቀመጫው ተነሣ፤ መደረቢያ ልብሱን አወለቀ፤ አገልጋዮች እንደሚያደርጉት ወገቡን በጨርቅ ታጠቀ፤ እናም የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ ቀጠለ። የማና ጥያቄ አልነበረም። ኢየሱስ ፍላጎትን ተመለከተ ምላሽም ሰጠ። በዚያውም ትህትናንና አገልግሎትን በሚመለከት ደቀመዛሙርቱን አስተማራቸው። አጋፔ ለተገነዘባቸው ፍላጎቶች ማስተዋል የተሞላበት ምላሽ በመስጠት ራሱን ይገልፃል። ይህም ማለት ሁኔታዎች በፈጠሯቸው ልማዶችና ዝንባሌዎች ላይ ተመስርቶ ፈጣን የሆነ ወይም ያለማስተዋል የሆነ ምላሽ አይሰጥም ማለት ነው። በሚስቱ ልብሶችን ያለማጠብ ችግር ምክንያት የመጣው የባል ቁጣ፤ በቀላሉ ለእርሷ ካለቀመጠላት የሚና ግንዛቤ አንጻር ተግባሯን ባለመፈጸሟ ምክንያት የተከሰተ ወቅታዊ ምላሽ ነው። የአጋፔ ምላሽ ቢሆን ግን፤ ልብሱ ያልታጠበበት አሳማኝ የሆነ ምክንያት ምን እንደሆን ያጠያይቃል፤ ተግባሩን ለማከናወን የማያስችል አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተከሰተው እንደሆነ ይገመግማል፤ አንድን ድርጊት ከማድረግ ወይም ከመናገር በፊት ያስባል። ምናልባትም ቀኑን ሙሉ የታመመውን ህፃን ልጅ ስትንከባከብ ቆይታ ይሆናል። ምናልባትም በስራዋ ቦታ በተፈጠረው ከፍተኛ የሥራ ጫና ምክንያት አለዚያም ለማታው የትምህርት ጊዜዋ የቤት ሥራዋን ስትሠራ ቆይታ ይሆናል። ምክንያቱ ምንም ይሁን፤ አጋፔ አሰፈላጊ የሆነውን ፍላጎት ለማሟላት የእርዳታ እጁን ይዘረጋል እንጂ በችግር ውስጥ ነቀፌታን አይሰነዝርም። ምንም እንኳን እነዚህ ባልና ሚስቶች በተለምዶ ልብሶችን ማጠብ ያለባት እርሷ መሆኗን የጋራ ግንዛቤ ቢኖራቸውም፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የአጋፔ ወይም የሚና አልባነት ምላሽ፤ ምናልባትም ልብሶችን እርሱ ራሱ ማጠብና ከላይዋ ላይ ሽክምን ማቃለል ይሆናል። አጋፔ ሚናን አይመለከትም፤ አጋፔ ለፍላጎት ምላሽ ይሰጣል።



አጋፔ ለተገነዘባቸው ፍላጎቶች ማስተዋል የተሞላበት ምላሽ በመስጠት ራሱን ይገልጻል።

ከማና አልባነት አንጻር ጋብቻቸውን የሚመለከቱ ባልና ሚስቶች፤ በእያንዳንዱ የህይወት ጉዳይ ላይ የጋራ ባለቤትነት እንዳላቸው በመገመት በአንድነት ይሠራሉ። ይሄ "የእሱ" እና "የእርሷ" ሚና ነው የሚባል ነገር የለም፤ ይልቁን "የእኛ" ሃላፊነት! ማን ምን መስራት፣ መቼስ መስራት አለበት የሚወሰነው በተለዩ ሁኔታዎች ተመሥርቶ ነው። ባለትዳሮቹ በተናጠል ለየትኛው ተግባር ወይም ፍላጎት ማናቸው ቀዳሚ ሀላፊነት እንዳለባቸው የጋራ ወደሆነ ስምምነት መምጣትና በዋናነትም ሁሉንም ሃላፊነቶች በጋራ መካፈል እንዳለባቸው መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

በጋብቻ ውስጥ የሚሰጡ ሀላፊነቶች የሚመሠረቱት በእያንዳንዱ ሰው ልምምድ፣ ልዩ ችሎታ ወይም በተፈጥሯዊ ባህሪዎች አንጻር ነው። ምግቡን በቅድሚያ ማን ማዘጋጀት አለበት? ለቁጥሮችና የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ጥሩ አይምሮ ያለው ማነው? በቤቱ ውስጥ ከሚኖሩት የቤቱን ጽዳት ማን መስራት አለበት? በሃግብ መመገቢያ ሣህኖች ማንም ይጠቀምባቸው፤ ግን ማን ይጠባቸው? በእነርሱ ላይ ማንም ይተኛ፤ አልጋዎቹን ማን ያንጥፋቸው? ጊዜውና ሁኔታው የሚያመቸው ማንም ይሁን የግቢውን ሣር ማን ይጨድ?

በባልና በሚስት መካከል የሚሰጡ ቀዳሚ የስልጣንና የሃላፊነት ተግባራት ሥርዓትን የሚያለፍኑ፣ ምስቅልቅል ያሉ ሁኔታዎችንና ግራ መጋባትን የሚያስወግዱ ናቸው። በዚሁ ጊዜ በግንኙነት ውስጥ ግትር የሆኑ ሁኔታዎችን ከመፍጠር ይልቅ፤ ለእያንዳንዱ ተንዳኝ በተመሰነው ጊዜ ውስጥ ያለውን ፍላጎት ለማከናወን ዘና ያለ ሁኔታን ይፈጥርለታል። የሚችለው እርሱ ያደርገዋል፤ ያየው እርሱ ያከናውነዋል። ነገሩ እንዲህ ቀላል ነው።

የትዳርን ሀላፊነቶች ለማከናወን ሁለቱም ባለትዳሮች ወይስ አንደኛው ከቤት ውጭ ይሠራሉ? የሚለው ወሳኝ ጉዳይ ነው። ከቤት ሆነ የምትሠራ ሚስት በሙሉ ጊዜ ለዓታ ውጭ ወጥታ ከምትሠራው ሚስት ይልቅ፤ በቤት አካባቢ የሚሠሩትን በርካታ ሃላፊነቶች ልትሸከም ይጠበቅባታል። ሁለቱም ባልና ሚስት ቀኑን በውጭ ሠርተው በሚገቡበት ሁኔታ ውስጥ ሃላፊነቶችን መከፋፈል በጣም ጠቃሚ ይሆናል። እያንዳንዳቸው የሌላኛውን የተግባር ቅደም ተከተልና ግዴታዎች፤ የሥራውንም ጫምሮ ግንዛቤ ውስጥ

ማስገባት ይኖርባቸዋል። የጋራ የሆነ ግንዛቤና ትብብር መሠረታዊ ጉዳይ ነው።



የሚችው እርሱ ያደርገዋል፤ ያየው እርሱ ያከናውነዋል። ነገሩ እንዲህ ቀላል ነው።

ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ የባል ሚና ምንድነው? እርሱ የቤቱ ራስ ነው፤ የቤተሰቡን መንፈሳዊ አቅጣጫ አስመልክቶ ሃላፊነት ያለበት መንፈሳዊ መሪ ነው። ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት፤ መስዋእትነት ባለበትና ቅድመ ሁኔታን በማይጠይቅ ፍቅር ሚስቱን ይወዳል። የሚስትስ ሚና ምንድን ነው? ለእርሱ አመራር መገዛትና ለባሏ ከበሬታን መስጠት ነው። የእለት ተእለት ተግባራዊ ጉዳዬችን አስመልክቶ ሁለቱም እንደ ፍላጎቱ አይነት በችሎታቸው እንደ አስፈላጊነታቸውም ምላሽ ይሰጣሉ።

መርሆዎች

1. መሠረታዊ በሆነ ደረጃ ባልና ሚስት ቅድመ ሁኔታ ከተወሰነላቸው ሚናዎች ይልቅ፤ በጋራ መፈቃቀርና አንዱ ለሌላው ራሱን በማስገዛት ግንኙነት እርስ በእርስ ሊተሣሰሩ ይገባል።
2. በመሠረቱ፤ ጋብቻ ሚና አልባ ግንኙነት ነው።
3. የክርስቶስ ፍቅር፤ ምላሽን በመስጠት ላይ እንጂ ምላሽን በመጠበቅ ላይ ያልተመሠረተ ሚና አልባ ፍቅር ነው።
4. ምላሽ የማንጠብቅ ከሆነ ውስን የሆነ ሚና የለም። ስለዚህም ጋብቻ ግትር በሆኑ ቅድመ ግንዛቤዎች ላይ የሚጣበቅ ሳይሆን ሰፍላጎት ምላሽ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ይሆናል።
5. ያለ ውስን ሚና የሆነ ግንኙነት ማለት፤ እያንዳንዱ ተጓዳኝ እንደ ተከሰተው ፍላጎት፣ እንደ ችሎታውና እንደ ተፈጠረለት መልካም አጋጣሚ ምላሽ ይሰጣል ማለት ነው።
6. ሚና፤ ምላሽ በሚሰጠው ሰው ልዩ ችሎታ ላይ የተመሠረተ ጊዜያዊ ሃላፊነት ነው።
7. አጋፔ ሚናን የሚመለከት አይደለም፤ አጋፔ ለፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ ነው።
8. ሚና አልባ በሆነ ጋብቻ ውስጥ "የእርሱ" እና "የእርሷ" ሚና ነው የሚባል ነገር የለም፤ የእኛ ሃላፊነት ብቻ!
9. በጋብቻ ሃላፊነቶች ውስጥ የሚሰጡ ተግባራት ምናልባትም የሚመሠረቱት በእያንዳንዱ ሰው ልምምድ፣ ልዩ ችሎታ ወይም ተፈጥሯዊ ባህሪ ላይ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

በመገዛት ላይ የተነሳ ጥያቄ

ለባለትዳሮች፤ በተለይም ባህላዊ የሆነው የሚና ጽንሰ ሃሳብ ወደ አይምሯቸው ስር ሰዶ በሰረጸበት ሁኔታ ውስጥ ላሉት፤ ያለውስን ሚና መተሳሰርን መማር ዋነኛ ተግዳሮት ነው። በዚህ ረገድ ውጤታማ የሆነ ለውጥን ለማምጣት ወሳኝ የሆነ የአመለካከት ተሃድሶ ማድረግን ይጠይቃል። ምክንያቱም አብዛኞቹ ባህሎች ለረዥም ጊዜ ሲከተሉ የኖሩት በወንድ የበላይነት ላይ በተመሠረተ ማህበራዊ ሥርዓት በመሆኑ፤ መገለጫው ሚና አልባነት የሆነው በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የጋብቻ ጽንሰ ሃሳብ በቀላሉ ወደ ብዙዎች ልብ ሊደርስ ስለማይችል ነው። ይሁን እንጂ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ያመላከተን ፈለግ ነው።

በመጀመሪያው፤ እግዚአብሔር ለውን ፈጠረ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸውም፤ የፈጠራቸውም በራሱ መልክ ሲሆን በአንድነት ሆነው ምድርን ይገዟት ዘንድ ስልጣንን ሰጥቷቸዋል (ዘፍ 1፥26 ይመልከቱ)። የመጀመሪያዎቹ ሰብአዊ ባለትዳሮች በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ባልንጀርነት፤ እኩል መብትና ሃላፊነትን በመካፈል የጋብቻን ደስታ አጣጥመውታል። በግልጽና ባልተቋረጠ ሁኔታ እርስ በእርሳቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት አድርገዋል።

አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ የመረጡበት ቀን መጣ። ወዲያውኑም ሁኔታቸው ተለወጠ። ኀጢያታቸው ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ህብረት አቋረጠው፤ ይህም በእኩልነት ላይ የተመሠረተውን ጋብቻ ቀድሞ ከነበረው ዝቅ አድርጎ ሚስት በባሏ አገዛዝ ሥር የምትሆንበትን ሁኔታ ፈጠረ። ይህ ፍትሀዊ ያልሆነ በባል የበላይነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ፤ በኀጢያት በተመረዘው ዓለም ውስጥ የወንድና የሴት ግንኙነት የተለመደ ሥርዓት ሆነ።

ገና ከመጀመሪያውም እግዚአብሔር ከለምች ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲታደስ አቅደን ነበር። ስለዚህም ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለፍጥረት ኀጢያት ሁሉ በመስቀል ላይ እንዲሞት፤ የኀጢያትንም ሃይል እንዲሰብርና ውጤቶቹንም እንዲያስወግድ ላከው። አንደኛው የእግዚአብሔር የተሀድሶ ሀሳብ ደግሞ የጋብቻን ተቋም ወደ ቀደመ ንጹህ ሁኔታው መመለስ ነው።



የመጀመሪያዎቹ ሰብአዊ ባለትዳሮች በእኩልነት ላይ በተመሠረተ ባልንጀርነት፤ እኩል መብትና ሃላፊነት በመካፈል የጋብቻን ደስታ ስጣጥመውታል። ግልጽ በሆነና ባልተቋረጠ ሁኔታ እርስ በእርሳቸውና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን ስድርገዋል።

በአማኞች መካከል ያለው ጋብቻ፤ ሚና አልባ በሆነው፤ ሁለቱ ባለትዳሮች በእኩል ባልንጀርነት በሚሳተፉበት ግንኙነት መገለጽ መቻልና መገለጽም አለበት። ይሁን እንጂ ይህ፤ በጋብቻ ውስጥ በእኩልነት መሳተፍ የሚለው መጽሀፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ ሃሳብ፤ ሚስት ለባሏ ትገዛ ከሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ ሀሳብ ጋር እንዴት መታረቅ እንደሚገባው የተገባ ጥያቄ ያስነሣል። ላይ ላዮን ስንመለከት ይህ እርስ በእርሱ የሚቃረንና ሊታረቅ የማይችል ሀሳብ ይመስላል። ባለፈው ምዕራፍ ላይ ርእሱን በሰፊው ዳስነዋል፤ ይሁን እንጂ የመገዛት ጽንሰ ሀሳብ ጥያቄ በአግባቡ መረዳት ዘለቄታ ላለው የጋብቻ ስኬትና ደስታ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ በጣም ቀረብ ብለን እንመለከተዋለን።

ባሎች እንደ ሲየሱስ ሲመሳሰሉ ይገባቸዋል

መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው ጋብቻ፤ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት የጋራ በሆነ መፈቃቀር፤ መገዛት፤ መከባበር መገለጽ አንዳለበት ቀደም ሲል ተመልክተናል። ይሁን እንጂ በእርግጥ ይህ ምን ማለት ነው? አንድ ጊዜ መለስ ብለን ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን የዳፈውን ምክር እናጢን። "ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን እሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያንን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁ ባሎች ደግሞ እንደገዛ ስጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ስጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን

ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል፤ ይንከባከበውማል። ስለዚህ ለው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ። ይህ ሚስጥር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህን ስለክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደራሱ አድርጎ ይውደዳት፤ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ" (ኤፌ 5፥21-33)።

የጳውሎስ ቀዳሚው መመሪያ በእኩልነት ደረጃ መገዛትን የሚመለክት ነው፤ "ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ" ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚናገረው ሁሉ አንዱ ለሌላኛው በሚገዛበት አውድ ውስጥ ነው። ሚስት ለክርስቶስ እንደምትገዛ ለባሏ ትገዛለች፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደወደዳት ባል ሚስቱን ይወዳል። ወንዱን በሚመለከት ያለው፤ ራስን የመስጠት ፍቅር በራሱ የመገዛት አንድ መገለጫው ነው። ብዙ ጊዜ በትምህርትም ይሁን በተግባር ይህ ባል ሚስቱን አስመልክቶ ያለው መገዛት ትኩረት ተነፍጎት ይታያል። በተጠቀለው የመጽሐፍ ክፍል ውስጥ ሁሉ ጳውሎስ ባሎችን ከክርስቶስ ጋር ያወዳድራቸዋል። ሚስቶች ለክርስቶስ እንደሚያደርገ ሁሉ ባሎቻቸውን ያክብራሉ ይገዙላቸዋል። "ባል የሚስቱ ራስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ ነው"። "ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እንደወደዳት ለእርሷም ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ"። በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ባል የራሱን ባህሪ በሚመለከት የክርስቶስን ምሳሌነት እንዲከተል ያስፈልገዋል።

ተግባራዊ በሆነ አገላለጽ ይህ ማለት፤ ባል እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሰ የሕይወት ደረጃ ቢኖርና ቢመላለስ፤ በዚያው ልክ ከሚስቱ ተገቢ የሆነውን አክብሮትና መገዛት ሊጠብቅ መብት አለው ማለት ነው። ባል የሚስቱን መገዛት ሊያገኝ የሚችለው እንደ ጌታ እስከተመላለሰ ጊዜ ድረስ ነው። እንደ ጌታ ሊመላለስ ካልቻለ ሚስት ለጌታ እንደምትገዛ ትገዛለት ዘንድ ሊጠብቅ ምንም አይነት መብት የለውም።



ባል የሚስቱን መገዛት ሊያገኝ የሚችለው እንደ ጌታ እስከተመላለሰ ጊዜ ድረስ ነው።

ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ለጌታ እንደምትገዛ ሚስቶች ለባሎቻቸው ይገዙ ነው የሚለው። ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ለእርሱ እንድትገዛ ያደረገው እንዴት ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ

ድንገት በቤተክርስቲ ያናችሁ እየተመላለሰ፤ የሆነ የገና ዱላ እየወዘወዘና ስንት ራሶችን እንደሚገጭ እየተመለከተ፤ "እድምጠ! እኔ ያልኳችሁን አድርጉ ያለበለዚያ!" እያለ ቢጮህ የሚፈጠረውን ልብ በሉ። እሽ የእርሱ የሆነችውን ቤተክርስቲያን ቢራገም ወይም ቢረጋግጣትና ቢለያያት፤ ክፉ ነገር ቢናገራትስ? ጌታን ትቶ ወደ ኋላ የመመለስ ወረርሽኝ በሽታ ይከሰታል። ከእነዚህ ሰዎችም አንዱ እኔ ነኝ። በግራና በቀኝ ተከታዮቹን ያጣል። እንዲህ አይነቱን ጌታ ለመከተል ማን ይፈልጋል?

እንዲህ አይደለም፤ ኢየሱስ የእርሱ ለሆነችው ቤተክርስቲያን መስዋእትነት በተሞላው ፍቅሩ በራሱ ፈቃድ በሆነ መገዛቱ ፍቅሩን፤ አክብሮቱንና መገዛቱንም አሳይቷል። በነፃና በፈቃደኝነት ህይወቱን ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል። በደሙም ቤተክርስቲያንን ከኃጢያትና ከበደል አነጻት፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ነቀፋና ጉድለት የሌለባት ትሆን ዘንድ አደረጋት። በመንፈሱም በኩል እበረታት፤ አጸትም፤ ዘላለማዊ በሆነ ፍቅር ወደዳት፤ ርህራሄውንም አሳያት፤ በዘላለም ምህረት ይቅር አላት፤ እንደ ክብሩም ባለጠግነት መጠን የሚያስፈልጋትን ሁሉ ሞላባት (ፊሊ 4፥19)።

ኢየሱስ እንከን የለሽ ምሳሌ ነው። ባሎች የሚስቶቻቸውን ፍቅር፤ ከበሬታና መገዛት ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ቤተክርስቲያኑን እንደተንከባከባት ሊመለከቱና ፍለጋውንም ሊከተሉ ያስፈልጋቸዋል።



ባሎች የሚስቶቻቸውን ፍቅር ከበሬታና መገዛት ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ቤተክርስቲያንን እንደተንከባከባት ሊመለከቱና ፍለጋውንም ሊከተሉ ያስፈልጋቸዋል።

ብዙ ባሎች ግዴታቸውን አልተወጡም

እንደአለመታደል ሆኖ መሠረታዊው እውነት ያ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ካመለከተው መመዘኛ በተቃራኒው ብዙ ወንዶች የገዥነትን ክብር አልተቀበሉም። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት ፍቅር ሚስቶቻቸውን መውደድን በሚመለከትም ብዙ ባሎች ግዴታቸውን አልተወጡም። ይህ ማለት ግን አብዛኞቹ ባሎች ሚስቶቻቸውን በእውነተኛ ፍቅር አይወዱም፤ ለእነርሱም የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ አይፈልጉም ማለት አይደለም። የባሎች

በክርስቶስ ኢየሱስ የመመዘኛ ልክ ሚዛን አለመድፋት የሚያመለክተው በእያንዳንዱ ወንድ ልብ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ጉድለትና፤ ይህንንም ጉድለት ሴቶች የተካፈሉት መሆኑን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጉድለት ኀጢያት ሲል ይጠራዋል። እርሱም ገና በኤድን ገነት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሰብአዊ ባለትዳሮች እግዚአብሔርን በድፍረት ካልታዘዙትና በራሳቸው መንገድ መሄድ ከመረጡ ጊዜ ጀምሮ የሰዎች ባህሪ አካል ሆኖ ቆይቷል። ኀጢያት ባሎች እስከ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ድረስ መዘርጋት እንዳይችሉ ያገደ ጉድለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ካመለከተው መመዘኛ በተቃራኒው፤ ብዙ ወንዶች የገዥነትን ከብር ስልተቀበሉም።

በኤድን ገነት ውስጥ አዳምና ሄዋን ምንም እንኳን የጋራ በሆነ እኩልነትና ስልጣን ደስተኞች የነበሩ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር አዳምን ሁሉን በሁሉ በሆነ ሃላፊነት ሚስቱን በእግዚአብሔር መንገድ ይመራትና ያስተምራት ዘንድ የቤተሰቡ ራስ አድርጎ ሃላፊነትን ሰጥቶታል። አዳምና ሄዋን እግዚአብሔርን ባልታዘዙ ጊዜ ኀጢያት የተፈጥሯቸው አንድ ክፍል ሆነ . . . ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ህብረት አጠፋው፤ እርሱንም እንዲፈሩት በማድረጉ ራሳቸውን ደበቁ። እግዚአብሔር ሊያያቸው በመጣ ጊዜ መጀመሪያ የተመለከተው አዳምን ነበር። ምንም እንኳ አስቀድማ አለመታዘዙን የፈጸመችውና ባልዋን ወደ ስህተቱ የጨመረችው ሄዋን ብትሆንም፤ አዳም ራስ ስለነበር እግዚአብሔር የቅድሚያ ተጠያቂነቱን ያደረገው በእርሱ ላይ ነበር።

"እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ጠርቶ፤ ወዴት ነህ አለው። እርሱም አለ በገነት ድምጽህን ሰማሁ ራቁቴንም ስለሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸኩም። እግዚአብሔር አለው፤ ራቁትህን እንደሆንህ ማን ነገረህ? ከእርሱ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍ በውኑ በላህን? አዳምም አለ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ። እግዚአብሔር አምላክ ሴቲቱን ይህ ያደርግሽው ምንድን ነው? አላት። ሴቲቱም አለች፤ እባብ አሳተኝና በላሁ" (ዘፍ 3፥9-13)።

ውድቀቱን አስመልክቶ እግዚአብሔር ፊት ለፊት በተናገረው ጊዜ ወዲያውኑ ነቀፌታውን ወደ ሄዋን ለማዞር መከራ አደረገ። በደሉን አምኖ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ፤ አዳም ሃላፊነቱን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ ሞከረ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ሰዎች ለወድቀታቸው ሃላፊነቱን በሌሎች ላይ ማስተላለፋቸውን ቀጠሉ።

አዳም እግዚአብሔርን ባልታዘዘ ጊዜና ኀጢያትም በፍጥረቱ ውስጥ ሲገባ ወዲያውኑ በህይወቱ ውስጥ አራት ነገሮች ተከስተዋል። የመጀመሪያው በደለኛ መሆኑን ማወቁ ነው። ምንም እንኳን አምኖ መቀበል ባይፈልግም በደለኛነቱን አውቋል። ሁለተኛ መፍራቱ ነው። ኀጢያት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መለያየትን ያመጣል፤ ያ መለያየት ደግሞ ፍርሃትን ይፈጥራል። ሦስተኛው ራሱን መደበቁ፤ አራተኛውም ሀፍረት መስማቱ ነው።

በደሉን አምኖ ስመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኑ፤ አዳም ሃላፊነቱን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ ሞከረ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰዎች ለውድቀታቸው ሃላፊነቱን በሌሎች ላይ ማስተላለፋቸውን ቀጠሉ።

እነኝህ ሁሉ የሰው የተለመዱ ልምምዶች ናቸው። በዚህም ዘመን እንኳን ሰዎች ስህተታቸውን በጭራሽ አምነው ባይቀበሉትም ስህተታቸውን ያውቁታል። ውድቀታቸው የመጋለጡ ሀሣብ በፍርሃት ይሞላቸዋል። ዛሬም ለዎች ከውድቀታቸው ይደበቃሉ። ብዙዎቹ ከማንነታቸው፤ ከአካላዊ ጥንካሬያቸው ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ስልጣንና ስፍራ ጀርባ ይደበቃሉ። ሌሎቹ ደግሞ ከገንዘብ፤ ካላቸው ተጽእኖ፤ ከፖለቲካ ስልጣን፤ ከሥራቸው፤ ከስፓርትና በውድቀታቸው ላይ በግልጽ ከመነጋገር ከሚከላከልላቸው ማንኛውም ነገር ጀርባ ይደበቃሉ።

ምንም እንኳን ጥቂቶች ውድቀታቸውን አምነው ቢቀበሉና ጠንካራ ተግባራዊ እርምጃ ቢወስዱም፤ ነገሮች ሲወሳሰቡና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ሰው ፍርሃት ይሰማዋል። ከዚህ ለማምለጥ ጉራ የተቀላቀለበት ንግግር ይናገራል ወይም እልህና ቁጣ በተሞላ ባህሪ ሀፍረቱን ይሸፋፍናል። ካልሆነም አልኮል በመጠጣት ሀፍረቱን ሊያደበዝዘው ወይም ልጆቹንና ሚስቱን በመደብደብ የራስ ጥላቻውን ሊያረግብ ይሞክራል። ምናልባትም ውድቀት ያጋጠመው ጋብቻው ሀፍረት፤ ከጋብቻ ውጭ ወደሚደረግ ወሲባዊ ግንኙነት ያመራዋል። ምናልባትም ይህንኑ ሀፍረቱን በሚስቱ ላይ በማሣበብ ስለወድቀቱ ሊኮንናት ይፈልጋል።

እንደ ውድቀት የሰውን ማንነት የሚያፈራርስ ነገር የለም። ሰዎች መላው አለም ያየው ዘንድ የውድቀታቸው መጋለጥ "ራቁትነታቸው" እጅግ ያስፈራቸዋል። ለዚህ ነው ብዙ ሰዎች፤ ጉድለታቸውን ሳያጋልጥ ወንድነታቸውን የሚያረጋግጥላቸውን ሀሰተኛ የሆነ ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን የሚፈልጉት። ስለራሳቸው

ያለውን እውነት ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ ስለራሳቸው ማንነት ሀሰት በሆነ መቀት ዘና ይላሉ።

ባሎች ሀላፊነታቸውን ሲሸከሙ ደገባል

እንግዲህ በሁለት ሣጥ መዋለል የሚከሰተው እዚህ ጋ ነው፤ ባሎች እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመላለሱ ይጠበቅባቸዋል፤ ይሁን እንጂ እንዲህ የሚያደርጉት ጥቂቶች ብቻ ናቸው። እርግጥ ነው ማንም ቢሆን ፍጹም አይደለም፤ የትኛውም ባል ቢሆን የክርስቶስን ባህሪ መሳ ለመሳ በህይወቱ ሊተረጉመው አይችልም። ችግሩ ብዙዎቹ ባሎች እንዴት መመላለስ እንደሚጠበቅባቸው ወይም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጥቂትም ፍንጭ የሚሰጥ እውነተኛ እውቀት የላቸውም። መለወጥ እንደሚገባቸው ቢገነዘቡም፤ ከእውተኛ ማንነታቸው ይደበቃሉ እንጂ እንዴት መለወጥ እንዳለባቸው አያውቁም።

ኢየሱስ ክርስቶስን የመከተላቸው እውነት የምር የሆነ ባሎች፤ ለሚስቶቻቸው ምሳሌ በመሆን ሀላፊነታቸውን ለመወጣት የግድ ፈቃደኞች ሊሆኑ ይገባቸዋል። ለድርጊቶቻቸው ሁሉ፤ ያለምንም ክህደት፣ ወይም ነቀፌታቸውን በሌላው በተለይም በሚስቶቻቸው ላይ ሳይለጥፉ፤ ሃለፊነትን ለመውሰድ ሊፈቅዱ የግድ ነው። ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት እንዳንድ ጊዜ ሊወድቁ እንደሚችሉ ሊገነዘቡ ያስፈልጋቸዋል፤ ይሁን እንጂ ይህ ለህፍረትና ከፍተኛ ለሆነ ቀውስ ምክንያት ሊሆን አይችልም። በአጋፔ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የምህረትንና የመደጋገፍን ሁኔታ የሚፈጥር ነው። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት በእውነት ሚስቱን ሊወድ የሚሞክር ማንኛውም ባል፤ ስኬትን ያገኘ ዘንድ ልትረዳው በከፍተኛ ጉጉት፣ ተዘጋጅታ ሚስቱን ከጎኑ ያገኛታል። የትኛዋ በትክክል ማሰብ የምትችል ሴት ናት፤ በእውነት ለሚወዳት፣ ለሚሸፍናት፤ አስፈላጊውን አቅርቦት ለሚያደርግላት፣ ራሱን ለእርሷ ለሚሰጥ፤ በትህትና ለሚያናግራት፣ የህይወቱ ሁሉ ማዕከል ላደረጋት ወንድ መልካም ምላሽ መስጠት የማይቻላት?

ሚስቱን መውደድን በሚመለከት ሁለንተናዊ እውድ ውስጥ፤ የባል የመጀመሪያና ቀዳሚ ሚና የቤቱ መንፈሳዊ መሪ፤ ጠባቂና አስተማሪነት ነው። በቃሉ፤ በህይወት እካሄዱና በግለሰባዊ ባህሪው ውስጥ ባል ቃሉን ሊያስተምር ለሚስቱና ለልጆቹ የጌታን ፈቃድና መንገድ ሊያሣይ ይገባዋል።

በዚህ ዘመን በጋብቻና በቤተሰብ ህይወት ውስጥ ዋነኛ ከሆኑት ችግሮች አንዱ፣ በብዙ ቤቶች ውስጥ ሀላፊነትን ለመውጣት ብቃት በማጣት ወይም ከእውቀት ማነስ የተነሣ ባሎች የመሪነት ስፍራቸውን መልቀቃቸው ነው። በብዙ አማኞች ቤት ውስጥ ሚስት ከባሏ ይልቅ ስለጌታ፣ ስለቃሉና መንገዶቹ አብልጣ ታውቃለች፤ ምክንያቱም ለእነዚህ ነገሮች ብዙውን ጊዜዋን መስጠቷ ነው። ባሏ የራሱ በሆነ ጉዳይ በሌላ ስፍራ በሆነ ጊዜ እርሷ ግን በቤተክርስቲያን ነች። አብሯት በቤተክርስቲያን በሆነ ጊዜ እንኳን ከሚስቱ አብዛኛውን ጊዜ በመንፈሣዊ ጉዳዮች ራሱን የሚሰጠውና የሚሳተፈው በመጠኑ ነው። የማያውቀውን ነገር ባል እንዴት ሊያስተምር ይችላል? ምንም በማያውቅበት ሁኔታ ውስጥ በህይወቱ ምሳሌነት እንዴት እድርጎ ነው ለቤተሰቡ አርአያ የሚሆነው?



በዚህ ዘመን በጋብቻና በቤተሰብ ህይወት ውስጥ ዋነኛ ከሆኑት ችግሮች አንዱ፤ በብዙ ቤቶች ውስጥ ሀላፊነትን ለመወጣት ብቃት በማጣት ወይም ከእውቀት ማነስ የተነሣ ባሎች የመሪነት ስፍራቸውን መልቀቃቸው ነው።

ክርስቶስ ቤተክርስቲንን እንደወደዳት ብዙ ባሎች ሚስቶቻቸውን ለመውደድ ታማኞች ቢሆኑና እንደ ቤተሰብ ራስነታቸው ሀላፊነታቸውን በብቃት ቢወጡ፤ ስለሚስቶች መገዛት ጉዳይ ባለው ግራ መጋባት ሊኖር የሚችለው ችግር መጠነኛ ይሆን ነበር።

ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደማረካት ባሎች ሚስቶቻቸውን ሊማርኩ ያስፈልጋል

ጳውሎስ ባልን ከክርስቶስ ጋር እንደሚያመሳስል እንዲሁ ደግሞ ሚስትን ከቤተክርስቲን ጋር ያመሳስላል። ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ ሚስት ለባልዋ ልትገዛ ያስፈልጋል። እንዲሁ ደግሞ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደደ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ይገባቸዋል። እነዚህ ሁለቱ ተወራራሽ ድርጊቶች ናቸው። መስዋእትነት ባለበት ፍቅር ባል ሚስቱን ሲወድ፤ ሚስቱ ደግሞ ለእርሱ ትገዛለታለች።

ባሎች የከበረ ህይወት በመኖር ሚስቶቻቸው ለእነርሱ እንዲገዙ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደደበትን መንገድ ሊማሩና ሚስቶቻቸውን እንደዚያው ሊወዱ ያስፈልጋል። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደዳት

እንዴት ነው? ህዝቡስ እንዲታዘዙት ወደ እርሱ የሳባቸው እንዴት ነው?



እነዚህ ሁለቱ ተመራመሽ ድርጊቶች ናቸው። መስዋእትነት ባለበት ቆቅቢ ባሷ ሚስቱን ሲመድ፤ ሚስቱ ደግሞ ለስርቆ ትገዛለታለች።

ኢየሱስ በእጁ ያስገባን እንድንወደው በማድረግ ነው። በመጀመሪያ በሆነ መንገድ ራሱን ገለጸልን። በፍቅሩም ልባችንን ተቆጣጠረው። ከዚያ በትህትና ወደራሱ አቀረበን፤ "በዘላለም ፍቅር ወድጀሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብኩሽ" (ኤር 31÷3)። ወደ እርሱ እንድንቀርብ ግልጽ የሆነ ግብዣውን በማቅረብ አሰፋልን፤ ጎጢያታችንንም ይቅር አለን፣ የዘላለምን ህይወት ስጦታም ተቀበልን። አንድ ጊዜ ምን ያህል እንደሚወደን ከተረዳን፣ ለእኛ ያደረገው ምን ያህል እንደሆነ ከተገነዘብን በኋላ ላንከተለው ብንቅር አይምሮ የለሾች መሆናችንን አወቅን። ይህ የተከናወነው ትህትና ለተሞላበት አቀራረቡ መልስ በሰጠንና ነፃ ፈቃዳችንን ተጠቅመን ወደ እርሱ በቀረብን ጊዜ ነው።

ለክርስቶስ ራሳችንን ማስገዛታችን የእኛ ምርጫ ነው። ወደ ራሱ መንገድ ገፍቶን አያውቅም። ኢየሱስ ክንዳችንን ይዞ የወዘወዘበት ወይም በማንኛውም መንገድ ጫናን አሳድሮብን አያውቅም፤ እርሱ በቀላሉ "እኔ በዚህ ነኝ፤ ወደ እኔ ና" ነው የሚለን። መገዛት በምንም አይነት ሁኔታ ከፈቃድህ ውጭ የሃይል ተጽእኖ አይጭንብህም። መገዛት ነፃ የሆነ ምርጫና በፈቃደኝነት መስጠት ነው። አንድ ጊዜ ህይወታችንን ለኢየሱስ ከሰጠን እርሱ የህይወታችን ማዕከል ይሆናል። የእርሱ ውሳኔ አስዘንና እጅግ እንወደዋለን እናም ለእርሱ ወደ የትም ሥፍራ ለመሄድ ሁሉንም ነገር ለማድረግ ዝግጁዎች ነን።

በዚህ ሁኔታ፤ ባል ሚስቱን ሊማርካት ያስፈልጋል። ሁልጊዜም በትልቅ ክብር፤ እንደ ሰው መስጠት የሚገባውን የመጨረሻ ክብር ለእርሷ በመስጠት መያዝ፤ በፀሎት መሸፈንና መጠበቅ በትህትና፤ በአስዋይነትና በርህራሄ ሊንከባከባት ያስፈልጋል። ስሜትን ሊያነቃቃ የሚችል ርህራሄ የተሞላበት ሁኔታ ለማሳየት አትፍራ። ለእርሷ እንደምታስብላት የሚያሳይ ጥቂት ተግባራዊ ነገር ማድረግንም አትርሳ።

አበቦችን ግዛለት፤ ምርጥ ወደሆነ ምግብ ቤት ወስደህ ራት ጋብዛት። የሳምንቱን መጨረሻ ሁለታችሁ ብቻ ወጣ ብላችሁ የምትዝናኑበትን ሁኔታ ፍጠር። በቃላት፤ በተግባርና በማናቸውም አመች በሆነ ሁኔታ ሁሉ፤ የተወደደች ዋጋ ያላትና ከሌሎች ሁሉ የተለየች እንደሆነች እንድታውቅ አድርግ።

የሚስት መገዛት በፈቃደኝነት ነው

እስከ እሁን ድረስ ትኩረት ያደረግነው በባሎች ሃላፊነት ጉዳይ ላይ ነበር። ይህ ደግሞ በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ባል የቤቱ ራስ እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ሃላፊነት በመሸከሙ፤ ሁለተኛውም የእርሱን ሃላፊነት በሚመለከት በሰፊው የተሳሳተ ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑና ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት በመሆኑ ምክንያት ነው።

ባል የሚስቱ ራስ እንጂ የሚስቱም ይሁን የቤቱ አለቀ አይደለም። እዚህ ላይ ነው ብዙ ባሎች የሚሳሳቱት። እርስ በእርስ የሚቃረን ይመስላል፤ ይሁን እንጂ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን መርቷታል እንጂ ብርቱ በሆነ የብረት ዘንግ አልገዛትም ። ክርስቶስ መንግስቱን ይገዛል፤ ቤተክርስቲያኑን ግን ይመራታል። ቤተክርስቲያኑን ይወዳታል በፍቅርም ይንከባከባታል፤ ቤተክርስቲያኑም በነፃና በፈቃደኝነት ትገዛለታለች።

ታዲያ ሴቶችን በሚመለከትስ ነገሩ እንዴት ነው? ባልዋን በሚመለከት ሀላፊነቷ ምን ድረስ ነው? ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን የሰጠውን መመሪያ ልብ በሉ፤ "ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ . . . ዳሩ ግን ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ" (ኤፌ 5÷22፤24)። ቤተክርስቲያን ጌታዋ ለሆነው ለክርስቶስ የምትገዛው እንዴት ነው? በነፃ፣ በፈቃደኝነትና ከፍቅር በመነጨ መገዛት ነው። ሚስት ለባሏ ልትገዛ የሚያስፈልጋት ይሄው ብቃት ባለው ባህሪ ነው።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ የጳውሎስ ቃላት ትእዛዝን የሚደነግጉ ናቸው። "ሚስቶች ሆይ ለባሎቻችሁ ተገዙ"። ልብ በሉ ይህ ትእዛዝ የተሰጠው ለሚስቶች እንጂ ለባሎች አይደለም። ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ ታዘዋል። ጳውሎስ በየትኛውም ስፍራ ሚስቶቻቸው ይገዙላቸው ዘንድ ባሎች እንዲያስገድዷቸው ባሎችን አላዘዘም ወይም ስልጣንን አልሰጣቸውም። በግዳጅ የሆነ መገዛት

እውነተኛ መገዛት ሳይሆን በሀይል ተጽእኖ ስር መሆን ነው። እውነተኛ መገዛት ሁልጊዜም በነፃ ምርጫና በፈቃደኝነት መሰጠት ነው።

ምንም እንኳ ሚስት እንድትገዛ የታዘዘች ብትሆንም፤ መገዛቷ በፈቃደኝነት ነው። የመምረጥ ፈቃድ አላት። ባሏ ሃላፊነቱን እስከተወጣ ድረስ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት መስዋእትነትና ራስን መስጠት ባለው ፍቅር ሊወዳት የሚፈልግ ከሆነ፤ ሚስት በሁሉ ለባሏ ልትገዛ ሃላፊነት አለባት። ይህን ልታደርግ ካልቻለች፤ በባሏም ዘንድ ብቻ ሳይሆን በጌታ ዘንድ ተጠያቂነት አለባት። ለባሏ ራስነት ለመገዛት አለመቻል ኀጢያት ነው።



በግዳጅ የሆነ መገዛት እውነተኛ መገዛት ሳይሆን በዘይሰ ተጽእኖ ስር መሆን ነው።

ለሚስቱ በሚያደርገው ነገር ሁሉ በባህሪውና በዝንባሌው ኢየሱስን ለመምሰል ትልቅ ጥረት ለሚያደርግ መልካም ባል መገዛት፤ ክብርን የሚያሳጣና ስብእናን የሚያዋርድ ተግባር አይደለም። መገዛት ለራስ ያለን ለመሰካከት ዝቅ ማድረግ ወይም የሚስት ስብእናና ፈቃድ በመራራ ሀዘን ለባሏ ፍላጎትና ፈቃድ ታልፎ መሰጠት አይደለም።

ከሚስቱ ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ እንደ ኢየሱስ የሚመላለስ ባል በማንኛውም መንገድ እንዲህ ላለው ጉዳይ ሚስቱ ታልፋ እንድትሰጥ አያደርግም።

መገዛት ማለት፤ ሚስት እንደ መንፈሳዊና የቤተሰብ መሪነቱ የባሏን ራስነት አምና መቀበሏ ነው። ይህ ማለት ፈቃዷን፣ መንፈሷን፣ እውቀቷን፣ ልዩ ችሎታዋን ወይም ስብእናዋን የማያስክድና በግዳጅ የሚያስጥላት ነው ማለት አይደለም። መገዛት ማለት እግዚአብሔር ለባሏ የሰጠው መላውን ቤተሰብ የመምራት ሃላፊነት እውቅና መስጠት፤ ማጽደቅና መደገፍ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ሚስት ለባሏ መገዛት፤ ባል ስተሰጠው የመሪነት ስፍራ መገዛት ማለት እንጂ ለግለሰባዊ ማንነቱ መገዛት ማለት አይደለም። መገዛት ሥርዓት እንዲከበር፣ መረጋጋት እንዲፈጠርና የእግዚአብሔርን እቅድ ለመታዘዝ እንዲያስችል፤ እኩልነትን ያማከለ ነፃና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ራስን ለሌላው ዝቅ ማድረግ ነው። እንደ ወንድነቱ፤ ባል የሃላፊነት

ግዴታውን ለመወጣት የመሪነት ተግባሩን በፀሎትና ለኢየሱስ ክርስቶስ ራስን በፈቃደኝነት በመሰጠት ይለማመዳል። መስዋትነት ባለበት ፍቅርም ራሱን ለሚስቱ አሳልፎ ይሰጣል። እንደ ሴትነቷ፤ ሚስት ሴትነቷን በመገንዘብ ጌታን ለማክበር ለባሏ ትገዛለች። የባሏን ፍቅርና መሪነቱንም ትቀበላለች። የጋራ የሆነ እንዱ ለሌላው መገዛት ያለበት እግባብ ያለው ግንኙነት ሲኖር፤ ሴት እግዚአብሔር እንደሚፈልጋት አይነት ሴት ለመሆን ትለቀቃለች፣ ሀይልንም ታገኛለች።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለለ ሆነው መገዛት በሁለቱም ባልና ሚስት ዘንድ እግባብነት ያለው ግንዛቤና ልምምድ መኖር ዘላቂነት ላለው ስኬታማና ደስተኛ ጋብቻ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ያለእነዚህ ነገሮች፣ ባለትዳሮቹ በክርስቶስ ሙሉ ስለሆነ ማንነታቸው ወይም በእግዚአብሔር መልክ እንደተፈጠረ ሰብአዊ ፍጥረትነታቸው ያላቸውን እምቅ ክህሎት ሊገነዘቡት ከቶውንም አይችሉም።

መርሆዎች

1. ባል ሚስቱን በሚመለከት ነገር ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን በመምሰል በተመላለሰበት ስፋትና መጠን፤ የሚስቱን መገዛትና ከበሬታ ለማግኘት የመጠበቅና የመቀበል መብት አለው።

2. ጎጢያት፤ ባሎች የኢየሱስን ምሳሌነት መጠን እንዳይዘረጉ ግርዶሽ የሚሆን በደለኝነት ነው።

3. ሚስትን መውደድን በሚመለከት ባለ አጠቃላይ አውድ ውስጥ፤ የባል የመጀመሪያውና ቀዳሚው ሚና የቤቱ መንፈሳዊ መሪነት አስተማሪነትና ጠባቂነት ነው።

4. ባሎች የከበረ ህይወት በመኖር ሚስቶቻቸው ለእነርሱ እንዲገዙ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የወደደበትን መንገድ ሊማሩና ሚስቶቻቸውን እንደዚያው ሊወዱ ያስፈልጋል።

5. እውነተኛ መገዛት በምንም አይነት ሁኔታ ከፈቃድህ ውጭ የህይል ተጽእኖ አይጭንብህም። መገዛት ነፃ የሆነ ምርጫና በፈቃደኝነት መሰጠት ነው።

6. ባሏ ሀላፊነቱን እስከተወጣና መስዋእትነት በተሞላበት፤ ራስን መስጠት ባለበት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክስቲያንን በወደደበት ፍቅር ሊወዳት እስከፈለገ ድረስ፤ ሚስት በነገር ሁሉ ለባሏ የመገዛት ሀላፊነት አለበት።

7. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የሚስት ለባሏ መገዛት፤ ባል ለተሰጠው የመሪነት ስፍራ መገዛት ማለት እንጂ ለግለሰባዊ ማንነቱ መገዛት ማለት አይደለም። መገዛት፤ ሥርዓት እንዲከበር፤ መረጋጋት እንዲፈጠርና የእግዚአብሔርን እቅድ ለመታዘዝ እንዲቻል እኩልነትን ያማከለ ነፃና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ራስን ለሌላው ዝቅ ማድረግ ነው።

ምዕራፍ ሰባት

የግንኙነትን ጥበብ መካን

አብዛኛውን ጊዜ ከባለትዳሮች ከሚለሙት ቅሬታዎች መካከል፤ "እሷ እኔን አልተረዳችኝም" ወይም "ፊጽሞ እኔን አይለማኝም" የሚሉ ይገኙባቸዋል። በታላቅ ነውጥ ውስጥ እጅግ ብዙ ትዳሮች እያሽቆለቆሉ ያሉት፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ባለትዳሮቹ እርስ በእርሳቸው በግንኙነታቸው ውስጥ መግባባት ባለመቻላቸው ነው።

በትዳር ውስጥ የሚነሱ ችግሮችን እስመልክቶ፤ ለረዥም ዓመታት በቆየው አገልግሎቴ በመቶዎች የሚቆጠሩ ባለትዳሮችን እማክራያለሁ። ከጥቂቶቹ ጉዳዮች በስተቀር ሁሉም ማለት ይቻላል በዋናነት የግንኙነት ችግር የተመሠረተው ግንኙነቱ ከመሠረቱ የተሰበረ በመሆኑ ነው። ባለትዳሮችን ባመከርኩ ጊዜ ሁሉ፤ መሠረታዊ የሆኑ ሀሳቾችን እንተገብራለን። በመጀመሪያ ባል ሲናገር ሚስት ትሰማለች። ሁለተኛም ሚስት ስትናገር፤ ባል ያደምጣል። ሦስተኛ ሁለቱም ከተናገሩ በኋላ እኔ እናገራለሁ እነርሱ ይሰማሉ። እንድ ለው እየተናገረ እያለ ማንም ጣልቃ አይገባም። እንደኛው ወገን በሚናገርበት ሰዓት ብዙውን ጊዜ በሌላኛው ወገን ፊት ላይ የሚታየውን የመደነቅ እይታ መመልከት የሚያስደንቅ ነው። በብዙዎቹ ጉዳዮች ውስጥ፤ በወሩ እንዲያውም በአመቱ ውስጥ በእግባቡ ሲነጋገሩ ገና የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነው፤ እናም በሚሰሙት ነገር ሙሉ በሙሉ ይገረማሉ።

ግንኙነት ልንማረው የሚገባ ጥበብ ነው፤ ልንካንበት የሚገባ ክህሎት። በጋብቻም ውስጥ ቢሆን እንኳን ፈጥኖ ሊመጣ የሚችል ነገር አይደለም። እውነተኛ ግንኙነት ሊመጣ የሚችለው ሁኖ የሆነ የራስ ግልጽነት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ ነው። ብዙ ባለትዳሮች እርስ በእርሳቸው ለረዥም ጊዜ ይነጋገራሉ፤ ይሁን እንጂ በእግባቡ የሚነጋገሩት እጅግ ጥቂቱን ጊዜ ብቻ ነው። ስለተናገሩ ብቻ ግንኝ ነት አድርገዋል ማለት አይደለም።

እንዳንድ ባለትዳሮች የሚነጋገሩት ሊጨቃጨቁ ብቻ ነው። እንዳንድ ጊዜ በእዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው አብዛኞቹ ባልና ሚስት ወቀሳን ያዘሉ ንግግሮች፤ አሉታዊ የሆኑ አስተያየቶችን አንዳቸው ከሌላው የሚሰሙት። ግንኙነትን በጥሩ ሁኔታ የምንማረው ግልጽ፤

ሀቀኛና ክርክር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ነው። በተረጋጋና ዝግ ባለ መንገድ እንዴት መግባባት እንዳለባቸው ያልተማሩ ባለትዳሮች ክርክር በተሞላበት መንገድ መቼም ቢሆን መግባባት አይችሉም።

ቀና የሆነ ግንኙነት እንዲኖር አመች ሁኔታዎችን መፍጠር ታስቦበት ሊታቀድ አስፈላጊና ግድ ነው። ጥሩ የሆነ የአትክልት ስፍራ እንዲኖረኝ የምፈልግ ከሆነ፤ በአድሉ ይደግ ብየ አልተወውም። ብዙ ብርሃን የሚያገኝበትን ስፍራ አመርጣለሁ፤ አፈሩን አዘጋጃለሁ፤ ዘሩን እተክላለሁ፣ ማዳበሪያ እጨምርለታለሁ፣ አረሙን በየጊዜው እነቅላለሁ እንዲሁም ተክሉ በቂ ውሃ ማግኘቱን አረጋግጣለሁ። እንደዚሁ ደግሞ ለግንኙነት አመች የሆነውን ሁኔታ፤ በታላቅ ጥንቃቄ መገንባትና ስራየ ብሎ እድገቱንም መከታተል ያስፈልጋል። በሚነጋገሩባቸው ቀላል የሆኑ ጉዳዮች ላይ ግልጽነት፣ መተማመንንና ሞገስ ያለውን ንግግር የገነቡና እየዘለቁበትም ያሉ ባለትዳሮች፤ ጠንካራ የሆኑ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ ለመነጋገር ቀላል ሆኖ ያገኙታል።



ግንኙነትን በጥሩ ሁኔታ የምንማሪው ግልጽ፤ ዘቀኛና ክርክር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ነው።

ግንኙነት ደግሞ ለህይወት ዋነኛው ነገር እንደሆነ ሁሉ ለፍቅርም ግንኙነት እንዲሁ ነው። ያለ ግንኙነት ማንኛውም ጤናማ የሆነ ህብረት ማድረግ በጭራሽ አይቻልም። ይህ በሰዎች መካከልም ይሁን ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት የሚሠራ እውነት ነው።

ግንኙነትን መገንዘብ


በጋብቻ ውስጥ ባለ ግንኙነት ከፊሉ ችግር የሚመሠረተው ብዙ ባለትዳሮች ግንኙነት ማለት በእውነት ምን ማለት እንደሆነ ባለማወቅ ግራ በመጋባታቸው ነው። እውነተኛ የሆነ ግንኙነት መናገርንና መረዳትን ሁለቱንም ይጠይቃል። ንግግር ሃሳብን፣ አመለካከትን፣ ስሜትን፣ በድምጽ፣ በአካል እንቅስቃሴ ወይም በፊት ገጽታ መግለጽን የሚያመላክት ነው። መረዳት ደግሞ የተነገረውን ማድመጥ ብቻ ሳይሆን፤ በተናጋሪው አመለካከት አውድ ውስጥ የተነገረውን መተርጎምን ያካትታል።

በወንዶችና በሴቶች ወይም በባልና በሚስት መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ የሚሆነው፤ ወንዶችና ሴቶች በተለያየ መንገድ ስለሚያስቡ፤ በተለያየ መንገድ ነገሮችን ስለሚገነዘቡና በተለያየ መንገድ ምላሽ ስለሚሰጡ ነው። በጥቅሉ ወንዶች ምክንያታዊነት

ላይ ተመስርተው ያስባሉ፤ ሴቶች ደግሞ በፍልቅ ስሜታቸው ላይ ተመስርተው የሚያስቡ ናቸው። ወንዶች የሚያስቡትን ይናገራሉ፤ ሴቶች የሚናገሩት ደግሞ የተሰማቸውን ነው። ወንዶች የሚሰሙትን ከእውነታና ከምክንታዊነት ማነጻጸሪያ አቅጣጫ በመነሳት ይተረጉሙታል፤ ሴቶች ደግሞ ከፍልቅ ስሜት ማነጻጸሪያ አቅጣጫ በመነሳት ይተረጉሙታል። በሌላ አገላለጽ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች አንድ አይነት መልዕክት፣ በአንድ አይነት ጊዜ፣ በአንድ አይነት ተናጋሪ ሊሰሙ ይችላሉ፤ እናም ያንኑ መልዕክት በሁለት ሙሉ በሙሉ በተለያዩ መንገዶች ይገነዘቡታል። እርስ በእርሳቸው ግንኙነት ሊያደርጉ በሞከሩ ጊዜም ተመሳሳይ ችግር በቀላሉ ይነሳል።

ብዙ ሰዎች የቃላት ልውውጥን ከግንኙነት ጋር አኩል አድርገው ይመለከቱታል። ሁለት ሰዎች ስለተነጋገሩ ብቻ የግድ ተግባብተዋል ማለት አይደለም። አንደኛው የሚናገረውን ምናልባትም ሌላው የሚሰማውን ላይሆን ይችላል። አንደኛው የማሰማውም ሌላኛው የሚናገረውን ላይሆን ይችላል። የሁለት ሰዎች የቃላት ልውውጥ ግንኙነትን አያረጋግጥልንም። አሁንም እንደገና ቁልፉ ጉዳይ መረዳት ነው።

አንድን ነገር መረዳት ከአንድ ሰው የተነገረውን ቃል በቀላሉ ከመቀበል የላቀ ነገር ነው፤ ቃላዊ የሆነው አላባ ትልቅ ክሆነው የለብአዊ ፍጥረት ግንኙነት ውስጥ ትንሹ ክፍል ብቻ ነው። በአካል እንቅስቃሴና በፊት ገጽታ የሚገለጹ ቃላዊ ያልሆኑ የግንኙነት አላባዎች የተቀበልነውን መልእክት እንዴት እንደምንተረጉም በቃል ከተነገረው የላቀውን ሚና ይጫወታሉ። ሞቅ ካለ ፈገግታ ጋር ወይስ ጥርሶቼን ነክሼ፣ በፊቴ ላይ ቁጣ እየነደደ፣ እጀን ቡጢ ጨብጬ፤ "እወድሃለሁ" ብየ ብናገር የትኛውን ነው የምታምኑት? ምንም እንኳን ቃላቶቹ ያው ቢሆኑም ቃላቶቹ የተሸጋገሩበት ሁኔታ ፈጽሞ የተለየ ነው።



በአካል እንቅስቃሴና በፊት ገጽታ የሚገለጹ ቃላዊ ያልሆኑ የግንኙነት አላባዎች የተቀበልነውን መልዕክት እንዴት እንደምንተረጉም በቃል ከተነገረው የላቀውን ሚና ይጫወታሉ።

ግንኙነት በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል የተለመዱ ምልክቶችና ባህሪዎችን በመጠቀም መልዕክት የሚተላለፍበት ሂደት ነው። ግንኙነት መልእክትን፣ ሀሳብን ወይም ስሜትን ማስተላለፊያ

በመሆኑ በእጥጋቢ ሁኔታ ተቀባይ ማግኘት ወይም በቀላሉ መረዳት የሚያስችል መሆን አለበት። ግንኙነት መልዕክቱን ባስተላለፉትና መልእክቱን በሚቀበሉት እንዲሁም እንዱ ሌላኛው ምን ማለት እንደፈለገ በተረዱ ሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ የሁለትዬሽ ተሳትፎ ነው። እኔ ለእንተ አንድ ነገር ብናገር፤ የለማኸውን እንደተረዳሀና ምን ማለት እንደፈለግሀ እንደገባህ በማረጋገጥ መልሰህ ብትናገረኝ፤ ያንን ነው እውነተኛ የሆነ ግንኙነት የምለው። ለግንኙነት ቁልፍ የሆነው ነገር መረዳት ከሆነ፤ ለመረዳት ቁልፍ የሆነው ነገር ደግሞ ማዳመጥ ነው።

ስድምጥ!

ፈጣን እንቅስቃሴና እጅጉን ውጥረት በበዛበት በዛሬው የሰለጠነ ዓለም ውስጥ ማድመጥ ሊጠፋ የታቀረበ ጥበብ ሆኗል። በግንኙነት ውስጥ ከሚፈጠሩ ችግሮች ማድመጥ አለመቻል እንደኛ ውና ተደጋግሞ የሚከሰተው ነው። ብዙውን ጊዜም ተፈጥሯዊ የሆነው ዝንባሌያችን ከመስማት በፊት መናገር ነው። በቀላሉ ከመናገራችን በፊት ማድመጥን ብንማር፤ ጉዳትን፣ ግራመጋባትንና ሀፍረትን ልናስወግድ እንችላለን።

ኢፒስትዮስ የተባለው የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የግሪክ ፈላስፋ፤ "ሁለት ጆሮዎችና እንድ እፍ አለን፤ በተናገርን ጊዜ ሁሉ ሁለት እጥፍ ማድመጥ እንችላለን" ሲል ተናግሯል። ይህ ትልቅ እውነትን የያዘ መግለጫ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የመሰሉ በርካታ ጥበቦችን ይዟል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማድመጥ ከጥበብና ከመረዳት ጋር ተያይዟ እናገኛለን። መጽሐፈ ምሳሌ ደግሞ ደጋግሞ የጥበብን ቃል እንድናደምጥና እንድንማር ያሳስበናል። ኢየሱስ ክርስቶስም ደጋግሞ የሚከተሉት እንዲሰሙት እንዲህ ብሏል "ስሙ፣ አስተውሉ" (ማቴ 15፥10)።

ኢየሱስ "የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" እያለ የተናገረውም ብዙ ጊዜ ነው። ምናልባትም በማድመጥና በመናገር መካከል ሊኖር ስለሚገባው ሚዛናዊነት እጅግ ቀጥተኛ የሆነ ማብራሪያ የተሰጠው በእዱስ ኪዳን በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ ነው። "የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ይህንን አትርሱ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርና ለቁጣም የዘገየ ይሁን። ምክንያቱም የሰው ቁጣ የእግዚአብሔር ጽድቅ በሰው ህይወት ውስጥ ፍጹም እያደርገውም።" (ያዕ 1፥19-20)።

ያዕቆብ ለማድመጥ መዘጋጀትን፤ አንድን ነገር ሳይረዱ መናገርን፣ አላስፈላጊ ወይም አግባብነት የሌለው ቁጣን ከማስወገድ ጋር አያይዞ ይገልጸዋል። መጀመሪያ ለማድመጥ ጊዜ ሳለመስጠታቸው ምክንያት ባልና ሚስት ምን ያህል ጊዜ ሃይለ ቃል ተነጋግረዋል፣ ተቆጥተዋልስ? የያዕቆብን ምክር ምናልባትም እንዲህ ልንለው እንችላለን። "አስቀድመህ አድምጥ! ለመናገር የፈጠንክ አትሁን፤ እንዲያውም ምን እንደምትናገርና እንዴት እንደምትናገረውም ጥንቃቄ አድርግ። ፈጥነህ በንዴት አትገንፍል፤ ምክንያቱም የሚፈነዳ ቁጣ ለመንፈሳዊ እድገትህ እንቅፋት ሆኖ የተጠመደልህ ሴራ ነው"።

ማድመጥ በቀላሉ አንድ ሰው የሚናገረውን ከመስማትና ከመረዳት የበለጠ ነገሮችን የሚያካትት ነው። የምንሰማቸው ማንኛውም ነገሮች በራሳችን እምነት፣ በልምምዳችን፣ ስለተናጋሪው ባለን እውቀትና እመለካከት ማጣሪያ ውስጥ እየተጣሩ ያልፋሉ። እነኚህ ማጣሪያዎች የሰማነውን እንዴት እንደምንተረጉመው ዕልክ ይሰጡታል፤ እንዳንድ ጊዜም ተናጋሪው የተናገረውን በአግባቡ እንዳንረዳ ምክንያት ይሆናሉ። ጥሩ እድማጭነት ሌሎች ሰዎች የተናገሩት በእርግጥ ምን እንደሆነ ከምናጣራባቸው ማጣሪያዎቻችን ያለፈ፤ የሚናገሩትን ቃል ብቻ ሳይሆን በተጨማሪ የድምጻቸውን ስሜት፣ የፊት ገጽታ ገለጻቸውንና የሰውነት ቋንቋቸውን የሚያካትት ነው።

ከማድመጥ ጋር የተያያዘው ሌላኛው ችግር፤ ሌላው ሰው ከሚናገራቸው ቃላት ይልቅ በራሳችን ቃላት ላይ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት ሰናደርግ ነው፤ ከሰዎች ጋር እየተነጋገራችሁ ሣለ እነርሱን ከማድመጥ ይልቅ ቀጥሎ ምን እንደምትናገሩ እያሰባችሁ ሥራ የበዛባችሁ ጊዜ የለም? በተመሳሳይ ምክንያት ሌላው ሰው የማያደምጣችሁ እንደሆነ የተሰማችሁ ጊዜ የለም? እንደነዚህ ዓይነት ነገሮች ሁልጊዜም ይከሰታሉ እናም የንግግር ልውውጦች እንላቸዋለን። ይህ የንግግር ልውውጥ ሊሆን ይችላል ግንኙነት ሊሆን ግን አይችልም፤ ምክንያቱም የሚያደምጥ ማንም የለም። የጋራ በሆነ መግባባት የተረጋገጠ የመረጃ ልውውጥ የለም። የማድመጥ ጥበብ አንድ ክፍል የሆነው ለሌላው ሰው ሙሉ ትኩረታችንን መስጠት ማመር፤ እውነተኛ በሆነ የመረዳት ፍላጎት አለ ወይም እርሷ በሚናገሩት ነገር ላይ እውነተኛ የሆነ ፍላጎት ማሳደር ነው። ግንኙነትን ግባችን አድርገን ከተነሳን ከራሳችን ይልቅ በሌላው ሰው ቃላት፣ ሃሳብና እሴት ላይ ትኩረት ማድረግ

ይኖርብናል። በዚህ ዓለም ውስጥ አንድን ሰው ከመደመጥ፣ በእውነት ከመደመጥ ይልቅ የሚባርከው ነገር የለም።



በዚህ ዓለም ውስጥ አንድን ሰው ከመደመጥ፣ በእውነት ከመደመጥ ደልቅ የሚባርከው ነገር የለም።

አግባብነት ያለውና ውጤታማ የሆነ ማድመጥ የሁለንተናችንን ተሳትፎ የሚያካትት ነው። እውነተኛ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር ሙሉ ለሙሉ ማድመጥን ልንማር ያስፈልጋል፤ ይህም የአካልተሣትፎን፣ አይምሯችንን ፍልቅ ስሜታችንን፣ አይኖቻችንን፣ ጆሮዎቻችንን በእጭሩ ሁለንተናችንን ያካተተ ነው። ሌላውን ሰው ለመስማትና ለመረዳት እንዲያስችለን በመጀመሪያ ደረጃ የራሳችንን ሃሣብ፣ ቃላትና እጀንዳ ወደ ጎን አድርገን ማድመጥ ያስፈልገናል። አንድ ጊዜ ከተረዳንና መረዳታችንንም ሌላው ሰው ካወቀ፤ ከዚያ በኋላ ከዚህ መረዳት በመነሣት አግባብነት ያለው ምላሽ መስጠት እንችላለን። ይህ እውነተኛ የሆነ የሁለትዬሽ ግንኙነት እንዲኖር ግልጽ የመሸጋገሪያ ድልድይ ይፈጥራል።

ሁለን ስቀፍ ግንኙነት

ግንኙነት ጥበብ በመሆኑ ምክንያት፤ ይሁነኝ ብለን፣ በትእግስትና በጥንቃቄ በጊዜ ሂደት ውስጥ ልንማረው የግድ ያስፈልጋል። ውጤታማ የሆነ የፊት ለፊት ግንኙነት በባህሪው ሁልጊዜም ሁሉን አቀፍ የስሜታችንንና የአካላችንን ሙሉ ተሳትፎ፤ የእውቀታችንንና የአይምሯችንን ሃይል የሚያካትት ነው።

ግንኙነት በግለሰቦች መካከል የጋራ የሆነ መግባባት እንዲፈጠር የመረጃና የመልእክት ልውውጥ ነው። ማንኛውም መልዕክት ሦስት አላባዎች አሉት፤ ይዘት፣ የድምጽ ቅላጼና ቃላት ያልሆኑ ምልክቶች ማለትም የአካል እንቅስቃሴ፣ በፊት ገጽታ የሚገለጽ ስሜትና፣ የሰውነት ቋንቋ ናቸው። እነዚህ ሦስቱም ህብር ባለው መልኩ ሲሠሩ የጋራ የሆነ መግባባት የመፈጠሩን ሁኔታ ከፍ ያደርገዋል። ከነዚህ አላባዎች ማንኛውም ቢጎድል ወይም ሌላው ሰው በተቃራኒው ከተረዳው ውጤታማ ግንኙነት የመፈጠሩን ሁኔታ እጅጉን ዝቅ ያደርገዋል።

የሰውን ፍልቅ ስሜትና ስብእና በሚያካትቱ በማናቸውም ግንኙነቶች ውስጥ ቃላዊ ከሆኑት ይልቅ ቃላዊ ያልሆኑት አላባውያን እጅጉን የጎሉ ናቸው። ይህ በቀላሉ በህይወት እውነታ

ውስጥ የሚገለጽ ነው። ጓደኛህ የሚወደውን አንድ ሰው በሞት አጥቷል። ሀዘንህን በመግለጽ ልትረዳው ፈልገሃል፤ ምን እንደምትል ግን አታውቅም። በጣም ብዙ ጊዜ እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ቃላት ሊባል የታሰበውን ነገር ሊገልጡ አቅም የላቸውም። ለጓደኛህ አሁን ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር በቀላሉ የእንተ በአካል እዚያ መገኘት ነው። ከንዱን ጠበቅ አድርገህ ትይዛለህ፣ በሞቀ የማጽናናት መንፈስ በአንድነት ታለቅሳላችሁ፤ እነዚህ በቀላሉ ቃላዊ ያልሆኑ ለጓደኛህ ያለህን ፍቅርና ረዳትነት የምትገልጽባቸው ድርጊቶች ናቸው። ታስቦባቸውና ታቅደው በሰውነት እንቅስቃሴ ከሚገለጹ ከብዙ ቃላት ይልቅ በላጭ ገላጮች ናቸው።

ጥናቶችም ይህንኑ እውነት ያረጋግጣሉ። በግንኙነት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ቃላዊ የሆነው አላባ ወይም ይዘት፤ ከምንልው ወይም ሌላው ሰው ከሚቀበለው መልዕክት የሚይዘው ሰባት በመቶ የሆነውን ብቻ ነው። የድምጽ ቅላጼ 38 በመቶ ሌሎች ቃላዊ ያልሆኑ መግለጫዎች ደግሞ ቀሪውን 55 በመቶ ይሸፍናሉ። በሌላ ቋንቋ ሌላው ሰው እንዴት እንደሚገነዘበንና እንደሚረዳን የሚወሰነው፣ በቃላት ከምንናገረው 7 በመቶ፣ እንዴት እንደተናገርነው 38 በመቶ እንዲሁም እየተናገርን ሣለ ስንሰራው የነበረው ነገር 55 በመቶ ይይዛል ማለት ነው።

አለመግባባትን፣ ስሜትን የሚጎዱ ነገሮችንና ክርክሮችን ማስወገድ የምንሻ ከሆነ፤ የድምጽ ቅላጼያችን፣ የሰውነት እንቅስቃሴያችን፣ የፊት ገጽታ ገለፃችን፣ የሰውነት ቋንቋችን፤ በከንፈራችን ከሚነገሩት ቃላችን ጋር ተመሳሳይ መልእክት ማስተላለፋቸውን በጥንቃቄ እርግጠኞች መሆን አለብን።

እጅግ ብዙ ሰዎች ባለትዳሮችንም ጨምሮ በዚህ ቃላዊ ባልሆነ ግንኙነት ዙሪያ ብዙ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት የንግግር ልውውጥ፤ ምን እንዳሉና ያንን ነገር እንዴት እንዳሉት ባለው ልዩነት መካከል በሚፈጠር የግንኙነት መቋረጥ ምክንያት ችግሮች ይከሰታሉ። በተለይም ደግሞ የተዛባ የድምጽ ቅላጼ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ፤ ጥቂት የሆነውን አለመግባባት በፍጥነት ከፍተኛ ወደ ሆነ የጩኸት ውድድር ወይም አስፈላጊነት የሌላቸው የቃላት ጦር መወራወሪያ የጦር ሜዳ ይፈጥራሉ።



ባልና ሚስት ስርስ በስርሳቸው በሚያደርጉት የንግግር ልውውጥ፤ ምን እንዳሱና ያንን ነገር እንዴት እንዳሱት ባለው ልዩነት መካከል በሚፈጠር የግንኙነት መቋረጥ ምክንያት ችግሮች ይከሰታሱ።

በዚህ ምክንያትት ባለትዳሮች የያዕቆብን ምክር ሊያስታውሱ ያስፈልጋቸዋል፤ "ለመስማት የፈጠንክ፤ ለመናገርና ለመቆጣት የዘገየህ ሁን"። በተጨማሪ ምሣ 1÷51 ሌላ ጠቃሚ ምክር ይለግሰናል፤ "የለዘበች ምላስ ቁጣን ትመልሳለች፤ ሻካራ ቃል ግን ቁጣን ታነሣሣለች" ባልና ሚስት የንግግር ልውውጥ ግንኙነት በሚያደርጉ ጊዜ፤ የድምጻቸው ቅላጼና ፊታቸው ከሚናገሩት ነገር ጋር አብሮ እንደሚሄድ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው።

አምስት የግንኙነት ደረጃዎች

ብዙዎቹ ግንኙነቶች ላይ ላዩን ከሚደረጉ የቃላት ልውውጦች አልፈው የሚሄዱ አይደሉም። የማድመጥ ግንኙነቶች ግን በጣም ጠለቅ ያለ ነው፤ ጤናማና ታዳጊ የሆነ ግንኙነት ምልክት አንዱ፤ በግንኙነት ውስጥ በሚሳተፉት ሰዎች መካከል ባለ የግንኙነት ትስስር ውስጥ ጥልቀት ያለው ህብረት መኖሩ ነው።

ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከአምስቱ የግንኙነት ደረጃዎች በአንዱ ወይም ከዚያ በበለጡ ደረጃዎች ግንኙነት ያደርጋሱ፤ እያንዳንዱ ደረጃ ደግሞ ከእርሱ በፊት ካለው ደረጃ ይልቅ ጥልቅና የቀረበ ህብረት ያለው ነው። በዝቅተኛው ደረጃ ያለው ቀለል ያለ የቃላት ምልልስ ነው። ጥልቀት የሌለውና ችግር የማይፈጥርም ሲሆን፤ ለምሳሌም በአንድ የሸቀጣሸቀጥ መሸጫ መደብር ውስጥ ተሰልፈን ሳለ ካገኘነው አንድ እንግዳ ሰው ጋር የምናደርገውን ጭውውት አይነት ማለት ነው። "ሰላም፤ እንደምነህ አባክህ፤" "እኔ ደህና ነኝ፤ አንተስ እንዴት ነህ? " "ደህና ነኝ፤" "ልጆች እንዴት ናቸው?፤" "ደህና ናቸው፤" "በዚህ ሳምንት ስላለው የአየሩ ጠባይ ምንትላለህ እባክህ?" ጠለቅ ያሉና ችግር የሚያስከትሉ ጥያቄዎች የሉም፤ ወደ ግል ጉዳይ ዘልቀው ገብተው ሀዘንን የሚፈጥሩ ወይም ትኩረት የምንጥልባቸውን እይታዎች የሚያስከትሉ አይደሉም። ትህትናና አክብሮት የተሞላባቸው ቀጣይነትም የሌላቸው ቀለል ያሉ ጭውውቶች ናቸው። ሁሉም ሀላፊነት የማንወስድባቸው ወደ ቀጣይ ችግርም የማይጎትቱን ናቸው።

ቀጥሎ ያለው ከፍ ያለው የግንኙነት ደረጃ ሌሎችን በሚመለከት ያሉ እውነቶችን አስመልክቶ ዘገባ ማቅረብን ያካተተ ነው። በእንደዚህ አይነቱ ግንኙነት ውስጥ ደስተኞች ሆነን አንድ ሌላ ሰው ስለተናገረው ወይም ስላደረገው ነገር እያነሳን፤ ስለሰውየው ግላዊ ሁኔታ መረጃዎች ሳንሰጥና በነገሮቹ ላይ የግል አስተያየታችንን ሳናክልበት፤ ከሌሎች ለዎች ጋር የምናደርገው የንግግር ልውውጥ ነው። ይህ አይነቱ የግንኙነት ደረጃ ከራስ ስሜትና አስተያየት ነፃ እንደሆነ ጋዜጠኛ፤ ድርጊቶች የተከናወኑበትን እውነታና ብዙ ጊዜ ሌላ ሰው የተናገረውን የሚያካትት ዘገባ አይነት ነው። ግንኙነቱ ግላዊ የሆኑ ጉዳዮችን አይጨምርም።

ሦስተኛው እውነተኛ የሆነ የግንኙነት ደረጃ ሲሆን በመጀመሪያውም ግንኙነቱ የሚፈጠረው፤ ሃሳባችንን፤ አስተያየታችን ወይም ውሳኔያችንን በመግለጥ በሌሎች ለዎች ዘንድ ለመደመጥና ሀሣባችንን እንዲረዱ እቅደን በመጀመራችን ምክንያት ነው። ግልጽነትን የሚጠይቅ ግንኙነት በመሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ግለሰባዊ በሆነ ሀላፊነት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ይከተናል። ማንኛውም የውስጣችንን ክፍሎች ማለትም ሀሣባችንን፣ እምነታችንን፣ አመለካከታችንን በገለጥን ጊዜ ሁሉ ሊከሰት ለሚችል ተቃውሞ ወይም ፌዝ በር እንከፍታለን። በዚህ ስፍራ የግንኙነቱ ቅርበት ያደገ ነው፤ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ለጥቃት አጋልጦ በሚሰጥ ደረጃ አይደለም። በዚህ ደረጃ ባለ ግንኙነት ውስጥ ግለሰባዊ እምነታችንና አመላካከታችን፤ እንደ ፍልቅ ስሜታችንና ውስጣዊ ማንነታችን አደጋ ለሚያስከትል ጥቃት የተጋለጡ አይደሉም። በዚሁ የግንኙነት ደረጃ ላይ ፍልቅ ስሜታችንና ውስጣዊ ማንነታችንም ቢሆኑ ሙሉ ለሙሉ ለከፋ ችግር የተጋለጡ አይሆኑም።

በአራተኛው የግንኙነት ደረጃ ፍልቅ ስሜታችንን ገልጸን ለሌሎች ማካፈል ለመጀመር የመተማመንና ግንኙነት ከምናደርገው ሰው ጋር የመቀራረብ ስሜት ይሰማናል። ምንም እንኳን በዚህ ደረጃ የሚከናወነው ግንኙነት የተለቀቀና ከፍተኛ ቁምነገር ያዘለ ቢሆንም፤ ቁጥብነት የሚታይበት ግንኙነት ነው። በዚህ ደረጃ ሙሉ ለሙሉ ራሳችንን ለመግለጥና ለሌላው ሰው እውነተኛውን እኛ ነታችንን በጥልቀትና ወደ ውስጥ ዘልቆ እንዲያይ ገና ዝግጁዎች አይደለንም።

የመጨረሻው ደረጃ፤ ፍጹማዊ በሆነ ግልጽነት ሀቀኝነት የሚገለጠው ሙሉ የሆነ የፍልቅ ስሜትና የግለሰባዊ ማንነት ግንኙ

ነት ነው። በዚህ ደረጃ ድብቅ የሆኑ ሚስጥሮች ወይም ከገደብ አልፈዋል የሚባሉ ነገሮች የሉም። ልባችንን ሙሉ ለሙሉ ለመግለጥና የቀረበ ፍተሻ ይካሄድባቸው ዘንድ እያንዳንዱን የልባችንን ክፍሎችና ጓዳዎች ሁሉ ለመክፈት ዝግጁዎችና ፈቃደኞች እንሆናለን። ሁለት ለዎች እርስ በእርሳቸው ሙሉ ለሙሉ ሀቀኞች ሆነው ለመነጋገር ነፃነትና መተማመን ከሚለማቸው የተሻለ የላቀና የጠለቀ የቅርብ ግንኙነት የለም። በዚህ ጊዜ ውስጥ ነው ተቀባይነት ያለማግኘትና ማፌዣ የመሆን አደጋ በከፍተኛ ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉት። እውነተኛ የቀረበ ግንኙነት ባለበት ሁኔታ ሁሉ አደጋ ልናስቀረው የምንችለው ነገር አይደለም። የቀረበ ግንኙነት ከሚገለጥባቸው ሁኔታዎች አንዱ፣ ውስጣዊ ማንነትን ለሌላው ለው ሙሉ ለሙሉ ለማጋለጥ ፍቃደኛ መሆንና የመተማመን ስሜት ነው። ራስን ገልጦ ማሳየት ምን ጊዜም አደጋ አለው፣ ይህን እንጂ ጥልቅ ወደ ሆነው በዚህ ደረጃ ወዳለው እውነተኛ የቀረበ ግንኙነት ለመድረስ ሌላ ምንም አማራጭ መንገድ የለም።



እውነተኛና የቀረበ ግንኙነት ባለበት ሁኔታ ሁሉ ስደጋ ልናስቀረው የምንችለው ነገር ስይደለም።

በጋብቻ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ስኬትና ውጤታማነት በከፍተኛ ሁኔታ የሚወሰነው፣ ባልና ሚስት የግንኙነት ጥበብ ባዳበሩበት ስፋትና ጥልቀት ልክ ነው። እንዴት ማድመጥና እርስ በእርስ መግባባት እንደሚገባቸው፣ እንዲሁም ጥልቅና ውስጣዊ የሆኑ ሀሣቦቻቸውን፣ ስሜቶቻቸውን፣ ደስታዎቻቸውን፣ ሀዘኖቻቸውን፣ ተስፋዎቻቸውን፣ ራእዬቻቸውን ለመካፈል ደስተኛ መሆንን መማር እጅግ ጠቃሚያቸው ነው። ጋብቻ በእያንዳንዱ ቅያስ ላይ አስገራሚ ነገሮችና ተግዳሮቶች የሞሉበት የህይወት ዘመን አስደናቂ ጉዞ ነው። ውጤታማ ግንኙነት መፍጠር የመማር ሂደትም እንዲሁ የህይወት ዘመንን ሙሉ ጉዞ የሚጠይቅ ነው። ፈጣንም ቀላልም ያልሆነ ነገር ግን ጠንካራ ሥራን በሚጠይቁ ወርቃማ አመታት ውስጥ የቀረበ ግንኙነትንና ውጤታማነትን ያቀዳጃል።

መርሆዎች

1. እውነተኛ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችለው ለግንኙነቱ መከለት አመቺ ሁኔታን የሚፈጥረው ሀቀኛ የሆነ ራስን የመግለጥ ሁኔታ ሲኖር ነው።

2. እውነተኛ የሆነ ግንኙነት መነጋገርን እንዲሁም መግባባትን ይጠይቃል።

3. ግንኙነት ማድረግ ማለት፤ በአግባቡ ተቀባይ እንዲያገኙ ወይም ግንዛቤን እንዲፈጥሩ፤ መረጃዎችን፣ ሀሣብን ወይም ስሜትን ማስተላለፍ ማለት ነው።

4. ለግንኙነት ቁልፍ የሆነው ጉዳይ አንድን ነገር መረዳት ሲሆን፣ ለመረዳት ቁልፍ የሆነው ጉዳይ ደግሞ ማድመጥ ነው።

5. ጥሩ የሆነ የማድመጥ ችሎታ ሌሎች ለዎች ምን እንደሚናገሩ ከምናጣራበት ወንፊት የላቀ ነገርን ይጠይቃል፤ ይህም ቃላቸውን ብቻ ሳይሆን የድምጻቸውን ቅላጼ፣ የፊት ገጽታ ገለጻቸውንና የአካላቸውን ቋንቋ ሁሉ ማድመጥን ግድ ይላል።

6. ውጤታማ የሆነ የፊት ለፊት ግንኙነት በባህሪው ሁሉን አቀፍ የሆነ የሁሉንም ስሜቶችና የአካልን፣ የእውቀትን እንዲሁም የአይምሮን ሀይል ሁለንተናዊ ተሣትፎ የሚያካትት ነው።

7. ከምንናገረው ነገር አንድ ለው ሊገነዘበንና ሊረዳን የሚችለው 7 መቶ ያህል፤ የልነውን ነገር እንዴት እንደተናገርነው አስመልክቶ 38 በመቶ ያህል ሲሆን፣ 55 በመቶ የሆነው ደግሞ ያንን ነገር ስንናገር እየሠራን ያለው ነገር ላይ ተመስርቶ ነው።

8. የጤናማና ታዳጊ የሆነ ግንኙነት አንዱ ምልክት፤ በግንኙነት ውስጥ የሚሳተፉ ለዎች ግንኙነታቸው ጥልቀት ያለውን የቀረበ ትስስር ማካተቱ ነው።

9. የቀረበ ግንኙነትን ከምንገልጽበት አንደኛው መንገድ ውስጣዊ ማንነትን ሙሉ በሙሉ ለመግለጥና ራስን ገልጦ ለማሣየት ያለ ፈቃደኝነትና መተማመን ነው።

ምዕራፍ ስድስት

ጥቃቅን ነገሮችን ስትርሱ

የጋብቻ ሃላፊነት፤ ለትዳር አላማ ሙሉ ለሙሉ መሰጠት እና ግንኙነትን የመሳለሉ አጠቃላይ ጽንሰ ሀሳቦችን መገንዘብና ተግባራዊ ማድረግ ደስተኛና ውጤታማ ጋብቻ እንዲኖር ቁልፍ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ከነዚሁ ጽንሰ ሀሳቦች እኩል ከፍተኛ ስኬት ለማግኘት ወሳኝ የሆነ ጉዳይ አለ፤ ይሄውም ጥቃቅን ነገሮች ለምንላቸው ትኩረት መስጠት ነው። እነዚህ ጥቃቅን፤ በሂደት ላይ ያሉና ዕለታዊ ተግባራት፤ ግንኙነትን የሚያሻሽሉና ጣፋጭ ጣእም የሚጨምሩ ናቸው። አነስተኛ ነገሮች በመሆናቸው ምክንያት፤ ብዙ ትኩረት ልንለጣቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ልባችንን በማሳረፋችን እነዚህን ጥቃቅን ነገሮች ቸል ልንላቸው እንችላለን።

በሌሎች ተግባራን በምንሠራባቸው ጉዳዮች ላይ እንደምናደርገው ሁሉ በጋብቻም ውስጥ ሁለንተናዊ ለሆነ ስኬት ጥቃቅን ነገሮች ያላቸውን ጠቃሚነት ቸል ብለን ዋጋ ልንከፍል አያስፈልግም። ታላቁ የቻይና ግንብ የተገነባው አንድ ጡብ በአንድ ጊዜ በማስቀመጥ ነው። በግብጽ ውስጥ በጊዛ አምባ ላይ የሚገኘው ትልቁ ፒራሚድ ቁመቱ እየጨመረ የሄደው አንድን ድንጋይ በአንድ ድንጋይ ላይ በመከመር ነው። ዝርዝር የሆኑ ጥቃቅን ነገሮችን ቸል ማለት ጠንከር ያሉ ቀጣይ ችግሮችን ያስከትላሉ። የ17ኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዛዊ ባለቅኔ ጆርጅ ሀርበርት እንዲህ ሲል ጽፏል።

ሚስማር ባለመግኘቱ፤ የፈረስ ኩቴ ጫማ ጠፋ
የፈረስ ኩቴ ጫማ ባለመግኘቱ፤ ፈረስ ጠፋ
ፈረስ ባለመግኘቱ፤ ጋላቢው ጠፋ
ጋላቢው ባለመግኘቱ፤ መልዕክት የሚያመጣ ጠፋ
መልዕክተኛ ባለመግኘቱ፤ በጦርነቱ ተሸነፍን
በጦርነት በመሸነፋችን፤ አገር ራሱ ጠፋ
ይህ ሁሉ በሚስማር እጦት!

በብሉይ ኪዳን፤ መሀልየ መሀልይ መጽሐፍ፤ ንጉስ ስሎሞን "የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ቀበሮዎች" (መኃ 2፤15) ሲል ይናገራል።

ብዙ ትዳሮች ወደ ችግር የሚገቡት ባለትዳሮች ትናንሽ የተባሉ ዝርዝር ጉዳዮችንና እለት እለት ሊታለፁባቸው የሚገቡ ነገሮችን ቸል በማለታቸው ምክንያት ነው። እነዚህ ቸል የተባሉ ዕለታዊ ጉዳዮች አንድም ግንኙነታቸውን ሲያጠናክሩ የሚችሉ አለዚያም እርካታና መፍትሄ ያላገኙባቸው "ጥቃቅን" ቀበሮዎቻቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ናቸው እንግዲህ የደስታቸውን የወይን አትክልት ስፍራ ቅርጥፍ አርገው የሚበሉት። የተጋቡ ባለትዳሮች ዘለቄታ ያለው ስኬት፣ ጤነኛና ጠንካራ የሆነ ትዳር እንዲኖራቸው አስተማማኝ የሚሆነው፤ ከፍተኛ ለተባሉትም ሆነ ጥቃቅን ለተሰኙት ለሁለቱም አይነት ጉዳዮች ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ሲወስዱ ነው።

ገጽጽ ነገር ግን ትችት ስትሰንዝር

ቸል ብለን ለጥፋት በር ከምንከፍትላቸው ጥቃቅን ቀበሮዎች መካከል እጅግ አደገኛ ከሆኑት አንዱ ትችት መሰንዘር ነው። ጋጠወጥ፤ የሚሰብሩና የሚያንቋሽሹ አስተያየቶችን ያህል ፈጥነው የግንኙነትን በር የሚዘጉና በግንኙነት ውስጥ ያለውን ህብር የሚያበላሹ ነገሮች የሉም። ከትችት የሚጠቀም ማንም የለም። የሚተቸው ሰው ወይም ትችት የሚቀርብበት እንዲሁም ትችቱን መስማት በሚችልበት ርቀት ውስጥ ያለ ማንም ሰው ቢሆን ከዚህ ተጠቃሚ አይሆንም። የማያባራ ትችት የሰውን መንፈስ ያወድማል። ነቀፌታ፤ ስብራትን ፤ መራራነትን፣ ሞገደኝነትንና ጥላቻንም እንኳን ያፈራል። ነቀፌታ ግልጽነትንና ሀቀኝነትን አያበረታታም፤ ያለ እነዚህ ነገሮች ደግሞ ማንኛውም ግንኙነት ጤናማ ሊሆን አይችልም። ነቀፌታ በባህሪው ራሱ አውዳሚ ነው፤ ምክንያቱም መፍትሄ ፈላጊ ከመሆን ይልቅ ችግሮችን አነፍንፎ በመፈለግ ጉዳት ለማስከተል ታስቦ የሚደረግ በመሆኑ ነው። አዘውትረው ትችቶችን የሚሰነዝሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ህይወት ምላሽ ያላገኘ ፍላጎት ወይም መፍትሄ ያላገኘ ጉዳይ ያላቸው ሲሆኑ፤ እነዚህ ችግሮችም በነቀፌታ መንፈስ ራሳቸውን ይገልጣሉ።



ጋጠወጥ፣ የሚሰብረና የሚያንቋሽሹ አስተያየቶችን ያህል ፈጥነው የግንኙነትን በር የሚዘጉና በግንኙነት ውስጥ ያሉትን ህብር የሚያበላሹ ነገሮች የሉም።

ማንኛውም ግንኙነት ቢሆን በሆነ ጊዜ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠር ግጭት ሳያጋጥመው አያልፍም፤ እነዚህ ግጭቶች በግንኙነቱ ውስጥ ለተሳተፉት ሰዎች የጋለ ጠቀሜታ ሲባል

በአግባቡ መፍትሄ ሊያገኙ የሚገባቸው ናቸው። ውጤታማ የሆነ ግንኙነት አንዱ ገጽታ ችግሮች በሚከሰቱ ጊዜ ጤናማ በሆነ መልኩ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። ጎጂ የሆነ ነቀፌታ በጭራሽ መልስ ሊሆን አይችልም። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ደግሞ ለተቃውሞ በር ከፋች ነው።

ነቀፌታና ግሳጼ አንድ አይነት ነገሮች አይደሉም። በሁለት ጠቃሚ መንገዶች ግሳጼ ከነቀፌታ የተለየ ነው። አንደኛው የሚመነጭበት መንፈስ ሲሆን ሌላኛው የሚቀርብበት አላማ ነው። ነቀፌታ ከቆሰለና ራስን ካማከለ መንፈስ መልሶ ለማቁሰል የሚሰነዘር ነው። ነቀፌታ ስለተሰነዘረበት ሰው ሁለንተናዊ ደህንነት ወይም ለተፈጠረው ችግር ገንቢ የሆነ መፍትሄ የመፈለግ ፍላጎት የለውም። በሌላ አንጻር ግሳጼን የተመለከትን እንደሆን ፍቅርና ርህራሄ ከተሞላበት መንፈስ የሚመነጭ ነው። በተጨማሪም ችግር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ክልብ በመነጨ ለሌላው ሰው ደህንነት በሚጠቅም መልኩ ለችግሮች አግባብነት ያላቸውና ተመጣጣኝ መፍትሔ ይፈልጋል። በአጭሩ ግሳጼ ከፍቅር የሚነሣ ሲሆን ነቀፌታ ግን እንዲህ ያለ ባህሪ የለውም። ግሳጼ የሚያተኩረው መፍትሄ ላይ ሲሆን ነቀፌታ ግን የሚያናፍሰው ችግርን ነው። ግንኙነታችሁን ቀስ በቀስ የሚቦጠቡጥን ጥቃቅን ቀበሮዎች ልብ ብላችሁ አስተውሉ። ከመናገር በፊት የማስብን ሥነስርዓት አዳብሩ። መቼም መች ይሁን ችግሮች ሲነሱ ወይ ግጭቶች ሲፈነዱ ነቀፌታ ለመሰንዘር ባስብክ ጊዜ ቆም ብለህ ራስህን ጠይቅ፤ ግሳጼና የእርምት እርምጃ የሚያስፈልገው አግባብነት ያለው የጎደ ችግር ወይስ ቀላል ግለሰባዊ ችግር ብቻ ነው? ልትነቅፍ ያልክበትን ለበበ ነገር አጢነው፤ ከፍቅር ወይስ ከቁጣ የመነጨ ነው።

ነቀፌታ አንዳች ትርፍ የለውም፤ ግሳጼና የእርምት እርምጃዎች ግን አላቸው። ይሁን እንጂ ለዚህም እንደ ሳንቲም ሁለት ገጽታ አለው። አንደኛው ገጽታ እርምትን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ሲሆን ሌላኛው ገጽታ ደግሞ እርምትን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ነው። እርምትን ለመቀበል ክፍት መሆን ለእድገት ዋነኛ የሆነ አላባ ነው። እርምትን ሲቀበሉ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች መቼም ቢሆን አያድጉም። ሁል ጊዜም ያልበሰሉ ሆነው ይኖራሉ።



እርምትን ለመቀበል ክፍት መሆን ለእድገት ዋነኛ የሆነ አለባ ነው።

እጅግም ስትሳመዱ

ሌላው አተኩረን ልንመለከተው የተገባ "ጥቃቅን ቀበሮ" የመላመድ ቀበሮ ነው። በባልና ሚስት መካከል አደገኛ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ እርስ በእርሳቸው እጅግ የመላመድ ጉዳይ ነው። ይህ እርስ በእርስ ከመተዋወቅ ጋር አንድ አይደለም። ባለትዳሮች በምድር ላይ ከሚያውቋቸው ሰዎች ሁሉ ይልቅ እርስ በእርሳቸው ይበልጥ ሊታዋወቁና ሊቀራረቡ ይገባቸዋል። ባልና ሚስት አንዳቸው የአንዳቸው የቅርብ ጓደኛ ሊሆኑም ይገባቸዋል። መላመድ ስል ባልና ሚስት አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ባላቸው የንግግር ልውውጥ ዘና ያለ በቀላሉ እርካታን የሚያገኙበት መተማመን ሲፈጥፉ ነው። መላመድ ቢያንስ በሦስት ሁኔታዎች ራሱን ይገልጻል። በመጀመሪያ የሚያፈራው ቸል መባባልን ነው። ባልና ሚስት እጅግ ከመላመዳቸው የተነሳ፤ ሊገነዘቡት አንኳን እስከማይችሉ ድረስ በብዙ ጥቃቅን ጉዳዮች እርስ በእርሳቸው ቸል ሊባባሉ ይጀምራሉ። በሁለተኛ ደረጃ መላመድ የሚያፈራው ግምታዊነትን ነው። ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው አንዱ ሌላው ምን እንደሚያስብ እንደሚያውቁ መገመት ይጀምራሉ። ባልየው እርሱ ምን እንደሚያስብ ሚስቱ እንደምታውቅ ብቻ ሳይሆን እርሷ ምን እንደምታስብ እንደሚያውቅ ይገምታል። ሚስቲቱም ይህንኑ ግምት ትገምታለች። በሦስተኛ ደረጃ መላመድ የሚያፈራው ግምታዊ ድምዳሜን ነው። ሚስት ባሏ ምንም ይናገር ምንም ይሥራ ገና ሳትጠይቀው እንኳን "እንዲህ ማለቱ" ወይም "እንዲህ ማድረጉ" ይሆናል የሚል ቅድመ ጽምዳሜ ያለው አቋም ትወስዳለች። ባልም ሚስቱን በሚመለከት ተመሳሳይ ስህተት ሲሠራ ይችላል። እነኝህ ሦስት ገጽታዎች ቀጣይነት ባለው መልክ የሚከሰቱ ከሆነ፤ የመጨረሻው ውጤት በመጽሐፍ ምሳሌ እንደተገለጸው "መላመድ መናናቅን ይወልዳል"።

ይህ እንዲት እንደሚከሰት ተግባራዊ የሆነ ምሳሌ ወስደን እንመልከት። ከጋብቻቸው በፊት በሚገናኙ ጊዜ ያለማቋረጥ አንዳቸው ስለሌላቸው የሚለማቸውን ይነጋገራሉ። ምንም ነገር አይገምቱም፤ ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ነገር፤ መጠነኛ ለሆነ የድምጽ ለውጥ፤ ለአካል እንቅስቃሴና የፊት ገጽታ ገለጻ ትኩረት ይሰጣሉ። አንዳቸው ስለ አንዳቸው በጭራሽ ግምታዊ ነገር አይኖራቸውም። ለሦስት ለዓታት ያህል በቴሌፎን እርስ በእርሳቸው ጣፋጭ የሆኑ ቃላት ይለዋወጣሉ፤ በአካል ሳይገናኙ አንድ ሰዓት ጊዜ እንኳን መቆየት አይችሉም፤ ለሁለት ለዓታት ወይም ለበለጠ ጊዜ በአንድ

ጉዳይ ላይ ይጨዋወታሉ። እንዳቸው ስለእንዳቸው ያላቸውን አስተያየት ይሰጣሉ፣ ስጦታን ይለዋወጣሉ፣ ማንኛውንም አመቺ የሆነች ቅጽበት አብረው ያሳልፋሉ።

እንዲህ ያለው እንዳቸው ለሌላቸው የሚሰጡት ያላሰለሰ ትኩረት መልካም የሆነና ጠንካራ ግንኙነት ለመመስረት እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በእያንዳንዳቸው ውስጥ ጥልቅ የሆነ የመረጋጋትን ስሜት ይፈጥራል። እንዳቸው በእንዳቸው ፍቅር ይረጋጋሉ፣ ተራርቀው ባሉበት ሁኔታ ውስጥ እንኳን እነርሱን የሚያፈቅርና የሚጠነቀቅላቸው አንድ ሰው እንዳለ በማወቃቸው ፍቅሩ ይሞቃቸዋል። እንደተወደድን ደጋግሞ በተነገረን ቁጥር መረጋጋታችን እየጨመረ ይሄዳል።

ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በሆነ ምክንያት ነገሮች መለወጥ ይጀምራሉ። ብዙ ጊዜ እንደሚሆነው ይህ ፈጥኖ የሚያጋጥም ነገር አይደለም። በዝግታ ባልና ሚስቱ እንዳቸው ስለሌላቸው ነገሮችን መገመት ይጀምራሉ። ባል ሚስቱን ሌላ ግዜ አዘውትሮ እንደሚያደርገው "እወድሻለሁ" ማለቱን ያቆማል። "እንደምወዳት ታውቃለች ሁልጊዜ ይህን ደጋግሜ ማለት የለብኝም" ሲል ያስባል። ምን አልባትም ይህ ሀሳብ ሆን ብሎ እስተውሎ ያሰበው ሀሳብ ላይሆን ይችላል። አብረው ወደራት ግብግ ወይም ወደሌሎች ቀጠሮዎች መሄዳቸውን ያቆማሉ። "ስለምወድህ . . . " እያሉ ይለዋወጧቸው የነበሩ ስጦታዎችን፣ ካርዶችንና አበባዎችን መለዋወጥ ያቆማሉ። በመካከላቸው ዘና ያለና የተደላደለ ሁኔታ ይፈጠራል፤ ይህ መደላደል ነው እንግዲህ መላመድን የሚወልደው፤ በመላመዳቸውም ሳያስተውሉት በዝግታ እንዳቸው ከእንዳቸው ይወሰዱና መራራቅ ይጀምራሉ።

ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው ከተገቢው በላይ የሚላመዱ ከሆነ ብዙ እንግዳና አስደናቂ የሆኑ ልምምዶቻቸው ከትዳራቸው ተጠርገው ይወሰዳሉ። እርግጥ ነው ትዳር የተረጋጋና ጠንካራ ይሆን ዘንድ፤ ሁለቱም ባለትዳሮች በትዳራቸው ውስጥ የተረጋጋ ስሜት እንዲለማቸው ያስፈልጋል፤ ይሁን እንጂ በዚህ ሁኔታቸው ውስጥ ሁልጊዜም አዲስና አስደናቂ ለሆነ ነገር ክፍተት ሊኖር ይገባል። ትዳርን ሕይወት ያለው፣ ጠንካራና አስደሳች ሆኖ እንዲቀጥል ከሚረዱት እጅግ ጠቃሚ ነገሮች አንዱ፤ አልፎ አልፎ ያልተለመዱ እንግዳ ድርጊቶች ለማድረግ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንዲህ አይነቱ ድርጊት ተለቅ ያለ ማለትም ሁለቱ ብቻ የሳምንቱን

መጨረሻ ቀኖች ወጣ ብለው የሚያሣልፉበት፤ ወይም በምሽት ሻማ አብርቶ እራት መብላት፣ የእበባ እቅፍ ገጸበረከት መለዋወጥን የመሰሉ ትንሽና ቀለል ያሉ ድርጊቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እዚህ ጋ ቁልፍ የሆነው ጉዳይ መላመድንና በዚህም ሳቢያ የሚከተለውን ተለምዷዊ የሆነውን ግምት ማስወገድ ነው። ይህ ማለት ደግሞ ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ እንዳቸው ለእንዳቸው ባላሰለሰ ሁኔታ አድናቆትን የመስጠት ልምድን ማዳበር ነው።



ባልና ሚስት እርስ በእርሳቸው ከተገቢው በላይ የሚላመዱ ከሆነ ብዙ እንግዳና አስደናቂ የሆኑ ልምምዶቻቸው ከተዳፈቸው ተጠርገው ይወሰዳሉ።

እውነተኛ የሆነ አድናቆትን መግለጥ

ሰዎችን ማድነቅን መማር ግልጽ ለሆነ ግንኙነት ውጤታማ ሁኔታን ለማመቻቸት እንደኛው መንገድ ሊሆን በተጨማሪም ጤናማ የሆነ ግንኙነትን ለመገንባት ልክ እንደ ጠቃሚ ምግብ አስፈላጊ ነው። አድናቆት መስጠት ሌሎች ለእኛ ያደረጉትን ነገር ከግምት ውስጥ ማስገባትን፣ የተደረገልንን ነገር ከግምት ውስጥ ማስገባታችንን እንዲያውቁት ማድረግንና ለተደረገልን ነገር ማመስገንን የሚያካትት ነው። እንደገናም ደግሞ አድናቆትን መስጠት ማለት ለሰች ለእኛ ያደረጉት አንድ ነገር ስኬታማ በመሆኑ ላደረጉልን ሰዎች ልባዊና ከደስታ በመነጨ ስሜት ምስጋናን ማቅረብ ማለት ነው። እንዳንድ ጊዜ ሰዎች ባገኙት ውጤት ወይም ትኩረትን በማግኘታቸው ነቀፌታን መሰንዘርና መቅናት እጅግ በጣም ቀላል ነው። ብዙዎቻችን ለሰችን ማድነቅን ለመማር ብዙ መስራት ይጠበቅብናል ምክንያቱም አድናቆት መስጠት ራስ ወዳድ ከሆነው ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ በተቃራኒ ነው።

እውነተኛ የሆነ አድናቆትን መግለጽ ለእኛ ጠቃሚ ከሚሆንበት ምክንያት አንዱ፤ እንዳችን ለእንዳችን እጅግ አስፈላጊ ለሰች መሆናችንን ግንዛቤ ውስጥ እንድናስገባ መርዳቱ ነው። ማናችንም ብንሆን በራሳችን ብቻ ስኬትን ወይንም ደስተኛነትን መቼም ቢሆን ማምጣት አንችልም። ባለፍንበት የህይወት ጎዳና ሁሉ በመንገዳችን የረዱን ሰዎች አሉ፤ ብዙ ጊዜ ደግሞ አስተዋጽአዋቸውን እንዘነጋለን ወይም ቸል ብለን እናልፈዋለን። ይህ እጅጉን እውነት የሚሆንበት ከትዳር የበለጠ ስፍራ የለም። በለውኛ ቋንቋ ለባል የስኬቱና የደስተኛነቱ ታላቅ መዋዕለንዋይ ሚስቱ ናት፤

ለሚስትም እንዲሁ ባሏ ነው። አንዳቸው የአንዳቸው ታላቅ ረዳት፣ የእድገት መሰላልና እጽናኝ ሊሆኑ ያስፈልጋቸዋል። በሌሎች የህይወት ገዳዮች ውስጥ ምንም ይከሰት ምን የባለትዳሮች ቤት ሁል ጊዜም ያልተቋረጠ ፍቅር፣ አድናቆትንና በጎነትን የሚያገኙበት ስፍራ ሊሆን ይገባዋል።

ነገሮች ቀናና መልካም በሆኑበት ጊዜ፣ ፍቅራቸውንና አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን አድናቆት ያለማሳለስ መግለጽን በመለማመዳቸው ምክንያት መረጋጋት የሚሰማቸው ባልና ሚስት፣ ይህ ጥልቀት ያለው የሁለንተናዊ ደህንነት ስሜት አለቸጋሪ የሆኑ ጊዜዎች ባጋጠሟቸው ሁኔታዎች ውስጥ አጽንቶ ሊያቆማቸው ያገኙታል። በሌሎች መወደዳችንንና መደነቃችንን ካወቅን፣ በህይወት ከፍታና ዝቅታዎቻችን ያሉ ሌሎች አቅጣጫዎችን ሁሉ እንዲሁ እንድንመለከታቸው ይረዱናል። እኔ ሁሉም ነገሮች በትክክል ሊሄዱ ያልቻሉባቸውን ቀናቶች አስታውሳቸዋለሁ። በቢሮ ውስጥ ምንም ነገር በአግባቡ ሊሠራ አልቻለም፣ አንዳንድ ለምች የለጠናቸውን ቀጠሮዎች ያፈርሳሉ፣ ሌሎች ደግሞ (እናደርጋለን ያሉትን ነገር ባለማድረጋቸው ከነርሱ ጋር መቀጠል አልቻልኝም። በዶና፡ ገዢነብ መካከል የመኪናው ነዳጅ ያልቃል፣ ቀጥሎ ደግሞ ጎማው ይተነፍሳል። እነዚያን በመሰሉ ጊዜያቶች በርትቼ ገደፊት እንድገፋ ያደረገኝ ብቸኛው ነገር፣ በቤቴ ውስጥ የምትወደኝና የምትጠነቀቅልኝ እጅግ ታላቅ የሆነች ሌት - ሚስት እንዳለችኝ ማወቄ ነው።

እውነተኛ የሆነን አድናቆት ያለማቋረጥ መግለጽ ጤነኛ ለሆነ ትዳር ጠቃሚ ነገር በመሆኑ ለፍልቅ ስሜታችን የምንተወው ነገር አይደለም። አንዳንድ ጊዜ አድናቆት ልንሰጥ በምንችልበት ስሜት ውስጥ ላንሆን እንችላለን። ምናልባት ደክሞናል፣ ታመናል ወይም ተቆጥተናል፣ ባልሆንም በዘነ ሀሳብ ውስጥ ተጠምደናል። በፍልቅ ስሜታችን ላይ ሳይሆን በእውቀት ላይ ተመስርተን አድናቆት የመስጠት ልማድ ማዳበር የግድ ያስፈልገናል። ፍልቅ ስሜታችን ምናልባትም፣ ያሂን ነገር እንደምወደው አይሰማኝም ወይም እባክህ አሁን በምንም ነገር አታስቸግረኝ ይል ይሆናል። ይሁን እንጂ እውቀት የሚለው እንዲህ ነው፣ "አሁን መልካም የሆኑ አምንታዊ ቃላት ያስፈልጉታል" ወይም "ሁሉም ነገር ትክክል እንደሆነ እንዳረጋግጥላት ተፈልጋለች"።

በዚህ ረገድ ከሌቶች ይልቅ ችግሩ የሚበረታው በወንዶች ላይ ነው። በሆነ ምክንያት ብዙ ወንዶች ስሜታቸውን ሳያለልሱ በግልጽ ለሚስቶቻቸው መግለጥ ወንዳወንድነት የሌለውና የድክመት ምልክት እንደሆነ ያስባሉ። በተቃራኒው ባል ሚስቱን "የኔ ወለላ እወድሻለሁ" ቢል የወንድነቱን ክብር የሚነካ ነገር የለም። እንዲህ የሚያደርግ ወንድ ጥንካሬውን እንጂ ድክመቱን እየገለጠ አይደለም።

ለወንድ በገዛ ጡንቻው የተማመነ ጽኑእ አለት የሆነ ያህል እየተለማው "እኔ ብርቱ ነኝ፣ እንደዚያ ያለ ነገር መናገር አያስፈልገኝም" ከሚል ይልቅ፣ ራሱን ዝቅ አድርጎ ደካማ የሆነ ጎኑን አጋልጦ መስጠት ብርቱ ጥንካሬን ይጠይቀዋል።

እንደዚያ ማድረግ ጥንካሬን የሚያሳይ አይደለም። እንዲያውም አይምሮ የጎደለው ሰው ተግባር ነው። ምክንያቱም ከእኛ ይልቅ ታላቅና ጠቢብ ሳለ እግዚአብሔር እንኳን እንዲህ አይነቱን ሁኔታ በእኛ ላይ ላሳየም። በየቀኑ በብዙ መንገዶች እግዚአብሔር እንደሚወደን ይናገረናል፣ ያሳየናልም። እርሱ ይህንን ለአጋጣሚ የተወው ነገር አይደለም። እንደሚወደን ደጋግሞ እንዲያረጋግጥልን እንደምንፈልግ ያውቃል። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑና የእርሱ ተከታዮች የሆኑ ከህይወት ልምምዳቸው መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንደሚያረጋግጥላቸው ያውቃሉ።

ባልና ሚስት በእያንዳንዱ ዕለት አንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን ፍቅርና አድናቆት የመግለጽ ልምድ እንዲያዳብሩ ያስፈልጋቸዋል። ከአንድ ጣራ ሥር አብሮ ማደርና አንድ አልጋ መጋራት ለመፋቀር ማስረጃ አይደለም። ይህን ማወቅ ብትፈልጉ ደስተኛ ባልሆነ ትዳር ውስጥ ፍቅርን ተርበው እያንዳንዱን ቀን ከሚገፉ በሽህ ከሚቆጠሩ ወንዶችና ሌቶች መካከል ሄዳችሁ አንዱን ጠይቁት።

ፍቅር የሚመገበው በፍቅር እንጂ ጊዜ በፈጠረው ሁኔታ አይደለም። ሁኔታዎች ምቹ እንደሆኑ ባልተሰማን ጊዜ ውስጥም አንዳችን ለለላችን ያለንን ፍቅርና አድናቆት መግለጽ ልንለምደ ያስፈልገናል። እውነተኛ የሆነ ፍቅርና አድናቆት ደስተኛ ለሆነ ትዳር የደም ስር ናቸው። ተራ የሆኑ ነገሮች አድርጋችሁ አትውሰዷቸው።



ባልና ሚስት በእያንዳንዱ ዕለት እንዳቸው ለሌላቸው ያላቸውን ፍቅርና ለድናቆት የመግለጥን ልምድ እንዲያዳብሩ ያስፈልጋቸዋል።

ፍቅርን በመጠ ምት ስትገምቱት

ፍቅር ያለማቋረጥና ደጋግሞ ሊገለጥ ያስፈልገዋል፤ እንዲያው በመላ እንዳለ የምንገምተው ነገር አይደለም። ባል ሆይ ሚስትህ እንደምትወዳት እንደምታውቅ አድርገህ አትገምት ንገራት! ትላንትና የነገርካት ቢሆንም እንኳን ዛሬም ደግመህ ንገራት። በያንዳንዱ ቀን ልትሰማው ትፈልጋለች። ሚስት ሆይ! ባልሽ እንደምትወጂው እንደሚያውቅ አትገምቺ-ንገሪው! ምንም እንኳን ከእርሱ አፍ እንዲህ አይነት ቃል ስምተሽ ባታውቂም አንቺ ግን እንድታረጋግጭለት ይፈልጋል። ውጭውን ምንም ያህል ጠንካራና ሃያል ቢመስልም አንቺ ራስሽ እንደምትወጂው እንድትነግሪው ይፈልጋል። ሰዎች ስንባል ይህ በየቀኑ እንዲረጋገጥልን እንድንፈልግ የሚያደርግ ተፈጥሯዊ መሻት አለን። ፍቅርን በሚመለከት ስግምት ወይም ለመላምት ስፍራ የለም።

ይህንን እስመልቶ እንደሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ኢየሱስ አስደናቂ ምሳሌ ይሰጠናል። ኤፌ 5፥21-23 ባልና ሚስት ኢየሱስና ሙሽራው የሆነችው ቤተክርስቲያን በተያያዘበት መንገድ አርአያ በሕርሳቸው ሊያያዙ እንደሚገባቸው ያስተምረናል። ቁጥር 25 "ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳትና ስለርሷም ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ" ይላል። ይህ በመስቀል ላይ እንደሞተ የሚያመለክት ነው። በዮሐ 15፥13 ኢየሱስ ሰተክታዩቹ፤ "ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ፣ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ስግንም የለውም" ሲል ይነግራቸዋል። የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለእኛ መሞት በታሪክ ውስጥ ታላቁ የፍቅር መገለጫ ነው። ይህ ቢሆንም እንኳን ኢየሱስ ምሳሌ የሆነው ይህ የመስቀል ሞቱ ብቻውን ሁልጊዜም እንደሚወደን እርግጠኞች እንደ ሆንን ግምታዊ የሆነ ግንዛቤ አልወሰዱም። ይልቁንም በእየእለቱ እንዲያረጋግጥልን እንደምንፈልግ ያውቃል። ከአረገበ በኋላ መንፈስ ቅዱስን በመላክ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ እንዲኖር ካደረገባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው።

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንደተዘገበ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን አማካሪ ወይም አጽናኝ ሲል ይገልጸዋል። (ዮሐ

14፥16፤ 15፥26፤ 16፥7 ይመልከቱ)። የግሪኩ ቃል "ፓራቅሊጦስ" የሚል ሲሆን ይህ በቀጥታ ትርጉም "በቅርበት ሆኖ አብሮ መጓዝ" ማለት ነው። የአጽናኙ አንደኛው ጠቃሚ ሚና በየዕለቱ የክርስቶስን ፍቅር በመግለጽ ማጽናናት ወይም አርግጠኞች አንድንሆን ማድረግ ነው። ጳውሎስ ሰሮሜ ሰዎች በጻፈላቸው መልዕክቱ፤ "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ ኢያሰፍርም" (ሮሜ 5፥5) ሲል ይህንን ማመልከቱ ነው። ክርስቶስን ላመኑና ስሚከተሉት መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ውስጥ ለዘለቄታው በመቀመጥ ያለማቋረጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ሲያሳስባቸው ይኖራል። ኢየሱስ ያለማቋረጥ ፍቅሩን የሚያሳስበን አጽናኝ ሰጥቶናል። እንደምንወደው እንደምናውቅ ፊጽሞ ገምቶ አያውቅም።

እንደዚሁ ሁሉ እኛም ደግሞ ሚስቶቻችን እንደምንወዳቸው እንደሚያውቁ ልንገምት አይገባንም። እርግጥ ነው ፍቅር የዘላለም ከሆነ ምንጭ የሚቀዳ ነው፤ ይሁን እንጂ የእኛ ፍቅርን መግለጽ በእየለቱ እንዲታደስ ያደርገዋል። ለምንወዳቸው ልነግራቸው ከምንወዳቸውም ልንሰማው ያስፈልገናል። ከእለታት በአንዱ ቀን አንድ ጊዜና አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም። እስኪ አንድ ምሳሌ እንመልከት።

አንድ ባል ለሚስቱ ያለውን ፍቅር ሲገልጽላት ፈልጎ ምርጥ የሆነች አዲስ መኪና ገዛላት እንበል። እጅግ ከመደሰቷ የተነሳ በነገሩ ሀሴት አረገች። እናም ባል መኪናዋን መስጠት በመቻሉ ተደሰተ። ከጥቂት ቀናት በኋላ፤ "ወለላየ ሆይ፤ ትወደኛለህ?" ስትል ጠየቀችው። በጥያቄዋ በመጠኑ አየተደነቀ "ያችን መኪና እኮ ገዝቼልሻለሁ እልገዘሁልሽም?" ሲል መለሰላት። ከብዙ ወራት በኋላ እንደገና፤ "ወለላዬ ሆይ፤ ትወደኛለህ?" ስትል ጠየቀችው። "ያችን መኪና እኮ ገዝቼልሻለሁ! አልገዛሁልሽም?" ሲል እንደገና መለሰላት።

አንድ አመት አለፈ፤ ደግሞ ሌላ አመት፤ እንደናም ሌላ እናም ሁልጊዜ ተደጋግሞ የሚነገረው ይህ ሆነ። በመጨረሻ ከ15 ዓመታት በኋላ፤ "ወለላየ ሆይ፤ ትወደኛለህ?" ስትል ሚስት ጠየቀች "ያችን መኪና እኮ ገዝቼልሻለሁ! አልገዛሁልሽም እንዴ?።



እርግጥ ነው ፍቅር የዘላለም ከሆነ ምንጭ ነው የሚቀዳው፤ ዱሩን እንጂ የስኛ ፍቅርን መግለጽ በየዕለቱ እንዲታደስ ያደርገዋል።

ይህ እጅግ እንግዳ የሆነ ነገር አይመስልም? ይሁን እንጂ ብዙ ትዳሮችን በሚመለከት ከእውነት የራቀ ጉዳይ አይደለም። አንዳንድ ለምች ከትዳር ጓደኞቻቸው የቃልም ይሁን የሌላ አንዳችም የተጨበጠ የፍቅር መግለጫ ሳይቀበሉ ሳምንታት ወራትና አመታትም እንኳን ያልፋሉ። ለአይምሯችን፤ ትላንት ፍቅር የተገለጸበት ተግባር የግድ ፍቅርን ወደ ዛሬ ያሸጋግራል ማለት አይደለም። ሁላችንም የየዕለቱ ማረጋገጫ ያስፈልገናል።

ምንም እንኳ ከሌላ ለምች ጋር በሚኖረን ግንኙነት በቃል የምንገልጸው ነገር 7 በመቶ ብቻ ድርሻ ያለው ቢሆንም፤ በተለይ ሴቶችን አስመልክቶ ፍቅርን ለመንከባከብና ለመመገብ አሁንም እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው። ወንዶች በሚያዩት ነገር ውስጥ ያድጋሉ፤ ሴቶች በሚሰሙት ነገር ውስጥ ያድጋሉ፤ ሁለቱም ደግሞ በሚለማቸው ስሜት ውስጥ ያድጋሉ። ቃላት ድርጊትን ያጠናክራሉ፤ ሴቶችም ከባሎቻቸው የፍቅርን የርህራሄንና የአድናቆትን ቃል መስማት ይፈልጋሉ።

ብዙ ወንዶች ከሚስቶቻቸው ጋር ለመጫዋወት ጊዜ አያጠፉም። ባለፉት አመታት በዚሁ ምክንያት በፍች አፋፍ ላይ የደረሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ባለትዳሮችን አማክሬያለሁ።

በዚሁ ጉዳይ ላይ ከባሎች ጋር ባደረኳቸው ውይይቶች ሁሉ ከዚህ በታች የጠቀስኩትን የቃለ ምልልስ አይነቶች ምን ያህል ጊዜ እንዳደረኩ ልቆጥርላችሁ አልችልም።

"ከሚስትህ ጋር ትነጋገራለህ?"

"እርግጥ እንደምወዳት ታውቃለች። ከእርሷ ጋር መነጋገርና ይህንን ልነግራት አያስፈልገኝም። ደግሞም እኮ ቀለበትና ሌሎች ጥሩ ጥሩ ነገሮች ገዝቼላታለሁ።"

"ስለገዛህላት ነገር አልጠየኩህም። አናግረሃት ታውቃለህ?"

"እንደምወዳት ታውቃለች"

"ግምት ነው የወሰድከው?"

"ተመልከት እንጂ፤ ለእርሷ፣ ለልጆቿ ምግብ የምገዛው . . ."

"ያንን እኮ አልጠየኩህም። አናግረሃት ታውቃለህ?"

"እርግጥ ነው፤ በእናቶች ቀን ዕለት አበባ ገዝቼላታለሁ። በዚህ ምክንያት እርግጠኛ ነኝ እንደምወዳት ታውቃለች።"

"እንደገናም ግምትህን እየነገርከኝ ነው፤ ስጦታህም የፍቅርህ አቻ መግለጫ እንደሆነ ቅድመ ግምት እየወሰድክ ነው፤ ይህ ግን እውነት አይደለም።"

የሆነ ነገር ለሰዎች መስጠት የፍቅራችን ማረጋገጫ አይደለም። በቅድሚያ ራሳችንን ልንሰጥ ይገባናል። ኢየሱስ ያደረገው በተጥያቄ እንዲህ ነው፤ ራሱን አሳልፎ ለእኛ ሰጠ። ስለዚህ ፍቅራችንን በቃል ልንገልጽ ይገባናል። ቃላችን ከድርጊታችን ጋር እንዲመጥን ልናደርግ ግድ ነው። በፍቅር ግንኙነታችን ፍቅራችንን በቃል ካልገለጽነው የመጨረሻው ውጤታችን በሰውና በዕቃ መካከል ያለው ልዩነት ጠፍቶን ግራ መጋባት ነው። እርስ በእርስ አድናቆትን መስጣጠት፤ እርስ በእርስ መገናኘትና አንዳችን ከአንዳችን ጋር መነጋገርን ልንማር ያስፈልገናል። ለድርጊታችን ትርጉም ለመስጠት ንግግር ወንካራ የሆነው መንገድ ነው። በግንኙነታችን ውስጥ በተለይም ፍቅርን በተመለከተ፤ ምንንም ነገር በመላምት እንዳንገምት ጥንቃቄ ልንወስድ ይገባናል።

"ጥቂት ትኩረት" ስጡ

ማንኛቸውንም ደስተኛ የሆኑ ባልና ሚስት የደስታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ብትጠይቋቸው፤ በየቀኑ ኑሯቸው ውስጥ አንዳቸው ለአንዳቸው የሚሰጡት ዕለታዊ መተሳሰብና ጥቂት ትኩረት እንደሆነ ፈጥነው ይመልሳሉ። ይህ በብዙ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል። አስተያየትን መለዋወጥ ሁልጊዜም ቀዳሚው ነው። ጣፋጭ ሆኖ ስለተዘጋጀው ምግብ፤ በስራ ቦታቸው ስላገኙት እድገት፤ ስለ አዲሱ በሌት ፀጉር ላይ ጣል የሚደረግ ሻርፕ፤ ስለተጠናቀቀ የስዕል ሥራ ወይም ግጥም ወይም ማንኛውንም ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ሀቀኛ የሆነ ትህትና የተሞላበትን ምስጋና መግለጽ ሁልጊዜም አሸናፊ ያደርጋል። ወትሮስ የአይምሮ ጤንነቱ የተቃወሰ ሰው ካልሆነ በቀር ከጥልቅ ስሜት የመነጨን ምስጋና የማይቀበል ማነው? እንዳለመታደል ሆኖ ግን ባልና ሚስት እርስ በእርስ በመላመዳቸው ብዙውን ጊዜ በበርካታ ቤቶች ውስጥ

አስተያየት መስጣጠትና ምስጋና መቀባበላቸው የተመጠነ አለዚያም ችል ተብሎ የሚታለፍ ነው።

"ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" (ሉቃ 6÷31) የሚለውን ወርቃማ ህግ በየዕለቱ ሀይወታቸው ተግባራዊ የሚያደርጉ ባለትዳሮች፤ ብዙውን ጊዜ የየቀኑን መተሳሰብ በሚመለከት መመሪያቸው የሚያደርጉት ቀላል ግንዛቤያቸውን ነው። በሌላ ቋንቋ ሌሎች አንተን እንዲንከባከቡህ በምትፈልገው መንገድ አንተም ሌሎችን ተንከባከብ። አንተም ሌሎች እንዲያስቡልህና ትኩረት እንዲሰጡህ እንደምትፈልግ ያንኑ ለሌሎች አድርግላቸው።

ሌሎች ሰዎች ለአንተ ትኩረት እስኪለጠህ አትጠብቅ፤ ይልቁንም አንተ ቀዳሚውን እርምጃ በመውሰድ ራስህን ምሳሌ አድርገህ አቅርብ። ሚስትህን ወደ አንድ የተወሰነ ስፍራ በሆነ ጊዜ ውስጥ ከቤት ልትወስዳት ከተስማማህ በኋላ፤ መድረስ ሳትችል ቀርተህ ብትዘገይ፤ ምንም እንኳን ለመልካምና ሊሰረዝ በማይችል ጉዳይ የዘገየህ ቢሆንም ቆም በልና ስልክ ደውልላት። ሊታሰፍ በማይችል ጉዳይ ምክንያት እንደዘገየህ እንደምታውቅ አድርገህ በጭራሽ አትገምት። ለቃልህ ታማኝ ሁን። አንዳንድ ሁኔታዎች አቅድህን እንድትለውጥ ቢያስገድዱህ፤ ይሄንን እርሷ እንድታውቀው አድርግ። ይህንን ጨዋነት የተሞላውን ድርጊት ለክብሯ የለጠኸው ዋጋ እንደሆነ ትገነዘባለች። ከዚህ በተጨማሪ ያደረከው ይህ ትኩረት የመስጠትና የግንኙነት ትንሽ ጥረትህ፤ በኋላ ለፈጠር ከሚችል አስደሳች ካልሆነ ጭቅጭቅና ግራ መጋባት ይጠብቅሃል።

ደስተኛ የሚያደርጉህን ወይም የተወደድህ እንደሆንክ እንዲሰማህ የሚያደርጉና መረጋጋትን የሚሰጠህ ነገሮች ምን እንደሆኑ አስብና እነዚያኑ ነገሮች ለትዳር ጓደኛህ አድርግ። ልክ እርሱ በሚወደው መንገድ አይነት ሽሚዙን ተኩሰሽ አዘጋጅለት። የምትወደውን የአበባ አይነት ላክላት። ሚስጥርነት ያለው የፍቅር ደብዳቤ ጽፈሽ ባልሽ በመደነቅ አሁንም አሁንም እንዲመስክተው በሚያደርገው ባልተለመደ ቦታ አስቀምጭለት። ለምሳሌ ካልሲ በሚያስቀምጥበት መሳቢያ ውስጥ ወይም በሸሚዙና በቡታንታው ኪስ ውስጥ ወይም ጌጣጌጥ በሚያስቀምጥበት ሳጥን ውስጥ ወይም በቤቱ ዙሪያ በአንድ አሳቻ ስፍራ ሊሆን ይችላል። እርግጥ ነው እንዲህ አይነቱን ማስታወሻ መጻፍ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ይሁን እንጂ በትዳር ውስጥ የሚኖረውን ህብረትና ደስታ ሊያስገኝ

የሚችል ሽልማት ሊያስገኝ የሚችል በመሆኑ የጠፋው ጊዜ ዋጋ ያለው ነው።

ግምታዊነታችሁና መላምታችሁ ከእናንተ ይወገድ። የመፍጠር ክህሎታችሁን ተጠቀሙ። ሁልጊዜም የትዳር ጓደኛችሁን ለማስደነቅና ለማስደሰት "ያልተጠበቀ የመተሳሰብ ተግባር" የምትፈጽሙበትን መንገድ ፈልጉ። ጥቂት ትኩረትን መስጠት ከጋብቻ ብዙ አመታት በኋላ እንኳን ፍቅርንና የእጮኝነት ዘመንን ግንኙነት አይነት ሁኔታዎችን ጠብቆ ለማቆየት ይረዳል።



ሁልጊዜም የትዳር ጓደኛችሁን ለማስደነቅና ለማስደሰት ያልተጠበቀ የመተሳሰብ ተግባር የምትፈጽሙበትን መንገድ ፈልጉ።

ሁልጊዜም መልካም ቃል ተነጋገሩ መልካም ተግባር ስሩ

ከሁሉም በላይ፤ ሁልጊዜም መልካም ቃል ተነጋገሩ መልካምን ተግባር ፈጽሙ። ሁላችንም ብንሆን በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርን በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሰዎችን መልካምነትና አክብሮት ማየት እንፈልጋለን። ባልና ሚስት ለሌሎች ሰዎች ከሚናገሩት መልካም ቃልና ከሚያደርጉት መልካም ሥራ ይልቅ አብልጠው እርስ በእርሳቸው ሊቀባበሉ ይገባል። ብዙ ጊዜ ግን በትዳር ውስጥ ባልና ሚስት ከሚገባው በላይ በመላመዳቸው ምክንያት እንዲህ አይነቱ ተግባር የቀዘቀዘና ፈጥኖ ወደ አለመቀባበል የሚለወጥ ነው።

መልካም ቃልና መልካም ተግባር በሁለት በኩል የሚሠራ ነው። ሚስቶች ባሎቻቸው መልካም ቃል እንዲናገሯቸውና መልካም ተግባር እንዲፈጽሙላቸው እንደሚፈልጉ ሁሉ እነርሱም ለባሎቻቸው ይህንኑ ሊያደርጉ ይገባቸዋል። ባሎች ለሚስቶቻችሁ የመኪናውን በር ከፍታችሁ አስገቧቸው። ወደ ምግብ ቤት በገባችሁ ጊዜ ወንበሩን ስባችሁ እንድትቀመጥ አድርጓት። ሁልጊዜም ትህትና ባልተለየው አክብሮት ተንከባከቧት። የሆነው ሁሉ ሆኖ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ልቧን ሊያሸንፈው የሚችል ነገር አሁንስ ቢሆን ልቧን ለጠብቅ እንዲችል ለምን አይቀርብላትም። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በግልም ይሁን በአደባባይ ከፍ ያለውን ክበሬታ አሳያት። በፍጥረት ሁሉ ዘንድ አክብሮትንና አድናቆትን እንድትሰጣት፤ በሁሉም ለዎች ዘንድ ከማንም ይልቅ እርሷ ለአንተ ጠቃሚ ሌት እንደሆነች ግልጽ እንድታደርግ ትጠብቅብሃለች።

ሚስቶች ሆይ፤ ባሎቻችሁ መልካምን ቃል እንዲናገሯችሁና መልካምን ነገር እንዲያሳዩዋችሁ ለመፍቀድ እጅግም ኩሩዎች ወይም ያልተገባ ነፃነት ያላችሁ እትሁኑ። ካልሆነ ግን የመባረክ ብቃቱንና አጋጣሚውን ልታበላሹ ትችላላችሁ። እግዚአብሔር ወንድን ለሴቷ ራሱን በመስጠትና በመባረክ የውጤታማነቱን መንገድ በእዚያ ውስጥ እንዲፈልግ አድርጎ ፈጥሮታል። እንቺም ውጤታማ በማድረግ ውጤታማ የመሆን እድሉን አትንፈጊው።

በተለይ ሰዎች በተሰበሰቡበት ስፍራ በመልካም ቃል ተናገሪው፣ አክብሪው። ይህ እንድ ሠራተኛ ሰጌታው እንደሚያሳየው አይነት መሽቆጥቆጥ ሳይሆን፤ አንድ ሰው አቻው ሰሆነ ባልንጀራው የሚያሳየው አክብሮትና የሚሰጠው እድናቆት ነው። በተሰይ ወንዶች በስራ ባልደረቦቻቸውና በጓደኞቻቸው ፊት አክብሮትንና እድናቆትን ማግኘት ይፈልጋሉ፤ ይህንን ደግሞ ከሚሰቶቻቸው በላይ ሊተገብረው የሚችል ማንም የለም። እርሱን ለመደገፍ፣ ከፍ ከፍ ለማድረግና ለማጽናናት የምታገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቀሚ።

ባልና ሚስት በሰዎች መካከል አብረው በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የተመሠረተው የጋራ በሆነ ፍቅር፤ እድናቆትና አክብሮት ላይ መሆኑ የማንም አይምሮ የሚጠራጠረው መሆን የለበትም። እንደነዚህ ያሉ ብቃቶችን ለማጎልበትና ለማሣደግ የሚረዱ እጅግ ጥቃቅን ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ ነቀፌታን ማለወገድ ከበሬታንና እድናቆትን ማሳየት፣ ፍቅርን በግልጽ ማሳየት፣ ትኩረት መስጣጠት፣ የተለመደ መልካም ቃልና መልካም ተግባር ማድረግን የመሳሳሉ ቀላል ነገሮች ናቸው። እነዚህ ደግሞ ትዳራቸውን ከመሠረቱ የሚገነቡ ናቸው።



ጥቃቅን የሆኑትን ነገሮች ስትርሷቸው። ትልልቆቹ ነገሮች የሚገነቡባቸው ጡቦች ናቸው።

ጥቃቅን የሆኑትን ነገሮች አትርሷቸው። ትልልቆቹ ነገሮች የሚገነቡባቸው ጡቦች ናቸው። ውጤታማ የሆኑ ግንኙነት፣ እውነተኛ የሆነ ፍቅር እድገትና በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተ ህብረት ደስተኛና ዘላቂታ ላለው ትዳር መሠረት ናቸው።

መርሆዎች

1. በጋብቻ ውስጥ ትልቅ ስኬት እንዲኖር አስፈላጊ የሆነው ነገር ጥቃቅን ሰሚባሉ ነገሮች ትኩረት በመስጠት ነው። እነዚህ ጥቃቅን፣ የማያቋርጡና ዕለታዊ የሆኑ መልካም ቃላት፣ መልካም ተግባራትና ትኩረት መሰጣጠት ግንኙነትን የሚያጎለብቱ ከመሆኑም በላይ ጣዕም የሚሰጡ ናቸው።

2. ነቀፌታ በባህሪው አፍራሽ ነው፤ ምክንያቱም መፍትሔ ከመፈለግ እንጻር ሳይሆን ጉዳትን ለማድረስ በታቀደ ዓላማ ስህተትን ስለሚፈልግ ነው።

3. ግሳጼ ፍቅርና ርህራሄ ከተሞላው መንፈስ የሚመነጭ ከመሆኑም በላይ በችግር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ከልብ በመነጨና ሌላውን ሰው በሚጠቅም መልኩ ለችግሮች አግባብነት ያላቸውና ተመጣጣኝ መፍትሔዎችን ይፈልጋል።

4. ሰባልና ሚስት በትዳር ውስጥ ትልቁ አደጋ እንዳቸው ሌላኛውን በመተማመን ከመጠን ያለፈ የመላመዳቸው ነገር ነው።

5. ለባልና ሚስት ለሁለቱም ትዳርን ህይወት ያለው፤ ጠንካራና አስደሳች እንዲሆን ከሚያደርጉት እጅግ ጠቃሚ መንገዶች አንዱ፤ እንዳንድ ጊዜ እንግዳ የሆኑና ያልተለመዱ ነገሮችን መተግበር ነው።

6. እውነተኛ የሆነ ፍቅርና አድናቆት ደስተኛ ለሆነ ትዳር የህይወቱ ምንጭ ናቸው።

7. ፍቅር ያለማቋረጥና ደጋግሞ ሊገለጥ ያስፈልገዋል እንጂ በመላ ምት ወይም በግምት ላይ የተመሠረተ አይደለም።

8. በግንኙነት ውስጥ መጠነኛ የሆነ ትኩረትን በየዕለቱ መሰጣጠት ከረጅም የጋብቻ አመታት በኋላ እንኳን ፍቅራቸው በመሸከርመሚያ የእጮኝነት ጊዜያቸው እንደነበረ ያህል እንዲቆይ ይረዳል።

9. ከሁሉም በላይ ምንጊዜም ትህትና የተሞላህ፣ አክብሮትና ትኩረት የምትሰጥ ሁን።

ምዕራፍ ሰምስት

ከእግዚአብሔር መንግሥት ስባስትዳሮች የተሰጡ መርሆዎች

በጋብቻ ህይወት ዙሪያ በባለትዳሮች መካከል ብዙ ችግሮች የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ቢኖሩም ከሌሎቹ ሁሉ በላይ ቀደምት ተጠቃሽ የሚሆነው የንብረት አስተዳደር ነው። ምንም እንኳን የንብረት አስተዳደር ስንል ገንዘብ ነክ ጉዳዬችን እንደሚያጠቃልል አርግጥ ቢሆንም፤ ከባልና ሚስት የገንዘብ አጠቃቀም ጉዳይ ልቆ የሚሄድ ነው። የንብረት አስተዳደር በባለትዳሮች በጋራ የሚኖራቸውን ማንኛውም የህይወት ገጽታ የሚያካትት ነው። የሥራ ቅጥርና የሥራ ምርጫ፣ የገንዘብ አወጣጥ፣ የገንዘብ ቁጠባና የመዋዕለንዋይ ፍለት፣ በጊዜያዊነት የሚሠሩዋቸው የሥራ ሁኔታዎች፣ መደበኛ ሥራቸው፣ የትምህርት ግብ፣ ለወደፊቱ የሚያቅዱት አቅድና የልጆች ምጣኔም ጭምር በዚህ ውስጥ ይካተታሉ።

የንብረት አስተዳደር ሌላው ቃል አቃቢነዋይነት /መጋቢነት/ ነው። አቃቢንዋይ /መጋቢ/ የሌላውን ለው ንብረትና ጉዳይ የሚያስተዳድር ለው ነው። አቃቢንዋይ ምንም እንኳን የንብረቱ ባለቤት ባይሆንም ባለንብረቱን ተክቶ ንብረቶቹን ለማስተዳደር ከፍ ያለ የሃላፊነትና የስልጣን ደረጃ አለው። የአቃቢነዋይነቱ ቀጣይነት ያለውና አስተማኝ የሚሆነው፤ አቃቢነዋዩ ለባለንብረቱ ፍላጎት ባለው ታማኝነትና የሥራ ቅልጥፍና ነው። ውጤታማ የሆኑ አቃቢነዋያን በሃላፊነት የተሰጣቸውን ንብረት ያበዙታል ይጨምሩበታል፤ ይህም የበለጠ ንብረትን የማስተዳደርና ሃላፊነትን የሚጨምር ነው።

በመላው ያዐመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህ መርህ በግልጽ ክባድ እንደሆነ ተገልጿል። የአቃቢነዋይነት ስእላዊ መግለጫ ሆነው ከተቀመጡት ታሪኮች አንዱም የዮሴፍ ታሪክ ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ክ37-50 ያሉት ምዕራፎች ዮሴፍ ክህደትን በፈጸሙበት ወንድሞቹ ለባርነት ተሸጦ እንደነበር ይገልጹልናል። ይሁን እንጂ መልካም የሆኑ አጋጣሚዎች በግብጽ ምድር ውስጥ ከፈርያን ቀጥሎ ታላቅ ስልጣን ያለው አስተዳዳሪ እንዲሆን አደረገው።

የፈርኦን ዘቦች አለቃ ለነበረ ሰው ባሪያ በመሆን፤ በእርሱ አቃቢነዋይነት ጌታውን እጅግ አበለጸገው፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ ታማኝና ውጤታማ የሆነ አስተዳዳሪ መሆኑንም አስመስከረ።

የጌታውን ሚስት ለመድፈር መከራ በማድረግ በሀሰተኛ ወንጀል ከተወነጀለና ወደ ወህኒ ከተጣለ በኋላ እንኳን ታማኝነቱን ቀጥሎ ነበር። የእስር ቤቱ አለቃ የዮሴፍን ተስጥኦና ብቃት በማስተዋል በእስረኞቹ ሁሉ ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው። በዚህ ቦታ እንደገና ደግሞ ዮሴፍ እንዲያስተዳድረው በተሰጠው ነገር ሁሉ ላይ በእግዛቡ ማስተዳደሩን ቀጠለ።

ቀስ እያለም የዮሴፍ ተስጥኦ የንጉሱን የራሱን ቀልብ የሳበበት ጊዜ መጣ። በዚህ ለው ጥበበኝነት ብቃትና ግልጽ የሆነ አስተዳደራዊ ችሎታ የተደነቀው ፈርኦን ዮሴፍን ክባርነት አንስቶ በግብጽ ምድር ሁሉ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ሾመው። በዚህ ስፍራ በተሰጠው ሃላፊነት ዮሴፍ ያሳየው ጥበብ የተሞላው አስተዳደር፤ በስባቱ የጥጋብ ዓመታት በተገኘው ከፍተኛ ምርት ቀጥለው በተከተሉት ስባት የርሃብ ዓመታት ህዝቡ ችግሩን እንዲቋቋምና እንዲያልፍ አስቻለ።

በዚህ ጊዜ ውስጥም የራሱ ቤተሰቦች የሆኑትን ወገኖቹን፤ ከብዙ ዓመታት በፊት በሞካኔ ያንገላቱትንና የሸጡትን ወንድሞቹን ጨምሮ ከርሃብ ጥፋት እንዲያመልጡ ምክንያት ሆኖላቸዋል።

ዮሴፍ አቃቢንዋይ ሣለ በለጠን፤ ምክንያቱም ለአምላኩና እንዲያስተዳድረው ሃላፊነት በተጣለበት ንብረት አስተዳዳር ታማኝ ለው ነበረ። የሁሉም ነገር ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን በመገንዘብ ዮሴፍ ሀላፊነቱን በተቻለው አትምና በክበረ መንገድ ለመወጣት ታላቅ ጥንቃቄ ወስዶ ነበር።

ስኬታማና ረኻርም ርቀት ከሚንዝ ትዳር ጋር ይህ ምን ግንኙነት አለው? በቀላሉ ጉዳዩ እንዲህ ነው፤ መልካም የሆነ አቃቢነዋይነት ለእድገት፣ ለብልጥግናና ለደስተኛነት ጠንካራ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው። እጅግ ብዙ ባለትዳሮች ገንዘብንና ሌሎች ጉዳዬችን በሚመለከት በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አለ፤ ምክንያቱ ደግሞ እንደ ፈጣሪነቱ እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ባለቤት፤ እነርሱም አቃቢነዋያት ብቻና እግዚአብሔር ያስተዳድሩት ዘንድ ሀላፊነት በሰጣቸው ነገር ሁሉ ላይ በእርሱ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ያለውን እውነት በአግባቡ አለመገንዘባቸው ነው።

ስአቃቢነዋይነት (ስመጋቢነት) አዘጋጅቶናል

አቃቢነዋይነት በመጀመሪያው የእግዚአብሔር አትድ ውስጥ ለሰው ህይወትና በኑሮውም እንዲተገብረው በእግዚአብሔር የተረቀቀ

አቅድ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥራቸውና "የባህር አሶችንንና የሰማይ ወፎችን፣ እንሰሳትን ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ" (ዘፍ 12፥6) ሲል የመግዛትን ስልጣን ሰጥቷቸዋል። ይህ የማስተዳደር ስልጣን የመቆጣጠር ስልጣን ነው። እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን የፈጠረው ሉአላዊ ከሆነው ከፍተኛ ስልጣኑ በታች እኩል በሆነ ደረጃ የተፈጠሩትን እንዲቆጣጠሩ ነው። በምድርና በተሸከመችው ሀብት ሁሉ ላይ አቃቢነዋያት ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ሁሉ ሃላፊነትን ጥሎባቸዋል።

ምንም እንኳን በፍጥረት መጀመሪያ በኤደን ገነት አውድ ውስጥ ይህ እኩል ተሳትፎ ያለበት ገዥነት በትዳር ሁኔታ ውስጥ የታየ ቢሆንም፤ ምድርን የማስተዳደር መርህ በማንኛውም ሁኔታዎች ውስጥ በማንኛውም ሰው ወንድ ይሁን ሴት፣ ያገባ ይሁን ያላገባ ሊተገበር እንደሚችል ግልጽ ነው።



አቃቢነዋይነት (መጋቢነት) በመጀመሪያው የእግዚአብሔር አቅድ ውስጥ ሰዎች ሕይወትና በኑሮውም እንዲተገብሩ በእግዚአብሔር የተሬቀቀ አቅድ ነው።

ምድርን መግዛትን መስማመድ ማለት፤ ማስተዳደር፤ መቆጣጠር ወይም በላይዋ ላይ መሰልጠንና ጌታዋ መሆን ማለት ነው። በላይዋ ጌታ መሆን ማለት ግን ያልተቋረጠ ቡጥቦጣ ማካሄድና የተፈጥሮ ሀብት ብክነት ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ጥንቃቄ የተሞላበት የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ማለት ነው። በአግባቡ የተስተዳደረ ግዛት ሁልጊዜም የቅርብ ክትትልን ያካተተ ነው። እንደ ሀያው ፍጥረትነታችን ምድርን ሁሉ የመግዛታችን ስልጣን ዝቅተኛ የሆኑትን ፍጥረታት ሁሉ መግዛትን ያጠቃልላል፤ አንዱ ሌላውን የመግዛቱ ጉዳይ ላይ ግን ነገሩ በአጭሩ ይቆማል። እውነት ነው፤ ሰብአዊ የሆነው ማህበረሰብ ስርዓት እንዲከበር ለማስቻል መንግስታትን ይመሰርታል፤ አስተዳዳሪዎችን ይመርጣል፤ የስልጣንና የሃላፊነት ተዋረዶች ሰንሰለቶችን ያበጃል፤ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ሀጋዊ የሚሆኑት ስልጣናቸውን በህዝቡ ምርጫና ፈቃድ እስከተገለገሉበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ማናችንንም ቢሆን ሌሎችን እንድንጨቁን አልፈጠረንም፤ ይልቁንም ሁላችን የተፈጠርነው ምድርንና በእርሷ ውስጥ ያለውን ሁሉ እንድንገዛና እንድንቆጣጠር ነው። የገዥነት ስልጣን ያለን በነገሮች ላይ እንጂ በሰዎች ላይ አይደለም።

ባለንበት ዘመን ሌሎች ሰዎችን እንዴት እንደምንቆጣጠር የሚያስተምሩ የአስተዳደር ትምህርት ቤቶች አሉ፤ ብዙዎቹ ግን የሚያተኩረት ሰዎችን በጥበብ በቁጥጥር ስር የሚያውሉበትን፤ የሚቀጠቅጡበትን እነርሱ እንዲያደርጉ የፈለጉትን ሌሎች ያለፈቃዳቸው እንዲያደርጉ በሚያስችላቸው መንገድ ሰዎችን በተሳሳተ መንገድ በሚመሩበት ሁኔታ ላይ ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሆነ ከመሆኑም በላይ ሰዎችን ለመቆጣጠርና እንዲያም ሲል ከመጨቆን በሚመነጭ ሃሳብ የታቀደ ነው።

አንደ ሰብአዊ ፍጥረትነታችን የመጀመሪያው ሃላፊነታችን ማስተዳደር ነበር፤ እግዚአብሔር ያንን ብቃት በእኛ ውስጥ አዳብሮታል። የመግዛትን ስልጣን የተሰየ ችሎታ ላላቸውና ለተመረጡ ጥቂት ሰዎች ጠብቆ አላቆየውም፤ ይልቁንም ይህን እድል የከፈተው ፍጥረቱ ሰሆኑ ሰዎች ሁሉ ነው። በተገለጠው የእግዚአብሔር አቅድ ብርቱ የመሆን ዘር፣ የመሪነት አምቅ ችሎታና መሠረታዊ የሆነ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ብቃት በእያንዳንዳችን ውስጥ አለ።

"እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ባረካቸው እንዲህም አላቸው፤ ብዙ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፤ የባህርን አሳዎችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው" (ዘፍ 1፥26-28)።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ያልሰጠውን ማንኛውንም ነገር በጭራሽ አይጠይቅም። እግዚአብሔር እንድንሠራው ያዘዘንን ነገር ሁሉ መስራት እንድንችል አቅም ሰጥቶናል። "ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት" ብሎ ከማዘዙ በፊት፤ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይህንን ነገር ለመፈጸም የሚያስችለንን ብቃት አስቀምጧል።

የፍጥረት ሁሉ ጌታ አቃቢነዋያት እንድንሆን አቅዶናል። ቀዳሚ የሆነው ዓላማችንም "ምድር" ተብሎ የሚጠራውን ግዛት መግዛትና መቆጣጠር ነው። እግዚአብሔር እኛን የፈጠረበትን አላማ ባልፈጸምነው ጊዜ ሁሉ ችግር ውስጥ እንወድቃለን። ብዙ ጊዜ የተፈጠርንበትን አላማ ለማከናወን አለመቻል ወደ መንፈሳዊ፣ አይምሯዊና አካላዊ ድህነት ውስጥ እንድንወድቅ ያደርገናል። መለኮታዊ ከሆነው እግዚአብሔር ለሰእኛ ካቀደው አቅድ ሰንለይ

በድህነት ላይ እንወድቃለን። ምናልባትም ፈሪዎች ወይም ከዚህ በከፋ መንገድ አጅግ ተስፋ ቆርጠን የተደበርን ልንሆንም እንችላለን።



ብዙውን ጊዜ የተፈጠርንበትን ስላማ ስማከናወን ስስመቻል ወደ መንፈሳዊ፣ ስደምሯዊና ስካላዊ ድህነት ውስጥ እንድንጠድቅ ያደርገናል።

በሌላው መንገድ ከተመለከትን፤ እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን እቅድ ጠንቅቀው የተረዱና በህይወት ሊተገብሩትም በሚፈልጉ፤ ችግርና ተግዳሮቶች ባሰባቸው ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን ጤንነትን፣ ውጤታማነትን፣ ደስተኝነትንና አርካታን በሁሉም የህይወታቸው ዘርፍ ይለማመዱታል። ይህ ደግሞ በግለሰቦች ህይወት ውስጥ እንደሚሠራ ሁሉ በባለትዳሮችም ህያወት ውስጥ እኩል የሚሠራ እውነት ነው። ብዙ ባለትዳሮች የሚገባውን ያህል ላይበለጥጉ እየወደቁ ይነሳሉ፤ ምክንያቱም ባለትዳሮቹ በእግዚአብሔር ንብረት ሁሉ ላይ አቃቢነዋያን የመሆናቸውን አላማ በጭራሽ አልተገነዘቡም ወይም የመንግስቱን የአስተዳደር መርሆዎች መተግባር አልተማሩም።

እግዚአብሔር የሥራ መሪዎችን ይፈልጋል

ገና ከመጀመሪያው የፍጥረት ሁሉ አምላክ "አስተዳደሮን" በምድር ላይ ህይወትን ለመምራትና ለዎች ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመወሰን ገዥ የሆነ መሠረታዊ መርህ አድርጎ አቋቁሞታል። እድገት የሚወሰነው በአቃቢነዋይነት ላይ በሚደረግ ውጤታማ አስተዳደር ነው። ይህን ግንኙነት የተገለጸበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ውስጥ እናገኛለን።

"እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድን ባደረገ ቀን፤ በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው። የሜዳ ቁጥቋጦ ሁሉ በምድር ላይ ገና አልነበረም፤ የሜዳውም ቡቃያ ሁሉ ገና አልበቀለም ነበር፤ እግዚአብሔር አምላክ በምድር ላይ አላዘነበም ነበርና፣ ምድርም የሚሠራባት ሰው አልነበረም፤ ነገር ግን ጉም ከምድር ትወጣ ነበር፣ የምድርንም ፊት ሁሉ ታጠጣ ነበር። እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን አፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍ 2÷4-7)።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የተመለከተውን አድገት ልብ በል። ምንም እንኳን እግዚአብሔር አስቀድሞ ምድርን ቢመሠርትም በሁለት ምክንያቶች ሳቢያ የሜዳው ቡቃያ ገና አልበቀለም ነበር። የመጀመሪያው በምድር ላይ ዝናብ ባለመዝነቡ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምድር የሚሠራባት ሰው አልነበረም። የሥራ መሪው እስኪመጣ ድረስ እግዚአብሔር አድገትን ሁሉ አቅቦ ይዞ ነበር። ህይወት ሙሉ ለሙሉ የምታብበው አቃቢነዋዩ መጥቶ ይንከባከባት ዘንድ ሲጀምር ብቻ ነው።

ብቃት የሌለው አስተዳደር አድገትን ቁልቁል የሚጎትት ነው። እግዚአብሔር ብቃት ያለው አስተዳደር እስኪያገኝ ድረስ አድገትን አቅቦ ይይዛል። የሚበዛውን ነገር የማስተዳደር አቅም ያለው አንድ ሰው እስኪያገኝ ድረስ ምንም አይነት መብዛትን አይፈቅድም፤ ለሚገኘው አድገት ተጠያቂነት ያለበት አንድ ሰው እስኪያገኝ ድረስ ምንም አይነት አድገት አይኖርም።



ብቃት የሌለው አስተዳደር አድገትን ቁልቁል የሚጎትት ነው። እግዚአብሔር ብቃት ያለው አስተዳደር እስኪያገኝ ድረስ አድገትን አቅቦ ይይዛል።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የሚዘምር፣ የሚያሸበሽብና ወደ እርሱ የሚጸልይ መንፈሳዊ የሆነ ፍጥረት አስፈልጎት አይደለም። ይልቁንም ፍጥረተ ዓለምን የሚያስተዳድር ሰው ይፈልግ ስለነበረ ነው። በአምልኳችንና አገልግሎታችን ወቅት ከዚያ ቀጥሎን የምናደርገውን ያህል የሚያስደንቀው ወይም ልቡን የሚጥልበት አይደለም። እንዴት አድርገን በመልካም ሁኔታ ጉዳዮቻችንን እንደምናከናውን ማየት ይፈልጋል። ጊዜያችንን እንዴት እንደምንጠቀም፣ በገንዘባችን ምን እንደምንሠራ፣ ያሰንን ብርቅየ ጥሬ ቁስ እንዴት በጥበብ ወይም እንዴት በአንዝህላልነት እንደምንጠቀምበት ማየት ይፈልጋል። እግዚአብሔር መብዛትን ማየት ይሻል ምክንያቱም መልካም አስተዳደር ሁልጊዜም መብዛትን የማያመጣ በመሆኑ ነው።

አስተዋይነት የተሞላው አስተዳደር የእግዚአብሔርን ትኩረት ይስባል። በጥቂቱ የምንታመን ከሆነ እግዚአብሔር በበዛው ነገር ላይ ይሾመናል። ይህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው። አንድ ቀን ኢየሱስ እንደየአቅማቸው የተለያየ መጠን ያለው ገንዘብ ለሙያተኞች በመስጠት ወደ ሩቅ አገር ስለሄደ ባለጠጋ ሰው ታሪክ ተናገረ (ማቴ 25÷14-30 ተመልከት)። የመጀመሪያዎቹ ሁለት

መያተኞች ወዲያውኑ ሄደው ጥንቃቄ በተሞላበት አስተዳደርና ጥበበኝነት ባለው ምዕዋለንዋይ ገንዘባቸውን እጥፍ አደረጉት። ሦስተኛው መያተኛ ግን ጌታው ከሄደበት እስኪመለስ ድረስ ገንዘቡን ከመቅበር ያለፈ ያደረገው ሌላ ነገር የለም። ጌታው በተመለሰ ጊዜ ሁለቱን መያተኞች ስለታማኝነታቸውና ስላበዙት ነገር አመሰገናቸው፤ ሦስተኛውን ግን ደካማ ስለሆነ አቃቢነዋይነቱ ኮነነው። ከሦስተኛው መያተኛ የተሰጠው ገንዘብ ተወስዶ ለሌሎቹ ሁለት መያተኞች እንዲሰጥ አዘዘ። ጌታው እንዲህ አለ፤ "ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል ከሌላው ግን ያው ያለው እንኳን ይወሰድበታል" (ማቴ 25፥29)።

አስተዋጽኦነት የተሞላው አስተዳደር የእግዚአብሔርን ትኩረት ይስባል። በጥቂቱ የምንታመን ከሆነ እግዚአብሔር በበዛው ነገር ላይ ይሾመናል።

በሕይወታችን በአገልግሎታችንና በተለይ በትዳራችን ውጤታማና ስኬታማ ለመሆን ተስፋ የምናደርግ ከሆነ፤ መልካም አስተዳደሪ መሆንን ልንማር ያስፈልገናል። አቃቢነዋይ ማለት በእጃችን ላለው ማንኛውም ጥሬ ቁስ ለእግዚአብሔር ተጠሪዎች መሆን ማለት ነው። ውጤታማ የሆነ አስተዳደር ነገሮችን በነበሩበት መልኩ ከማስኬድ የላቀ ሥራን ይጠይቃል። በሀላፊነት በተሰጣቸው ነገር ሁሉ ላይ ተጨማሪ እሴት ያከሉበታል። ኢየሱስ በተናገረው ታሪክ ውስጥ የምናገኘው ሦስተኛው መያተኛ የተቀጣው የጌታውን ገንዘብ በማጥፋቱ አይደለም፤ (ገንዘቡ በእጁ ላይ ነበር) ነገር ግን በገንዘቡ ምንም አልሠራበትም ነበር።

የተፈረደበት አንዳች እሴት በላዩ ላይ ስላላከለበት ነው። በሀላፊነት በተሰጠው ንብረት ላይ አንዳችም የመብዛት ለውጥ አላመጣም።

ባለትዳሮች ሁሉ ራሳቸውን በየወቅቱ መመርመርና፤ "እግዚአብሔር በሰጠን ጥሬ ቁስ ላይ ምን እያደረግን ነው? ከእርሱ የተቀበልነውን በረከት እንዴት እየያዝነው ነው? ገንዘባችንን ጥበብ በተሞላው ሁኔታ እየተጠቀምንበት ነው? ባለፉት አመታትስ እድገት እያሳየን ነው? እግዚአብሔር እንድንሄድበት በፈለገው መንገድ እየተጓዝን ነው? የእርሱን ፈቃድ እየታዘዝን ነው? በአስተዳደራችን እግዚአብሔር ደስተኛ ነው? ቀጥሎ ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?" እያልን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል።

ገቢነት የአቃቢነዋይነት (የመጋቢነት) ውጤት ነው

በትዳር ውስጥ ለማደግ ቁልፍ ከሆኑ ነገሮች አንዱ፤ ባለትዳሮች ውጤታማ የሆነ አቃቢነዋይነት እድገት ያለው ነገር እንጂ ሳይንቀሳቀስ እንደነበረ የሚቆይ ነገር እንዳልሆነ መረዳታቸው ነው። በኤድን ገነት ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ባለትዳሮች መካከል የታየው ይሄው ነበር። ዘፍ 11፥18 ይህንን እድገት ያለው እርምጃ ይገልጽልናል። "እግዚአብሔር ባረካቸው እንዲህም አላቸው፤ ብዙ፣ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት ግዙአትም የባህር አሳዎችንና የሰማይ ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዙአቸው"።

እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ የነበረው እቅድ የተፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ እንዲገዙ ሲሆን፤ ይህንን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ግን አስቀድመው ውጤታማዎች፣ የሚበዙ፣ ምድርን የሚሞሉና የሚገዙም ይሆኑ ዘንድ ያስፈልጋቸው ነበር። ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር የሰው ፍጥረት ሙሉ የሆነ አገዛዝ ሊኖረው የሚችለው። በመሠረቱ ገቢነት በራሱ ግብ ሳይሆን የአራትዮሽ ገጽታ ሂደት ማለትም የውጤታማነት፣ የመብዛት፣ ምድርን የመሙላትና የመግዛት ውጤት ነው።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረገው ነገር ወንድና ሴት አድርጎ የፈጠራውን የሰው ዘር መባረክ ነበር። መባረክ ማለት ብቃትን መልቀቅ ማለት ነው። በባረካቸውም ጊዜ ብቃት ለቆላቸው ነበር። በምድርና በእርስዋ ላይ ባለው ነገር ላይ ሁሉ አቃቢነዋያት እንዲሆኑ ብቃትን ለቆላቸው ነበር። ከዚያ በኋላም ግዛታቸውን እንደ'ት እንደሚያስተዳድሩ መመሪያዎችን ሰጥቷቸዋል።

ገቢነት በፊት ግብ ሳይሆን የአራትዮሽ ገጽታ ሂደት ማስትም የውጤታማነት፣ የመብዛት፣ ምድርን የመሙላትና የመግዛት ውጤት ነው።

ብዙ፡ በዘፍ 1፥28 ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብዙ ጊዜ የምንረዳው ከመዋለድ ጋር አያይዘን ነው፤ ይሁን እንጂ ምድርን በሰዎች መሙላት የትርጉም አንድ ክፍል ብቻ ነው። "ብዙ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል በጾታዊ ግንኙነት ከመብዛት ያለፈ ትርጉም አለው፤ ይህም ቃል በቃል በሆነ ወይም ተምሳሌታዊ በሆነ ትርጉም መብዛትን የሚያመለክት ነው። መብዛት ማለት በባህሪው የጥራትና የብዛት ሊሆን ይችላል። የሰው ፍጥረት በመብዛት ጉዳይ ላይ ምንም ችግር የለበትም፤ ከስድስት ቢሊዬን በላይ የሆነውን

የአሁኑን የአለምን ህዝብ ቁጥር ዋቢ ማድረግ ይቻላል፤ ይሁንና ችግር ያለብን በሌላው አቅጣጫ እንደ እግዚአብሔር እቅድ ውጤታማ በመሆን ጉዳይ ላይ ነው።

በመሠረቱ መብዛት ማለት እምቅ የሆነ ከህሎታችንን መልቀቅ ማለት ነው። ፍሬ በመጨረሻው የሚገኝ ውጤት ነው። የፓምፕ ዛፍ ለውነትን ቀዝቀዝ ለማድረግ የማረፊያ ጥላና ወበት ያለውም ዛፍ ሊሆን ይችላል፤ ይሁንና ፍሬን እስኪሰጥ ድረስ የሚጠበቅበትን ከፍተኛ ውጤታማነት አያስገኝም። የፓምፕ ዛፎች ቀጣይ ለሆኑት የፓምፕ ዛፎች ዝርያ መባዛት አስፈላጊ የሆነውን ዘር ይዘዋል። ይሁን እንጂ የፓምፕ ዛፎች በተጨማሪ ይሰጡ ዘንድ የሚጠበቅባቸው ነገር አለ። የለውን አካላዊ ርሃብ ሊያረካ የሚችል ጣፋጭና ለውነት የሚገነባ ምግብ። በዚህ መልኩ ፍሬ ራሱን ከማባዛት የላቀ እጅግ ከፍተኛ አላማ አለው፤ ይሄውም በዚህ ምድር ላይ ለአለም ባርኮት መሆን ነው።

እያንዳንዱ ለው የተወለደው ከታላቅነት ዘር ጋር ነው። እግዚአብሔር አየተሟሟርን ፍሬን እንድንፈልግ አላዘዘንም - አስቀድሞውንም ዘሩ በእኛ ውስጥ አለ። በእያንዳንዳችን ውስጥ ለአለም ታላቅ በረከት የሚሰጥ ጥቅጥቅ ያለ ደን እጅግ ውጤታማ ሰብልም ሊሆን የሚችል እምቅ ዘር አለ። ገና ከማህፀን ሳለን እያንዳንዳችን ልዩ ተሰጥኦን ተቀብለናል። ይህ ተሰጥኦ ልንተገብረው የተፈጠርንለትን ተግባር ከእኛ በቀር ሌሎች በተሻለ ሁኔታ ውጤታማች ሊሆኑ በማይችሉበት ደረጃ ልንተገብረው ብቃት ይሆነናል። የእግዚአብሔር አላማ እጅግ የተትረፈረፈ ፍሬ እንድናፈራና የተሰጥኦዎችን ውጤት የሆነውን ባርኮትና እምቅ ከህሎታችንን ለዓለም እንድንለቅ ነው።

እያንዳንዱ ለው የተወለደው ከታላቅነት ዘር ጋር ነው።

በምድር ላይ ብዙ መታበሮች ገና ያልተሰቀቀ በዘር ደረጃ ያለ እምቅ ተሰጥኦን ይዘው በሞቱ በርካታ ለሞች መሞላታቸው አሳዛኝ እውነት ነው።

እዚህ ቦታ ላይ ነው የለው ዘር ብዙውን ጊዜ "ብዙ" የሚለውን አምላካዊ ቃል ውጤታማ ለማድረግ አቅቶት የሚወድቀው። ዓለም ለዘለዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ ከድህነት ወደከፋ ድህነት የምታሽቆለቁልበት ምክንያት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሚሊዮኖች ባርኮታቸውን ሳይለቁት ስለሚሞቱ ነው።

ምን ጊዜም ቢሆን "ለአለም የምስጠው ምንም ነገር የለኝም" እያልክ ለእግዚአብሔር በመናገር ስህተትን አትፈጽም። የምትናገረው ስህተት ነው። እግዚአብሔር ጥቅም የሌለው ባዶ ነገር ፈጥሮ አያውቅም። እያንዳንዳችን ዘር አርግዘናል፤ እግዚአብሔርም ይህ ዘር እንዲገለጥ፣ እንዲያድግና የተትረፈረፈ ፍሬ እንዲሰጥ ይፈልጋል። ፍሬያችንን ዓለም ሊቋደሰውና ሊዳብርበት ሊባረክበትም ወደሚችል የጎመራ ብስል ፍሬነት እንድናሳድገው ይሻል።

የአንተ ዘር ምንድነው? አላምረህ ምግብ ማዘጋጀት ትችላለህ? ጥሩ ሰዓሊ ነህን? የስነጽሁፍ ችሎታስ አለህ? ጥሩ የንግድ አስተሳሰብ አለህ? እንደ ባለትዳሮች የተቀናጀ ችሎታ ያላችሁ እንደሆነ አስኪ አስተውሉ። ምን አይነት የፀንዘብ፣ የአካልና የአይምሮ ጥሬ ቁስ ነው እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ ያስቀመጠው? የራሳችሁን ንግድ ለመጀመር ተሰጥኦውና ብቃቱስ አላችሁ? በተለየ ወይም ተፈላጊ በሆነ አገልግሎት ቢጋራ ለመሥራት አስፈላጊው ነገር አላችሁ? ገና ከእናታችሁ ማህጸን ስትወጡ እግዚአብሔር በእናንተ ያስቀመጠውን አላማ ውጤታማ ታደርጉ ዘንድ ምን አይነት መደዊና ግለሰባዊ ጥሬ ቁስ ልታወጡ ትችላላችሁ? በእናንተ ውስጥ ዓለም የሚፈልገው ነገር አለ። ፍሬያማዎች ሁኑ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ ያኖረውን ይገልጠው ዘንድ ፍቀዱለት።

ተባዙ: መብዛት መልካምና አስፈላጊ መነሻ ነው፤ ነገር ግን ቀጣይ ወደሆነው ወደ "መባዛት" ደረጃ ሊያድግ ያስፈልገዋል። እንደገናም በዚህ ስፍራ ያለው ሀሳብ በመዋለድ መባዛትን የማያመለክት ቢሆንም፤ ጸታዊ በሆነ ግንኙነት መዋለድ የትርጉሙ ከፊል ብቻ ነው። "ተባዙ" የሚለው ቃል እንደዚሁ "መትረፍረፍ" "በስልጣን ላይ መሆን" "መስፋፋት" እና "ታላቅ መሆን" የሚል ትርጉም የያዘ ነው። ያለህ ተሰጥኦ እየረቀቀ ሄዶ ልዩ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚገልጽ ቃል ነው።

በዚህ አውድ ውስጥ ስንቃኘው፤ መባዛት ማለት ልጆችን በመውለድ መባዛትን ብቻ የሚያመለክት ሳይሆን ይልቁንም መሻሻልንና ከፍ ማለትን፣ ተሰጥኦን በብቃት መግለጥንና በምትሠራው ሥራ እጅግ በጣም ከፍተኛ የስኬት ክንውን ማሳየትን የሚያካትት ትርጉም የያዘ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር የሰጠህን ጥሬ ቁስ እንዴት ማስተዳደር እንደምትችል መማርንና በመሻሻሉ ሂደት ውስጥ የተባዛውን ነገር ለማስተዳደር አስፈላጊ

የሆነውን የረዥም ጊዜ እቅድ ማሳደግን የሚመለከት ትርጉም አለው። ተሰጥኦህን በማሻሻል በአለም ውስጥ ተፈላጊነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ትችላለህ። ተሰጥኦህን እያሳደከው በሄድክ መጠን በዚህ ዓለም ላይ ተፈላጊነትህ እየጨመረ ይሄዳል። በምሳሌ 18፥16 "የሰው ስጦታ መንገዱን ታስፋፋለች፤ በታላላቆችም ፊት ታገባዋለች" የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን።



ተሰጥኦህን እያሳደከው በሄድክ መጠን በዚህ ስሰም ሳይ ተፈላጊነትህ እየጨመረ ይሄዳል።

ፍሬህ ወይም ተሰጥኦህ ምንድን ነው? ስለዚህስ ምን ታውቃለህ? ሊበዛ የሚችል ምን ነገር አለህ? ሰዎች አንተን ይፈልጉህ ዘንድ የሚያስችል ምን አይነት ብቃትና ምን ዓይነት ልዩ ችሎታ አለህ? የሚያስደስትህ ነገር ምንድን ነው? ለነፍስህ እርካታን የሚለጣት ከፍተኛ ስሜትህ ምንድን ነው? እንዲያው በጥቂቱም ቢሆን እንኳን ለአለም የምትለጠው ምን ነገር አለህ?

ፍሬ ሊባዛ የሚችል መሆን አለበት፤ ካልሆነ ግን እውነተኛ ፍሬ አይደለም። "ብዙ" ማለት ፍሬን አብዙ ማለት ነው። ተባዙ ማለት ደግሞ ፍሬን አባዙ ማለት ነው።

ሙሉአት: ሦስተኛው የመብዛት ገጽታ ደግሞ ምድርን "መሙላት" ወይም "በጎደለው ስፍራ ሁሉ እንደገና መተካት" ማለት ነው። ፍሬን ማፍራት፤ ተሰጥኦዋችንን ማሻሻልና ያለንን ጥሬ ቁስ በአግባቡ ለማስተዳደር መቻል፤ በተፈጥሮው ወደ ሰፋ ስፍራ ወጥቶ መሰራጨትን ያመጣል። ምድርን መሙላት ማለት ተሰጥኦዋችንን፤ ተደማጭነታችንን፤ ጥሬ ቁሳችንን፤ ልክ እያደገና የምርቱንም ጥራት እያሻሻለ አዳዲስ መስኮችንም እየከፈተ፤ ብዙ ሠራተኞችንም እየቀጠረ እንደሚሄድ የንግድ ተቋም ማሳደግ ማለት ነው።

ይህንን በሌላ መንገድ መመልከት የፊለግን እንደሆነ እንደገና የፖምን ዛፍ ማለብ ጠቃሚ ነው። አንዲት የፖም ፍሬ የፖም ዛፍ ፍሬ እስክትሆን ድረስ ታድጋለች። በዚህም የፖም ፍሬ ታፈራለች፤ እነዚህ ፍሬዎችም ደግሞ ብዙ የፖም ዛፎች ማፍራት የሚችሉ ዘሮችን በውስጣቸው ይዘዋል። እነዚህን ዘሮች መዝራት፤ አንዲን የፖም ዛፍ ወደ ፖም ዛፍ የአትክልት ስፍራነት ፈጥነው ዩለውጣታል።

ይህ "ምድርን ለመሙላት" መስፋፋት በእኛና በጌታ የጋራ ጥረት የሚፈጸም ነው። የእኛ ድርሻ ከእርሱ በተለጠን ጥሬ ቁስ ላይ ታማኝ መሆን ነው። መስፋፋቱን የሚፈጽመው ደግሞ እርሱ ነው። በአቃቢነዋይነት ወይም በመጋቢነታችን ላይ ይበልጥ ታማኞች ስንሆን እግዚአብሔር የበለጠ ጥሬ ቁስ በእኛ ላይ ይጨምራል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መርህ ነው።

ግዙአት: መብዛት፤ መባዛትና መመላት በተፈጥሮው የመጨረሻ ውጤት ወደሆነው ወደ መግዛት የሚያመራ ነው። መግዛት ማለት ተጽእኖ ማሳደር ወይም መቆጣጠር ማለት ነው። እንዲህ ሊባል አለ፡ታዊ ገጽታ ባለው የመጨቆን ባህሪው ሳይሆን አምንታዊነት ባለው የማስተዳደር ገጽታው ነው። የንግድ ቋንቋ እንጠቀምና መግዛት ማለት ገበያውን መቆጣጠር ማለት ነው። ያለንን ጥሬ ቁስ እንደፋት ማስተዳደር እንደምንችል በተማርን መጠን እግዚአብሔር እነዚያን ጥሬ ቁሶች ያለፋቸዋል የእኛንም ተጽእኖ ያሰፋዋል። በዚህ ቋንቋ ከተነጋገርን በገበያው ላይ ያለውን ድርሻ ይጨምረዋል።

ራሳቸውንና የተሰጣቸውን ጥሬ ቁስ መሉ ለመሉ እያበዙ በሚሄዱ በማንኛውም ግለሰቦች ወይም ባለትዳሮች ውስጥና በእነርሱም ጌታ የሚያደርገው ነገር አንዳችም ገደብ የለውም። በዚህ የእርሱ በዞን የሰብአዊ ፍጥረት ውጤታማ የአትክልት ስፍራ አለምን ሁሉ መመላት ይፈልጋል። በዕንባቆም 2፥14 እንዲህ ተጽፏል፤ "ውሃ ባህርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች"። እናም ጌታ ይህንን የተስፋ ቃል አንድን ለው በአንድ ጊዜ አንድንም ትዳር በአንድ ጊዜ እየለጠ ፈጽሞታል።



ሱሳቸውንና የተሰጣቸውን ጥሬ ቁስ ሙሉ በሙሉ እያበዙ በሚሄዱ በማናቸውም ግለሰቦች ወይም ባለትዳሮች ውስጥና በእነርሱም ጌታ የሚያደርገው ነገር አንዳችም ገደብ የለውም።

ሁለት ጠቃሚ ገንዘብ ነክ መርሆዎች

አማኞች የሆኑ ባለትዳሮች በጥሬ ቁስ አቃቢነዋይነት (መጋቢነት) ሙረያ ለገንዘቢቸውና ለተገብሪቸው የሚገቡ ዋነኛ የሆኑ ሁለት መሠረታዊ ገንዘብ ነክ መርሆዎች አሉ። እነዚህም አስራት መስጠትና በጀት መበጀት ናቸው። እንግዲህ እዚህ ጋ ነው የመግዛት ዘር ማለትም የመብዛት፤ የመባዛትና የመመላት

ሚስጥር። **አስራት**፤ ያሰን ጥሬ ቁስ ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ እውቅና የምንለጥበት ሲሆን፤ **በጀት** ደግሞ የተሰጠንን ጥሬ ቁስ በማስተዋል እንድንጠቀምበት ለእግዚአብሔር ያለብንን ሀላፊነት የሚያመለክት ነው።

ውስንነት ካለው፣ እንደ ሀግ ከምንቆጥረውና እንደ ተግባራዊ ግዴታም አድርገን ከምንመለከተው፤ ከገቢያችን 10 በመቶ ከምንሰጠው ገንዘብ ይልቅ፤ አለን ለምንለው ነገር ሁሉ እውነተኛ ፈጣሪና ባለቤት እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን በመገንዘብ ለበዛልን ነገር ሁሉ ነፃ የሆነ ስጦታ መሆኑን በተረዳ ልብ አስራትን ለእግዚአብሔር ልናቀርብ ያስፈልገናል። ከዚህ በተጨማሪ ያሰን ማንኛውንም ነገር ባለንብረቶች ሳንሆን አቃቢነዋያት መሆናችንን እንድንገነዘብና ሁሉን ጨምቀን መያዝ እንደሌለብን ያሳስበናል። በተጨማሪም ቅድሚያ ልንሰጣቸው የሚገቡ ነገሮችን በአግባቡ ቅደም ተከተል እንድናሲዝ የሚረዳን፤ ያገኘነው ንብረትና ባለጠግነታችን በህይወታችን ውስጥ ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት ቀዳሚውን ስፍራ እንዳይወስድ ያግዘናል። በእርግጠኝነት አስራት እግዚአብሔር የብልጥግናችን ሁሉ ምንጭና ሰጭያችን መሆኑን የሚያሳስበን ነው፤ "... ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ስጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ" (ዘዳ 8፥18)።

አስራትን ማውጣት በእምነት ዘርን የመዝራት አንደገናም ተመልሶ የመባረክን መርህ የሚያመለክት ነው። ይህም እግዚአብሔር ዕለት ዕለት አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ እንደሚያሟላልን የገባውን ኪዳንና የማድረግ ብቃቱን መታመናችንን የሚያሳይ መግለጫ ነው። የእግዚአብሔርን ባርኮትና ብልጥግናን እንዲሁም ሀይሉን በህይወታቸው ሲለራና በየዕለቱም ያለውን ርዳታውን ማየት የሚፈልጉ ባለትዳሮች ሁሉ አስራትን ማውጣታቸው የማይታለፍ ተግባራቸው ነው። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ግልጽና የማያሻማ አድርጎ ገልጾታል፤ "በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አስራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ሚል 3፥10)።



አስፈት ማውጣት በእምነት ዘርን የመዝራት እንደገናም ተመልሶ የመባረክን መርህ የሚያመለክት ነው።

ምንም እንኳን መስጠት አስፈላጊ ቢሆንም የሰጭው ሁኔታ ግን በጣም አስፈላጊው ነገር ነው። የምንሰጥበት መንፈስ ከምንለጠው ነገር መጠን ይልቅ ለእግዚአብሔር እጅግ የበለጠ ነገር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስና ተከታዮቹ ከዕለታት በአንድ ቀን የተሰያዩ ሰዎች በመቅደሱ መዝገብ ውስጥ ስጦታቸውን የሚጥሉበት ሁኔታ እየተመለከቱ ይህን ትምህርት አስተማረ (ማር 12፥41-44 ተመልከት) ብዙዎች ባለጠጎች ብዙ ገንዘብ ይሰጡ ነበር፤ ነገር ግን አንዲት ደሀ መበለት ሁለት ሣንቲሞች ብቻ ሰጠች። ኢየሱስ መበለቲቱ በእግዚአብሔር ላይ ያላትን መታመን እያደነቀ እንዲህ አለ፤ "እውነት እላችኋለሁ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ደሀ መበለት አብልጣ ጣለች፤ ሁሉ ከትርፋቸው ጥሰዋልና ይህች ግን ከጉድለቷ የነበራትን ሁሉ ትዳሯን ሁሉ ጣለች አላቸው" (ማር 12፥43)።



የምንሰጥበት መንፈስ ከምንሰጠው ነገር መጠን ይልቅ ለእግዚአብሔር እጅግ የበለጠ ነገር ነው።

ለእግዚአብሔር ስንሰጥ በግዴታ ስሜት ሳይሆን እርሱ የበረከቶቻችን ምንጭ እንደሆነ እውቀን በደስታ እንድንሰጥ ይፈልጋል። የ1ኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ ሚሲዮናዊና የአዲስ ኪዳን ፀሐፊ የሆነው ጳውሎስ ለቆርንቶስ ከተማ አማኞች እንዲህ ብሎ ነበር፣ "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፣ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም" (2ቆሮ 9፥7)።

እንዳለመታደል ሆኖ፤ ብዙ ባለትዳሮች የቱንም ያህል ጥረት ቢያደርጉ፤ መሠረታዊ በሆነው የብልጥግና ደረጃ ወይም በተረጋጋ የገንዘብ አቋም ላይ ለመድረስ አልቻሉም። ብዙውን ጊዜ ሰዚህ ዋንኛ ምክንያት የሚሆነው የአስራትን መሠረታዊ አላማ ባለመረዳታቸው ወይም አስራት የማውጣት ተግባር ባለመፈጸማቸውና የመስጠትንና የመቀበልንም መርህ ባለመገንዘባቸው ነው።

የእግዚአብሔር የመባረክ አቅድ ዓለማዊ በሆነ መርህ የሚተዳደር አይደለም። የራሳችን ንብረት ባለቤቶች ራሳችን እንደሆንን ካሰብን፤ እንደ እራሳችን ንብረት አጥብቀን ስለምንይዛቸው ለእግዚብሔር ሥራ ለመልቀቅ ፈቃደኞች ሆነን አንገኝም። ይህ ደግሞ በበለጠ ባርኮት እንዳንባረክ መንገድ የሚዘጋ ነው። እግዚአብሔር አላማ አገልጋይ በመሆን ከሚገኘው በረከትና

እንዲሁም ለበለጠ ጥሬ ቁስ ሀላፊነት በመቀበል ከሚገኘው በረከት የሚያቋርጥ ይሆናል። ይሁን እንጂ እንደ አቃቢነዋይ (መጋቢ) ላላ አድርገን የምንይዝ ከሆነ፤ እንደ ጌታ ምሪት ለእግዚአብሔር ጥቅም እንለቃቸዋለን። በዚህም በጥቂቱ ታማኞች በመሆናችን ብዙውን ይለቅልናል።

አስራት በባለትዳሮች ሁለንተናዊ የገንዘብ እቅድ ውስጥ ዋነኛ የሆነውን ስፍራ ሊይዝ ይችላል። ማንኛውም ቤት በበጀት ወይም ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች እቅድ ሊተዳደር ይገባዋል። በጀትን መበጀት ጥሬ ቁስን ለማስተዳደር መሠረታዊ የሆነ መርህ ነው።

የአንድ ቤተሰብ በጀት የቤተሰቡን ጥሬ ቁስ በአግባቡ ለመጠቀም ከሚያስፈልገው በበለጠ ሁኔታ ውስብስብ መሆን አይገባውም። እንደ ባለትዳሮቹ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነው ነገር ምናልባትም ወጭና ገቢን መመዝገብ የሚያስችል ቀለል ያለ የሂሳብ መዝገብ ሊሆን ይችላል። በጥቅሉ የባለትዳሮቹ ንብረት ያደገና የተወሳሰበ እየሆነ በሄደ መጠን ለመቆጣጠር የሚያስችል የበለጠ ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያሟይ እቅድ ሊኖራቸው ይችላል።



የስንድ ቤተሰብ በጀት የቤተሰቡን ጥሬ ቁስ በአግባቡ ስጠቀም ከሚያስፈልገው በበለጠ ሁኔታ ውስብስብ መሆን አይገባውም።

የቤተሰቡ በጀት አበጃጀት ውስብስብነት በባለትዳሮቹ የፍላጎት መጠንና አቅድ የሚወሰን ነው። ቤት መግዛት ትፈልጋላችሁ? እንዲዚያ ከሆነ ገንዘባችሁን መደበኛ በሆነ ሁኔታ ለመቆጠብ ግልጽ የሆነ እቅድ ማድረግ፣ ዱቤ ግዥ አጠቃቀማችሁ ላይ ጥንቃቄ መውሰድና አዳችሁን ለመክፈል በምትችሉበት ሁኔታ ላይ ማሰብ ይኖርባችኋል። በሆነ ነገር ላይ መዋዕለንዋይ ማፍሰስ ትፈልጋላችሁ? እንዲህ አይነቱ እቅድ በተለይ በበጀት ወይም በገንዘብ ነክ እቅዳችሁ ላይ መስፈር ያለበትና ለተግባራዊ አፈጻጸሙም በጋራ መስማማት ያስፈልጋችኋል።

ለመዝናናት የሚያስፈልጋችሁንም ገንዘብ በበጀት እቅዳችሁ ውስጥ መያዝን ቸል አትበሉ። መዝናናት ለአካላዊ፣ ለአምሮዊና፣ ለፍልቀስሜታዊ ሁለንተናችን ጤንነት እጅግ ጠቃሚ ነው፤ ስለዚህም አስፈላጊ የሆነው ወጭ በበጀታችን ውስጥ ሊያዝለት ይገባል። ይህ ግን የግድ ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ መሆን የለበትም፤ ባልና ሚስቱ እንዲህ አይነቱን ወጭ ከገንዘብ አቅማቸው ጋር

አያገናዘቡ ሊተገብሩት ይገባል። ባልና ሚስት ሁለቱም ከቤት ውጭ ይሥሩም አይስሩም አያንዳንዳቸው መደበኛ የሆነ በራሳቸው የሚያወጡት ገንዘብ ሊኖራቸው ያስፈልጋል።

የገንዘብ አያያዝ እቅዳችሁ አይነት ወይም ውስብስብነት አንድን እቅድ በአግባቡ የማስፈራችሁንና ተግባራዊ የማድረጋችሁን ያህል ጠቃሚነት የለውም። በጀታችሁ ፍላጎታችሁን ለማሟላት በቂ እስከሆነ ድረስ ምን አይነት ቅርጽ መያዙ ያን ያህል ዋጋ ያለው አይደለም። ለሥራ ያዘጋጀነው በጀት የሚያመለክተው መልካም የሆነ አስተዳደርን፣ ጥበብ የተሞላው የአቃቢነዋይነት (መጋቢነት)፣ የታማኝነትን ጥረት ነው። እግዚአብሔር ሁለቱንም ያከብራል።

መርሆዎች

1. መልካም የሆነ አቃቢነዋይነት (መጋቢነት) ለእድገት፣ ለብልጽግናና ለደስተኝነት ጠንካራ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው።
2. እግዚአብሔር የሰውን ፍጥረት የምድርና በእርሷ ላይ ባለው ጥሬ ቁስ ሁሉ የአቃቢነዋይነት (የመጋቢነት) ሃላፊነት ሰጥቷል።
3. የገዥነት ስልጣን ያለን በነገሮች ላይ እንጂ በሰዎች ላይ አይደለም።
4. በተገለጠው በእግዚአብሔር እቅድ በእያንዳንዳችን ውስጥ፣ የታላቅነት ዘር፣ የአመራር ለጭነት ክህሎት፣ መሠረታዊ የሆነ የማስተዳደርና የመቆጣጠር ብቃት አለ።
5. አቃቢነዋይነት (መጋቢነት) ማለት በእጃችን ስለገባው ማንኛ ውም ጥሬ ቁስ ለእግዚአብሔር ተጠያቂ መሆን ማለት ነው።
6. "መብዛት" ማለት ክህሎታችንን ማውጣት፣ መልቀቅ ማለት ነው።
7. "መባዛት" ማለት መዋለድ ወይም ልጆችን መውለድ ማለት ብቻ አይደለም፣ ይልቁንም መሻሻልና ታላቅ የሆነ እድገት ማሣየት፣ ተሰጥኦዋችንን ሙሉ በሙሉ መጠቀምና በምንሠራው ነገር ሁሉ በተቻለው መጠን ውጤታማ መሆን ማለት ነው።
8. "ምድርን መሙላት" ማለት ልክ እያደገ የሚሄድ የንግድ ተቋም ያለማቋረጥ ምርቱን እያሻሻለ፣ አዳዲስ መስመሮች እየከፈተና በርካታ ስራተኞች እየቀጠረ እንደሚሄድ እንዲሁ ተሰጥኦዋችንን፣ ተደማጭነታችንንና ያለንን ጥሬ ቁስ እያሻሻልንና እያሳደግን መሄድ ማለት ነው።
9. "መግዛት" ማለት ገበያውን መቆጣጠር ማለት ነው።
10. አስራትን መውጣት እግዚአብሔርን ያለን ጥሬ ቁስ ሁሉ ባለቤት መሆኑን ማረጋገጫ የምንለጥበት ነው።
11. በጀትን መበጀት ያለንን ጥሬ ቁስ በማስተዋል ለማስተዳደር በእግዚአብሔር ዘንድ ሀላፊነት እንዳለብን የሚያመላክት ነው።

ምዕራፍ ስድስት

በጋብቻ ውስጥ የጸታዊ ግንኙነት ህብረት

ምንም እንኳን አብዛኞቹ ባለትዳሮች ከሚገጥማቸው ተግዳሮት ዋነኛው የጥሬ ቁስ አስተዳደር ጉዳይ ቢሆንም በጸታዊ ግንኙነት ሙሉ የሆነ እርካታን ማግኘት ምናልባትም ሌላው ትልቁ ተግዳሮት ነው። ብዙ ባለትዳሮች በጸታዊ ጉዳዮች እጅጉን ግራ ይጋባሉ፤ ግራ የሚያጋባቸው የጸታዊ ማንነታቸው ጉዳይ ሳይሆን ይበልጡን እርስ በእርሳቸው በአግባቡ እንዴት ጸታዊ ግንኙነት ማድረግ እንዳለባቸው ያለመገንዘባቸው ጉዳይ ነው። ወሲባዊ እርካታን አለማግኘት በብዙ ጋብቻ ውስጥ የፍርሃት የግጭትና ደስተኝነት የራቀው ህይወት ዋነኛ ምክንያት ነው። ብዙውን ጊዜ በወሲብ ያለመርካት ባለትዳሮች ከትዳራቸው ውጭ ለሚመሰርቱት ጸታዊ ግንኙነት ዋነኛው የሆነ መሠረታዊ መንስኤ ነው። ከቤታቸው ያላገኙትን በውጭ ሊፈልጉት ይወጣሉ። እጅግ ብዙውን ጊዜ ይህ ወሲባዊ ግራመጋባት የሚፈጠረው የወሲብን ባህሪና ዓላማ ባለመረዳት እንደዚሁም ደግሞ ጸታዊ ፍቅርን ለመግለጽ አመች ሁኔታዎች ያለ መኖራቸው ችግር ነው።

እንዳለመታደል ሆኖ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የተጨበጠ መልስ የሚሹ ባለትዳሮች ብዙውን ጊዜ የመሻታቸውን ያህል አጥጋቢ መልስ ለማግኘት ይቸገራሉ። በወሲባዊ ጉዳዮች ላይ ልቅነት የሚታይበት የሰለጠነው ማህበረሰብ ለዚህ ጥያቄያቸው ያህን ያህል አጥጋቢ መልስ አይሰጣቸውም። ምንም እንኳን ጸታዊ ጉዳዮች ከመቸውም ጊዜ ይልቅ በግልጽ ውይይት በሚደረግባቸው ዘመን ውስጥ ብንኖርም፤ አብዛኞቹ ተደማጭነት ያገኙ ጸታዊ ውይይቶች የተመሰረቱት በእውነት፣ በተጨባጭ ሁኔታዎችና ለዘመኑ በሚመች ጥበብ ላይ ሳይሆን በህልም፤ ተምኔታዊ በሆኑ ፍላጎቶችና በለዎች አስተሳሰብ ላይ ነው።

በዛድንበት ስፍራ ሁሉ አንገቶቻችንን ዘወር ስናደርግ ወሲባዊ በሆኑ ስእሎችና መልእክቶች ያለማቋረጥ አይኖቻችን ይያዛሉ። የመዝናኛውንና የማስታወቂያውን ኢንዱስትሪ እየመራ ያለውም ይሄው ወሲባዊ ጉዳይ ነው። የሬዲዮ ሞገድ ስርጭቶችንና የፊልም ትያትሮችንም የሞላው ይሄው ነው። ጢማችንን ከተላጨን በኋላ ከምንጠቀምባቸው ቅባቶች እስከ አውቶሞቢሎች ድረስ ምንንም ነገር ለመሸጥ ጠቀሜታ ላይ የዋለውም እርሱ ነው። ከዚህም አልፎ

በየዕለቱ የምናደርጋቸው ንግግሮች የሚዘጋጁት ወሲባዊ ጉዳዮች ታክለውበት ነው። አንዳንድ ሰዎች በንግግራቸው ውስጥ ውሲባዊ መግለጫዎች ካልጨመሩ በስተቀር ከሰዎች ጋር መነጋገር የሚችሉ አይመስሉም። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ወሲባዊ በሆነ ንግግራችንና አስተሳሰባችን፤ አብዛኛው ማህበረሰብ በጉዳዩ ላይ በሰፊው እውቀት የጎደለው ሆኖ ቆይቷል። ምክንያቱም ብዙው ንግግራችን የተመሰረተው ስህተት በሆኑና በአግባቡ ባልተረዳናቸው አስተሳሰቦች ላይ በመሆኑ ነው።

ሌላው አሳዛኝ እውነት ደግሞ በዚህ ዘመን ያለች ቤተክርስቲያን በዚህ ውይይት ላይ ልትጨምረው የምትችለው የተለየ ነገር እጅግ ጥቂት መሆኑ ነው። ይህ በተለይ አሳዛኝ የሚሆንበት ምክንያት፤ ወሲብን የፈጠረውንና አግባብነት ያለው የአጠቃቀም መርህ የመሠረተለትን እግዚአብሔር የሚያውቁና የሚከተሉ አማኞች ከማንም ይልቅ በጉዳዩ ላይ አስተዋይነት የተሞላበትና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መናገር ሲገባቸው አለመቻላቸው ነው። የአማኙ ማህበረሰብ ብዙውን ጊዜ በህዝባዊ የውይይት መድረኮች ወሲብን በሚመለከት ዝምታን መርጦ እናገኘ ዋለን። ይህ ደግሞ አንድም በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር በማፈር፣ ግራ በመጋባት፣ በራስ የመተማመን ችግር ወይም የወሲብ ርዕስ ግላዊ የሆነ ጉዳይ አለዚያም ቤተክርስቲያን ይህን ጉዳይ በአደባባይ እንድትገልጠው መንፈሳዊ ብቃት የሌለው ተደርጎ በመቆጠሩ ሊሆን ይችላል።

ወሲብ በእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ጎን የሚተው ጉዳይ አይደለም። ሰዎች ሲገምቱት ከሚችሉት በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብና ስለወሲባዊ ግንኙነት የሚለው ብዙ ነገር አለው። እግዚአብሔር ለሰብአዊው ፍጡር ባለው እቅድ ውስጥ ወሲብ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። "እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ እንደ ምሳሌውም ፈጠረው። ወንድና ሴት አድርጎም ፈጠራቸው" (ዘፍ 1÷27) "ወንድና ሴት" የጾታ ልዩነትን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ገና ነገሮችን ሁሉ ሲመሠርት ወሲብም መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ ነበር። እግዚአብሔር ለመጀመሪያዎቹ ሰብአዊ ባለትዳሮች የሰጠው ትእዛዝ፤ ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉዋት ግዙአትም የሚል ነበር (ዘፍ 1÷28)። ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተመለከትነው ምንም እንኳን ይሄ ትእዛዝ በመሠረታዊ ደረጃው መግዛትንና በተሰጠው ጥሬ ቁስ ላይ ያለ አቃቢነዋይነት

(መጋቢነትን) የሚመለከት ቢሆንም፤ በተጨማሪ ደግሞ ወሲባዊ ጉዳዮችን አስመልቶ የተቀመጠ መሰረታዊ መርህ ነው።



ወሲብ በእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ጎን የሚተው ነገር አይደለም።

በሰብአዊው ሰው የህይወት ልምምድ ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ በመሆኑና በዚህም ዘመን በርዕሱ ላይ በሰፊው የተሰፋፋ የተሳሳተ አመለካከት በመኖሩ ምክንያት፤ ባለንበት ማህበረሰብ ውስጥ የተሰፋፋውን ይህንን ስህተት የሆነና የተዛባ አመለካከት ለመቃወም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጾታዊ ጉዳዮች ወዳለው የሀሳብ መረዳት መምጣት እጅግ ወሳኝ ነው። ወሲብ ማለት ምን ማለት እንዳልሆነና ምን ማለትስ እንደሆነ እንዲሁም አላማው ምን እንደሆነ በመተንተን፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አውዱ ውስጥ ባለው ትዳር፤ አግባብነት ያለው ወሲባዊ ግንኙነት ምን መሆን እንደሚገባው መመሪያ የሚሆኑ ነገሮችን እናስቀምጣለን።

ወሲብ ፍቅር ማለት አይደለም

ዓለማዊ በሆነው አመለካከት ወሲብና ፍቅር አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው። ያለ ብዙ ትኩረት የዛሬዎቹ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ መጽሐፍት፣ ፊልሞችና የቴሌቭዝን ፕሮግራሞች እንኳን ይህንን አስረግጠው ይነግሩናል። በነኝህ የህዝብ መገናኛዎች የምናገናኛቸው አብዛኞቹ ዘገባዎች ወሲብንና ፍቅርን ሊነጣጠሉ እንደማይችሉና ልዩነትም እንደሌላቸው አድርገው ይነግሩናል። የዚህ አይነቱ ፍልስፍና መነሻ ምንጭ የሆነው፤ "የምትወደኝ ከሆነ፤ ትፈቅድልኛለህ" የሚል አመለካከት ነው። እንዲያው ለነገሩስ፤ ፍቅርና ወሲብ አንድ ከሆኑ አንድን ሰው እወድሀለሁ እያልን ከእርሱ ወይም ከእርሷ ጋር ወሲብን ለመፈጸም እንዴት ፈቃደኛ ላንሆን እንችላለን?

ከዚህ አመለካከት ጋር በጣም ተያይዞ የሚቀርበው ደግሞ ወሲብ የፍቅር ማረጋገጫው ነው የሚል ነው። ምን ያህል ጊዜ ነው እንደነዚህ አይነት አመለካከት ያላቸውን መጽሐፍትና ፊልሞች በየአጋጣሚው ያነበብነው? የተመለከትነውስ? አንድ ወንድና አንድ ሴት ይገናኛሉ ይፈቃቀዳሉም! ከዚያ በኋላ የምናውቀው ቀጣዩ ነገር አብረው አልጋ ላይ መሆናቸውን ነው። ይህንን ነው እንግዲህ "ይዋደዳሉ" ብለው የሚነግሩን። ወሲብን በማድረጋቸው ምክንያት የግድ ተፋቅረዋል፤ አልተፋቀሩም እንዴ? ምናልባትም አንዳቸው

ወይም ሁለቱም ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ ያላቸው ሲሆኑ ይችላሉ፤ በመሆኑም ዝሙትን እያደረጉ ይሆናል፤ ይህ ግን ከቁጥር ውስጥ የማገባ አይደለም። ዋጋ ያለው ነገር እንደሆነ ተደርጎ የሚቀርበው "መዋደዳቸው" ነው። ወደ አልጋ ይሄዳሉ፤ የስሜታቸውን ያደርጋሉ፤ በሚቀጥለው ጠዋት ከአልጋ ይነቃሉ በቃ ሁሉ ነገር መልካም ነው።

ዓለም ስዕሉን የምትሰለው እንዲህ አድርጋ ነው። እንደነዚህ አይነት መጽሐፍትና ፊልሞች የእንደዚህ ያለውን አመለካከት ጎጂ ጎን ቢገልጹ እንኳን እጅጉንም አልፎ አልፎ ብቻ ነው። በገሀዱ አለም ውስጥ እንዲህ አይነቱ ወሲባዊ ግንኙነት በብዙ ሰዎች ውስጥ ራስን እንደወንጀለኛና ተራ ቆሻሻ ነገር አድርጎ የመቁጠር ስሜትንና ሀፍረትን የሚፈጥር በተጨማሪም ስኬት አልባነትን የሚያመለክት ነው። ለጊዜው አስደሳች ሲሆን ይችላል ነገር ግን የባዶነትን ስሜት ጥሎ የሚሄድ ነው። ብዙ ጊዜም ለምን እንዲህ እንደሚሆን አያውቁትም።

ወሲብና ፍቅር አንድ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ ዓለም እግዚአብሔር ወሲብን የገለጠበትን፣ በእርሱም ያለውን ደስታና የመባዛት ሀሳብ የምትቃወምበት እንደኛውና ትልቁ ውሸት ነው።



ወሲብና ፍቅር አንድ ናቸው የሚሰው አስተሳሰብ ዓለም እግዚአብሔር ወሲብን የገለጠበትን፣ በእርሱም ያለውን ደስታና የመባዛት ሀሳብ የምትቃወምበት አንደኛውና ትልቁ ውሸት ነው።

ወሲብ መንፈሳዊ ስጼደሰም

ፍቅር:- እውነተኛ የሆነው ፍቅር በባህሪው መንፈሳዊ ነው። ወሲብ ግን አይደለም። ወሲብ መቶ በመቶ አካላዊና ኬሚካላዊ ነው። ለዚህም ነው ወሲብንና ፍቅርን አንድ አድርገን ማየት ስንጀምር ችግር ውስጥ የምንገባው። ፍቅር በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ መንፈሳዊ አንድነት ነው፤ መንፈስ ከመንፈስ ጋር የሆነ ጥምረት ወሲብ የሁለት ሰዎች አካላዊ የሆነ ሥጋ ከስጋ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ነው። እግባብነት ባለው አጠቃቀሙ ወሲብ ማራኪ የሆነና የመንፈሣዊ ጥምረት ውጤት የሆነው እውነተኛ ፍቅር አካላዊ መግለጫ ነው።



ፍቅር በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ መንፈሳዊ አንድነት ነው። መንፈስ ከመንፈስ ጋር የሆነ ጥምረት። ወሲብ የሁለት ሰዎች አካላዊ የሆነ-ሥጋ ከስጋ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ነው።

ይህንን ልዩነት መረዳት፤ መንፈሳዊ ከሚመስሉና በዙሪያችን ከሚንሳፈፉ፤ "ወሲብ ወደር የማይገኝለት መንፈሳዊ ጥምረት ነው ወይም ሲሆን ይችላል፤ እንዲሁም ደግሞ ከህይወት መንፈሳዊ ነገሮች ጋር ንክኪ ያለው ጉዳይ ነው" በማለት ሲያሳምኑንን ከሚሞክሩ በርካታ አመለካከቶች ሰለባነት እንድንድን ይረዳናል። ከእውነታው ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ወሲብ ደስታን የሚያጭር አካላዊ የሆነ ልምምድ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ግንኙነት ውስጥ ምንም መንፈሳዊነት የለበትም። ወሲባዊ ግንኙነት ከሌላው ሰው ጋር መንፈስ ለመንፈስ በሆነ ግንኙነት እንድንጣመር አያደርገንም። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ላይ ወሲባዊ ልምምድ እግዚአብሔርን እንድናይ ወይም ወደ እርሱ ሲያቀርበን እንደሚችል አያስተምረንም። ወሲብ ለብአዊ የሆነው የሰው ፍጥረት አካል ውጤት የሆነ ከመንፈሳችንም ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነው። ይልቁንም ደግሞ በእግዚአብሔር የተሰጠን ወሲባዊ ርሃባችን በመንፈሳችን ቁጥጥር ሥራ ሲውልና ወደ መገዛት ሲመጣ የተገባው ነው። መንፈሳችን በስጋችን ላይ ሲሰለጥን ያስፈልገዋል።

ወሲብ ፍላጎት ነው

ወሲብ ፍላጎት ነው። እግዚአብሔር በፈጠረን ጊዜ በውስጣችን ካኖራቸው በርካታ ፍላጎቶች መካከል አንዱ ወሲብ ነው። ነገሮችን የመምራትና የመቆጣጠር መሻት፣ አንድን ነገር ለማግኘት የምናደርገው ብርቱ ጥረት፣ ለነገሮች ያለን ከፍተኛ ጉጉት፣ ለሆነ ነገር ያለን ቁርጠኝነትን የመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ ምንም አይነት ስም እንስጣቸው ዞሮ ዞሮ ፍላጎቶች ናቸው። የምግብ ፍላጎት፣ የውሃ ፍላጎት፣ የመተኛት ፍላጎት፣ የወሲብ ፍላጎት ለእግዚአብሔር ያለን ፍላጎት . . . እያልን መቀጠል እንችላለን። እነዚህ ሁሉ እግባብነት ያላቸው እውነተኛ ፍላጎቶች ናቸው ። እግዚአብሔር ፍላጎት እንዲኖረን አድርጎ ነው የፈጠረን።

የማንኛውም ፍላጎቱ ጥንካሬ የሚወሰነው የፍላጎቱ አቅም በተንቀሳቀሰበት መጠን ነው። ማንኛውም ፍላጎት የሚጀምረው

በአቅሙ መጠን በዜሮ (በባዶ) ደረጃ ላይ ሆኖ ነው። ፍላጎትን የማሟላት ብቃት ሁልጊዜም እንዳለ ነው፤ ይሁን እንጂ መንቀሳቀስ እስክንጀምር ድረስ የብቃቱ መጠን ደረጃው ዜሮ (ባዶ) ነው። አንድ ህፃን የምግብ ፍላጎትንና የመመገብ አቅሙን የሚያዳብረው፤ ገና ከመወለዱ በፊት ከእናቱ በእትብቱ በኩል ለህይወት አስፈላጊ የሆነውን ምግብ በመቀበል ነው። ስለዚህም ነው አንድ ህፃን ከተወለደ በሁዋላ መጀመሪያ ሊያደርገው የሚፈልገው መመገብ የሚሆነው፤ የምግብ ፍላጎቱ መንቀሳቀስ ይጀምራል።

ምንም እንኳን አሁን የተወለደ ህፃን የምግብ ርሃብን ቢያውቅም የርሃቡ አቅም ግን ገና ትንሽ ነው። ህፃን የሚራበው ፍላጎቱ በተንቀሳቀሰበት መጠን ብቻ ነው። ህፃናት የተለማመዱት ከመወለዳቸው በፊት በእትብት በኩል የሚተላለፍን ፍሳሽ ምግብ፤ ከዚያም በሁዋላ የጡት ወይም የዱቄት ወተት፤ በመቀጠልም ቅመምና ጨው ያልበዛበትን ምግብ ወይም ደግሞ ስኳርና ማንኛውንም ሌላ ጣፋጭነት ያለውን ነገር ነው። እነዚህ ፍላጎቶች መንቀሳቀስ ከመጀመራቸው በፊት ልክ እንደ ሞቱ ያህል ናቸው። ወላጆች ናቸው ተጨማሪ የሆኑ ምግቦችንና ጣፋጭ ኬክ፤ ከረሜላ ተጨማሪም ጣፋጮችን በማለማመድ እነዚህን ፍላጎቶች የሚያንቀሳቅሷቸው። ከዚያ በፊት ግን ህፃኑ ለእነዚህ ነገሮች ፍላጎት አይኖረውም በመሆኑም እነርሱን ለማግኘት መሻት የለውም።

ርሃብ የሚሰማን በሆዳችንና በአንጀታችን ውስጥ ያሉ ኬሚካሎች መንቀሳቀስ ሲጀምሩና ምግብ እንደሚያስፈልገን ለአንጎላችን መልዕክት ሲያስተላልፉ ነው። የመጨረሻውን ምግብ ከበላን ምን ያህል ጊዜ እንደሆነን ያለውን የጊዜ መጠን ሌሎች ሁኔታዎችን ለምሳሌም ለመመገብ ከፍተኛ መሻት ያለንን የምግብ አይነቶች መሠረት አድርጎ የፍላጎታችን መጠን እየጨመረ ይሄዳል። በመመገብ እስክንረካ ድረስ የርሃብ ስሜታችን እያደገ መሄዱን ይቀጥላል። ተመግበን ከጠገብን በኋላ እንደገና ሌላ የመገቢያ ጊዜ ደርሶ እስኪንቀሳቀስ ድረስ እየወረደ ይሄዳል።

አስደሳች የሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ፤ ይሁን እንጂ ያልረካው ፍላጎት በዝግታ እየወረደ ይሄድና ይጠፋል። ረዘም ያለ የጾም ጊዜ የሚያሳልፉ ሰዎች ይህንን በፍጥነት ያውቁታል። የመጀመሪያዎቹ የጾም ቀኖች ጠንካሮች የሚሆኑት የምግብ ፍላጎታችን እንደገና ተጠናክሮ በመከሰቱ ምክንያት ነው። ሰውነታችን መለማመድ ከጀመረ በኋላ ግን ጾመ ቀላል ይሆናል።

ማስረዳት የምፈልገው ነጥብ ይህ ነው። ፍላጎቶቻችንን ማርካት ብቻ ሳይሆን መቆጣጠርም እንችላለን። ማንኛውም ፍላጎት እንደዚያ ነው። እርሃባችንና አንድን ነገር ለማግኘት ያለን ከፍተኛ ፍላጎት በፈቃዳችን ቁጥጥር ሥር የሚውሉ ናቹው። እንደ ሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ለወሲባዊ ፍላጎትም ይህ የሚሠራ እውነት ነው።

ጳውሎስ በኢፌያዊቷ ከተማ በተሰሎንቄ ለሚኖሩ አማኞች በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን መልዕክቱ ይህን ግልጽ አድርጎታል። "የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤ ከዝሙት እንድትርቁ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አህዛብ በፍትወት ምኞት አይደለም እንጂ ከእናንተ አያንዳንዱ የራሱን ዕቃ በቅድስናና በክብር ያገኝ ዘንድ" (1ተሰ 4፥3-5)። ይህን ምንባብ እጅግ አስደሳች የሚያደርገው "ስኩሆስ" (አካል) የሚለው የግሪክ ቃል በተጨማሪም "ሚስት" ተብሎ ሊተረጎም መቻሉ ነው። በዚህ መንፈስ ከሆነ ጳውሎስ እየሰነዘረ ያለው "ባሎች ከገዛ ሚስቶቻቸው ጋር በተቀደሰና በከበረ አኗኗር መኖርን ሊማሩ ይገባቸዋል የሚል ሃሳብ ነው። በሁለቱም መንገድ ቢሆን መልዕክቱ የሚያተኩረው ወሲባዊ ፍላጎትን ስለመቆጣጠር፤ በጋብቻ ውስጥ ብቻ ለሚሆን ግንኙነትም ጠበቆ ስለማቆየት ነው።



ርሃባችንና ስንድን ነገር ለማግኘት ያለን ከፍተኛ ፍላጎት በፈቃዳችን ቁጥጥር ሥር የሚውሉ ናቹው።

ስለ ወሲብ የእግዚአብሔር ዓላማ

እግዚአብሔር የፈጠረን ወሲብን መፈጸም የምንችል ወንድና ሴት አድርጎ ነው። የወሲብ ፍላጎታችንም እንዲሁ በሰውነታችን ውስጥ አብሮ የተፈጠረ ነገር ነው። እኛ የወሲብ መፈጸሚያ አካላት ነን ማለት እንችላለን። ፍላጎትና እውነተኛ የሆነ ውጤታማ ወሲባዊ መግለጫ የሚከሰተው፤ እግዚአብሔር በመሠረተውና ባከበበለት አጥር ውስጥ በጥንቃቄና በተወሰነው ሁኔታ ውስጥ ብቻ ነው። ከነዚህ አጥር ውጭ ችግሮች ይከሰታሉ፤ ወንጀለኝነት፤ ሀፍረት፤ ፍርሃት፤ ሀዘን፤ ግራ መጋባትና የልብ ስብራት ይከተላሉ። በዚህ አጥር ውስጥ ግን አንዳቸው ለአንዳቸው ብቻ የተሰጡ ባልና ሚስት፤ ታላቅ ነፃነት፤ መተሳሰብና ደስታ አላቸው።

ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የሰው ወሲባዊ እንቅስቃሴ ሦስት ቀዳሚ አላማዎች ምን እንደሆኑ ከተለያዩ ስፍራዎች ላይ

እንቃርማለን። ልጆችን መውለድ፣ በመዝናናት መሰቀቅ እንዲሁም ግንኙነት።

ወሲብ ልጆችን ስለመውለድ ነው

አስቀድመን እንደተመለከትነው መዋሰድ በእግዚአብሔር ልብ አስቀድሞውንም የነበረና ሰውም የሰጠው ትእዛዝ እንዲፈጽመውም የጣለበት ሀላፊነት ነው። "እግዚአብሔር ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት ግዙአትም የባሕርን አሳዎችና የሰማይንም ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙዋቸው" (ዘፍ 1፣28)። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የተፈጠረውን ፍጥረት እንዲገዛ ነው። ይህንን ተግባር ለመፈጸም አንደኛው መንገድ መዋለድ ነው። በመባዛት ምድርን መመላት።

ለዚህ የፍጻሜ ውጤት ነው እግዚአብሔር ሰውን በሁለት ጾታ የፈጠረው፣ ወንድ ሰው እና ሴት ሰው። ወንዱና ሴቷ ከአንድ መንፈስ ከአንድም ቁስ አካል የተገኙ ነበሩ። አስቀድሞ እግዚአብሔር ወንዱን አዳምን ፈጠረ። በመቀጠልም ከአዳም ጎን ሴቷን ሄዋንን ፈጠረ፣ ለአዳምም አቀረባት፣ "አዳምም አለ፣ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋየ ናት እርስዋም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል፣ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።" (ዘፍ 2፣23-24)። "አንድ ስጋ" የሚለው ቃል በባልና በሚስት መካከል የሚፈጠረውን አካላዊ አንድነት የሚያመላክት ነው።

መጽሀፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰው ፍጥረት ባለው አቅድ ውስጥ መዋለድ መሠረታዊ የሆነው ክፍል እንደሆነ የሚያስገነዝበው በዙ ሌሎች መረጃዎችን ይሏል። አግባብነት ባለው ሁኔታ ወሲብ የከበረና ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰመባረክ ምንጭ ነው።

"እንዲህም ይሆናል፣ ይህችን ፍርድ ሰምተህ ብትጠብቃትና ብታደርጋትም፣ አምላክህ እግዚአብሔር ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳንና ምህረት ለአንተ ይጠብቅልሃል፣ ይወድድህማል፣ ይባርክህማል፣ ያበዛህማል፣ ይሰጥህ ዘንድ ለአባቶችህ በማለላቸው ምድር የሆድህን ፍሬ፣ የመሬትህንም ፍሬ፣ እህልንም፣ ወይንንም፣ ዘይትንም፣ የከብትህንም ብዛት የበግህንም መንጋ ይባርክልሃል። ከአህዛብም ሁሉ ይልቅ የተባረክ ትሆናለህ። በሰውና በከብትህም ዘንድ ወንድ ቢሆን ወይም ሴት ብትሆን መካን አይሆንብህም" (ዘዳ 7፣12-14)።

በዚህ ሥፍራ በእርግጥ እግዚአብሔር ለህዝቡ፣ ለእርሱ ታዛዦችና ታማኞች ቢሆኑ ልጅን ያጡ መካኖች እንደማይሆኑ ቃል እየገባላቸው ነው። እግዚአብሔር የራሱ የሆኑት ህዝብ እንዲዋለዱ ይፈልጋል። አለምን በልጆች በመሙላት ምድር በክብሩ እንድትሞላ ይሻል።

> "እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው
> የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው
> በሀያል እጅ እንዳሉ ፍላፃዎች
> የጎልማሳነት ልጆች እንዲሁ ናቸው።
> ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው
> ጠላቶቻቸውን በአዳባባይ በተናገሩ ጊዜ እርሱ
> አያፍርም" (መዝ (127)፣3-5።

ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ውርሶች ናቸው። "ቢን" (ወንድ ልጅ) የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሰፋ ያለ የተለያየ ትርጉም ያለውና ወንዶችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ልጆች የሚያካትት ነው። ውርስ ማለት ንብረት ማለት ነው። ልጆች የእግዚአብሔር ንብረቶች በመሆናቸው እግዚአብሔር እርግዝናን፣ ልደትን አስተዳደግን የሚመለከተው አትኩሮትን ሰጥቶ ነው። ለዚህም ነው ውርጃና በልጆች ላይ የሚደርስ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃት በጣም ከፍተኛ የሆኑ ሀጢያቶች የሚሆኑት። እነዚህ የእግዚአብሔርን ንብረቶች የሚያበላሹ ናቸው።



ልጆች የእግዚአብሔር ንብረቶች በመሆናቸው እግዚአብሔር እርግዝናን፣ ልደትንና አስተዳደግን የሚመለከተው አትኩሮትን ስጥቶ ነው።

የወሲብ ዋነኛ አላማ መባዛት መሆኑን ለሚጠራጠር ሲጠቀሱ የሚገባቸው በርካታ ምንባቦች ቢኖሩም ነገሩን በግልጽ ለማብራራት እነዚህ በቂዎች ናቸው።

ወሲብ ለመዝናናት

መዋለድ ዋነኛውና ጠቃሚው የወሲብ ጎን ከሆነ መዝናናት ትርፍ የሆነው ጎኑ ይሆናል። ወሲብን የምንፈጽመው ለመዋለድ ብቻ ሣይሆን ከእርሱ የሚገኘውን ደስታ ለማግኘት ነው። እስኪ

እውነቱን እንነጋገር፤ ወሲብ አስደሳች ነገር ነው። እግዚአብሔር በዚህ እንድንደሰት ይፈልጋል፤ እንዲያ ባይሆን ለምን እጅግ ማራኪ አድርጎ አቀደው?

አማኞችን ጨምሮ እንዳንድ ሰዎች ወሲብን በሚመለከት እንዲህ ያለውን ግልጽነት አይፈልጉትም። የእግዚአብሔር ቃል ያለችግር ወሲባዊ ጉዳዮችን ዘርዝሮ በግልጽ የሚናገርባቸውን እንዳንድ ክፍሎች ሲመለከቱ ሀመማቸው ይጨምራል። ያም ሆነ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ወሲባዊ ጉዳዮችን ያካተቱ በተለይም ደግሞ እንደ መሀልየ መሀልይ ዘ ለሎሞን የመሳለሉ ክፍሎች ያሉት መሆኑ እውነት ነው። ይህ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በቋንቋው ግልጽና ገሀዳዊ በመሆኑ ብዙ አማኞች ተምሳሌታዊ ይዘቱ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ያለውን ፍቅር የሚያመለክት በመሆኑ አብዝተው ይደሰታሉ። ምናልባትም እርግጥ ነው የዚህ እይነት ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ የለለሞን ዝማሬ በጋብቻ ፍቅር ውስጥ ያለውን ደስታና በረከት የሚገልጽ ግልጽና ምንም ያልተሸፋፈነ የፍቅር ዝማሬ ነው።

[redacted] በወሲብ እንድንደሰት እግዚአብሔር ይፈልጋል፤ እንደዚህ ባይሆን ኖሮ እንዲህ ማራኪና እጅግ አስደሳች አድርጎ ለምን አቀደው?

መጽሐፍ ቅዱስ በጋብቻ ውስጥ ያለው ወሲብ ከመዋለድ አልፎ የሚያዝናና እንደሆነ እንደሚናገር ለማሳየት አንድ ምሳሌ ብቻ መጥቀስ በቂ ነው። እስኪ በመሀልየ መሀልይ ምዕራፍ አራት ቁጥር 1፣3፣5፣9-16 ያለውን እንመልከት።

"ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
እነሆ እንቺ ውብ ነሽ
በእይነርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ
ፀጉርሽ በገለአድ ተራራ እንደሚወርድ
እንደ ፍየል መንጋ ነው . . .
ከንፈሮችሽ እንደቀይ ሀር ፈትል ናቸው
አፍሽም ያማረ ነው
በእይነ ርግብ መሸፈኛሽ ውስጥ ጉንጭና ጉንጭሽ
እንደተከፈለ ሮማን ናቸው . . .

ሁለቱ ጡቶችሽ መንታ እንደተወለዱ
በሱፍ አበባ መካከል እንደሚሰማሩ
እንደ ሚዳቋ ግልገሎች ናቸው . . .
እህቴ ሙሽራየ ሆይ ልቤን በደስታ አሳበድሽው
እንድ ጊዜ በአይኖችሽ፤ ከአንገትሽስ ድሪ በአንዱ
ልቤን በደስታ አሳበድሽው
እህቴ ሙሽራየ ሆይ ፍቅርሽ እንዴት መልካም ነው!
ፍቅርሽ ከወይን ጠጅ ይልቅ እንዴት ይሻላል!
የዘይትሽ መአዛ ከሽቱ ሁሉ
ሙሽራየ ሆይ ከከንፈሮችሽ ማር ይንጠባጠባል
ከምላስሽ በታች ማርና ወተት አለ
የልብስሽም መአዛ እንደሊባኖስ ሽታ ነው
እህቴ ሙሽራየ የተቆለፈ ገነት
የተዘጋ ምንጭ የታተመም ፈላሽ ናት።
ቡቃያሽ ሮማንና የተመረጠ ፍሬ
ቆዕ ከናርዶስ ጋር ያለበት ገነት ነው።
ናርዶስ ከቀጋ ጋር የሽቱ ሣርና ቀረፋ ከልዩ ልዩ እጣን ጋር
ከርቤና እሬት ከክቡር ሽቱ ሁሉ ጋር
አንቺ የገነት ምንጭ የህይወት ውሃ ጉድጓድ
ከሊባኖስም የሚፈስ ወንዝ ነሽ
የሰሜን ነፋስ ሆይ፣ ተነስ
የደቡብም ነፋስ ና
በገነቱ ላይ ንፈስ
ሽቱውም ይፍሰስ
ውዴ ወደ ገነቱ ይግባ

መልካሙንም ፍሬ ይብላ"

ይህ ገሀድ የወጣና ግልጽ የሆነ በሁለት ፍቅረኞች መካከል የተደረገ ወሲባዊ ጨዋታ (ንግግር) ነው። ነገር ግን ምንባቡ በተጨማሪ ፍቅረኞቹ ባልና ሚስት መሆናቸውን ይናገራል። አፍቃሪው ፍቅረኛውን ሦስት ጊዜ "የእኔ እህት፣ የእኔ ሙሽራ" እያለ ይጣራል። እነዚህ ጥቅሶች ባልየው የሚስቱን አካላዊ ውበት ዘና ብሎ እያወደሰ ሲገልጽ ያመለክታሉ። በቁጥር 12 ላይ "የተቆለፈች ገነት"፣ የተዘጋ ምንጭ እንዲሁም "የታተመም ፈሳሽ" የሚሉት ቃላት የሚገልጹት በጋብቻዋ ምሽት የተገኘውን ድግልናዋን ነው። በባሏ አይኖች ፊት እርሷ "የውበት ገነት"፣ "የተመረጠች የገነት ፍሬ"፣ መልካም ጠረን ያላት "እጣን"፣ እጅግ የተወደደም "ቅመም" ነች። በቁ. 16 ላይ ደግሞ ሙሽሪት ለባሏ የሰጠችውን የፍቅር ቃል ያመለክታል። የእርሱ ወደሆነው ገነት መጥቶ የተመረጠውን ፍሬ እንዲበላ ትጋብዘዋለች።

የቋንቋው ግልጽነትና ገሀዳዊ ባህሪው የሚያስደነግጥህ ከሆነ እግዚአብሔርን ያላስደነገጠው መሆኑን ልብ በል። ወሲብን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው፤ እኛም ደስታውን እንድናጣጥመው ይፈልጋል። አግባብነት ባለው የጋብቻ አውድ ውስጥ ባለ የወሲብ ግንኙነት አስፈሪ የሆነ ስህተት ያለበት ወይም ግብረገብነት የጎደለው ነገር የለም።

ወሲብ ደስታ ነው ማለት በባልና በሚስት መካከል በሚደረግ ግንኙነት ውስጥ የሚከሰት ደስታ ነው ማለት ነው።

ወሲብ ስለግንኙነት ነው

እግዚአብሔር ወሲብን ያቀደበት ሦስተኛው ምክንያት ግንኙነት ነው። ወሲብ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባውን ግልጽና እውነተኛ የንግግር ልውጥ የሚተካ ነገር አይደለም፤ ይሁን እንጂ ፍቅር በነገሰበት ሁኔታ ውስጥ ቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ ወሲብ ከፍ ያለ አንድነትንና ህብረትን ይፈጥራል። ከባልና ሚስት የበለጠ ማንም ቢሆን በአካል፣ በአይምሮም ይሁን በስሜት እጅግ የተቀራረበና የተያያዘ ሊሆን አይችልም። ጓደኝነታቸውም ወደረኛ ሲኖረው አይገባም፤ ምድራዊ የሆነ የትኛውም ግንኙነት ቀዳሚ ስፍራ አይሰጠውም። "ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን

ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ (ዘፍ 2፥24) ከሚለው ቃል ጀርባ ያለው እውነት ይሄ ነው።

በእግዚአብሔር የመሰረት ደረጃ ወሲባዊ እንቅስቃሴ በጋብቻ ክልል ውስጥ የታጠረ ነው። የባልና የሚስት ግንኙነት አንድ ለአንድ የሆነ ግንኙነት ነው። እንደዚሁም ደግሞ ወሲባዊ ጨዋታና ግንኙነት እጅግ የተለየ አንድነት ያለበትን ህብረት የሚያመጣ በመሆኑ አንዳቸው ለአንዳቸው ብቻ ጠብቀው ሊጋሩት የሚገባ ነው።

ስንዳችሁ ስለንዳችሁ የወሲብ ፍላጎት ምላሽ የምትሰጡ ሁኑ

ብዙውን ጊዜ በትዳር ውስጥ ለወሲባዊ ስንፈትና አለመርካት ምክንያት የሚሆነው የባልና የሚስት ወሲባዊ ተግባርን ለመፈጸም አለመቻላቸው ሳይሆን፤ የጥንዶቹ ለወሲባዊ ጉዳይ ንቁዎች ያለመሆን፣ መረዳትን ያላገኙና አንዳቸው የአንዳቸውን ወሲባዊ ፍላጎት ለማሟላት ዝግጁዎች ያለመሆናቸው ችግር ነው። ውጤታማ የሆነ ግንኙነትን በሚመለከት እንደገለጽነው ሁሉ ወሲብንም አስመልክቶ ለጥቃቅን ነገሮችም ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው።

ከራሳችን የግል ፍላጎትና እይታ በላይ የትዳር ጓደኞቻችንን ልንመለከት ፈቃደኞች ልንሆን ይገባናል። በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እኛ የወሲብ ፍላጎት የሌለን ብንሆን የትዳር ጓደኛችንም የግድ እንደዚያው ይለማዋል ማለት አይደለም። እንዲህ አይነቱን ግምታዊ ድምዳሜ መውሰድ ለግንኙነታችን ጤናማነት መልካም አይደለም። እዚህ ጋር ነው እንግዲህ የበለለና ውጤታማ ግንኙነት የማድረግ ጥበብ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው። በጋብቻ ውስጥ ውጤታማና ደስተኛ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት የሚወለነው፤ ባልና ሚስት ፍላጎታቸውንና ሀሳባቸውን አንዳቸው ለአንዳቸው በማሳወቅ በግልጽነት፣ በፍቅር፣ በመቀባበልና በመደጋገፍ የሚመች ሁኔታን በመፍጠራቸው ነው።

ምንም እንኳን በቅርብ አመታት ውስጥ የሚታይ ለውጥ ቢኖርም፤ በተለይም ደግሞ በምዕራቡ የአለም ክፍል ከባሎቻቸው ጋር ወሲብን ለመፈጸም የማነሳሳት ተግባር መፈጸም አሁንም ድረስ በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ባሉ ሌቶች አሳፋሪ ስሜትን የሚፈጥር ነው። በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ እንዲህ ያለው የሚስቶች ድፍረት ተሰምቶም የማይታወቅ ነው። ሌሎች ደግሞ ሴቶች ወሲብን

ቢቀለቅሉ አንደ ስድ አደግና ራሳቸውን ከወንድ ላይ አንደጣሉ አንዲያምኑ ተደርገው ነው ያደጉት። ምክንያቱ ምንም ይሁን፤ ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ቢኖራቸውም እንኳን ባሎች የመጀመሪያውን አንቅስቃሴ እስኪያደርጉ ድረስ ሚስቶች በዝምታ ነው የሚቆዩት።

ወንዱን በሚመለከት፤ ምናልባትም የሚስቱን ዝምታ የሚተረጉመው ፍላጎት እንደሌላት እድርጎ በመሆኑ ይተዋታል፤ ለዚህ ምክንያት የሚሆነው ደግሞ ሚስቱ አንዳስገደዳት እንዳይሰማት በማሰቡ ነው። በውጤቱም ሁለቱም ለቀናት፣ ለሣምንታት ወይም ለወራትም ቢሆን እንኳን ችግር ውስጥ ይገባሉ፤ አንዳቸው ለሌላቸው ፍላጎታቸውን መግለጽ ባለመቻላቸው ምክንያት በወሲብ ምድረ በዳ ሲባዝኑ ይከርማሉ። ያልተሟላ ፍላጎታቸው ከሚችሉት በላይ የሄደ እንደሆነ ደግሞ ከትዳር ግንኙነታቸው ውጭ ወሲባዊ እርካታን ለማግኘት ሊፈልጉ ይችላሉ።

ባልና ሚስት ይልቁንም ደግሞ ሚስቶች ወሲባዊ ፍላጎታቸውን አስመልክቶ በግልጽ መናገርን ሲማሩ ያስፈልጋቸዋል። ሚስቶች ሆይ፤ ባሎቻችሁን በሚመለከት የውስጥ ስሜታችሁን ለመግለጽ ለቀቅ ያለ ሁኔታ ቢኖራችሁ መልካም ነው። እናንተ እንዲህ ለቀቅ ያለ ሁኔታን ካላሳያችሁት ምናልባት ሌላዋ ሴት ልታሳየው ትችላለች። ባላችሁ ህጋዊ ተቃውሞ ሊቀርብበት የማይችል ወሲባዊ ፍላጎት አለው፤ እናም እናንተ ልታሟሉለት ካልቻላችሁ ሌላዋ ልታደርገው ትችላለች። የመገመት ችሎታችሁን ተጠቀሙ! ደፋሮች ሆኑ! ጀብድ የተሞላበትን ድንቅ ነገር እድርጉ፣ አንዳንድ ጊዜም ወሲባዊ ሁኔታን ለማነሳሳት ፍርሃት አይግባችሁ። ባላችሁን በትንኮሳችሁ እስደንቁት! ይህን እስተውሉ፤ ባላችሁ እንደ ወንድ በሚያየው ነገር ሊነቃቃና ሊቀስቀስ የሚችል ነው። የሚነቃቃበትን አንድ ነገር ስጡት!

ባሎችም ደግሞ እንዲዚሁ፤ ሚስታችሁ እንደ ሴት በመዳሰስና በምታደምጠውም ነገር ልትነቃቃና ልትነሳሳ እንደምትችል ልብ በሉ። ክንዶቿን እቅፊህ ወደራስህ እስጠጋት። ምን ያህል ቆንጆ እንደሆነች፣ ጾታዊ ውበቷን ምን ያህል እንደምትወዳት፣ ምን ያህል እንደምታስብላትና ምን ያህል እንደምታስፈልግህ እንድትነግራት ትፈልጋለች። ምን ያህል ጣፋጭ እንደሆነች ሽክሽክታህን በጆሮዋ መስማት ትሻለች።



ባልና ሚስት ይልቁንም ደግሞ ሚስት ወሲባዊ ፍላጎታቸውን ስለመለክት በግልጽ መነጋገርን ሲማሩ ያስፈልጋቸዋል።

ምናልባት ይህ በጣም ትንሽ ነገር መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ነገር ግን በትዳር ውስጥ እሳቱ እየነደደ እንዲቀይ የሚያደርጉ ነገሮች ናቸው። ባልና ሚስት ሁልጊዜም እርስ በእርስ በመዋደድና ፍቅርንም በወሲባዊ ግንኙነት በመግለጽ አንዳቸው ሌላቸውን እስኪያረኩ ድረስ በቂ ጊዜን የመውሰድ ሀላፊነት አለባቸው። እርግጥ ነው ምን ያህል ጊዜ ነው በቂ የሚባለው የሚለው ጥያቄ የሚመለሰው በባለትዳሮቹ በራሳቸው ነው። በጋብቻ ውስጥ ወሲባዊ ግንኙነት የተገባ ነገር ነው። እያንዳንዱም ተጓዳኝ ከሌላው የትዳር አጋሩ የሚጠብቀው፣ ለሌላውም ምላሽ የመስጠት ሀላፊነት ያለበት ጉዳይ ነው። ይህንን በሚመለከት የእዲስ ኪዳን ጸሐፊ የሆነው ጳውሎስ የሚለው አለው።

"ነገር ግን ስለዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፤ ለእያንዳንዷም ደግሞ ለራሷ ባል ይኑራት። ባል ለሚስቱ የሚገባውን ያድርግላት። እንደዚሁም ደግሞ ሚስት ለባልዋ። ሚስት በገዛ ስጋዋ ላይ ስልጣን የላትም ስልጣን ለባልዋ ነው እንጂ። እንዲሁ ደግሞ ባል በገዛ ስጋው ላይ ስልጣን የለውም ስልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በእርሳችሁ አትከላከሉ። ራሳችሁን ስለአለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ" (1ቆሮ 7፥3-5)።

ከዚህ ምንባብ እውድ በግልጽ እንደምንረዳው በጋብቻ ውስጥ ያለ ሀላፊነት ወሲባዊ ግንኙነትን የሚመለከት ነው። ባልና ሚስት ሁለቱም አንዳቸው ለአንዳቸው ወሲባዊ ፍላጎት መልስ የመስጠት ሀላፊነት አላባቸው። ሀላፊነት ብዙውን ጊዜ ከስሜት ይልቅ አግባብነት ላላቸው ሁኔታዎች ቅድሚያን ይሰጣል። ይህንን በአግባቡ መገንዘብ፤ አንደኛው ወገን ወሲባዊ ፍላጎት ባለውና ሌላኛው ደግሞ በሌላው ጊዜ መሆን የሚገባውን ለመረዳት ይጠቅማል። የራሳችን ፍላጎት ምንም ይሁን ምን የትዳር ጓደኞችንን ጥያቄ ከፍቅርም ከሀላፊነትም ውጭ ሆነን ልንመልስ የሚያስፈልገን ጊዜ አለ።



በጋብቻ ውስጥ ወሲባዊ ግንኙነት የተገባ ነገር ነው፤ ስያንዳንዱም ተጓዳኝ ከሌላው የትዳር አጋሩ የሚጠብቀው፣ ስሌላውም ምላሽ የመስጠት ሀላፊነት ያለበት ጉዳይ ነው።

አንዳንድ ጊዜ በወሲባዊ ግንኙነቶቻችን ውስጥ ያሉ ጥቃቅን ነገሮች መላውን የትዳር ጉዳያችንን ሙሉ ወደ ሆነ ሀብረትና አንድነት የሚያመጡ ጉዳዮች መሆናቸውን እንዘነጋለን። እነዚህ ጥቃቅን የምንላቸው ነገሮች ፍቅራችንን ለትዳር ጓደኞቻችን የምንገልጽባቸው እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ከመሆናቸውም በላይ፤ አንዳንድ ጊዜም ስሜታችንን በሚመለከት ምንም ልናደርግ የማንችልበት ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚያሳዩ ናቸው።

ይህ ያንጸባርቃል?

በትዳር ውስጥ ስላለ ወሲባዊ ግንኙነትን በሚመለከት ልንመለከተው የተገባ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አለ። ወሲባዊ እንቅስቃሴን በሚመለከት በአለም ውስጥ ካሉ እጅግ በርካታ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች መካከል፤ ብዙ ባለትዳሮች ይልቁንም አማኞች በባልና በሚስት መካከል ሀጋዊ የሆነውና ያልሆነው፤ አግባብነት ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ግራ መጋባት አለ። ለነምግባር፣ መብት፣ አግባብ ምንድን ነው? ምንስ አይደለም? ብዙዎቹ ባለትዳሮች የመጡት "ሁሉም ነገር ወደ ወሲብ የሚጠጋ ነው" የሚል አመለካከት ካለው አለም ብመሆኑ ግራ መጋባቱ ግልጽ ነው። ዓለማዊ በሆነው ማህበረሰብ እይታ ምንም ነገር ይሁን በማንም ደንብና ሥርዓት ህግም ሲወጣለት ያልተገባ ነው። ራስን በራስ ማርካት፣ ቃላዊ ወሲብ፣ ሶዶማዊ ግንኙነት፣ የህብረት ወሲብ፣ ወሲባዊ ስዕሎችና ፊልሞች፣ ከህጻናት ጋር ወሲብን መፈጸም፣ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ወሲብን መፈጸም፣ ከእንስሳት ጋር ወሲብን መፈጸም፣ በራስና በሌላው ላይ አይምሯዊና አካላዊ ስቃይ በማምጣት ወሲባዊ እርካታን ለማግኘት መሞከር፤ እናንተ ሌሎችንም መጨመር ትችላላችሁ፤ ዓለም የሚላችሁ ግን "ይህ ለአንተ መብትህ ነውና ፈጽመው!" ነው።

ይሁን እንጂ እዚህ ጋ ልናነሳው የተገባ ጥያቄ፤ ወሲብን የፈጠረው እግዚአብሔር ነውና የእግዚአብሔር ቃል ምን ይላል? የሚል ጥያቄ ነው። ወሲብን የፈጠረው፣ መመሪያዎቹንም የመሠረተው፣ መመዘኛዎች ያስቀመጠለት፣ አግባብ ባለው ሁኔታ ይፈጸም ዘንድ ገደብን ያደረገለት እግዚአብሔር ነው። የተፈጥሮ አንደኛው መሠረታዊ መርህ "ሁሉ በልክ" የመሆኑ መርህ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው አግባብነት ባለው ስፍራውና ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር ልክ እንዲሆን አድርጎ ነው። ይህ ደግሞ እንደሌሎች የህይወት ገጽታዎች ሁሉ በሰዎች ወሲባዊ ግንኙነትም

ውስጥ የሚሠራ ነው። የወንድና የሴት ወሲባዊ ብልቶች ታቅደው የተፈጠሩት ልክ እንዲሆኑና የጋራ ለሆነ ተግባር አመች ስፍራ ላይ እንዲቀመጡ ተደርገው ነው። ከዚህ ታቅዶ ከተደረገው ነገር ውጭ አልፎ የሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ ከ"ሁሉ በልክ" መርህ ጋር የሚጣረስና አግባብነት የሌለው ወሲባዊ ባህሪ ነው። አግባብነት የሌለው ወሲባዊ ባህሪ ማለት በአጭሩ፣ ክፉ ውጤት ያለው እላማ፣ አግባብነት የሌለው አጠቃቀም ወይም የነገሮችን የመነሻ ተፈጥሯዊ አላማ ባልተገባ መንገድ መጠቀም ማለት ነው። ለዚህም ነው ለምሳሌ ያህል ግብረሰዶማዊነት፤ ለሰዎች በተገባ መንገድ አስቀድሞ የታቀደውን ወሲባዊ ግንኙነት ባልተገባና አስቀድሞ ባልታቀደበት መንገድ የሚፈጸም በመሆኑ ሀጢያት የሆነው።

አግባብነት ስለሌለው ወሲባዊ ባህሪ ሀግን የሰጠው ምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች ባለትዳሮችን የሚመለከት፤ ተስማምተው የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ጥሩ ነው ይላሉ። ባልና ሚስት በጓዳቸው ባለ አልጋቸው ውስጥ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ የግል ጉዳያቸው ነው፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር የተሰወረ እንዳች ነገር የለም። ሁልጊዜም ቢሆን አግባብነት የሌላቸው የተወሰኑ ባህሪያት እንዳሉ መናገር ለጥንቃቄ የሚያመች ይመስለኛል። የ"ሁሉ በልክን" መርህ ከሚጣረሉ ተግባራት በተጨማሪ፤ ያልተገባ ወሲባዊ ባህሪ፤ ሆን ተብሎ በአካል ላይ ህመም የሚያስከትልን፣ ጎጅ የሆነ ወይም ጤናማ ያልሆነ፣ በተጨማሪም እንዱ ሌላኛውን በማስገደድ ይልቁንም የተገደደው ወገን በግንኙነቱ ደስ ያልተሰኘበት ሆኖ ሲገኝ የሚፈጸምን ወሲባዊ ግንኙነትን ሁሉ የሚያካትት ነው።

ወሲባዊ ግንኙነትን ጨምሮ በሁሉም የህይወት ዘርፎች ጠንካራ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መርህ "ይህ ያንሳልን" የሚል ጥያቄ መጠየቅ ነው። በቆሮንቶስ ከተማ ለሚገኙ አማኞች ጳውሎስ ግልጽ ያደረገው ነጥብ ይህ ነው። "ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅደልኛል ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም። እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ እንድም ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ" 1ቆሮ 10÷23-24። የጳውሎስ ሀሳብ ያነጣጠረው ምንም እንኳን ክርስቲያን አማኞች በህግ ያልታሰሩ በመሆኑ "ሁሉም ነገር የተፈቀደ" ቢሆንም ሁሉም ነገር የሚጠቅም ወይም "ገንቢ" አይደለም። ገንቢ ለሚለው ተለዋጩ ቃል "የሚያንጽ" የሚል ነው። ማነጽ ማለት ደግሞ መገንባት ወይም ደግሞ ማጠናከር ማለት ነው።

የአንድን ድርጊት ወይም ባህሪ ትክክለኝነት ወይም ስህተትነት ስንገመግም፤ ራሳችንን ልንጠይቅ የሚያስፈልገው ጥያቄ ያ ባህሪ ራሳችንንም ይሁን ሌላውን የሚገነባና የሚያንጽ ወይስ ቁልቁል የሚቀብር መሆኑን ነው። ጥያቄው ከዚያ ምን ጥቅም አገኝ ን የሚለው ሳይሆን ነገሩ ጤነኛና ገንቢ ነውን? የሚለው ነው። ነገሩ ተብሎ ካለቀና ተደርጎ ከተጠናቀቀ በኋላ በመንፈስ ታንጸንበታልን? ከጌታ ጋር ወይም ከትዳር ጓደኞችን ጋር ያለን ግንኙነት ተገንብቷል ወይም ተጠናክሯል ወይስ ተዳክሟል? በነገሩ ተበረታተናል ወይስ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ ሁኔታ ውስጥ ገብተናል? በራስ መተማመናችን ጎልብቷል ወይስ በበደለኝነትና በሀፍረት ስሜት ውስጥ ተዘፍቀናል? አይምሯችንስ ንጹህ ነውን?

ጥያቄው ከዚህ ምን ጥቅም አገኝን የሚሰው ሳይሆን፤ ነገሩ ጤነኛና የሚያንጽ ነውን የሚሰው ነው።

የአንድ ወሲባዊ ባህሪ አግባብነት ያለው ወይም የሌለው ለመሆኑ መመዘኛው በባህሪው ታንጸናል ወይስ አልታነጽንም የሚለው ነው። ያደረግነው ማንኛውም ድርጊት ቀጣይ ሁኔታችንን አንጸት ቢሆን ህጋዊና አግባብነት ያለው ነው። ያላነጸን ከሆነ ግን አግባብነት የሌለው ነው። እግዚአብሔር ባህሪያችንን ለመምራት በቃሉ ጠንካራ የሆኑ መርሆዎችን ሰጥቶናል፤ እነዚህ መርሆዎች ደግሞ ሁልጊዜም አስተማማኝ መመዘኛዎች ናቸው።

መርሆዎች

1. ወሲብ ፍቅር አይደለም።
2. ወሲብ መንፈሳዊ አይደለም።
3. ወሲብ መቶ በመቶ አካላዊና ኬሚካላዊ ነው።
4. ወሲብ ፍላጎት ነው።
5. ወሲብ ለመዋለድ ነው።
6. ወሲብ ለመዝናናት ነው።
7. ወሲብ ለግንኙነት ነው።
8. በጋብቻ ውስጥ በወሲብ መባዛትና ደስተኛነት የሚለካው፤ ባለትዳሮች አንዳቸው ለአንዳቸው ፍላጎታቸውንና መሻታቸውን ግልጽ በማድረግ፤ በፍቅር፤ በመቀባበልና፤ በመካባበር, በሚያገኙት ምቾት ነው።
9. ወሲባዊ ባህሪን ጨምሮ በየትኛውም የህይወት ገጽታ ጠንካራ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ይህ የሚያንጽ ነውን? ብለን የምንጠይቀው ጥያቄ ነው።

ምዕራፍ ሰባት


የቤተሰብ ምጣኔ

በቅርብ አመታት ውስጥ ከመንግስታት ባለስልጣኖች፣ የሀይማኖት መሪዎች ጋር ለመገናኘት በተጓዝኩባቸው በየትኛዎቹም የዓለም ክፍሎች በተመሳሳይ ሁኔታ የማህበረሰባቸው ዋነኛው ችግር ምን እንደሆነ ለጠየኳቸው ጥያቄ በተደጋጋሚ ያገኘሁት መልስ ተመሳሳይ ነው። የቤተሰብ ጉዳይ። ይህንን ምላሽ በካሪቢያን፣ በደቡብ አሜሪካ፣ በአሜሪካ፣ በእስራኤልና በሄዱኩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ሰምቼዋለሁ። የቤተሰብ ዝቅጠት ጉዳይ አለም ዓቀፋዊ ችግር ሆኗል።

የቤተሰብ ተቋም ይህንን በመሰለ ጥቃት ከጠላት የሚደርስበት የመሆኑ ጉዳይ ለእኛ አስገራሚ አይደለም። ቤተሰብን የማውደም ተግባር የስልጣኔን መበታተን የሚያስከትል ነው። ቤተሰብ የመጀመሪያውና መሠረታዊ የሆነ የሰብአዊው ፍጥረት ማህበረሰብ አንድ ክፍል ነው። ቤተሰቦች ማንኛውም ማህበረሰብና ባህል የሚገነባባቸው የግንባታ ጡቦች ናቸው።

በባህሪው ቤተሰብ ማህበረሰብ የሚገነባበት ደቂቅ አካል ነው። ደቂቅ አካል ማለት በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነና የአካሉን ቀጣይ መሠረታዊ ባህሪያት የሚያመላክት ነው። በሌላ አገላለጽ የአንድ ማህበረሰብ ሁኔታ በውስጡ ያቀፈውን ቤተሰብ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው። ልክ የአንድ ህንጻ ጥንካሬ የሚወሰነው በተሠራበት የግንባታ ጥሬ ዕቃ አይነት እንደሆነ ሁሉ፤ የማንኛውም ማህበረሰብ ጥንካሬ በውስጡ ያለውን ቤተሰብ ጥንካሬ ያህል ብቻ ነው።

ገና ከፍጥረት መጀመሪያው ላይ እግዚአብሔር ቤተሰብን ፈጠረ፤ አሁንም ቢሆን ለብአዊውን ማህበረሰብ ለመመስረት ለእግዚአብሔር አመች የሆነው ተቋም ቤተሰብ ነው። በመሆኑም ማህበረሰባችን ካጋጠመው ማህበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ችግሮች ለመፈወስ የቤተሰብ እንደገና መመሥረት፣ መታደስና እንደገና መገንባት ወሳኝ ጉዳይ ነው።



የአንድ ማህበረሰብ ሁኔታ በውስጡ ያቀፈውን ቤተሰብ ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው።

በምድር ላይ ያለው ማንኛውም ነገር እንዲኖር የተደረገበት አለማ አለ። እግዚአብሔር እንደፈጣሪነቱ ማንኛውም ነገር ሲፈጥር

በልቡ ውስጥ የተለየ አላማ አለው። ይህ ለሌሎች ነገሮች ሁሉ እውነት እንደሆነ ሁሉ በቤተሰብ ጉዳይ ላይም እውነትነት ያለው ነው። የሰብአዊው ሰው የመጀመሪያው ቤተሰብ የተመሠረተው እግዚአብሔር ሄዋንን ከአዳም ጎን ሠርቶ ወደ አዳም ባቀረበበት ጊዜ ነበር (ዘፍ 2፥21-24)። የዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር ለቤተሰብ ስላለው አላማና እቅድ የተለየ አቀራረብ አለው። "እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ባረካቸው፤ እንዲህም አላቸው፤ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፤ ግዙአትም፤ የባህርን አሳዎችና የሰማይንም ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዙአቸው" (ዘፍ 1፥27-28)። የእግዚአብሔር እቅድ ምድርን በመልኩ በተፈጠረው የሰው ፍጥረት መሙላት ሲሆን፤ ይህንንም እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የመረጠው መንገድ ቤተሰብን ነበር።

እግዚአብሔር ስለቤተሰብ ያለውን እቅድ የሚያመለክት ሌላ ፍንጭ በሚልክያስ መጽሐፍ ውስጥ እናገኛለን።

"ይህንን ደግሞ አድርጋችኋል፤ እግዚአብሔር ቁርባኑን ዳግመኛ እንዳይመለከት ከእጃችሁም በደስታ እንዳይቀበለው መሰዊያውን በእንባና በለቅሶ በሀዘንም ትከድናላችሁ። እናንተም ስለምንድን ነው? ብላችኋል። ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳን ሚስትህ ሆና ሳለች እርስዋን አታለሃታልና። እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የህይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድን ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል" (ሚል 2፥13-15)።

ህፃናት በእግዚአብሔር ልብ የተወደዱ ናቸው። የአንድ ማህበረሰብ እድገትና ቀጣይነት ሁለቱም በህፃናት ላይ ያረፈ ነው። ገና ከመጀመሪያውም እግዚአብሔር ማህበረሰብ የሚገነባበትን ጠንካራ መሠረት መስርቷል። የመጀመሪያው ደረጃ የሰው መፈጠር ነበር-ወንድና ሴት። ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ጋብቻ ሲሆን ይህም ሁለት ሰብአዊ ግለሰቦች አካላዊ በሆነ ወሲባዊ ግንኙነት በመጣመር ወደ አዋዳዊነት የሚመጡበት መንፈሣዊ አንድነት ነው። ጋብቻ በባህሪው ወደ ሶስተኛው ደረጃ ያመጣናል፤ አባት፣ እናትና አንድ ወይም ከዚያ በላይ ልጆችን ወዳቀፈ ቤተሰብ። ይህ ቤተሰብ የሚለው ቃል ተለምዷዊ (ባህላዊ) ትርጉም ነው። ምንም እንኳን ባልና

ሚስትን ብቻ ያቀፈ ቤተሰብና ብቻቸውን የሚኖሩ ያላገቡ ግለሰቦች፤ ሰፋ ባለው አመለካከት በእርግጠኝነት የቤተሰብን መመዘኛ የሚያሟሉ ቢሆኑም፤ ተለምዷዊ (ባህላዊ) በሆነው ግንዛቤ ግን የሰብአዊውን ማህበረሰብ ቀጣይነትና ምድርን በሰዎች በመሙላት ጉዳይ ያለው አመለካከት እጅጉን የተለየ ነው።

ባልና ሚስት በእንድነት ሆነው ጋብቻን ይመሰርታሉ። ጋብቻም ቤተሰብን ይፈጥራል። ህፃናት ይወለዳሉ፤ ወደ ብስለት ያድጋሉ እናም የራሳቸውን ቤተሰቦች ይመሠርታሉ። በርካታ ቤተሰቦች ማህበረሰብን፤ በርካታ ማህበረሰቦችም ህብረተሰብን፤ በርካታ ህብረተሰቦችም ህገርን ይፈጥራሉ።

እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ትእዛዝ ሁሉ የሰው ልጅ በታማኝነት የታዘዘው ቢኖር "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት" የሚለውን ትእዛዝ ነው። እኛ ሰዎች ይህንን ትእዛዝ በጥንቃቄና በትጋት የተከተልን በመሆኑ ምክንያት በህያ እንደኛው ከፍለ ዘመን የዓለም ህዝብ ብዛት አስደንጋጭ ወደ ሆነ ጣራ ላይ ደርሷል። በሚሊዬን የሚቆጠሩ ሰዎች በተመጣጣኝ ምግብ አጥረትና በርሃብ ውስጥ ይኖራሉ። በዚህ ቀውስ ውስጥ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ባለ አይምሮ የሆኑ የእግዚአብሔር ህዝቦች ተስተውሎ ለሚተገበር የቤተሰብ ምጣኔ ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት የመስጠት ህላፊነት አለባቸው።

ዘመኑስ ጊዴስ ስለዘመኑስ?

እንደ ባህላቸው ምንነት ወይም እንደ አስተዳደጋቸው ብዙ አማኞች የቤተሰብ ምጣኔን አስመልክቶ ለመወያየት ደስተኞች አይደሉም። አንዳንዶቹ ብቃት በሌለውና በተሳሳተ ትምህርት ምክንያት በርዕሱ ላይ ግራ ተጋብተዋል፤ ሌሎች ደግሞ ልጆችን ማግኘትን ለመሰለው "ለተቀደሰ" ጉዳይ "ምጣኔን" ማድረግ የሆነ ያልተቀደሰ ነገር አድርገው በማሰብ ጨፍጋጋ ስሜት ይፈጥርባቸዋል። የቤተሰብ ምጣኔ ምን እንደሆነና ምንስ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈለገበት ምክንያት ይሄው ነው።

በቀላሉ ለማስቀመጥ፤ የቤተሰብ ምጣኔ እንድ ቤተሰብ በአግባቡ ሊወዳቸው፤ ሊመግባቸው፤ አስፈላጊውን ነገር በማቅረብ ሊንከባከባቸውና ሊከታተላቸው፤ ሊያሰለጥናቸውና ሊጠብቃቸው በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ለመገኘት፤ ያልተፈለገ እግርዝናን ለማስቀረትና የቤተሰብን ቁጥር ለመወሰን አስቀድሞ የታሰበበትን

ውሳኔ የሚያካትት ነው። ይህንን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ በግልጽ የተቀመጠና የተጨበጠ አስቀድሞ የመከላከል ተግባርን የሚጠይቅ ነው። በሌላ አገላለጽ የቤተሰብ ምጣኔ የወሊድ መቆጣጠርን ያካትታል። በዚህ ዘመን ያሉት የተለመዱ ወሊድን የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች ኮንዶም፤ ዲያፍራምና የወሊድ መከላከያ እንክብሎች ናቸው። እነዚህ ሁሉም ከወንድ የሚወጣው ዘር በሴቲቱ ማህፀን ውስጥ የሚገኘውን እንቁላል በመገናኘት እንዳያኮርት በመካለከል እርግዝናን የሚከላከሉ ናቸው። የወሊድ መከላከያዎች የአዲስን ሰብአዊ ሰው መረገዝ ይከላከላሉ።

የቤተሰብ ምጣኔ የህፃንን መወለድ መከላከልንና አስቀድሞ እርግዝናን በመቆጣጠር ላይ የሚያተኩር ነው። ሆን ተብሎ ከሚደረግ እርግዝናን ከማቋረጥ ተግባር ጋር የሚያያዘው ነገር የለም። በመሆኑም ውርጃ የቤተሰብ ምጣኔ አይደለም። እንደዚሁም ወሊድን የመቆጣጠሪያ ወይም የጤንነት እንክብካቤ መንገድ አይደለም። ውርጃ ሆን ተብሎ የሚደረግ ህይወት ያለውን ሰብአዊ ፍጡር የማውደም ተግባር በመሆኑ ስነ ምግባር የጎደለውና ሃጢያትም ነው። እንዲሁ ደግሞ በእግዚአብሔር የታቀደውንና አስቀድሞ የታሰበውን ሀሳብ በቀጥታ የሚቃረን ነው።

ብዙ ቤተሰብን ማካተት እንደ ተገቢ ሁኔታ የሚቆጠርበትና እንዲያውም በህይወት ለመቆየት አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ ነበር። ይህ ሁኔታ በተለይም ደግሞ በግብርና ላይ በተመሠረቱ ማህበረሰቦች መካከል የተለመደ ነበር። በበሽታና በጉዳት ምክንያት የህፃናት ልጆች ሞት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረበት ዘመን፤ ወላጆች ዘራቸው እንዲቀጥልና ልጆች አሳድገው በእርሻ ሥራ እንዲያግዟቸው በርካታ ልጆችን ለመውለድ ምክንያት ሆኖላቸዋል። በዛሬው ኢንዱስትሪያዊ ማህበረሰብና በወቅቱ ኢኮኖሚያዊ ተጨባጭ ሁኔታ የቤተሰብ ምጣኔና የወሊድ ቁጥጥር መልካም ነገሮችን ፈጥሯል። ድህነት በተስፋፋባቸውና የተመጣጠነ የአመጋገብ ችግር ባላቸው በብዙ ሀገሮችና የህዝብ ብዛትም በእውቀት ማነስና ህጋዊ የሆነውን የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ አማራጭ ባለማወቅ ምክንያት ያለገደብ እየጨመረ በሄደባቸው በብዙ የሦስተኛው ዓለም ባህሎች ውስጥም ይህ እውነት የሚሠራ ነው።



የቤተሰብ ምጣኔ የህፃንን መወለድ መከላከልንና አስቀድሞ እርግዝናን በመቆጣጠር ላይ የሚያተኩር ነው። ሆን ተብሎ



የሚፈጸም ስርግዝናን ከማቋረጥ ተግባር ጋር የሚያያዘው ነገር የለም።

እያንዳንዱ ባለትዳር ቢቻልና ተመራጭ የሆነው ከመጋባታቸው በፊት ካልሆነም በእርግጠኝነት በተጋቡ በጥቂት ወራት ውስጥ ሊመልሷቸው የሚገቡ ቢያንስ ሦስት ጥያቄዎች አሉ። የመጀመሪያው "ልጆችን እንፈልጋለን?" የሚል ነው። በተለያዩ ምክንያቶች አንዳንድ ጥንዶች ምንም ልጆች ባይኖራቸው ይመርጣሉ። ምናልባትም በሰራቸው ጠባይ፣ በጤንነት ስጋት፣ ከቡተሰብ የዘር ግንድ የሚተላለፍ በሽታን ችግር በመስጋት ወይም በሌላ ምክንያቶችም ይሁን ባለትዳሮች በራሳቸው ሊወስኑት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ባለትዳሮቹ ልጆች እንዲኖራቸው የወሰኑ ከሆነ ሊመልሱት የሚገባው ሁለተኛው ጥያቄ "መቼ?" የሚለው ይሆናል። ይህ እጅግ ጠቃሚ ጥያቄ ነው። ቤተሰብን ለመጀመርና ጊዜውንም ለመወሰን ልናጤናቸው የሚገቡ በርካታ እውነታዎች አሉ። ለምሳሌም ያህል ብለለት፣ ከተጋቢዎቹ እንደኛው ወይም ሁለቱም በትምህርት ላይ መሆናቸውና ቋሚ የሆነ ሥራና ገቢ ተጠቃሾች ናቸው። ጤነኛ የሆኑ ልጆችን ለማሳደግ በገቢ፣ በስሜትና በመንፈሳዊ ጉዳዮች የተረጋጋ ሁኔታና የመኖሪያ ቤትም ያስፈልጋል።

ልጆችን በሚመለከት ባለትዳሮች ሊመልሱት የሚገባ ሦስተኛው ጥያቄ "ስንት ልጆች?" የሚል ነው። እዚህ ጋ ሊጤን የሚገባው ትልቁ ጉዳይ የባለትዳሮቹ የገንዘብ ምንጭ ነው። በቀላሉ ባለትዳሮች ብዙ ልጆች ካላቸው ልጆቻቸውን በእግባቡ ለመንከባከብና ለማሳደግ ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። ለምሳሌ ያህል በሣምንት 300 ዶላር ገቢ ያለው ቤተሰብ አሰር ህፃናትን በእግባቡ ለመመገብና አስፈላጊውን አቅርቦት ለማዘጋጀት እንደሚችል መገመት የለበትም። ምን ያህል ልጆችን እንደሚወልዱ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ልጆችን በእግባቡ አስፈላጊውን አቅርቦት በማዘጋጀት ማሳደግ እንደሚችሉ መወሰን የወላጆች ሀላፊት ነው።

ልጆችን ማሳደግ በእግዚአብሔር ዘንድ ትኩረት የሚሰጠው ጠቃሚ ጉዳይና ወላጆችም እንዴት እንደሚንከባከቧቸውና እንደሚይዟቸው በእርሱ ዘንድ ተጠያቂነት ያለባቸው ናቸው። "ነገር ግን የራስ ሰለሆኑት ይልቁንም ሰለቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ሀይማኖትን የካደ ከማያምኑትም ይልቅ የሚከፋ ነው" (1ጢሞ

5፥8) እግዚአብሔር ባለትዳሮች ብዙ ልጆች ቢኖሯቸው ችግር የለበትም፤ ነገር ግን እንዲወዷቸው፣ እንዲደግፏቸውና ሀላፊነት በተሞላበት ሁኔታ አስፈላጊውን ነገር እንዲያቀርቡላቸው ይጠብቅባቸዋል፤ ይፈልግባቸዋልም።



ምን ያህል ልጆችን እንደሚወልዱ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል ልጆችን በአግባቡ አስፈላጊውን አቅርቦት በማዘጋጀት ማሳደግ እንደሚችሉ መወሰን የወላጆች ሀላፊነት ነው።

የወሊድ ቁጥጥር፤ እርስ በእርሳችው እስኪግባቡና ልጆችን ከመውለዳቸው በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዘግጅት ለማድረግ ጊዜ ለሚያስፈልጋቸው ወጣት ተጋቢዎች በረከት ሊሆን ይችላል። ምንም ልጆች እንዲኖራቸው ላለቀዱ ወይም የሚፈልጓቸውን ልጆች ቁጥር ላገኙ ጥንዶች ቀጣይ እርግዝናን በመከላከል አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች ማወቅያስፈልጋቸዋል። ለወንዶች የዘር መተላለፊያ ቧንቧዎችን በቀዶ ጥገና መቁረጥና መዝጋት ወይም ደግሞ የሴቷን የዘር መተላለፊያ ተቦ መቋጠር ሊሆን ይችላል። ለቴክኖሎጂ ምስጋና ይግባውና እነዚህ ሁሉ ባለትዳሮች የቤተሰባቸውን ቁጥር በሚመለከት ለሚያደርጉት አስተዋይነት ለተሞላበትና መረጃን ያገናዘበ ውሳኔ ጠቃሚ ረዳቶች ናቸው።

ልጆች የጌታ ስጦታዎች ናቸው

ልጆች እንዲኖሯቸው የወሰኑ ባለትዳሮች መልካምን እቅድ እቅደዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ልጆችን መውለድና ማሳደግ በረከት እንደሆኑ በሚገልጽ ብዙ ምንባቦች የተሞላ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ብዙ ልጆች የነበሯቸው ወላጆች ከመጠን ባለፈ ባረከት በእግዚአብሐር እንደተባረኩ ይቆጠር ነበር። እንደዚሁ ደግሞ ልጆች መውለዱ ያልቻሉ ሌቶች ከእግዚአብሔር መርገም በታች እንደ ሆኑ ይታሰብ ነበር። ምንም እንኳን በዚህ ዘመን የቤተሰብ ስፋት ከእግዚአብሔር ባርኮት ጋር ምንም እንደማይገናኝ ብንገነዘብም፣ ይህ ሁኔታ በጥንት ዘመን በተለይም የእግዚአብሔር ልጆች ሰሆኑት ለዕብራውያን ልጆች ምን ያህል ዋጋ ያላቸውና ጠቃሚዎች እንደነበሩ የሚያሳይ ነው።

እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው
የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው
በሀያል እጅ እንዳሉ ፍላጻች

የጐልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው።

ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው

ጠላቶቻቸውን በአደባባይ በተናገሩ ጊዜ

እርሱ አያፍርም መዝ (127)÷3-5።

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ እንደገለጽኩት "ወንድ ልጆች" የሚለው በቁጥር 3 እና 4 ላይ የተጠቀሰው የዕብራይስጥ ቃል "ልጆች" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በቁጥር 3 ላይ የሰፈረው "ልጆች" የሚሰው ቃል ከሁለት የዕብራይስጥ ቃል የወጣ በቀጥተኛ ትርጓሜውም "የማህጸን ፍሬ" የሚል ነው። ልጆች ከወላጆቻቸው የማባዛት ውጤት የተገኙ ፍሬዎች ናቸው። በመሆኑም ልጆች ያሏቸው ባለትዳሮች እግዚአብሔር ለትዳር ያቀደውን አንዱን "ብዙ ተባዙ" ዘፍ 1÷28 የሚለውን አላማውን እያሳኩ ነው።



ልጆች እንዲኖሯቸው የወሰኑ ባለትዳሮች መልካምን ስቅድ ስቅደዋል።

መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ (27)÷4 ልጆችን በሃያላን እጅ ካለ ፍላፃ ጋር ያመሳስላቸዋል። በቁጥር 5 ደግሞ ኮሮጆው በልጆች የተሞላ ሰው የተባረከ እንደሆነ ይናገራል። ፍላጻ በኮሮጆ ውስጥ ሊቀመጥ አልተሠራም። ይልቁንም በቀስት ተሰጥጦ በኢላማ ላይ ይወነጨፋል። ፍላጻ በኮረጆ ውስጥ እስከተቀመጠ ድረስ የተሠራበትን አላማ አይፈጽምም። ልጆችንም በሚመለከት እንደዚሁ ነው። እስኪያድጉና ወደ ብስለት እስደርሱ ድረስ ልጆች ሰጊዜው በቤታቸው ኮሮጆና በቤተሰቦቻቸው ውስጥ ይቀመጣሉ፤ ነገር ግን በቆይታ ውለጥ ወደ አለም የሚለቀቁበት ጊዜ ይመጣል። በዚያን ጊዜ ብቻ ነው እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ ያኖረው አላማ ግቡን ሊመታ ሙሉ በሙሉ እንደ ፍላፃ መወንጨፍ የሚጀምረው። ልጆቻቸው ከኮረጆው ውስጥ ይወጡ ዘንድ ማዘጋጀት የወላጆች ሚና ነው።

እግዚአብሔር መልካም የሆኑ የሰውን ቀጣይ ዝርያዎችን ይፈልጋል። (ሚል 2÷15 ይመልከቱ)፤ መልካም የሆኑ ዝርያዎች የሚገኙት ደግሞ መልካም ከሆነ ቤተሰብ ነው። እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው የፍጻሜ አላማ እርሱን ይመስሉ ዘንድ የእርሱ ባህሪ እንዲኖራቸው ነው። እግዚአብሔርን ለመምሰል ቀልጣፋው መንገድ እርሱን መከተል ነው። ይህ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ

የመኖርን እውነት የሚጠይቅ በመሆኑ በእውነተኝነት አግዚአብሔርን መምሰል የሚችሉት አማኞችና የክርስቶስ ተከታዮች ብቻ ናቸው።

በኤፌሶን ለሚኖሩ አማኞች በጻፈው መልእክቱ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ነበር፤ "እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፤ ክርስቶስም ደግሞ እንደወደዳችሁ ለእግዚአብሔር የመአዛ ሽታ የሚሆንን መባና መስዋእትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ በፍቅር ተመላለሱ" (ኤፌ 5÷1-2)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለእኛ ሞዴላችን ነው። ኢየሱስ ለእኛ ም ሞዴል ከሆነ እኛ ደግሞ ለልጆቻችን እንዲሁ ልንሆን ይገባል። ከወላጅነት ግቦች ውስጥ አንዱ እንደ ወላጆቻቸው አደራረግ የሚያደርጉ፤ ተመሣሣይ እምነትንና እሴትን የሚጋሩ ልጆችን ማሳደግ ነው። ምሳሌ መሆን ከምንም ይልቅ ታላቅ አስተማሪነት ከመሆኑም በላይ ልጆችም የሚማሩት ወላጆቻቸው ከሚናገሩት ነገር ሳይሆን ወላጆቻቸው አርአያ ሆነው ከሚያሳዩዋቸው የህይወት ተሞክሮ ነው። በእርግጥም ድርጊት ከቃላት ይልቅ ጮሆ ይናገራል።

ምሣሌ 20÷11 እንዲህ ይላል፤ "ህፃን ቅንና ንጹህ መሆኑ በሚያደርገው ሥራ ይታወቃል፤" በመልካምም ይሁን በመጥፎ ጎኑ የልጆች ዝንባሌና ጠባይ ከወላጆቻቸው የተቀበሉትን የሚያንጸባርቅ ነው። እጅግ በርካታ በሆኑ ጉዳዮች በልጆችና በወጣቶች ላይ የሚታየው የባህሪ ችግር መነሻው ሲፈተሽ ደካማ የሆነ የቤተሰብ ምሳሌነት ሆኖ ይገኛል።



ኢየሱስ በእኛ ሞዴል ከሆነ እኛ ደግሞ ለልጆቻችን እንዲሁ ልንሆን ይገባል።

መልካም ወላጅነት እንዲሁ በአጋጣሚ የሚመጣ ነገር አይደለም። በአካላዊም ሆነ በስሜታዊ መልኩ በግዴለሽነትና በርቀት ሆነን የምናደርገውም አይደለም። ውጤታማ የሆነ ወላጅነት ትኩረት የሚሰጥ፤ በእቅድ የሚመራና ታስቦበት የሚደረግ ነው። ወላጆች ለስኬት ማቀድ አለባቸው፤ መልካም የሆነ የዘር ፍሬም ግባቸው ነው። ልጆቻችን ስንምግባራችንንና መንፈሳዊ ዝንባሌያችንን ይዘው ካደጉልን እንደ ወላጅ ስኬታሞች ነን። ጌታን መውደድ፤ ማምለክ፤ መከተልና ማገልገል ከተማሩልን ተሳክቶልናል።

በእጃችን ውስጥ ያለውን የከበረ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ትልቅ ጥንቃቄ የማናደርግ ስንቶቻችን ነን? ከልጆቻችን ይልቅ የከበረ ትልቅ ሀብት በምድር ላይ የለም። ከእግዚብሔር የተቀበልናቸው ስጦታዎች በመሆናቸው እንደ መልካም ወላጆች እንዲሁ ልንንከባከባቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሀላፊነትና ግዴታም ጭምር አለብን። እንደ ወላጆች የፍፃሜ ግባችን የለማዩን አባታቸውን የሚያከብሩና የሚያገኑ መልካምን ዘር ማፍራት ነው።

የወላጅነት መሠረታዊ መርሆዎች

እጅግ እውነተኛ በሆነ መልክ እግዚአብሔር የመጀመሪያው ወላጅ ነው፤ ምክንያቱም እርሱን ይመስሉ ዘንድ የታቀዱ ልጆችን ፈጥሯል። ይህ የተገለጸው ደግሞ ለውን በሚመለከት ገና በመጀመሪያው እግዚአብሔር በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ በለጠው መግለጫ ነው "እግዚአብሔር አለ ለውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" (ዘፍ 1÷26)።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ወላጅነትን በሚመለከት "መልክ" እና "ምሳሌ" በሚሉ ቃላት ውስጥ የታቀፉ ሦስት መርሆዎች አሉ። መልክ ከስር መሠረቱ የነበረውን ነገር በቀጥታ መምሰልና የተፈጥሮውንም ባህሪ የሚያሳይ ነው። ምሳሌ የሚለው ቃል ደግሞ በመልክ መምሰል፣ ተመሳሳይ ድርጊትን መተግበርና አንድን ለው ወይም ነገር መምሰል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ለዎችን የፈጠረው በቀጥታ ራሱን እንዲመስሉ ነው። እርሱን መስለው እንዲኖሩና በማንኛውም አስፈላጊ መንገድ እንዲመሳሰሉት። ይህ ወላጆች በግልጽ ሊተገብሩት የሚገባውን እውነት የያዘ ነው።

መሠረታዊ መርህ አንድ:- ወላጅነት የወላጅን ተፈጥሮ በልጁ ውስጥ ሊያፈራ ይገባዋል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ለውንም የፈጠረው ቅዱስ እንዲሆን ነው። ጎጢያት የለውን ቅድስና አበላሽ፣ በውስጡም የነበረውን የእግዚአብሔር መልክ አጠፋው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእግዚአብሔር እቅድና ፕሮግራም ለውን አስቀድሞ ወደነበረበት የተቀደሰ ተፈጥሮው እንደገና ማደስ ሆነ። ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ እንዲኖር የላከበት ዋነኛ አላማ ይሄው ነው። ኢየሱስ በህይወቱ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አሳየን፣ ለጎጢያታችንም በመሞት የእግዚአብሔር መልከና ቅድስና ሙሉ በሙሉ በእኛ ውስጥ መታደስ እንዲችል አደረገው።

በዚህ መንገድ መልካም ልጆች እንዲኖሩን የምንፈልግ ወላጆች ከሆንን ምላሌ ሆነን መልካም ህይወት መኖር አለብን። በባህሪው እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ነው፤ በመሆኑም ይህንኑ አይነት ባህሪ ያላቸው ልጆች እንዲኖሩ ይፈልጋል። ወላጅነት በልጁ ውስጥ የወላጁን ባህሪ ሊያፈራ ይገባዋል። በእኛ ወይም በልጆቻችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ባህሪ ሊያፈራ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

ለዚህ ነው ልጆቻችንን በማስተዋልና ውጤታማ ሆነን ለማላደግ እንድንችል በጌታ ላይ ሙሉ ለሙሉ መተማመንና በቅርበት እርሱን መከተል የሚያስፈልገን።



መልካም ልጆች እንዲኖረን የምንፈልግ ወላጆች ከሆንን ምላሌ ሆነን መልካም ህይወት መኖር አለብን።

መሠረታዊ መርህ ሁለት:- ወላጅነት የወላጅን ባህሪ በልጁ ውስጥ ማፍራት መቻል አለበት። ተፈጥሮና ባህሪ እጅግ የተያያዙ ናቸው። ባህሪያችን እኛን በተቆጣጠረ ተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነው። እራሳችንን ለሌሎች ከገለጥንበት ሁኔታ ውጭ በእርግጥ ማን መሆናችንን ያላያል። ቅርበት ያለው ከዘር የተወረሰ ባህሪያችን ስነምግባራዊ ብቃታችንንና ጥንካሬያችንን ወይም ደግሞ ድካማችንን ያመለክታል። ከዚህም በላይ አይምሯዊና በስነምግባራዊ መርሆች ላይ ያለንን ትኩረትና ግለሰባዊ ማንነታችንንም የሚነካ ነው። ባህሪ ማንም ለው በአካባቢያችን ላይና ር የሚገለጠው እኛነታችን ነው።

ከወላጅነት አመለካከት አንፃር፤ ይህ እጅግ ጠቃሚ ነው። ውጤታማ ወላጆች መሆናችን ከሚለካባቸው መንገዶች አንዱ እኛ በሌለንበት ስፍራ ልጆች የሚያደርጉት ድርጊት ነው። በአካባቢያቸው ሆነን ትክክለኛነታቸውን ወይም እንደተሳሳቱ ልንነግራቸው፤ ልናዛቸውና ልናርማቸው በማንችልበት ጊዜና ሁኔታ ውስጥ፤ የሚናገሩት ወይም የሚሠሩት ነገር ምንድን ነው? ወደድነውም ጠላነውም ልጆቻችን እኛን እጅግ መስለውን ነው የሚወጡት። ይህ የተፈጥሮ አንድ አካል ነው፤ ልጆች ወላጆቻቸውን መስለው ይወጣሉ። ጥሩ ባህሪ ይዘው የሚወጡ ልጆችን የምንፈልግ ከሆነ ጥሩ ባህሪ ያላቸው ወላጆች ልንሆን የግድ ነው።

መሠረታዊ መርህ ሦስት :- ወላጅነት የወላጅን ጠባይ በልጁ ውስጥ ማፍራት ይገባዋል። ተፈጥሮ ባህሪን ይወስናል፣ ባህሪም

ደግሞ ጠባይን ይወስናል። ወላጆች በልጆቻቸው ባህሪ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ከሆነ በመጨረሻው በውድቀትና በፍርሃት ላይ የሚወድቁ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም ጠባይ ከባህሪ ጋር እጅጉን የተያያዘ በመሆኑ ነው።

ስለ ባህሪ እንደገለጽነው ሁሉ ከልጆቻቸው መልካም ጠባይ የሚፈልጉ ወላጆች ለልጆቻቸው አርአያነት ያለው መልካም ጠባይ ሊያሳዩዋቸው ይገባል። "እኔ የምለውን አድርግ እንጂ እኔ የማደርገውን አታድርግ" የሚለው አሮጌ ብሂል ግብዝነት የተሞላው ከመሆኑም ባሻገር የሚሠራም አይደለም። ልጆች በግብዝነት የሚሠራውን ነገር ማየት ስለሚችሉ አንድን ነገር ተናግረው ሌላን ድርጊት የሚፈጽሙ ሰዎች በመመልከት በፍጥነት ክብርን ይነፍጓቸዋል።

መልካሞችና መልካም ወላጆች ከሆንን፤ ልጆቻችን መልካሞችና መልካም ተፈጥሮ ያላቸው ይሆናሉ። በንግግራችን ሁሉ ቀጥተኞች ከሆንን ልጆቻችን ጠንካራ የሆነ ባህሪ ያዳብራሉ። ለወላጅ የተገባ ጠባይ እንዲኖረን ራሳችንን ካስለመድን፤ ልጆቻችንም ይሄው ጠባይ እንዲኖራቸው ራሳቸውን ያስለምዳሉ።

ሁልጊዜም ወደ ልጆቻችን ብቻ በጭራሽ መመልከት የለብንም፤ ይልቁንም ወደ ልጆቻቸው ጭምር እንጂ። እንደወላጅ የፍጻሜው ስኬታማነታችን መመዘኛ የልጅ ልጆቻችን እንዴት እንደሚወጡ ነው። የሚጠበቅብንን ተግባር በአግባቡ ተወጥተን ከሆነ ልጆቻችን ተፈጥሯችንን የራሳቸው ተፈጥሮ አድርገው ከመውረሳቸውም ባሻገር ለገዛ ልጆቻቸውም ያስተላልፉታል። በዚህ መንገድም ጽድቅ ከአንድ ትውልድ ወደሌላው በቀጣይነት ይተላለፋል። እግዚአብሔር መልካምን ዘር የሚፈልግ በመሆኑ በዚህ ውስጥ አቅዱ ውጤታማ ይሆናል።



እንደወላጅ የፍፃሜው ስኬታማነታችን መመዘኛ የልጅ ልጆቻችን እንዴት እንደሚወጡ ነው።

የወላጅነት ሃላፊነት

ወላጅነት ደስታን የሚሰጥ ነው፤ ይሁን እንጂ ትልቅም ሃላፊነት አለበት። እግዚአብሔር የእርሱ ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ከወላጆች ምን እንደሚፈልግና እንደሚጠብቅ ምንስ ተጠያቂነት እንዳለባቸው በግልጽ አስቀምጧል።

"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፤ በሸመገለ ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም" (ምሳ 22÷6)።

"በትርና ተግሳጽ ጥበብን ይሰጣሉ፤ ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳፍራል" (ምሳ 29÷15)።

"በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፤ ልጁን የሚውድ ግን ተግቶ ይገስጸዋል" (ምሳ 13÷24)።

"ተሰፋ ገና ሳለች ልጅህን ገስጽ፤ መሞቱንም አትሻ" (ምሳ 19÷18)

"እኔም ዛሬ አንተን የማዝህን ይህንን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፤ በቤትህም ስትቀመጥ፤ በመንገድም ስትሄድ፤ ስትተኛም፤ ስትነሳም ተጫወተው" (ዘዳ 6÷6-7)።

መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 22÷6 ልጆቻችን ገና ለጋ ሣለ የማለማመድን ጠቃሚነት በምሳሌ ይገልጻል፤ ባደጉ ወይም በሸመገሉ ጊዜ ከዚያ መንገድ ፈቀቅ አይሉም። ተደጋጋሚ የሆኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የህፃን መሠረታዊ የሆነ ተፈጥሯዊ ባህሪ የሚመሠረተው እድሜው ሰባት ዓመት በሆነ ጊዜ ነው። በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመታት ውስጥ ልጆቻችንን ልናስተምራቸውና በውስጣቸው ልናስቀምጥ ያልቻልናቸውን ነገሮች፤ ከዚያ እድሜ በኋላ ምናልባት ሊማሯቸው ቢችሉ እንኳን የሚማሯቸው በከፍተኛ ችግር ነው። ገና ከመጀመሪያው የሚደረግ የማለልጠን ተግባር ለቀጣዩ ህይወታቸው መሠረት የሚጥል ነው። ያደጉ ልጆችና ጎልማሳነት ጊዜያቸውን የጨረሱ ወጣቶች የሚመለሱት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ውስጥ ወደተማሯቸው እምነቶችና እውነቶች ነው። ይልቁንም እነዚህን ትምህርቶች ህብር ባለው መልኩ፤ በተከታታይነትና የወላጆች ምሳሌያዊ ህይወት ተጨምረውበት የተማሯቸው ከሆነ እውነታው አይቀሬ ነው።



የህፃን ተፈጥሯዊ የሆነው ባህሪ የሚመሠረተው ሰባት ዓመት በሆነ ጊዜ ነው።

መልካም ወላጅነት ምንጊዜም የማለማመድን ተግባር ያካትታል። ይህ የሚሆነው ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ልጆች ልምምድን ስለሚፈልጉ ነው። ማለማመድ የምክር አገልግሎትን እንደመስጠት አይደለም። አንዳንድ ወላጆች በልጆቻቸው እድሜ ላይ ትኩረት ሳያደርጉ ለመምከር ይፈልጋሉ። በጥቅሉ ለመናገር ልጁ

ገና ህፃን ሣለ የምንሰጠው ምክር እጅግም ውጤታማ አይደለም። ለጋ የሆኑ ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ መታዘዝን እንዲያውቁ ሊለማመዱ ይገባቸዋል፤ ቀጥሎም ለምን እንደታዘዙ መረዳት ይኖርባቸዋል። ይህ ለራሳቸው ጥበቃ ተብሎ የሚደረግ ነው። ድርጊታቸውን በምክንያት እንዲያደርጉና ነገሮችን ተንትኖ የመረዳትን ክህሎት እየተማሩ ካደጉ፤ በልምምዳቸው ውስጥ ለምን ብለው ለሚጠይቁት ጥያቄ የተሻለ መረዳት ይኖራቸዋል። ልጆቻችን ምክርን ለመቀበል ብቁዎች እስኪሆኑ ድረስ የምክር አገልግሎት በመስጠት ልናለለጥናቸው በመሞከር ስህተትን እንዳንፈጽም ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል።

መልካም የሆነ ወላጅነት ዘልጊዜም የማለማመድን ተግባር ያካትታል።

በሁለተኛ ደረጃ፤ ልጆች ራሳቸውን ማለማመድ አይችሉም። ይህ ያለ ምንም ትንተና መታለፍ ያለበት ነው፤ ይሁን እንጂ እንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ገና በለጋነት እድሜያቸው የራሳቸውን ውሳኔ በራሳቸው እንዲወስኑና ራሳቸውም ራሳቸውን እንዲጠብቁ ይተዋቸዋል። በዚህም ልጆችን የማለልጠን ተግባር ፈጽሞ አያከናውኑም። ይህን ለምን እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ፤ የራሳቸውን እምነትና አመለካከት በልጆቻቸው ላይ በሀይል ለመጫን እንደማይፈልጉ ወይም ልጆቻቸው የራሳቸውን መንገድ እንዳይመርጡ በማድረግ የልጆቻቸውን ነፃነት መገደብ እንደማይፈልጉ በመግለጽ የድርጊታቸውን ትክክለኝነት ያረጋግጣሉ። ይህ አስተዋይነት የጎደለውና ለጥፋት የሚደረግ ዝግጅት ነው፤ ምክንያቱም ልጆች አስተዋይነትና ብስለት የተሞላበትን ውሳኔ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ገና አላዳበሩም። መንገዳቸውን የሚያመላክቷቸው የጠራና የተመጣጠነ የአዋቂዎች አመራር ያስፈልጋቸዋል። የወላጆቻቸው ስልጠና ያሻቸዋል።

በሦስተኛ ደረጃ፤ ስልጠና የታቀደበት ሊሆን ይገባል። ልጆችን የማሳደግና የማለልጠን ሥራ እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ሥርዓት የለሽ ለሆነ አቀራረብ ወይም ለአጋጣሚ ታልፎ የሚተው አይደለም። ወላጆች በፍቃደኝነትና አስበውበት ይህን ሽክም ሊሸከሙ ይገባል። ስለልጆቻችን የመጀመሪያውን ተጠያቂነት የምንወስደው እኛ ነን፤ የልምምዳቸው አስጀማሪዎችና ምንጮቻቸው፣ ምሳሌዎቻቸውም እኛው ነን። ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ ትክክለኛም ይሁን ስህተት ልጆቻችን መመሪያን የተቀበሉት ከእኛ ነው።

ልምምዳችንና ምሳሌነታችን ትክክለኛ፣ የማያቋርጥና ወጥነት ያለው ሊሆን ይገባል። በቤት ውስጥ ያለውን ህግ፣ የዕለት ተግባራዊ ክንውን፣ ሥነ ሥርዓትን በሚመለከት ወላጆች ሁልጊዜም ወጥነት ያለው በተባበረ ግንባር ለልጆቻቸው ሊለጡ ይገባል። እንዲህ ከሆነ ልጆች በአንደኛው ወላጅ ድክመት በሌላኛው ላይ እንዲጫወቱ መንገድ አይከፍትላቸውም።

መልካም ጀሁን መጥፎ፣ ትክክለኛም ጀሁን ስህተት ልጆቻችን መመሪያን የተቀበሉት ከእኛ ነው።

በአራተኛ ደረጃ ስልጠና የሚያተኩረው በረዥም ርቀት ላይ ነው። ልጆቻችን ወዲያውኑ መልካሞች እንዲሆኑ ወይ የነገርናቸውን ሁሉ ገና ከመጀመሪያው ፈጥነው እንዲማሩ መጠበቅ የለብንም። ስልጠና እያደገ የሚሄድ ሂደት ነው። ብስለትም በእንድ ሌሊት የሚመጣ ነገር አይደለም። እንደ ወላጆች ሁልጊዜም ቢሆን ከልጆቻችን መሳኢ ህይወትና ከእነርሱም ልጆች የወደፊት ህይወት ጆርባ እሻግረን ልንመለከት ያስፈልጋል። ስልጠናንና ሥነ ሥርዓትን በሚመለከት፤ ለአጭር ጊዜ የሆነ ስቃይ ለረዥም ጊዜ የሚሆን መልካም ግኙት ያመጣል። ልጆቻችንን በምንቀጣበት ጊዜ ስቃያቸው ከአይኖቻቸው የሚፈስ እንባ ልባችንን ሊሰብር ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ በረዥም ርቀት ሃላፊነት የሚሰማቸው፣ አዋቂዎችና እውነተኞች እንዲሆኑ የምንሰጣቸው ስልጠና በመሆኑ፤ የአጭር ጊዜው የሥነ ሥርዓት ህመም ባደጉ ጊዜ ጠቃሚያቸው ይሆናል።

በመጨረሻም፤ ለማለልጠን አለመቻል ልጁን ፈጽሞ ለጥፋት ለመዳረግ ሃላፊነት መውሰድ ነው። በምሳሌ 19÷18 የተጻፈውን ልብ ይበሉ፤ "ተስፋ ገና ሳለች ልጅህን ገስጽ፤ መሞቱንም አትሻ" ይህ ጥቅስ የሚነግረን ልጆቻችንን ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ ማድረግ አለመቻላችን ለጥፋታቸው ተባባሪዎች እንደሆንን ነው። ልጆቻችን በተጣመመ መንገድ የሚሄዱና ህይወታቸው የተበላሸ ከሆነ ምክንያቱ በእግባበ ስላላስተማርናቸው ነው፤ ለዚህ ነው እጅግ ታላቅ የሆነ ሀላፊነትን ልንሸከም የተገባን። በውድቀታቸው ልንተባበራቸው ፈቃደኞች አንሁን፤ ልጆቻችንን ሊያበላሹ ከሚፈልጉ በዓለም ካሉት ሃይላት ጋር ሚስጥራዊ የሆነ ስምምነት እናድርግ።

ስንቀሳቃሽ ሞተር እንጂ ተሳቢ ፍርግ ስትሁን

ለወላጆች ወይም ገና ወላጆች መሆን ቱስፋ ለሚያደርጉ አንድ የሚጨረሻ ምክር አለኝ፤ ቋንቀሳቀሽ ሞተር እንጂ ተሳቢ

ፍርጎ አትሁኑ። የባቡሩ ሞተር ሰባቡሩ በጉዞው ላይ ሀይል ይሰጣል አቅጣጫውንና ፍጥነቱን ይወስናል። እንደ ሌሎች መኪናዎች ሁሉ ፍርጎው የሚከተለው ሞተሩን ነው፤ በጭራሽ መሪ ሊሆን አይችልም። ሞተሩ ሊንቀሳቀስና ሲሄድ ብቻ ፍርጎው ይሄዳል። ባቡሩ ለአንድ ቤተሰብ እንደ ምሳሌ ቢሆን፤ ወላጆች የባቡሩ ሞተር ልጆችም እንደ ፍርጎው ማለት ናቸው። ልጆች ወላጆች ወደመሯቸው ሊሄዱ ይገባቸዋል። ወላጆች ከልጆቻቸው ፊት በመቅደም መነሻና መድረሻውን እንዲሁም ፍጥነቱን ሊወስኑ ይገባል። ሞተሩ ወደ ጉዞው መድረሻ በሰላም እስከደረሰ ድረስ ቀሪው የባቡሩም ክፍል አብሮ ይደርሳል።

በብዙ ቤተሰቦች ውስጥ ትልልቅ ከሆኑት ችግሮች አንዱ ወላጆች ራሳቸውን እንደ ፍርጎ ሰመሆን መፍቀዳቸው ነው። ልጆች የሞተሩን መቆጣጠሪያ ነጥቀው በመያዝ አቅጣጫቸውን ሳያውቁና ያለአላማም ሞተሩን በማንቀሳቀስ ይሮጣሉ፤ በዚህ ጊዜ ወላጆች ሊያደርጉ የሚችሉት ከቤተሰባቸው ባቡር ጀርባ እየተጎተቱ በሀዲዱ ላይ የመጨረሻውን ሥፍራ ይዞ መጓዝ ብቻ ነው። እየቆየም የሞተሩና የፉርጎው መለያየትና መበታተን በርግጥ አይቀሬ እውነታ ነው። እንደ ወላጆች ምንም አይነት ነገር እናድርግ፤ ልጆቻችን ባቡሩን እንዲነዱት በጭራሽ ልንፈቅድላቸው አይገባም።

ባቡሩ በየትኛው የህዲድ መስመር ላይ መሄድ እንዳለበት የሚወስነው ሞተሩ ነው። በዚሁ መንገድ እኛ እንደ ወላጆች ልጆቻችን ወዴት እንደሚሄዱና እኛ የራሳችንን ህይወት ባስቀመጥንበት የህዲድ መስመር ላይ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ልንወስን ያስፈልገናል። ከፊት ለፊታችን የባቡሩ ህዲድ መንታ ሆኖ የሚከፈልበት ሁኔታ ይጠብቀናል፤ ባቡራችን በየትኛው መስመር ላይ መጓዝ እንዳለበት ትእዛዝ እንሰጣለን። አንደኛው መስመር ወደ ህይወት፣ ወደ ጤንነትና ወደ ብልጥግና የሚያመራ ነው፤ ሌላው ግን ወደ ሞትና ወደ ጥፋት የሚወስድ ነው። እንግዲህ ምርጫው የእኛ ነው፤ በየትኛው መንገድ ነው የምንሄደው?

እንደ ወላጆች ምንም ስልጣን ነገር እንስራ፤ ልጆቻችን ባቡሩን እንዲመሩት በጭራሽ መፍቀድ የለብንም።

እግዚአብሔር መልካም የሆነ ዝርያን ይፈልጋል። ለእኛና ለልጆቻችን ህይወትን እንድንመርጥም ይሻል። የእግዚአብሔር ወዳጅ እንደሆነው እንደ ሙሴ ቃል፤ "በፊታችሁ ህይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥኩ፤ እኔ ዛሬ ሰማይና ምድርን

በእንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በህይወት ትኖሩ ዘንድ ህይወትን ምረጥ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሀቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፤ እርሱ ህይወትህ የዘመንህም እርዝመት ነውና እምላክህን እግዚአብሔርን ትወዳው፣ ትጠብቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ" (ዘዳ 30፥19-20)

ልጆች ወላጆቻቸው ብቻ ሊሰጧቸው የሚችሉትን መወደድን፣ መመራትን፣ መሰልጠንን፣ ሥነ ሥርዓት መያዝንና ጥበቃን ይፈልጋሉ። የሚቀጥለው ትውልድ ጥንካሬና ጤነኛነት የሚወሰነው፤ በወላጆች ታማኝነት፣ ጥንቃቄና እስተዋይነት ላይ ነው። ልጆች እንዲኖሯቸው የወሰኑ ባለትዳሮች መልካም የሆነውን ነገር መርጠዋል። አዎን፤ ልጆችን ማሳደግ መጠነኛ የሆነ ስጋት፣ የልብ ህዘንና ውጥረትን የያዘ አስደሳች የሆነ ህላፊነትን መቀበል ነው። ይሁን እንጂ ከዚህም በላይ ወላጆች ታላቅ ደስታን፣ ጥልቅ የሆነ እርካታንና ሰፍር የሌለው ተስፋን ከፊታቸው ባለ ዘመን ሊቀበሉ በብዙ እድለኞች የሆኑ ናቸው።

መርሆዎች

1. የቤተሰብ ምጣኔ አንድ ቤተሰብ በአግባቡ ሊወዳቸው፣ ሊመግባቸው፣ አስፈላጊውን ነገር በማቅረብ ሊንከባከባቸውና ሊከታተላቸው፣ ሊያሰለጥናቸውና ሊጠብቃቸው በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ለመገኘት፤ ያልተፈለገ እርግዝናን ለማስቀረትና የቤተሰብን ቁጥር ለመወሰን አስቀድሞ የታሰበበትን ውሳኔ የሚያካትት ነው።

2. የቤተሰብ ምጣኔ ልጆችን በተመለከተ፤ ልጆችን እንፈልጋለን? መቼ? እና ስንት? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስን ያካተተ ነው።

3. ልጆች ጤናሞች ሆነው ያድጉ ዘንድ፤ በኢኮኖሚያዊ አቋሙ፣ በስሜትና በመንፈሳዊ ጉዳዮች የተረጋጋ ቤተሰባዊ ሁኔታን ይፈልጋሉ።

4. ምሳሌነት ከምንም ይልቅ ታላቅ አስተማሪነት ነው፤ አናም ልጆች ወላጆቻቸው ከሚናገሩት ነገር ይልቅ ከወላጆቻቸው የህይወት ምሳሌነት የበለጠ ይማራሉ።

5. ውጤታማ የሆነ ወላጅነት አትኩሮትን የሚሰጥ፣ በእቅድ የሚመራና ሆን ተብሎ የታሰበበት ነው።

6. ወላጅነት የወላጅን ተፈጥሮ በልጁ ውስጥ ሊያፈራ ይጠበቅበታል።

7. ወላጅነት የወላጅን ባህሪ በልጁ ውስጥ ሊያፈራ ይጠበቅበታል።

8. ወላጅነት የወላጅን ጠባይ በልጁ ውስጥ ሊያፈራ ይጠበቅበታል።

9. እግዚአብሔር ለወላጆች የሰጠው ሃላፊነት ቀላል ነው፤ ወላጆች ልጆቻችሁን አለልጥኑ።

10. ወላጆች ሞተር አንጂ ተሳቢ ፍርጎ ሊሆኑ አይገባቸውም።

ምዕራፍ ስምንት

በትጋት ውስጥ ጠፍር

አስከ ህይወት ዘመን ፍጻሜ የሚዘልቅ ፍቅር በማይበሰብስ፣ አየተሸረሸረ በሚይሄድና በጊዜ ብዛት በሚያረጅ ጠንካራ መሠረት ላይ ሊገነባ ይገባዋል። ውጤታማ፤ ደስተኛና ፍሬያማ የጋብቻ ግንኙነት፤ ቋሚ እንጂ ጊዜያዊ ባልሆኑ፣ አላቂ ከሆኑ ነገሮች ተመሳስለው ባልተሰሩና ጊዜ በማያደበዝዛቸው መርሆዎች ላይ የግድ ሊመሠረት ያስፈልገዋል።

አካላዊ የሆነ ውበት ሊሠራ አይችልም። ውጫዊ የሆነ ቁንጅና በጊዜ ውስጥ ይደበዝዛል። ፀጉር ይሸብታል ወይም ይመለጣል፣ ቆዳ ይሸበሸባል፤ ሆድ ቦርጭ ያወጣል፣ ጥርስ ይወልቃል፣ አይታ ይደበዝዛል፣ ጆሮ ከመስማት ይደክማል። ጋብቻችሁን አካላዊ በሆነ ውበት ላይ መስርታችሁ ከሆነ እርስ በእርስ እንድትቀራረቡ ያደረጋችሁ ያ አካላዊ ውበት ሲጠፋ ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ?

ወሲብ ይህን ሊያደርግ አይችልም። ስሜቶችና ዝንባሌዎች ይለወጣሉ፣ ይጠፋሉም። እድሜ እየገፋ በሄደ ቁጥር ወሲብን የመፈጸም ብቃትና ፍላጎት ሁለቱም እየቀነሱ ይሄዳሉ። በዚሁ ጊዜ ውስጥ መቶ ፐርሰት የሆነው አካላዊና ኬሚካላዊ ፍላጎት በመሠረታዊ ባህሪው መንፈሳዊ የሆነውን ግንኙነት ለመመገብና ለማቆየት በራሱ በቂ ከማይሆንበት ደረጃ ላይ ይደርሳል።

ገንዘብ ይህን ሊያደርግ አይችልም። በኢኮኖሚ ማሽቆልቆል ሳቢያ ከስራ መባረር፣ በአካል መጉደል፣ ሰረቾርም ጊዜ በሚቆይ ህመም ወይም በሌላ ብዙ ምክንያቶች የገንዘብ አቋም በአስገራሚ ፍጥነት ሊለወጥ ይችላል። በነፍስ ፈቃድ ወይም የገንዘብን ጉዳይ ተጠሚ በማድረግ ወይም በገቢ አቅም ላይ መሠረት ተደርጎ የተመሠረተ ትዳር የውድቀት መገለጫ ነው።

ንብረት ይህን ሊያደርግ አይችልም። ቋሚ የሆኑ ንብረቶችና ቁሳቁሳዊ የሀብት ነገሮችም ዘላቂ መስለው ቢታዩም ጊዜያዊ የሆኑና እንደ ማለዳ ጠል ፈጥነው የሚጠፉ ናቸው። በእሳት አደጋ ወይም ውሽንፍር በቀላቀለ ከባድ አውሎ ነፋስ በድንገት ያላቸውን ሁሉ ያጡ ሰዎችን ሂዱና ጠይቋቸው። እንግዲህ ምን ቀረ፤ ህይወታችንንና ትዳራችንን በንብረት ይዞታና ክምችት ዙሪያ

ማማከል በቀላሉ ሌላ ተጨማሪ ነገር ለማግኘት የማይረካ ረሀብ፣ የማይቆረጥን ጥም ይፈጥራል።

እንግዲያውስ፣ ባለትዳሮች ደስተኛ፣ የተረጋጋና ዘላቂነት ያለው ግንኙነትን ሊገነቡ የሚገባቸው በምን ላይ ነው? የጊዜንና የችግርን ተግዳሮት ሊቋቋም የሚችል መሠረትስ ምንድነው? ባነበባችኋቸው በዚህ መጽሐፍ ምዕራፎች ውስጥ ይህንን ግልጽ እንዳደረኩ ተስፋ አደርጋለሁ፣ ዘላቂነት ላለው ትዳር ብቸኛ የሆነው አስተማማኝ መሠረት፣ ምንጩና መሠረቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ራስን አሳልፎ ለሌላው የሚሰጥ አጋፔ ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነው ብቻ እርሱ የሚፀና ሌላው ሁሉ ደግሞ ጊዜያዊና ሃላፊ የሆነ ነው። በቆሮንቶስ ለሚገኙ የአማኝ ማህበረሰብ አጋፔን አስመልክቶ ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ነበር።

"ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፣ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፣ ልሣኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፣ እውቀትም ቢሆን ይሻራል። ከእውነት ከፍለን እናውቃለን፣ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና ፍጹም የሆነው ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል። . . . እንዲህም ከሆነ እምነት ተስፋ፣ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፣ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው" (1ቆሮ 13፥8-10፣ 13)።

በመጨረሻው የሚቀሩት፣ እምነት፣ ተስፋ፣ ፍቅር ናቸው። እነዚህ ምንጫቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ሲሆን ከሦስቱ በላጭ የሆነው ደግሞ ፍቅር (አጋፔ) ነው። እንዲህ የሆነው እምነትና ፍቅር የሚመነጩና የሚኖሩትም የእርስ ህልውና ባለበት ሁኔታ ውስጥ ብቻ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ በመሆኑና አጋፔም የእርሱ የባህሪው ዋነኛ መገለጫ በመሆኑ ምክንያት የእርሱ ፍቅር ከቶውንም አይወድቅም። ትንቢት፣ ልሳንና እውቀት ለእኛ ዘላቂነት ያላቸው መስለው ቢታዩንም አንድ ቀን ግን ይሻራሉ። እርግጥ ነው እነዚህ ነገሮች ምንጫቸው ከእግዚአብሔር ነው፣ ነገር ግን በእርሱ እቅድ ውስጥ በባህሪያቸው ጊዜያዊ ሆነው ነው የተሠሩት። የእላማቸውን ግብ ከመቱ በኋላ ሁሉም ያልፋሉ። ፍቅር ግን እንዲህ አይደለም። አጋፔ ዘላለማዊ ነው፣ በፍጹም ሃላፊ አይደለም።

አጋፔ ዘላለማዊ ነው፤ በፍጹም ሃላፊ አይደለም።

ፍቅር ሰዳ አይደለም

በምዕራፍ አንድ ውስጥ አጋፔ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ፍቅር እንዳይደለ ተምረናል። ይህ ኢየሱስ ስለ ጎጢያታችን በመስቀል ላይ በመሞት ያሳየው፣ መስዋእትነት፣ ራስን ስለሌላው አሳልፎ የመስጠት ባህሪ ያለው ፍቅር ነው። ያለ ምንም ምክንያት መውደድ ማለት የሚወደዱትን ሰዎች ሁኔታ ያላገናዘበ ወይም ምላሽን የማይጠብቅ ነው።

በመሆኑም በአጋፔ ላይ የተመሠረተ ፍቅር አንዱ ከሌላው ምንም የማይጠብቅበት ነው፣ ምክንያቱም በዚህ ፍቅር ውስጥ ባልና ሚስት የሚዋደዱት ቅድመ ሁኔታ ላይ ሳይመሰረቱ፣ መስዋእትነት ባለበትና እርስ በእርሳቸውም ውስን የሆኑ ሚናዎችን አንዳቸው ከአንዳቸው ሳይጠብቁ ነው።

ለአማኞች፣ በትዳር ውስጥም ይሁን በሌሎች ግንኙነቶች ውስጥ ሊመራችውና ሊያንቀሳቅሳቸው የሚገባው ይሄው አጋፔ የሆነ ፍቅር ሊሆን ይገባዋል። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የቅርብ ወዳጅና ተከታይ የነበረው ስምኦን ጴጥሮስ፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ ስላልተመሠረተውና ከሌላኛው ምንም ስለማይጠብቀው አጋፔ ስለ ሆነው ፍቅር እንዲህ ብሏል፣ "ፍቅር የኃጢያትን ብዛት ይሸፍናልና፣ ከሁሉ በፊት እርስ በእርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ" (1ጴጥ 4፥8)። አጋፔ ኃጢያትን ቸል አይልም ይልቁን ሀጢያትን ይሸፍናል። ይህ ደግሞ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ የሆነ ግንኙነት ይኖረን ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሃጢያታችንን እንደሸፈነው ማለት ነው። በጋብቻም ውስጥ አጋፔ ማለት ባለትዳሮች አንዳቸው የአንዳቸውን ስህተትና ድክመት ቸል ከማለት ይልቅ አንዳቸው የሌላኛውን በደል በሚሸከሙበት ሁኔታ መባመርና ፍቅርም እንዳቸው በሌላኛው ውስጥ የሚያዩትን ጉድለት እንዲያሸንፈው መንገድ መክፈት፣ እንዲሁም አንዳቸው ከሌላቸው የመናቆርና የግጭት መነሻ ምክንያት እንዳይሆኑ መንገድ ዘማይከፍቱበት ሁኔታ ውስጥ መሆን ማለት ነው። ፍቅር አንዳችን በአንዳችን ላይ የባልነው ዕዳ ፈጽሞውንም መልሰን ልንከፍለው የማንገደድ ዕዳ ነው። ጳውሎስ በሮም ለሚገኙ አማኞች ይህን ግልጽ አድርጎላቸዋል። "እርስ በእርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ ሌላውን የሚወድ ህግን ፈጽሞታልና" (ሮሜ 13፥8)።

በትዳር ጓደኞችን ላይ የጣልነው የፍቅር ዕዳ እንዳለ ሁልጊዜም ስለራሳችን የማለብ ዝንባሌ ካለን፤ እኛ የማንወደውን አንድ ነገር ባደረጉ ወይም በተናገሩ ጊዜ የአፀፋ መልስ ለመስጠት የተበረታታን እንሆናለን።



በትዳር ጓደኞችን ላይ የጣልነው የፍቅር ዕዳ እንዳለ ሁልጊዜም ስለራሳችን የማለብ ዝንባሌ ካለን፤ እኛ የማንወደውን አንድ ነገር ባደረጉ ወይም በተናገረ ጊዜ የአፀፋ መልስ ለመስጠት የተበረታታን እንሆናለን።

ፍቅር ዘንቶ ጀናፈሰ

በአጋፔ ሥር የሚኖሩ ባለትዳሮች ተግባራዊ እንድምታዎች ምን ሊሆኑ ይገባቸዋል? የዚህን ጥያቄ መልስ ለመረዳት በመጀመሪያ ደረጃ ተግባራዊ በሆነ እሳቤው የአጋፔን ትርጓሜ መረዳት ያስፈልገናል።

"ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነት ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፣ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፣ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም በደልንም አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፣ ሁሉን ይታገሣል ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል በሁሉ ይፀናል" (1ቆሮ 13÷4-8)።

በባልና ሚስት መካከል ባለ ግንኙነት ላይ ተመስርተን እነዚህን ነጥቦች እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን። መቼም ቢሆን በሁሉም ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ለማስተዋል ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። "ሌሎች ለእናንተ እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም ለሌሎች አድርጉ" (ሉቃ 6÷31)።

ፍቅር ይታገሳል። ማንም ሰው ፍጹም እንዳልሆነ ሁልጊዜም ልናስተውስ ይገባናል። ሁላችንም ብንሆን የራሳችን የሆነ ስህተት፣ ጉድለት፣ ልዩ የሆነ ጠባይ፣ የመቆጣት ባህሪ ወይም ያልተለመደ የንግግር ጠባይ ሊኖረን ይችላል። ማንኛውም ሰው ወደ ጋብቻ ሲገባ የተወለነ መጠን ካለው ስሜታዊ፣ ስነ አይምሯዊና መንፈሳዊ ድካም ጋር ነው። አንዳችንን ከአንዳችን ሁኔታ ጋር ለማላመድ ጊዜና ትዕግስት የሚፈልግ ነገር ነው። የኪንግ ጀምስ የመጽሐፍ ቀዱስ ቅጅ ሁልጊዜም ትእግስት ለሚለው ቃል "ረዥም ጊዜ በመከራ

ውስጥ ታግሶ መቆየት" የሚል ቃል ይጠቀማል። እዚህ ላይ ለምንነጋገርበት ሀሣብ እውነተኛ የሆነውን ትርጉም የያዘ ነው። ትእግስት ያለው ፍቅር ለግለሰባዊ ማንነትና ልዩነት ስፍራ የሚለጥ ነገር ከመናገርና ፍርድን ከመስጠት በፊት ነገሮችን መረዳትን ይፈልጋል። በጋብቻ ግንኙነታችን ውስጥ ሁላችንም ብንሆን ጤነኛ በሆነ መልኩ፤ እኛ ለትዳር ጓደኞቻችን የምናሣየው ብቻ ሳይሆን እነርሱም ለእኛ የሚያሳዮትን በፀጋ ለመቀበል መንገድ መክፈት ይኖርብናል። ፍቅር ያለበት ትእግስት በፀጋ የተሞላ ነው። ስህተትን ከመፈለግ ይልቅ ሌላው ሰው ሙሉ አቅሙንና በክርስቶስ ያለው ማንነቱ እንዲገለጥ ለመርዳት ይፈልጋል።



ትእግስት ያለበት ፍቅር በዚጋ የተሞላ ነው።

ፍቅር ቸርነትን ያደርጋል። በቁጥር አራት ላይ የተጠቀሰው ቸርነት የሚለው ቃል የግሪክ ቃል አቻ ፍችው ለሌላው መልካም ነገርን ማለየት ወይም ትርፍን ሳይፈልጉ የቸርነትን ተግባር መፈፀም ማለት ነው። ቸር የሆነ ፍቅር ሁልጊዜም ለሌላው ሰው ፍላጎት እጅግ ጥሩ የሆነውን የሚፈልግ ነው። ሁልጊዜም ለመርዳት፣ ምኞት ለመስጠት፣ ለማጽናናት፣ ለማበረታታትና የወደቁትን ለማንሳት ነቅቶ የሚመለከት ነው። እዚህ ጋ ነው የጥቃቅን ነገሮችን ጠቃሚነት፤ ማለትም መልካም አስተያየት የመለንዘር፣ የደስታ መግለጫ ካርዶችና የአበባ አቅፍ ስጦታዎችን ማበርከት አስፈላጊነት ማስታወስ የሚገባው። ይሁን እንጂ ይህ ለሌላው ከማሰብ በላይ የላቀ ነገርን የሚያካትት ነው። ቸርነት የሌላውን ሰው ሁለንተናዊ ደህንነት አስመልክቶ በንቃትና ታስቦበት የሚደረግ ቃል ኪዳን የሚሻ ነው። ጨዋ የሆነና ትሁትም ነው። ነገር ግን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጽኑ እና ጠንካራ የሆነ፤ የተዋደዱትንም አንዳቸው ለአንዳቸው አሳልፈው እስኪሰጡ ድረስ ራስን ወደ መጉዳት ባህሪ የሚያመጣ ጉልበት ያለው ነው። አንዳንድ ጊዜ ትልቁ የቸርነት ተግባር የሚገለጸው የምንወዳቸውን ከውድቀት ለማዳን በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ጣልቃ መግባት ነው። ቸርነት በተጨማሪም ጠንካራ የሆነ ፍቅር ነው።

ፍቅር አይቀናም። አጋፔ በራስና በግንኙነት ውስጥ በደህንነት ተረጋግቶ የሚቆም ፍቅር ነው። በአጋፔ ውስጥ ስንኖር አብረን ካለነው ሰው ጋርና ከሌሎችም ሁሉ ጋር ባለን ግንኙነት ምኞት ይለማናል በስኬታማነታቸው ቅሬታ አይለማንም ወይም በደስታኛ

ነታቸው አንቀናም። በተቃራኒው ደግሞ በእነዚህ ነገሮቻቸው በንቃትና በትህትና ከእነርሱ ጋር ሀሴት እናደርጋለን። መቅናት ማለት በአንድ ሰው ላይ በመልካምም ይሁን በክፉ ቅናት ማሳደር፣ መጓጓትና መቅበጥበጥን ማሳየት ማለት ሲሆን መመቅኘት ከሚሰው ቃል ተቀራራቢ የሆነ ነው። አጋፔ ሰላማዊና አስተማማኝ በመሆኑ የቅናትና የምቀኝነትን ሰንኮፍ ነቅሎ በማውጣት አቅም አልባ ያደርጋቸዋል። ቅናትን የማያውቅ ፍቅር ማለት፤ ሚስት በስራ ቦታዋ መልካም እድገትን ስታገኝ፤ ባል ከእርሷ ጋር በመፎካከር የማዘን ስሜት የማያሳይበት ይልቁንም በእውነት ከእርሷ ጋር ደስ የሚሰኝበት ፍቅር ማለት ነው። እንደገናም ባል በስራ ባልደረቦቹ መካከል አክብሮትና አድናቆት ሲያገኝ፤ ሚስት ሰዎች ትኩረታቸውን ከእኔ ላይ ያነሳሰ በሚል ፍርሃት ሳትሸማቀቅበት ባሏ ባገኘው ክብር ከልባ ኩራት እንዲሰማት የሚያደርግ ፍቅር ማለት ነው። ቅናት የሌለበት ፍቅር ማለት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርካታ የሚሰጥ ፍቅር ማለት ነው።



አጋፔ በፌሱና በግንኙነቶችም ውስጥ በደህንነት ተፈጋግቶ የሚኖር ፍቅር ነው።

ፍቅር አይመካም። ቀጥተኛ በሆነ ትርጉሙ መመካት ማለት ጉረኝነት ማለት ነው። ጉረኛ የሆነ ሰው ሁልጊዜም ሰራሱ ምስጋናን የሚያመጣ፣ የራሱንም ክብር የሚያውጅ ነው። እያንዳንዱ ሰው ስእርሱ ስሰተሰጠው ስጦታና ስላከናወናቸው ነገሮች ሌላው ሰው ማወቁን እርግጠኛ መሆኑን ይፈልጋል። እንደ እውነታው ከሆነ ጉረኛ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለማንም ቢሆን ያላቸው ጠቀሜታ ጥቂት ነው፤ ምክንያቱም ጊዜያቸውን የሚያጠፉት የጉራ ወሬያቸውን በመሰለቅ በመሆኑ ነው። ፍቅር ግን በሌላው ጎኑ ሰሌሎች መልካም ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በመነጋገር ጊዜውን የሚወስድ ነው። በአጋፔ ስር የሚኖሩ ጉራን ለመንዛት አይፈልጉም ወይም አይበረታቱም፤ ምክንያቱም ስኬታማነታቸውንና ዓላማቸውን የሚያገኙት ከሰዎች ባገኙት ትኩረት ምስጋና ሳይሆን፤ ይልቁንም የሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እድል በማግኘ ታቸው ነው። ስለ አንድ ነገር ጉራ መንዛት ወይም ያለንን ፍቅር በወሬ የመሰፈፍ ዓይነት ስሜት የሚሰማን ከሆነ ምንም ዐይነት ፍቅር እንደሌለ ምልክት ነው። አጋፔ ግን ራስን ማስተዋወቅ አይፈልግም ወይም አይናፍቅም። እውነተኛ የሆነ ፍቅር ራሱን የሚገልጸው በተግባሩ ነው፤ በተገለጸም ጊዜ ሁሉ ሰው ያውቀዋል።



ፍቅር ስሌላው ሠልካም ማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በመነጋገር ጊዜውን የሚወስድ ነው።

ፍቅር አይታበይም። በዚህ ዘመናዊ ማህበረሰብ ብዙ ክፍሎች ውስጥ ጋጠወጥነት የተለመደ እንዲያውም ከሰዎች የሚጠበቅ ነገር ሆኗል። ይሁን እንጂ ትህትና የተሞላው ባህሪ የሚያረጅ ወይም ጎላ ቀር ሊሆን አይችልም። መልካም ባህሪ ሁልጊዜም አግባብ ያለው ነው። ጋጠወጥነት ማለት ልክ ባልሆነ፣ አግባብነት በሌለው ወይም ተቀባይነት ባጣና ጥሩ አቀባበልን በማያሳይ ሁኔታ ነገሮችን መፈጸም ነው። ፍቅር ሁልጊዜም በአግባቡ የሚያደርግና በማንኛ ውም ሁኔታና የሕይወት ግንኙነት ውስጥ ልክ የሆነውን ነገር የሚተገብር ነው። ይህ ማለት ደግሞ በከፍታም ይሁን በዝቅታ ስፍራ ላሉት ሁሉ አመሰካከታቸው ተገቢ የሆነውን አክብሮት መስጠት ማለት ነው። ማንኛቸውም ሰዎች ማንነታቸውን ባላገናዘበ መልኩ ክብርን የሚገባቸውን እንክብካቤ ሊቀበሉ የተገባቸው ናቸው። በአጋፔ ስር የሚኖሩ ሰዎች በህይወት ውስጥ ባላቸው በማንኛውም ግንኙነት አግባብ ያለውን አክብሮትና መልካም ባህሪን ለማሳየት ይጠነቀቃሉ። ይህም ባልን፣ ሚስትን፣ ወላጅን፣ ህፃናትን፣ ወንድምን፣ እህትንና ልጆችንም ያካተተ ይሆናል። ጋጠወጥ ያልሆነ ፍቅር አግባብነት ያለውን ግንኙነት የሚቃረንን ማንኛውንም ነገር ለመከላከል እርምጃ ይወስዳል።



ፍቅር የተፈጸመበትን ስህተት፣ ጉዳት፣ ስድብ ወይም ስሳዛኝ ተግባር መልሶ በሌላው ሰው ላይ ስመፈጸም በማቀድ የቂም መዝገብ ስያዘጋጅም።

በአመፃ ደስ አይለውም። መዝሙረኛው እንዲህ ይላል፤ "ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፤ በሀጢያተኞችም መንገድ ያልቆመ፤ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ" (መዝ 1፥1)። በዚህ ስፍራ ሊገለጥ የተገባው ህሳብ ይሄ ነው። አጋፔ በማንኛውም መንገድ ቢሆን ከአመጸኞችና ከኀጢያተኞች ጋር አለመተባበር ብቻ ሳይሆን አመጻና ኀጢያት በሰዎች ጉዳይና ህይወት ውስጥ በመኖራቸው ያዝናል። በአጋፔ ህግ ውስጥ የምንኖር ከሆነ በራሳችንም ይሁን በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ በሚፈጸም ኀጢያት ደስተኞች አንሆንም። በሌሎች ሰዎች ላይ የደረሰ የክፉ አጋጣሚ ዜና በጠላቶቻችን ላይ እንኳን ቢሆን በህዘን ውስጥ ይከተናል፤ ምክንያቱም አጋፔ ሰሁሉም ሰው ያለው መልካም ምኞት ነው።

ይልቁን ደግሞ ከእግዚአብሔር ተነጥለው የነበሩ ወደ ንስሀና ደህንነት ሲመጡ ማየት ደስታው ወሰን የለውም::



በስጋዊ ህግ ውስጥ የምንኖር ከሆነ በፈሳችንም ይሁን በሌሎች ሰዎች ህይወት ውስጥ በሚፈጸም ጎጢያት ደስተኞች አንሆንም::

ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል:: መዝሙር ምዕራፍ አንድ ስለተባረከው ሰው እንዲህ ይላል "ነገር ግን በእግዚአብሔር ህግ ደስ ይለዋል፤ ህጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል" (መዝ 1÷2):: እንደ እግዚአብሔር ቃል ያለ እውነተኛ ቃል የለም:: በአጋፔ ሥር የሚኖሩ እነርሱ እውነተኛ የሆነ ደስታ ከቃሉ ያገኛሉ:: እናነበዋለን፤ እናጠናዋለን፤ እንወያይበታለን፤ እንከፋፈለዋለን፤ ለልጆቻችንም እናስተምረዋለን እንዲሁም በጨለማ ላለው፣ እየሞተ ላለው አለም እናውጀዋለን:: በእውነት ደስ መሰኘት ማለት በተጨማሪ ሀቀኛና ክብር ባለበት ሁኔታ ከተሳካላቸው ሰዎች ጋርና ከእኛ ጋር የማይስማሙና ችግር ፈጣሪዎች ከሆኑብን ጋር እንኳን ቢሆን በእውነተኛ ደስታ አብረን መደሰት ማለት ነው:: ይህም ማለት ደግሞ በእውነት አሸናፊነትና በውሸት ውርደትና ውድቀት ሀሴት ማድረግ ማለት ነው:: በእውነት ደስ መሰኘት ማለት ሰዎች ከውስንነት፤ ራስን በድንቁርና አስሮ ከማቆየት ወደ እውቀት ብርሃን ሲወጡ መደሰት መቻል ማለት ነው:: አጋፔ እውነትን ለማገልገልና ከእውነት ጋር ለመስራት በግል ለመቀላቀል የነቃና ደስተኛም ነው::

ፍቅር ሌላውን ይጠብቃል:: "መጠበቅ" ለሚለው ቃል የግሪክ አቻ ትርጓሜው በቀጥተኛ አገላለጽ "መሸፈን" በተለይም በጣራ መክደን እንዲሁም "መደበቅ ወይም መሸሸግ" የሚል ነው:: በዚህ አሳቤው፤ አጋፔ የሰዎችን ስህተትና ውድቀት ለአለም ከማወጅ ይልቅ ሁልጊዜም ሊደብቀው ጥንቃቄ የሚያደርግ ነው:: ጋብቻንና ቤተሰብንም አስመልክቶ ይህ ማለት፤ ባል ሚስቱን ይሸፍናል:: በሚጠብቅና በሚሸፍን አጋፔ በሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር በህይወታቸው፤ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥና በሁለንተናዊ ደህንነታቸው ዙሪያ በተጠበቁበት መጠበቅና በተሸፈኑበት መሸፈን ሁለቱም በጋራ ሆነው ልጆቻቸውን ይሸፍናሉ፤ ይጠብቃሉ ማለት ነው:: አጋፔ መልካምነት ከሌላት አለም በቤተሰብ ላይ የሚለነዘረውን ህይወትን ከሚቀስፍ ፈጣን ጥቃትና የህይወት ድርቀት፤ ወደሞትም ከሚነዳ ረብ ከሌለው ገዳይ አመለካከት እንደ ጋሻ ሆኖ የሚጠብቅ ነው::

ፍቅር ሁሉን ያምናል:: ይህ እውነት የሚሆነው አስቀድሞ እግዚአብሔርን በሚመለከት ነው:: የአጋፔ ምንጩ ራሱ እግዚአብሔር በመሆኑ ምክንያት ህይወት ደስተኛ የሚሆነው በእግዚአብሔር ህልውና ውስጥ ብቻ ነው:: በአጋፔ የምንመራ ከሆነ በሁሉ ነገር በጌታ እንታመናለን፤ በቤታችን፤ በሥራችን፤ በማንኛውም ጉዳይና በሕይወታችን አቅጣጫ ከእርሱ ጥበብን፤ አመራርንና መገለጥን እንጠብቃለን:: በእግዚአብሔር መታመን በንግግራችንና ከቤተሰቦቻችን እንዲሁም ከጓደኞቻችን ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ ሁሉ እምነትን ይጨምርልናል:: ከዚህ በተጨማሪ ሁልጊዜም የሚታመን ፍቅር ማለት በሌሎች ሰዎች እምነትን የሚጥል ነው:: ይህ ማለት ግን በቀላሉ ማንንም ያምናል ማለት ሳይሆን፤ ሊታመኑ ላለመቻላቸው የተጨበጠ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ መልካም የሆነውን ማንነታቸውን መታመን መቻል ማለት ነው:: በዚህም እሳቤው መጥፎ የሆኑ ትዝታዎችን መዝግቦ ያለመያዝ ብቃትንም ያካትታል:: አጋፔ ሰዎች መልካም እንደሆኑ በመገመት፤ ለሌሎች መልካም በመመኘት ይደሰታል፤ እንዲህም ያለ ስነምግባራዊ ከፍታ አለው::

ፍቅር ሁልጊዜም ተስፋ ያደርጋል:: እዚህ ጋ መናገር የምፈልገው አለም የምትገምተውን በፍላጎት ላይ የተመሰረተውን አስተሳሰብና ህልማዊ የሆነውን ተስፋ አይደለም:: የአጋፔ ተስፋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ ነው:: ተግባራዊ በሆነ እውነት ላይ እና በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ የተመሠረተም ነው:: በዚህም ምክንያት በአጋፔ ሥር የምንኖር ከሆነ በመተማመንና ያለ ስጋት መልካም ተስፋ በህይወታችን እንደሚፈጸም ልንጠብቅ እንችላለን:: እኛ ያለነው ሁሉን ማድረግ በሚችልና "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የከፋ ነገር አይደለም" ሲል ቃል በገባልን በአባታችን እጅ ውስጥ ነው:: አጋፔ ሁልጊዜም በፍጥረታዊውም ይሁን በመንፈሳዊው አለም ውስጥ የነገሮችን መልካም ጎን ይመለከታል:: እርግጥ ነው ህዘን፤ ስቃይ፤ መከራ የመኖራቸውን እውነት ስለመቀበል አይሸፍጥም፤ ይሁን እንጂ በማይወድቀው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተመስርቶ ከግራ መጋባት ለመጠበቅ መልካም ነገሮች እንደሚሆኑ በተስፋ ይጠብቃል::



የአጋፔ ተስፋ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ ነው። ተግባራዊ በሆነ እውነት ላይና በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ የተመሠረተ ነው።

ፍቅር በሁሉ ይፀናል። ሁሉም ነገሮች ሊወድቁ (ወይም የሚወድቁ ሊመስሉ) ፍቅር በጭራሽ ተስፋ አይቆርጥም። እስከ መጨረሻው ጸንቶ ይኖራል። ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር መቼም የሚያቋርጥ አይደለም። ምንም ያህል አመጸኞችና ያልተገባ ባህሪ ያላቸው ቢሆኑም እንኳን እነርሱን ከመውደድ አያቋርጡም፣ ለእነርሱ ከመጸለይ አይታክቱም። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፤ የአጋፔም ምንጭ ከእግዚአብሔር በመሆኑ እርሱም እንዲሁ ዘላለማዊ ነው። በዚህ ምክንያት በባህሪውና በትርጓሜውም አጋፔ ሁልጊዜም ፀንቶ ይኖራል። አጋፔ በስደት፣ በሀሰተኞች ውንጀላ፣ በመከራ፣ በጥቃትና ተቀባይነት በማጣት ውስጥ ፀንቶ መቆም ይችላል። የአጋፔ የመጽናት ብቃት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀሉ ላይ ሆኖ ለጠላቶቹና የሞትን ፍርድ ለሚፈጽሙበት "አባት ሆይ፤ የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ሲል በፀለየው ጸሎት የተገለጠ ነው።

ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም። ይህ መግለጫ ቀደም ብለን ለተነጋገርናቸው ነገሮች ሁሉ እንደ ማህተም ነው። በዚህ ስፍራ መውደቅ የሚለውን ቃል የተጠቀመው ሃላፊ የሆነውን ነገር፣ የሚወድቀውን ነገር ወይም ከመኖር የሚሻረውን ነገር ለመግለጽ ነው። ፍቅር ዘላለማዊ ነው። ትንቢቶች፣ ልሳናትና እውቀት አንድ ቀን ሁሉም ያልፋሉ፤ አጋፔ ግን ለዘላለም አይወድቅም። የምንኖርባትን ይህችን አለምና መላውን ፍጥረታዊ አካል ጨምሮ በቆይታ ውስጥ ሁሉም ይጠፋሉ፤ አጋፔ ግን ለዘላለም አይወድቅም። አጋፔ አሁን እንኳን በምድር ላይ ትንሽ መንግስተ ሰማይ ነው፤ ሊመጣ ላለው አዲስ ምድርና ሰማይ አስፈላጊ የሆነውን ባህሪ በእግዚአብሔር ህዝብ ሁሉ ውስጥ ሊቀርጽ ይኖራል። ሁሉም ነገሮች ቢያልፉ እንኳን ፍቅር ፀንቶ ይኖራል። አጋፔ ለዘወትር አይወድቅም።

በአጋፔ ውስጥ መኖርን መማር ለዘለቄታው አልፎ የሚሄድን ፍቅር ለመረዳት ቀዳሚው ቁልፍ ጉዳይ ነው። አያንዳንዱ ባለትዳር ይህ ጥያቄ ከፊቱ ይጠብቀዋል። መልካም፤ መጋባቱን ለተጋባን እና ቀጣዩ ነገር ምንድን ነው? የዘመነው ማህበረሰብ በርካታ አማራጮችን ይሰጣቸዋል። ቁጥር ስፍር የሌላቸው ድምጾች

ለምክር አገልግሎት ራሳቸውን ያቀርቡላቸዋል። ዓለም ስለፍቅር የምትናገረው እጅግ ብዙ ነገር አላት። ጥሩና መጥፎ፣ ትክክለኛና ስህተት የሆኑም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ፍቅርን በሚረዳበት መንገድ ማንም አልተረዳውም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፥16 ይመልከቱ)። በእውነት ፍቅርን መረዳት የምንፈልግ ከሆነ ወደ ምንጩ ልንሄድ ያስፈልገናል። ስኬታማና እስከ ህይወት ዘመን ፍጻሜ የሚሆን ትዳር ውስጥ ማደግ የምንፈልግ ከሆነ የፍቅር ፈጣሪ የሆነውን ምክር ልንጠይቅ ይገባል።

ትዳር አስደናቂ ነገሮች የሞሉበት የህይወት ጉዞ ነው። በዚህ ጎዳና ላይ የሚጓዝ ማንኛውም መንገደኛ አስተማማኝ የሆነ መመሪያና የታመነ መጽሐፍ ያስፈልገዋል። ምንም አይነት ለውጥ ልትሆኑ ትችላላችሁ፤ ገና ጉዞውን የጀመራችሁ አዲስ ሙሽሮች ወይም የረዥም ጊዜ ልምድ ያላችሁ በመንገዱም ላይ በትዳር ጉዳይ የበለጠገ አመለካከት እንዲኖራችሁና ለመታደስም የምትፈልጉ ከሆናችሁ፤ ህይወታችሁንና ትዳራችሁን ለጌታ ስጡ። ለእርሱ ኑሩ፣ ቃሉንም ተከተሉ፣ እናም እርሱ ጉዟችሁን ይባርካል፣ ስኬትን ይሰጣችኋል በመንገዳችሁም ሁሉ በደስታ ይሞላችኋል፣ ሰላምንም ይሞላባችኋል። እንዲህ የሚሉትን የጠቢቡን ቃሎች ልብ በሉ፤

"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን

በራስህ ማስተዋል አትደገፍ

በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ

እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል።" (ምሳ 3፥5-6)።